*መጽሐፍ ቅዱስን ሊረዱት ይችላሉ!*

# በአስቸጋሪ ጊዜያት ተስፋ—
# የመጨረሻው መጋረጃ፡
# የዮሐንስ ራዕይ


*ቦብ አትሊ*

*የትርጓሜ ፕሮፌሰር*

*(የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ)*



የጥናት መመሪያ ተከታታይ ሐተታ

አዲስ ኪዳን፣ ቅጽ 12

ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ ማርሻል፣ ቴክሳስ

1998 (በ2007-2011 የተከለሰ)

# የይዘት ማውጫ


የደራሲው ማስታወሻ፡ ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል?...............i

ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡ የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ ...............iii

ሐተታው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ አሕጽሮተ ቃላት ...............ix

ሐተታ፡ ዋነኛ የመግቢያ ጽሁፍ (ክርስቲያኖች ስለምን በርካታ ቀኖናዊ የራዕይ ትርጓሜ ይኖራ...............1

መግቢያ ለብሉይ ኪዳን ትንቢት ...............6

የዮሐንስ ራዕይ መግቢያ...............9

የዮሐንስ ራዕይ 1 ...............18

የዮሐንስ ራዕይ 2 - 3 ...............40

የዮሐንስ ራዕይ 4 - 5 ...............72

የዮሐንስ ራዕይ 6 - 7 ...............85

የዮሐንስ ራዕይ 8 - 9 ...............97

የዮሐንስ ራዕይ 10 - 11 ...............105

የዮሐንስ ራዕይ 12 - 14 ...............121

የዮሐንስ ራዕይ 15 - 16 ...............147

የዮሐንስ ራዕይ 17 - 18 ...............161

የዮሐንስ ራዕይ 19 ...............170

የዮሐንስ ራዕይ 20 ...............184

የዮሐንስ ራዕይ 21 - 22 ...............192

ተጨማሪ መግለጫ  አንድ: የግሪክ ሰዋሰዋዊ ቃላት አጭር መግለጫዎች...............207

ተጨማሪ መግለጫ ሁለት: ጽሑፋዊ ትንተና...............214

ተጨማሪ መግለጫ  ሦስት: የቃላት ፍቺ ...............217

ተጨማሪ መግለጫ አራት: የእምነት መግለጫ ...............225

ተጨማሪ መግለጫ አምስት፡ የተለያዩ የሚሊንያል አመለካከቶችን የሚያሳይ ቻርት ...............226

ግጥም በዮሐንስ ራዕይ ላይ ...............229

# የዮሐንስ ራዕይ የልዩ ርዕሶች ማውጫ


መስህ፣ 1:1....19
ፈጥኖ መመለስ፣ 1:3....20
ተምሳሌት (ምልክት) ቁጥሮች በቅዱስ ቃሉ1:4 ....22
ቤተክስቲያን (ኤክሌሽያ)፣ 1:4 ....23
ሰባቱ መናፍስት፣ 1:4 . ....24
በኩር፣ 1:5....24
የጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ኬሪግማ (ስብከተ ወንጌል)፣ 1:5....25
ክርስትና የተጠቃለለ ነው፣ 1:6 ....25
ዘላለም (የግሪክ ፈሊጥ) 1:6 ....26
ዘላም ('ኦላም)፣ 1:6 ....26
አሜን፣ 1:6 ....28
ከደመና ጋር ይመጣል፣ 1:7 . ....29
የኀዘን ሥነ-ሥርዓት1:7....29
የመለኮት ስሞች፣ 1:8 ....30
የእግዚአብሔር መንግሥት፣ 1:9 ....33
በእስራኤል ጥቅም ላይ የሚውሉ ቀንዶች 1:10....34
ሙታን የት ናቸው?፣ 1:18....37
እግዚአብሔር እንደ ሰው ተገልጧል (አንትሮፖሞርፊያዊ ቋንቋ) 2:1....44
ማወቅ፣ 2:2 ....46
ጽናት፣ 2:2....46
ለፈተና የግርክ ቃላት 2:2 ....48
መከራ፣ 2:9....51
የሽልማቶች ደረጃና ቅጣት፣ 2:10 ....52
የጌታ ስም፣ 2:13....54
እምነት፣ 2:13....55
እስራኤል (ስም)፣ 2:14....56
የእግዚአብሔር ልጆች፣ 2:18 ....58
ሴቶች በመጽሐፍቅዱስ ውስጥ፣ 2:20 ....59
ልብ፣ 2:23 ....61
መናዘዝ፣ 3:5 ....64
በአዲስኪዳን ውጥ የበር አጠቃቀም፣ 3:7 ....65
አረኪ ፣ 3:14....67
ሀብት፣ 3:17 ....68
የቡብ ወንጌላዊ ቅድመ-ዝንባሌዎች4:1 ....73
ሰማያት፣ 4:1 ....74

ሽማግሌዎች፣ 4:4 ...76
ኪሩቤል፣ 4:6...76
ቅዱሳን፣ 5:8...80
መዋጀት/መቤዠት 5:9 ...81
በእግዚአብሔር መንግሥት መንገሥ 5:10 ...83
በፍልስጥኤም በኢየሱስ ጊዜ ጥጭቅም ላይ የነበሩ ሳንቲሞች፣ 6:6 ...87
ማህተም፣ 7:2...92
አሥራ ሁለት ቁጥር፣ 7:4 ...92
ምስጢር፣ 10:7...108
የብሉይ ኪዳን ትንቢት፣ 10:7 ...109
አርባ ሁለት ወራት፣ 11:2 ...113
መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 11:11 ...115
ቀን 11:18 ...119
ሰይጣን፣ 12:3 ...124
ጦርነት በሰማይ፣ 12:7 ...126
አካላዊ ከፉ፣ 12:9...127
የኢየሱስ በሆነ ሰዓት መመለስ በተቃርኖ ገና ነው (የአዲስ ኪዳን ፓራዶክስ (አያዎ)12:12 ...129
ክርስቲያንና መንግሥት የምእራፍ 13 መገቢያ ...131
ነውር የሌለበት፣ ንጹሕ፣ ኃጢአት የሌለበት፣ ያለ ነቀፋ፣ 14:5 ...139
ሰዓት 14:7...141
መጽሐፍ ቅዱሳዊ አዝማሚያ በአልኮል እና በአልኮለኝነት፣ 14:10 ...142
ክብር፣ 15:8 ...151
የአዲስ ኪዳን ትንቢት፣ 16:6 ...152
እሳት፣ 16:8 ...154
አጋንንት (ርኩሳን መናፍስት)፣ 16:13 ...156
ስለዳግም ምጽአትቃላት 16:14 ...158
ማውደም፣ ማበላሸት፣ ማጥፋት (PHTHEIRō)19:2...171
ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ እና ታማኝነት በብሉይ ኪዳን (rma 19:4 ...172
"እውነታ" (ጽንሰ-ሐሳብ) በዮሐንስ ጽሑፎች፣ 19:11 ...178
"እውነት" (ቃሉ) በዮሐንስ ጽሑፎች 19:11 ...178
ጽድቅ፣ 19:11 ...179
ግሪክ የሎጎስ ዳራ፣ 19:13 ...181
የናዝሬቱ ኢየሱስ 22:16 ...202
ሥላሴ 22:17 ...204
ማራናታ፣ 22:20...205

# የጸሐፊው መልእክት፡ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ አስተውሎት እና መንፈሳዊ ሂደት ያለበት የጥንቱን ተመስጧዊ ጸሐፍት በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልእክት በዘመናችን ለመረዳትና ለመተግበር የተዘጋጀ ነው።

መንፈሳዊ ሂደቱ ወሳኝ እና ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው። ለእግዚአብሔር መሰጠትንና ግልጽነትን ይጠይቃል።(1) ለእሱ፣ (2) እሱን ለማወቅ እና (3) እሱን ለማገልገል ጉጉትን ይፈልጋል። ይህ ሂደት ደግሞ ጸሎት፣ ንስሐ እና የሕይወትን አኗኗር ለመለወጥ ፍቃደኝነትን ይጠይቃል። በትርጓሜ ሂደት መንፈስ ወሳኝ ነው፣ ዳሩግን ትሑታንና፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በተለየ መልኩ እንደሚረዱት ምስጢር ነው።

የማስተዋሉን ሂደት ለመግለጽ ቀላል ነው። እኛ ለጽሑፉ የማናወላውልና ተገቢ ልንሆን፣ በራሳችን ወይም በእምነት ክፍላችን አስተሳሰብ ላንወሰድ ይገባል። ሁላችንም በታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ነን። ማናችንም ብንሆን ጉዳዩ የማይነካንና ገለልተኛ ተርጓሚዎች አይደለንም። ይህ ሐተታ በጥንቃቄ ማስተዋል ሂደት የተቀመረ ሦስት የትርጓሜ መርሖዎችን አዋቅሮ የያዘና አድልዎአዊ የሆኑ አስተሳሰቦቻችንን ለመቅረፍ የሚረዳ ነው።

## የመጀመሪያው መርሕ

የመጀመሪያው መርሕ የቅዱሱ መጽሐፍ ክፍል የተጻፈበትን ታሪካዊ መቼት ማጤን ነው፤ እንዲሁም የጸሐፊውም የወቅቱ ታሪካዊ ሁኔታ ይታያል። ዋነኛው ጸሐፊ ለማስተላለፍ የፈለገው ተግባርም ሆነ መልእክት አለው። ጽሑፉ ለእኛ አንዳች የሚሆን ዋነኛው፣ ጥንታዊው፣ ተመስጧዊው ጸሐፊ የጻፈው አይደለም ማለት ፈጽሞ አይደለም። የእሱ ፍላጎት የእኛ ታሪካዊ፣ ስሜታዊ፣ ባህላዊ፣ ግላዊም ሆነ ክፍለ ሃይማኖታዊ ፍላጎት ይደለም ቁልፉ ነው። ተግባር ዋነኛው ጓደኛ ነው፣ በትርጓሜ ሰዓት፣ ዳሩግን ሁልጊዜ ትክክለኛ ትርጓሜ ተግባርን መቅደም ይኖርበታል። እሱም ግሞ የሚያጠናክረው እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ አንድ እና አንድ ብቻ ፍቺ እንዲኖረው ነው። ይህም ፍቺ የሚሆነው ዋነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በመንፈስ ተመርቶ በዘመኑ ሊለው የፈለገውና ሊገናኝበት ያለውን ነው። ይሄው አንዱ ፍቺ ምናልባት በርካታ አማራጭ አግባቦች ለተለያዩ ባህሎችና ሁኔታዎች ሊኖረው ይችላል። እነዚህ አገባቦች ግን ከዋነኛው ጸሐፊ ማእከላዊ እውነት ጋር የተገናኙ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህን ምክንያት፣ ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ መግቢያ እንዲሆን ነው።

## ሁለተኛው መርሕ

ሁለተኛው መርሕ ሥነ ጽሑፋዊ አሀዶችን መለየት ነው። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ሙሉ ዶሴ ነው። ተርጓሚዎች አንደኛውን የእውነት ገጽታ ሌሎች የመነጠል መብት የላቸውም። ስለሆነም እያንዳንዱን የመጽ/ፍ ቅዱስ ክፍል ከመተርጎማችን በፊት የሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ መረዳት ይኖርብናል። ተናጠላዊ የሆኑት ክፍሎች ማለትም ምእራፎች፣ አንቀጾች፣ ወይም ቁጥሮች ሙሉው ክፍል ያላለውን የማይሉ ላይሆኑ ይችላሉ። ርጓሜ ከሙሉ አጠቃላይ አቀራረብ ወደ ዝርዝር ክፍላዊ አቀራረብ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም የዚህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ተማሪዎች የእያንዳንዱን ጽሑፋዊ ክፍል በአንቀጽ በመተንተን እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው። የአንቀጽን ሆነ የምእራፍ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም፤ ነገር ግን የዋና ሐሳብ ክፍሎችን ለመገንዘብ ያስችሉናል። ዓረፍተ ነገርን፣ ንዑስ አንቀጽን፣ ሐረግን ወይም በቃል ደረጃ ሳይሆን በሙሉ አንቀጽ ደረጃ መተርጎም፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ጸሐፊ ዋነኛ ሐሳብ መረዳት ቁልፉ ነገር ነው። አንቀጾች ብዙውን ጊዜ የተመሠረቱት አንድነት ባለው ርእስ፣ ማለትም ጭብጥ ወይም መሪ ዓረፍተ ነገር በሚባለው ነው።

ያንዳንዱ ቃል፣ ሐረግ፣ ንዑስ አንቀጽ፣ እና ዓረፍተ ነገር በአንቀጹ ስጥ ያለው፣ ይብዛም ይነስም ከዋነኛው ጭብጥ ጋር ይገናኛል። ይወስኑታል፣ ስፋፉታል፣ ያብራሩታል፣ ብሎም/ወይም ይጠይቁታል። ለትክክለኛ ትርጓሜ ቁልፉ ነገር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ መከተል ሆኖ አንቀጽ በአንቀጽ ላይ በተመሠረተ አካሄድ የመጽሐፍ ቅዱሱን መጽሐፍ ባስገኙት በተናጠላዊ የጽሑፍ ክፍል በሚደረግ አግባብ ነው። ይህ የጥናት መመሪያ የሆነ ሐተታ ተዘጋጀው ተማሪዎች አዲሶቹን የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እያነጻጸሩ እንዲያዩ ለመርዳት ጭምር ነው። እነዚህ ትርጓሜዎች ተመራጭ የሆኑበት ክንያት የተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ-ሐሳቦችን በመጠቀማቸው ነው:

1. የተባበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበረሰብ የግሪክ ቅጂ የተለከሰው አራተኛ እትም የተመጽማ)። ይህ ጽሑፍ በዘመናዊ የጽሑፍ ሊቃውንት አንቀጹ ተሰናድቶለታል።
2. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ) ቃል በቃል የተደረገ ጥሬ ርጉም ሲሆን የተመሠረተውም የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ባህል በሆነው ቴክስተስ ሪሴፐተስ በሚባለው ነው። የአንቀጽ አደራደሩ ከሌሎቹ ትርጉሞች ረዘም ይላል። እነዚህ ረጃጅም ክፍሎች ተማሪዎች የተዋሐዱትን ርእሶች እንዲረዱ ያስችላቸዋል።
3. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ትርጉም (አየተመት) ልታዊ የሆነ የቃል በቃል ትርጉም ነው። እሱም የሚከተሉት ሁለት ዘመናዊ ቅጅዎች ማእከላዊ የሆነ ነጥብ ይዟል። የአንቀጽ አደራደሩ ርእሰ ጉዳዮችን ለመገንዘብ በእጅጉን ይረዳል።
4. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት) ዋነኛ አቻ ትርጉም ሲሆን በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ (ማኅበረሰብ) የታተመ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ትርጉም የሚሞክረውም ዘመናዊ እንግሊዝኛ አንባቢ ወይም ተናጋሪ የግሪኩን ትርጉም እንዲረዳው ማድረግ ነው። በተለይ ደግሞ የወንጌላትን አንቀጾች የሚደረድረው በርእሰ-ጉዳዩ ሳይሆን በተናጋሪው ቃል ነው የሚደረድረው፣ በአኢ ት እንደተደረገው። ተርጓሚዎች ተግባር ይሄኛው የሚረዳ አይሆንም። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሁለቱም (የተየመቅሶ) እና (የጊእት) የታተሙት በአንድ ዓይነት ሀድ ሆኖ አንቀጻቸው ይለያያል።
5. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢ. መቅ) ዋነኛው አቻ ትርጉም ሲሆን በፈረንሳይ ካቶሊክ ትርጉም ላይ ነው። የአውሮጳውያንን የአንቀጽ አደራደር ስልት ለማነጻጸር በእጅጉን ይረዳል።
6. በ1995 የታተመው የተሻሻለው አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ዱስ (አአመመቅ)፣ የቃል በቃል ትርጉም ነው። ይህንን የአንቀጽ አደራደር ተከትሎም የየቁጥሩ አስተያየቶች ሰፍረዋል።

## ሦስተኛው መርሕ

ሦስተኛው መርሕ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ትርጉሞችን በማንበብ ሰፋ ያለ የትርጉም አገባቦችን ማወቅ ይቻላል (በትርጉም መስክ) መጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ወይም ሐረጎች የያዙትን። ብዙ ጊዜ የግሪክ ሐረግ ወይም ቃል በተለያየ መንገድ ነው መረዳት የሚቻለው። እነዚህ የተለያዩ ትርጉሞች እነዚህን አማራጮች በማቅረብ የተለያዩ የግሪክ አማራጭ ጽሑፎችን ለመለየት ያስችላሉ። ይህም መሠረተ እምነትን አይጻረርም፣ ዳሩግን ተመልሶ ወደ ዋናው ጽሑፍ በመውሰድ በተመስጦ የጻፈው የጥንቱ ጸሐፊ ጋ እንድንጓዝ ይረዱናል። ይህ ሐተታ፣ ፈጠን ባለ ሁኔታ፣ ተማሪ የራሱን ትርጉሞች ይመረምር ዘንድ እንዲረዳው የታሰበ ነው። ይህም ማለት ግብ ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ነው ማለት ሳይሆን መረጃ ሰጪ እና በጥልቀት እንድናስብ የሚያነቃቃ ነው። እርግጥ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችም ይረዱናል፣ አስተጋቢ፣ ቀኖናዊ፣ ወይም በመሠረተ እምነት የታጠርን እንዳንሆን። ተርጓሚዎች ሰፋ ያለ የትርጉም ዳርቻዎች እና አማራጮች ያሿቸዋል፣ የጥንቶቹ ጽሑፎች የቱን ያህል አሻሚ እንደነበሩ ለመረዳት። በጣም የሚረብሸው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ምንጫችን ነው የሚሉት ክርስቲያኖችም ያላቸው ስምምነት ጥቂት መሆኑ ነው።

እነዚህ መርሖዎች ብዙዎቹን ታሪካዊ ችግሮቼን እንዳሸንፍ ረድተውኛል፣ ከጥንቱ ጽሑፍ ጋር እንድተጋ በማስገደድ። እርሶንም ደግሞ ደሚባርክዎት ተስፋ አደርጋለው።

ቦብ አትሊ
ሰኔ 27፣1996

# ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡ የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ

እውነትን ለማወቅ እንችላለን? የት ይገኛል? ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ እንችላለን? የመጨረሻ ወሳኝ ይኖር ይሆን? ሕይወታችንንም ሆነ ዓለማችንን ሊመሩ የሚችሉ የተሟሉ (ፍጹማን) ይኖራሉ? ለሕይወት ትርጉም አለው? እዚህ መሆናችን ለምድነው? የትስ እንሄዳለን? እነዚህ ጥያቄዎች፣ አስተዋይ ሰዎች የሚሰላስሏቸውና ከዘመናት መጀመሪያ አንሥቶ የሰዎችን እውቀት የሚፈትሹ ናቸው (መክ. 1፡13-18፤ 3፡9- 11)። የኔን ግላዊ ጥናት የማስታውሰው የሕይወቴ ዋነኛ ማእከል አድርጌ ነው። በየየሱስ አማኝ የሆንኩት በወጣትነት ጊዜዬ ነው፤ በቅድሚያም በዋነኛነት በሌሎች የቤተሰቤ አባላት ምስክርነት። እየጎለመስኩ ስመጣ ስለራሴም ሆነ ስለ ዓለሜ ያሉኝ ጥያቄዎች እያደጉ መጡ። ተራ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድግግሞሾች ስለ አነበብኳቸውና ስለተረዳኋቸው የሕይወት ልምዶች፣ ትርጉም ሊሰጡ አልቻሉም። የውዥንብር ፤ የምርምር፣ የመናፈቅ እና ብዙውን ጊዜም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነበር፣ በምኖርበት በድን በሆነው ደንዳና ዓለም ውስጥ።

ለእነዚህ ዋነኛ ጥያቄዎች ብዙዎች ምላሽ እንዳላቸው ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከፍተሻ እና ከማገናዘብ በኋላ የእነሱ መልሶች የተመሠረቱት (1) በግል የሕይወት ፍልስፍናዎች፣ (2) በጥንታዊ አፈ-ታሪኮች፣ (3) በግል የሕይወት ልምዶች፣ ወይም (4) በሥነልቦናዊ ቅድመ እይታዎች ላይ ነው። በማስተዋል የሆነና ስለ ዓለም ያለኝ አመለካከት መሠረት፣ የሕይወቴ ዋነኛ ማእከል፣ የመኖሬ ዋነኛ ምክንያት ላይ ማረጋገጫ አስፈልጎኝ ነበር፣ ማስረጃ። እነዚህን መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና አገኘኋቸው።

ታማኝ እንዲሆንም ማስረጃ መፈለጌን ጀምሬ ያገኘሁትም፣ (1) በጥንታዊ ቅርስ ምርምር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ታሪካዊ ማረጋገጫ፣ (2) የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ትክክለኛለት፣ (3) በአስራ ስድስት መቶ የመጻፍ ጊዜው ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ የመልእክት ኅብርና መኖር እና (4) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከተገናኙ በኋላ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያገኙት ሰዎች የግል ምስክርነት ናቸው። ክርስትና ኅብር እንዳለው የእምነትና የሃይማኖት ሥርዓት የሰው ልጆችን ውስብስብ ጥያቄዎች የመመለስ ችሎታ አላቸው። ይህን ማድረግም የማስተዋል ውቅር ብቻ አይሰጥም፣ ነገር ግን በፍትነታዊ ገጽታው የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት የስሜት ደስታ እና መረጋጋትን ይሰጣል።

እንደማስበው፣ የሕይወቴን ዋነኛ ማእከል— ክርስቶስን በቃሉ ውስጥ አግኝቼዋለሁ። በሕይወት ልምዴ ንቁ እና ስሜተ-ስሱ ነበርኩ። ቢሆንም እስካሁን ድረስ የማስታውሰው ወገግ ሊልልኝ ሲል የነበረብኝን ነውጥ እና ሥቃይ ሲሆን፣ የቱን ያህል የመጽሐፉ ትርጓሜዎች እንደሚከራከሩና፣ አልፎ አልፎም በአንድ አብያተ ክርስቲያን እና አስተምህሮዎች እንዳሉ ሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የተመስጦ መሆንና ጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የመጨረሻው ሳይሆን የመጀመሪያው ብቻ ነው። የተለያዩ እና ተቃርኖ ያላቸውን የመጽሐፉን ከባባድ አንቀጾች ትርጓሜዎች፣ ሁሉም ትክክለኛ እና በሥልጣን ነን እያሉ እንዴት አድርጌ እንደምቀበል ወይም እንደምተው ላውቅ እችላለሁ? ይህም ተግባር የሕይወቴ ግብ እና የእምነቴ ምናኔ ሆነ። የተረዳሁት ነገር በክርስቶስ ያለኝ እምነት፣ (1) ታላቅ ሰላምና ደስታ እንዳመጣልኝ፣ (2) የተቀናቃኝ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች (የዓለም ሃይማኖቶች) ቀኖናዊነት፤ እና (3) የአንድ ክፍለ ሃይማኖት እብሪተኝነት እንዳለበት ተረድቻለሁ።

የጥንታዊውን ሥነ ጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ ዋጋ ያለው ፍለጋዬን ሳካሂድ ያስደነቀኝ ነገር ቢኖር የራሴን የግሌን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ክፍለ ሃይማኖታዊ እና በሕይወት ልምድ አድልዖዎች መለየት ነው። የራሴን አመለካከት ለማጠናከር መጽሐፍ ቅዱስን እንደዋዛ አዘውትሬ አነባለሁ። የራሴን ያልተሟላ ዋስትናና የብቃት ማነስ ያመላከተኝ ሌሎችን የማጠቃብት ቀኖናዊ ምንጭ አድርጌ እወስደዋለሁ። ይህንን ሀቅ መረዳት ለእኔ የቱን ያህል አስቸጋሪ ነበር! ምንም እንኳ የተሟላ ተጨባጭነት ባይኖረኝም የመጽሐፍ ቅዱስ ደጎና አንባቢ ለመሆን እችላለሁ። ያሉብኝን አድሏዊነቶች ለመለየትና እንዳሉም እውቅና በመስጠት የተወሰኑ ላደርጋቸው እችላለሁ። ከእነሱ ገና አሁንም ነጻ አይደለሁም፣ ነገር ግን ከራሴ ድክመት ተሟግቻለሁ። ተርጓሚ ዘወትር የመልካም መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጠላት እንደሆነ ነው! እስቲ ጥቂት ቅድመ ግምቶችን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ ገኘኋቸውን እርሶ አንባቢው ከእኔ ጋር ሆነው ይመረምሯቸው ዘንድ ልዘርዝራቸው፡

## 1. ቅድመ ግምቶች

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ የሆነ የእውነተኛው አምላክ የራሱ መገለጥ መሆኑን አምናለሁ። ስለሆነም፣ መተርጎም ያለበት በዋነኛው መነሻ ብርሃን ለኮታዊ ጸሐፊ (መንፈስ) ሆኖ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በነበረ ሰው ጸሐፊነት ነው።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለተራ ሰዎች፣ ለሁሉም ሰዎች እንደተጻፈ አምናለሁ! እግዚአብሔር ለእኛ በግልጽ ለመናገር በታሪካዊና በባህላዊ ግባብ ራሱን አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር እውነትን አይሸሽግም— እንድንረዳው ይፈልጋል! ስለሆነም በእኛ ሳይሆን በራሱ ጊዜ ብርሃን የግድ ተርጎም አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከሰሙት ወይም ካነበቡት በተለየ መንገድ የምንረዳው ማለት አይደለም። በተራ ሰው ልቦና ሊረዱት የሚችል እና ተገቢ የሆነ የሰው ልጆች መግባቢያ አግባቦችና ስልቶችን የሚጠቀም ነው።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ኅብር ያለው መልእክትና ተግባር እንዳለው አምናለሁ። ምንም እንኳ አያአዎአዊ የሆኑ አንቀጾች ቢኖሩትም ራሱን በራሱ ይቃረንም። ስለሆነም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።

መ. እያንዳንዱ አንቀጽ (ትንቢታትን ጨምሮ) አንድ እና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳላቸውና ይህም በዓይነተኛው ተመስጧዊ ጸሐፊ መነሻ ሐሳብ ሆኑን አምናለሁ። ምንም እንኳ ፍጹም ርግጠኞች ባንሆንም የዓይነተኛውን ጸሐፊ ሐሳብ እንረዳዋለን፣ ብዙ ጠቋሚዎች አቅጣጫውን ስለሚያመላክቱን፡

1. የዘውግ (የሥነ ጽሑፋዊ) ዓይነቱ፣ መልእክቱን ለማስተላለፍ የተፈለገበት
2. ጽሑፉ ሊያወጣ የፈለገው እውነት ታሪካዊ ዳራ እና /ወይም የተለየ አውድ
3. የአጠቃላይ የመጽሐፉ ሥነ ጽሐፋዊ ሁኔታ እና እንዲሁም የእያንዳንዱ የጽሑፍ አሀድ
4. ጽሑፋዊ ንድፉ (ዋና ዋና ይዘቱ) ማለትም እያንዳንዱ ጽሑፍ አሀድ ከአጠቃላይ መልእክቱ ጋር ያለው ዝምድና
5. መልእክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመበት የተለየ ሰዋሰዋዊ ባሕርይ
6. መልእክቱን ለማቅረብ የተመረጡት ቃላት ትይዩ አንቀጾች

በእነዚህ በእያንዳንዳቸው  አካባቢ የሚደረገው ጥናት በአንቀጽ ላይ የምናደርገው ጥናት  ላማ ሆኗል።ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሆነውን የእኔን ዘዴ ከመግለጤ በፊት ጥቂት ተገቢ ያልሆኑ በአሁን ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያሉትንና በርካታ የተለያዩ ትርጉሞች እንዲፈጠሩ ያደረጉትና   ግድ መወገድ ያለባቸውን ላመላክት፡

## II. ተገቢ ያልሆኑ ዘዴዎች


*ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት ሥነጽሑፋዊ አውድ ችላ በማለት  እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ እንዲያውም ግለሰባዊ ቃላትን እንደ እውነታዊ  ግለጫ፣ ከጸሐፊው ዓላማ ባልተገናኘ መልኩ ወይም ከሰፊው የጽሑፉ ክፍል ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ መውሰድ። ይህም ዘወትር "የጽሑፍ ማጣራት" ይባላል።*

*ለ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት እና በግምታዊ ታሪካዊ ዳራ በመቀየር ከጽሑፉ ጋር መጠነኛ ግንኙነት ወይም ምንም ዓይነት ድጋፍ በሌላቸው ጋር ማያያዝ*


*ሐ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት እንደ አካባቢያዊ የጧት ጋዜጣ ዓይነት ቀድሞውኑ ለዘመናዊ ክርስቲያን እንደተጻፈ ዓይነት ማንበብ*

*መ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት ለጽሑፉ ተምሳሌታዊ ፍቺ በመስጠት ፍልስፍናዊ/ሥነ- መለኮታዊ በማድረግ በመጀመሪያ ቃሉን ከሰሙት እና ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ሐሳብ በማይገናኝ መልኩ መያዝ*

*ሠ. ዋነኛውን መልእክት ችላ በማለትና የራስን የሥነ-መለኮት ሥርዓት፣ አባባይ መሠረተ- እምነት፣ ወይም የወቅቱን ጉዳይ በመቀየር፣ እና ከማይገናኝ ጋር በማያያዝና፣ ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ቁምነገርና ከተቀመጠው መልእክት መውጣት። ይህ የአካሄድ ክስተትም ዘወትር የሚደረገው የተናጋዊውን ሐሳብ ለማጠናከር በቅድሚያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ነው። ይህን ዘወትር፣ "የአንባቢ ምላሽ" ("ጽሑፉ ለእኔ የሚሰጠኝ" ትርጉም ተብሎ ይታወቃል። በሰዎች የጽሑፍ መግባቢያ ላይ ቢያንስ ሦስት አካላት ያስፈልጋሉ፡*




ቀደም ሲል የተለያዩ የምንባብ ስልቶች ከሦስቱ በአንደኛው ክፍሎች አተኩረው ነበር። ነገር ግን በእውነት ለማጽናት ልዩ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ  መስጦ የተሻሻለው ንድፍ ይበልጥ ተገቢነት አለው።




እንደ እውነቱ ሦስቱም አካሎች በትርጓሜ ሂደት የግድ መካተት ይኖርባቸዋል። ለማረጋገጥ ያህልም የእኔ ትርጓሜ ያተኮረው በቀዳሚዎቹ በሁለቱ  ካላት ላይ ነው፡ ዋነኛው ጸሐፊ እና ጽሑፉ። ምናልባት የእኔ ተቃርኖ ባስተዋልኩት ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ላይ ይሆናል። (1) ተምሳሌታዊ ወይም መንፈሳዊ በተደረጉ ጽሑፎች እና (2) "የአንባቢ ምላሽ" (ለእኔ የሚረዳኝ) ትርጓሜዎች። በዛባት በሁሉም ደረጃ ላይ ሊከሰት ይችላል። ዘወትር የእኛን መሻት፣ አድሏዊነት፣ አግባብ፣ እና አፈጻጸማችንን መመርመር ይኖርብናል። ምንም ዓይነት ወሰኖች ለትርጉሞች በሌሉበትና፣ ገደብና መስፈርት በሌለበት  እንዴት  አድርገን መፈተሽ  እንችላለን?  ለዚህ ነው የጸሐፊው መነሻ ሐሳብና የጽሑፉ አወቃቀር የተወሰኑ መስፈርቶችን ሰጥቶኝ ዳራውን ለመወሰንና ተገቢ የሆነ ይሁንታ ያለው ትርጓሜ እንዳደርግ ያስቻለኝ።

በእነዚህም ተገቢ ባልሆኑ ስልቶች ጭላንጭል ምን ዓይነት ታሳቢ አግባቦች ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እና ትርጓሜ በተረጋገጠ ደረጃ የሚያመጡ እና ቋሚነት ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ?

## III. ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ተገቢ አገባቦች

በዚህ ነጥብ የተወሰኑ የትርጓሜ ዘውጎችን የተለዩ ስልቶችን  አላብራራም፤ ነገር ግን ለሁሉም ዓይነት የቅዱሳን መጻሕፍት  አጠቃላይ የጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ መርሖዎች ላይ ነው። ለተወሰነ ዘውጋዊ  አግባብ መልካም የሆነው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣ በጎርዶን ፊ እና ዳግላስ ስቱአርት፣ በዞንደርቫን የታተመው ነው። የኔ ዘዴ በመነሻው ያተኮረው  አንባቢ ለመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ያበራላቸው ዘንድ ሲፈቅዱ የሚያልፉባቸውን አራት የግል የንባብ ሀደቶችን ነው። ይህም መንፈስን፣ ጽሑፉን እና አንባቢውን ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ ተከታይ ሳይሆን። ይህም ደግሞ አንባቢው በተንታኞች ሐሳብ አለቅጥ እንዳይወሰድ ያደርገዋል። ሲባል የሰማሁትም፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብርሃን በሐተታዎች ላይ ያበራል" የሚል ነው። ይህም ማለት ግን የጥናት መርጃዎችን ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ለአጠቃቀማቸው ተገቢ ጊዜ ማስፈለጉን ለማመላከት ነው እንጂ። ትርጓሜዎቻችንን ከቃሉ ከራሱ ለማስደገፍ መቻል ይኖርብናል።

ስድስቱ አካባቢዎች ምናልባት የተወሰኑ የእውነት ማረጋገጫ ይሰጡናል፡፡

1. የዋናው ጸሐፊ
   ሀ. ታሪካዊ መቼት
   ለ. ሥነ-ጽሑፋዊ አውድ
2. የዋናው ጸሐፊ ምርጫ
   ሀ. ሰዋሰዋዊ መዋቅር (አገባብ)
   ለ. የተመሳሳይ ሥራዎች አጠቃቀም
   ሐ. የጽሑፍ ዓይነት (ዘውግ)
3. የእኛ ተገቢ የሆነውን የመረዳት ችሎታ
   ሀ. የጊዜው ትይዩ አንቀጾች
   ለ. ከአስተምህሮቶች ጋር ያለው ግንኙነት

ከትርጓሜአችን ጀርባ ምክንያቶችንና አመክኖዎችን (ሎጂክ) ማሳየት መቻል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የእምነትና የድርጊት ምንጫችን ነው። ቢያሳዝን መልኩ፣ ክርስቲያኖች በሚያስተምረው ወይም በሚያጸናው ላይ ዘወትር አይስማሙም። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ መሆኑን ተቀብሎ ከዚያም አማኞች ለሚያስተምረውም ሆነ ለሚጠይቀው ላለመስማማት መቻል በራስ እንደመሸነፍ ነው!

አራቱ የንባብ ሀደቶች የተነደፉት የሚከተለውን ጠለቅ ያለ ትርጓሜ ለመስጠት ነው።

ሀ. የመጀመሪያው የንባቡ ኡደት

1. መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ ያንብቡት። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች አገኛለሁ ብለው ተስፋ በማድረግ በድጋሚ በተለያዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   ሀ. ቃል በቃል (NKJV, NASB, NRSV)
   ለ. ንቁ ቀጥተኛ TEV, JB)
   ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
2. የሙሉ ንባቡን ማእከላዊ ሐሳብ ይፈልጉ። ጭብጡን ይግለጡት።
3. የጽሑፋዊ አሀዱን (ከተቻለ) ይለዩት፤ ምእራፍ፣ አንቀጽ ወይም ዓረፍተ ነገር በትክክል ሊያብራራ የሚችለውን፣ የጭብጡን ማእከላዊ ሐሳብ ለማግኘት።
4. ዋነኛውን ገገር የሥነ-ጽሑፋዊ ጭብጥ ዘውግ (ዓይነት) ይግለጡት

   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   (1) ይእብራይስጥ ትረካ
   (2) የእብራይስጥ ቅኔ (መጽሐፈ- ጥበብ፣ መዝሙራት)
   (3) የእብራይስጥ ትንቢት (ስድ ንባብ፣ ቅኔ)
   (4) ሕግጋት

   ለ. አዲስ ኪዳን
   (1) ተራኪ (ወንጌላት፣ ግብረ-ሐዋርያት)
   (2) ምሳሌዎች (ወንጌላት)
   (3) ደብዳቤዎች/መልእክቶች
   (4) ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ

ለ. ሁለተኛው የንባብ ሀደት

1. ሙሉ መጽሐፉን እንዳለ በድጋሚ ያንብቡት፣ ዋናውን ርልሰ-ጉዳይ፣ ቁም-ነገሮች ለመለየት ፈልጉ
2. ዋናዎቹን ርእሶች በዋና ሐሳብ ለይተው አጠር ባለ እና በቀላል መግለጫ ይዘቱን ያስቀምጡ
3. የድርጊት መግለጫውን ይፈትሹና ሰፋ ያለ የርእስ ጉዳይ ዝርዝር በጥናት መርጃ ይጠቀሙ

ሐ. ሦስተኛው የንባብ ኡደት

1. ሙሉ መጽሐፉን በድጋሚ ያንብቡት፣ ለጽሑፉ ታሪካዊ መቼትና የተለየ አውድ ለማግኘትና ለመለየት ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይሞክሩ
2. በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ዓይነቶች ይዘርዝሩ
   ሀ. ጸሐፊው
   ለ. ዘመኑ
   ሐ. ተቀባዮች
   መ. ለመጻፍ የተለየ ምክንያት
   ሠ. ከመጽሐፉ ዓላማ ጋር የተያያዙ ባህላዊ መቼቶች ገጽታ
   ረ. ከታሪካዊ ሰዎችና ሁነቶች የሚጠቀሱ

3. የምትተረጉመውን ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የዋና ፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር ወደ አንቀጽ ደረጃ አስፋፉት። ዘወትር የሥነ ጽሑፉን አሀድ ለዩት፣ እንዲሁም የፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር አውጡ። ይህም ምናልባት በርካታ ምእራፎች ወይም አንቀጾች ይሆናል። ይህም የዋናውን ጸሐፊ የሐሳብ ተገቢነት (ሎጂክ) ጽሑፋዊ ንድፍ ለመከተል ያስችልዎታል።vi
4. የጥናት መረጃዎችን በመጠቀም የርሶን ታሪካዊ መቼት ይፈትሹ።

መ. አራተኛው የንባብ ሀደት

1. የተለየውን የጽሑፍ ክፍል በልዩ ልዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   ሀ. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሰመቅ፣ አየተመት)
   ለ. ንቁ አቻ (የአእቅ፣ 1መቅ)
   ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
2. ሥነ-ጽሑፋዊ ወይም ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ይፈልጉ
   ሀ. ተደጋጋሚ ሐረጎች፣ ኤፌ. 1፡6፤12፤13
   ለ. ተደጋጋሚ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች፣ ሮሜ. 8፡31
   ሐ. ተጻጻሪሪ ጽንሰ-ሐሳቦች
3. የሚከተሉትን ዓይነቶች ይመዝግቡ
   ሀ. ወሳኝ ቃላት
   ለ. ያልተለመዱ ቃላት
   ሐ. ዋነኞቹ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች
   መ. የተለዩ አስቸጋሪ ቃላት፣ ሐረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮች
4. ዋነኞቹን ትይዩ አንቀጾች ይለዩ
   ሀ. ከርእሰ ጉዳዩ ጋር በጣም ግልጽ የሆነውን የማስተማሪያ አንቀጽ ይፈልጉ
      (1) "ስልታዊ ሥነ-መለኮት" መጻሕፍት
      (2) የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ
      (3) የቃላት ዝርዝር
   ለ. በርእሰ ሐሳብህ ዙሪያ ተስማሚ  አያዎአዊ ጥንዶችን ከጽሑፉ ይፈልጉ። አብዛኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነታዎች  ሚቀርቡት በአከራካሪ ጥንዶች ነው፤ በርካታ የመሠረተ እምነት ግጭቶች የሚመነጩት ከጽሑፍ ኢቃቂር ማውጣት  ለትም ከፊል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርክሮች ነው። መላው መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ ነው፣ እኛም የተሟላውን መልእክት በመፈለግ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ሚዛን በትርጓሜአችን መጠበቅ ይኖርብናል።
   ሐ. በዛው በመጽሐፉ ውስጥ ፣ በዛው ጸሐፊ ወይም በዛው የሥነ ጽሐሁፍ ዓይነት፣ አቻዊ ትይዩ ይፈልጉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ ምርጥ ተርጓሚ ነው፤ ምክንያቱም፣ አንድ ብቸኛ ጸሐፊ ስላለው— መንፈስ ቅዱስ።
5. ታሪካዊ መቼቱንና የተለየ አውዱን ለመፈተሽና ለማስተዋል የጥናት መረጃዎችን ይጠቀሙ።
   ሀ. የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ
   ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ አውደ-ጥበባት፣ መምሪያ መጻሕፍ እና መዝገበ ቃላት
   ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያዎች
   መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታዎች  (በዚህ ነጥብ ላይ በጥናትዎ፣  አማኝ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ለትም የቀደምቱም ሆኑ ያሁኖቹ የራስዎን ጥናት ለማገዝና ለማረም ይጠቀሙባቸው።)

## IV. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አተገባበር

በዚህ ነጥብ ወደ አተገባበር እንቃኛለን። ጽሑፉን ከዋናው መቼት አንጻር ለመረዳት ጊዜ ወስደዋል፤ አሁን ደግሞ ይሄንኑ በሕይወትዎ፣ በባህልዎ  ተገብሩት ይገባል። የመጽሐፍ ቅዱስ የመረዳት ሥልጣን ማለት በእኔ አገላለጽ፣  "ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በእሱ ጊዜ ሊለው የፈለገውን መረዳትና ያንን በራሳችን ጊዜ መተርበር" ማለት ነው።   ድርጊት መከተል ያለበት የዋናውን ጸሐፊ የትርጓሜ ሐሳብ በጊዜም ሆነ በሎጂክ አኳያ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን  አንቀጽ በጊዜው ምን ለማለት  እንደፈለገ  እስካላወቅን ድረስ በዘመናችን ልንተገብረው  አንችልም! የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ  ለው ያልፈለገውን ፈጽሞ ሊሆን አይችልም!  የእርስዎ የተዘረዘረ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር በአንቀጽ ደረጃ (የንባብ ሀደት ቁጥር 3)፣ የእርስዎ መመሪያ ይሆናል። ትግበራ መደረግ ያለበት በአንቀጽ ደረጃ  እንጂ በቃላት ደረጃ መሆን የለበትም። ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ሐረጎች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው።

ብቸኛው ተመስጧዊ ሰው በትርጓሜው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ጸሐፊው ነው። በመንፈስ ቅዱስ  አብራሪነት  (ማብራሪያ)  የእሱን ምሪት ብቻ መከተል ይኖርብናል። ማብራሪያ ግን ተመስጦ ማለት አይደለም። "እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣" ለማለት ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር የግድ መኖር አለበት። ትግበራ በተለይ መያያዝ ያለበት በሙሉ መጽሐፉ ሐሳብ ላይ ሲሆን፣ የተለየው የጽሑፍ አሀድ እና በአንቀጽ ደረጃ እያደገ በሚሄድ መልኩ።   የዘመናችን ጉዳዮች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተረጉሙ አትፍቀዱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር! ይህ ምናልባት የተወሰኑ ከጽሑፉ እንድናወጣ ይጠይቀን ይሆናል። ይህም ተገቢ  የሚሆነው ጽሑፉ ለመርሐቹ ድጋፍ ሲሆን ነው። በሚያሳዝን መልኩ ግን፣ ብዙውን ጊዜ የእኛ መርሐዎች፣ "የእኛ" መርሐዎች ናቸው— የጽሑፉ መርሕ በመሆን ፈንታ።

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተግበር፣ (ከትንቢት ብቻ በቀር) ማስታወስ የሚገባን ጠቃሚ ነገር ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድና አንድ ብቻ ርጉም እንዳለው ነው። ያም ትርጉም ግንኙነቱ ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር፣ እሱም የዘመኑን ውድቀትም ሆነ ፍላጎት እንዴት እንዳቀረበው ነው። በርካታ ተስማሚ ድርጊቶች ከዚህ ከአንዱ ትርጉም ሊመነጩ ይችላሉ። አተገባበሩም የሚመሠረተው በተቀባዮቹ መሻት ላይ ሆኖ፣ መገኖኘት ያለበት ግን ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ላይ ነው።

## V. የትርጓሜ መንፈሳዊ ገጽታዎች

እስካሁን አመክኖአዊ የሆነ እና የሥነ ጽሑፋዊ ሂደት በምን መልኩ በትርጉምና በአተገባበር ላይ መሆን እንዳለበት ለማብራራት ሞክሬአለሁ። አሁን ደግሞ ስለ ትርጉም መንፈሳዊ ገጽታ በአጭሩ ላብራራ። የሚከተሉት የመቆጣጠሪያ ዝርዝሮች ረድተውኛል፡

ሀ. ለመንፈስ ርዳታ ይጸልዩ (1ኛ ቆሮ. 1፡26-2፡16)።

ለ. ከሚታወቅ ኃጢአት በግልዎ ምሕረትንና መንጻትን እንዲያገኙ ይጸልዩ (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)።

ሐ. ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲያድርብዎ ይጸልዩ (መዝ. 19፡7-14፤ 42፡1፤ 119፡1)።

መ. አዲስ ማስተዋልን በሕይወትዎ ወዲያውኑ ይተግብሩ።

ሠ. ትሑትና ለመማር የተዘጋጁ ይሁኑ።

በሎጂካዊ ሂደት እና በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ መሪነት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ በጣም አዳጋች ነው። የሁለቱን ሚዛን ለመጠበቅ የሚከተሉት ጥቅሶች ረድተውኛል፡

ሀ. ከ ጀምስ ደብሊዩ. ሲር፣ ቃሉን መጠምዘዝ (ማጣመም) ገጽ 17-18

"ማብራሪያ የሚመጣው ወደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ሐሳብ ነው— ወደ መንፈሳዊ ምሑር ሳይሆን።በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የተለየ የመሚሪያ ክፍል የለም፣ ምንም የተለየ የሚያብራራ፣ ተገቢው ትርጓሜ የሚመጣላቸው የተለዩ ሰዎች የሉም። እና ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስ ልዩ የጥበብ፣ እውቀት፣ እና መንፈስን የመለየት ጸጋ ሲሰጥ፣ እነዚህ ባለጸጋ ክርስቲያኖች ብቻ የቃሉ ሥልጣናዊ ተርጓሚዎች እንዲሆኑ መመደቡ አይደለም። ሁሉም የራሱ ሕዝቦች ሊማሩ፣ ሊዳኙ እና ሊለዩ፣ በእነሱ፣ እግዚአብሔር የተለየ ችሎታ ለሰጣቸው እንኳ ሥልጣን ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ እንደሚችሉ ነው። ለማጠቃለል፣ በሙሉው መጽሐፍ ያቀረብኩት ሐሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፣ በሚናገረው ሁሉ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ በጥቅሉ ምሥጢራዊ ሳይሆን በማንኛው ባህል ባሉ ተራ ሰዎች በበቂ መልኩ ለመረዳት የሚቻል ነው።"

ለ. በኬርኪጋርድ፣ በቤርናንድ ራም በሚገኘው፣ የፕሮቴስታንት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ፣ ገጽ 75፡

እንደ ኬርኪጋርድ ከሆነ ሰዋሰዋዊ፣ ቃላዊ፣ እና ታሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸው፤ መቅደም ያለበት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ልባዊ ንባብ ነው። "መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለማንበብ፣ ማንም አፍ ከልብ ሆኖ፣ በተጠንቀቀ ሆኖ፣ በጉጉትና ተስፋ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ማንበብ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስን በሐሳብ ቢስነት ወይም በግዴለሽነት ወይም እንደ ትምህርት ወይም እንደ ልዩ ሞያ ማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማንበብ አይደለም። አንዱ የፍቅር ደብዳቤ እንደሚነበብ የሚያነበው ከሆነ እሱ እንደ እግዚአብሔር ቃል እያነበበው ነው።"

ሐ. ኤች. ኤች. ሮውሊ በየመጽሐፍ ቅዱስ ጠቀሜታ፣ ገጽ 19፡

"የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራዊ መረዳት፣ ምንም ያህል ፍጹም ቢሆን ሁሉንም ሀብቶች ሊያስገኝ አይችልም። ይህን መሰሉን መረዳት ዝቅ ለማድረግ አይደለም፣ ለፍጹም መረዳት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ፍጹም ይሆን ዘንድ ወደ መጽሐፉ መንፈሳዊ ሀብቶች የሚያመራ መንፈሳዊ መረዳት ማስፈለጉን ለማሳየት ነው። እናም ለዛ መንፈሳዊ መረዳት ከምሑራዊ ንቁነት የተሻለ ነገር ያስፈልጋል። መንፈሳዊ ነገሮች በመንፈሳዊነት የሚለዩ ናቸው፤ እናም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የመንፈሳዊ ተቀባይነት አዝማሚያ ሊኖረው ይገባል፣ ራሱን ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጉጉት ያለው፣ ከሳይንሳዊ ጥናቱ ባሻገር ወደ ተትረፈረፈ ሀብት ወራሽነት ወደሚያስገኝ ወደዚህ ከመጻሕፍት ሁሉ ታላቅ ወደ ሆነ።"

## VI. የሐተታው ዘዴ

የጥናት መመሪያ ሐተታው የተሰናዳው የእርስዎን የትርጉም አግባብ በሚከተሉት መንገዶች ለማገዝ ነው፡

ሀ. እያንዳንዱን መጽሐፍ የሚያስተዋውቅ አጭር ታሪካዊ የዋና ሐሳብ መግለጫ። "የንባብ ሀደት ቁጥር 3" ካነበበቡ በኋላ ይህን መረጃ ያረጋግጡት።

ለ. ጽሑፋዊ ማብራሪያዎች በየአንዳንዱ ምእራፍ መጀመሪያ ላይ ይገኛል። ይህም ሥነ ጽሑፋዊ አሀዱ እንዴት እንደተዋቀረ ለመመልከት ይረዳል።

ሐ. በእያንዳንዱ ምእራፍ ወይም ሥነ ጽሑፋዊ አሀድ፣ የአንቀጽ ክፍሎች እና መግለጫ ጽሑፎች ከተለያዩ በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች ተሰጥተዋል፡

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት ሶሳይቲ የግሪክ ጽሑፍ፣ አራተኛ እትም (የተመቅሶ)
2. አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 1995 የተሻሻለ (አአመመቅ)
3. አዲሱ ኪንግ ጀምስ እትም (አኪጀእ)
4. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አየመመቅ)
5. አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አእመቅ)
6. የኢሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)

የአንቀጽ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም። ከጽሑፉ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች እና ሥነመለኮታዊ አስተሳሰቦች የተለያዩ ዘመናዊ ትርጉሞችን በማወዳደር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን ለመተንተን እንችላለን። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋነኛ እውነት ይዟል። ይህም "መሪ ዓረፍተ ነገር" ወይም "የጽሑፉ ማእከላዊ ሐሳብ" ተብሎ ይጠራል። ይህም ኅብር ያለው ሐሳብ አግባብነት ላለው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊ ርጉም ቁልፉ ነው። ማንም ከአንድ አንቀጽ ባነሰ መተርጎም፣ መስበክ ወይም ማስተማር ይኖርበትም! በተጨማሪም እያንዳንዱ አንቀጽ ከአካባቢው አንቀጾች ጋር እንደሚዛመድ አስታውሱ። ለዚህ ነው በአንቀጽ ደረጃ ያለ የዋና ሐሳቦች ርዝር ለሙሉ መጽሐፉ በጣም አስፈላጊ የሆነው። በዋናው ተመስጧዊ ጸሐፊ የተገለጠውን ርእሰ ጉዳይ አመክኖአዊ ፍሰት መከተል መቻል ኖርብናል።

መ. የቦብ ማስታወሻዎች በትርጓሜ የሚከተሉት ቁጥር በቁጥር የሆነውን አግባብ ነው። ይህም የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ እንድንከተል ያስገድደናል። ማስታወሻዎቹ ከብዙ አካባቢዎች መረጃዎችን ይሰጡናል።

1. ሀ. ሥነ ጽሑፋዊ ተጓዳኝ ጽሑፍ
2. ለ. ታሪካዊ፣ ባህላዊ መረዳቶች
3. ሐ. ሰዋሰዋዊ መረጃ
4. መ. የቃላት ጥናቶች
5. ሠ. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ሠ. በተወሰኑ ነጥቦች በሐተታው ውስጥ፣ አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ ትርጉም (በ1995 የተሻሻለ) የኀትመትጽሑፍ፣ ከሌሎች በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በደጋፊነት ይኖራሉ፦

ሀ. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ)፣ የጽሑፋዊ እጅ ጽሑፎችን ማለት "ቴክስተስ ሪሴፕተስ" የሚከተል ነው።

ለ. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ቅጂ (አየተመቅ)፣ ማለትም ቃል በቃል የሆነ ትርጉም ሲሆን፣ እሱም የተከለሰው መደበኛ ትርጉም ከቤተክርስቲያን ብሔራዊ ምክር ቤት ነው።

ሐ. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት)፣ ከአሜሪካን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ነው።

መ. የእየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (እመቅ)፣ ከፈረንሳይ ካቶሊክ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ላይ የተመሠረተ የእንግሊዝኛ ትርጉም ነው።

ረ. ግሪክኛን ለማያነቡ፣ ተነጻጻሪ እንግሊዝኛ ትርጉሞች በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን አስቸጋሪ ክፍሎች ለመረዳት ይጠቅማሉ፦

1. ሀ. የእጅ ጽሑፍ ልዩነቶች
2. ለ. አማራጭ የቃላት ፍቺዎች
3. ሐ. ሰዋሰዋዊ አስቸጋሪ ጽሑፎችና አወቃቀሮች
4. መ. አሻሚ ጽሑፎች የእንግሊዝኛ ትርጉም እነዚህን ችግሮች ባያቃልልም እንኳ፣ ጠለቅ እና ውስጣዊ የሆነ ጥናት ይደረግ ዘንድ አላማና ስፍራውን ያሳያሉ።

ሸ. በእያንዳንዱ ምእራፍ መዝጊያ ላይ ጠቃሚ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል፣ እነዚህም የምእራፉን ዋነኞቹን የትርጓሜ ጉዳዮች ዓላማ ለማድረግ የሚሞክሩ።

# ሐተታው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ አሕጽሮተ ቃላት

| | |
|---|---|
| AB | መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣ ዊሊያም ፎክስ ዌል ኦልብራይት እና ዳቪድ ኖኤል ፍሪደም ያዘጋጁት |
| ABD | መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (6ቅጾች)፣ ዴቪድ ኖኤል ፍሪደም ያዘጋጀው |
| AKOT | ትንተናዊ ቁልፍ የብሉይ ኪዳን በጆን ጆሴፍ ኦውንስ |
| ANET | ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ ጽሑፎች፣ ጀምስ ቢ. ፕሪቻርድ |
| BDB | እብራይስጥ እና እንግሊዝኛ ሥርወ-ቃል በብሉይ ኪዳን በኤፍ. ብራውን፣ ኤስ. አር. ድራይቨር እና ሲ. ኤ. ብሪግስ |
| BHS | ቢብላ ሄብሪካ ስቱትጋርቴንሲያ፣ ጂቢስ፣ 1997 |
| IDB | የተርጓሚ መዝገበ ቃላት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ (4 ቅጾች)፣ አዘጋጅ ጆርጅ ኤ. በትሪክ |
| ISBE | ዓለም አቀፍ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ እንሳይክሎፔድያ (5 ቅጾች) አዘጋጅ ጀምስ ኦር |
| JB | የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ |
| JPSOA | ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ማሶረቲክ ጽሑፍ፡ አዲስ ትርጉም (የአይሁድ የሕትመት ማኅበረሰብ የአሜሪካ) |
| KB | የእብራይስና የአራማዊ ሥርወ-ቃል የብሉይ ኪዳን በሉድዊግ ኮህለር እና ዋልተር ባዉምጋርትነር |
| LAM | መጽሐፍ ቅዱስ ከጥንታዊ የምስራቅ የብራና ጽሑፎች (ፓሺታ) በጆርጅ ኤም ላምሳ |
| LXX | ሰባ ሴፕቱዋጊንት (የግሪክ እንግሊዝኛ) በ ዞንደርቫን፣ 1970 |
| MOF | አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በጀምስ ሞፋት |
| MT | ማሶረቲክ እብራይስጥ ጽሑፍ |
| NAB | አዲሱ የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ |
| NASB | አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| NEB | አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| NET | አእትመጽሐፍ ቅዱስ፡ አዲሱ የእንግሊዝኛ ትርርጉም፣ ሁለተኛ ቤታ ትርጉም፡፡ |
| NIDOTTE | አዲሱ ዓለም አቀፍ መዝገበ ቃላት የብሉይ ኪዳን ሥነመለኮት እና ትርጓሜ (5 ቅጾች)፣ አዘጋጅ ዊሊም ኤ. ቫንጀሚረን |
| NRSV | አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| NIV | አዲሱ ዓለም አቀፍ ቅጂ |
| NJB | አዲሱ የየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ |
| OTPG | የብሉይ ኪዳን የምስጋና መመሪያ በቶድ ኤስ. ቤል፣ ዊሊየም ኤ. ባንክስ እና ኮሊን ስሚዝ |
| REB | የተከለሰ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| RSV | የተከለሰ መደበኛ ቅጂ |
| SEPT | ሴፕትዋጊንት (ግሪክ-እንግሊዝኛ) በዞንደርቫን፣ 1970 |
| TEV | የአሁን እንግሊዝኛ ቅጂ ከተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረተሰብ |
| YLT | የወጣቶች ጽሑፋዊ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ በሮበርት ያንግ |
| ZPBE | ዞንደርቫን ስእላዊ መጽሐፍ ቅዱስ እንሳይክሎፔድያ (5ቅጽ)፣ አዘጋጅ ሜሪል ሲ. ቴኒ |

# ዋነኛ የመግቢያ አንቀጽ
# “ክርስቲያኖች ስለምን በርካታ ቀኖናዊ የራዕይ ትርጓሜ ይኖራቸዋል”

በዓመታት የትርጓሜ ጥናቶቼ ውስጥ የተማርኩት ብዙዎቹ ክርስቲያኖች የዳበረ፣ ስልታዊ የሆነ፣ የፍጻሜ ዘመን ዜና መዋዕል የላቸውም፣ ወይም አይፈልጉም። ጥቂት ክርስቲያኖች አሉ፣ በዚህ አካባቢ ክርስትና ያተኮሩ፣ ለሥነ-መለኮታዊ፣ ለሥነ-ልቦናዊ፣ ወይም ለክፍለ-ሃይማኖታዊ ምክንያቶች። እነዚህ ክርስቲያኖች ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም እንዴት እንደሚፈጸም በማተኮር ነው፣ እናም ዋነኛውን የወንጌላዊነት አስቸኳይነት ይስታሉ! አማኞች በእግዚአብሔርን የመጨረሻው ዘመን (የፍጻሜ ዘመን) አጀንዳ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ አይችሉም፣ ነገር ግን በወንጌል ተልዕኮ ሊሳተፉ ይችላሉ (ማቴ. 28፡19-20፤ ሉቃስ 24፡47፤ ሐዋ 1፡8)። አብዛኞቹ አማኞች የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እና የፍጻሜ ዘመንን ማጠቃለያ ያስረግጣሉ፣ እሱም የእግዚአብሔር ተስፋ። የዚህ ዓለምን ፍጻሜ በተመለከተ በመረዳት ረገድ የሚነሡት የትርጓሜ ችግሮች የሚመጡት ከበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ፓራዶክሶች (አያዎ) ነው።

1. በብሉይ ኪዳን የትንበያ ሞዴሎችና በአዲስ ኪዳን ሐዋርያዊ ሞዴሎች መካከል ያለው ተቃርኖ
2. በመጽሐፍ ቅዱስ አሀዳዊነት (ለሁሉም አንድ አምላክ) እና በእስራኤል መመረጥ (የተለየ ሕዝብ) መካከል ያለው ተቃርኖ
3. በመጽሐፍ ቅዱስ ኪዳናትና ተስፋዎች ሁኔታዊ ገጽታዎች (“ከ... በኋላ”) እና ሁኔታዊ ያልሆነው የእግዚአብሔር ታማኝነት፣ ለወደቀው የሰው ልጅ መዋጀት መካከል ያለው ተቃርኖ
4. በቅርብ ምስራቅ ሥነ-ጽሑፋዊ ዘውግ እና በምዕራባዊ ሥነ-ጽሑፋዊ ሞዴሎች መካከል ያለው ተቃርኖ
5. በእግዚአብሔር መንግሥት አሁን መሆንና ገና ወደፊት በመምጣቱ መካከል ያለው ተቃርኖ
6. በክርስቶስ ምጽአት መዳረስ በማመንና አንዳንድ ሁነቶች የግድ ቀድመው መሆን እንዳለባቸው መካከል ያለው ተቃርኖ

እስቲ እነዚህን ተቃርኖዎች አንድ በአንድ እንመልከታቸው።

***የመጀመሪያው ተቃርኖ*** (የብኪ ዘራዊ፣ ብሔራዊ፣ እና መልክዓ ምድራዊ ምድቦች አልያም ሁሉም አማኞች በመላው ዓለም)

የብሉይ ኪዳን ነቢያት የአይሁድን መንግሥት መመለስ ተንብየዋል፣ እሱም በፍልስጥኤም ኢየሩሳሌምን ማዕከል አድርጎ፣ የምድር ሕዝቦች ሁሉ ዳዊታዊውን ገዥ ለማመስገንና ለማገልገል፣ ነገር ግን ኢየሱስም ሆነ የአኪ ሐዋርያት በዚህ አጀንዳ ላይ ፈጽሞ አላተኮሩም። ብኪ ተመስጧዊ አይደለምን (ማቴ. 5፡17-19)? የአኪ ደራስያን ዋነኛውን የፍጻሜ ሰዓት ሁነቶች ገድፈዋቸዋልን?

ስለ ዓለም ፍጻሜ በርካታ የመረጃ ምንጮች አሉ፡

1. የብኪ ነቢያት (ኢሳይያስ፣ ሚኪያስ፣ ሚልኪያስ)
2. የብኪ አፖካሊፒቲካዊ (የፍጻሜ ዘመን) ጸሐፍት (ሕዝ. 37-39፤ ዳን. 7-12፤ ዘካ.)
3. በይነ ኪዳናውያን፣ ካኖናዊ ያልሆኑ የአይሁድ አፖካሊፒታዊ ጸሐፍት (እንደ 1 ሔኖክ ያሉት፣ ስለ ጁዲ የሚጠቅሱ)
4. ኢየሱስ ራሱ (ማቴ. 24፤ ማርቆስ 13፤ ሉቃስ 21)
5. የጳውሎስ ጽሑፎች (1 ቆሮ. 15፤ 2 ቆሮ. 5፤ 1 ተሰ. 4-5፤ 2 ተሰ. 2)
6. የዮሐንስ ጽሑፎች (1 ዮሐንስ እና ራዕይ)።

እነዚህ ሁሉ የፍጻሜ ዘመኑን አጀንዳ በግልጽ ያስተምራሉን (ሁነቶች፣ ዜና መዋዕል፣ ሰዎች)? ካልሆነ፣ ለምን? ሁሉም ተመስጧዊ አይደሉምን (ከአይሁድ በይነ ኪዳናዊ ጽሑፎች በቀር)?

መንፈስ እውነትን ለብኪ ጸሐፍት ገልጿል፣ ሊረዱት በሚችሉት ቃላትና ምድቦች። ሆኖም፣ ቀጣይነት ባለው መገለጥ፣ መንፈስ እነዚህን የብኪ የፍጻሜ ዘመን ጽንሰ-ሐሳቦች ወደ ሁለንተናዊ ደረጃ አስፋፋቸው (“የክርስቶስ ምሥጢር፣” ኤፌ. 2፡11-3፡13። 10፡7 ላይ ልዩ ርዕስ ተመልከት)። አንዳንድ ጠቃሚ ምሳሌዎች እነሆ፡

1. የኢየሩሳሌም ከተማ በብኪ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በዘይቤነት ጥቅም ላይ ውሏል (ጽዮን)፣ ነገር ግን አመላካችነቱ ለአኪ ነው፣ እግዚአብሔር ንስሐ የገቡትን፣ የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ እንደተቀበለ ለመግለጽ (ራዕይ 21-22 አዲሲቷ ኢየሩሳሌም)። ሥነ-መለኮታዊ መስፋፋት፣ የላይ ላዩ፣ አካላዊ ከተማ ወደ አዲስ የእግዚአብሔር ሕዝብ (አማኝ አይሁድ እና አሕዛብ) በእግዚአብሔር ተስፋ በንግር ተቀምጧል፣ ዘፍ. 3፡15 ላይ የወደቀውን የሰው ልጅ ለመዋጀት፣ አንዳችም አይሁድ ወይም የአይሁድ ዋና ከተማ ከመኖሩ በፊት። የአብርሃም መጠራት እንኳ (ዘፍ. 12፡1-3) አሕዛብን አካቷል (ዘፍ. 12፡3፤ ዘጸ. 19፡5)።
2. በብኪ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት የጥንቱ ቅርብ ምስራቅ አካባቢ ሕዝቦች ነበሩ፣ በአኪ ግን ወደ ማያምኑት ሁሉ፣ ጸረ-እግዚአብሔር፣ ሰይጣናዊ ተመስጦ ወዳላቸው ሰዎች ተስፋፋ። ውጊያው ከመልክዓ ምድራዊ፣ ክልላዊ ግጭት ወደ መላው ዓለም፣ ሰፊ ክልል ግጭት ተሸጋገረ (ቆላስያስ)።
3. የተስፋው ምድር እሱም <u>እጅግ</u> በብኪ ዋነኛ ነገር የሆነ (የአባቶች ተስፋ የዘፍ. 12፡7፤ 13፡15፤15፡7፣15፤ 17፡8) አሁን ለመላው ዓለም ሆኗል። አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከሰማይ የምትመጣው አዲስ ለተፈጠረችው ዓለም ነው እንጂ፣ ለቅርብ ምስራቅ ብቻ ወይም በተናጠላዊ አይደለም (ራዕ. 21-22)።
4. አንዳንድ ሌሎች የብኪ ትንቢታዊ ጽንሰ-ሐሳብ ምሳሌዎች የተስፋፉት፡
   ሀ. የአብርሃም ዘር አሁን በመንፈስ የተገረዙት ናቸው (ሮሜ 2፡28-29)
   ለ. የኪዳኑ ሕዝቦች አሁን አሕዛብንም ያካትታሉ (ሆሴ. 1፡10፤ 2፡23፣ በሮሜ 9፡24-26 የተጠቀሰ፤ እንዲሁም ሌዋ. 26፡12፤ ዘጸ. 29፡45፣ በ2 ቆሮ. 6፡16-18 እና ዘጸ. 19፡5፤ ዘዳ. 14፡2 የተጠቀሰ፣ በቲቶ 2፡14 የተጠቀሰ)
   ሐ. መቅደሱ አሁን ኢየሱስ ነው (ማቴ. 26፡61፤ 27፡40፤ ዮሐንስ 2፡19-21) በእሱ በኩልም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን (1 ቆሮ. 3፡16) እና ግለሰብ አማኝ (1 ቆሮ. 6፡19)

መ. እስራኤልና የእሱም ባሕርይ እንኳ የብኪ ሐረጎች አሁን ሙሉውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያመለክታሉ (ማለትም፣ “እስራኤል፣” ሮሜ 9:6፤ ገላ. 6:16፣ ማለትም፣ “የንጉሥ ካህናት፣” I ጴጥ. 2:5፣ 9-10፤ ራዕ. 1:6)

ትንቢታዊው ሞዴል (ማለትም፣ ዲ. ብሬንት ሳንዲ፣ *የማረሻ ጫፍ እና መቁረጫ ማጭድ*) የፈጽሟል፣ ተስፋፍቷል፣ እናም አሁን እጅግ አጠቃላይ ነው። ኢየሱስና ሐዋርያዊ ጸሐፍት የመጨረሻው ዘመንን እንደ ብኪ ነቢያት በተመሳሳይ መንገድ አላቀረቡትም (ማርቲን ዋይንጋርደን፣ *መጻኢው መንግሥት በትንቢትና በፍጻሜው*)። ዘመናዊ ተርጓሚዎች፣ እነርሱም የብኪን ሞዴል በጥሬው ወይም ላይላዩን ለማድረግ የሚሞክሩ ራዕይን ወደ አይሁድ ሁነኛ መጽሐፍ አድርገው ይጠመዝዙታል፣ እናም ፍችዎቹንም በጣም ወደ ደቀቀና፣ አሻሚ ወደ ሆነ የኢየሱስና የጳውሎስ ሐረጋት ያደርጓቸዋል! የአኪ ጸሐፍት የብኪ ነቢያትን አይቃረኑም፣ ነገር ግን የመዳረሻ አጠቃላይ አንድምታውን ያሳያሉ። ምንም ዓይነት የተደራጀ፣ ሎጂካዊ ሥርዓት የለም ለኢየሱስም ሆነ ለጳውሎስ የፍጻሜ ዘመን ሥነ-መለኮት። የእነርሱ ዓላማ በቅድሚያ የሚቤዥ ወይም መጋቢያዊነት ነው (1 ቆሮ. 15፡58፤ 1 ተሰ. 4፡18)።

ሆኖም፣ በአኪ እንኳ ተቃርኖ አለ። ግልጽ የሆነ ስልታዊ የፍጻሜ ዘመን ሁነቶች የለም። በብዙ መንገዶች ራዕይ በሚያስገርም መልኩ የብኪን ጠቃሽ ዘይቤዎችን ይጠቀማል፣ ፍጻሜውን ለመግለጽ፣ ከክርስቶስ ትምህርቶች ይልቅ (ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ ወይም ጳውሎስ)! እሱም ጽሑፋዊ ዘውጎቹን ይከተላል፣ በሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ እና ዘካርያስ የተጀመሩትን፣ ነገር ግን በበይነ ኪዳናት ዘመን ዳብሯል (የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ)። ይህም የዮሐንስ መንገድ ሊሆን ይችላል፣ ብሉይና አዲስ ኪዳናትን ያያያዘበት። እሱም ረጅም ዕድሜ ያለውን ፈርጅ ያሳያል፣ የሰውን ዐመጸኝነት እና እግዚአብሔር ለመዋጀት ያለውን ቁርጠኝነት! ግን ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት፣ ምንም እንኳ ራዕይ የብኪን ቋንቋ፣ ሰዎች፣ እና ሁነቶች ቢጠቅስም፣ ዳግም የሚተረጉማቸው በአንደኛው ክፍለ ዘመን ሮም ሁኔታ አንጻር ነው (ራዕ. 1፡7)።

***ሁለተኛ ተቃርኖ*** (አሀዳዊነት አልያም የተመረጠ ሕዝብ)

መጽሐፍ ቅዱሳዊው አጽንዖት በአንድ ማንነት፣ መንፈሳዊ፣ ፈጣሪ-የሚቤዥ፣ አምላክ ላይ ነው (ዘጸ. 8:10፤ ኢሳ. 44:24፤ 45:5-7፣14፣18፣21-22፤ 46:9፤ ኤር. 10:6-7)። የብኪ የተለየነት በገዛ ራሱ ጊዜ አሀዳዊነቱ ነው። በአካባቢው የነበሩ ሕዝቦች ብዙ (ድርብ) አምላኪዎች ነበሩ። የእግዚአብሔር አንድነት የብኪ ራዕይ ዋነኛ ነገር ነበር (ዘዳ. 6፡4)። ተፈጥሮ መድረክ ነበር በእግዚአብሔር እና በአምሳሉና በመልኩ ለተፈጠረው ሰው ኅብረታዊ ዓላማ (ዘፍ. 1፡26-27)። ሆኖም፣ የሰው ልጅ ዐመጸ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር፣ አመራር፣ እና ዓላማ ላይ ኃጢአት ሠራ (ዘፍ. 3)። የእግዚአብሔር ፍቅርና ዓላማ እጅግ ጠንካራና ርግጠኛ ነበር፣ የወደቀውን ሰው ለመዋጀት ቃል ገባ (ዘፍ. 3፡15)!

ተቃርኖው የሚነሣው እግዚአብሔር አንድ ሰው፣ አንድ ቤተሰብ፣ አንድ ሕዝብ ሲመርጥ ነው፣ ወደ ቀሪው የሰው ልጅ ለመድረስ። የእግዚአብሔር አብርሃምንና አይሁድን መምረጥ፣ እንደ የንጉሥ ካህናት (ዘጸ. 19፡4-6) ትምክሕትን ፈጥሯል፣ ከአገልግሎት ይልቅ፤ መነጠል፣ ከማጠቃለል ይልቅ። የእግዚአብሔር አብርሃምን መጥራት ሁሉምን የሰው ልጆችን መባረክ ያካትታል (ዘፍ. 12፡3)። መታወስና አጽንዖት ሊሰጠው የሚገባው የብኪ መመረጥ ለአገልግሎት እንጂ ለደኅንነት አለመሆኑ ነው። እስራኤል ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ፈጽሞ ልክ አልነበረም (ማለትም፣ ሮሜ 9፡6)፣ ፈጽሞ ለዘላለም አትድንም በመወለድ ሙብቷ ተጠቅማ (ዮሐንስ 8፡31-59፤ ማቴ. 3፡9)፣ ግን በግል እምነትና መታዘዝ እንጂ (ዘፍ. 15፡6፣ ሮሜ 4፤3፣9፣22፤ ገላ. 3፡6 ላይ የተጠቀሰ)። እስራኤል ተልእኮዋን አጥታለች (ቤተ ክርስቲያን አሁን የካህናት መንግሥት ነች፣ ዝኪ. 1፡6፤ II ጴጥ.2፡5፣9)፣ ውክልናን ወደ መታደል ቀየረ፣ አገልግሎትን ወደ ልዩ አቋም! እግዚአብሔር አንዱን መረጠ ሁሉንም ለመምረጥ!

***ሦስተኛ ተቃርኖ*** (ሁኔታዊ ኪዳናት አልያም ሁኔታዊ ያልሆኑ ኪዳናት)

በሁኔታዊ ኪዳናትና ሁኔታዊ ባልሆኑ ኪዳናት መካከል ሥነ-መለኮታዊ ተቃርኖ ወይም አያዎ (ፓራዶክስ) አለ። ርግጥ ነው የእግዚአብሔር የመዋጀት ዓላማ/ዕቅድ ሁኔታዊ ያልሆነ ነው (ዘፍ. 15፡12-21 እና የመሲሑ መምጣት)። ሆኖም፣ ኃላፊነት ያለው የሰው ምላሽ ዘወትር ሁኔታዊ ነው!

የ “ከ… በኋላ” አገባብ በሁለቱም፣ በአኪ እና በብኪ ይከሰታል። እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ የሰው ልጅ ያልታመነ ነው። ይህ ተቃርኖ በርካታ ውዥንብር ፈጥሯል። ተርጓሚዎች የሚያተኩሩት በአንደኛው “አደናጋሪ ቀንድ፣” ላይ ብቻ ነው፣ የእግዚአብሔር ታማኝነት ወይም የሰው ጥረት፣ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ወይም የሰው ልጅ ነጻ ፍቃድ። ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊና አስፈላጊ ናቸው።

ይህም ከፍጻሜ ዘመን ትንቢት ጋር ይዛመዳል፣ ከእግዚአብሔር የብኪ ተስፋ ለእስራኤል። እግዚአብሔር ተስፋ ከሰጠ፣ ያ ያጸናዋል! እግዚአብሔር ለተስፋው እስረኛ ነው፤ የእሱ ማንነት ተካቶበታል (ሕዝ. 36፡22-38)። ሁኔታዊ ያልሆነውና ሁኔታዊ የሆኑት ኪዳናት በክርስቶስ ተጋጥመዋል (ኢሳ. 53)፣ እስራኤል ሳይሆን! የእግዚአብሔር ሁለንተናዊ ታማኝነት ሁሉንም በመዋጀት ላይ ያረፈ ነው፣ ንስሐ የሚገቡና የሚያምኑ፣ በአባትና በእናታችሁ ማንነት ላይ ሳይሆን! ክርስቶስ፣ እስራኤል ሳይሆን፣ ለሁሉም የእግዚአብሔር ኪዳናትና ተስፋዎች ቁልፍ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሥነ-መለኮታዊ ቅንፍ ካለ፣ ቤተ ክርስቲያን አይደለም፣ እስራኤል እንጂ (ሐዋ. 7 እና ገላ.3)።

ወንጌልን ለዓለም የማወጅ ተልእኮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተላልፏል (ማቴ. 28፡19-20፤ ሉቃስ 24፡47፤ ሐዋ. 1፡8)። እሱ ገና ሁኔታዊ ኪዳን ነው! ይህ ማለት እግዚአብሔር አይሁድን ሙሉ ለሙሉ ትቷል ማለት አይደለም (ሮሜ 9-11)። ለመጨረሻው ዘመን፣ አማኝ እስራኤል ስፍራና ዓላማ አለ (ዘካ. 12፡10)።

***አራተኛ ተቃርኖ*** (የቅርብ ምስራቅ ጽሑፋዊ ሞዴሎች አልያም ምዕራባዊ ሞዴሎች)።

ዘውግ ዋነኛ ነገር ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ለመተርጎም። ቤተ ክርስቲያን ያደገችው በምዕራባዊ (ግሪክ) ባህላዊ መቼት ነው። ምስራቃዊው ሥነ-ጽሑፍ ይበልጡን ፍካሬያዊ፣ ዘይቤአዊ፣ እና ተምሳሌታዊ ነው ከዘመናዊው፣ ምዕራባዊ ባህል ሥነ-ጽሑፋዊ ሞዴሎች። የሚያተኩረው በሰዎች፣ በግጭቶች፣ እና ሁነቶች ላይ ነው፣ ከተጠቃለሉ የእውነት ሐሳቦች ይልቅ። ክርስቲያኖች ተላላፊ

ሆነዋል፣ የእነሱን ታሪክ እና ጽሑፋዊ ሞዴሎች በመጠቀማቸው፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ለመተርጎም (በብኪና በአኪ)። እያንዳንዱ ትውልድና መልክዓ ምድራዊ አህድ የራሱን ባህል፣ ታሪክ፣ እና እማሬያዊነት ይጠቀማል፣ ራዕይን ለመተርጎም። እያንዳንዳቸው ተሳስተዋል! ዘመናዊው ምዕራባዊ ባህል የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ትኩረት ነው ብሎ ማሰብ አላዋቂነት ነው!

ዋነኛው ተመስጧዊ ደራሲ ለመጻፍ የመረጠው ዘውግ ከአንባቢው ጋር የሚደረግ ጽሑፋዊ ውል ነው። የራዕይ መጽሐፍ ታሪካዊ ትርክት አይደለም። እሱ የመልእክቶች ድብልቅ ነው (ምዕራፍ 1-3)፣ ትንቢት፣ እና ባብዛኛው አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፍ። መጽሐፍ ቅዱስ በዋነኛው ደራሲ ሊባል ከተፈለገው በላይ እንዲል ማድረግ ስሕተት ነው፣ ሊለው ከፈለገው በታች እንዲል እንደ ማድረግ ሁሉ! የተርጓሚዎች አላዋቂነትና ቀኖናዊነት እጅግ ተገቢ ያልሆኑ ናቸው እንደ ራዕይ ለመሳሰሉ መጻሕፍት።

ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ተስማምታ አታውቅም ራዕይን በትክክል በመተርጎም ረገድ። እኔን የሚገደኝ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ማድመጥና ማድረግ ነው እንጂ፣ የተወሰኑ የተመረጡ ክፍሎችን አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ ምስራቅ-ተኮር ቅንብር እውነትን የሚያቀርበው በተቃርኖ ሞል ጥንዶች ነው። የእኛ ምዕራባዊ አዝማሚያችን ወደ ሐሳባዊ እውነት ዋጋ ቢስ አይደለም፣ ሚዛናዊ አይደለም እንጂ! እንደማስበው አንዳንድ የማይለወጡ ነገሮችን ማስወገድ ይቻላል፣ ራዕይን በመተርጎም፣ የዓላማ ለውጦቹን በመመዝገብ፣ በተከታዩ አማኝ ትውልድ። በአብዛኞቹ ተርጓሚዎች ዘንድ ግልጽ ነው፣ ራዕይ በገዛ ራሱ ጊዜና ዘውግ አንጻር መተርጎም እንደሚኖርበት (ፊ እና ስቱዋርት፣ *መጽሐፍ ቅዱስን ከነ ሙሉ ጠቀሜታው ስለማንበብ፣* ገጽ 249-264)። በራዕይ ላይ ታሪካዊ አገባብ የግድ መያዝ ያለበት የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ያላቸውን፣ ሊኖራቸው የሚችለውን፣ የሚረዱትን ነው (ማለትም፣ ጆን ኤል. ብሬይ፣ *የማቴዎስ 24 ፍጻሜ*)። በብዙ መንገዶች ዘመናዊ ተርጓሚዎች የመጽሐፉን አብዛኞቹን ምስያዎች ፍቺ አጥተዋቸዋል። የራዕይ መነሻው ዋነኛ እምነት የተሰደዱትን አማኞች ማበረታታት ነበር። እሱም እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚቆጣጠር ያመለክታል (የብኪ ነቢያት እንዳደረጉት)፤ እሱም የሚያስረግጠው ታሪክ ወደ ተቀጠረ ፍጻሜ ማምራቱን ነው፣ ፍርድ ወይም በረከት (የብኪ ነቢያት እንዳደረጉት)። እሱም የሚያስረግጠው በአንደኛው ክፍለ ዘመን የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ቃላት ነው፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ መገኘት፣ ኃይል፣ እና ሉዓላዊነት!

እሱም የሚሠራው በእነዚህ ተመሳሳይ *ሥነ-መለኮታዊ* መንገዶች ነው፣ በእያንዳንዱ አማኝ ትውልድ ዘንድ። እሱም የመልካምና የክፉውን ሁለንተናዊ ትግል ያሳያል። የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ዝርዝር ጠፍቶብን ሊሆን ይችላል፣ ግን ኃይለኛው፣ አበረታች እውነት ሳይሆን። ዘመናዊዎቹ ምዕራባዊ ተርጓሚዎች የራዕይን ዝርዝር ለማስገደድ ሲሞክሩ፣ ወደ ራሳቸው ዘመነኛ ታሪክ፣ የስሕተት ትርጓሜ ፈርጅ ይቀጥላል!

የመጽሐፉን ዝርዝር በሚያስደንቅ መልኩ በድጋሚ እማሬያዊ ማድረግ ይቻላል (ልክ በብኪ እንደተደረገው በክርስቶስ ልደት፣ ሕይወት፣ እና ሞት እንደተደረገው) ላለፉት የአማኞች ትውልድ በጸረ እግዚአብሔር መሪ መከራን እንደተጋፈጡት (2 ተሰ. 2) እና ባህል። እነዚህን እማሪያዊ የራዕይን ፍጻሜዎች ማንም አያውቅም፣ እስከ ኢየሱስ ቃል ድረስ (ማቴ. 24፤ ማርቆስ 13፤ እና ሉቃስ 21) እና ጳውሎስ (1 ቆሮ. 15፤ 1 ተሰ. 4-5፤ እና 2 ተሰ. 2) ደግሞም ታሪካዊ ማስረጃ ሆኗል። ግምት፣ ምርምር፣ እና ቀኖናዊነት ሁሉም ተገቢ አይደሉም። አፖካሊፕቲካዊ *ሥነ-ጽሑፍ* ይህንን ተጣጣፊነት ይፈቅዳል። ስለ ምስሎችና ምስያዎች እግዚአብሔር ይመስገን፣ ከታሪካዊ ትርክት ስለሚያልፉት! እግዚአብሔር እየተቆጣጠረ ነው፤ ይነግሣል፤ ይመጣል!

አብዛኞቹ አታቾች የዘውግን ነጥብ ይዘነጉታል! ዘመናዊዎቹ ምዕራባዊ ተርጓሚዎች ዘወትር ግልጽ፣ ሎጂካዊ የሥነ መለኮት ሥርዓት ይፈልጋሉ፣ አሻሚ፣ ምስያዊ፣ ድራማዊ ዘውግ የሆነውን የአይሁድን አፖካሊፕቲካዊ ሥነ ጽሑፍ በአግባቡ ከመያዝ ይልቅ። ይህ እውነት በሚገባ ተገልጿል፣ በራልፍ ፒ. ማርቲን፣ በዘገባው፣ "የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ አገባብ፣" የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ በሚለው መጽሐፍ፣ በ አይ. ሀዋርድ ማርሻል የተዘጋጀ፡

> "የዚህን ጽሑፍ ድራማዊ ይዘት እስካልተገነዘብን ድረስ፣ እንዲሁም ቋንቋው እንዴት እንደተገለጸ እስካላስታወስን፣ ሃይማኖታዊ እውነታን እንደሚገልጽ መኪና፣ አፖካሊፕስን ከመረዳት በከፋ መልኩ እንስታለን፣ እንዲሁም እይታውን በስሕተት ለመተርጎም እንሞክራለን፣ መጽሐፉን ልክ እንደ ተራ ጽሑፍ በመውሰድ፣ ሁነቶቹን በማራኪነትና በታሪክ ማስረጃ ላይ እናተኩራለን። ኋለኛው ሂደት ላይ ማተኮር ወደ ሁሉም ዓይነት የትርጓሜ ችግሮች መግባት ነው። እጅግ በበረታ መልኩም እሱ መሠረታዊውን የአፖካሊፕቲክ ፍችን ማዛባት ያስከትላል፣ እናም ይህኛውን የአዲስ ኪዳን ክፍል ትልቅ ዋጋ ማሳጣት ያስከትላል፣ እንደ ድራማዊ ማስረገጫ በአፈ-ታሪካዊ ቅኔ ቋንቋ፣ የሉዓላዊው እግዚአብሔር በክርስቶስ እና የእርሱን አገዛዝ አያዎነት፣ ይኸውም ኃይልና ፍቅርን የሚቀላቅለውን (ዝከ. 5፡5፣6፤ አንበሳው በጉ ነው)" (ገጽ 235)።

ደብልዩ. ራንዶልፍ ታቲ በመጽሐፉ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜዎች* እንዳለው፡

> "የትኛውም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ዘውግ በዚህ ዓይነቱ ስሜታዊነት አይነበብም ይህን መሰሉ የአፖካሊፕቲክ የመደበት ውጤት፣ በተለይም የዳንኤል እና የራዕይ መጽሐፍ። ይህ ዘውግ አጥፊ በሆነ የተዛባ ትርጓሜ ታሪክ ተጎሳቁሏል፣ መሠረታዊ የሆነውን ቅርጹን፣ አወቃቀሩን፣ እና ዓላማውን ባለመረዳት። በቅርቡ የሚሆነውን የፍጻሜ ሁኔታ በመግለጡ ምክንያት የመጪው ጊዜ የማሳያ ካርታ ተደርጎ ተወስዷል። የዚህ አተያይ አሳዛኙ ሂደት፣ የመጻሕፍቱ ማጣቀሻ ቅንብብ (ፍሬም) የአንባቢው ዘመነኛ ጊዜ መሆኑ ነው፣ ከደራሲው ይልቅ። ይህ የተዛባ አገባብ በአፖካሊፕቲክ ላይ (በተለይም ራዕይ) ሥራውን አበላሽተውታል፣ የምሥጢር ጽሑፍ እንዲመስል፣ የየዘመኑ ሁነቶች የጽሑፉን ምስያዎች ለመተርጎም ጥቅም ላይ እንዲውሉ… አንደኛ፣ ተርጓሚው መረዳት የሚኖርበት አፖካሊፕቲክ መልእክቱን የሚያስተላልፈው በምስያዎች በኩል መሆኑን ነው። ምስያን ደግሞ በጥሬው መተርጎም፣ ዘይቤ ሆኖ ሳለ፣ የተዛባ አተረጓጎም ነው። ጉዳዩ በአፖካሊፕቲክ ያሉት ሁነቶች ታሪካዊ መሆናቸው አይደለም። ሁነቶቹ ታሪካዊ ሊሆኑ ይችላሉ፤ በርግጥም ተከስተው ሊሆን ይችላል፣ ወይም ይከሰታሉ፣ ነገር ግን ደራሲው ሁነቶቹን የሚያቀርበውና ፍችዎቹን የሚያያይዘው በምስልና ለየት ባለ አጻጻፍ ነው" (ገጽ 137)።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ምስያ መዝገበ ቃላት፣ በራይከን፣ ዊልሆስት እና ሎንግማን III የተዘጋጀ፡

"የዘመኑ አንባቢዎች በዚህ ዘውግ ዘወትር ግራ እንደተጋቡና ተስፋ እንደቆረጡ ነው። ያልተጠበቀ ምናብ እና ከዚህ ዓለም ውጭ የሆነ ልምምድ ያልተለመደና ቅንብራዊ ሊመስል ይችላል፣ በበርካታ ቅዱስ ቃሉ ዘንድ። ይህን ጽሑፍ በፊት ለፊት ዋጋው መውሰድ፣ አብዛኞቹን አንባቢዎች 'ምን መቼ ይሆናል' ወደሚል ግራ መጋባት ይመራቸዋል፣ እናም የአፖካሊፒታዊውን መልእክት ይስታሉ" (ገጽ 35)።

**አምስተኛ ተቃርኖ** (የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን እንደሆነ አልያም ወደፊት እንደሚሆን)

የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን ነው፣ ገና ወደፊት ነው። ይህ ሥነ-መለኮታዊ አያዎ (ፓራዶክስ) በፍጻሜ ዘመን ትንቢት ነጥብ ላይ ይተኮርበታል። አንዱ የብኪን ትንቢቶች ለእስራኤል በጥሬው እንዲፈጸሙ ቢጠብቅ፣ እንግዲያውስ መንግሥቱ የእስራኤል መታደስ፣ ይኸውም ወደ መልከዓ ምድራዊው ስፍራ እና ሥነ መለኮታዊ ቅድመ-ልዕልና ይሆናል! ይህም በቀዳሚነት የሚያደርገው ቤተ ክርስቲያን በምሥጢር መነጠቋን ነው፣ ምዕራፍ 5 ላይ፣ እናም ቀሪዎቹ ምዕራፎች ከእስራኤል ጋር ይዛመዳሉ (ግን ራዕ. 22፡16 ሳይሆን)።

ሆኖም፣ ትኩረቱ በብኪ ተስፋ የተገባው መሲሕ መንግሥት ምርቃት ከሆነ፣ እንግዲያውስ ከክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት ጋር ሆኗል፣ እና ከዚያም ትኩረቱ የክርስቶስ ሥጋዌ፣ ሕይወት፣ ትምህርት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ ሆኗል። ሥነ-መለኮታዊው አጽንዖት የአሁኑ መዳን ነው። መንግሥቱ መጥቷል፣ ብኪ ተፈጽሟል፣ በክርስቶስ መዳንን ለሁሉም በመስጠት፣ የእሱ የሚሊኒየም ገዥነት በጥቂቶች ላይ ሳይሆን!

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሁለቱም የክርስቶስ ምጽአቶች መናገሩ እውነት ነው፣ ግን አጽንዖቱ መቀመጥ ያለበት የት ነው? ለእኔ የሚመስለኝ አብዛኞቹ የብኪ ትንቢቶች የሚያተኩሩት በመጀመሪያ ምጽአቱ ላይ ነው፣ የመሲሐዊ መንግሥት መመሥረት (ዳንኤል 2)። በብዙ መንገዶች ይህ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ገዥነት ምስያ ነው (ዳንኤል 7)። በብኪ ትኩረቱ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ገዥነት ላይ ነው፣ ሆኖም የዛ አገዛዝ አገባቡ የሚገለጠው በመሲሑ አገልግሎት ነው (1 ቆሮ. 15፡26-27)። ጥያቄው የትኛው እውነት ነው የሚል አይደለም፤ ሁለቱም እውነት ናቸው፣ ግን አጽንዖቱ የቱጋ ነው? መባል ያለበት አንዳንድ ተርጓሚዎች በመሲሑ የሚሊኒየም አገዛዝ ላይ ማተኮራቸው ነው (ራዕይ 20) እነሱም የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትኩረት የሆነውን የአብን ዘላለማዊ ገዥነት ይስታሉ። የክርስቶስ ግዛት ቀዳሚ ሁነት ነው። የክርስቶስ ሁለቱም ምጽአቶች በብኪ ግልጽ እንዳልሆኑ ሁሉ፣ እንዲሁ የመሲሑ ጊዜያዊ አገዛዝ!

የኢየሱስ ስብከትና ትምህርት ቁልፉ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። እሱ የአሁን ነው ደኅንነት እና አገልግሎት)፣ መጻዒ ነው (መስፈንና ኃይል)። ራዕይ በመሲሑ የሚሊኒየም አገዛዝ ላይ ካተኮረ (ራዕይ 20)፣ ቀዳሚ ነው እንጂ የመዳረሻ ግብ አይደለም (ራዕይ 21-22)። እሱ ግልጽ አይደለም ከብኪ አኳያ ጊዜያዊ አገዛዝ ማስፈለጉ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ዳንኤል 7 ላይ ያለው የመሲሑ አገዛዝ ዘላለማዊ ነው፣ ሚሊኒየማዊ ሳይሆን።

**ስድስተኛው ተቃርኖ** (የክርስቶስ በቅርቡ መመለስ አልያም የዘገየ ዳግም ምጽአት)

አብዛኞቹ አማኞች ኢየሱስ በቶሎ እንደሚመለስ አስበው ነበር፣ በድንገትና ሳይጠበቅ (ማቴ. 10፡23፤ 24፡27፣34፣44፤ ማርቆስ 9፡1፤ 13፡30፤ ራዕ. 1፡1፣3፤ 2፡16፤ 3፡11፤ 22፡7፣10፣12፣20)። ነገር ግን እያንዳንዱ ተጠባባቂ የአማኞች ትውልድ እስካሁን ድረስ ተሳስቶ ነበር! የኢየሱስ በቅርቡ (ወዲያውኑ) መመለስ ለእያንዳንዱ ትውልድ ብርቱ ቃል ኪዳን ተስፋ ነው፣ በተጨባጭ ግን ለአንዱ ብቻ (ያም የተሳደደው)። አማኞች መኖር ያለባቸው ነገ እንደሚመጣ አድርገው ነው፣ ነገር ግን ዕቅድና ትግበራው ታላቁ ተልዕኮ ነው (ማቴ. 28፡19-20) ቢዘገይ።

አንዳንድ ምንባቦች በወንጌላት (ማርቆስ 13፡10፤ ሉቃስ 17፡2፤ 18፡8) እና 1እና2 ተሰሎንቄ የተመሠረቱት በዘገየው ዳግም ምጽአቱ ላይ ነው (ዳግም ምጽአት)። ቀድመው መሆን ያለባቸው ታሪካዊ ሁነቶች አሉ፡

1. ዓለም አቀፍ ወንጌላዊነት (ማቴ. 24፡14፤ ማርቆስ 13፡10)
2. "የኃጢአት ልጅ መገለጥ" (ማቴ. 24፡15፤ II ተሰ. 2፤ ራዕ. 13)
3. ታላቁ መከራ (ማቴ. 24፡21፣24፤ ራዕ. 13)

የሆን ተብሎ አሻሚነት አለ (ማቴ. 24፡42-51፤ ማርቆስ 13፡32-36)! እያንዳንዱ ቀን የመጨረሻህ እንደሆነ ኑር፣ ነገር ግን ለቀጣዩ አገልግሎት አቅድ ተለማመድም!

**ጽኑዕነት እና ሚዛናዊነት**

ሊባል የሚቻለው ዘመናዊዎቹ የተለያዩ የፍጻሜ ዘመን የትርጓሜ ትምህርት ቤቶች ግማሽ እውነት እንደያዙ ነው። አንዳንድ ጽሑፎችን ደኅና አድርገው ያብራራሉ ይተረጉማሉም። ችግር ያለው ቋሚነትና ሚዛናዊነት ላይ ነው። አዘውትሮም የተቀናበረ ቅድመ-ግምት አለ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ጽሑፍ የሚጠቀም፣ ቀደም ብሎ የተሰናዳውን ሥነመለኮታዊ መዋቅር የሚሞላ። መጽሐፍ ቅዱስ ሎጂካዊ፣ ቅደም ተከተላዊ፣ ስልታዊ የፍጻሜ ትንቢትን አይገልጥም። እሱ እንደ ቤተሰብ ፎቶ ማሳያ ዓይነት ነው። ምስሎቹ እውነት ናቸው፣ ግን ዘወትር በቅደም ተከተል፣ በይዘት፣ በሎጂካዊ አደራደር አይደሉም። አንዳንዶቹ ፎቶዎች ከመያዣው ወጥተዋል እናም ኋለኞቹ ትውልዶች የሆኑ የቤተሰቡ አባላት እንዴት መልሰው እንደሚያስገቧቸው በትክክል አያውቁም። ራዕይን ለመተርጎም ቁልፉ የዋናው ደራሲ ሐሳብ ነው፣ በእሱ ጽሑፋዊ ዘውግ ተመርጦ እንደተገለጠው። አብዛኞቹ ተርጓሚዎች የራሳቸውን የትርጓሜ መሣርያዎች እና ደንቦች ለመጠቀም ይሞክራሉ፣ ከሌላው የአኪ ዘውግ፣ ለራሳቸው የራዕይ ትርጓሜ። በብኪ ላይ ያተኩራሉ፣ የኢየሱስንና የጳውሎስን ትምህርቶችን ከመፍቀድ ይልቅ፣ ሥነ መለኮታዊውን መዋቀር ከማዋቀርና ራዕይ ማሳያ እንዲሆን ከማድረግ ይልቅ።

መቀበል የሚኖርብኝ ይህንን ሐተታ ያደረግሁት በፍርሃትና በድንጋጤ መሆኑን ነው፣ በራዕ. 22፡18-19 ርግማን ሳይሆን፣ ግን ይህ መጽሐፍ በፈጠረው የትርጓሜ ውዝግብ ምክንያት፣ እናም በእግዚአብሔር ሕዝብ መሐል እየፈጠረ ባለው። የእግዚአብሔርን

መገለጥ እወዳለሁ። እሱ እውነት ነው፣ ሰዎች ሁሉ ሐሰተኞች ሲሆኑ (ሮሜ. 3፡4)! እባክዎን ይህንን ሐተታ ሐሳብ ለመቀስቀሻ ሙከራ አድርጋችሁ ውሰዱት እንጂ እንደ ተጠናቀቀ ሐሳብ አትመልከቱት፣ እንደ መንገድ ላይ ምልክት እንጂ እንደ መንገድ ካርታ አትዩት፣ እንደ "ቢሆንስ፣" እንጂ "ጌታ እንዲህ ይላል" ሳይሆን። እኔ ፊት ለፊት መጥቻለሁ፣ ከነ ገዛ ራሴ ጉድለት፣ ፍርደ ገምድልነት፣ እና ሥነ መለኮታዊ አጀንዳ። ሌሎች ተርጓሚዎችንም ተመልክቻለሁ። እሱም ከሞላ ጎደል የሚመስለው፣ ሰዎች የፈለጉትን ሁሉ ከራዕይ ውስጥ እንደሚያገኙ ነው። ዘውጉ ራሱን ለመዛባት አመቺ አድርጓል! ሆኖም፣ እሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው፣ ለሆነ ዓላማ። አቀማመጡም እንደ ማጠቃለያ "ቃል" መሆኑም በድንገት አይደለም። ከእግዚአብሔር መልእክት አለው፣ በየአንዳንዱ ትውልድ ላሉት ልጆቹ። እግዚአብሔር እንድንረዳ ይፈልጋል! እጃችንን እናያይዝ፣ ከተወሰነ ወገን ሳይሆን፤ ግልጽና ማዕከላዊ የሆነውን እናጽና፣ የሚሆነውን፣ ሊሆን የሚችለውን፣ ምናልባት የሚሆነው እውነት ሁሉ ሳይሆን። እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን!

ይህንን ባዶ ቦታ የገዛ ራስህን ቅድመ ግምት ለመዘርዘር ተጠቀምበት፣ ራዕይን እንዴት እንደምትተረጉም። ሁላችንም የራሳችንን ግምቶች ይዘን ወደዚህ መጽሐፍ ትርጓሜ እንመጣለን። እነሱን መለየት ተጽዕኗቸውን ለማስቀረትና የራሳችንን ቀኖናዊነት ለመገደብ ይረዳናል።

1.
2.
3.
4.

# መግቢያ ለብሉይ ኪዳን ትንቢት

I. መግቢያ

ሀ. የመክፈቻ መግለጫ

1. አማኙ ማኅበረሰብ ትንቢትን እንዴት እንደሚተረጉም አይስማማም። ሌሎች እውነቶች የጸኑት ቀጥተኛ በሆነ አቋም ነው፣ በዘመናት መሐል ሁሉ፣ ይሄኛው ግን ሳይሆን።
2. የብኪ ትንቢት እጅግ የተደራጁ በርካታ ደረጃዎች አሉ
   ሀ. ቅድመ-ንጉሣዊ (ከንጉስ ሳኦል በፊት)
      1) ነቢያት ተብለው የሚጠሩ ግለሰቦች
         ሀ) አብርሃም - ዘፍ. 20፡7
         ለ) ሙሴ – ዘኍ. 12:6-8፤ ዘዳ. 18:15፤ 34:10
         ሐ) አሮን – ዘጸ. 7:1 (የሙሴ ቃል አቀባይ)
         መ) ማርያም – ዘጸ. 15:20
         ሠ) ሜዳድና ኤልዳድ – ዘኍ. 11:24-30
         ረ) ዲቦራ – መሳ. 4:4
         ሰ) ስሙ ያልተጠቀሰ – መሳ. 6:7-10
         ሸ) ሳሙኤል – 1 ሳሙ. 3:20
      2) እንደ ቡድን የተጠቀሱ ነቢያት – ዘዳ. 13:1-5፤ 18:20-22
      3) የነቢያት ወገን ጉባዔዎች – 1 ሳሙ. 10:5-13፤ 19:20፤ 1 ነገሥ. 20:35፣41፤ 22:6፣10-13፤ II ነገሥ. 2:3፣7፤ 4:1፣ 38፤ 5:22፤ 6:1፣ ወዘተ.
      4) መሲሕ ነቢይ ተብሎ ይጠራል - ዘዳ. 18:15-18
   ለ. ያልተጻፉ ንጉሣዊ ነቢያት (ለንጉሥ ያቀርባሉ)
      1) ጋድ – 1 ሳሙ. 7:2፤ 12:25፤ II ሳሙ. 24:11፤ 1 ዜና. 29:29
      2) ናታን – II ሳሙ. 7:2፤ 12:25፤ 1 ነገሥ. 1:22
      3) አሂጃ – 1 ነገሥ. 11:29
      4) ጀሁ – 1 ነገሥ. 16:1፣7፣12
      5) ስሙ ያልተጠቀሰ – 1 ነገሥ. 18:4፣13፤ 20:13፣22
      6) ኤልያስ – 1 ነገሥ. 18፤ II ነገሥ. 2
      7) ሚልክያስ – 1 ነገሥ. 22
      8) ኤልሳዕ – II ነገሥ. 2:8፣13
   ሐ. የጥንታዊ ጽሑፍ ነቢያት (እነሱም ለሕዝብ እንዲሁም ለንጉሥ ያቀርባሉ)፡ ኢሳይያስ — ሚልክያስ (ከዳንኤል በቀር)

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት

1. *ro'eh* (BDB 909) = ነቢይ፣ 1 ሳሙ. 9፡9። ይህ ማጣቀሻ የሚያሳየው *Nabi፣* የሚለውን ቃል ትርጉም ነው፣ እሱም "ነቢይ" ማለት ነው፣ የመጣበትም ሥር፣ "መጣራት" ነው። *ro'eh* ከአጠቃላይ የዕብራይስጥ ቃል "ማየት" ነው። ይህ ሰው የእግዚአብሔርን መንገዶችና ዕቅዶች ይገነዘባል፣ እናም በአንድ ነገር ላይ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማጽናት ይማከራል።
2. *hozeh* (BDB 302) = ነቢይ፣ II ሳሙ. 24፡11። እሱም በመሠረቱ የ *ro'eh* ተመሳሳይ ነው። እሱም ከማይዘወተረው የዕብራይስጥ ቃል "ማየት" ነው። የግስ ዓይነቱ ነቢያትን ለማመልከት አዘውትሮ ይጠቀሳል።
3. *nabi'* (BDB 611) = ነቢይ፣ የአካድያን ግስ *nabu* = "መጠራት" ተጓዳኝ ነው እና የዓረብ *naba'a* = "ማስታወቅ።" ይህ እጅግ የለመደ የብኪ ቃል ነው፣ ነቢይን ለመግለጽ። እሱም ከ300 ጊዜ በላይ ተብሏል። ርግጠኛው ሥርወ-ቃል በትክክል አይታወቅም፣ ግን "መጥራት" በአሁን ጊዜ የተሻለ አማራጭ ይመስላል። ሊሆን የሚችል የተሻለ ግንዛቤ የሚመጣው ከያህዌ የሙሴ ገለጻ ነው፣ ከፈርዖን ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በአሮን በኩል መሆኑ (ዘጸ. 4:10-16፤ 7:1፤ ዘዳ. 5:5). ነቢይ በእግዚአብሔር በኩል ለሕዝቡ የሚናገር ነው (አሞጽ 3:8፤ ኤር. 1:7፣17፤ ሕዝ. 3:4)።
4. ሁሉም ሦስቱም ቃላት ለነቢይነት አገልግሎት 1 ዜና 29፡29 ጥቅም ላይ ውለዋል፤ ሳሙኤል - *Ro'eh*፤ ናታን - *Nabi'*፤ እና ጋድ - *Hozeh.*
5. *'ish ha - 'elohim*፣ "የእግዚአብሔር ሰው" የሚለው ሐረግ፣ ደግሞ ለእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ሰፋ ያለ ትርጉም አለው። እሱም 76 ጊዜ ያህል በብኪ ለ"ነቢይ" ጥቅም ላይ ውሏል።
6. "ነቢይ" የሚለው ቃል መነሻው ግሪክ ነው። የመጣውም (1) *pro* = "ቀድሞ" ወይም "ለ"፤ (2) *phemi* = "መናገር" ነው።

II. የትንቢት ፍቺ

ሀ. "ትንቢት" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ሰፋ ያለ የፍቺ መስክ አለው፣ ከእንግሊዝኛ ይልቅ። አይሁድ የታሪክ መጻሕፍት የሆኑትን ከኢያሱ እስከ ነገሥት (ከሩት በስተቀር) ያሉትን ለይተዋቸዋል፣ "ቀደምት ነቢያት።" ሁለቱም፣ አብርሃም (ዘፍ.

20፡7፤ *መዝ.* 105፡5) እና ሙሴ (ዘዳ. 18፡18) እንደ ነቢያት ተሰይመዋል (ደግሞም ማርያም፣ ዘጸ. 15፡20)። ስለዚህ፣ ከይሆናል የእንግሊዝኛ ፍቺ ተጠበቁ!

ለ. "ትንቢታዊነት ተቀባይነት ባለው መንገድ ታሪክን ከመረዳት አኳያ ሊገለጽ ይችላል፣ እሱም ፍችን የሚቀበለው ከመለኮታዊ ይዘት፣ ከመለኮታዊ ዓላማ፣ ከመለኮታዊ ተሳትፎ አኳያ ብቻ ነው" (*የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች መዝገበ-ቃላት*፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 896)።

ሐ. "ነቢይ ፈላስፋ አይደለም፣ አልያም ስልታዊ ሥነ-መለኮታዊ፣ ነገር ግን የኪዳን መካከለኛ ነው፣ እሱም የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ሕዝቡ የሚያመጣ፣ መጻዒያቸውን መልክ የሚያስይዝ፣ የአሁኗቸውን ተሓድሶ በማድረግ" ("ነቢያትና ትንቢት፣" ኢንሳይክሎፔዲያ ጁዳይካ፣ ቅጽ 13፣ ገጽ 1152)።

III. የትንቢት ዓላማ

ሀ. ትንቢት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይናገር ዘንድ መንገድ ነው፣ አሁን ላሉበት መቼት ምሪት በመስጠት፣ እንዲሁም እሱ ሕይወታቸውንና የዓለም ሁነቶችን እንደሚቆጣጠር ተስፋ እንዲያደርጉ። መልእክታቸውም በመሠረቱ የተጠቃለለ ነው። ማለትም ለመገሠጽ፣ ለማበረታታት፣ እምነትንና ንስሐን ለመፍጠር፣ እና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ራሱና ስለ ዕቅዱ ለመጠቆም። ዘወትር እሱ ጥቅም ላይ የሚውለው በእግዚአብሔር የተመረጠውን ቃል አቀባይ በግልጽ በመግለጥ ነው (ዘዳ. 13፡1-3፤ 18፡20-22)። ይህ በጥቅሉ ሲወሰድ መሲሕን ያመለክታል።

ለ. ነቢዩ ዘወትር የዘመኑን ታሪካዊ ወይም ሥነ-መለኮታዊ ቀውስን ይወስድና በፍጻሜአዊ መቼት ያቀናብረዋል። ይህ የታሪክ የፍጻሜ ዘመን አተያይ (ፍጻሜያዊ) ለእስራኤል እና ለስሜቷ የተለየ ነው፣ መለኮታዊ መመረጥና የኪዳን ተስፋዎች።

ሐ. የትንቢት አገልግሎት ለማመዛዘን ይመስላል (ኤር. 18፡18) የሊቀ ካህናቱን አገልግሎት ለመተካት፣ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማወቂያ መንገድ። ኡሪምና ቱሚም ወደ ቃላዊ መልእክት ላቅ አሉ፣ በእግዚአብሔር ቃል አቀባይ። የነቢይ አገልግሎት በእስራኤል ያለፈ ይመስላል፣ ከሚልክያስ በኋላ (ወይም ከዜና መዋዕል መጻፍ በኋላ)። እሱም እስከ 400 ዓመት ድረስ አልተከሰተም፣ እስከ ዮሐንስ መጥምቁ። የአዲስ ኪዳን "የትንቢት" ስጦታ ከብኪ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ግልጽ አይደለም። የአዲስ ኪዳን ነቢያት (ሐዋ. 11፡27-28፤ 13፡1፤ 14፡29፣32፣37፤ 15፡32፤ 1 ቆሮ. 12፡10፣28-29፤ ኤፌ. 4፡11) የአዲስ መገለጥ ገላጮች አይደሉም፣ በተወሰነ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ቀደም ብለው የሚገልጡ ወይም የሚተነብዩ ናቸው።

መ. ትንቢት በተፈጥሮው ያላጠቃለለ ወይም ቀድሞ የተተነበየ አይደለም። ትንበያ የእሱን አገልግሎት፣ እና የእሱን መልእክት ለማጽናት አንደኛው መንገድ ነው ፣ ግን መታሰብ ያለበት "…ከ2% ያነሰው የብኪ ትንቢት መሲሐዊ ነው። ከ5% ያነሰ በተለይ የሚገልጸው የአዲስ ኪዳኑን ዘመን ነው። ከ1% ያነሰው ወደፊት ስለሚመጡ ሁነቶች ነው" ፊ እና ስቱዋርት፣ *መጽሐፍ ቅዱስን ከነ ሙሉ ጠቀሜታው ስለማንበብ*፣ ገጽ 166)።

ሠ. ነቢያት ለሕዝቡ እግዚአብሔርን ሲወክሉ፣ ካህናት ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይወክላሉ። ይህ አጠቃላይ መግለጫ ነው። የተለየነት ያላቸው አሉ፣ እንደ ዕንባቆም፣ እግዚአብሔርን በጥያቄ የሚያናግር።

ረ. አንደኛው ነቢያትን መረዳት አስቸጋሪ የሚሆንበት ምክንያት መጽሐፋቸው እንዴት እንደተዋቀረ አለማወቃችን ነው። ቅደም ተከተላዊ አይደሉም። ጭብጣዊ ይመስላሉ፣ ግን ሁሌ አንዱ እንደሚጠበቀው አይደሉም። ዘወትርም ግልጽ የሆነ ታሪካዊ መቼት፣ የጊዜ ቅምብብ፣ ወይም ግልጽ የሆነ ምድብ በትንበያዎቹ መሐል የለም፤ አስቸጋሪ ነው (1) መጻሕፍቱን በአንድ ጊዜ ቁጭታ ማንበብ አለመቻሉ፤ (2) በርዕሰ ጉዳይ ዝርዝሩን ማውጣት አለመቻሉ፤ እና (3) በእያንዳንዱም ትንቢት ላይ ማዕከላዊውን ሐሳብ ወይም የደራሲውን ሐሳብ ለማስረገጥ አይቻልም።

IV. የትንቢት ባሕርያት

ሀ. በብሉይ ኪዳን "ነቢይ" እና "ትንቢት" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ እያደገ የመጣ ይመስላል። በጥንታዊው እስራኤል የነቢያት ኅብረት እየጎለበተ መጥቷል፣ እንደ ኤልያስና ኤልሳዕ ባሉ ጠንካራና ሞገስ ባላቸው መሪዎች እየተመራ። አንዳንድ ጊዜ "የነቢያት ልጆች" የሚለው ሐረግ ይህን ቡድን ለመጥራት ጥቅም ላይ ውሏል (2 ነገሥት 2)። ነቢያቱ በጊዜው በተመስጦ ዓይነቶች የመወሰድ ባሕርይ ነበራቸው (1 ሳሙ. 10፡10-13፤ 19፡18-24)።

ለ. ሆኖም፣ ጊዜው ፈጥኖ ወደ ግለሰብ ነቢያት ተላለፈ። ነቢያት ነበሩ (ሁለቱም፣ እውነተኛና ሐሰተኛ) ከንጉሡ ጋር የሚገለጡና በቤተ ምንግሥት የሚኖሩ (ጋድ፣ ናታን)። ደግሞም፣ ነጻ የሆኑ ነበሩ፣ አንዳንዴም ከእስራኤል ማኅበረሰብ አቋም ጋር ፈጽሞ የማይገናኙ (አሞጽ)። እነርሱም ወንድም ሴትም ናቸው (2 *ነገሥ.* 22፡14

ሐ. ነቢይ ዘወትር መጻኢውን የሚገልጽ ነው፣ በግለሰቡ ወይም በሕዝቡ የወዲያውኑ ምላሽ ላይ በመመርኮዝ። ዘወትርም የነቢዩ ተግባር የእግዚአብሔርን ሁለንተናዊ ዕቅድ ለፍጥረቱ ማሳየት ነበር፣ ይኸውም በሰዎች ምላሽ የማይታጠፈውን። ይህ ሁለንተናዊ የፍጻሜ መዳረሻ ዕቅድ በእስራኤል ነቢያት ዘንድ የተለየ ነበር፣ በጥንታዊው ቅርብ ምስራቅ። ትንበያና የኪዳን ታማኝነት የትንቢታዊው መልእክት መንታ ማዕከላዊ ነጥብ ነው (ፊ እና ስቱዋርት፣ ገጽ 150)። ይኸም የሚያመለክተው ነቢያት በቀዳሚነት በትኩረታቸው የተጠቃለሉ መሆኑን ነው። እነርሱም ዘወትር፣ ግን ያላጠቃለለ ባልሆነ፣ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራሉ።

አብዛኞቹ ትንበያዎች የሚቀርቡት በቃል ነበር። ኋላ ላይ ነው በጭብጥና በቅደም ተከተል የተደባለቁት፣ ወይም በሌሎቹ የቅርብ ምስራቅ ሥነ-ጽሑፍ ዘውጎች፣ አሁን እኛ የማናገኛቸው። ቃላዊ ከመሆኑ የተነሣ እንደ ጽሑፍ ስድ ንባብ

የተዋቀረ አልነበረም። ይህም መጻሕፍቱን በቀጥታ ዘልቆ ለማንበብ አስቸጋሪ አድርጓቸዋል እንዲሁም ለመረዳት አስቸጋሪ፣ የተለየ ታሪካዊ መቼት እስከሌለ ድረስ። ነቢያት በርካታ ፈርጆችን ተጠቅመዋል መልእክታቸውን ለማስተላለፍ

1. የፍርድ ቤት ትዕይንት — እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ፍርድ-ቤት ይወስዳል፤ እሱም ዘወትር የፍቺ ጉዳይ ነው፣ እዚያም ያህዌህ ሚስቱን ሲተው (እስራኤል) ታማኝ ስላለመሆኗ (ሆሴዕ 4፤ ሚኪያስ ^)።
2. የቀብር ሙሾ — የዚህ ዓይነቱ መልእክትና ባሕርይ የተለየ ልኬታ "ወየው" እንደ ልዩ ቅርጽ ይታያል (ኢሳይያስ 5፤ ዕንባቆም 2)።
3. የኪዳን ባርኮት መግለጫ — የኪዳኑ ሁኔታዊ ተፈጥሮ አጽንዖት ይሰጠዋል እንዲሁም የሚያስከትለው ውጤት፣ በአዎንታም ሆነ በአሉታ፣ ለመጻኢው ጊዜ ይገለጣሉ (ዘዳግም 27-28)።

V. ለእውነተኛ ነቢይ መለያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫዎች

ሀ. ዘዳግም 13፡1-5 (ትንበያዎች/ምልክቶች)
ለ. ዘዳግም 18፡9-22 (ሐሰተኛ ነቢያት/እውነተኛ ነቢያት)
ሐ. ሁለቱም ወንዶችና ሴቶች እንደ ነቢያት ወይም ነቢይት ይጠራሉ

1. ማርያም - ዘጸአት 15
2. ዲቦራ - መሳፍንት 4፡4-6
3. ሁልዳህ - 2 ነገሥት 22፡14-20፤ 2 ዜና 34፡22-28

በአካባቢያዊው ባህል ነቢያት በመተንበይ ስጦታቸው ይታወቃሉ። እነርሱም በእስራኤል የሚታወቁት

1. በሥነ-መለኮታዊ ፍተና - የያህዌን ስም በመጠቀም
2. በታሪካዊ ፍተና - ትክክለኛ ትንቢቶች

VI. ትንቢትን ለመተርጎም ረጂ መመሪያዎች

ሀ. የዋናውን ነቢይ (አዘጋጅ) ሐሳብ ፈልግ፣ ታሪካዊ መቼቱን በመመዝገብ እና የእያንዳንዱን ትንበያ ጽሑፋዊ ዐውደ-ጽሑፍ በመመዝገብ። እሱም ዘወትር እስራኤል የሙሴን ኪዳን መስበሩን ያካትታል።
ለ. ሙሉውን ትንበያ አንብብና ተርጉም፣ ክፍሉን ብቻ ሳይሆን፤ የይዘቱን ዝርዝር አውጣ። ከአካባቢው ትንበያዎች ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ተመልከት። የሙሉውን መጽሐፍ የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር ለማውጣት ሞክር (በጽሑፋዊ ምድብ እና በአንቀጽ ደረጃ)።
ሐ. የምንባቡን እማሬያዊ (ጥሬያዊ) ትርጉም ገምት፣ ከራሱ ከጽሑፉ ፍካሬያዊ (ዘይቤአዊ) አጠቃቀም እስከምታገኝ ድረስ፤ ከዚያም ዘይቤአዊ ቋንቋውን ወደ ስድ ንባብ ለመቀየር ሞክር።
መ. ተምሳሌታዊ ድርጊቶችን ከታሪካዊ መቼትና ከትይዩ ምንባቦች አኳያ ተንትን። ማስታወስህን ርግጠኛ ሁን፣ ይህ ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ ጽሑፍ መሆኑን፣ ዘመናዊ ምዕራባዊ ጽሑፍ ሳይሆን።

ሠ. ትንበያዎችን በጥንቃቄ ያዝ

1. እነሱ በተለየ መልኩ በደራሲው ጊዜ ናቸውን?
2. እነሱ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ተፈጽመዋልን?
3. የወደፊት ሁነቶች ናቸውን?
4. በዘመኑ የሚሆን ፍጻሜ አላቸውን እንዲሁም ወደፊት የሚሆን ፍጻሜ?
5. የመጽሐፍ ቅዱስ ደራስያን ምላሾችህን እንዲመሩ ፍቀድ፣ ዘመናዊዎቹ ደራስያን ሳይሆኑ።

ልዩ ትኩረቶች፡

1. ትንበያው በሁኔታዊ ምላሽ ተመልክቷልን?
2. ትንቢቱ ለማን እንደሆነ ርግጠኛ ነውን (ለምን)?
3. ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እና/ወይም ለታሪካዊ የበዛ ፍጻሜ ዕድል አለውን?
4. የአዲ ደራስያን በተመስጦ ሥር መሲሑን በብሉ በብዙ ቦታ መመልከት ችለዋል፣ ለእኛ ግልጽ ባይሆኑም። ሰፊ ምድቦችን ወይም ቃላትን የተጠቀሙ ይመስላሉ። እኛ ስላልተመሰጥን፣ ይሄንን አገባብ ለእነርሱ ብንተወው የተሻለ ነው።

VII. ረጂ መጻሕፍት

*የማረሻ ጫፍ እና የመቁረጫ ማጭድ፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት እና የአፖካሊፕትን ቋንቋ ዳግም ማሰብ* በዲ. ብሬንት ሳንዲ
*የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መመርያ* በካርል ኢ. አርመርዲንግ እና ደብልዩ. ዋርድ ጋስኩ
*መጽሐፍ ቅዱስን ከነሙሉ ጠቀሜታው ማንበብ* በጎርደን ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት
*ባሪያዎቹ ነቢያት* በኤድዋርድ ጄ. ያንግ
*የአብራሪ መጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣* ቅጽ 6፣ "ኢሳይያስ - ሕዝቅኤል፣" ዞንደርቫን
*የኢሳይያስ ትንቢት* በጄ. ኤ. አሌክሳንደር፣ 1976፣ ዞንደርቫን
*የኢሳይያስ ማብራሪያ* በኤች. ሲ. ሉፖልድ፣ 1971፣ ቤከር

# የዮሐንስ ራዕይ መግቢያ

## የመክፈቻ መግለጫዎች

ሀ. አብዛኛው የአዋቂነቴ የትምህርት/ሥነ-መለኮት ሕይወቴ የነበረኝ ቅድመ-ግምት፣ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑ "በጥሬው" ይወስዱታል የሚል ነበር (እና ያም ለታሪካዊ ትርክት በርግጥ እውነት ነበር)። ሆኖም፣ በጣም ግልጽ እየሆነልኝ መጣ፣ ማለትም፣ ትንቢትን፣ ቅኔን፣ ምሳሌዎችን፣ እና አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፎችን በጥሬው መውሰድ የተመስጧዊ ጽሑፉን ነጥብ መሳት ነው። የደራሲው ሐሳብ፣ ጥሬነቱ ሳይሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ሁነኛ ቁልፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ መልኩ በጣም እንዲናገር ማድረግ (በተለይ ዶክትሪናዊ) አደገኛና አሳሳች ነው፣ ከዋናው ተመስጧዊ ጸሐፊ ሐሳብ ባነሰ መልኩ እንደ ማድረግ። ትኩረቱ መሆን ያለበት ሰፋ ባለ ዐውደ-ጽሑፍ ነው፣ በታሪካዊ መቼት፣ እና ደራሲው በጽሑፉ ውስጥ በገለጸበት ሐሳብ እና በዘውግ ምርጫው። ዘውግ የሚታየው በደራሲውና በአንባቢው መካከል እንዳለ ውል ነው። ይህንን ማስረጃ መሳት በርግጥ ወደ ተሳሳተ ትርጉም ያመራል!

የራዕይ መጽሐፍ በርግጥ እውነት ነው፣ ነገር ግን ታሪካዊ ትርክት አይደለም፣ በጥሬው የሚወሰድ አይደለም። ዘውጉ ራሱ ይህንን ነጥብ ያስጮኻል፣ ዝም ብለን ብናደምጠው እንኳ። ይህ ማለት ተመስጧዊ ወይም እውነት አይደለም ማለት አይደለም፤ ፍካሬያዊ ነው፣ ምሥጢራዊ፣ ተምሳሌታዊ፣ ዘይቤአዊ፣ እና ምናባዊ። የአንደኛው ክፍለ ዘመን አይሁድና ክርስቲያኖች የዚህ ዓይነቱን ጽሑፍ የለመዱት ነበሩ፣ እኛ ግን አይደለንም! የክርስቲያን ተምሳሌታዊነት *በቀለበቶቹ ጌታ* ወይም *የናርኒያ ዜና መዋዕል* ምናልባት ዘመናዊ ትይዩዎች ይሆናሉ።

ለ. ራዕይ የተለየ የአይሁድ ጽሑፋዊ ዘውግ ነው፣ አፖካሊፕቲካዊ። እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ተቃርኖ በተሞሉ ጊዜያት ነው (ማለትም፣ እስራኤል በአሕዛብ ኃይል ሲጨቆኑ) እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚቆጣጠርና ለሕዝቡም መዳንን እንደሚያመጣ ቁርጠኝነቱን ለማሳየት። የዚህ ዓይነቱ ሥነ-ጽሑፍ ባሕርይ የሚያደርገው

1. የእግዚአብሔርን ሁለንተናዊ ሉዓላዊነት ጠንካራ ስሜት (አሀድነት እና ቁርጠኝነት)
2. በመልካምና በክፉ መሐከል ያለውን ትግል፣ ይህ ክፉ ዘመንና መጪው የጽድቅ ዘመን (ምንታዌነት)
3. የምሥጢራዊ ቃላት አጠቃቀም (ዘወትርም ከብሉይ ወይም ከበይነ ኪዳናት የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ)
4. ቀለሞችን፣ እንስሳትን፣ አንዳንዴም እንስሳትን/ሰዎችን መጠቀሙ
5. ተምሳሌታዊ ቁጥሮችን መጠቀሙ (ማለትም፣ 4፣ 6፣ 7፣ 10፣ 12)
6. የመላእክትን ማዕከላዊነት፣ በራዕይና በሕልም መጠቀሙ፣ ግን ዘወትር በመላእክት ትርጓሜ በኩል
7. በቅድሚያም የሚያተኩረው ቶሎ በመምጣቱ ላይ ነው፣ የመጨረሻው ዘመን (የአዲሱ ዘመን) ጫፍ የወጡ ሁነቶች
8. የተወሰኑ ተምሳሌታዊ ስብስቦችን መጠቀሙ፣ እውነታን ሳይሆን፣ የፍጻሜ ዘመኑን መልእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመገናኘት
9. አንዳንድ የዚህ ዓይነት ዘውግ ምሳሌዎች፡
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
      (1) ኢሳይያስ 13-14; 24-27; 56-66
      (2) ሕዝቅኤል 1፤ 26-28፤ 33-48
      (3) ዳንኤል 7-12
      (4) ኢዩኤል 2:28-3:21
      (5) ዘካርያስ 1-6፣ 12-14
   ለ. አዲስ ኪዳን
      (1) ማቴዎስ 24፣ ማርቆስ 13፣ ሉቃስ 21፣ እና I ቆሮንቶስ 15 (በአንዳንድ መንገዶች)
      (2) II ተሰሎንቄ 2 (በብዙ መንገዶች)
      (3) ራዕይ (ምዕራፍ 4-22)
   ሐ. ዳንኤል 7-12 እና ራዕ. 4-22 የታወቁ ምሳሌዎች ናቸው፣ የዚህ ዘውግ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ
10. ካኖናዊ ያልሆኑ (ከዲ. ኤስ. ሩሴል የተወሰዱ፣ የአይሁድ አፖካሊፕቲክ ዘዴና መልእክት፣ ገጽ 37-38)
   ሀ. 1 ሔኖክ፣ 2 ሔኖክ (የሔኖክ ምሥጢራት)
   ለ. መጽሐፍ ጁቢሊስ
   ሐ. የሲቢሊን ትንቢቶች III፣ IV፣ V
   መ. የአስራ ሁለቱ አባቶች ምስክርነት
   ሠ. የሰሎሞን መዝሙራት
   ረ. የሙሴ ቃል (መወሰድ)
   ሰ. የኢሳይያስ ሰማዕትነት
   ሸ. የሙሴ አፖካሊፕስ (የአዳምና ሔዋን ሕይወት)
   ቀ. የአብርሃም አፖካሊፕስ
   በ. የአብርሃም ምስክርነት
   ተ. 2 ኢስድራስ (4 ኢስድራስ)

ቸ. 2 እና 3 ባሮክ

II. በዚህ ዘውግ ውስጥ የምንታዌነት ስሜት አለ። እሱም እውነታን የሚያየው ተለጣጣቂነት ባለው ምንታዌነት፣ ተቃርኖ፣ ወይም ክርክር ነው (ይህም በዮሐንስ ጽሑፎች የተለመደ ነው) መካከሉም፡
ሀ. ሰማይ - መሬት
ለ. ክፉ ዘመን (ክፉ ሰዎችና ክፉ መላእክት) - አዲሱ የጽድቅ ዘመን (መልካም ሰዎችና መልካም መላእክት)
ሐ. የአሁኑ ሕላዌ - የወደፊቱ ሕላዌ
እነዚህ ሁሉ እያመሩ ያሉት በእግዚአብሔር እየመጣ ያለውን ለመቀዳጀት ነው። ይህ ዓለም እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገው አይደለም፣ ነገር ግን እሱ ማቀዱን፣ መሥራቱን፣ ፍቃዱን ማካሄዱን ቀጥሏል፣ በዔድን ገነት የተጀመረውን የቅርብ ወዳጅነት ለመመለስ። የክርስቶስ ሁነት የእግዚአብሔር ዕቅድ ዋነኛ አካል ነው፣ ግን ሁለቱ ምጽአቶች የአሁኑን ምንታዌነት አምጥተዋል።

ሐ. እነዚህ አፖካሊፕቲካዊ ሥራዎች በቃል ፈጽመው አይቀርቡም፤ ዘወትር ይጻፋሉ። እጅግ መዋቅራዊ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ናቸው። መዋቅሩም ለሁነኛ ትርጓሜ አስፈላጊ ነው። የራዕይ መጽሐፍ የታቀደ መዋቅር ዋነኛ ክፍል ሰባት ጽሑፋዊ ምድቦች ናቸው፣ እነሱም በተወሰነ መልኩ እርስ በርሳቸው ትይዩ የሆኑ (ምሳ. ሰባቱ ማኅተሞች፣ ሰባቱ መለከቶች፣ እና ሰባት ጽዋዎች)። በያንዳንዱ ዑደትም ፍርዱ ይጨምራል፡ ማኅተሞች፣ ¼ ጥፋት፡ መለከቶች፣ 1/3 ጥፋት፡ ጽዋዎች፣ አጠቃላይ ጥፋት። በእያንዳንዱ ጽሑፋዊ ምድብ የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ወይም አንዳንድ የፍጻሜ ዘመን ሁነት ይኖራል፡ (1) ስድስተኛ ማኅተም፣ 6፡12-17፤ (2) ሰባተኛ መለከት፣ 1፡15-18፤ የመጨረሻው ዘመን መልአክ ፍርድ 14፡14-20፤ (3) ሰባተኛው ጽዋ፣ 16፡17-21 በድጋሚም 19፡11-21 ገናም በድጋሚ 22፡6-16 (ደግሞም የእግዚአብሔርን ሦስትዮሽ መጠርያ ተገንዘብ፣ በ1፡4፣8 እና ክርስቶስ በ1፡17፣18፣ “ያለው፣ የነበረው፣ የሚመጣውም፣” ቀሪው ገጽታ በ11፡17 እና 16፡5 ላይ እንደተተወ ተገንዘብ፣ ማለትም የወደፊቱ መጥቷል [ማለትም ዳግም ምጽአት])። ይህ የሚያመለክተው መጽሐፉ በቅደም ተከተል አለመቀመጡን ነው፣ ነገር ግን በብዙ ትዕይንቶች ያለው ድራማ ተመሳሳይ የሆነ ጊዜና ሰዓትን፣ እየጨመረ በሚሄድ ኃይለኛ የብኪ የፍርድ ሐሳብ ያመለክታል (ጀምስ ብሊቪንስ፣ *ራዕይ እንደ ድራማ* እና “የራዕይ ዘውግ” <u>በቅኝትና በአብራሪ፣</u> ሴፕቴ. 1980፣ ገጽ 393-408)።
ሰባት ጽሑፋዊ ክፍሎችና ቅድመ-ታሪክ እና ድኅረ-ታሪክ አለው

1. ቅድመ-ታሪክ፣ 1፡1-8
2. ምዕራፍ 1፡9-3 (ክርስቶስና ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት)
3. ምዕራፍ 4-8፡1 (ሰማይና ሰባቱ ማኅተሞች [2፡1-17 በ6ኛ እና 7ኛ ማኅተሞች መካከል ጣልቃ ገብቷል])
4. ምዕራፍ 8፡2-11 (ሰባት መላእክት በመለከት [10፡1-11፡13 በ6ኛ እና 7ኛ መለከቶች መካከል ጣልቃ ገብቷል])
5. ምዕራፍ 12-14 (ሁለቱ ማኅበረሰቦችና መሪዎቻቸው)
6. ምዕራፍ 15-16 (ሰባት መላእክት ከጽዋ ጋር)
7. ምዕራፍ 17-19 (ባቢሎንና ፍርዷ)
8. ምዕራፍ 20-22፡5 (ፍርድና አዲስ ሰማይና መሬት)
9. ድኅረ-ታሪክ፣ 22፡6-21

ሌለኛው በማጠቃለያ ንድፈ-ሐሳብ የሚያምነው ደራሲ ዊሊየም ሄንድሪክሰን ነው። በመጽሐፉ፣ *ከአሸናፊዎች የሚበልጥ፡* መጽሐፉን በዚህ መልኩ ፍሬ-ሐሳቡን አስቀምጧል፡

1. ምዕራፍ 1-3 (ክርስቶስ በሰባቱ መቅረዞች መካከል)
2. ምዕራፍ 4-7 (የሰባቱ ማኅተሞች መጽሐፍ)
3. ምዕራፍ 8 -11 (ሰባቱ የፍርድ መለከቶች)
4. ምዕራፍ 12-14 (ሴቲቱና ወንዱ ሕፃን በዘንዶውና በረጂዎቹ ተሳደዱ [አውሬውና ጋለሞታዋ])
5. ምዕራፍ 15-16 (ሰባቱ የቁጣ ጽዋዎች)
6. ምዕራፍ 17-19 (የታላቋ ጋለሞታና የአውሬዎቹ ውድቀት)
7. ምዕራፍ 20-22 (በዘንዶው (ሰይጣን) ላይ ፍርድ፣ ቀጥሎም አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም) ገጽ 28

*ከአሸናፊ እንበልጣለን* ላይ፣ ዊሊየም ሄንድሪክሰን፣ ራዕይ ሰባት ክፍሎች አሉት ይላል፡ 1-3፤ 4-7፤ 8-11፤ 12-14፤ 15-16፤ 20-22 እናም እነዚህ እያንዳንዳቸው ትይዩና የክርስቶስን የመጀመሪያ ምጽአትና ዳግም ምጽአት ያለውን ጊዜ የሚሸፍኑ ናቸው (ገጽ 22-31)።

ምንም እንኳ በርግጥም በማኅተሞች፣ መለከቶች፣ እና ጽዋዎች ድራማዊ ትይዩነት ብስማማም፣ ደግሞም በጣም የምማረከው 17-19 ከ20-22 ባለው ትይዩነት ነው (ዳግም ምጽአቱ 19፡11-21 ላይ አለ እና ሌለኛው ዳግም ምጽአት 22፡6-16 ላይ)፣ እያንዳንዳቸው ሰባቱ ክፍሎች በዳግም ምጽአቱ ፍርድ ላይ የቱጋ እንደሚያበቁ ማየት አልቻልኩም፣ በተለይም ምዕራፍ 1-3፣ አንድ አንድ ዓይነት የፍርድ ገጽታ እንደ ፍጻሜ ዘመን ሁነት ካልታየ በቀር (ዝከ. 2:5፣7፣11፣ 16-17፣25-26፤ 3:5፣10፣12፣18-21)። ሆኖም፣ ለእኔ፣ እነዚህ ሰባትዮሽ ማጠቃለያዎች የሙሉውን መጽሐፍ ትይዩአዊ አወቃቀር በደንብ ለመመልከት የሚረዱ ሆነዋል።

መ. ቁጥር “ሰባት” በመጽሐፉ አወቃቀር ላይ ትልቁን ስፍራ እንደሚጫወት ግልጽ ነው፣ በሰባቱ ቤተ ክርስቲያኖች፣ ሰባቱ ማኅተሞች፣ እና ሰባቱ ጽዋዎች ላይ እንደሚችለው። ሌሎች “የሰባት” ምሳሌዎች፡

1. 7 በረከቶች፣ 1:3፤ 14:13፤ 16:15፤ 19:9፤ 20:6፤ 22:7፣14
2. 7 መቅረዞች፣ 1:12
3. 7 የእግዚአብሔር መንፈሶች፣ 1:4፤ 3:1፤ 4:5፤ 5:6
4. 7 ከዋክብት፣ 1:16፣20፤ 2:1
5. 7 የእሳት መብራቶች፣ 4:5
6. 7 የታተሙ ጥቅሎች፣ 5:1
7. 7 ቀንዶች፣ 7 የበጉ ሰባት ዓይኖች፣ 5:6
8. 7 የኢየሱስ የምስጋና ቃሎች፣ 5:12
9. 7 የተፈጥሮ ምልክቶች፣ 6:12-14
10. 7 የሰው ዓይነቶች፣ 6:15
11. 7 የእግዚአብሔር ምስጋና ቃሎች፣ 7:12
12. 7 መላእክት በእግዚአብሔር ፊት፣ 8:2፣6
13. 7 በሰባቱ መላእክት የተያዙ ሰባት መለከቶች፣ 8:6 (15:1፣6፣7፣8፤ 17:1፤ 21:9)
14. 7 ምልክቶች፣ 12:1፣3፤ 13:13፣14፤ 15:1፤ 16:14፤ 19:20
15. 7 ራሶች፣ 7 የቀዩ ዘንዶ ዘውዶች፣ 12:3
16. 7 የባሕሩ አውሬ ራሶች፣ 13:1፤ 17:3፣7
17. 7 መላእክት፣ 14:6-20
18. 7 መቅሠፍቶች፣ 15:1፤ 21:9
19. 7 ተራሮች፣ 17:9
20. 7 ነገሥታት 17:10
21. 7 ነገሮች፣ እነርሱም በምዕራፍ 21-22 ከእንግዲህ ወዲያ የማይኖሩ (21:1፣4[አራት ጊዜ]፤ 21:25፤ 22:3)

ሠ. የዚህ መጽሐፍ ትርጓሜ ለሥነ-መለኮታዊ አድሏዊነት የተጋለጠ ነው። የአንዱ ቅድመ-ግምት ትርጓሜውን ወደ አሻሚ ዝርዝሮች ያመራዋል። እነዚህ ሥነ-መለኮታዊ ቅድመ-ግምቶች በብዙ ደረጃዎች ይታያሉ

1. በተምሳሌቶቹ መገኛ
   ሀ. የብሉይ ኪዳን ጠቃሾች
      (1) የብኪ ጭብጦች፣ እንደ ፍጥረት፣ መውደቅ፣ ዘጸአት፣ የኢየሩሳሌም መታደስ ያሉት
      (2) በመቶዎች የሚቆጠሩ ጠቃሾች (ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች) ከብኪ ነቢያት
   ለ. በይነ-ኪዳናዊ (ተያያዥ) የአይሁድ ሥነ-ጽሑፍ (1 ሔኖክ፣ 2 ባሮክ፣ ሲቢሊኒ ትንበያዎች፣ 2 ኢስድራስ)
   ሐ. የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ግሪክ-ሮማ ዓለም
   መ. የጥንት ቅርብ ምስራቅ የፍካሬ ከዋክብት ፍጥረታት ታሪኮች (በተለይም ራዕ. 12)
2. የመጽሐፉ የጊዜ ቅምብብ
   ሀ. አንደኛ ክፍለ-ዘመን
   ለ. እያንዳንዱ ክፍለ-ዘመን
   ሐ. የመጨረሻው ትውልድ
3. ስልታዊ ሥነ-መለኮታዊ ፈርጆች (ገጽ 14 ላይ ያለውን መግለጫ ተመልከት፣ "የትርጓሜ ታሪካዊ ንድፈ-ሐሳቦች፣" ሲ፤ መልካም ማጠቃለያ፤ የራዕይ መጽሐፍ አራት አተያዮች፣ አዘጋጅ ሲ. ማርቪን ፔቲ)
   ሀ. ራዕይ ቀድሞ ተፈጽሟል የሚል
   ለ. ታሪካዊ
   ሐ. የወደፊታዊ
   መ. ሐሳባዊ
4. በምዕራፍ 20 ላይ ሥነ-መለኮታዊ አቋም (ገጽ 193 ላይ ያለውን ሰንጠረዥ ተመልከት፤ መልካም ማጠቃለያዎች፡ (1) የሚሊኒየሙ ፍቺ፡ አራት አተያዮች፣ አዘጋጅ ሮበርት ጂ. ክሎስ እና የሚሊኒየሙና ከዚያም ወዲያ ሦስት አተያዮች፣ አዘጋጅ ዳሬል ኤል. ቦክ)
   ሀ. ሚሊኒየማዊ
   ለ. ድኅረ-ሚሊኒየም
   ሐ. ቅድመ-ሚሊኒየም
   መ. ቅድመ-ሚሊኒየም ክፋይ

   በሥነ-ትርጓሜ ልዩነት ሲታይ (ለትርጓሜ የተለያዩ አገባቦች) እና ተገቢ ያልሆነ ቀኖናዊነት (የሁሉን እወቀው አዝማሚያ)፣ እንዴት አንድ ተርጓሚ ሊቀጥል ይችላል?

1. እንቀበል፣ ዘመናዊ ምዕራባዊ ክርስቲያኖች ዘውጉን አይረዱትም እንዲሁም ታሪካዊ ጠቃሾቹን ሊገነዘቡ አይችሉም፣ የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ክርስቲያኖች ወዲያውኑ የተረዱትን።
2. እንቀበል፣ የእያንዳንዱ ትውልድ ክርስቲያን ራዕይን ወደራሳቸው ግላዊ ታሪካዊ መቼት እንዳስገደዱት እና እስካሁን ሁሉም እንደተሳሳቱ።

3. መጽሐፍ ቅዱስን እናንብብ ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓቶችን ከማንበባችን በፊት። የያንዳንዱን ራዕይ/ትንቢት ጽሑፋዊ ዐውደ-ጽሑፍ ፈልግ እና ማዕከላዊውን እውነት አስቀምጥ በአንድ ገላጭ ዓረፍተ-ነገር። ማዕከላዊው እውነት ተመሳሳይ ነው የሚሆነው፣ ለእያንዳንዱ የአማኞች ትውልድ፣ የዝርዝሩ የተለየነት ምናልባት ሊጠቅም የሚችለው ለመጀመሪያው እና/ወይም ለመጨረሻው የአማኞች ትውልድ ነው። ዝርዝሩ ሊጠቅም ይችላል፣ ታሪክ ግን፣ ሥነ-መለኮት ሳይሆን፣ ፍጻሚያቸውን ይገልጣል።
4. ይህ መጽሐፍ በቅድሚያ የማጽናኛና የማበረታቻ ቃል መሆኑን እናስታውስ፣ ለታማኝነት፣ በማያምኑት በስደት ላይ ላሉ አማኞች። ይህ መጽሐፍ የእያንዳንዱን አማኝ ትውልድ አስቸጋሪ ነገር የሚመልስ አይደለም፣ አልያም የፍጻሜ ዘመን ሁነቶች ዝርዝር ዕቅድ።
5. ቢያጸኑት ደኅና የሚሆነው፣ የወደቀው ማኅበረሰብ ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር በግጭታዊ ጉዞ ላይ መሆኑ ነው። በመጀመሪያም ይከሰታል፣ ማለትም ዓለም እንዳሸነፈ (እንደ ቀራንዮ)፣ ግን ቆዩ፤ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው፣ እሱ ታሪክን ይቆጣጠራል፣ ሕይወትንና ሞትን። የእሱ ሕዝቦችም በእርሱ ድል አድራጊዎች ናቸው!

ረ. ከትርጉም አስቸጋሪነትና አሻሚነት የተነሣ፣ ይህ መጽሐፍ መልእክት አለው፣ ብሎም ከእግዚአብሔር የተመስጦ ቃል ነው፣ ለሕዝቡ በዘመናት ሁሉ። ይህንን የተለየ መጽሐፍ ለማንበብ ተጨማሪ ጥረት አስፈላጊ ነው። የእሱ ስልታዊ አቋም በአኪ ካኖን የእሱን የድምድማት ድንጋይ መልእክት ያመለክታል። አለን ጆንሰን፣ የአብራሪ መጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣ ቅጽ 12፣ እንዲህ ይላል

"በርግጥ፣ እንደዚያ ሊሆን ይችላል፣ በወንጌላት የተለየነት፣ አፖካሊፕስ እጅግ መሠረታዊና አንቀሳቃሽ ትምህርቶችን ይዟል፣ በክርስቲያን ዶክትሪንና ደቀ-መዝሙርነት በቅዱስ ቃሉ የትም ስፍራ የሚገኘውን። የአንዳንዶች ያፈነገጠ መሆን፣ እነርሱም ሐሳባቸውን ትንቢት ላይ ያደረጉ፣ በክርስቶስ ላይ ከማድረግ ይልቅ፣ አልያም የትርጓሜ አተያይ ነጥቦች ብዝኃነት በዚህ አስደናቂ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት እውነቶች እንዳንሳተፍ አዳከመውናል" (ገጽ 299)።

በርግጥ የኢየሱስ የመጨረሻ ቃል ለቤተ-ክርስቲያኑ እንዳለ አስታውሱ! ዘመናዊዋ ቤተ ክርስቲያን እነርሱን ችላ ለማለት ወይም ለመቀነስ መድፈር የለባትም! እነርሱ አማኞችን የሚያዘጋጁ ናቸው ለስደትና ለመከራ፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በኩል (አሀዳዊነት)፣ የክፋውን እውነታ (የተወሰነ ምንታዌነት)። እየቀጠለ ያለው የውድቀት ውጤት (የሰው ልጅ ዐመጸኝነት)፣ እና የሰው ልጆችን ለመዋጀት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን (ሁኔታዊ ያልሆነ ኪዳን፣ ዘፍ. 3:15፤ 12:1-3፤ ዘጸ. 19:5-6፤ ዮሐንስ 3:16፤ II ቆሮ. 5:21)።

## ደራሲው

ሀ. በውስጣዊው ማስረጃ ሐዋርያው ዮሐንስ ደራሲው ነው

1. ደራሲው እሱ ዮሐንስ እንደሆነ አራት ጊዜ ጠቅሷል (ዝከ. 1:1፣4፣9፤ 22:8)
2. እሱም ደግሞ ራሱን ጠርቷል
   ሀ. ባርያ (ዝከ.1:1፤ 22:6)
   ለ. ወንድምና የመከራውም ተካፋይ (ዝከ. 1:9)
   ሐ. ነቢይ (ዝከ. 22:9)፣ መጽሐፉንም ትንቢት ብሎታል (ዝከ. 1:3፤ 22:7፣10፣18፣19)
3. እሱም ብሉይ ኪዳንን ያውቃል (LXX ሳይጠቀም፣ ታርጉምን) እንዲሁም የምድረ በዳው የመንከራተት ዘመን፣ የማደሪያው ድንኳን እና የዘመኑን የምኩራብ ደንቦች።

ለ. ሐዋርያው ዮሐንስ ደራሲው ለመሆኑ ውጫዊ ማስረጃ፣ ከጥንት ክርስቲያን ደራሲዎች

1. ሐዋርያው ዮሐንስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ
   ሀ. ጀስቲን ማርቲን (ሮም ዓ. ም 110-165) *በትሪፖ ምልልስ* 81.4
   ለ. ኢሬኑስ (ሊዮንስ ዓ. ም 120-202)*መናፍቃንን መቃወም* IV.14.2፤ 17.6፤ 21.3፤V.16.1፤ 28.2፤ 30.3፤ 34.6፤ 35.2
   ሐ. ተርቱሊያን (ሰሜን አፍሪካ ዓ. ም 145-220) *ፕራቅሲያስን መቃወም* 27
   መ. ኦሪጅን (አሌክሳንድሪያ ዓ. ም 181-252) በ
   (1) *በነፍስ*፣ L:8:1
   (2) *ማርሲዮንን መቃወም*፣ II:5
   (3) *መናፍቃንን መቃወም*፣ III:14፣ 25
   (4) *ሴልሰስን መቃወም*፣ VI:6፣ 32፤ VIII:17
   ሠ. የሙራቶሪያን ካኖን (ሮሜ ዓ. ም. 180-200)
2. ሌሎች አስረጅዎች
   ሀ. ጆን ማርክ — ይህ በቅድሚያ በዳዮኒሰስ የተጠቀሰ ነው፣ የአሌክሳንደርያ ጳጳስ (247-264 ዓ. ም)፣ እሱም የሐዋርያው ዮሐንስን ደራሲነት ያልተቀበለ፣ ግን ቢሆንም ሥራውን እንደ ቅዱስ ቃል ወስዶታል። አለመቀበሉን መሠረት ያደረገው በቃላትና በስልቱ እንዲሁም ከሌሎች የዮሐንስ ጽሑፎች ጋር ባለመመሳሰል ባሕርዩ ነው። እሱም የቂሳርያውን ኢዩሲቢዩስ አሳምኖታል።

ለ. ሽማግሌው ጆን — ይህ የሚመጣው ኢዩሲቢዩስ ከፓፒያስ ከጠቀሰው ነው (የጥበብ ታሪክ 3.39.1-7)። ሆኖም፣ የፓፒያስ ጥቅሻ ምናልባት ይህን መጠሪያ ለሐዋርያው ዮሐንስ ተጠቅሞበት ይሆናል ሌላ ደራሲ ከማስረገጥ ይልቅ።

ሐ. ዮሐንስ መጥምቁ — (ኋላ ላይ ከሆነ የአራሚዎች ተጨማሪ) እንደሚለው፣ በጄ. ማሲንግበርዲ ፎርድ በመልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣ በዮሐንስ መጥምቁ የ"በግ" አጠቃቀም ላይ በመመሥረት፣ ለኢየሱስ። ይህ መጠሪያ የተከሰተበት ሌለኛው ብቸኛ ስፍራ ራዕይ ነው።

ሐ. ዲዮኒሰስ፣ የአሌክሳንደሪያ ጳጳስ ( 247-264 ዓ. ም) እና የኦሪጅን ደቀ-መዝሙር፣ ጥርጣሬን በመግለጽ የመጀመሪያው ነው (ይህ መጽሐፍ ጠፍቶ ነበር፣ ግን እሱ በቂሳርያው ኢዩሲቢዩስ ተጠቅሷል፣ ከእሱ ጋር በሚስማማው) ስለ ሐዋርያው ዮሐንስ ደራሲነት፣ የተመረኮዘውም

1. ሐዋርያው ዮሐንስ ራሱን በወንጌል አልያም በመልእክቶቹ እንደ ዮሐንስ አልጠቀሰም፣ ራዕይ ግን ከ "ዮሐንስ" ነው
2. የራዕይ አወቃቀር ከወንጌልና ከመልእክቶቹ ይለያል
3. የራዕይ ቃል ከወንጌልና ለመልእክቶቹ ይለያል
4. የራዕይ ሰዋሰዋዊ ስልት ከወንጌልና ከመልእክቶቹ ዝቅ ያለ ደረጃ ያለው ነው

መ. ምናልባትም ዋነኛው ዘመናዊ ሙግት በዮሐንስ ደራሲነት ላይ የመጣው ከአር. ኤች ቻልረስ ነው፣ *ቅዱስ ዮሐንስ*፣ ቅጽ 1 ገጽ xxxix።

ሠ. አብዛኛው ዘመናዊ ሊቅ የአብዛኞቹን የአኪ መጻሕፍት ልማዳዊ ደራሲነት አልተቀበለም። ለዚህ አዝማሚያ ጥሩ ምሳሌ የሚዛመደው፣ ለራዕይ ደራሲነት፣ ሬይሞንድ ኢ. ብራውን ሊሆን ይችላል፣ የታወቀ የካቶሊክ ጆሐኒን ሊቅ፣ የመልጎቅ መጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ መግቢያ ቅጽ፣ "የተጻፈው በአይሁድ ክርስቲያን ነቢይ ስሙም ዮሐንስ እሱም ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጅ ያይደለ፣ አልያም የጆሐኒን ወንጌል ወይም መልእክቶቹን የጻፈ" (ገጽ 774)።

ረ. በብዙ መንገዶች ደራሲነት ርግጠኛ አይሆንም። አስገራሚ የሆኑ ትይዩዎች ከሌሎች የሐዋርያው ዮሐንስ ጽሑፎች ጋር አሉት፣ እንዲሁም አስገራሚ የሆኑ ልዩነቶች። ይህን መጽሐፍ ለመረዳት ቁልፉ የሰው ደራሲነት ሳይሆን፣ መለኮታዊ ደራሲነት ነው! ደራሲው ተመስጧዊ ነቢይ ለመሆኑ ታምኗል (ዝከ. 1:3፤ 22:7፣10፣18፣19)።

## ጊዜው

ሀ. ይህ በርግጥ በተጠናከረ መልኩ የሚያያዘው ከደራሲውና ከትርጓሜ አተያይ ጋር ነው (ታሪካዊ ንድፈ-ሐሳቦች ሲ።)

ለ. አንዳንድ ታሳቢ ጊዜያት

1. ልማዳዊ ጊዜው በዶሚቲያን ግዛት ላይ ነው (ዓ. ም 81-96) ምክንያቱም ከስደቱ ውስጣዊ ማስረጃ ጋር ስለሚገጥም
   ሀ. ኢሪኒዩስ (በኢሲቢዩስ የተጠቀሰ) በ*መናፍቃንን መቃወም* ላይ፣ 5.30.3። "እሱ (ይህ ስደት) በጣም ርቆ አልታየም፣ ቢያንስ በእኛ ትውልድ፣ በዶሚቲያን አገዛዝ መዝጊያ ላይ"
   ለ. የአሌክሳንደሪያው ክሌመንት
   ሐ. የአሌክሳንደሪያው ኦሪጅን
   መ. የቂሳርያው ኢዩሲቢዩስ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ iii.23.1
   ሠ. ቪክቶሪነስ፣ አፖካሊፕስ x. 11
   ረ. ጄሮም
2. ኢጲፋንያ፣ የሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጸሐፊ፣ በሀር፣ 51.12፣ 32፣ እንደሚለው ዮሐንስ የጻፈው ለጳጥሞስ ከተለቀቀ በኋላ ነው፣ ይኸውም በክላውዲዮስ አገዛዝ (41-54 ዓ. ም)።
3. ሌሎች የሚገምቱት በኔሮ አገዛዝ ነው (54-68) ምክንያቱም፡
   ሀ. በሚታወቀው የአጼ አምልኮ ስደት ዳራ ሳቢያ
   ለ. ቄሳር ኔሮ፣ በዕብራይስጥ የተጻፈ፣ ከአውሬው ቁጥር (666) ጋር እኩል የሆነ
   ሐ. ራዕዩ ቀድሞ ተፈጽሟል የሚሉት ትክክል ከሆኑ፣ የዮሐንስ ራዕይ ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስ ያመለክታል፣ ከዚያም መጽሐፉ ትንቢታዊ እስከሆን ድረስ ከ70 ዓ. ም በፊት ተጽፏል ማለት ነው

## ተቀባዮች

ሀ. ከ1፡4 ግልጽ እንደሆነው ዋነኞቹ ተቀባዮች ሰባቱ ቤተ-ክርስቲያኖች ናቸው፣ በእስያ ያሉት የሮሜ አውራጃዎች። እነዚህ ቤተ-ክርስቲያኖች የተመለከቱት በዚህ መልኩ የጉዞ መስመሩን ተከትሎ በደብዳቤው አድራሽ ነው።

ለ. የራዕዩ መልእክት በተለየ መልኩ የሚዛመደው ለሁሉም ቤተ-ክርስቲያኖችና አማኞች ጋር ነው፣ እነርሱም ስደትን የሚቀበሉ ከወደቀው የዓለም ሥርዓት።

ሐ. በአኪ ካኖናዊ ማጠቃለያ መሠረት ይህ መጽሐፍ በሁሉም አማኞች የሚፈጸም ነው፣ በሁሉም ዘመናት ባሉት አማኞች።

## ሁነቱ

ሀ. መቼቱ ስደት ነው፣ የአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያኖች ተለይቶ የሮሜን ሕጋዊ ከለላ ማጣት ነው፣ ለይሁዲነት የተፈቀደው። ልዩነቱ በይፋ የተከሰተው በ70 ዓ. ም ነው፣ የጃምኒያ ራቢዎች የመሀላ መግለጫ ስላሰናዱ ነው፣ እሱም የአጥቢያ ምኩራቦች አባላት የናዝሬቱ ኢየሱስን እንዲረግሙ የሚጠይቅ።

ለ. የሮሜ መዛግብት እንደሚያመለክቱት የአጼ አምልኮ ዋነኛው ግጭት ሆኖ ነበር፣ ከኔሮ ግዛት ክርስቲያኖች ጋር (54-68 ዓ. ም) ወደ ዶሚቲአን (81-96)። ሆኖም፣ ሰፊውን ግዛት (ኢምፓየር) ያካተተ ስደት ለመኖሩ ይፋ ሰነድ የለም። ባጠቃላይ ራዕይ የሚያንጸባርቀው የአጥቢያ አጼአዊ አምልኮ ሥርዓት በምስራቅ አውራጆች በሮሜ ኢምፓየር መኖሩን ነው (ዝኪ. "መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥንታዊ ቅርስ ምርምር ቅኝት፣" ግንቦት/ሰኔ 1993 ገጽ 29-37)።

## አገባብ (የቋንቋ)

ሀ. በርካታ ሰዋሰዋዊ ችግሮች በግሪኩ ጽሑፍ ላይ አሉ።

ለ. ለእነዚህ ችግሮች ታሳቢ ምክንያቶች

1. የዮሐንስ አራማዊ የአስተሳሰብ ፈርጆች።
2. በጳጥሞስ ጸሐፊ አልነበረውም፣ የሚጽፍለት።
3. የራዕዩ አስደሳችነት የሚያጥለቀልቅ ነበር።
4. እነሱም ለውጤታማነቱ ዓላማ ነበራቸው።
5. ዘውጉ (አፖካሊፕታዊ) እጅግ ዘይቤአዊ ነበር።

ሐ. ተመሳሳይ ሰዋሰዋዊ የተለየ ባሕርይ በሌሎች የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፎች ላይ ተገኝቷል። ስለዚህ፣ ራዕይ በደካማ ሰዋሰዋዊ ስልት አልተጻፈም፣ ግን በተለየ ሰዋሰዋዊ ዘውግ።

## ቅዱስ ቃላዊ እውቅናው

ሀ. እሱ ቀደም ሲል በምስራቅ ቤተ-ክርስቲያን ተቀባይነት አላገኘም ነበር፤ መጽሐፉ በፔሺታ ላይ አልተገኘም (አምስተኛ ክፍለ-ዘመን የሶርያ ቅጂ)።

ለ. በቀደምቱ የአራተኛ ክፍለ-ዘመን ኢዩሴቢዩስ፣ የአሌክሳንደሪያውን ዲኦኒሲዩስ ተከትሎ፣ በኋለኛው ሦስተኛ ክፍለ-ዘመን፣ እንዳለው ራዕይ በሐዋርያው ዮሐንስ አልተጻፈም። እሱም "ከአጨቃጫቂዎቹ" መጽሐፎች ዝርዝር ውስጥ አካቶታል፣ ግን በራሱ ካኖናዊ ዝርዝር ውስጥ አካቶታል *(የጥበብ ታሪክ*፣ III.24.18፤ III.25.4፤ እና III.39.6)

ሐ. የሎዶቅያ ጉባኤ (360 ዓ. ም ገደማ) ከካኖናዊ መጻሕፍት ዝርዝር አውጥቶታል። ጄሮም እንደ ካኖናዊ መጽሐፍ አልተቀበለውም፣ ግን የካርታጌ ጉባኤ (397 ዓ. ም) አካቶታል። ራዕይ ተቀባይነት ያገኘው በምስራቅና ምዕራብ ቤተ-ክርስቲያኖች መካከል በተደረገ መቻቻል ነው፣ ይኸውም ሁለቱም ዕብራውያንና ራዕይ በአኪ ካኖን ተቀባይነት አግኝተዋል።

መ. እውቅና መስጠት ያለብን የአማኞች የእምነት ቅድመ-ግምት፣ መንፈስ ቅዱስ ታሪካዊ ሂደቱን በመምራት ክርስቲያናዊ ካኖኑ እንዲዳብር ማድረጉን ነው።

ሠ. ሁለቱ ዋነኛ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ሥነ-መለኮታውያን በክርስቲያን ዶክትሪን ያለውን ስፍራ አልተቀበሉትም

1. ማርቲን ሉተር ትንቢታዊ ወይም ሐዋርያዊ ብሎ አልጠራውም፣ ተመስጧዊነቱን ባለመቀበል እሳቤ።
2. ጆን ካልቪን፣ በእያንዳንዱ የአኪ መጻሕፍት ላይ ሐተታ የጻፈ፣ ራዕይን ትቶታል፣ ጠቀሜታውን ባለመቀበል እሳቤ።

## የትርጓሜ ታሪካዊ ንድፈ-ሐሳቦች

*ሀ. ለመተርጎም እጅግ አስቸጋሪ ነበር፤ ስለዚህ፣ ቀኖናዊነት ተገቢ አይደለም!*

ለ. ምስያዎቹ የመጡት ከ

1. ከብሉይ ኪዳን አፖካሊፕቲካዊ ምንባቦች
   - ሀ. ዳንኤል
   - ለ. ሕዝቅኤል
   - ሐ. ዘካርያስ
   - መ. ኢሳይያስ
2. በይነ-ኪዳናዊ የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ *ሥነ-ጽሑፍ*
3. የአንደኛው ክፍለ-ዘመን *ግሪክ-ሮማን ታሪካዊ መቼት* (በተለይ *ራዕይ* 17)
4. ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ *አፈታሪካዊ የተፈጥሮ ታሪኮች* (በተለይ *ራዕይ* 12)

ሐ. ባጠቃላይ አራት የትርጓሜ ዘርፎች ወይም ቅድመ-ግምቶች አሉ

1. *ቀድሞ ተፈጽሟል ባዮች — ይህ ወገን መጽሐፉን የሚያስቀምጠው በቀዳሚነት ወይም በተለየ መልኩ ከአንደኛ* ክፍለ ዘመን ቤተ-ክርስቲያኖች ጋር እንደሚያያዝ ነው፣ በእስያ የሮሜ አውራጃ። ሁሉም ዝርዝር እና ትንቢቶች በአንደኛው ክፍለ-ዘመን ተፈጽመዋል (ጆን ኤል. ብሬይ፣ *ማቴዎስ 24 ተፈጸሟል* ተመልከት)።
2. *ታሪካውያን — ይህ ወገን መጽሐፉን የሚመለከተው እንደ ታሪክ እይታ ነው፣ በቀዳሚነትም የምዕራብ ሥልጣኔ* እና በአንዳንድ መልኩ የሮሜ ካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን። የሰባቱ ቤተ-ክርስቲያኖች መልእክቶች ምዕራፍ 2 እና 3 ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉት የተወሰነ ጊዜን ነው። አንዳንዶች እነዚህን የሚመለከቱት እንደ ጊዜያዊ በአንድ ጊዜ እንደተከሰቱ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ በቅደም ተከተል እንደተቀመጡ ነው።
3. *መጺአዊ — ይህ ወገን መጽሐፉን የሚመለከተው ከዳግም ምጽአቱ ተከትሎ ወዲያውኑ የሚሆኑትን ሁነቶች* ለማመሳሰል ነው (የክርስቶስ ዳግም ምጽአት)ይኸውም በጥሬውና ከታሪካዊነት አኳያ የተፈጸመ (*ቀጣይነት ያለው ማከፋፈል*፣ በክሬግ ኤ. ብሌሲንግ እና ዳረል ኤል. ቦክ ተመልከት)።
4. *ሐሳባዊ — ይህ ወገን መጽሐፉን የሚመለከተው ሙሉ ለሙሉ እንደ ተምሳሌት አድርጎ ነው፣ በመልካምና በክፉ* መካከል እንደሚደረግ ትግል፣ ይኸውም፣ ምንም ዓይነት ታሪካዊ ማጣቀሻ የለውም (ሬይ ሰመርስ፣ *በጉ ይገባዋል*፤ ዊሊያም ሄንድሪክሰን፣ *ከአሸናፊዎች የሚበልጥ*)።

እነዚህ ሁሉ የተወሰነ ዋጋ አላቸው፣ ነገር ግን፣ ሆን ብሎ አሻሚ የሆነውን የዮሐንስን የዘውግና ምስል ከሳችነት ምርጫ ዘንግተውታል። ችግሩ የማመዛዘን ነው፣ የትኛው ነው ትክክል የሚለው ሳይሆን።

## የመጽሐፉ ዓላማ

ሀ. የራዕይ ዓላማ የእግዚአብሔርን የታሪክ ሉዓላዊነት እና ሁሉም ነገር በእርሱ እንደሚጠቃለል ቃል መግባት ነው። ታማኞች በእምነትና በተስፋ ጸንተው ይቆያሉ፣ በስደትና በመከራ መካከል፣ በዚህ በወደቀው ዓለም ሥርዓት ውስጥ። የመጽሐፉ ትኩረት ስደት ነው (የአጼ አምልኮ በምስራቃዊ አውራጃዎች) እና ታማኝነት (ሐሰተኛ መምህራንና ባህላዊ መቻቻል) የአማኞች፣ በአንደኛው ክፍለ-ዘመንና በእያንዳንዱ ክፍለ-ዘመን (ዝኪ. 2፡10)። ነቢያት ስለ መጻኢው እንደሚናገሩ አስታውሱ፣ በአሁኑ ላይ ለሚደረግ የተሐድሶ ጥሪት። ራዕይ እንዴት እንደሚፈጸም ብቻ አይደለም፣ ግን እንዴት እንደሚካሄድ እንጂ። በጽሑፉ፣ *የአብራሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ*፣ ቅጽ 1 ርዕሱ፣ *"የመጽሐፍ ቅዱስ የፍጻሜ ራዕይ፣"* ላይ ሮበርት ኤል. ሳንሲ እንዲህ ብሏል፣

> "መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነቢያት በቅድሚያ ስለ መጻኢው እውነቶች ጊዜ እና ስለ ቅደም ተከተላዊ ቅንብሩ አይገዳቸውም ነበር። ለእነርሱ የዘመነኞቻቸው መንፈሳዊ አቋም ነበር ጠቃሚ ነጥባቸው፣ እንዲሁም የታላቁ የፍጻሜ ዘመን የእግዚአብሔር ጉብኝት፣ የኃጢአተኞች ፍርድ እና የጻድቃን መባረክ ተተኩሮበት ነበር፤ በአሁን ጊዜ ላለው *ሥነ-ምግባራዊ አንድምታ*" (ገጽ 104)።

ለ. አጠቃላይ ዓላማው በአጭር መግቢያ አእት እና አኢመቅ ትርጉሞች ላይ ደኅና ሆኖ ተጠቅሷል

1. አእት ገጽ1122፣ "የዮሐንስ ራዕይ የተጻፈው ክርስቲያኖች በሚሳደዱበት ጊዜ ነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታ አድርገው ባላቸው እምነት ምክንያት። የጸሐፊው ዋነኛ ዓላማ ለአንባቢዎቹ ተስፋንና ማበረታቻን መስጠት ነው፣ እንዲሁም በመከራና በስደት ሰዓት ታማኝ ሆነው እንዲገኙ ማሳሰብ ነው።"
2. አኢመቅ፣ ገጽ 1416፣ "መጽሐፍ ቅዱስ የተስፋ መልእክትና የዳበረ ተምሳሌት ባለው በዚህ መጽሐፍ ተጠቃሏል። ከመከራ የመጠበቅ ራዕይ አለው፣ ይኸውም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከያዘው፣ እንዲሁም የቀጣዩ ክብር ተስፋ። መልእክቱ የሚገለጠው በስዕላዊ ነው፣ ይኸውም ከሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የሚመነጭ፣ ስለዚህ እያንዳንዱ ፍጥረት፣ እንስሳት፣ ቀለማት፣ ቁጥሮች አስታዋሽ ናቸው፣ እንዲሁም የዳበሩ ናቸው፣ ብኪን በደንብ በሚያውቁት ዘንድ። በዚህ መንገድም፣ ምሥጢርና ጠቃሽ ራዕይ ነው፣ ስለሚመጣው ነገር፣ ተፈጥሯዊ ምስያነት ይኸውም

ታላቁ የአምልኮ ድርጊት እና የመጨረሻው ራዕይ፣ የመሲሑ ታላቅ ክብር፣ አዲሲቷ ቅዱስ ከተማ በግልጽ ተቀምጠዋል። የዚህ ዓይነቱ ጽሑፍ ወግ (ልማድ) በይሁዲነት ከዳንኤል ወዲህ ነበር፣ በመከራ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጠንከር፣ የመዳረሻ ዋስትናንና ማዳንን እንዲሁም ድልን በመስጠት።"

ሐ. ተርጓሚው ለመቤዠቱ ጭብጥ ቅድሚያ መስጠቱ ዋነኝነት አለው።
1. እግዚአብሔር ግለሰባዊ፣ የተጠቃለለ፣ እና ሁለንተናዊ ደኅንነትን በክርስቶስ አምጥቷል።
2. የእግዚአብሔር መቤዠት መንፈሳዊና አካላዊ ነው። ቤተ-ክርስቲያን ድናለች፣ ደኅና ግን አይደለችም! አንድ ቀን ትሆናለች!
3. እግዚአብሔር ገና (አሁንም) የወደቀውን፣ ዐመጸኛውን፣ ራስ ወዳዱን ሰብአዊነት ይወዳል። የእግዚአብሔር ቁጣ፣ በማኅተሞቹና በመለከቶቹ፣ ለመቤዠት ነው (ዝኪ. 9:20-21፤ 14:6-7፤ 16:9፣11፤ 21:6b-7፤ 22:17)።
4. እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ልጅ ብቻ አያድንም፣ ግን ደግሞ የወደቀውን ተፈጥሮ እንጂ (ሮሜ 8:18-25)። ክፉው በየደረጃው ይባረራል!

በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰው ልጅ በወንጌል ለመድረስ መሞከሩ የእግዚአብሔርን ቸርነት ባሕርይ ያጎላል። የጽዋው ፍርዶች የክፉው እምቢተኝነት ውጤቶች ናቸው እንጂ የእግዚአብሔርን አለመውደድ አይደለም። እግዚአብሔር በክፉው ላይ የሚፈርደውና የሚያጋልጠው በንስሐ ለመመለስ ደግሞ ደጋግሞ እምቢ ሲል ብቻ ነው። በብዙ መንገዶች የእግዚአብሔርን ፍርድ ጽድቅነት ያረጋግጣል፣ በወደቀው፣ አሻፈረኝ በሚለው ስብዕና! መጽሐፉ የሚያበቃው በወንጌል ግብዣ ነው (ዝኪ. 22:17)።

መ. መጽሐፉ እንደ ሁነቶች ቅደም ተከተላዊ ሠንጠረዥ፣ ጊዜያት፣ እና እንደ ዳግም ምጽአቱ ሁኔታ ተደርጎ የግድ መወሰድ አይኖርበትም። እሱ ዘወትር በምዕራባዊው ታሪክ የሚተረጎመው እንደ "ምሥጢር" ነው (ሰባቱ ቤተ-ክርስቲያኖች እንደ ዘመናት ይታያሉ)። እያንዳንዱ ትውልድ የእሱን ታሪክ ወደ አፖካሊፕታዊ ምስያዎች ያስገድደዋል፤ እስካሁን ድረስ እያንዳንዱ ተሳስቷል።

የእነዚህ ትንቢቶች ዝርዝር እጅጉን የሚያያዘው ለመጨረሻው የአማኞች ትውልድ ነው፣ በክርስቶስ ተቃዋሚ መከራን የሚቀበሉ። የዚህ መጽሐፍ በጥሬው መተርጎም በአንዳንዶች ችላ እንዲባል አድርጓል (ካልቪን)፣ በሌሎች ተንኳሷል (ሉተር)፣ "ሐዋርያዊ ወይም ትንቢታዊ ያልሆነ") ፣ እንዲሁም በሌሎች እጅግ ተጋንኗል (ሚሊኒየማውያን)።

## የቡብ የትርጓሜ ቁልፎች

ሀ. የብኪን ገጽታ ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን
1. የብኪ አፖካሊፕታዊ ዘውግ በጣም ምስያዊ የጽሑፍ ዓይነት ነው።
2. በርካታ ጠቃሾች (ዘይቤዎች) ከብኪ ተወስደዋል (አንዳንዶች እንደሚገምቱት 404 ቁጥሮች 275 ተጨማሪ ጠቃሾች (ዘይቤዎች) በብኪ ጽሑፎች ውስጥ ተካተዋል)፤ የእነዚህ ምስያዎች ፍቺ በአንደኛው ክፍለ-ዘመን የሮሜ ሁኔታ አንጻር ድጋሚ ተተርጉመዋል።
3. ትንቢታዊ ንግሮች የወቅቱን ሁነቶች ወስደው የፍጻሜ ዘመኑን ትንቢት ሁነቶች ንግር አድርገውባቸዋል። ዘወትር እነዚህ የአንደኛ ክፍለ ዘመን ታሪካዊ ፍጻሜዎች ወደ ፍጻሜ ዘመን ታሪካዊ ፍጻሜ መዳረሻዎች ያመለክታሉ።

ለ. የመጽሐፉ አጠቃላት አወቃቀር የደራሲውን ዓላማ እንድናይ ይረዱናል
1. ማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ የሚሸፍኑት በመሠረቱ ተመሳሳይ ጊዜና ሰዓት ነው (ምዕራፍ 6-16)። ራዕይ የቅደም ተከተላዊ ድርጊቶች ድራማ ነው።
2. ምዕራፍ 17-19 ከ 20-22 ጋር ትይዩ መሆን ይችላሉ። የምዕራፍ 19 የተወሰኑ ክፍሎች (ማለትም፣ 19:11-21) 20:7-10 ላይ ድጋሚ ተመልክተዋል።
3. በመከፈቻው መግለጫ ላይ ያሉትን ሰባት ጽሑፋዊ አህዶች ተመልከት፣ ሐ።

ሐ. ታሪካዊው ዐውደ-ጽሑፍ በየትኛውም የመጽሐፉ ትርጓሜ ላይ ግምት ውስጥ መግባት አለበት
1. የአጼ አምልኮ መኖሩ
2. የአጥቢያ ስደቶች በምስራቅ አውራጃዎች
3. መጽሐፍ ቅዱስ የማይሆነውን ሊሆን አይችልም። የራዕይ ትርጓሜ በቅድሚያ መዛመድ የሚኖርበት ከዮሐንስ ቀን ጋር ነው። እሱም ምናልባት በርካታ አፈጻጸምና አተገባበር ሊኖረው ይችላል፣ ነገር ግን መሠረት መያዝ የሚኖርባቸው አንደኛውን ክፍለ-ዘመን ነው።

መ. የአንዳንድ ምሥጢራዊ ቃላት ፍቺ ለእኛ ተሰውሮብናል፣ ከባህላችን፣ ከሥነ-ቋንቋ እና ከነበረው መቼት የተነሣ። የፍጻሜ ሰዓት ሁነቶች ራሳቸው በእነዚህ ምስያዎች ተገቢ የሆነ አተረጓጎም ላይ ብርሃን ሊያሳርፉ ይችላሉ። እነዚህን የአፖካሊፕቲካዊ ድራማ ዝርዝሮች ሁሉ ወደ ጎን እንዳትሉ ተጠንቀቁ። ዘመናዊ ትርጓሜዎች ዋነኞቹን እውነቶች ከእነዚህ ራዕዮች መፈለግ ይኖርባቸዋል።

ሠ. አንዳንድ ቁልፍ የሆኑትን የትርጓሜ ይዘቶች ላጠቃልል

1. *የምስያነት ታሪካዊ መገኛ*
   ሀ. የብኪ ጭብጦች፣ የብኪ ጠቃሾች
   ለ. የጥንት ቅርብ ምስራቅ አፈ-ታሪክ
   ሐ. በይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ
   መ. ግሪክ-ሮማ የአንደኛ ክፍለ-ዘመን መቼት
2. ደራሲው ምስያነትን የሚገልጽበት መንገድ
   ሀ. ከመልአካዊ መሪዎች ጋር ያለ ንግግር
   ለ. የመልአካዊ ዘማርያን መዝሙር
   ሐ. ደራሲው ራሱ ፍችውን ሲያስቀምጥ
3. የመጽሐፉ አወቃቀር (ድራማዊ ትይዩነት)

ረ. ተጨማሪ እገዛ

1. ሁለቱ ተወዳጅ ሐተታዎቼ በራዕይ ላት ጆርጅ ኢልደን ላድ እና አለን ኤፍ. ጆንሰን ናቸው። እነሱ አይስማሙም። በርካታ አለመግባባት በመልካም፣ የተማሩ፣ ቅን ሊቃውንት መካከል ስለሚኖር የማስጠንቀቂያ ቃል ተገቢ ነው። አለን ጆንሰንን ልጥቀስ፣ ከ*ራዕይ ሐተታው* ላይ፣ በዞንደርቫን የታተመ፡

   "በምስል ከሳችና በራዕይ አጠቃቀም ማብራሪያ አመለካከት ላይ ከ4፡1 እስከ ራዕይ ማጠቃለያ ድረስ እና ይሄ ነገር ከምዕራፍ 1-3 ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ላለው ጥያቄ፣ ሐተታዎች እነዚህን ምዕራፎች እንዴት እንደሚመለከቱ በስፋት መለያየታቸው አያስገርምም። አንደኛው ችግር የትርጉም ነው። ምስል ከሳቾቹና ራዕዩ ምን ማለታቸው ነው? ሌለኛው ችግር የሚመለከተው ቅደም ተከተሉን ነው፡ እነዚህ ነገሮች መቼ ነው የሚሆኑት? በተጨማሪም፣ ዮሐንስ ተደጋጋሚ የብሉይ ኪዳን ምስሎችን፣ ከትክክለኛ የብሉይ ኪዳን ምንጮች አኳያ ተርጉሟልን፣ ወይስ እነዚህን ምስሎች ነጻ ሆኖ ነው የተረጎማቸው? ምስላዊው ምንድነው ጥሬአዊው ምንድነው? የእነዚህ ጥያቄዎች መልሶች የተርጓሚውን አገባብ ይወስነዋል። ከእነዚህ ጥያቄዎች ጥቂቱ ቀኖናዊ ምላሽ ማግኘት ቢችሉም፣ ያፈነገጡ አገባቦችን በብልሃት መያዝ ይጠይቃል፣ መንፈስ ቀና የሆነ ውይይትን ሊጠቀም ይችላል ወደ አፖካሊፕቲካዊ ፍቺ ለመድረስ እንዲመራን" (ገጽ 69)።
2. ራዕይ ከብኪ ጋር ላለው ዝምድና እንዳጠቃላይ መግቢያ፣ የጆን ፒ. ሚልተንን *የተተረጎመ ትንቢት* እና የጆን ብራይትን *የብሉይ ኪዳን ሥልጣን* እመርጣለሁ። ለመልካም ማብራሪያ፣ ራዕይና ጳውሎስ እንዴት እንደሚገናኝ፣ የጀምስ ኤስ. ስቲዋርትን *ሰው በክርስቶስን* እመርጣለሁ።

## የንባብ ምድብ አንድ ገጽ (ገጽ v ተመልከት)

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መጽሐፍ በአንድ ቁጭታ አንብበው፡፡ የሙሉውን መጽሐፍ ማዕከላዊ ጭብጥ በራስህ ቋንቋ አስፍር።

1. የሙሉው መጽሐፍ ጭብጥ
2. የሥነ-ጽሑፉ (ዘውጉ) ዓይነት

## የንባብ ምድብ ሁለት (ገጽ v ተመልከት)

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

የመጽሐፍ ቅዱሱን መጽሐፍ ሙሉውን ለሁለተኛ ጊዜ በአንድ ቁጭታ አንብበው፡፡ ዋነኛ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይተህ በአንድ ዓረፍተ ነገር ፍሬ ሐሳቡን ግለጽ።

1. የመጀመሪያው ጽሑፋዊ ምድብ ፍሬ ሐሳብ

2. የሁለተኛው ጽሑፋዊ ምድብ ፍሬ-ሐሳብ

3. የሦስተኛው ጽሑፋዊ ምድብ ፍሬ ሐሳብ

4. ወዘተርፈ

# ራዕይ 1፡1-20
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| የተመቅሶ4 | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| *መግቢያ እና ሰላምታ* | *መግቢያና ቡራኬ* | *መቅድም* | *መግቢያ* | *መቅድም* |
| 1:1-3 | 1:1-3 | 1:1-2 | 1:1-3 | 1:1-3 |
| | | 1:3 | | |
| | ሰላምታ ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት | የመግቢያ ሰላምታ | ሰላምታ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት | ሰላምታ ማቅረብ |
| 1:4-5ሀ | 1:4-8 | 1:4-5ሀ | 1:4-5ሀ | 1:4-8 |
| 1:5ለ-7 | | 1:5ለ-7 | 1:5ለ-6 | |
| | | | 5:7 | |
| 5:8 | | 5:8 | 5:8 | |
| የክርስቶስ ራዕይ | የሰው ልጅ ራዕይ | የመሰናዶ ራዕይ | የክርስቶስ ራዕይ | ቀዳሚ ራዕይ |
| 1:9-11 | 1:9-20 | 1:9-11 | 1:9-11 | 1:9-16 |
| 1:12-16 | | 1:12-16 | 1:12-20 | |
| 1:17-20 | | 1:17-20 | | 1:17-20 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ vii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

---

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው። እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ማዕከላዊ ርዕስ፣ እውነት ወይም አስተሳሰብ አለው። እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል። ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕስ ጒዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብሃል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጒዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን)። ከዚያም ያንተን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጒሞች ጋር ማወዳደር ይኖርብሃል። መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አመክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው። ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው— አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም። የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

ማስታወሻ፡- ሁሉም ሙያዊ ቃላትና አጽሕሮተ ቃላት በሙሉ በቅጥያ አንድ፣ ሁለት፣ እና ሦስት ላይ ተብራርተዋል።

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘቶች ለ1፡1-3፡22

ሀ. ቁጥር 1-8 ከመቅድሙ እስከ ሙሉው ትንቢት። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ቁጥሮች ደራሲውን፣ ጊዜውን፣ ዘውጉን፣ እና ቡራኬውን ያስተዋውቃሉ።

1. ደራሲው ዮሐንስ ነው (የተለመደ የአይሁድ ስም)
2. ጊዜው ቅርብ ነው (1ለ፣ 3ሐ)።
3. መልእክቱ በራዕይና በመላእክት በኩል በተደረገ ተግባቦት ነው፣ እናም ትንቢት ይባላል (ቁ. 3)። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች እጅግ ተመሳሳይ ናቸው፣ በአንደኛው ክፍለ ዘመን በተለመደው የደብዳቤ አጻጻፍ ስልት።
4. ባርኮቱ ጽሑፉን ለሚያደምጡትና ለሚታዘዙት ነው፣ በቅንነትና በታማኝነት፣ በመከራ መካከል።

ለ. ቀጣዮቹ አራት ቁጥሮች (4-7) ተቀባዮቹን ያመለክታል፣ እንደ ሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት (1-11) እና የእነሱን ሰባት መናፍስት (ዝከ. 1:4፣20፤ 3:1፤ 4:5፤ 5:6)። ይህ ክፍል የተመለከተው

1. ያህዌ ባሕርዩ የሆነው (ቁ. 4)
2. ኢየሱስ ባሕርዩ የሆነው (ቁ. 5፣ 6ለ፣ 7)
3. የአማኞች ባሕርይ መሆን ያለበት (ቁ. 6ሀ)
4. ያህዌ ሲናገር (ቁ.8)

ሐ. ቁጥር 1፡9-3፡22 የኢየሱስ የመጨረሻ ቃላት ናቸው፣ ለቤተ ክርስቲያኑ(ኖቹ)። በ1፡9-20 እና ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን፣ ለሰባቱም መልእክት መጀመሪያ ላይ፣ ኢየሱስ ባሕርዩ የተገለጠው በብኪ የያህዌ መጠሪያዎች ነው።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

### ራዕይ 1፡1-3

**[1]ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥ [2]እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ። [3]ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።**

**1፡1 "ራዕይ"** ይህ የግሪክ ቃል *apocalypsis* በመጽሐፉ ውስጥ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። እሱም የተገኘው ከሁለት የግሪክ ቃላት ሲሆን "ከተሸሸገ ስፍራ" ወይም "መግለጥ ወይም አንድን ነገር መግለጥ" ማለት ነው። እሱም በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል (ቢኤጂዲ ገጽ 92)።

1. እውነትን መግለጥ — ሉቃስ 2:32፤ ሮሜ. 16:25፤ I ቆሮ. 14:6፣26፤ ገላ. 1:12፤ ኤፌ. 1:17
2. የተገለጠ ምሥጢር – ኤፌ. 2:11-3:13
3. መገለጥ በራዕይ/ሕልም – II ቆሮ. 12:1፣7፤ ገላ. 2:2
4. ከፍጻሜ ዘመን ጋር የተያያዙ ምሥጢራት – ሉቃስ 17:30፤ I ቆሮ. 1:7፤ II ተሰ. 1:7፤ I ጴጥ. 1:7፣13፤ 4:13፤ 5:1

በዚህ መጽሐፍ የሚለው ከእግዚአብሔር የሆነ እውነት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በራዕይ እና በመላእክት በኩል ተተርጉሟል ነው። የሚያተኩረውም በክፉው መኖርና በሚመጣው የጽድቅ ድል፣ ይኸውም በእግዚአብሔር ከአዕምሮ በላይ በሆነ ጣልቃ ገብነት ነው። እግዚአብሔር ነገሮችን መልክ ያስይዛል!

▣ **"የኢየሱስ ክርስቶስ"** ይህ አንድም የማን እንደሆነ፣ መልእክቱ ስለ ኢየሱስ መሆኑን የሚያሳይ (ገላ. 1፡12)፣ ወይም ተያያዥ ባለቤትነት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰጠው መልእክት ጋር የሚያያዝ ነው።

▣ **"ኢየሱስ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ፍችው "ያህዌ ያድናል፣" "ያህዌ መዳን ነው፣" "ያህዌ ደኅንነትን ያመጣል" ማለት ነው። እሱም ከብኪ ስም "ኢያሱ" ጋር አንድ ነው። "ኢየሱስ" የመጣው ከዕብራይስጡ ቃል ማዳን፣ "*hosea*፣" ከእግዚአብሔር የኪዳን ስም ጋር ተያይዞ ነው፣ "ያህዌ" (ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች ቆላ. 1፡3 ተመልከት)። እሱም በእግዚአብሔር የተሰየመ ነው፣ በጌታ መልአክ በኩል (ማቴ. 1፡21)።

▣ **"ክርስቶስ"** ይህ የግሪክ አቻ የሆነ የዕብራይስጥ ቃል "*messiah*፣" ነው፣ ፍችውም "የተቀባው።" የሚያመለክተውም "አንዱ ለተለየ ሥራ በእግዚአብሔር የተጠራና የበቃ ነው።" በብኪ ባለ ሦስት ምድብ መሪዎች፡ ካህናት፣ ነገሥታት፣ እና ነቢያት ይቀቡ ነበር። ኢየሱስ እነዚህን ሦስቱንም ሁሉ የቅባት ሹመቶች አሟልቷል (ዕብ. 1፡2-3)።

### ልዩ ርዕስ፡ መሲሕ

ይህ የተወሰደው ከእኔ ሐተታዊ ማስታወሻ ከዳንኤል 9፡8 ላይ ነው። ይሄንን ቁጥር ለመተርጎም ያለው አስቸጋሪነት ምክንያቱ፣ መሲሕ ወይም የተቀባው ለሚለው ቃል ተያያዥ የሆኑት ታሳቢ ፍችዎች ናቸው (ቢዲቢ 603)።

1. ለአይሁድ ነገሥታት ጥቅም ላይ ውሏል (ምሳ. 1ኛ ሳሙ. 2፡10፤ 12፡3)

2. ለአይሁድ ካህናት ጥቅም ላይ ውሏል (ምሳ. ሌዋ. 4፡3፣5)
3. ለሳይረስ ጥቅም ላይ ውሏል (ኢሳ. 45፡1)
4. ቁ. 1 እና 2 በመዝሙር 110 እና ዘካርያስ 4 ላይ ተደባልቀዋል
5. ለእግዚአብሔር ልዩ ምጽዓት ጥቅም ላይ ውሏል፣ ዳዊታዊ ንጉሥ አዲሱን የጽድቅ ዘመን ለማምጣት
   ሀ. የይሁዳ የዘር ሐረግ (ዘፍ. 49፡10)
   ለ. የእሴይ ቤት (2ኛ ሳሙ. 7)
   ሐ. አጠቃላይ ግዛት (መዝ. 2፤ ኢሳ. 9፡6፤ 11፡1-5፤ ሚክ. 5፡1-4)

እኔ በበኩሌ የተማረክሁት የተቀባው አንዱን ለመለያነት በሚለው ነው፣ እሱም ለናዝሬቱ ኢየሱስ ምክንያቱም

1. ለዘላለማዊ መንግሥት መቅድም፣ በምዕራፍ ሁለት በአራተኛው ኢምፓየር (ግዛት)
2. "ለሰው ልጅ" መቅድም በ7፡13 ዘላለማዊ መንግሥት የተሰጠው
3. የመቤዣ ሐረጎች 9፡24፣ እሱም የሚያመለክተው ወደ ወደቀው ዓለም ታሪክ ድምዳሜ
4. የኢየሱስ የዳንኤልን መጽሐፍ አጠቃቀም፣ በአኪ (ማቲ. 24፡15፤ ማርቆስ 13፡14)

▣ **"እግዚአብሔር የሰጠው"** ኢየሱስ ከአብ ሳይገለጥለት ወይም ሳያስፈቅድ አላስተማረም ወይም ምንም አላደረገም (ዮሐንስ 3፡11-13፣ 31-36፤ 4፡34፤ 5፡19-23፣30፤ 6፡38፤ 7፡16፤ 8፡26፣28-29፣40፤ 12፡49-50፤ 14፡10፣24፤ 15፡15)። ከሥነ መለኮት አኳያ ይህ የዮሐንስ አጻጻፍ ስልት ነው።

▣ ***"ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ"*** ይህ የመክፈቻ አንቀጽ 22፡6-21 ላይ እንዴት እንደተንጸባረቀ ተገንዘቡ። ይህ የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ጽሑፋዊ ዘዴ ነው።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | ***"ቶሎ የሚሆኑትን ነገሮች"*** |
| **አየተመት** | ***"ቶሎ የሚሆነውን"*** |
| **አእት** | ***"በቅርቡ የሚሆነውን"*** |
| **አኢመቅ** | ***"አሁኑኑ ቶሎ የሚሆነውን"*** |

የጊዜ ጉዳይ እጅግ አስፈላጊ ነው፣ ሙሉውን መጽሐፍ ለመተርጎም፣ ምክንያቱም እሱ ለይቶ እንዳስቀመጠው የዮሐንስ መልእክት ለእሱ ቀንና ብሎም ለሚመጣው ጠቀሜታ ስላለው ነው። "የግድ" የሚለው ቃል (*dei*) ፍችው "አሳሪ የሆነው፣ ከሞራል አኳያ አስፈላጊ የሆነው፣ ተገቢ የሆነው፣ ወይም ተመራጭ የሆነው" ማለት ነው (ራዕ. 22፡6)።

## ልዩ ርዕስ፡ ፈጥኖ መመለስ

"ቶሎ ይሆን ዘንድ" ለሚለው ጽንሰ-ሐሳብ ራዕ. 1፡3፤ 2፡16፤ 3፡11፤ 22፡7፣10፣12፣20 አወዳድር። ይህ ምናልባት የብኪ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል ዳን. 2፡28፣ 29፣ እና 45። ዮሐንስ ብኪን ፈጽሞ አልጠቀሰም ግን ብዙ ጠቃሽ አድርጓል። ከ404 ቁጥሮች፣ 275 ያህሉ የብኪ ዳራ አላቸው። ተርጓሚዎች በዚህ ሐረግ ትርጓሜ ላይ ተከፋፍለዋል፣ በራዕይ መጽሐፍ ላይ ባላቸው *ሥነ-መለኮታዊ ቅድመ-ግምት* ምክንያት፡

1. በድንገት
2. አንዴ ከተጀመረ በፍጥነት ይሆናል
3. በቅርቡ ይጀምራል
4. በርግጥ ይሆናል
5. *ወዲያውኑ*

የዚህ ቃል አጠቃቀም ራዕ. 22፡7፣ 12፣ 20 ላይ እንደሚያመለክተው ዮሐንስ እነዚህ ሁነቶች በእርሱ የሕይወት ጊዜ ላይ ፈጥነው እንደሚደርሱ ተጠባብቆ ነበር (ቁ. 3፤ 10፡6 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት)። ይህ መጽሐፍ ከተጻፈና በእኛ ዘመን መካከል የ2000 ዓመት ልዩነት በመኖሩ፣ ብዙዎች ዮሐንስ ተሳስቶ ነበር ብለዋል። ሆኖም፣ የወዲያውኑ የጊዜ ቅምብብ (ፍሬም) መጠቀም የትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ ደንብ ይመስላል፣ ይኸውም ከብሉይ ኪዳን፣ የአሁኑ ሁነቶች የፍጻሜ ሰዓቱን ሁነቶች ከሚያስረግጠው። ዮሐንስ የአንደኛውን ክፍለ-ዘመን ሮም ተጠቅሟል ፍጻሜውን ለማሳየት (የመጨረሻ ቀኖች) ኢሳይያስና ሕዝቅኤል መመለስን እንደተጠቀሙ (ድኅረ-ግዞት) ይሁዳ፣ እንዲሁም ዳንኤል አንቲከስ ኢፒፋነስ IVን እንደ ተጠቀመበት። አዲሱ የጽድቅ ዘመን ምጽአት ለእያንዳንዱ የአማኞች ትውልድ ተስፋና ማበረታቻ ነው። ሙሉውን ማስታወሻ 22፡6 ላይ ተመልከት።

ደግሞም ዲ. ብሬንት ሳንዲ፣ *የማረሻ ጫፍ እና መቁረጫ ማጭድ* ገጽ 101-102 ተመልከት፣ ለትንቢታዊ ምስያ ቃል የከፋና ያልተጠበቀ ስለመሆኑ፣ ገጽ 173-175

▣ **"የተገለጠው እሱ"** ይህ በጥሬው "የታወቀው" ነው (*semain0*) (አኪጀት)። "ምልክቶች" አንደኛው ጽሑፋዊ አወቃቀር ነው፣ ዮሐንስ መልእክቱን በወንጌሉ ለማስተላለፍ የተጠቀመበት (*semeion*፣ ዝከ. 12፡33፤ 18፡32፤ 21፡19)። ይህ የብኪ ግንኙነት ሊኖረው

ይችላል፣ ከብኪ ነቢያት ጋር (ኢሳ. 7:11፣14፤ 8:18፤ 19:20፤ 20:3፤ 37:30፤ 38:7፣22፤ 55:13፤ 66:19፤ ኤር. 10:2፤ 32:20-21፤ 44:29 እና ሕዝ. 4:3፤ 14:8፤ 20:12፣20)። ይህ መጽሐፍ "ራዕይ" ተብሎ የተጠራበት ሐቅ፣ በ "ምልክቶች" እና "ትንቢት" ለዚህ መጽሐፍ ጽሑፋዊ ዘውግ ፍንጭ ይሰጠናል። ዘመናዊው ጽሑፋዊ ቃል "አፖካሊፕቲክ" ዘውጉን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለው በዮሐንስ አይታወቅም ነበር።

▣ **"ለባርያው"** በዚህ የመግቢያ ቁጥር ይህ ሐረግ የመጽሐፉን ሐዋርያዊ ደራሲ ይጠቅሳል። በመጽሐፉ ሌሎች ስፍራዎች የብዙ ቁጥሩ ጥቅም ላይ የዋለው ለእግዚአብሔር ነቢያት/መልእክተኞች/ሰባኪያን ነው (ዝከ. 10:7፤ 11:18፤ 22:6)።

ሆኖም፣ በሌሎች ስፍራዎች በመጽሐፉ መጠሪያው ጥቅም ላይ የዋለው ለሁሉም አማኞች ነው (ዝከ. 7:3፤ 19:2፣5፤ 22:3)፣ የእሱም አንድምታ ሁሉም አማኞች ምስክር ለመሆናቸው (ማቴ. 28:18-20፤ ቆላ. 4:6፤ II ጢሞ. 2:24-25፤ I ጴጥ. 3:15)። ኢየሱስ የምንከተለው ሞዴላችን ነው (ዝከ. 1:5፤ 3:14፤ ዮሐንስ 20:21)! ብዙዎች ይገደላሉ፣ ኢየሱስ እንደሆነው (ዝከ. 6:9፤ 12:17፤ 17:6፤ 18:24፤ 20:4). የመጽሐፉ ጭብጥ እስከ ሞት ድረስ መታመን እንደሆነ አስታውሱ! እኔ (ኢየሱስ) ድል ነሥቻለሁ!

▣ **"ዮሐንስ"** ከሌሎቹ አፖካሊፕቲካዊ ደራስያን በተለየ ሁኔታ፣ ዮሐንስ ራሱን ገልጧል፣ እንዲሁም የትንቢት ምስክርነት መከፈቻ መዋቅሩን በሰባት መልእክቶች ዓይነት (ምዕራፍ 1-3)። አንዳንዶች የራዕይ መጽሐፍ ደራሲ ዮሐንስ እንደሆነ አይቀበሉም፣ ምክንያቱም ከሌሎቹ ጽሑፎቹ ጋር ስለሚቃረን (እሱ ራሱን "ተወዳጁ ደቀ-መዝሙር" በወንጌል፣ እና "ሽማግሌው" በ2 እና 3 ዮሐንስ፣ ብሎ ስለጠራ)፣ ግን በራዕይ ላይ ራሱን ጠርቷል ራዕ. 1:4፣ 9፤ 22:8።

**1:2 "ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር"** እንደ ቁ.1፣ ይህ ሌለኛው ተሳቢ ሊሆን ይችላል፣ ስለ ኢየሱስ ምስክርነት፣ ወይም ባለቤት አመላካች፣ ምስክርነቱ የተሰጠው በኢየሱስ ነው። አንዳንድ ጊዜ በዮሐንስ ጽሑፎች ሆን ተብሎ የተደረገ አሻሚነት አለ፣ እሱም ሁለቱንም ፍቺዎች የሚደባልቅ።

**1:3 "የተባረከ"**ይህ ከሰባቱ ቡራኬዎች የመጀመሪያው ነው፣ በዚህ መጽሐፍ (ዝከ. 1:3፤ 14:13፤ 16:15፤ 19:9፤ 20:6፤ 22:7፣14)። የሚያነቡት እንደሚባረኩ የሚለው ሐቅ የሚያመላክተው ተመስጧዊ ባሕርዩን ብቻ አይደለም፣ ግን ደግሞ ለዛን ዘመንና ለሁሉም ዘመን ያለውን ጠቀሜታ ደግሞ እንጂ።

▣ **"የሚያነበው"** አየተመት "ጮኾ" የሚል ይጨምራል፣ ያደባባይ ንባብን ሲያመላክት (1 ጢሞ. 4:13)። በማኅበረ-ምዕመናን ፊት የሚደረግ የቅዱስ ቃሉ ንባብ በዋነኛነት ይደረግ የነበረው በተለየ መልኩ በሠለጠኑ የቤተ-ክርስቲያን አባላት ነበር፣ ልክ እንደ ምኩራብ (የምኩራብ አለቃ)። ቤተ-ክርስቲያን የቀድሞውን ምኩራብ የአምልኮ ሥርዓት ተከትላለች (ሉቃስ 4:16፤ ሐዋ. 13:15፤ ቆላ. 4:16፤ I ተሰ. 5:27)። የቅዱስ ቃሉ የአደባባይ ንባብን በተመለከተ ታሪካዊ ማረጋገጫ አለን፣ ከጀስቲን ማርቲየር፣ 167 ዓ. ም፣ እሱም እንደጠቀሰው ቤተ-ክርስቲያን እኩሌታውን ከወንጌላት እንዲሁም እኩሌታውን ከነቢያት ታነብ ነበር።

▣ **"የሚሰማው... እና የሚጠብቀው"** ይህ ማድመጥና ማድረግ (ሁለቱም የአሁን የድርጊት አንቀጾች) የዕብራይስጡ ቃል "*Shema*" ፍቺ አላቸው (ዘዳ. 5:1፤ 6:4-6፤ 9:1፤ 20:3፤ 27:9-10፤ ሉቃስ 11:28)። የባርኮቶቹን ሁኔታዊ ተፈጥሮ ተገንዘብ። የሚሰሙ የግድ ምላሽ መስጠት አለባቸው። ይህ "እንደ... ከዚያም" ውላዊ ፈርጅ ለሁለቱም ለብኪ እና አኪ ነው። ባርኮት የሚያያዘው ከማወቅ ጋር ብቻ አይደለም፣ ከሕይወት ስልት ደግሞ እንጂ።

▣ **"ይሄንን ትንቢት"** ይህ ቃል የሚያመለክተው የዚህን መጽሐፍ መለኮታዊ ይዘትና ጽሑፋዊ ዘውጉን ነው። ይህ መጽሐፍ የመልእክቶች ድብልቅ ነው (ምዕራፍ 1-3)፣ አፖካሊፕቲካዊ አቀራረብ (ማኅተሞች፣ መለከቶች፣ ጽዋዎች)፣ እና ትንቢት (ዝከ. 22:7፣ 10፣18፣19)። "ትንቢት" ሁለት ፍቺዎች እንዳሉት ማስታወስ ጠቃሚ ነው፡ (1) የጊዜውን አድማጮች በእግዚአብሔር መልእክት ለመድረስ እና (2) የጊዜው እምነት በመጻኢዎቹ ሁነቶች ላይ ተጽዕኖ እንዳለው። እሱ ሁለቱንም ነው፣ አዋጁንና ትንበያውን። የመግቢያውን ጽሑፍ ተመልከት።

▣ **"ዘመኑ ቀርቧልና"** ይህ በድጋሚ የሚያመለክተው የትንቢቱን ጠቃሚነት ነው፣ ለገዛ ራሱ ጊዜ (ዝከ. 22:10፣ ሌላ ምሳሌ ሮሜ. 16: 20 ላይ አለ)። ልዩ ርዕስ፡ በቅርብ መመለስን ቁ. 1 ላይ ተመልከት።

### ራዕይ1:4-7

**[4-5]ዮሐንስ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤ ካለውና ከነበረው ከሚመጣውም፥ በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፥ ከታመነውም ምስክር ከሙታንም በኵር የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥ [6]መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን። [7]እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።**

**1:4 "ለሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት"** በትክክል ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ መጠቀሳቸው ግልጽ አይደለም። በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡

1. አንዳንዶች የሚያስረግጡት፣ የሐንስ የተለየ የአገልግሎት ግንኙነት የነበረው ከእነዚህ ቤተ-ክርስቲያኖች ጋር ነበር ይላሉ
2. ሌሎች የሚያስረግጡት እነሱ የደብዳቤ መላላኪያ መስመር በእስያ አውራጃ ሮሜ ዘርግተው ነበር ይላሉ
3. ቁጥር ሰባት በአይሁድ ዘንድ ጉልህ ጠቀሜታ አለው፣ በተለይም በበይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-ጽሑፍ

እሱም የፍጽምና ቁጥር ነው፣ በዘፍጥረት 1 ላይ ካለው የቀን አጠቃቀም የተነሣ። ስለዚህ፣ እሱ ምናልባት በሁለቱም ጥቅም ላይ ውሎ ይሆናል፣ በጥሬ መልኩ — ዮሐንስ ለበርካታ ቤተ ክርስቲያኖች ጽፎ ይሆናል፣ በትንሹ እስያ በሮሜ የደብዳቤ መስመር ለመሠረቱ — እና በምስያነት በሁሉም ዘመናት ላሉ ለሁሉም ቤተ-ክርስቲያኖች መጥቀሻ መንገድ ይሆናል።

**ልዩ ርዕስ፡ ተምሳሌት (ምልክት) ቁጥሮች በቅዱስ ቃሉ**

ሀ. አንዳንድ ቁጥሮች እንደ መቁጠሪያ እና ተምሳሌት ያገለግላሉ፡

1. አንድ — እግዚአብሔር (ምሳሌ፣ ዘዳ. 6፡4፤ ኤፌ. 4፡4-6)
2. ስድስት — የሰው የፍጽምና ጉድለት (ከ7 አንድ ሲቀነስ፣ ምሳሌ፣ ራዕ. 13፡18)
3. ሰባት — መለኮታዊ ፍጽምና (ሰባቱ የፍጥረት ቀናት)። በራዕይ ያሉትን ተምሳሌታዊ አጠቃቀሞች ተገንዘብ።
   ሀ. ሰባት መቅረዞች፣ 1፡12፣20፤ 2፡1
   ለ. ሰባት ኮከቦች፣ 1፡16፣20፤ 2፡1
   ሐ. ሰባት ቤተ-ክርስቲያናት፣ 1፡20
   መ. ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት፣ 3፡1፤ 4፡5፤ 5፡6
   ሠ. ሰባት መብራቶች፣ 4፡5
   ረ. ሰባት ማኅተሞች፣ 5፡1፣5
   ሰ. ሰባት ቀንዶች እና ሰባት ዓይኖች፣ 5፡6
   ሸ. ሰባት መላእክት፣ 8፡2፣6፤ 15፡1፣6፣7፣8፤ 16፡1፤ 17፡1
   ቀ. ሰባት መለከቶች፣ 8፡2፣6
   በ. ሰባት ነጎድጓድ፣ 10፡3፣4
   ተ. ሰባት ሺህ፣ 11፡13
   ቸ. ሰባት ራሶች፣ 13፡1፤ 17፡3፣7፣9
   ኀ. ሰባት መቅሠፍቶች፣ 15፡1፣6፣8፤ 21፡9
   ነ. ሰባት ጎድጓዳ ሳህኖች፣ 15፡7
   ኘ. ሰባት ነገሥታት፣ 17፡10
   አ. ሰባት ጽዋዎች፣ 21፡9
4. አስር — ፍጽምና
   ሀ. በወንጌል አጠቃቀማቸው፡
      (1) ማቴ. 20፡24፤ 25፡1፣28
      (2) ማርቆስ 10፡41
      (3) ሉቃስ 14፡31፤ 15፡8፤ 17፡12፣17፤ 19፡13፣16፣17፣24፣25
   ለ. በራዕይ አጠቃቀሙ፡
      (1) 2፡10፣ የአስሩ ቀን መከራ
      (2) 12፡3፤ 17፡3፣7፣12፣16፣ አስር ቀንዶች
      (3) 13፡1፣ አስር ዘውዶች
   ሐ. የ10 ብዜት በራዕይ፡
      (1) 144,000=12×12×1,000፣ ዝከ. 7፡4፤ 14፡1፣3
      (2) 1,000= 10×10×10፣ ዝከ. 20፡2፣3፣6
5. አስራ ሁለት — የሰው አደረጃጀቶች
   ሀ. የያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች (ማለትም፣ የእስራኤል አስራ ሁለት ነገዶች፣ ዘፍ. 35፡22፤ 49፡28)
   ለ. አስራ ሁለት ዐምዶች፣ ዘጸ. 24፡4
   ሐ. አስራ ሁለት የዕንቁ ድንጋዮች፣ በሊቀ ካህኑ ደረት ላይ የሚሆኑ፣ ዘጸ. 28፡21፤ 39፡14
   መ. አስራ ሁለት ሙልሙል ዳቦዎች፣ በቅዱስ ስፍራ ጠረጴዛ ላይ የሚሆኑ (ለእግዚአብሔር የአስራ ሁለቱ ነገዶች በጋቢነት ተምሳሌት)፣ ሌዋ. 24፡5፤ ዘጸ. 25፡30
   ሠ. አስራ ሁለት ሰላዮች፣ ዘዳ. 1፡23፤ ኢያ. 3፡22፤ 4፡2፣3፣4፣8፣9፣20
   ረ. አስራ ሁለት ሐዋርያት፣ ማቴ. 10፡1
   ሰ. በራዕይ አጠቃቀሙ፡
      (1) አስራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ 7፡5-8
      (2) አስራ ሁለት ከዋክብት፣ 12፡1
      (3) አስራ ሁለት ደጆች፣ አስራ ሁለት መላእክት፣ አስራ ሁለት ነገዶች፣ 21፡12
      (4) አስራ ሁለት የመሠረት ድንጋዮች፣ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ስሞች፣ 21፡14
      (5) አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አስራ ሁለት ሺህ ስኴር ሜዳ ነች፣ 21፡16

(6) አስራ ሁለት ደጆች ከአስራ ሁለት እንቁ የተሠሩ፣ 21፡12
(7) የሕይወት ዛፍ አስራ ሁለት ዓይነት ፍሬዎች፣ 22፡2

6. አርባ —የጊዜ ቁጥር፡
   ሀ. አንዳንዴ በጥሬው (ዘጸዓት እና የምድረ በዳ መንከራተት፣ ምሳ. ዘጸ. 16፡35)፤ ዘዳ. 2፡7፤ 8፡2
   ለ. በጥሬው ወይም ተምሳሌታዊ ሊሆን ይችላል
   (1) የጥፋት ውኃ፣ ዘፍ. 7፡4፣17፤ 8፡6
   (2) ሙሴ በሲና ተራራ፣ ዘጸ. 24፡18፤ 34፡28፤ ዘዳ. 9፡9፣11፣18፣25
   (3) የሙሴ ሕይወት ምድቦች፡
   (ሀ) አርባ ዓመት በግብፅ
   (ለ) አርባ ዓመት በምድረ በዳ
   (ሐ) አርባ ዓመት እስራኤልን በመምራት
   (4) ኢየሱስ አርባ ቀናት ጾመ፣ ማቴ. 4፡2፤ ማርቆስ 1፡13፤ ሉቃስ 4፡2
   ሐ. (በኅብራዊ መልኩ) ይህ ቁጥር የሚከሰትበት ጊዜ ብዛት ከጊዜ አኳያ መጽሐፍ ቅዱስ መመደቡን (መለየቱን) ተገንዘብ!
7. ሰባ — ለሕዝብ የጥቅል ቁጥር፡
   ሀ. እስራኤል፣ ዘጸ. 1፡5
   ለ. ሰባ ሽማግሌዎች፣ ዘጸ. 24፡1፣9
   ሐ. የፍጻሜ መዳረሻ፣ ዳን. 9፡2፣24
   መ. የተልዕኮ ቡድን፣ ሉቃስ 10፡1፣17
   ሠ. ይቅርታ (70×7)፣ ማቴ. 18፡22

ለ. የተሻሉ ማጣቀሻዎች
1. ጆን ጄ. ዳቪስ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-ቁጥር
2. ዲ. ብሬንት ሳንዲ፣ ማረሻና መኮትኮቻ መንጠቆ

**ልዩ ርዕስ፡ ቤተክርስትያን**

ላይ ይህ የግሪኩ ቃል ኤክሌሲያ ይባላል ቃሉ የሁለት ቃላት ጥምረት ነው፤ የመጡ እና የተጠሩ ከሚባሉት ስለዚህ ቃሉ የሚያመለክተው በመለኮት ተጠርተው የወጡትን የሚያሳይ ነው፡፡ የቀደመችው ቤተክርስትያን ይህን ቃል የወሰደችው ከዓላማዊው አጠቃቀም ነው (ሐዋ 19፡32፣ 39፣41) እንዲሁም ደግሞ የሰብትዋጅንት ትርጉም ይህን ቃል የእስራኤልን "ማህበር" ለማመልከት በመጠቀሙም ጭምር ነው (ዘኁልቁ 16፡3፣20፡4)፡፡ የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ቀጣይነታቸውን ለማመልከት ለራሳቸው ተጠቀሙት እነርሱም አዲሷ እስራኤል ነበሩ (ሮሜ 2፡28-29፣ ገላ 6፡16፣ 1ጴጥ 2፡5፡ 9፣ ራዕ 1፡6) የእግዚአብሔርን አለም አቀፋዊ ተልዕኮ መሪውም ለማመልከት (ዘፍ 3፡15፣ 12፡3 ዘፀ 19፡5-6፤ ማቴ 28፡18-20፤ ሉቃ 24፣47፤ ሐዋ 1፡8)፡፡

ይህ ቃል በወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተለያዩ ትርጓሜዎችን ይዟል፡፡

ሀ. በከተማ ውስጥ ያለን መገናኘት ሐዋ 19፡32፤ 39፡41
ለ. በክርስቶስ ያለን አጠቃላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማቴ 16፡18 እና ኤፌሶን
ሐ. በአንዲት አጥቢያ በክርስቶስ የሚገኙ አማኞችን ማቴ 18፡17፤ ሐዋ 5፡11 (በእነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ያለችውን ቤተክርስትያን ያመለክታል፡፡
መ. የእስራኤል ሕዝብ በጥቅሉ ሐዋ 7፡38፤ በእስጢፋኖስ ስብከት
ሠ. በአንድ አካባቢ ያለን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሐዋ 8፡3 (በይሁዳ ወይም በፍልስጤም ምድር)

▣ **"በእስያ"** ይህ የሚያመለክተው የምዕራባዊ ዳርቻ የሆነውን ዘመናዊውን የቱርክ አገር ነው፣ እሱም ሰፊ ስፍራው የድሮው የፔርጂያ አገር፣ "በትንሹ እስያ" የሮሜ አውራጃ የነበረው።

▣ ***"ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን"*** *ይህ* ልማዳዊ የሰላምታ ዓይነት ነበር፣ ይኸውም ተዘውትሮ በጳውሎስ ጽሑፎች ላይ የሚገኝ። ብዙዎች እንደሚያስረግጡት ክርስቲያኖች ልማዳዊውን የግሪክ ሰላምታ ቀይረውታል፣ ከ"*charein*" (ያዕቆብ 1፡1) ወደ ክርስቲያናዊ ተመሳሳይ ሰላምታ *charis*፣ ፍችውም "ጸጋ" የሆነ። "ሰላም" የዕብራይስጡን ቃል "*shalom*"ን ያመለክታል፣ እንዲህም የግሪክና የዕብራይስጥ ሰላምታዎችን በማደባለቅ ሁለቱን ወገኖች በቤተ-ክርስቲያኖች ለማዛመድ ነው። ሆኖም፣ ይህ የእንዲያው ግምት ነው።

▣ **"ካለው ከነበረው ከሚመጣውም"** ይህ በግልጽ የማይለወጠው የእግዚአብሔር ኪዳን መጠሪያ ነው (መዝ. 102፡7፤ ሚል. 3፡6፤ ያዕቆብ 1፡17)። ሰዋሰዋዊ መልኩ በግሪክ አስቸጋሪ ቢሆንም አራማዊ ዳራን ያንጸባርቅ ይሆናል። ጽሑፋዊ ሐረጉ "ካለው፣ ከነበረው፣ እና ከሚመጣው" ነው (ዝከ. 4፡8)። ይህ ሐረግ የብኪን የኪዳን ስም ይጠቅሳል "ያለና የሚኖር" (ያህዌ፣ ዘጸ. 3፡14፣ ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች 1፡8 ላይ ተመልከት)። ይህ ሐረግ ለእግዚአብሔር አብ ጥቅም ላይ ውሏል ቁ. 4 እና 8 ላይ፣ እንዲሁም ለኢየሱስ

ክርስቶስ ቁ. 17 እና 18 ላይ (ዕብ. 13፡8)። ሆን ተብሎ የተደረገው ከያህዌ ወደ ኢየሱስ የስም መዘዋወር፣ የአኪ. ደራስያን የተጠቀሙበት አንደኛው መንገድ ነው የኢየሱስን መለኮትነት ለማስረገጥ።

ይህ ሦስትዮሽ ሐረግ፣ እግዚአብሔር ያለፈው፣ የአሁኑ፣ እና የወደፊቱ መሆኑ 11፡17 እና 16፡5 ላይ ተቀምጧል፣ በመለከቶቹ መጨረሻ ላይ ለሚሆነው ዳግም ምጽአት፣ ያሁኑና ያለፈውን እውንነት ለማሳየት፣ የወደፊቱ (የፍጻሜ ሰዓት) በመቃረቡ።

▣ **"በዙፋኑም ፊት ካሉ ከሰባቱ መናፍስት"** ከሥር ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ሰባቱ መናፍስት

እነዚህን ሰባት መናፍስት ለመግለጽ በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ።

1. ይህ ሐረግ የመጣው እግዚአብሔር አብን እና ኢየሱስን እንደ መሲሕ በመጥቀስ መካከል በመሆኑ፣ በርካታ አታቾች የሚያስረግጡት በትክክል የተጠቀሰው ለመንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ ይቻላል፣ ርግጠኛ ግን አይደለም። ይህ ስማዊ ሐረግ ደግሞ 3፡1፤ 4፡5 እና 5፡6 ጥቅም ላይ ውሏል። በእነዚህ ሌሎች አጋጣሚዎች ሙሉ ለሙሉ ርግጠኛ መሆን አይቻልም፣ እሱ ለመንፈስ ቅዱስ የተጠቀሰ ለመሆኑ፣ ዘካርያስ 4 ላይ ያለው ጠቃሽ ግምት ውስጥ እስካልገባ ድረስ።
2. ሌሎች የሚያምኑት የኢሳ. 11፡2 ጠቃሽ እንደሆነ ነው፣ ከሴፕቱዋጂንት፣ ሰባትዮሾቹ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የተጠቀሱበት። ሆኖም፣ ከማሶረቲክ ጽሑፍ (የዕብራይስጥ) ስድስት ስጦታዎች ብቻ ናቸው የተጠቀሱት።
3. ከአይሁድ በይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዳራ የሆኑት እነዚህን የሚገልጿቸው ስለ መላእክት መገኘት ነው፣ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ካሉት ሰባቱ ሊቃነ-መላእክት (ዝከ. 8፡2)።
4. ሌሎች የሚያዛምዷቸው ከመላእክት ወይም መልእክተኞች ጋር ነው፣ ከሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት፣ እነርሱም 1፡20 ላይ የተጠቀሱት።

**1፡5 "ከኢየሱስ ክርስቶስም፣ ከታመነው ምስክር"** ይህ ከሦስቱ ሐረጎች የመጀመሪያው ነው፣ ኢየሱስ መሲሑን የሚገልጽ። እነዚህ የመክፈቻ ቁጥሮች ከ20፡6-21 ጋር ትይዩ ናቸው። "የታመነ" የብኪ ፍቺ አለው፣ ለሚታመን፣ ለእውነተኛ፣ እና ለሚጠጉበት (ኢሳ. 55፡ 3-5)። የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) እንደሚታመን፣ እንዲሁ ደግሞ የመዳረሻ ራዕዩ፣ ሕያው ቃሉ፣ ኢየሱስ (ዝከ. 3፡14)። ወንጌል እንዲታመን የሆነ መልእክት ነው፣ ሰው እንዲቀበለው፣ ያ ሰው ሊኖረው የሚገባ ሕይወት።

የግሪኩ ሐረግ፣ "የታመነ ምስክር፣" ሊሆን የሚችለው

1. "የእኔ ምስክር፣ የእኔ የታመነ፣" — እንደ ሁለት ሐረጎች፣ 2፡13ን ተመልከት (ከሐረጋዊ ተውላጠ ስም ተጨማሪ ጋር)
2. "የታመነና እውነተኛ ምስክር፣" 3፡14ን ተመልከት ("እና እውነተኛ" ከሚለው ተጨማሪ ጋር)

▣ **"ከሙታንም በኩራት"**

## ልዩ ርዕስ፡ በኩር

ይህ ቃል "በኩር"(*prōtotokos*) በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ላይ የዋለው በበርካታ የተለያዩ መልኮች ነው።

1. የእሱ የብኪ ዳራ የሚያመለክተው ቀዳሚ የሆነ የበኩር ልጅ በቤተሰቡ ሲኖር ነው (መዝ. 89፡27፤ ሉቃስ 2፡7፤ ሮሜ. 8፡29፤ ዕብ. 11፡28)
2. የእሱ የቆላ. 1፡15 አጠቃቀም የሚናገረው ኢየሱስን እንደ ፍጥረት በኩር ነው፣ ይሄውም የብኪ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል ምሳ. 8፡22-31፣ ወይም የእግዚአብሔር የፍጥረት ወኪል (ዮሐንስ 1፡3፤ 1ቆሮ. 8፡6፤ ቆሮ. 1፡15-16፤ ዕብ. 1፡2)
3. የእሱ አጠቃቀም በቆላ. 1፡18፤ 1ቆሮ. 15፡20 ላይ (እና እዚህ) የሚያመለክተው ኢየሱስ ከሙታን በኩር እንደሆነ ነው
4. እሱም የብኪ መጠሪያ ነው ለኢየሱስ (መዝ. 89፡27፤ ዕብ. 1፡6፤ 12፡23)። እሱም በርካታ የኢየሱስን ገጽታዎች ደባልቆ የያዘ ነው፣ ቀዳሚነቱንና ማዕከላዊነቱን። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ቁ. 3 ወይም ቁ. 4 የተሻለ ይስማማል።

▣ **"የምድር ነገሥታት ገዥ"** ይህ ሐረግ፣ እንደ ቀዳሚው ሁሉ፣ የመዝ. 89፡27 ጠቃሽ ነው (መዝ. 72፡11፤ ኢሳ. 48፡23)፣ እሱም ስለ ኢየሱስ የሚናገር፣ እንደ ተስፋው መሲሕ። እሱ ደግሞ የዮሐንስን ምላሽ ያንጸባርቃል

1. ለአጼ አምልኮ የሮሜ ግዛት ምስራቃዊ አውራጃ
2. የንጉሣዊ የሜሶፖታሚያ ሐረግ አጠቃቀም "የነገሥታት ንጉሥ" (ራዕ. 11፡15፤ 17፡14፤ 19፡16)

▣ **"ለወደደን"** ይህ የአሁን የድርጊት አንቀጽ፣ ፍችው "ኢየሱስ እንደወደደን ይቀጥላል።" ይህ ማጽኛ እጅግ ጠቃሚ ነው ከሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት መካከል ለአምስቱ ድካምና ውድቀት አኳያ (ምዕራፍ 2-3)።

▣ **"ከኃጢአታችንም የፈታን"** ይህ ያለፈ ድርጊት አንቀጽ ነው። የቫልጌትና የኮፕቲክ ቅጅዎች፣ እንዲሁም አንዳንድ በአነስተኛ ፊደላት የተጻፉ የግሪክ እጅ ጽሑፎች፣ እና ኪንግ ጀምስ ቅጂ "ያጠበን" የሚል ቃል አላቸው (*louō*) እሱም "መፈታት" (*luō*) በሚል በትክክል የሚነበብ። የጥንት ጸሐፍት የአኪን ጽሑፎች የሚያዘጋጁት፣ አንድ ሰው ጮኽ ብሎ ሲያነብ ሌሎች እየጻፉ ነው።

"መፈታት" የሚለው ቃል (በተጨማሪነት) በጥንታዊ የግሪክ ጽሑፎች ይገኛል ፒ[18]፣ ℵ* (ከመስተጻምር ጋር)፣ ℵ[2]፣ ሀ፣ እና ሐ፣ "መታጠብ" ደግሞ በባለ ከብ ትልቅ ፊደላት ኋላ ላይ በእጅ ጽሑፍ ይገኛል፣ ፒ (ስድስተኛ ክፍለ-ዘመን) እና 046፣ እንዲሁም በሌሎች ኋለኛ አናሳ ጽሑፎች (ቅጥልጣይ የግሪክ ጽሑፎች) የእጅ ጽሑፎች። እናም፣ "መፈታት" ወይም "ነጻ መውጣት" ተመራጭ ምንባብ ነው። ዩቢኤስ[4] ለ "መፈታት" "ትክክለኛ" ደረጃ ይሰጣል። ዕዝል ሁለት ተመልከት፡ ጽሑፋዊ ትንተና።

▣ ***"በደሙ"*** ይህ የተለመደው ጠቃሽ ነው ለመሥዋዕትነት (ሌዋውያን 1-7)፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ተለዋጭ የኃጢአት ማስተሠረያ (ዝክ. 5:9፤ 7:14፤ 12:11፤ ማርቆስ 10:45፤ II ቆሮ 5:21፤ ኢሳ. 52:13-53:12)። "በደሙ" የወቅቱ የወንጌል እውነት ነው (ሮሜ. 3:25፤ ኤፌ. 1:7፤ 2:13፤ ቆላ. 1:20፤ I ጴጥ. 1:18-19። እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር፣ የእሱ ፍርድና ምሕረት ለወደቁት ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ ተለዋጭ ሞት ላይ ይገኛል (ዕብ. 9:11-28)።

## ልዩ ርዕስ፡ የጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ኬሪግማ (ስብከተ ወንጌል)

*ሀ.* በአዲስ ኪዳን የተሰጠው የእግዚአብሔር ተስፋ በአየሱስ መሲሑ መምጣት ሳቢያ ተፈጽሟል። (ሐዋ. 2፡30፤ 3፡19፣24፤ 10፡ 43፤ 26፡6-7፣22፤ ሮሜ. 1፡2-4፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ ዕብ. 1፡1-2፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡10-12፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡18-19)።

ለ. ኢየሱስ እንደ መሲሕ በእግዚአብሔር የተቀባው በጥምቀቱ ነው (ሐዋ. 10፡38)

ሐ. ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው በገሊላ ከጥምቀቱ በኋላ ነው (ሐዋ. 10፡37)።

*መ.* የአገልግሎቱም ባሕርይ መልካምን በማድረግና ታላላቅ ሥራዎችን (ተአምራትን) በመከወን ሲሆን ይህም በእግዚአብሔር ኃይል ነው (ማርቆስ 10፡45፤ ሐዋ. 2፡22፤ 10፡38)።

*ሠ.* መሲሑ የተሰቀለው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ መሠረት ነው (ማርቆስ 10፡45፤ ዮሐንስ 3፡16፤ ሐዋ. 2፡23፤ 3፡13-15፣ 18፤ 4፡11፤ 10፡39፤ 26፡23፤ ሮሜ. 8፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡17-18፤ 15፡3፤ ገላ. 1፡4፤ ዕብ. 1፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፣19፤ 3፡18፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡10)።

ሸ. እሱም ከሞት ተነሥቶ ለሐዋርያት የተከሰተላቸው (ሐዋ. 2፡24፣31-32፤ 3፡15፣26፤ 10፡40-41፤ 17፡31፤ 26፡23፤ ሮሜ. 8፡34፤ 10፡9፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡4-7፣12፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፤ 3፡18፣21)።

*ቀ.* ኢየሱስ በእግዚአብሔር ከፍ ብሎ "ጌታ" የሚል ስያሜ ተሰጠው (ሐዋ. 2፡25-29፣33-36፤ 3፡13፤ 10፡36፤ ሮሜ. 8፡34፤ 10፡ 9፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16፤ ዕብ. 1፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡22)።

በ. አዲሱን የእግዚአብሔርን ማኅበረሰብ ለመፍጠር መንፈስ ቅዱስን ሰጠ (ሐዋ. 1፡8፤ 2፡14-18፣38-39፤ 10፡44-47፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡ 12)።

*ተ.* እሱም ዳግመኛ ተመልሶ ይመጣል፣ ለፍርድና ሁሉንም ነገር ለመመለስ (ሐዋ. 3፡20-21፤ 10፡42፤ 17፡31፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡20-28፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10)።

ቸ. መልዕክቱን የሚሰሙት ሁሉ ንስሐ ሊገቡና ሊጠመቁ ይገባል (ሐዋ. 2፡21፣38፤ 3፡19፤ 10፡43፣47-48፤ 17፡30፤ 26፡20፤ ሮሜ. 1፡17፤ 10፡9፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡21)።

ዘዴው የሚያገለግለው የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዋነኛ አዋጆች በተለያዩ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የተዉልንን ድርሻ ወይም አጽንዖት የሚሰጠውን በተለየ መልኩ በስብከታቸው ላይ ያለውን ነው። ሙሉው የማርቆስ ወንጌል በቅርበት የሚከተለው ስብከተ ወንጌል ጴጥሮሳዊ ገጽታ ነው። ማርቆስ ከባህል አኳያ የሚታየው የጴጥሮስን ስብከቶች በማዋቀር ነው፣ በሮም የተሰበከውን፣ ወደ ተጻፈ ወንጌል በመቀየር። ሁለቱም ማቴዎስና ሉቃስ የማርቆስን መሠረታዊ መዋቅር ተከትለዋል።

**1፡6 "እንድንሆን አደረገ"** ይህ የድርጊት የአሁን አመላካች ነው። ኢየሱስ ከኃጢአታችን እንድንፈታ እንዳደረገ (ቁ. 5)፣ እሱው የካህናት መንግሥት አደረገን፣ እሱን እንድንወክል!

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"መንግሥት፣ ካህናት ለአምላኩ"*** |
| **አኪጀት** | ***"ነገሥታትና ካህናት ለአምላኩ"*** |
| **አየተመት** | ***"መንግሥት፣ ካህናት አምላኩን ለማገልገል"*** |
| **አእት፣ አኢመቅ** | ***"የካህናት መንግሥት አምላኩን ለማገልገል"*** |

ይህ የብኪ ቃል ነው ለእስራኤል ጥቅም ላይ የዋለ ዘጸ. 19፡6 እና ኢሳ. 61፡6 ላይ፣ ሕዝቡ የካህናት መንግሥት እንዲሆን ታስቦ የነበረው። እግዚአብሔር አብርሃምን መረጠ እስራኤልን ለመምረጥ የጠፋውን ዓለም ለመምረጥ (ዘፍ. 3:15፤ 12:3)። እስራኤል ማለት ምስክር የሆነ ሕዝብ ነበር (ማለትም፣ ካህናት) እነሱ ግን ይህን የተሾሙበትን የወንጌላዊነት ተግባር መፈጸም አልቻሉም (ሕዝ. 36፡ 22-38)። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ቤተ-ክርስቲያንን መረጠ፣ ዓለምን እንድታስተምር (ማቴ. 28:19-20፤ ሉቃስ 24:47፤ ሐዋ. 1:8)። ለእስራኤል ጥቅም ላይ የዋሉት ሁነኛ ሐረጎች አሁን ለቤተ-ክርስቲያን ጥቅም ላይ ውለዋል (ገላ. 3:29፤ 6:16፤ ፊሊ. 3:3፤ I ጴጥ. 2:5፣ 9፤ ራዕ. 1:6፤ 5:10፤ 20:6)።

የተጠቃለለው፣ የመጽሐፍ ቅዱስ "የአማኞች የክህነት አገልግሎት"ን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ምዕራባዊው ክርስትና ግለሰባዊውን ስፍራና ሚና በጣም ሲያገንነው መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የተጠቃለለነት አሳንሶታል። የአኪ ዘይቤ የሆነው የክርስቶስ ሥጋ (1 ቆሮንቶስ 12) ተመሳሳይ ዘይቤ ነው። የብኪ መጠሪያ ለአማኞች ግለሰባዊ ነጻነት ማስረገጫ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም። ይህ አጽንዖት እየጎለበተ የመጣው በማርቲን ሉተርና በካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን መካከል በተካሄደው ታሪካዊ ትግል ነው። የዚህ ይዘት ትኩረት ወንጌላዊነት ነው (ዝክ. ቁ. 7)፣ እያንዳንዱን አማኝ በማሳተፍ፣ እያንዳንዱን የጠፋ እና ችግረኛ ሰው፣ እሱም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውንና ክርስቶስ የሞተለትን ለመድረስ ሙከራ ነው (ዮሐንስ 3:16፤ I ጢሞ. 2:4፤ II ጴጥ. 3:9፤ I ዮሐንስ 2:2፤ 4:14)።

## ልዩ ርዕስ፡ ክርስትና የተጠቃለለ ነው

*ሀ. የጳውሎስና የጴጥሮስ ዘይቤዎች*

1. አካል
2. መስክ
3. ሕንጻ

ለ. "ቅዱስ" የሚለው ቃል ዘወትር የብዙ ነው (ከፊሊጵ. 4፡21 በቀር፣ እዛም ቢሆን አጠቃሎሽ ነው)
ሐ. የማርቲን ሉተር የተሐድሶ አጽንዖትም፣ "የአማኝ የክህነት ሥርዓት" እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። እሱ የአማኞች የክህነት ሥርዓት ነው (ዘጸ. 19፡6፤ 1ጴጥ. 2፡5፣9፤ ራዕ. 1፡6)።
መ. እያንዳንዱ አማኝ ለጋራ ጥቅም ተሰጥዖ አለው (1ቆሮ. 12፡7)
ሠ. በአንድነት ብቻ ነው የእግዚአብሔር ሕዝብ ውጤታማ የሚሆነው። አገልግሎት በአንድነት ነው (ኤፌ. 4፡11-12)።

▣ **"ለአምላኩና ለአባቱ"** ይህ ሐረግ ምናልባት የሚያሳየው የወልድን ፍጹም መለኮትነት ነው (ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ 22፡17 ላይ ተመልከት)፣ ግን እሱ በርግጥ የኢየሱስን መታዘዝ ማስረገጫ መንገድ ነው፣ ሥጋ በመልበሱ። ተመሳሳይ ሐረግ በጳውሎስም ጥቅም ላይ ውሏል ሮሜ 15፡6 ላይ። የእኩልነት ስሜት 3፡21፤ 14፡1 ላይ ሊታይ ይችላል።

▣ **"ለእርሱ ክብርና ኃይል ይሁን"** "ክብር" የሚለው ቃል የብኪ የንግድ ቃል ነው (ለግብይት ሚዛኖችን መጠቀም) ማለትም "መከበድ"፤ ከባድ የነበረ (ምሳ. ወርቅ) ዋጋ ነበረው። ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ለእግዚአብሔር ብሩኅነት፣ ግርማ፣ ቅድስና ነው፣ ከ*Shekinah* የክብር ደመና፣ ዘጸአት ላይ ያለው። ክብር ተዘውትሮ ለእግዚአብሔር አብ ይያያዝ ነበር በአኪ (ሮሜ. 11:36፤ 16:27፤ ኤፌ. 3:21፤ ፊሊ. 4:20፤ I ጢሞ. 1:17፤ II ጢሞ. 4:18፤ I ጴጥ. 4:11፤ 5:11፤ II ጴጥ. 3:18፤ ይሁዳ 25፤ ራዕ. 1:6፤ 5:13፤ 7:12)። ልዩ ርዕስ፡ ክብር 15፡8 ላይ ተመልከት።

"ኃይል" የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር አብ ነው የተባለው፣ ተመሳሳይ ሥነ-መለኮታዊ የወልድ መታዘዝ ነው (ዮሐንስ 17)። ኢየሱስ በሁሉም ነገር የአብ ወኪል ነው፣ ግቡ ግን የመጨረሻው የአብ ክብር ነው (1 ቆሮ. 15፡27-28)።

▣ **"ከዘላለም እስከ ዘላለም"** ይህ በጥሬው "ከዘመናት እስከ ዘመናት" ማለት ነው። ይህ *Paiōnos*፣ ድርብ አጠቃቀም፣ ነጠላና ብዙ፣ በራዕይ የተለመደ ነው (ዝከ. 1:18፤ 4:9፣10፤ 5:13፤ 7:12፤ 10:6፤ 11:15፤ 15:7፤ 19:3፤ 20:10፤ 22:5)። የጥንት ግሪክ ምስክሮች ሁለተኛውን መግደፋቸው ያስገርማል (ኤምኤስኤስ ፒ[18]፣ ኤ፣ ፒ)።

## ልዩ ርዕስ፡ ዘላለም (የግሪክ ፈሊጥ)

አንደኛው የክሪክ ፈሊጣዊ ሐረግ "ለዘመናት" ነው (ሉቃስ 1:33፤ ሮሜ. 1:25፤ 11:36፤ 16:27፤ ገላ. 1:5፤ I ጢሞ. 1:17)፣ እሱም የዕብራይስጡን *'olam* የሚያንጸባርቅ። ሮበርት ቢ. ጊርድልስቶን፣ *የብሉይ ኪዳን መመሳሰል*፣ ገጽ 319-321፣ እና የብኪ ልዩ ርዕስ፡ ዘላለም *('olam)* ተመልከት። ሌሎች ተመሳሳይ ሐረጎች "ለዘመናት" (ማቴ. 21:19 [ማርቆስ 11:14]፤ ሉቃስ 1:55፤ ዮሐንስ 6:58፤ 8:35፤ 12:34፤ 13:8፤ 14:16፤ II ቆሮ. 9:9) እና "ከዘመን ዘመናት" (cf. ኤፌ. 3:21)። ከግሪኩ ፈሊጥ "ዘላለም" ጋር ልዩነት ያለው አይመስልም። "ዘመናት" የሚለው ቃል የብዙ ሊሆን ይችላል በዘይቤአዊ መልኩ ራቢያዊ ሰዋሰዋዊ ምሥረታ "የክብሩ ብዛት" ወይም በርካታ "ዘመናትን" ሊያመለክት ይችላል በአይሁድ "የክፉው ዘመን" "የሚመጣው ዘመን፣" ወይም "የጽድቅ ዘመን።"

## ልዩ ርዕስ፡ ዘላለም (አላም)

የዕብራይስጡ ስርወ ቃል ‹ עוֹלָם አላም› ትርጉም የተረጋገጠ አይደለም፡፡ ቃሉ በተለያዩ አገባቦች በብዙ ቦታ እጥቅም ላይ ውሎአል (በርግጥ ትርጉሙ በአውድ ይወሰናል)፡፡ ከዚህ የሚከተሉት ጥቅሶ ለምሳሌነት የተመረጡ ናቸው፡፡

1. የጥንት ነገሮች
   ሀ. ሕዝቦች፣ ዘፍ.6÷4፤1ኛ ሳሙ.27÷8፤ ኤር.5÷15፤ 28÷8
   ለ. ቦታዎች፣ ኢሳ.58÷12፤61÷፡4
   ሐ. እግዚአብሔር፣ መዝ.93÷2፤ምሳሌ 8÷23፤ ኢሳ.63÷16
   መ. ነገሮች፣ ዘፍ.49÷26፤ኢዮ.22÷15፤መዝ.24÷፡7፣9፤ኢሳ.46÷9
   ሠ. ጊዜ፣ ዘዳ.32÷7፤ኢሳ.51÷9፤63÷9፣11
2. የወደፊት ጊዜ
   ሀ. የሰው ሕይወት፣ ዘፀ.21÷6፤ዘዳ.15÷17፤1ኛ ሳሙ.1÷22፤27÷12
   ለ. ለንጉስ የተደረገ ግነትን፣ 1ኛ ነገ.1÷31፤መዝ.61÷7፤ነህ.2÷3
   ሐ. ቀጣይ ሕልውና
      (1) መሬት፣ መዝ.78÷69፤104÷5፤መክ.1÷4
      (2) ሰማያት፣ መዝ.148÷6
   መ. የእግዚአብሔር ሕልውና

(1) ዘፍ.21÷33
(2) ዘፀ.15፡18
(3) ዘዳ. 32÷40
(4) መዝ. 93÷2
(5) ኢሳ.40÷28
(6) ኤር.10÷10
(7) ዳን.12÷7

ሠ. ቃል ኪዳን
(1) ዘፍ.9÷12፤16፤ 17÷7፤13፤19
(2) ዘፀ.31÷16
(3) ዘሌ.24÷8
(4) ዘሑ. 18÷19
(5) 2ኛ.ሳሙ.23÷5
(6) መዝ.105፡÷10
(7) ኢሳ.24፡÷5፤55÷3፤61÷8
(8) ኤር.32÷40፤50÷5

ረ. ከዳዊት ጋር ልዩ ቃል ኪዳን
(1) 2ኛ ሳሙ 7÷19፤16፤25፤29፤22÷51፤23÷5
(2) 1ኛ ነገ.2÷33፤45፤9፡
(3) 2ኛ ዜና 13÷5
(4) መዝ.18÷50፤89÷4፤28፤36፤37
(5) ኢሳ.9÷7፤16÷5፤37፡35፤55÷3

ሰ. የእግዚአብሔር መሲህ
(1) መዝ.45÷2፤72፡17፤89÷35-36፤110÷4
(2) ኢሳ.9፡6

ሸ. የእግዚአብሔር ሕግ
(1) ዘፀ.29÷28፤30÷21
(2) ዘሌ.6÷18፤22፤7÷34፤10÷15፤24÷9
(3) ዘሑ.18÷8፤11፤19
(4) መዝ.119÷89፤160
(5) ኢሳ.59÷21

ቀ. የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል
(1) 2ኛ ሳሙ.7÷13፤16፤25፤22÷51
(2) 1ኛ ነገ. 9÷5
(3) መዝ.18÷50
(4) ኢሳ.40÷8

በ. የአብራሃም ዘሮችና የቃል ኪዳኑ ምድር
(1) ዘፍ.13÷15፤17÷18፤48÷4
(2) ዘፀ.32÷13
(3) 1ኛ ዜና 16÷17

ተ. የቃል ኪዳኑ ግብዣ
(1) ዘፀ.12÷14፤17፤24
(2) ዘሌ.23÷14፤21፤41
(3) ዘሑ.10፡8

ቸ. ዘላለማዊ/ዘላለምነት የዘላለም
(1) 1ኛ ነገ.8÷13
(2) መዝ.61÷7-8፤77÷8፤90፡2፤103÷17፤145÷13

(3) ኢሳ.26÷4፤45÷17

(4) ዳን.9÷24

ኘ. አማኞች ለዘላለም ስለሚያደርጉት ነገር መዝሙር የሚለው

(1) ምስጋና ማቅረብ፣ 30÷12፤79÷13

(2) በሕልውናው ማደር 41÷12፤61÷4፣7

(3) በምህረቱ መታመን 52÷8

(4) እግዚአብሔርን ማመስገን፣ 52÷9

(5) ምስጋናን መዘመር፣ 61÷7፤89÷1

(6) የእርሱን ፍትህ ማወጅ፣ 75÷9

(7) ስሙን ማክበር፣ 86÷12፤145÷2

(8) ስሙን መባረክ፣ 145÷1

3. ያለፈና የሚመጣ ጊዜ (ከዘላለም እስከ ዘላለም)

ሀ. መዝ.41÷13 (ምስጋና ለእግዚአብሔር)

ለ. መዝ.90÷2 (እግዚአብሔር ራሱ)

ሐ. መዝ.103፡17 (የእግዚአብሔር ቸርነት)

የቃሉን ትርጉም ቃሉ ያለበት አውድ እንደሚወስን አትርሳ፡፡ ዘላለማዊ ቃል ኪዳኖችና የተስፋ ቃሎች በሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ናቸው (ኤር.7)፡፡ በዘመንህ ስለጊዜ ያለውን አስተሳሰብ ወይም የተቀናጀ የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት እንደፈሳሽ የሆነው ይህ ቃል እጥቅም ላይ በዋለበት በማንኛው የብሉይ ኪዳን ክፍል ስታነብ ጥንቃቄ አድርግ፡፡ አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃሎች ሁሉ ጥንቅር ነው፡፡

▣ **"አሜን"** ይህ የብኪ ዕብራይስጥ ቃል ነው ለ "እምነት" (ዕንባ. 2፡4)። የእሱ ዋነኛ ሥርወ-ቃል "መጽናት ወይም ርግጠኛ መሆን" ነበር። ሆኖም፣ ፍችው ወደ ሚረጋገጠው ተቀየረ (2 ቆሮ. 1፡20)። እሱም በዘይቤአዊነት ጥቅም ላይ የዋለው ታማኝ፣ የሚታመን፣ ጽኑ፣ የሚታመን ነው (የኢየሱስ መጠሪያ 3፡14፣ II ቆሮ. 1፡20)።

**ልዩ ርዕስ፡ አሜን**

1. ብሉይ ኪዳን

ሀ. "አሜን" የሚለው ቃል የመጣው ከዕብራይስጥ ቃል

1. "እውነት"" (*emeth*፣ BDB 49)
2. "እውነተኛ"(*emun*፣*emunah*፣ BDB 53)
3. "እምነተ" ወይም " የሚታመን"
4. "ታማኝ"(*dmn*፣ BDB 52)

ለ. የቃሉ ሥረወ ግንድ ምንጭ አካላዊ አለመዋዠቅ ነው፡፡ የዚህ ቃል ተቃራኒ የማይጸና፣ ተንሸራታች (ዘዳ 28፡64-67፤ 38፡16፤ መዝ 40፡2፤ 73፡18፤ ኤር 23፡12)፡፡ ከዚህ የቃሉ ቀጥተኛ ትረርጉም ምሳሌያዊ ትርጓሜው ተወስዷል ይኼውም ታማኝነት፣ የሚታመን፣ ሀቀኛ እና የመሳሰሉት ናቸው (ዘፍ 15፡16፣ እንባቆም 2፡4)

ሐ. ልዩ የቃሉ አጠቃቀም

1. አማድ 1 ነገስት 18፡16 (1 ጢሞ 3፡15)
2. ማረጋገጫ ዘጸ 17፡12
3. የማይናወጥ ዘጸ 17፡12
4. የተረጋጋ ኢሳ 33፡6፤ 34፡5-7
5. እውነት 1 ነገ 10፡6፤ 17፡24፤ 22፡16፤ ምሳ 12፡22
6. ጽናት 2 ዜና 20፡20፤ ኢሳ 7፡9
7. የሚታመን መዝ 119፡43፣ 142፣ 151፣ 168

መ. በ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚሰራ እምነት ለማመልከት ሌላ የዕብራይስጥ ቃል አገልግሎት ላይ ውሏል

1. *bathach* (BDB 105)፤ባታች፣ መታመን ማለት ነው
2. *yra* (BDB 431)፣ ያራ መፍራት፣ ማክበር፣ ማልከም ማለት ነው

ሠ. የዚህ ቃል ሥነ መለኮታዊ እሳቤ የሰው ልጆች ታማኝነት ሳይሆን የያሕዌ ታማኝነት ነው (ዘጸ 34፡6፣ ዘዳ 32፡4፤ መዝ 108፡ 4፤ 115፡1፤ 117፡2፤ 138፡2)፡፡ የወደቀው የሰው ልጅ ብቸኛ ተስፋ የያሕዌ ምህረት የሞላበት የቃል ኪዳን ታማኝነት እና የእርሱ የተስፋ ቃል ነው፡፡ ያሕዌን የሚያውቁት ሁሉ እንደ እርሱ ልሆኑ ይገባል (ዕባ 2፡4) መጽሐፍ ቅዱስ እግዘኢብሔር በሰው ልጆች ውስጥ መልኩን ለመመለስ የሚያደርገው ጥት ታርክ እና ዘገባ ነው (ዘፍ 1፡26-27)፡፡ ድነት የሰው ልጆችን ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቅ ግንኙነት የማድግ ብቃትን የሚመለስበት ነው፡፡ ለዚህም ነው እኛ የተፈጠርነው፡፡

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. "አሜን" የሚለው ቃል የተለያዩ ሀይማታዊ አዎንታዎች ትክክለኝነታቸውን ለማረጋገጥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ (1ቆሮ 14፡16፤ 2ቆሮ 1፡20፤ ራዕ 1፡7፤ 5፡14፤ 7፡12)

ለ. ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከጸሎቶች ጋር ተያይዞ ይገኛል (ሮሜ 1፡25፤ 9፡5፤ 11፡36፤ 16፡27፤ ገላ 1፡5፤ 6፡18፤ ኤፌ 321፤ ፊል 4፡20፤ 2 ተሰ 3፡18፤ 1ጢሞ 1፡17፤ 6ለ16፤ 2ጢሞ 4፡18)፡፡

ሐ. ይህንን ቃል በጣም ጠቃሚ አረፍተ ነገርን ለመጀመር የተጠቀመበት ኢየሱስ ብቻ ነው (ይህም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተከታታይ ሆኖ ተገልጸዋል) (ሉቃ 4፡24፤ 12፡37፤ 18፡17፤ 29፤ 21፡32፤ 23፡43)

መ. በራዕ 3፡14 ላይ የኢየሱስ ማዕረግ ሆኗል (ምናልባትም ከኢሳ 65፡16 የያሕዌ ማዕረግ ሊሆን ይችላል)፡፡

ሠ. የታማኝነት ወይም የእምነት፤ የመታን የሚሉ ቃላት የግሪክ ቃል የሆነው ፒስቶ ወይም ፒስቲስ የሚያመለክቱ ሲሆን ወደ አማርኛ ስተረጎሙ "መታመን"፣ "እምት" ወይም" ማመን" ማለት ነው፡፡

**1፡7 "እነሆ፣ ከደመና ጋር ይመጣል"** ይህ ሐረግ በመልአክ የተደረገ መግለጫ ይሆናል ቁ. 1። እሱም የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የተለመደው የሆነ ማጣቀሻ ነው።

## ልዩ ርዕስ፡ ከደመና ጋር ይመጣል

ይህ ሐረግ የተለመደው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መጥቀሻ ነው። ይህ ከደመና ጋር መምጣት እጅግ ጠቃሚ የፍጻሜ ዘመን ምልክት ነው። እሱም በሦስት የተለየዩ መንገዶች በብኪ ተገልጧል።

1. የእግዚአብሔርን አካላዊ መገኘት ለማሳየት፣ *Shekinah* የክብር ደመና (ዘጸ. 13:21፤ 16:10፤ ዘኍ. 11:25)
2. ክብሩን ለመሸፈን፣ ሰው አይቶት እንዳይሞት (ዘጸ. 33:20፤ ኢሳ. 6:5)
3. መለኮትን ለማጓጓዝ (ኢሳ. 19:1፤ እንዲሁም መዝ. 18:7-15)

ዳንኤል 7፡13 ላይ ደመናት ሰው የሆነውን መለኮታዊ መሲሕ ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህ የዳንኤል ትንቢት ከ30 ጊዜ በላይ በአኪ ተጠቅሷል። ይኸው ተመሳሳይ የመሲሑና የሰማይ ደመና ግንኙነት ማቴ. 24:30፤ 26:64 ማርቆስ 13:26፤ ሉቃስ 21:27፤ 14:62፤ ሐዋ 1:9፣11 እና 1 ተሰ. 4:17።

▣ **"ዓይንም ሁሉ ያየዋል"** ይህ የሚያመለክተው ሥጋዊ፣ አካላዊ፣ የሚታይ፣ ሁሉን አቀፍ የክርስቶስን ምጽአት ነው፣ ምሥጢራዊ የአማኞችን መነጠቅ ሳይሆን። እንደ እኔ አስተያየት መጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢራዊ መነጠቅን ወይም ምጽአትን ፈጽሞ አይሰብክም። በወንጌላት ያሉት እነዚያ ቁጥሮች (ማቴ. 24:37-44፤ ሉቃስ 17:22-37) ዘወትር ምሥጢራዊውን መነጠቅ ለመደገፍ ጥቅም ላይ የሚውሉት፣ ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ የሚዛመዱት ከኖህ ዘመን ጋር ለማወዳደር ነው። እነዚህ ጽሑፎች የሚገልጹት ያልተጠበቀ ድንገተኛ ምጽአቱን ነው። በኖህ ዘመን በአንድ ጊዜ ተደምስሰዋል! የጽሑፍ አቃቂር ከማውጣት ተጠበቁ፣ አነስተኛ ምንባቦችን ከተመስጧዊው ዋነኛ የቃሉ መቼት በመውሰድ የራሳችሁን ቅድመ-ግምታዊ ሥነ-መለኮታዊ የፍጻሜ ዘመን ሥርዓት ከማድረግ!

▣ **"የወጉትም ሁሉ፣ የምድር ነገዶች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ"** ይህ የዘካ. 12:10፣12 (ዮሐንስ 19:37) ጠቃሽ ነው። ይህ መልካም ምሳሌ ነው፣ ዮሐንስ የብኪን ጽሑፎች እንዴት ዳግም እንደተጠቀመባቸው፣ ከሮሜ ሁኔታው ጋር (የአይሁድ ዓይነቱ ዳግም ትርጓሜ *pesher* ይባላል)። የዘካርያስ ጽሑፍ ለዮሐንስ አዲስ አጠቃቀም መፈናጠሪያ ሆኗል። ዘካርያስ ላይ ጽሑፉ የሚያመለክተው ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ነው፣ ስለ "ተወጋው" የሚያዝኑ፣ በማሶረቲክ የዕብራይስጥ ጽሑፍ ወደ "የምድር ነገዶች ሁሉ" በሚል ተቀይሯል (ማቴ. 24:30፤ ይህ ሐረግ ከሴፕቱዋጂንት አይደለም)። ደግሞም፣ "ዋይታ" በዘካርያስ ምንባብ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ ዘወትር የሚተረጎመው ከሮሜ 11 ጋር ተያይዞ ነው፣ አይሁድ ንስሐ ገብተው ኢየሱስን እንደ መሲሕ ሲያምኑ። ሆኖም፣ ራዕ. 1:7 ላይ ዋይታው ንስሐ ስለመግባት አይደለም፣ ግን የእግዚአብሔር ፍርድ በማያምኑት በሁሉም ነገዶች ላይ በመሆኑ ነው (ማቴ. 24:30)። የዘካርያስ ዐውደ-ጽሑፍ የሚጠቅሰው በሕዝቦች ላይ ለሚሆነው የፍጻሜ ዘመን ፍርድ ነው፣ "የሜጊዶን ሜዳ" በመጥቀስ፣ በዕብራይስጥ አርማጌዶን ይባላል (ዘካ. 12:11፤ II ዜና. 35:22 እና መዝሙር 2፤ ራዕ. 16:16)፣ የፍጻሜው የጦርነት ስፍራ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል እና በሰይጣንና በሕዝቡ መካከል፣ የማያምኑ ሕዝቦች።

## ልዩ ርዕስ፡ የኀዘን ሥነ-ሥርዓት

እስራኤላውያን ለተወዳጅ ሙቶቻቸው እና ለግላዊ ንስሐ፣ ብሎም ለጋራ በደሎች ኀዘንን የሚገልጹት በበርካታ መንገዶች ነው፡

1. ልብስን መቅደድ፣ ዘፍ. 37:29፣34፤ 44:13፤ መሳ. 11:35፤ II ሳሙ. 1:11፤ 3:31፤ I ነገሥ. 21:27፤ ኢዮብ 1:20
2. ማቅ መልበስ፣ ዘፍ. 37:34፤ II ሳሙ. 3:31፤ I ነገሥ. 21:27፤ ኤር. 48:37
3. ጫማን ማውለቅ፣ 2ኛ ሳሙ. 15:30፤ ኢሳ. 20:3
4. እጅን ራስ ላይ ማድረግ፣ 2ኛ ሳሙ. 13:19፤ ኤር. 2:37
5. በራስ ላይ አቧራ መነስነስ፣ ኢያ. 7:6፤ I ሳሙ. 4:12፤ ነህ. 9:1
6. መሬት ላይ መቀመጥ፣ ሰቆ. 2:10፤ ሕዝ. 26:16 (መሬት ላይ መጋደም፣ II ሳሙ. 12:16)፤ ኢሳ. 47:1
7. ደረትን መድቃት፣ I ሳሙ. 25:1፤ II ሳሙ. 11:26፤ ናሆ. 2:7 (የ"ኀዘን" ሥርወ-ፍቺ፣ " ቢዲቢ 704)
8. ገላን መቁረጥ፣ ዘዳ. 14:1፤ ኤር. 16:6፤ 48:37

9. ጾም፣ II ሳሙ. 1:12፤ 12:21-23፤ I ነገሥ. 21:27፤ I ዜና. 10:12፤ ነህ. 1:4
10. የኀዘን እንጉርጉሮ፣ II ሳሙ. 1:17፤ 3:31፤ II ዜና. 35:25
11. ፀጉርን መላጨት (ፀጉርን መንጨት ወይም መላጨት)፣ ኤር. 48:37
12. ፂምን ባጭሩ መቁረጥ፣ ኤር. 48:37
13. ራስን ወይም ፊትን መሸፈን፣ II ሳሙ. 15:30፤ 19:4

▣ **"ይሆናል። አሜን።"** ይህ የግሪክ ቃል ነው፣ ለማጽናት (*nai*) እና የዕብራይስጥ ቃል ለማጽናት (*amen*) ለአጽንዖት ጎን በጎን የተቀመጠ (ዝኪ. 22፡20)።

**ራዕይ፡ 1፡8**

**[8]ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ። አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል።**

**1፡8** ያህዌ ራሱ ይህን ቁጥር ተናግሯል፣ ስለ ኢየሱስ የተነገሩት ቀዳሚዎቹ አባባሎች ትክክል መሆናቸውን ለማጽናት። አራት መጠሪያዎችን ለእሱ ደባልቋል፣ ከሌላ አንድ ጠቃሽ ጋር ለአምስተኛ እንዲያውም ለስድስተኛ። ባጠቃላይ፣ ቁ. 8 እግዚአብሔር የጨመረው የራሱ ግላዊ ማረጋገጫ ነው፣ ለቀዳሚው መግለጫ፣ በእነዚህ አስደናቂ ስሞች ስለ መጠቀም።

1. "ያለና የሚኖር" እርሱም ለኪዳን ስም ለያህዌ ጠቃሽ ነው (ዘጸ. 3፡14)፣ "የመሆን ግሥ" ዓይነት። ኢየሱስ ይሄንን ስለ ራሱ ተጠቅሟል (ዮሐንስ 8፡56-59)። "ጌታ" የሚለው መጠሪያ (*kurios*) በአኪ የሚያንጸባርቀው ይህን የብኪ መጠሪያ ነው።
2. "አልፋ እና ኦሜጋ" የመጀመሪያውና የመጨረሻው የግሪክ ፊደላት ሲሆኑ እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ፣ ታሪክንም የሚቆጣጠር መሆኑን አመላካች ናቸው (ኢሳ. 44፡6፤ ራዕ. 21፡6)፤ ይኸው መጠሪያ ደግሞ ለኢየሱስ ጥቅም ላይ ውሏል ራዕ. 1፡17 እና 22፡13።
3. "ጌታ" ያህዌን ለመተርጎም ዘመናዊ ዘዴ ነው (ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት)።
4. "እግዚአብሔር" ዘፍ. 2፡4 ላይ፣ ያህዌ፣ እና *Elohim* ተደባልቀዋል (ጌታ እግዚአብሔር) እንደ መለኮት ስም። *El* ለአምላክ አጠቃላይ ስም ነው፣ በቅርብ ምስራቅ፣ "ጠንካራ መሆን" ከሚለው ሥር።
5. "ያለው፣ የነበረው፣ የሚመጣውም" ቀደም ብሎ ቁ. 4 ባለው ሐረግ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እሱም ለማይለወጠው፣ ዘላለም ኗሪ አምላክ (መዝ. 102፡27፤ ሚል. 3፡6፤ ያዕቆብ1፡17)። ይህ ሐረግ ለእግዚአብሔር አብ፣ ያህዌ ጥቅም ላይ ውሏል ቁ. 4 እና 8 እና ለኢየሱስ፣ ለእግዚአብሔር ወልድ፣ቁ. 17፡18 እና 22፡13 (ዕብ. 13፡8) ላይ።
6. "ኃያል" እሱም የብኪ ቃል ነው፣ (1) "*El-Shaddai*፣" ለእግዚአብሔር አባታዊ ስም (ዘጸ. 6፡3) ወይም (2) "ያህዌ *Sabaoth*፣" ከ LXX "ጌታ ኃያል አምላክ"። እሱም በዚህ መጽሐፍ ተዘውትሮ ይገኛል (ማለትም፣ *pantokratōr*፣ ዝኪ. 4፡8፤ 11፡17፤ 15፡3፤ 16፡7፣14፤ 19፡6፣11፤ 21፡22)፣ ግን አንድ ጊዜ ብቻ በሌሎቹ የአኪ መጻሕፍት (ማለትም፣ II ቆሮ. 6፡18)።

አንድ የጥንት የግሪክ ጽሑፍ፣ አሌፍ (א*)፣ እና በርካታ ሌሎች ኋለኛ ጽሑፎች "መጀመሪያና መጨረሻ" የሚል ሐረግ ጨምረዋል፣ ከ "አልፋና ኦሜጋ" ኋላ። ጸሐፍት እሱን ያስገቡት ከ21፡6 ነው፣ ግን ምናልባት እሱ ከዋነኛው ክፍል ላይሆን ይችላል፣ ከተመስጧዊው ዋነኛ የግሪክ ጽሑፍ። ዩቢኤስ[4] የእሱን አለመካተት "ትክክል" አድርጎታል።

## ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች

ሀ. ኢል ቢዲቢ 42፣ ኬቢ 48)

1. ዋነኛው የዚህ ጥንታዊ ቃል ዘውጋዊ ትርጉም ለመለኮት ርግጠኝነት የለውም፣ ምንም እንኳ በርካታ ሊቃውንት ከአካድያን ሥርወቃል የመጣ ነው ብለው ቢያምኑም፣ እሱም "ጠንካራ መሆን" ወይም "ኃይለኛ መሆን" የተገኘ ነው ቢሉም (ዘፍጥረት 17፡1፤ ዘኍ. 23፡19፤ ዘዳ. 7፡21፤ መዝ. 50፡1)።
2. በከነዓናውያን አፈ ታሪክ ታላቁ አማልክት ኢል ነው (ራስ ሻምራ ጽሑፎች)
3. በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ኢል ዘወትር ከሌሎች ቃላት ጋር አይደባለቅም። እነዚህ መደባለቆች የእግዚአብሔርን ባሕርይ መግለጫ መንገድ ሆነዋል።
   - ሀ. ኤል-ኢልዮን (እግዚአብሔር ቃላቁ ልዑል፣ ቢዲቢ 42 እና 751 II)፣ ዘፍ. 14፡18-22፤ ዘዳ. 32፡8፤ ኢሳ. 14፡14
   - ለ. ኤል- ሮይ ("የሚያይ አምላክ" ወይም "ራሱን የሚገልጽ አምላክ፣" ቢዲቢ 42 እና 909)፣ ዘፍ. 16፡13
   - ሐ. ኤል -ሻዳይ ("ሁሉን ቻይ አምላክ" ወይም "ፈጽሞ የሚራራ አምላክ" ወይም "የተራራው አምላክ፣" ቢዲቢ 42 እና 994)፣ ዘፍ. 17፡1፤ 35፡11፤ 43፡14፤ 49፡25፤ ዘጸ. 6፡3
   - መ. ኤል-አላም (ዘላለማዊው አምላክ፣ ቢዲቢ 42 761)፣ ዘፍ. 21፡33። ይህ ቃል ከሥነ መለኮት አኳያ የሚያያዘው እግዚአብሔር ለዳዊት ከሰጠው ተስፋ ጋር ነው፣ 2ኛ ሳሙ. 7፡13፣16
   - ሠ. ኤል -ቤሪት ("የቃል ኪዳን አምላክ፣"ቢዲቢ 42 እና 136)፣ መሳ. 9፡46

4. ኤል የሚያያዘው ከ
   ሀ. ያህዌ መዝ. 85፡8፤ ኢሳ. 42፡5
   ለ. ኤሎሂም ዘፍ. 46፡3፤ ኢዮብ 5፡8፣ "እኔ ኤል ነኝ፣ የአባቶቻችሁ ኤሎሂም
   ሐ. ሻዳይ ዘፍ. 49፡25
   መ. "ቀናተኛ" ዘጸ. 34፡14፤ ዘዳ. 4፡24፤ 5፡9፤ 6፡15
   ሠ. "መሐሪ" ዘዳ. 4፡31፤ ነህ.9፡31፤ "ታማኝ" ዘዳ. 7፡9፤ 32፡4
   ረ. "ታላቅና የሚያስፈራ" ዘዳ. 7፡21፤ 10፡17፤ ነህ. 1፡5፤ 9፡32፤ ዳን. 9፡4
   ሰ. "አዋቂ" 1ኛ ሳሚ. 2፡3
   ሸ. "ጠንካራ መጠጊያዬ" 2ኛ ሳሙ. 22፡33
   ቀ. "ተበቃዬ" 2ኛ ሳሙ. 22፡48
   በ. "ቅዱሱ" ኢሳ. 5፡16
   ተ. "ኃያሉ" ኢሳ. 10፡21
   ቸ. "አዳኙ" ኢሳ. 12፡2
   ኀ. "ታላቅና ኃይለኛ" ኤር. 32፡18
   ነ. "ፈራጅ" ኤር. 51፡56
5. የዋናዎቹ ብሉይ ኪዳን ሁሉም የእግዚአብሔር ስሞች ድብልቅ፣ በኢያሱ 22፡22 የሚገኙት (ኤል፣ ኤሎሂም፣ ያህዌህ፣ የተደገመ)

ለ. ኢሊዮን
1. የእሱ መሠረታዊ ፍች "ልዑል፣" "ከፍ ያለ፣" ወይም "ከፍ ያለ" (ዘፍ. 40:17፤ I ነገሥ. 9:8፤ II ነገሥ. 18:17፤ ነህ፣ 3:25፤ ኤር፣ 20:2፤ 36:10፤ መዝ. 18:13)።
2. እሱም ከሌሎች በርካታ ስሞች ጋር በአቻዊ አገባብ ጥቅም ላይ ውሏል/ለእግዚአብሔር ስም።
   ሀ. *ኤሎሂም* - መዝ. 47:1-2፤ 73:11፤ 107:11
   ለ. *ያህዌህ* - ዘፍ. 14:22፤ II ሳሙ. 22:14
   ሐ. *ኤል-ሻዳይ* - መዝ. 91:1፣9
   መ. *ኤል* - ዘኊ. 24:16
   ሠ. *ኢላህ* - ዘወትር ጥቅም ላይ የዋለው ዳንኤል 2-6 እና እዝራ 4-7፣ ከኢላር ጋር በመቀናጀት (በአራምኛ "ልዑል አምላክ") ዳን. 3:26፤ 4:2፤ 5:18፣21
3. እሱም ዘወትር እስራኤል ባልሆኑት ጥቅም ላይ ይውላል
   ሀ. መልከጼዴቅ፣ ዘፍ. 14:18-22
   ለ. በለዓም፣ ዘኊ. 24:16
   ሐ. ሙሴ፣ በዘዳ. 32:8 ስለ ሕዝቦች የተናገረው።
   መ. የሉቃስ ወንጌል በአዲስ ኪዳን፣ ለአሕዛብ የተጻፈው፣ የግሪኩን አቻ ሁፕሲስቶስን ይጠቀማል (ዝከ. 1:32፣35፣ 76፤ 6:35፤ 8:28፤ ሐዋ.7:48፤ 16:17)

ሐ. ኤሎሂም (ብዙ)፣ ኤሎሀ (ነጠላ)፣ በቅድሚያ ጥቅም ላይ የዋለው በቅኔ ነው (ቢዲቢ 43፣ ኬቢ 52
1. ይህ ቃል ከብሉይ ኪዳን ውጭ አይገኝም።
2. ይህ ቃል የሚያመለክተው የእስራኤል አምላክ ወይም የሕዝቦችን አማልክት ነው (ዘጸ. 12፡12፤ 20፡3)። የአብርሃም ቤተሰቦች ብዙ አማልክት አምላኪዎች ነበሩ (ኢያሱ 24፡2)።
3. እሱም ለሰው ፈራጆችም ይጠቀሳል ( ዘጸ. 21:6፤ መዝ. 82:6)
4. ኤሎሂም የሚለው ቃል ለሌሎች መንፈሳዊ ሕላዌዎችም ጥቅም ላይ ይውላል (መላእክት፣ አጋንንት) እንደ ዘዳ. 32:8 (LXX)፤ መዝ. 8:5፤ ኢዮብ 1:6፤ 38:7።
5. በመጽሐፍ ቅዱስ እሱ የመጀመሪያ ማዕርግ/የመለኮት ስም ነው (ዘፍ. 1፡1)። እሱ እስከ ዘፍ. 2፡4 ድረስ በአጠቃሎሽ አይቀርብም፣ ከዚያም ከያህዌ ጋር ይደባለቃል። እሱ በመሠረቱ (በሥነ መለኮት) ለእግዚአብሔር የሚያመለክተው እንደ ፈጣሪ፣ ደጋፊ፣ እና ሰጪ ነው፣ በዚህ ምድር ላይ ላለ ሕይወት (መዝ. 104)።
   እሱም ተመሳሳይ ነው፣ ከኢል ጋር (ዘዳ. 32:15-19)። እሱም ደግሞ ከያህዌህ ጋር ትይዩ ነው፣ እንደ መዝ.

14 (ኤሎሂም)፣ በትክክል መዝ. 53ን ይመስላል (ያህዌህ)፣ መለኮታዊ ስሞቹ ከመቀየራቸው በቀር።

6. ምንም እንኳ የብዙ ቁጥር ቢሆንና ለሌሎች አማልክት ጥቅም ላይ ቢውልም፣ ይህ ቃል ዘወትር የሚገልጸው የእስራኤልን አምላክ ነው፤ ግን ዘወትር ነጠላ ግሥ ይይዛል፣ አሀዳዊ አጠቃቀምን ለማሳየት።
7. ይህ ቃል የሚገኘው እስራኤላዊ ካልሆኑ አንደበት ነው፣ እንደ መለኮት ስም።
   ሀ. መልከጼዴቅ፣ ዘፍ. 14፡18-22
   ለ. በለዓም፣ ዘኍ. 24፡2
   ሐ. ሙሴ፣ ስለ ሕዝቦች በተናገረበት ጊዜ፣ ዘዳ. 32፡8
8. ያልተለመደ የሚሆነው የጥቅል ስም ለአንዱ የእስራኤል አምላክ በብዙ ቁጥር መሆኑ ነው! ምንም እንኳ እርግጠኝነት ባይኖርም፣ ንድፈ ሐሳቦቹ እነዚህ ናቸው።
   ሀ. ዕብራይስጥ በርካታ የበዙ ቁጥሮች አሉት፣ ዘወትር ለአጽንዖት የሚሆን። ከዚህ ጋር በቅርብ የሚዛመደው የዕብራይስጡ ሰዋሰዋዊ ተፈጥሮ የሚጠራው፣ "የግርማዊ ብዙ ቁጥር" ሲሆን፣ የብዙ ቁጥሩ ደግሞ ጠቅም ላይ የሚውለው ጽንሰ-ሐሳቡን ለማጉላት ነው።
   ለ. ይህ ምናልባት የሚገልጸው የመላእክትን ጉባዔ ነው፣ እሱም እግዚአብሔር በሰማይ እንደሰበሰበና ትዕዛዙን እንደሰጠ ነው (I ነገሥ. 22:19-23፤ ኢዮብ 1:6፤ መዝ. 82:1፤ 89:5፣7።
   ሐ. ይህም ሊያመለክት የሚችለው የአኪን መገለጥ ነው፣ አንድ አምላክ በሦስት አካላት። በዘፍ. 1፡1 እግዚአብሔር ፈጠረ፤ ዘፍ. 1፡2 መንፈሱ ሰፈፈ እናም በአኪ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ ወኪል ነው፣, በፍጥረት ላይ (ዮሐንስ 1፡3፣10፤ ሮሜ. 11፡36፤ I ቆሮ. 8:6፤ ቆላ. 1:15፤ ዕብ. 1:2፤ 2:10)።

መ. ያህዌህ (ቢ.ዲ.ቢ. 217፣ ኬ.ቢ. 394)

1. ይህ ስም የሚያንጸባርቀው መለኮትን ሲሆን፣ ኪዳንን እንደሚመሠርት አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር እንደ አዳኝ፣ ተቤዢ!

   ሰዎች ኪዳኑን አፈረሱ፣ እግዚአብሔር ግን ታማኝ ነው፣ ለቃሉ፣ ለተስፋው፣ ለኪዳኑ (መዝ. 103)።

   ይህ ስም መጀመሪያ የተጠቀሰው ከኤሎሂም ጋር ተደባልቆ ነው፣ በዘፍ. 2፡4። በዘፍ. 1-2 ሁለት የተፈጥሮ ሐተታዎች የሉም፣ ግን ሁለት አጽንዖቶች፡ (1) እግዚአብሔር እንደ ዩኒቨርስ (ሥጋዊ) ፈጣሪ እና (2) እግዚአብሔር ልዩውን ፍጡር የሰው ልጅን ፈጥሯል። ዘፍጥረት 2፡4 የሚጀምረው በተለየ መገለጥ ነው፣ እድላዊ ሥልጣንና ተግባር ስላለው የሰው ልጅ የሚያሳይ፣ እንዲሁም የኃጢአትና የዐመጸኝነት ችግር ልዩ ከሆነው ሥልጣን ጋር ስለ መያያዙ።
2. በዘፍ. 4፡26 የሚለው "ሰዎችም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ጀመሩ" (ያህዌህ)። ሆኖም፣ ዘጸ. 6፡3 የሚያመለክተው የቀድሞ የኪዳኑ ሕዝቦች (አባቶችና ቤተሰቦቻቸው) እግዚአብሔርን የሚያውቁት በኤል-ሻዳይነቱ ብቻ ነው። ያህዌህ የሚለው ስም በዘጸ. 3:13-16፣ በተለይም ቁ. 14. አንድ ጊዜ ነው የተጠቀሰው። ሆኖም፣ የሙሴ ጽሑፎች ዘወትር ቃላትን የሚተረጎሙት በታወቁት የቃላት አግባቦች ነው እንጂ፣ በሥርወ ቃል አይደለም (ዘፍ. 17:5 27:36፤ 29:13-35)። የዚህን ስም ትርጓሜ በተመለከተ በርካታ ንድፈ ሐሳቦች አሉ (ከአይዲቢ የተወሰደ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 409-11)።
   ሀ. ከዓረብ ሥርወቃል፣ "ፍጹም ፍቅርን ማሳየት"
   ለ. ከዓረብ ሥርወቃል "መምታት" (ያህዌህ እንደ ማዕበላዊ አምላክ)
   ሐ. ከዩጋርቲክ (ከነዓናዊ) ሥርወቃል "ቁንጮ ላይ መሆን"
   መ. የፎንቄውያንን ጽሑፍ ተከትሎ፣ መነሻዊ ቦዝ አንቀጽ ሲሆን ፍችውም "አንዱ የሚደግፈው፣" ወይም "የሚያጸናው አንዱ" ማለት ነው።
   ሠ. ከዕብራይስጡ ቃል "አንዱ የነበረው" ወይም "አንዱ ያለው" (በትንቢት ጊዜ ደግሞ፣ "አንዱ ወደፊት የሚኖረው")
   ረ. ከዕብራይስጡ ሂፊል ከ "ወደ መኖር የሚያመጣው"
   ሰ. ከዕብራይስጡ ሥርወቃል "መኖር" (ምሳ. ዘፍ. 3፡20)፣ ፍችውም "ለዘላለም የሚኖረው፣ ብቻውን ኗሪ"
   ሸ. ከዘጸ. ዐውደ ጽሑፍ 3:13-16 ያልተጠናቀቀ ቅርጽ በተጠናቀቀ አግባብ ጥቅም ላይ የዋለ፣ "እየሆንኩኝ በነበርኩበት በቀጣይም እሆናለሁ" ወይም "ፊት በነበርኩበት በቀጣይም እሆናለሁ" (ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ *የብሉይ ኪዳን ሰዋሰው ጥናት*፣ ገጽ 67) ሙሉው የያህዌህ ስም ዘወትር የሚገለጸው በአጽህሮተ ቃል ወይም በዋነኛ ቅርጹ ነው
      1) ያህ (ምሳ. ሃሌሉ -ያህ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 219፣ ዘጸ. 15:2፤ 17:16፤ መዝ. 89:9፤ 104:35)

2) ያሁ (“ኢአህ” የስሞች መጨረሻ፣ ምሳ. ኢሳይያስ)
3) ዮ (“ጆ” የስሞች መጀመሪያ፣ ምሳ. ኢያሱ ወይም ኢዩኤል)

3. በኋለኛው ይሁዲነት ይህ የኪዳን ስም በጣም ቅዱስ ስለሆነ (ቴትራግራማቶን) አይሁድ ለመናገር ይፈሩ ነበር፣ በዘጸ. 20:7፤ ዘዳ. 5:11፤ 6:13፣ ያለውን ትዕዛዝ እንዳይጥሱ በመስጋት። ስለሆነም የዕብራይስጡን ቃል ቀየሩት፣ “ባለቤት፣” “ጌታ፣” “ባል፣” “ጌታ” —አዶን ወይም አዶናይ (የኔ ጌታ)። ወደ ያህዌህ ሲመጡ በብሉይ ኪዳን ጽሑፍ ንባባቸው “ጌታ” ብለው ያነባሉ። በዚህን ምክንያት ነው ያህዌህ በእንግሊዝኛ ትርጉሞች ጌታ የሚባለው።
4. ልክ እንደ ኢል፣ ያህዌህ ከሌሎች ቃላት ጋር ይደባለቃል፣ የእስራኤልን የኪዳን አምላክ አንዳንድ ባሕርያት አጽንዖት ለመስጠት። በርካታ የተደባለቁ ቃላት ሲኖሩ፣ ጥቂቶቹ እኒህ ናቸው።
   ሀ. ያህዌህ - ዪሬህ (ያህዌህ ይሰጣል፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 እና 906)፣ ዘፍ. 22:14
   ለ. ያህዌህ - ሮፌከሃ (ያህዌህ ፈዋሽህ ነው፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 እና 950፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ ዘጸ. 15፡26
   ሐ. ያህዌህ - ኒሲ (ያህዌህ ዓርማዬ ነው፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 እና 651)፣ ዘጸ. 17፡15
   መ. ያህዌህ - ሜቃዲሽኬም (ያህዌህ የሚቀድስህ ነው፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 እና 872፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ ዘጸ. 31፡13
   ሠ. ያህዌህ - ሻሎም (ያህዌህ ሰላም ነው፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 እና 1022)፣ መሳ. 6፡24
   ረ. ያህዌህ - ሳቦዝ (ያህዌህ የሠራዊት፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 878)፣ 1ኛ ሳሙ. 1:3፣11፤ 4:4፤ 15:2፤ ዘወትር በነቢያት)
   ሰ. ያህዌህ - ሮ’ አይ (ያህዌህ እረኛዬ ነው፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 እና 944፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ መዝ. 23፡1
   ሸ. ያህዌህ - ሲድቄኑ (ያህዌህ ጽድቃችን ነው፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 እና 841)፣ ኤር. 23፡6
   ቀ. ያህዌህ - ሻማህ (ያህዌህ እዚያ አለ፣ ቢ.ዲ.ቢ 217 እና 1027)፣ ሕዝ. 48፡35

**ራዕይ፡ 1፡9-11**

**[9]እኔ ወንድማችሁ የሆንሁ ከእናንተም ጋር አብሬ መከራውንና መንግሥቱን የኢየሱስ ክርስቶስንም ትዕግሥት የምካፈል ዮሐንስ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ። [10]በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ፥ በኋላዬም የመለከትን ድምፅ የሚመስል ትላቅ ድምፅ ሰማሁ፥ [11]እንዲሁም። የምታየውን በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ኤፌሶንና ወደ ሰምርኔስ ወደ ጴርጋሞንም ወደ ትያጥሮንም ወደ ሰርዴስም ወደ ፊልድልፍያም ወደ ሎዶቅያም በእስያ ወዳሉት ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ላክ አለኝ።**

**1፡9-20** ይህ የዮሐንስ ራዕይ ነው፣ የተነሣው፣ ያረገው፣ የከበረው ክርስቶስ። እነዚህ ተመሳሳይ ማብራሪያዎች ጥቅም ላይ የዋሉት ሰባቱን አብያተ-ክርስቲያናት ለመድረስ ነው (ምዕራፍ 2-3)። ዮሐንስ ለአንባቢዎቹ የራሱን መለያ አሳይቷል (1) “ወንድማችሁ” የሚለውን ቃል በመጠቀም እና (2) የራሱን መከራ የመቀበል ልምምድ በመጥቀስ፣ መንግሥት፣ እና ጽናት። እነዚህ ቁልፍ ቃላት — መከራ፣ መንግሥት፣ እና ጽናት — ደግሞ የዮሐንስ ሕይወት ምሳሌዎች ናቸው፣ አንባቢዎች እንደ ዮሐንስ ሊቀበሉት ያሉት (ዮሐንስ 16፡33፤ ሐዋ. 14፡22፤ ሮሜ. 8፡17)።

ዘመናዊዎቹ ምዕራባዊ ተርጓሚዎች ራዕይን የማይረዱበት አንደኛው ምክንያት የአንደኛውን ክፍለ-ዘመን የሮሜ ዓለም ስደትና መከራ አለመቀበላችን ነው። ራዕይ እየተነዱ ላሉ፣ እየሞቱ ላሉ፣ በፍርሃት ላይ ላሉ አማኞች የሚሆን ቃል ነው።

**1፡9 “በመከራውም ተካፋይ የሆንኩ ወንድማችሁ”** 7፡14 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት

በብ.ኪ ያህዌ የሚታሰበው እንደ እስራኤል ንጉሥ ነው (1ኛ ሳሙ. 8፡7፤ መዝ. 10፡16፤ 24፡7-9፤ 29፡10፤ 44፡4፤ 89፡18፤ 95፡3፤ ኢሳ. 43፡15፤ 44፡4፣6) እና መሲሑን እንደ መጻዒ ንጉሥ ይቆጥሩታል፣ መዝ. 2፡6። ኢየሱስ በቤተልሔም በመወለዱ (6-4 ዓ.ም) የእግዚአብሔርመንግሥት ወደ ሰዎች ታሪክ በአዲስ ኃይል እና መቤዠት ገባ (አዲስ ኪዳን፣ ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 36፡17-36)። መጥምቁ ዮሐንስ የመንግሥቱን መቃረብ አውጇል (ማቴ. 3፡2፤ ማቴ. 1፡15)። ኢየሱስ በግልጽ መንግሥቱ በራሱ እና በትምህርቱ እንደሆነ አስተምሯል (ማቴ. 4፡17፣23፤ 9፡35፤ 10፡7፤ 11፡11-12፤ 12፡28፤ 16፡19፤ ማርቆስ 12፡34፤ ሉቃስ 10፡9፣11፤ 11፡20፤ 12፡31-32፤ 16፡16፤ 17፡21)። ቢሆንም መንግሥቱ ወደፊት ነው፣ ማቴ. 16፡28፤ 24፡14፤ 26፡29፤ ማርቆስ 9፡1፤ ሉቃስ 21፡31፤ 22፡16፣18)።

በማርቆስና በሉቃስ ትይዩነት የሚከተለው አቻ ሐረግ ይገኛል፣ “የእግዚአብሔር መንግሥት።” ይህ የኢየሱስ ትምህርቶች የታወቁ ርዕሶች በአሁኑ የእግዚአብሔር አገዛዝ በሰዎች ልብ ውስጥ መግባት፣ አንድ ቀን በመላው ዓለም ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ በኢየሱስ ጸሎት በማቴ. 6፡10 ላይ ተንጸባርቋል። ማቴዎስ፣ ለአይሁድ ሲጽፍ የእግዚአብሔርን ስም የማይጠቅስ ሐረግን መርጧል (የእግዚአብሔር መንግሥት)፣ በሌላ በኩል ማርቆስና ሉቃስ፣ ለአሕዛብ ሲጽፉ፣ በሁሉም ዘንድ የሚታወቀውን

የመለኮትን ስም መጠቀም መርጠዋል።

ይህ ክርክር የተፈጠረው በሁለቱ የክርስቶስ ምጽዓቶች ነው። ብ.ኪ. ያተኮረው በእግዚአብሔር መሲሕ፣ ወታደራዊ፣ ፈራጅ፣ ባለግርማ ሆኖ መምጣት ላይ ሲሆን፣ ነገር ግን አ.ኪ. የሚያመለክተው የመጀመሪያ ምጽዓቱ መከራን እንደሚቀበል ባርያ በኢሳ. 53 እንዳለው እንዲሁም ትሑቱ ንጉሥ ዘካ. 9፡9። ሁለቱ የአይሁድ ዘመናት፣ የኩነኔ ዘመናት እና አዲሱ የጽድቅ ዘመን ይደራረባሉ። ኢየሱስ አሁን በአማኞች ልብ ውስጥ ይገዛል፣ ነገር ግን አንድ ቀን በሁሉም ፍጥረታት ላይ ይገዛል። በብ.ኪ. እንደተተነበየው ይመጣል። አማኞች የሚኖሩት "በገና ድሮው" ወይም "ገና በሚመጣው" የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። (ጎርዶን ዲ. ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት *መጽሐፍ ቅዱስ ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት ይነበባል፣* ገጽ 131-134)።

▣ ***"ትዕግሥት"*** ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው 2:2፤3፤19፤ 3:10፤ 13:10፤ 14:12 ላይ ነው። ልዩ ርዕስ፡ ጽናት 2፡2 ላይ ተመልከት።

▣ **"ጳጥሞስ በምትባል ደሴት"** ሮማዎች እነዚህን አነስተኛ ደሴቶች፣ በታናሹ እስያ በባሕር ዳርቻ ያሉትን ለፖለቲካ እስረኞች ግዞት ይጠቀሙባቸው ነበር (ታሲተስ አናልስ፣ 3.68፤ 4.30፤ 15.71)። ባጠቃላይ ዮሐንስ በዚህ ትንሽ ደሴት ተግዞ ነበር፣ 37 ማይል ከሚሊተስ። ደሴቱ የአዲስ ጨረቃ ቅርጽ ነበረው፣ ወደ ምስራቅ ያቀና፣ አስር ማይል ርዝማኔና ስድስት ማይል ስፋት ያለው።

▣ **"ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር"** የዚህ ሐረግ ትርጓሜ ሁለት ታሳቢዎች አሉ። ሊያመለክት የሚችለውም (1) የዮሐንስ ወንጌልን መስበክ ወይም (2) የዮሐንስ ራዕዩን መቀበል ነው። በርካታ ታሪካዊ ማጣቀሻዎች አሉን፣ ለዮሐንስ የፖለቲካ ግዞት።

1. ተርቱሊያን፣ በመናፍቃን መግለጫ፣ 36
2. ኦሪጅን፣ ሆሚሊስ በማቴዎስ
3. የአሌክሳንደሪያው ክሌመንት፣ የሀብታሙ ሰው ደኅንነት፣ 47
4. ኢዩሲቢዩስ፣ የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ፣ III.20.8-9፤ እና (4) ጀሮም፣ ኢሉስትርዮስ ሰዎችን በተመለከተ፣ 9።

**1፡10 "በመንፈስ ነበርኩ"** ይህ የተለየ ሐረግ ነው ዮሐንስ የተቀበላቸውን የተለያዩ ራዕዮች የሚያመለክት (ዝኪ. 1፡10፤ 4፡2፤ 17፡3፤ 21፡10)። እሱም እንደ ተመስጦ ያለ አቋም ይመስላል፣ ራዕዩ የተሰጠበት ሁኔታ (ሐዋ. 10፡10፤ 22፡17፤ II ቆሮ. 12፡1)። ይህ የአይሁድ አፖካሊፕታዊ ጽሑፍ ባሕርይ ነው።

▣ ***"በጌታ ቀን"*** ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው ማጣቀሻ ነው፣ እሑድን የጠቀሰ፣ ይህን ሐረግ ተጠቅሞ። እሑድ የተጠቀሰው "ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን" በሚል ነው፣ ዮሐንስ 20፡19፤ ሐዋ. 20፡7 እና I ቆሮ. 16፡2።

▣ ***"እንደ መለከት ያለ ድምጽ"*** ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ አስርቱን ትእዛዛት ሲሰጥ ባለው መልኩ ነው (ዘጸ. 19፡16)። ሆኖም፣ ከቁ. 12ሀ እና 4፡1 የተነሣ፣ የመልአክን ድምጽ ሊያመለክት ይችላል። መልአካዊ ጣልቃ ገብነት የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ባሕርይ ነው። ራዕይ ስለ መላእክት በብዛት ይናገራል፣ ከሌላው የአኪ መጽሐፍ ይልቅ።

## ልዩ ርዕስ፡ በእስራኤል ጥቅም ላይ የሚውሉ ቀንዶች

በዕብራይስጥ አራት ቃላት አሉ ከቀንድ/መለከት ጋር የተያያዙ፡

1. "የበግ ቀንድ" (ቢዲቢ 901) - ወደ ድምጽ መሣርያነት የተቀየረ፣ ኢያ. 6፡5። ተመሳሳይ የሆነ ቃል፣ በቀንዱ የተያዘ፣ እሱንም አብርሃም በይስሐቅ የቀየረው ዘፍ. 22፡13 ላይ።
2. "መለከት" (ቢዲቢ 1051) - ከሶርያ ቃል ለዱር በግ (አይቤክስ)። ይህ ቀንድ እሱም ዘጸ. 19፡16፤19 ሲና/ኮሬብ ተራራ ጥቅም ላይ የዋለው ነው። ቁ. 1 እና ቁ. 2 ከኢያ. 6፡5 ጋር ትይዩ ነው። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው የአምልኮ ጊዜንና የውጊያ ጊዜን ለማጣጣም ነው (ማለትም፣ ኢያሪኮ ሁለቱም ነበር፣ ዝከ. 6፡4)።
3. "የበግ ቀንድ" (ቢዲቢ 385) - ከፊንቂያውያን ቃል ለበግ (ዝከ. 6፡4፤6፤8፤13)። እሱም ደግሞ ለኢዩቤልዩ ዓመት ይቆማል ሌዋ. 25፡13፤28፤40፤50፤52፤54፤ 27፡17፤18፤23፤24)።

(እነዚህ ሦስቱ ሁሉ ሲለዋወጡ ይታያሉ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው። ሚሽናህ (RH 3.2) የማንኛውም እንስሳ ቀንድ — በግ፣ ፍየል፣ ወይም አጋዘን፣እንዲሆን ይፈቅዳል፣ የላም ግን አይሆንም።)

4. "መለከቶች" (ቢዲቢ 348) - ሊሆን የሚችለው "መዘርጋት፣" ከሚለው ግሥ ነው፣ እሱም ቀጥ ያለ አጥንት (እንደ እንስሳ ቀንዶች ያልተጣመመ)። እነዚህ የተበጁት ከብር ነው (እንደ ግብፅ ቅርጽና መልክ ያለ)። እነዚህ ጥቅም ላይ የሚውሉት፡
   ሀ. ከአምልኮ ሥርዓት ጋር (ዘኍ. 10፡2፤8፤10)
   ለ. ለወታደራዊ አገልግሎት (ዘኍ.10፡9፤ 31፡6፤ ሆሴዕ 5፡8፤ ዕዝራ 3፡10፤ ነሀ. 12፡35፤41)
   ሐ. ለንጉሣዊ ተግባራት (2ነገ. 11፡14)

ከእነዚህ አንደኛው የብረት ቀንድ በቲቶ ቅስት ሮም ላይ ተጠቅሷል፤ ጆሴፈስም *Antiq.* 3.12.6. ላይ ጠቅሷቸዋል።

**1:11 "በመጽሐፍ"** ይህ የግሪክ ቃል *biblion* ነው። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው በመጽሔት ወይም በጥቅል መልኩ ነው። እሱም ኋላ ላይ ለጥንታዊ ጽሑፍ ወይም ለመጽሐፍ መጠሪያ ሆኗል። ዮሐንስ ራዕዩን ይጽፍ ዘንድ ታዟል። እሱም ከመለኮት ከራሱ የተገለጠ ነው። እሱም የዮሐንስ ለግል ጥቅም ሳይሆን ለቤተ-ክርስቲያን ነው። አንደኛው የአፖካሊፒቲካዊ ጽሑፍ ባሕርይ በጥብቅ አወቃቀር የተጻፈ ዘውግ መሆኑ ነው፣ እንደ ብኪ ትንቢቶች በቃል ሳይሰጥ። መጽሐፍ ወይም ጥቅል በተደጋጋሚ ይበጃል፣ በአይሁድ አፖካሊፒቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ፣ መልእክቱን ለወደፊቱ አንባቢ እንደማስተላለፊያ መንገድ።

▣ **"ወደ ሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት ላክ"** የእነዚህ አብያተ-ክርስቲያናት ትእዛዝ የሮሜን የደብዳቤ መስመር ተከትሎ ነው፣ ኤፌሶን ጀምሮ እሚያበቃ። የጳውሎስ ተዘዋዋሪ መጽሐፍ "ኤፌሶን" የሚባለው በዚህ መስመር ሳይጓዝ አይቀርም። የእግዚአብሔር ራዕይ ለአንድ ግለሰብ ብቻ ፈጽሞ አይደለም፣ ግን ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንጂ፣ ለክርስቶስ አካል።

▣ የኪንግ ጀምስ ትርጉም "አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ" የሚል ሐረግ በድጋሚ ይጨምራል፣ ነገር ግን ምንም የግሪክ ጽሑፍ የለም ይሄንን ሐረግ እዚህ ቁጥር ላይ የሚያጠናክር።

*ራዕይ:* **1:12-16**

**[12]የሚናገረኝንም ድምፅ ለማየት ዘወር አልሁ፤ ዘወርም ብዬ ሰባት የወርቅ መቅረዞች አየሁ፥ [13]በመቅረዞቹም መካከል የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ፥ እርሱም እስከ እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰው ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር። [14]ራሱና የራሱ ጠጕርም እንደ ነጭ የበግ ጠጕር እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፥ ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ፤ [15]እግሮቹም በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር፥ ድምፁም እንደ ብዙ ውኆዎች ድምፅ ነበረ። [16]በቀኝ እጁም ሰባት ከዋክብት ነበሩት፥ ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ወጣ፤ ፊቱም በኃይል እንደሚበራ እንደ ፀሐይ ነበረ።**

**1:12 "ሰባት የወርቅ መቅረዞችንም አየሁ"** ይህ ሜኖራህን አይጠቅስም (ባለ ሰባት ዘንግ መቅረዝ) እሱም በመቅደሱ የነበረ (ዘጸ. 25:31-40) አልያም መቅረዝ ዘካ. 4:2 ላይ ያለው። እነዚህ የተለዩ፣ ነጠላ መቅረዞች የሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት ተምሳሌታዊ መግለጫ መንገዶች ናቸው (ዝኪ. 1:20፤ 2:1)።

**1:13-18** በዚህ የኢየሱስ መግለጫ ላይ አብዛኞቹ ምስያዎች ሁለት ታሳቢ የብኪ ዳራ አላቸው: (1) ያህዌ፣ ግን ደግሞ (2) መልአክ የዳንኤል 10።

**1:13**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የሰው ልጅ የሚመስል"** |
| **አኪጀት** | **"የሰው ልጅ የሚመስለውን"** |
| **አየተመት** | **"የሰው ልጅ የሚመስለውን"** |
| **አእት** | **"የሰው ልጅ የሚመስል"** |
| **አኢመቅ** | **"የሰው ልጅ የሚመስል"** |

በትልቁ ፊደላት የተጻፉትን ልዩነቶች ተገንዘብ። ምክንያቱ የቃሉ አሻሚነት ነው። በብኪ እሱ ለሰው ልጅ የመግለጫ ቃል ነው (መዝ. 8:4፤ ሕዝ. 2:1 እና ሌሎች ተጨማሪዎች)። ሆኖም፣ እሱ ደግሞ ዳን. 7:13 እንዲሁም ሕዝ. 1:26 ጥቅም ላይ ውሏል፣ ሰው መሲሑን ለመጥቀስ፣ መለኮት የሆነውን (ዝኪ. 2:18፣ ተመሳሳዩ ሰው "የእግዚአብሔር ልጅ" ተብሎ የተጠራበት) ተገምቷል፣ ምክንያቱም

1. በእግዚአብሔር ፊት ስላለ
2. በሰማይ ደመና ስለሚጓዝ
3. ዘላለማዊ መንግሥት ስለ ተሰጠው።

ኢየሱስ ይህን ቃል ራሱን ለመጥቀስ ተጠቅሞበታል፣ ምክንያቱም ራቢያዊ አጠቃቀም ስለሌለው፣ ምንም ብሔራዊ ወይም ወታደራዊ ፍቺ። እሱም የኢየሱስን አካል ሰዋዊና መለኮታዊ ገጽታዎች ስለሚደባልቅ (1 ዮሐንስ 4:1-3፤ ዮሐንስ 1:1-2፣14)።

አኪጀት እና አየተመት የተወሰነ አንቀጽ ("the") እንዳላቸው አአመመቅ፣ አእት፣ እና ኢመቅ ደግሞ ያልተወሰነ አንቀጽ ("a") እንዳላቸው ተገንዘብ። በግሪክ ጽሑፍ የተወሰነ አንቀጽ የለም (ዳን. 7:13፤ ዕብ. 1:2፤ 3:6፤ 5:8፤ 7:28)። ሆኖም፣ የተወሰነ ያደረገው የመጠሪያው ሐቅ ነው። አሻሚነቱ ሆን ብሎ የተደረገ ይመስላል (የዮሐንስ ጽሑፎች አንዱ ገጽታ)። ኢየሱስ በርግጥ የሰው ልጅ ነው እንዲሁም ደግሞ መለኮታዊ መሲሕ።

▣ **"እርሱም እስከ እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰው ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር"** ይህ ሐረግ በብዙ መንገዶች ይረዳ ነበር።

1. እንደ ሊቀ-ካህኑ ማጣቀሻ (ዘጸ. 28:4፤ 29:5፤ ሌዋ. 16:4 እና ዘካ. 3:4)
2. እንደ ንጉሣዊ ባለጠጋ ሰው ማጣቀሻ (1 ሳሙ. 18:24፤ 24:12 እና ሕዝ. 26:16)
3. እንደ ባለግርማው ተርጓሚ መልአክ፣ የዳን. 10:5-21፣ እሱም ኢየሱስን የእግዚአብሔርን መልእክት እንደሚያመጣ የሚገልጽ።

ጆሴፈስ፣ በመጽሐፉ፣ የአይሁድ ቅርሶች III. 7.2.4፣ እንዳለው ሊቀ-ካህኑ ቀሚስ ይለብሳል፣ በወርቅ መታጠቂያ። ስለዚህ፣ ኢየሱስ ሊቀ ካህን ነው (መዝ. 110:4-7፤ ዘካርያስ 3) የሰማያዊው ቤተ-መቅደስ (ዕብ. 8:1-13፤ መዝሙር 110)።

**1፥14 "ራሱና የራሱ ጠጕርም እንደ ነጭ የበግ ጠጕር ነጭ ነበሩ"** ይህ የጥንት ጊዜ ጠቃሽ ነው ዳን. 7፡9። ይህ አንዱ ምሳሌ ነው የአኪ ደራስያን ለኢየሱስ የሰጡት የያህዌ መጠሪያና መግለጫ፣ የኢየሱስን መለኮትነት የሚያስረግጥ።

▣ **"ዓይኖቹም የእሳት ነበልባል ይመስላሉ"** ይህ ተምሳሌትነቱ የጠለቀ እውቀቱን ነው (ዳን. 10፡6፤ ራዕ. 2፡18፤ 19፡12)።

**1፥15**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስላል"** |
| **አኪጀት** | **"በእቶን የነጠረ የጠራ ናስ ይመስላል"** |
| **አየተመት** | **"በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስላል"** |
| **አእት** | **"እንደ ጠራና የነጠረ ናስ የሚመስል"** |
| **አኢመቅ** | **"በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስላል"** |

ይህ ቃል ለናስ (*chalkolibanon*) ርግጠኛ አይደለም። ናስ ተዛማጅ ቃል ነው፣ *chalkos* (ማቴ. 10፡9፤ 1 ቆሮ. 13፡1፤ ራዕ. 18፡22)። እሱም ሕዝ. 1፡7 ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለኪሩቤል እግር መሸፈኛ ዳን. 10፡6 ለመልአካዊ መልእክተኛ። የኢየሱስ እግሮች በእነዚሁ ቃላት ተገልጧል (ዝከ. 1፡15፤ 2፡18) የእርሱን ሰማያዊ መገኛ ወይም ግርማዊ ባሕርይ ያሳያል።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣** | |
| **አኪጀት፣** | |
| **አየተመት** | **"ድምጹም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምጽ ነበር"** |
| **አእት** | **"ድምጹም እንደ ውኃ ፏፏቴ ድምጽ ነበር"** |
| **አኢመቅ** | **"ድምጹም እንደ ውቅያኖስ ድምጽ ነበር"** |

ይህ ጥቅም ላይ የዋለው

1. ያህዌ ሕዝ. 1፡24፤ 43፡2
2. የኪሩቤል ክንፎች ሕዝ. 1፡24
3. ለመልአካዊ መልእክተኛ ዳን. 10፡6

ባጠቃላይ እሱ የሰማያዊ ሰው ሥልጣናዊ ድምጽ ተምሳሌት ነበር (ዝከ. 14፡2፤ 19፡6)።

**1፥16 "በቀኝ እጁም ሰባቱን ከዋክብት ይዟል"** ይህ ሐረግ 1፡16፣20፤ 2፡1፤ 3፡1 ላይ ተደግሟል። ይህም የሚያሳየው ኢየሱስ ለአጥቢያ አብያተ-ክርስቲያናት ያለውን ክብካቤ ነው።

▣ **"ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ይወጣ ነበር"** *Hromphaia* የሚያመለክተው ትልቁን ትራኪያን ነው፣ ሰፊ ሰይፍ፣ የሮሜ ወታደሮች ይይዙት የነበረ። ይህ ዘይቤ በብኪ ኢሳ. 11፡4፤ 49፡2 ላይ ይገኛል። ተምሳሌት የሚያደርገውም (1) ጦርነት (ዝከ. 2፡16፤ 6፡8) እና (2) የእግዚአብሔር ቃልን ኃይል ነው፣ በተለይም ፍርዱን (ዝከ. 2፡12፤ 19፡15፣21፤ II ተሰ. 2፡8)። ዕብራውያን 4፡12 ሌላ ዓይነት ሰይፍ ይጠቀማል (*machaira*)፣ ግን ተመሳሳይ ሐሳብ — የእግዚአብሔር ቃል ኃይል።

▣ **"ፊቱም በኃይል እንደሚበራ እንደ ፀሐይ ነበር"** ተመሳሳይ ሐረግ ጥቅም ላይ ውሏል፣ መልአካዊውን መልእክተኛ ለመግለጽ ዳን. 10፡6 እና ራዕ. 10፡1። ዳን. 12፡3 (ማቴ. 13፡43) ላይ እሱ ከሙታን ለተነሣው ለጻድቁ ተምሳሌት ነበር። ኢየሱስም በተመሳሳይ ቃላት በመለወጡ ተገልጿል (ማቴ. 17፡2)።

### ራዕይ፡ 1፥17-20

**[17]ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ [18]ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ። [19]እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ። [20]በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ምሥጢር ይህ ነው፤ ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ናቸው፥ ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።**

**1፥17 "በፊቱም እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ"** ይህ ዓይነቱ መገለጥ በሚቀበሉት ላይ ዘወትር ፍርሃትን ይፈጥራል (ዳን. 8፡17፤ 10፡9፤ ሕዝ. 1፡28፤ 3፡23፤ II ባሮክ 21፡26፤ IV ዕዝራ 5፡14)። ከተፈጥሮ በላይ የሆነ መንፈሳዊ ሕላዌ ራሱን ለሰው ልጅ ሲገልጥ የሚያስፈራ ነገር ነው።

▣ **"ቀኝ እጁንም ጫነብኝ"** ይህ አካላዊ ድርጊት የሚያሳየው ኢየሱስ ለሕዝቡ ያለውን ክብካቤና ትኩረት ነው (ዳን. 8፡18፤ 10፡10፣ 18)።

▣ **"አትፍራ"** ይህ የአሁን ተተኳሪ ነው በአሉታዊ አንቀጽ፣ ዘወትርም ፍችው ቀደም ብሎ በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ማቆም ነው። ሰዎች መንፈሳዊ ሕላዌን ይፈራሉ (የኢየሱስ ቃል በማቴ. 14:27፤ 17:7፤ 28:10፤ ማርቆስ 6:50፤ ሉቃስ 5:10፤ 12:32፤ ዮሐንስ 6:20 እና የመልአኩ ቃል በማቴ. 28:5፤ ሉቃስ 1:13፣30፤ 2:10)።

▣ **"ፊተኛውና መጨረሻው እኔ ነኝ"** ይህ ዘወትር ለያህዌ ነው የሚጠቀሰው (ኢሳ. 41:4፤ 44:6፤ 48:12)፣ እዚህ ግን ጥቅም ላይ የዋለው ለክርስቶስ መከበር ነው (ዝከ. ቁ. 8፤ 2:8፤ 22:13)። ይህ ከ "አልፋ እና ዖሜጋ" ሐረግ ጋር አቻ ነው። ቁ. 4 እና 8 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**1:18**

**አአመመቅ፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | **"ሕያው የሆንኩት"** |
| **አኪጀት** | **"ሕያው የሆንኩት እኔ ነኝ"** |
| **አእት** | **"ሕያው የሆንኩት እኔ ነኝ"** |
| **አኢመቅ** | **"ሕያው የሆንኩት እኔ ነኝ"** |

ይህ የእግዚአብሔር የኪዳን ስም፣ ያህዌ፣ ጠቃሽ ነው፣ እሱም ከዕብራይስጡ ቃል "መሆን" የመጣ ነው (ዘጸ. 3፡14)። ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች 1፡8 ላይ ተመልከት። እሱ ዘላለም ኗሪ፣ ብቸኛው ሕያው ነው (ዳን. 12፡7፤ ዮሐንስ 5፡26)። በድጋሚም፣ ይህ የአኪ ደራሲ አጠቃቀም ነው፣ በብኪ የእግዚአብሔር መጠሪያ፣ ኢየሱስን ለመግለጽ። ይህ ከኢየሱስ የያህዌ ስም አጠቃቀም ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው፣ ለራሱ፣ ዮሐንስ 8፡58 ላይ።

▣ **"ሞቼም ነበርኩ እነሆም ለዘላለም ሕያው ነኝ"** ትንሣኤው፡

1. የአብ የማረጋገጫ ማኅተም (ሐዋ. 2:24፤ 3:15፤ 4:10፤ 5:30፤ 10:40፤ 13:30፣33፣34፣37፤ 17:31፤ ሮሜ. 4:24፤ 10:9፤ 1 ቆሮ. 6:14፤ 15:15፤ ኤፌ. 1:20፤ ቆላ. 2:12፤ ዕብ. 13:20፤ 1 ጴጥ. 1:21)
2. የመንፈስን ኃይል ማሳያ (ሮሜ. 8:11)
3. የኢየሱስን ግላዊ ኃይል ማሳያ (ዮሐንስ 10:11፣15፣17፣18)

ይህ የኢየሱስ ሞት ማጣቀሻ፣ የሱን ሰብአዊነት የማይቀበሉትን የግኖስቲክ የሐሰት መምህራንን ለመመከት መንገድ ሆኖ ነበር።

▣ **"የሞትና የሲዖል መክፈቻ አለኝ"** አይሁድ ሞትን የሚመለከቱት በር እንዳለው እስር-ቤት ነው (ኢዮብ 38:17፤ መዝ. 9:13፤ 107:18፤ ኢሳ. 38:10፤ ማቴ. 16:19)። ቁልፎች የሥልጣን ዘይቤዎች ናቸው። ይህ ተምሳሌት ነው፣ የኢየሱስን በራሱ ሞት እና በተከታዮቹ ሞት ላይ ያለውን ሥልጣን የሚያሳይ (ዝከ. 5:9-10፤ 1 ቆሮ. 15)።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት፣ አኢመቅ** | **"ሲዖል"** |
| **አእት** | **"የሙታን ዓለም"** |

የኪንግ ጀምስ ትርጉም ይህንን የሚተረጉመው እንደ "ገሃነም፣" ነው፣ ይህ ግን የእንግሊዝኛ ትርጉም ውዥንብር ነው በግሪክ ቃላት፣ *Hades* እና *Gehenna*። *Hades* የሚገነዳኘው የብኪውን ቃል *Sheol* ነው (ዝከ. 6:8፤ 20:13-14)። በብኪ ሰዎች ተስለው ነበር፣ ወደ መሬት ሲወርዱ፣ ከቤተሰባቸው ጋር የሚገናኙበት። እሱም ንቁና ደስታ የሌለበት ሕላዌ ነበር። ቀስ በቀስ እግዚአብሔር በርካታ ተጨማሪ መገለጥ መስጠት ጀመረ (ቀጣይነት ያለው ራዕይ) ስለ ከሕይወት በኋላ። ራቢዎች የሚያስረግጡት የጽድቅ (ገነት) እና የኃጢአተኛ (ገሃነም) ምድብ በሲዖል ውስጥ (ሉቃስ 23፡43)። መጽሐፍ ቅዱስ የተብራራ አይደለም፣ ስለ ከሕይወት በኋላ ዝርዝር ነገር በማቅረብ። ስለ መንግሥተ ሰማያትም ዘይቤ ነው የሚናገረው (ማለትም፣ የወርቅ አደባባዮች፣ 1500 ማይል ኩብ ከተማ፣ ያልተዘጉ በሮች፣ ወዘተ) ገሃነምም (እሳት፣ ጨለማ፣ ትሎች፣ ወዘተ)።

## ልዩ ርዕስ፡ ሙታን የት ናቸው?

I. ብሉይ ኪዳን

ሀ. ሁሉም ሰዎች ወደ ሲኦል ይወርዳሉ (ከሥርወ ቃል አኳያ ርግጠኛ ያልሆነ፣ ቢዲቢ 1066)፣ እሱም ሞትን የሚያመለክት ወይም መቃብርን፣ ባብዛኛው በጥበብ ሥነ ጽሑፍ እና በኢሳይያስ። በብሉይ ኪዳን፣ ጥላማ፣ ንቁ፣ ነገር ግን ደስታ የሌለበት ሕላዌ ነበር (ኢዮብ 10፡21-22፤ 38፡17፤ መዝ. 107፡10፣14)።

ለ. ሲኦል በባሕርዩ

1. ከእግዚአብሔር ፍርድ ጋር ይያያዛል (እሳት)፣ ዘዳ. 32፡22
2. ከፍርድ ቀን በፊት ካለው ቅጣት ጋር ይያያዛል፣ መዝ. 18፡4-5
3. ከአባዶን (ጥፋት) ጋር ይያያዛል፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር የታወቀ፣ ኢዮብ 26፡6፤ መዝ. 139፡8፤ አሞጽ 9፡2
4. ከ "ጉድጓድ" (ከመቃብር) ጋር ይያያዛል፣ መዝ. 16፡10፤ ኢሳ. 14፡15፤ ሕዝ. 31፡15-17
5. ክፉዎች ከነሕይወታቸው ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፣ ዘኍ. 16፡30፣33፤ መዝ. 55፡15
6. ዘወትር ሰውኛ የሚሆነው አፈ ሰፊ በሆነ እንስሳ ነው፣ ዘኍ. 16፡30፤ ኢሳ. 5፡14፤ 14፡9፤ ዕንባ. 2፡5
7. ሰዎች እዚያ ሪፋይም ተብለው ይጠራሉ፣ (ኢሳ. 14፡9-11)

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. የዕብራይስጡ ሲኦል በግሪኩ ሀዳስ ነው የሚተረጎመው (ያልታየው ዓለም)

ለ. ሃዳስ (ሲኦል) በባሕርዩ

1. ሞትን ያመላክታል፣ ማቴ. 16፡18
2. ከሞት ጋር ይያያዛል፣ ራዕ. 1፡18፤ 6፡8፤ 20፡13-14
3. ዘወትር የሚመሰለው የቋሚ ቅጣት ስፍራ ነው (ገሃነም)፣ ማቴ. 11፡23 (የብሉይ ኪዳን ጥቅስ)፤ ሉቃስ 10፡15፤ 16፡23-24
4. ዘወትር የሚመሰለው ከመቃብር ጋር ነው፣ ሉቃስ 16፡23

ሐ. ይከፋፈላል (ራቢዎች)

1. የጻድቃኖች ክፍል ገነት ይባላል (በርግጥ የሰማይ ሌለኛው ስም፣ 2ኛ ቆሮ. 12፡4፤ ራዕ. 2፡7)፣ ሉቃስ 23፡43
2. የክፉዎች ክፍል እንጦርጦስ ይባላል፣ 2ኛ ጴጥ. 2፡4፣ እሱም ለክፉዎች መላእክት ማቆያ ስፍራ (ዘፍ. 6፤ 1ኛ ሄኖክ)

መ. ገሃነም

1. የብሉይ ኪዳንን ሐረግ ያንጸባርቃል፣ "የሄኖም ልጆች ሸለቆ፣" (ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ)። እሱም የፍንቄአውያን የእሳት ጣዖት፣ የሞሎክ አምልኮ የሚፈጸምበት (ቢዲቢ 574)፣ የሕጻናት መሥዋዕት የሚቀርብበት ነበር፣ (2ኛ ነገሥ. 16፡3፤ 21፡6፤ 2ኛ ዜና. 28፡3፤ 33፡6)፣ እሱም በሌዋ. 18፡21፤ 20፡2-5 የተከለከለው።
2. ኤርምያስ እሱን ከጣዖት ማምለኪያነት ወደ ያህዌ የፍርድ ስፍራ ቀይሮታል (ኤር. 7፡32፤ 19፡6-7)። እሱም የእሳት፣ የዘላለም ፍርድ ቦታ ሆኗል፣ 1ኛ ሄኖክ 90፡26-27 እና ሲ.ብ. 1፡103።
3. በኢየሱስ ጊዜ የነበሩት አይሁድ በአባቶቻቸው የሕጻናት መሥዋዕት ጣዖት አምልኮ በጣም ያፍሩ ስለነበር፣ ስፍራውን ለኢየሩሳሌም የቆሻሻ መጣያ ስፍራ አድርገውታል። አብዛኞቹ የኢየሱስ ዘይቤዎች፣ ስለ ዘላለማዊ ፍርድ የተገኙት ከዚህ ስፍራ (እሳት፣ ጭስ፣ ትሎች፣ ግማት፣ ነው፣ ማርቆስ 9፡44፣46)። ገሃነም የሚለው ቃል በኢየሱስ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ከያዕቆብ 3፡6 በቀር)።
4. የኢየሱስ የገሃነም አጠቃቀም

    ሀ. እሳት፣ ማቴ. 5፡22፤ 18፡9፤ ማርቆስ 9፡43

    ለ. ቋሚ፣ ማርቆስ 9፡48 (ማቴ. 25፡46)

    ሐ. የጥፋት ስፍራ (የነፍስም የሥጋም)፣ ማቴ. 10፡28

    መ. ከሲዖል ጋር ትይዩ ነው፣ ማቴ. 5፡29-30፤ 18፡9

    ሠ. ክፉዎችን "የሲኦል ልጆች" በሚያስብል ባሕርይ፣ ማቴ. 23፡15

    ረ. የፍርድ ውሳኔ ውጤት፣ ማቴ. 23፡33፤ ሉቃስ 12፡5

    ሰ. የገሃነም ጽንሰ ሐሳብ የሁለተኛ ሞት ትይዩ ነው (ራዕ. 2፡11፤ 20፡6፣14) ወይም የእሳት ባሕር (ማቴ. 13፡42፣50፤ ራዕ. 19፡20፤ 20፡10፣14-15፤ 21፡8)። እሱም ማለት የሚቻለው የእሳት ባሕር የሰዎች ቋሚ መኖርያ ስፍራ ተደርጎ ነው

    (ከሲዖል) እንዲሁም ክፉ መላእክት (ከእንጦርጦስ፣ 2ኛ ጴጥ. 2፡4፤ ይሁዳ 6 ወይም ጥልቁ፣ ሉቃስ 8፡31)፤ ራዕ. 9፡1-10፤ 20፡1፣3)።

    ሸ. ለሰዎች አልተሠራም ነበር፣ ነገር ግን ለሰይጣንና ለመላእክቱ፣ ማቴ. 25፡41

ሠ. በሲዖል፣ በሀዳስ፣ እና በገሃነም መካከል መነባበር ስላላ ማለት የሚቻለው፣

1. በዋነኛነት ሁሉም ሰዎች ወደ ሲዖል/ሀዳስ ይወርዳሉ
2. እዚያም ያደረጉት ሥራ (መልካም ቢሆን ክፉ) ከፍርድ ቀን በኋላ ይብስባቸዋል፣ ነገር ግን የክፉዎች ስፍራ እንደዛው ይቀራል (በዚህን ምክንያት ነው ኪጀት ሃዳስን ሲተረጉም (መቃብር) ገሃነምን (ሲዖል) ያለው።
3. የአዲስ ኪዳን ጽሑፍ ብቻ ነው ከፍርድ ቀን በፊት ያለው እሳት ምሳሌ መሆኑን የገለጠው፣ የሉቃስ 16፡19-31 (አልአዛርና ሃብታሙ ሰው)። ሲኦል ደግሞ እንደ አሁኑ ቅጣት ስፍራ ተገልጧል፣ (ዘዳ. 32፡22፤ መዝ. 18፡1-5)። ሆኖም፣ ማንም በምሳሌ ላይ መሠረተ እምነቱን አይጥልም።

III. በሞትና በትንሣኤ መካከል ያለ ማዕከላዊ ስፍራ

ሀ. አዲስ ኪዳን "የነፍስን መዋቲነት" አያስተምርም፣ እሱም ከበርካታ ጥንታዊ የከሕይወት በኋላ አመለካከቶች አንዱ የሆነው።

1. የሰዎች ነፍሳት ከሥጋዊ አካል በፊት ነበር
2. የሰዎች ነፍሳት ከሥጋዊ ሞት በፊትም ሆነ በኋላ ዘላለማዊ ናቸው
3. ሥጋዊ አካል የሚታየው እንደ እስር ቤት ሲሆን፣ ሞት ደግሞ ወደ ቅድም ተፈጥሮ ተፈትቶ መመለስ ነው

ለ. አዲስ ኪዳን ከአካሉ ስለ ተለየ ሕይወት፣ በሞትና በትንሣኤ መካከል ስላለው ፍንጭ ይሰጣል

1. ኢየሱስ በሥጋና በነፍስ መካከል ስላለው ክፍል ተናግሯል፣ ማቴ. 10፡28
2. አብርሃም አሁን ምናልባት አካል ሊኖረው ይችላል፣ ማርቆስ 12፡26-27፤ ሉቃስ 16፡23
3. ሙሴና ኤልያስ በመለወጥ ጊዜ ሥጋዊ አካል ነበራቸው፣ ማቴ. 17
4. ጳውሎስ የሚለው በዳግምምጽአት በኢየሱስ ያሉት ነፍሳት በመጀመሪያ አዲሱን አካላቸውን ይይዛሉ፣ 2ኛተሰ.4፡13-18
5. ጳውሎስ የሚለው አማኞች አዲሱን መንፈሳዊ አካል በትንሣኤ ቀን ያገኛሉ፣ 1ኛ ቆሮ. 15፡23፣52
6. ጳውሎስ የሚለው አማኞች ወደ ሲዖል አይወርዱም ነው፣ ነገር ግን በሞት ከኢየሱስ ጋር ይሆናሉ፣ 2ኛ ቆሮ. 5፡6፣8፤ ፊሊጵ. 1፡23። ኢየሱስ ሞትን ድል ነሥቷል፣ እናም ጻድቁን ከእሱ ጋር ወደ ሰማይ ይወስደዋል፣ 1ኛ ጴጥ. 3፡18-22።

IV. ሰማይ

ሀ. ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በሦስት መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

1. ከመሬት በላይ ያለው ከባቢ ዓየር፣ ዘፍ. 1፡1፤8፤ ኢሳ. 42፡5፤ 45፡18
2. ከዋክብታማ ሰማይ፣ ዘፍ. 1፡14፤ ዘዳ. 10፡14፤ መዝ. 148፡4፤ ዕብ. 4፡14፤ 7፡26
3. የእግዚአብሔር ዙፋን ስፍራ፣ ዘዳ. 10፡14፤ 1ኛ ነገሥ. 8፡27፤ መዝ. 148፡4፤ ኤፌ. 4፡10፤ ዕብ. 9፡24 (ሦስተኛው ሰማይ፣ 2ኛ ቆሮ. 12፡2)

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከሕይወት በኋላ ብዙም አይገልጽ። ምናልባትም የወደቀው ሰው ነገሩን የመረዳት መንገዱም ሆነ አቅሙ ስለሌለው ይሆናል፣ (1ኛ ቆሮ. 2፡9)።

ሐ. ሰማይ ስፍራም (ዮሐንስ 14፡2-3) እንዲሁም አካል ነው፣ (2ኛ ቆሮ. 5፡6፤8)። ሰማይ ምናልባት የኤደን ገነት መመለስ ይሆናል፣ (ዘፍ. 1-2፤ ራዕይ 21-22)። ምድር ትጸዳለች ትታደሳለችም (ሐዋ. 3፡21፤ ሮሜ 8፡21፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡10)። የእግዚአብሔር አምሳል (ዘፍ. 1፡26-27) በክርስቶስ ተመልሷል። አሁን የኤድን ገነት ወዳጃዊ ኅብረት ዳግም ተችሏል።

ሆኖም፣ ይህ ዘይቤአዊ ነው፣ (ሰማይ፣ እንደ ግዙፍ፣ ኩብ ከተማ የራዕይ 21፡9-27) እናም በጥሬ ቃሉ አይደለም። 1ኛ ቆሮንቶስ 15 የሚገልጸው የሥጋዊ አካልንና የመንፈሳዊ አካልን ልዩነት፣ እንደ ትልቅ ተክል ዘር አድርጎ ነው። ደግሞም 1ኛ ቆሮ. 2፡9 (ከኢሳ. 64፡4 እና 65፡17 የተጠቀሰ) ታላቅ ቃል ኪዳንና ተስፋ ነው! እሱን ስናየው እሱን እንደምንመስል አውቃለሁ፣ (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)።

V. የመርጃ ምንጮች

ሀ. ዊሊየም ሄንድሪክሰን፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከዚህ ሕይወት በኋላ*

ለ. ማውሪክ ራውሊንግስ፣ *ከሞት ደጅ ባሻገር*

**1፡19** ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የራዕይ መጽሐፍን ለመተርጎም እንደ ፈርጅ ነው። እርሱም እንደ ሁለትዮሽ ወይም ሦስትዮሽ ራዕይ ተደርጎ ነው። የግሪኩ ሐረግ ሁለትዮሽ ገለጻ ነው፣ አሁን ያለውና ወደፊት የሚሆነው። ዮሐንስ ስለ ራሱ ዘመን ነበር የተናገረው እንደዚሁም ለመጻዒው። ይህ መጽሐፍ ሁለቱንም ገጽታዎች ይደባልቃል፣ በተለምዷዊው ትንቢታዊ መልክ፣ የወቅቱን ሁነት ንግር በማድረግ፣ ለፍጻሜ ዘመን ሁነቶች። ይህ መጽሐፍ የዮሐንስ ቀንን ስደት ይገልጻል፣ እንዲሁም የእያንዳንዱን ዘመን ስደት፣ ግን ደግሞ በመዳረሻው የመጨረሻውን ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚን ስደት (ዳን. 9:24-27፤ II ተሰሎንቄ 2)።

**1፡20 "የከዋክብቱ ምሥጢር"** ይህ ቃል (*mustērion*) በብዙ መልኩ በጳውሎስ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ሁሉም ግን በዘላለማዊነት ይዘመዳሉ፣ ግን የተደበቀ የእግዚአብሔር ዕቅድ፣ ለሰዎች ደኅንነት፣ ይኸውም የሚያምኑ አይሁድና አሕዛብ በአንድ አዲስ አካል በክርስቶስ ይተባበራሉ (ኤፌ. 2:11-3:13)። እዚህ፣ ሆኖም፣ ጥቅም ላይ የዋለ የሚመስለው ከሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት ጋር በተያያዘ ነው፣ ኢየሱስ ምዕራፍ 2 እና 3 ላይ የተናገራቸው። ቁጥር 20 ላይ በግልጽ እንደምንመለከተው ሰባቱ መናፍስት፣ ሰባቱ ከዋክብት፣ ሰባቱ የወርቅ መቅረዞች፣ እና ሰባቱ መላእክት ሁሉ ተምሳሌታዊ ናቸው፣ በሆነ መልኩ ለሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት። ይህ ቃል 17፡7 ላይ ላለው ተምሳሌት ሽሽግ ፍቺ በተመሳሳይ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። ልዩ ርዕስ 10፡7 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"መላእክት"** የግሪኩ (*aggelos*) እና የዕብራይስጡ (*malak*) ቃላት "መልእክተኞች" ወይም "መላእክት" ተብለው ሊተረጎሙ ይችላሉ። በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች እንደየመለያዎቻቸው ይገኛሉ።

1. አንዳንዶች የሚሉት፣ እነርሱ ሰባቱ መናፍስት ናቸው ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሱት።
2. ሌሎች የሚሉት የእነዚህ አብያተ-ክርስቲያናት መጋቢዎች ነበሩ (ሚል. 2፡7)።
3. ሌሎች የሚሉት፣ የሚያመለክተው የእነዚህ ቤተ-ክርስቲያኖች ጠባቂ-መልአክን ነው (ዳን. 10:13፤20፤21)።

የተሻለ የሚመስለው እነሱ የሚያመለክቱት የእነዚህን ቤተ-ክርስቲያኖች እንደ አጠቃላይ ሰውኛነት ነው፣ በመጋቢ ተምሳሌት ቢሆን ወይም በመልአክ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ምዕራፍ 1 አንዳች ፍንጭ ይሰጥሃልን፣ የራዕይ መጽሐፍን ለመተርጎም? ከሆነስ ምን ናቸው?
2. የራዕይ መጽሐፍ በቀዳሚነት ለራሱ ዘመን ነው ወይስ ለመጨረሻው ዘመን? እንዴት?
3. ዮሐንስ ከብሉይ ኪዳን ለምን በርካታ ጠቃሽ አደረገ፣ ግን በቀጥታ ከእሱ ሳይጠቅስ?
4. በዚህ ምዕራፍ ላይ ለምን እጅግ በርካታ መጠሪያዎች ለእግዚአብሔር ተደረጉ?
5. ቁ. 12-20 ያሉት መግለጫዎች እያንዳንዱን ሰባቱን አብያተ-ክርስቲያናት ለማስተዋወቅ በምዕራፍ 2 እና 3 ለምን ጥቅም ላይ ዋሉ?
6. የከበረው ኢየሱስ እጅግ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ዳን. 10 ላይ እንደሚገኘው መልአክ ተገለጠ?

# ራዕይ 2 – 3
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የኤፌሶን መልእክት<br>2:1ሀ<br>2:1ለ-7 | ፍቅር አልባዋ ቤተክርስቲያን<br>2:1-7 | የመጀመሪያው መልእክት<br>2:1<br>2:2-7 | የኤፌሶን መልእክት<br>2:1ሀ<br>2:1ለ-7ሀ<br>2:7ለ | ኤፌሶን<br>2:1-7 |
| መልእክት ለሰምርኔስ<br><br>2:8ሀ<br>2:8ለ-11 | የተሰደደችው ቤተክርስቲያን<br>2:8-11 | ሁለተኛው መልእክት<br><br>2:8<br>2:9-11 | መልእክት ለሰምርኔስ<br>2:8ሀ<br>2:8ለ-10<br>2:11ሀ<br>2:11ለ | ሰምርኔስ<br><br>2:8-11 |
| መልእክት ለጴርጋሞን<br>2:12ሀ<br>2:12ለ-17 | ተጋላጭዋ ቤተክርስቲያን 2:12-17 | ሦስተኛው መልእክት<br>2:12<br>2:13-17 | መልእክት ለጴርጋሞን<br>2:12ሀ<br>2:12b-16<br>2:17ሀ<br>2:17ለ | ጴርጋሞን<br>2:12-13<br>2:14-17 |
| መልእክት ለትያጥሮን<br><br>2:18ሀ<br>2:18ለ-29 | የተበላሸችው ቤተ ክርስቲያን<br>2:18-29 | አራተኛው መልእክት<br><br>2:18<br>2:19-29 | መልእክት ለትያጥሮን<br>2:18ሀ<br>2:18ለ-23<br>2:24-28<br>2:29 | ትያጥሮን<br><br>2:18-29 |
| መልእክት ለሰርዴስ<br>3:1ሀ<br>3:1ለ-6 | ሙቷ ቤተክርስቲያን<br>3:1-6 | አምስተኛው መልእክት<br>3:1ሀ<br>3:1ለ-6 | መልእክት ለሰርዴስ<br>3:1ሀ<br>3:1ለ-5<br>3:6 | ሰርዴስ<br>3:1-6 |
| መልእክት ለፊልድልፍያ<br>3:7ሀ<br>3:7ለ-13 | ታማኟ ቤተክርስቲያን<br>3:7-13 | ስድስተኛው መልእክት<br>3:7<br>3:8-13 | መልእክት ለፊልድልፍያ<br>3:7ሀ<br>3:7ለ-12<br>3:13 | ፊልድልፍያ<br>3:7-13 |
| መልእክት ለሎዶቅያ<br><br>3:14<br>3:14ለ-22 | ለስ ያለችው ቤተክርስቲያን<br>3:14-22 | ሰባተኛው መልእክት<br><br>3:14<br>3:15-22 | መልእክት ለሎዶቅያ<br>3:14ሀ<br>3:14ለ-21<br>3:22 | ሎዶቅያ<br>3:14-22 |

**የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## አጠቃላይ ዳራ

ሀ. ይህ ጽሑፋዊ ምድብ (ምዕራፍ 2-3) ለያህዌ በብኪ ከተሰጡት መጠሪያዎች ጋር የተያያዘ ነው፣ ለመሲሕ ጥቅም ላይ ከዋሉት (ዝከ. 1፡12-20)። ይህም አንደኛው መንገድ ነው የአኪ ደራስያን የኢየሱስን መለኮትነት ያረጋገጡበት። የዮሐንስ ራዕይ የያህዌን የብሉይ ኪዳን መጠሪያዎችና ድርጊቶችን ወደ ኢየሱስ አስተላለፈ፣ ያረገው፣ የከበረው መሲሕ።

ለ. ዓላማውም እነዚህ የአንደኛው ክፍለ ዘመን አብያተ ክርስቲያናት የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊ መሻት ማሳየት ነው፣ በምስያም ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት (ማለትም፣ ቁጥር ሰባት)። የዮሐንስ አገልግሎት በሽምግልና ጊዜው በትንሹ እስያ ነበር፣ በተለይም በኤፌሶን። ዮሐንስ እርግጥ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናትና ከተማዎቹን በደንብ ያውቃል። እነዚህ መልእክቶች የክርስትናን ሥነ-ምግባራዊ ገጽታ ያሳያሉ። እነሱ ለታማኝነትና ለመልካምነት ጥሪ ናቸው። ቤተ ክርስቲያንም ይፈረድባታል (2 ቆሮ. 5፡10)።

ሐ. በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ፣ በትንሹ እስያ በሮሜ ግዛት፣ በዮሐንስ ጊዜ። ደራሲው ለሰባቱ ብቻ ለምን ጻፈ?

1. እሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቁጥር ነው፣ ለፍጽምና (ዘፍጥረት 1)። ሰባት ላይ በርካታ ጽሑፋዊ መዋቅሮች አሉ፣ በዮሐንስ ትንቢት።
2. እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የጉዞ መስመር አዘጋጅተዋል፣ ከኤፌሶን አንሥቶ ሎዶቅያ ላይ የሚያበቃ። እሱም የንጉሡ የመልእክት መስመር ሊሆን ይችላል።
3. እነርሱ በተወሰነ መልኩ በማንኛውም ጊዜና ባህል ሊገኙ የሚችሉትን አብያተ-ክርስቲያናትን ሊወክሉ ይችላሉ።

መ. የዚህ ጽሑፋዊ ምድብ ጠቀሜታ አሁን ለእኛ ምንድነው?

1. አንዳንዶች እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት እንደ ትንቢታዊ መግለጫ ይተረጉሟቸዋል፣ ለምዕራባዊ ታሪክ፣ ከጰንጠቆስጤ እስከ ዳግም ምጽዓቱ ድረስ
   ሀ. ኤፌሶን = ሐዋርያዊ ጊዜ፣ 33-100 ዓ.ም (ከጰንጠቆስጤ እስከ ዮሐንስ)
   ለ. ሰምርኔስ = የስደት ጊዜ፣ 100-313 ዓ.ም (ከዮሐንስ እስከ ቆስጠንጢኖስ)
   ሐ. ጴርጋሞን = የቆስጠንጢኖስ ጊዜ 313-590 ዓ.ም (ከቆስጠንጢኖስ እስከ ግሪጎሪ)
   መ. ትያጥሮን = የሮም ጳጳስ፣ 590-1517 (ከግሪጎሪ እስከ ሉተር)
   ሠ. ሰርዴስ = ተሐድሶ፣ 1517-1792 (ሉተር - ኬሪ)
   ረ. ፊልድልፍያ = ዘመናዊው የሚሲዮን ንቅናቄ፣ 1792-1914 (ከኬሪ እስከ መነጠቅ)
   ሰ. ሎዶቅያ = የክህደት ጊዜ፣ 1914 - ዳግም ምጽአት (አዓጦ WWI - ዳግም ምጽዓት)

   ይህ በአንጻራዊ መልኩ የቅርብ የትርጓሜ ፈርጅ ነው፣ እሱም ጠባይ አድርጎ የመጣው "ቅድመ ሚሊኒየም ከፋይ" ሲሆን (ዘወትር የሚመለከተውም ማቴዎስ 13ን ከ7ቱ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ትይዩ በማድረግ ነው)። ሆኖም፣ በራሱ በጽሑፉ ውስጥ ይህንን አመለካከት የሚያጸና የለም። ምንም እንኳ አንዳንድ ምዕራባዊ ታሪክ ገጽታዎች ከዚህ አባባል ጋር ቢስማሙም፣ ሌሎች ግን አይገጥሙም። መጽሐፍ ቅዱስ በተናጠል ከምዕራብ ባህል ጋር ብቻ እንዲገጥም አድርጎ ማስረገጥ አላዋቂነት ነው። ይህ አባባል ለአንደኛው ክፍለ ዘመን ምዕመናን ትርጉም አልባ ነው።
2. አንዳንዶች እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት የሚተረጉሟቸው በሁሉም ዘመንና ባህል ሊገኙ የሚችሉትን የቤተ ክርስቲያን ዓይነቶች ወካይ ናሙና አድርገው ነው።

ሠ. አንደኛው የረዳኝ መጽሐፍ፣ ትንቢትን/አፖካሊፕታዊ ለመተርጎም የረዳኝ ዲ. ብሬንት ሳንዲ፣ *የማረሻ ጫፍ እና መቀረጫ ማጭድ፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢትና አፖካሊፕትን ቋንቋ ዳግመኛ ማሰብ* ነው። እሱም አስደናቂ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ ነጥብ ያቀርባል፣ ስለ ስለ ታመኑ አማኞች የተደረጉትን ተስፋዎች፣ ምዕራፍ 2-3 (ገጽ 28-32)። ተስፋዎቹን እንዲህ ይዘረዝራል፡

1. የሕይወት ዛፍ
2. የሕይወት አክሊል
3. ነጭ ድንጋይ
4. በሕዝቦች ላይ ሥልጣን
5. የንጋት ኮከብ
6. ነጭ ልብስ መልበስ

7. በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ዐምድ
8. የእግዚአብሔር ስም
9. የኢየሩሳሌም ስም
10. በእግዚአብሔር ዙፋን መቀመጥ

እሱ የሚለው እነዚህ በጥሬው ወይም በተናጠል ይተረጎማሉ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን እንደ አጠቃላይ ፍጻሜ እንጂ፣ በ21፡3 ላይ እንደታየው። እኔም ይህ ለዚህ ዘውግ ተገቢ የሆነ የትርጓሜ አገባብ እንደሆነ አስባለሁ።

## የሰባቱ መልእክቶች መዋቅራዊ አንድነት

ሀ. አብዛኞቹ አታቾች የሰባት ነገሮች መዋቅር በአብዛኞቹ መልእክቶች ላይ ይመለከታሉ፣ ምንም እንኳ ሰባቱም ሁሉ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ላይ ባይኖሩም።

1. የኢየሱስ የተለመደ የአድራሻ ጥቅሻ "ለ---------------- ቤተ ክርስቲያን መልአክ ጻፍ..." (ዝከ. 2፡1፣8፣12፣18፤ 3፡1፣7፣14)።
2. የኢሱስ ገለጻ ከ1፡12-20 የተወሰደ፣ እነርሱም የብሉይ ኪዳን የያህዌ መጠሪያና ድርጊቶች የሆኑ፣ እያንዳንዱን መልእክት ያስተዋውቃሉ።
3. የኢየሱስ እውቀት፣ ስለ ቤተ-ክርስቲያኖቹ፣ በአዎንታም ሆነ በአሉታ፣ "አውቃለሁ..." (ዝከ. 2፡2፣፣ 9፣13፣19፤ 3፡1፣8፣ 15)።
4. ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኖቹ ይናገራል፣ ለባህላቸው፣ ለመልከዓ ምድራዊ እና መንፈሳዊ አጋጣሚዎች።
5. ኢየሱስ ይናገራል፣ ስለ ድንገተኛ፣ በቅርብ ስለመመለሱ፣ በጊዜያዊ ፍርድም ሆነ ስለ ዳግም ምጽአቱ፣ (ዝከ. 1፡1፣3፤ 2፡5፣ 16፣25፤ 3፡3፣11)።
6. ኢየሱስ መንፈሳዊ ማድመጥንና መረዳትን አሳስቧል (ዝከ. 2፡7፣11፣17፣29፤ 3፡6፣13፣22)። እየሱስ ተጠቅሟል "ጆሮ ያለው፣ ይስማ" በወንጌላት (ማቴ. 11፡15፣ 13፡9፣ 43፤ ማርቆስ 4፡24፡)
7. ኢየሱስ ለታማኝ ተከታዮች ሽልማት እንዳለ ቃል ገብቷል (ዝከ. 2፡7፣11፣17፣25-26፤ 3፡4-5፣11-12፣21)።

እነዚህ ሰባት ደረጃዎች በእያንዳንዱ መልእክቶች ቋሚ አይደሉም። ቅደም ተከተሉ ይለወጣል አንዳንድ ነገሮችም በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ተትተዋል፣ ነገር ግን በጥቅሉ ይህ አወቃቀር የሚያሳየው ከብዙዎቹ የዮሐንስ ሰባትዮሽ ጽሑፋዊ አወቃቀር አንዱን ነው።

## መልእክቶቹ የተመለከቱባቸው ከተሞች

ሀ. ኤፌሶን

1. ትልቁ ከተማ ነበር፣ በትንሹ እስያ በሮሜ ግዛት። ዋና ከተማ አልነበረም፣ ምንም እንኳ የሮሜ ገዥ እዚያ ቢኖርም። የንግድ ማዕከል ነበር፣ ግሩም ከሆነው የተፈጥሮ ወደቡ የተነሣ።
2. ነጻ ከተማ ነበር፣ አገረ ገዥ እንዲኖረው የተፈቀደለትና ብዙ ነጻነቶች ያሉት፣ የሮሜ ወታደሮች የጦር ሰፈር የሌለው ከመሆኑ ጭምር።
3. ብቸኛው ከተማ ነበር፣ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረገውን የእስያ ስፖርት ውድድር ለማካሄድ።
4. በአርጤምስስ ቤተ መቅደስ ክልል ነበር (በላቲን ዲያና)፣ እሱም በጊዜው ከዓለም ሰባቱ ድንቆች አንዱ የነበረ። እሱም 425'X220' በ127 ዐምዶች 60' ቁመት ያላቸው ነበር፤ 86ቱ በወርቅ ተለብጠው ነበር (የፐሊኒ ታሪክ 36፡95 ተመልከት)። የአርጤምስስ ምስል ተወርዋሪ ኮከብ ያለው ባለ ትልቅ ጡት የሴት አምሳያ እንደነበረ ይገለጻል። ይህም ማለት በርካታ ባዕድ አምልኳዊ ጋለሞቶች በከተማው እንደነበሩ ያሳያል (ሐዋ. 19)። እሱ እጅግ ሞራሉ የወደቀ፣ ባለ ኅብረ-ባህል ከተማ ነበር።
5. ጳውሎስ በከተማው ከሦስት ዓመት በላይ ቆይቷል (ሐዋ. 18፡18፤ 20፡13)።
6. ወግ እንደሚያስረግጠው የዮሐንስ መኖሪያ መሆኑን ነው ማርያም በፍልስጥኤም ከሞተች በኋላ።

ለ. ሰምርኔስ

1. ተመሠረተ የሚባለው በአማዞን ነበር (ጠንካራ የሴት መሪ) ሰምርኔ የምትባል። በዮሐንስ ጊዜ 200,000 ያህል ሰው ይኖርባታል።
2. በኤጂያን ባሕር ክልል ነበር። አመቺ የሆነ የተፈጥሮ ወደብ ነበረው፣ እናም የንግድ ማዕከል ነበር፣ በትንሹ እስያ በኤፌሶን ብቻ የሚበለጥ። እጅግ ባለጠጋ ከተማ ነበር።
3. በ600 ዓ.ዓ በሊዲያኖች ነው የተደመሰሰው፣ ግን በሊሲሚከስ ዳግም ተገነባ፣ የታላቁ እስከንድርን ዕቅድ ተከትሎ፣ የባሕሩ ነፋስ በየአደባባዩ እንዲነፍስ።
4. እሱም ደግሞ ነጻ ከተማ ነበር፣ የሮሜ ወታደሮች እንዲያፈገፍጉ ስለ ረዳ፣ በሜዝራዳተስ ከተሸነፉ በኋላ።
5. የሮሜ ጣዖት ማምለኪያ ማዕከል ነበር (195 ዓ. ዓ) እና የንጉሥ አምልኮ። እሱም ለአጼ ጥብርዮስ የመጀመሪያው ቤተ-መቅደስ ነበረው (26 ዓ.ም)።
6. ሃይማኖታዊ ማዕከል ነበር፣ የሲቢሊ እና የሆሜር ቤተ-መቅደስ የአምልኮ ስፍራ። ወግም ነበር፣ ሆሜር እዚያ ለመወለዱ። በርካታ ቤተ-መቅደሶቹም ፓጎስ በሚባለው አክሮፖሊስ ስፍራ ላይ ነበሩ፣ በወርቃማ መንገድ፣ በዜውስ እና ሲቢሊ ቤተ-መቅደስ መካከል።
7. በርካታ ጸረ-ክርስቲያን የአይሁድ ሕዝብ ነበረበት
8. ከተማውም ፖሊካርፐ (ሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ-መዝሙር) መሥዋዕት የሆነበት ነው 155 ዓ.ም።

ሐ.ጴርጋሞን

1. ትልቅ ሃብታም ከተማና የትንሹ እስያ ዋና ከተማ ነበር (282 ዓ.ም ጀምሮ)፣ ምንም እንኳ በዋነኛው የንግድ መስመር ላይ ባይሆንም።
2. ትልቁ ቤተ መጻሕፍት በሮሜ ዓለም፣ ከአሌክሳደርያ፣ ግብፅ ውጭ እንዳለው ይመካል። ከ200,000 በላይ የብራና ጥቅሎች ነበሩት!
3. ብራና እዚህ ነበር የተፈጠረው። የእንስሳትን ቆዳ ለመጻፊያ በማዘጋጀት። ይህ መጻፊያ የተዘጋጀው አሌክሳንደሪያ፣ ግብፅ ፓፒረስ ወረቀት ለመሸጥ እምቢ እሰላች ነው። ይህም ንጉሣቸው ኢዩሜነስ II (197-159 ዓ.ዓ) የአሌክሳንደራዊውን ቤተ-መጻሕፍተኛ፣ አሪስቶፋነስን ለመቅጠር በመሞከሩ ነው። የፕቶሌማዊው ንጉሥ፣ ኢፒፋነስ (205-182 ዓ.ዓ) የአሌክሳንደሪያው በደረሰበት ጊዜ፣ ቤተ-መጻሕፍተኛውን አስሮ ፓፒረስ ወደ ጴርጋሞን እንዳይሄድ አገደ። በእነዚህ ሁለት የትምህርት ማዕከላት የምር ባላንጣነት ነበር። ኋላ ላይ አንቶኒ የጴርጋሞንን ላይብረሪ ወደ አሌክሳንደሪያ ላከ፣ በስጦታ መልክ ለክሊዎፓትራ።
4. እሱም የሐኪሙ የጋለን አገር ነበር፣ እንዲሁም የአስክሊፒኦስ የፈውስ ጥበብ ማዕከል። እንዲያውም አስክሊፒኦስ "የጴርጋሞን ጣዖት" ይባል ነበር። የዚህ ጣዖት ምልክትም እባብ ነበር።
5. እሱም ደግሞ የሮሜና የአጼ አውግጦስ ቤተ-መቅደስ ነበረበት (29 ዓ.ም) እንዲሁም የአጼው የአምልኮ ተከታዮች የአስተዳደር ማዕከል (*neokopros*) ነበር። ለሮሜ ያለው ታማኝነት እጅግ የታወቀ ነበር።
6. እሱም የግሪክን አማልክት በማምለክና በመከላከል የታወቀ ነበር። ለዜውስ ትልቅ ቤተ-መቅደስ ነበር፣ ተከተማው ወጣ ያለ ሆኖ ሞላውን ከተማ የሚያሳይ። ቅርጹም እንደ ዙፋን ነበር (ማለትም፣ የሰይጣን ዙፋን)።

መ. ትያጥሮን

1. ትንሹ የንግድ ከተማ ነበር። በርካታ መዛግብት ይገኛሉ ለበርካታና ለተደራጁ የንግድ ማኅበረሰቦች፣ እያንዳንዳቸውም የራሱ ተመራጭ አማልክት ያሉት። የተቆረቆረውም በጴርጋሞንና ሰርዴስ መካከል ባለው አውራ መንገድ ላይ ሆኖ እስከ ፊልድልፍያና ሎዶቅያ ይዘልቃል። በሱፍ ምርቱ ዝነኛ ነው። ሊዲያ (ሐዋ 16፡14)፣ የሐር ልብስ ሻጪ፣ ከዚህ ከተማ ነበረች።
2. እያደገ የመጣውም በሴሉከስ ኒካትዮ ነው፣ እሱም የመቄዶንያ ወታደሮቹን እዚህ ስላሰፈረ።
3. በርካታ ቤተ-መቅደሶች ለአጥቢያ አማልክት ነበሩት
   ሀ. ታይሪምኖስ (አፖሎ) - የፀሐይ አምላክ
   ለ. አርጤምስ (ዲያና) - የፍቅር ጣዖት
   ሐ. ሲቢል ሳምባዚ - የአጥቢያ የሴት ጠንቋይ

ሠ. ሰርዴስ

1. እሱ ትልቅ፣ ሃብታም ጥንታዊ ከተማ ነበር። እሱ ለዓመታት የሊዲያ ኢምፓየር ሀብታም ከተማ ነበር፣ ባስገራሚ ወታደራዊ ስፍራው ምክንያት፣ 1500 በተራራ ጫፍ ላይ። እሱም በፋርስ መዛግብት ውስጥ ተጠቅሷል፣ ታላቁ ሳይረስ ከተማዋን በመያዙ ምክንያት። እንዲሁም በአብድዩ ቁ. 20 ላይ ተጠቅሷል። እሱም በዮሐንስ ጊዜ እጅግ ወድቆ ነበር።
2. እሱም በቀለመ የሱፍ ምርቶቹ ይታወቃል። ሂደቱ እዚያ ነው የተፈለሰፈው፣ እነሱም እንደዚያ ነው የሚያስረግጡት።
3. የሲቢሊ፣ እናት አማልክት የማምለኪያ ማዕከል ነበር። የመቅደሱ ፍርስራሽ በከተሞች አሁንም ይታያል። የዚህ አምልኮ መስፋፋት በመላው የሮሜ ግዛት የታወቀና ተቃውሞ ያስነሣ ነበር።

ረ. ፊልድልፍያ

1. እሱም በዐምባ ላይ ተቆርቁሮ በውኃ የተጠበቀ ነበር። ይህም እጅግ ተፈላጊ ወታደራዊ ስፍራ አድርጎታል። እሱም ከሰባቱ ከተሞች አዲሱ ነበር። የተቆረቆረውም በአታሉስ II ነው (159-138 ዓ.ዓ)።
2. እሱም ወደ ሰርዴስ በሚወስደው ዋነኛ የንግድ መስመር ላይ ነው የተቆረቆረው፣ ተስፋፍቷልም።
3. እሱም በተዋበ የእርሻ ስፍራ ላይ ነው፣ በተለይም ወይን። ባከስ፣ ወይም ዲዮኒሰስ ጣዖት አንደኛው አለቃ አማልክቱ ነበር። እሱም የመሬት መንቀጥቀጥ በሚሆንበት ስፍራ ሲሆን፣ በ17 ዓ.ም በነበረው ትልቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ወድሟል፣ እንዲሁም ሌሎች አስር ትልልቅ የአካባቢዎቹን ከተሞችን የደመሰሰ። ሆኖም፣ እንቅጥቅጡ በዚህ አካባቢ ቀጥሎ ሕዝቡም ወደ አካባቢው ገጠር ተዛወረ።
4. እሱም የአጼው አምልኮ ማዕከል ነበር (እንደ ሰምርኔስ እና ጴርጋሞን) ይኸውም የአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት በወረዳዎቹ የነበረው ስደት መነሻ ሊሆን ይችላል።
5. እሱም የሔለናዊው ባህል ዋነኛ ማዕከል ነበር፣ ተጽዕኖውን በኃይል የሚያስፋፋው። ለዚሁም ዓላማ ተብሎ በሚስያ፣ ሊድያ እና ጴርጋ ወሰን ጋ የተቆረቆረ ይመስላል።

ሰ. ሎዶቅያ በሊከስ ወንዝ

1. እሱም በሊከስ ወንዝ ሸለቆ ካሉት ከተሞች አንዱ ነው (ሌሎቹ ከተሞች ቆላስያስ እና ሒራፖሊስ ነበሩ)። አብያተ ክርስቲያናት በእነዚህ ሦስት ከተሞች ተቋቁመዋል፣ በጳውሎስ በተለወጠው፣ ኤጳፍራ (ቆላ. 1፡17፤ 4፡12-13)።

2. የተቆረቆረውም በሴሉሲድ ገዥ፣ በአንቲከስ II ነው፣ እሱም በሚስቱ ስም የሰየመው፣ ሎዲሲ፣ በ250 ዓ.ዓ። እሱም የተቋቋመው በወታደራዊ መከላከያ ስፍራ ነው፣ እንደ ፊልድልፍያ።
3. ስፍራውም በዋነኛው ምስራቅ/ምዕራብ የንግድ መስመር ላይ ነው። የንግድ ማዕከል እንደነበር ተመዝግቧል።
4. ስፍራውም በለም የእርሻና የከብት ማርቢያ ክልል ነው፣ በተለይም የተለዩ ጥቋቁር በጎችን በማርባት በዓለም ዙሪያ ይታወቃል። በብዛት የሚመረተውም ጥቁር መደረቢያ "ትሪሜታ" ይባላል።
5. በጣም በርካታ የአይሁድ ሕዝብ አሉበት።
6. እሱ፣ እንደ ጴርጋሞን፣ የፈውስ ጣዖቱ አስክሊፒዮስ የማምለኪያ ማዕከል ነበር። ከተማው የሕክምና ትምህርት ቤት ነበረው፣ የጆሮና የዓይን መድኃኒት እንደነበረውም ተመዝግቧል።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

> ***ራዕይ፡ 2፡1***
>
> **[1] በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት የያዘው በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው እንዲህ ይላል፡**

**2፡1 "*መልአኩ*"** በዕብራይስጥና በግሪክ ቃል መልአክ ማለት መልክተኛ ነው። የሚያመለክተውም
1. መጋቢ (ሚል. 2፡7)
2. የቤተ ክርስቲያን መልአክ (ዳንኤል 10)
3. የተለየ መንፈስ ወይም የአንድ ማኅበረ ምዕመናን መገለጫ

ይኸው ተመሳሳይ ሐረግ እያንዳንዱን መልእክት ያስተዋውቃል (ዝክ. 2፡1፣ 8፣ 12፣ 18፤ 3፡1፣ 14)።

▣ **"ቤተ ክርስቲያን"** የግሪክ ድብልቅ ቃል *ekklesia* የሁለት ግሪክ ቃላት ድብልቅ ነው፣ "መውጣት" እና "መጥራት።" እሱም በሴፕቱዋጂንት *qahal* ወይም "የእስራኤል ማኅበር" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ይተረጉማል። የጥንት ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለመጥራት ይጠቀሙበታል፣ ምክንያቱም
1. ራሳቸውን እንደ እስራኤል፣ እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ በመቁጠራቸው
2. ራሳቸውን በእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥሪ እንዳላቸው ስለሚቆጥሩ፣ ለደኅንነት እና ለአገልግሎት

ልዩ ርዕስ 1፡4 ላይ ተመልከት።

▣ **"ሰባቱን ከዋክብት የያዘ"** ይህ የኢየሱስ መግለጫ ነው፣ ከ1፡16 የተወሰደ። እነዚህ ሰባት ከዋክብት ቤተ ክርስቲያኖችን ያመለክታሉ (ዝክ. 1፡20)። "ያያዘ" የሚለው ቃል (የአሁን የድርጊት አንቀጽ) የሚናገረው ጽኑ የሆነ፣ ርግጠኛ መያዝን ነው (ዮሐንስ 10፡28)። ምንም ነበርና ማንም እነዚህን ቤተ ክርስቲያኖች ከኢየሱስ ሊለያቸው አይችልም (ሮሜ 8፡31-39) የገዛ ራሳቸው የንስሐ እምቢተኝነት እና እሱን አለመከተል ካልሆነ በቀር! ያለማመን ብቻ ነው መለየት የሚችለው።

▣ **"በቀኝ እጁ"** ይህ ሰውኛ አገላለጽ ነው (ስለ እግዚአብሔር በሥጋዊ ቋንቋ መናገር) ለኃይልና ለሥልጣን ዘይቤ (ዝክ. 1፡16፣17፣20፤ 2፡1፤ 5፡1፣7)።

▣ **"መካከል የሚሄደው"** ይህ ሰውኛ ዘይቤ በዘፍ. 3፡8 ጥቅም ላይ ውሏል፣ እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር ስለመገኘቱ እንደ ተምሳሌት (ሌዋ. 26፡12)።

> **ልዩ ርዕስ፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ተገልጧል (አንትሮፖሞርፊያዊ ቋንቋ)**
>
> I. ይህ ዓይነቱ ቋንቋ በብሉይ ኪዳን በጣም የተለመደ ነው (ጥቂት ምሳሌዎች)
>
> ሀ. የሥጋዊ አካል ክፍሎች
> 1. ዓይኖች - ዘፍ. 1:4፣31፤ 6:8፤ ዘጸ. 33:17፤ ዘኁ. 14:14፤ ዘዳ. 11:12፤ ዘካ. 4:10
> 2. እጆች - ዘጸ. 15:17፤ ዘኁ. 11:23፤ ዘዳ. 2:15
> 3. ክንድ - ዘጸ. 6:6፤ 15:16፤ ዘዳ. 4:34፤ 5:15፤ 26:8
> 4. ጆሮዎች - ዘኁ. 11:18፤ I ሳሙ. 8:21፤ II ነገሥ. 19:16፤ መዝ. 5:1፤ 10:17፤ 18:6
> 5. ፊት - ዘጸ. 33:11፤ ዘኁ. 6:25፤ 12:8፤ ዘዳ. 34:10
> 6. ጣት - ዘጸ. 8:19፤ 31:18፤ ዘዳ. 9:10፤ መዝ. 8:3
> 7. ድምፅ- ዘፍ. 3:8፣10፤ ዘጸ. 15:26፤ 19:19፤ ዘዳ. 26:17፤ 27:10
> 8. እግሮች - ዘጸ. 24:10፤ ሕዝ. 43:7
> 9. በሰው መልክ - ዘጸ. 24:9-11፤ መዝ. 47፤ ኢሳ. 6:1፤ ሕዝ. 1:26

10. የእግዚአብሔር መልአክ - ዘፍ. 16:7-13፤ 22:11-15፤ 31:11፣13፤ 48:15-16፤ ዘጸ. 3:4፣13-21፤ 14:19፤ መሳ. 2:1፤ 6:22-23፤ 13:3-22

ለ. ሥጋዊ ድርጊቶች

1. የተፈጥሮ አድራጊ እንደሆነ የተናገረው - ዘፍ. 1:3፣6፣9፣11፣14፣20፣24፣26
2. መራመድ (ማለትም፣ ድምፁ) በዔድን - ዘፍ. 3:8፤ ሌዋ. 26:12፤ ዘዳ. 23:14
3. የኖኅን መርከብ በሩን መዝጋቱ - ዘፍ. 7:16
4. መሥዋዕቱን ማሽተቱ - ዘፍ. 8:21፤ ዘጸ. 29:18፣25፤ ሌዋ. 26:31
5. መውረድ - ዘፍ. 11:5፤ 18:21፤ ዘጸ. 3:8፤ 19:11፣18፣20
6. ሙሴን መቅበሩ - ዘዳ. 34:6

ሐ. ሰብዓዊ ስሜቶች (ጥቂት ምሳሌዎች)

1. መቆጨት/መጸጸት - ዘፍ. 6:6፣7፤ ዘጸ. 32:14፤ መሳ. 2:18፤ I ሳሙ. 15:29፣35፤ አሞጽ 7:3፣6
2. መበሳጨት - ዘጸ. 4:14፤ 15:7፤ ዘኍ. 11:10፤ 12:9፤ 22:22፤ 25:3፣4፤ 32:10፣13፣14፤ ዘዳ. 6:15፤ 7:4፤ 29:20
3. ቅናት - ዘጸ. 20:5፤ 34:14፤ ዘዳ. 4:24፤ 5:9፤ 6:15፤ 32:16፣21፤ ኢያሱ. 24:19
4. መጥላት/መጸየፍ - ሌዋ. 20:23፤ 26:30፤ ዘዳ. 32:19

መ. ቤተሰባዊ ቃላት (ጥቂት ምሳሌዎች)

1. አባት
   ሀ. የእስራኤል - ዘጸ. 4:22፤ ዘዳ. 14:1፤ ኢሳ. 1:2፤ 63:16፤ 64:8
   ለ. የንጉሥ - II ሳሙ. 7:11-16፤ መዝ. 2:7
   ሐ. ለአባታዊ ድርጊት ዘይቤ - ዘዳ. 1:31፤ 8:5፤ መዝ. 27:10፤ ምሳ. 3:12፤ ኤር. 3:4፣22፤ 31:20፤ ሆሴዕ 11:1-4፤ ሚል. 3:17
2. ወላጅ - ሆሴዕ 11፡1-4
3. እናት - መዝ. 27፡10 (በምታጠባ እናት ምሳሌ)፤ ኢሳ. 49:15፤ 66:9-13
4. ወጣት ታማኝ አፍቃሪ - ሆሴዕ 1-3

II. የዚህን ዓይነት ቋንቋ አጠቃቀም ምክንያቶች

ሀ. ለእግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች መግለጹ አስፈላጊ ስለሆነ። እግዚአብሔርን እንደ ወንድ የመውሰድ ጽንሰ ሐሳብ በስፋት የተሰራጨው የአንትሮፖሞርፊያዊነቱ ምክንያት እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ነው!

ለ. እግዚአብሔር ከሁሉ የተሻለ ትርጉም ያለውን የሰው ሕይወት ገጽታዎች ነው የሚወስደው፣ እናም ራሱን ለመግለጫነት ይጠቀምባቸዋል፣ ለወደቀው የሰው ልጅ (አባት፣ እናት፣ ወላጅ፣ አፍቃሪ)

ሐ. ምንም ቢያስፈልግ እንኳ እግዚአብሔር ራሱን በምንም ዓይነት አካላዊ ቅርጽ እንዲወሰን አይሻም (ዘጸዓት 20፤ ዘዳግም 5)

መ. መዳረሻው አንትሮፖሞርፊም የኢየሱስ ሥጋዌነት ነው! እግዚአብሔር ሥጋዊ ሆነ፣ የሚዳሰስ (1ኛ ዮሐንስ 1፡1-3)። የእግዚአብሔር መልእክት የእግዚአብሔር ቃል ሆነ (ዮሐንስ 1፡1-18)።

▣ **"የወርቅ መቅረዞች"** ይህ የአይሁድን ቤተ መቅደስ መቅረዝ አያመለክትም፣ ነገር ግን ለሰባቱ ቤተ ክርስቲያኖች ሌለኛ ተምሳሌት ነው (ዝከ. 1፡12-13)።

▣ **"ይላል"** የኢየሱስ የመጨረሻ ቃል ለቤተ ክርስቲያን ማቴ. 28፡18-20 ወይም ሐዋ. 1፡7-11 አይደለም፣ ራዕይ ምዕራፍ 2-3 እንጂ።

**ራዕይ፡ 2፡2-7**

**2 ሥራህንና ድካምህን ትዕግሥትህንም አውቃለሁ፤ ክፉዎችንም ልትታገሥ እንዳትችል፥ እንዲሁም ሳይሆኑ። ሐዋርያት ነን የሚሉቱን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ፤ 3 ታግሠህማል፥ ስለ ስሜም ብለህ ጸንተህ አልደከምህም። 4 ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና። 5 እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ። 6 ነገር ግን ይህ አለህ፤ እኔ ደግሞ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃልና። 7 መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።**

**2.2 "አውቃለሁ"** ዓይነቱ የተጠናቀቀ ድርጊት አመላካች ነው የ*oida*፣ የተተረጎመው ግን እንደ አሁን ነው። ኢየሱስ ያያል፣ ይገነዘባል፣ እናም ይጠነቀቃል፣ ለቤተ ክርስቲያኖቹ። የሚገደውም ለማጽናትና ለሥነ ሥነ ሥርዓት ነው (ይኸውም የወላጅ ፍቅር በመሰለ)። ይኸው ተመሳሳይ ሐረግ በሰባቱም መልእክቶች ላይ ተደግሟል (ዝከ. 2:2፤4፤13፤19፤ 3:1፤8፤15)።

የዚህ ቃል የብሉይ ኪዳን ዳራ የሚያመለክተው የቅርብ፣ ግላዊ ግንኙነት ነው (ዘፍ. 4:1፤ ኤር. 1:5)። )።

## ልዩ ርዕስ፡ ማወቅ (ባብዛኛው ዘዳግምን እንደ ምሳሌ በመጠቀም)

የዕብራይስጡ ቃል "ማወቅ" (ቢ.ዲ.ቢ. 393) በርካታ ትርጉም አለው (የትርጉም መስኮች) በዓይነቱ።

1. መልካምንና ክፉውን ለመረዳት - ዘፍ. 3:22፤ ዘዳ. 1:39፤ ኢሳ. 7:14-15፤ ዮናስ 4:11
2. በመረዳት ለማወቅ - ዘዳ. 9:2፤3፤6፤ 18:21
3. በልምድ ለማወቅ - ዘዳ. 3:19፤ 4:35፤ 8:2፤3፤5፤ 11:2፤ 20:20፤ 31:13፤ ኢያሱ. 23:14
4. ለመገንዘብ - ዘዳ. 4:39፤ 11:2፤ 29:16
5. በግል ለማወቅ
   ሀ. ግለሰብ - ዘፍ. 29:5፤ ዘጸ. 1:8፤ ዘዳ. 22:2 ፤33:9
   ለ. አምላክ - ዘዳ. 11:28፤ 13:2፤6፤13፤ 28:64፤ 29:26፤ 32:17
   ሐ. ያህዌ - ዘዳ. 4:35፤39፤ 7:9፤ 29:6፤ ኢሳ. 1:3፤ 56:10-11
   መ. ፆታዊ - ዘፍ. 4:1፤17፤25፤ 24:16፤ 38:26
6. የቀሰሙት ክህሎት ወይም እውቀት - ኢሳ. 29:11፤12፤ አሞጽ 5:16
7. ጥበበኛ መሆን - ዘዳ. 29:4፤ ምሳ. 1:2፤ 4:1፤ ኢሳ. 29:24
8. የእግዚአብሔር እውቀት
   ሀ. የሙሴ - ዘዳ. 34:10
   ለ. የእስራኤል - ዘዳ. 31:21፤27፤29

▣ ***"ሥራህንና ድካምህን"*** ይህ ንቁ ቤተ-ክርስቲያን ነበር፣ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ላለው ኅብረታቸው ቅድሚያ መስጠትን ዘንግተዋል (ዝከ. 2:4)። ከተሻለው ላይ በርካታ ነገሮች ወስደዋቸዋል (ገላ. 3:1)።

▣ ***"ትዕግሥት"*** ይህ ቃል የሚያመለክተው ፍቃደኛ የሆነ፣ ንቁ፣ የማይታጠፍ ጽናትን ነው። ይህ ዋነኛው የመጽሐፉ ጭብጥ ነው (ዝከ. 1:9፤ 2:2፤3፤19፤ 3:10፤ 13:10፤ 14:12)።

ትዕግሥት ከደኅንነት ጋር መመዛዘን አለበት (ዝከ. 2:7፤11፤17፤26፤ 3:5፤11-12፤21)። አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የሚቀርቡት በዲያሌክቲካዊ፣ አያዎ መሰል (ፓራዶክስ)፣ ጥንዶች ነው። ሁለቱም እኩል እውነት ናቸው፣ አንዳቸውም ግን ብቻቸውን እውነት እይደሉም። ደኅንነት የመነሻ ንስሐና እምነት ሆኖ በሕይወት ስልት ንስሐ፣ እምነት፣ ታዛዥነት፣ አገልግሎት፣ እና ጽናት የሚከተሉት ነው! ከሥር ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ጽናት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዶክትሪኖች ከክርስቲያን ሕይወት ጋር የተያያዙትን መግለጽ ያስቸግራል፣ ምክንያቱም የቀረቡት በተለይ በምስራቃዊ ዲያሌክቲካዊ ጥንዶች በመሆኑ። እነዚህ ጥንዶች የሚቃረኑ ይመስላሉ፣ ግን ሁለቱም ጫፎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው። የምዕራብ ክርስቲያኖች የሚያደርጉት አንድ እውነት መርጠው ተቃራኒውን እውነት ይተዉታል ወይም ያንኳስሱታል። ምሳሌዎች፡

1. ደኅንነት በክርስቶስ ለማመን መነሻ ውሳኔ ነው ወይስ የሕይወት ዘመን ወሳኔ ደቀ መዝሙርነት?
2. ደኅንነት ከሉዓላዊው እግዚአብሔር የሚሆን በጸጋ መመረጥ ነው ወይስ የእምነትና ንስሐ ምላሽ በሰው ልጅ በኩል፣ ለመለኮት የሚቀርብ?
3. ደኅንነትን አንዴ ከተቀበሉ መጥፋት አይቻልም ወይስ ቀጣይነት ያለው ተግባር ያስፈልገዋል?

የጽናት ጉዳይ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ አወዛግቧል። ችግሩ የሚነሣው ከአኪ የሚጋጩ ምንባቦች ይመስላል፡

1. በዋስትና ላይ ጽሑፎች
   ሀ. የኢየሱስ ንግግሮች በዮሐንስ ወንጌል (ዮሐንስ 6:37፤ 10:28-29)
   ለ. የጳውሎስ ንግግሮች (ሮሜ. 8:35-39፤ ኤፌ. 1:13፤ 2:5፤8-9፤ ፊሊጵ. 1:6፤ 2:13፤ II ተሰ. 3:3፤ II ጢሞ. 1:12፤ 4:18)
   ሐ. የጴጥሮስ ንግግሮች (1ጴጥ. 1:4-5)
2. በጽናት አስፈላጊነት ላይ ጽሑፎች
   ሀ. የኢየሱስ ቃል በቀዳሚዎቹ ወንጌላት (ማቴ. 10:22፤ 13:1-9፤24-30፤ 24:13፤ ማርቆስ 13:13)
   ለ. የኢየሱስ ቃል በዮሐንስ ወንጌል (ዮሐንስ 8:31፤ 15:4-10)

ሐ. የጳውሎስ ቃል (ሮሜ. 11:22፤ 1 ቆሮ. 15:2፤ 11 ቆሮ. 13:5፤ ገላ. 1:6፤ 3:4፤ 5:4፤ 6:9፤ ፊሊጵ. 2:12፤ 3:18-20፤ ቆላ. 1:23፤ 11 ጢሞ. 3:2)

መ. የዕብራውያን ደራሲ ቃል (2:1፤ 3:6፣14፤ 4:14፤ 6:11)

ሠ. የዮሐንስ ቃል (1 ዮሐንስ 2:6፤ 11 ዮሐንስ 9፤ ራዕ. 2:7፣17፣26፤ 3:5፣12፣21፤ 21:7)

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ደኅንነት የሚመነጨው በሦስትነቱ አንድ ከሆነው ሉዓላዊ አምላክ ፍቅር፣ ምሕረትና ጸጋ ነው። ማንም ሰው ያለ መንፈስ አነሣሽነት ሊድን አይችልም (ዮሐንስ 6:44፣65)። መለኮት ቀድሞ ይመጣና ሐሳቡን ያዘጋጃል፣ ግን ሰዎች በእምነትና በንስሐ ምላሽ እንዲሰጡ ይጠይቃል፣ በመነሻውም ሆነ በቀጣይነት። እግዚአብሔር በኪዳን ግንኙነት ከሰው ጋር ይሠራል። መታደሎችም ኃላፊነቶችም አሉ!

ደኅንነት የተሰጠው ለሰዎች ሁሉ ነው። የኢየሱስ ሞት የተያያዘው ከወደቀው ፍጥረት የኃጢአት ችግር ጋር ነው! እግዚአብሔር መንገድን ሰጥቷል፣ እናም በአምሳሉ የተፈጠሩት ሁሉ ለፍቅሩና በኢየሱስ ላደረገው ስጦታ ምላሽ እንዲሰጡ ይሻል።

በዚህ ርዕስ ላይ በተጨማሪ ለማንበብ ከፈለግህ

1. ዳሌ ሞዲ፣ የእውነት ቃል፣ ኢርድማንስ፣ 1981 (ገጽ 348-365)
2. ሃዋርድ ማርሻል፣ በእግዚአብሔር ኃይል መያዝ፣ ቤታኒ ፌሎሺፕ፣ 1969
3. ሮበርት ሻንክ፣ ሕይወት በልጁ፣ ዌስትኮት፣ 1961

መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ አካባቢ ሁለት ችግሮችን ይገልጻል፡ (1) ዋስትናን ያለ ፍሬ ለመሆን፣ ለግለኝነት እንደ ፍቃድ ወረቀት መውሰድ ወይም (2) ከአገልግሎትና ከግል ኃጢአት ጋር የሚታገሉትን ማበረታታት። ችግሩ፣ ስሕተት ያለባቸው ወገኖች ስሕተተኛውን መልእክት ወሰደው፣ በተወሰነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባቦች ላይ ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓቶችን ሲያቋቁሙ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች የዋስትናን መልእክት እጅግ ይፈልጉታል፣ ሌሎች ደግሞ ብርቱ የጽናት ማስጠንቀቂያ ይሻሉ! ከየትኛው ወገን ነህ?

ታሪካዊ ሥነ-መለኮታዊ ተቃርኖ አለ፣ አውግስቲን እና ፐሌጊዩስ እና ካልቪንና አርሚኒየስን (ከፊል ፐሌጂያዊ) ያካተተ። ጉዳዩ የሚያካትተው የደኅንነትን ጥያቄ ነው፡ አንዱ በትክክል ከዳነ፣ በእምነትና በፍሬያማነት መጠበቅ አለበትን?

የካልቪናውያን መስመር ያለው፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና የመጠበቅ ኃይልን በሚያስረግጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ኋላ ላይ ነው (ዮሐንስ 10:27-30፤ ሮሜ. 8:31-39፤ 1 ዮሐንስ 5:13፣18፤ 1ጴጥ. 1:3-5) እና የግስ ጊዜያት፣ እንደ የተጠናቀቀ ተገብሮ አንቀጽ፣ የኤፌ. 2:5፣8።

የአርሚኒየስ መስመር ያለው፣ አማኞችን "ያዝ፣" "አጥብቅ፣" ወይም "ቀጥል" በሚሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ኋላ ላይ ነው (ማቴ. 10:22፤ 24:9-13፤ ማርቆስ 13:13፤ ዮሐንስ 15:4-6፤ 1 ቆሮ. 15:2፤ ገላ. 6:9፤ ራዕ. 2:7፣11፣17፣26፤ 3:5፣12፣21፤ 21:7)። እኔ በግሌ ዕብራውያን 6 እና 10 የሚተገበሩ አይመስለኝም፣ ግን በርካታ አርሚኒያውያን፣ ከሀዲዎችን ለማስጠንቀቅ ይጠቀሙባቸዋል። የዘሪው ምሳሌ ማቴዎስ 13 እና ማርቆስ 4 የሚናገሩት ግልጽ ስለሆነ እምነት ጉዳይ ነው፣ ዮሐንስ 8:31-59 ላይ እንዳለው። ካልቪናውያን የተጠናቀቀውን የግስ ጊዜ እንደሚጠቅሱ፣ ደኅንነትን ለመግለጽ፣ አርሜኒያውያን ደግሞ የአሁኑን ጊዜ ምንባቦች ይጠቅሳሉ፣ 1 ቆሮ. 1:18፤ 15:2፤ 11 ቆሮ. 2:15 የመሳሰሉትን።

ይህ ጥሩ ምሳሌ ነው፣ ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓቶች እንዴት አድርገው በጽሑፍ አቃቂር ማውጣት ዘዴ ትርጓሜን እንደሚያዛቡ። ዘወትር መሪ የሆነው መርሕ ወይም ዋነኛው ጽሑፍ ሥነ-መለኮታዊ አተያይ ለመገንባት ጥቅም ላይ ይውላል፣ ሌሎች ጽሑፎች ሁሉ የሚታዩበት። ከማንኛውም ምንጭ ከሆነ አተያይ ተጠንቀቁ። እነሱ የሚመጡት ከምዕራባዊ ሎጂክ ነው፣ ከራዕይ ሳይሆን። መጽሐፍ ቅዱስ ምስራቃዊ መጽሐፍ ነው። እውነትን የሚያቀርበውም ተቃርኖ-ሞል በሚመስሉ ፓራዶክሳዊ ጥንዶች ነው። ክርስቲያኖች ሁለቱንም እንዲያጸኑና በተቃርኖዎቹ ውስጥ እንዲኖሩ ያስፈልጋል። አኪ ሁለቱንም ያቀርባል፣ የአማኝን ደኅንነት እና ቀጣይነት ያለው እምነትና በጎነት ይጠይቃል። ክርስትና በመነሻው ያለ የንስሐና የእምነት ምላሽን ይጠይቃል፣ ቀጣይነት ባለው የንስሐና እምነት ምላሽ። ደኅንነት ውጤት አይደለም (ወደ መንግሥተ-ሰማያት መግቢያ ትኬት፣ ወይም የእሳት አደጋ የኢንሹራንስ ፖሊሲ)፣ ግን ግንኙነት ነው። ውሳኔና ደቀ-መዛሙርትነት ነው። እሱም በአኪ በሁሉም የግሥ ጊዜያት ተገልጿል፡

የተከናወነ (የተጠናቀቀ ድርጊት)፣ ሐዋ. 15:11፤ ሮሜ. 8:24፤ 11 ጢሞ. 1:9፤ ቲቶ 3:5

የተጠናቀቀ (የተጠናቀቀ ድርጊት፣ ቀጣይነት ባለው ውጤት)፣ ኤፌ. 2:5፣8

የአሁን (ቀጣይነት ያለው ድርጊት)፣ 1 ቆሮ. 1:18፤ 15:2፤ 11 ቆሮ. 2:15

መጻኢ (የወደፊት ሁነቶች ወይም አንዳንድ ሁነቶች)፣ ሮሜ. 5:8፣10፤ 10:9፤ 1 ቆሮ. 3:15፤ ፊሊ. 1:28፤ 1 ተሰ. 5:8-9፤ ዕብ. 1:14፤ 9:28

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ክፉ ሰዎች"** |
| **አኪጀት** | **"ክፉ የሆኑት እነሱ"** |
| **አየተመት** | **"ክፉ አድራጊዎች"** |
| **አእት** | **"ክፉ ሰዎች"** |
| **አኢመቅ** | **"በደለኛ ሰዎች"** |

ይህ በጥሬው *kakous* (*kakos*)፣ ነው፣ እሱም ዘወትር "ለክፉ ሰዎች" የሚጠቀስ። ተመሳሳዩ *pon'ēros* ለክፉ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል (ጾታውን ያልለየ) ወይም ክፉ ሰዎች በመዳረሻውም ክፉው (ተባዕታይ፣ ማቴ. 5:37፤ 13:38፤ ዮሐንስ 17:15)። ዐውደ-ጽሑፍና አጠቃቀሙ እንደሚያረጋግጡት ይህ ጽሑፍ የሚያመለክተው "ክፉ ሰዎችን" ነው (ሮሜ. 2:9፤ 13:4) በቤተ-ክርስቲያን (ሐሰተኛ መምህራን) ወይም በማኅበረሰቡ ሊሆን ይችላል።

*Kakos* ሁለት ጊዜ ብቻ ነው በራዕይ ጥቅም ላይ የዋለው፣ እዚ እና 16፡2፣ እሱም ጥቅም ላይ የዋለው "የእግዚአብሔርን የቁጣ ጽዋዎች" ውጤት ለማመልከት ነው (ማለትም፣ ቁስለት)።

◘ **"ሊፈትናችሁ"** ይህ የግሪክ ቃል (*peirazÔ*) ፍችው በመልካም ወይም በክፉ መፈተን ነው (ባብዛኛው) ሆን ተብሎ (ዝከ. 2:2፣10፤ 3:10)። ተዛማጅ የሆነው ቃል (*peirasmos*) የሚኖረው ፍች ወደ ጥፋት በሆነ አተያይ መፈተን የሚል ነው። ሚዛኑ 1 ዮሐንስ 4፡1 ላይ ይገኛል፣ አማኞች የሚፈተኑበት (*dokimazÔ*) ስለ እግዚአብሔር በተነገሩት ላይ ባላቸው አተያይ ነው። ስለ እግዚአብሔር በተነገሩት ላይ አማኞች እንዲመረምሩ ጥሪ የቀረበው በሁለቱም ኪዳናት ነው (ዘዳ. 13:1-5፤ 18:22፤ ማቴ. 7:15-23፤ 1 ዮሐንስ 4:1-6)።

በአኪ አማኞች እርስ በርሳቸው ከመፈራረድ ጋር የተያያዘ ተቃርኖ አለ (ማቴ. 7፡1-5)። ሆኖም፣ ክርስቲያኖች ለመሪነት ሚና እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ተጠርተዋል (ማቴ. 7:5፣6፣15፤ 1 ቆሮ. 5:1-12፤ 1 ጢሞ 3፤ 1 ዮሐንስ 4:1-6)። ዝንባሌና የውስጥ ሐሳብ የተገቢ ግምገማ ቁልፎች ናቸው (ገላ. 6:1፤ ሮሜ. 2:1-11፤ 14:1-23፤ ያዕቆብ 4:11-12)።

## ልዩ ርዕስ፡ የግሪክ ቃላት ለመፈተን እና ለፍችዎቻቸው

ሁለት የግሪክ ቃላት አሉ፣ እነሱም አንዱን ለዓላማ ለመፈተን ሐሳብ ያላቸው።

1. *Dokimazō፣ Dokimion፣ Dokimasia*
   ይህ ቃል ብረታዊነት የአንድን ነገር ጥንካሬ ለመፈተን የሚሆን ቃል ነው (ማለትም፣ ከሜታፎር አኳያ አንድን ሰው) በእሳት። እሳት እውነተኛን ብረት ያሳያል ያቃጥላለም (ማለትም፣ ያጠራል) ዝገትን። አካላዊው ሂደት ኃይለኛ ፈሊጥ ሆኗል፣ ለእግዚአብሔር እና/ወይም ሰይጣን እና/ወይም ሰዎች ሌሎችን ሲፈትኑ። ይህ ቃል ብቸኛው ጥቅም ላይ የዋለ ነው፣ በአዎንታዊ መልኩ ተቀባይነትን ለማግኘት የሚፈትን ለመሆኑ። እሱም ለመፈተን በአዲስ ኪዳን ጥቅም ላይ የዋለው
   ሀ. በሬዎችን - ሉቃስ 14፡19
   ለ. ራሳችንን - 1ቆሮ. 11፡28
   ሐ. እምነታችንን - ያዕቆብ 1፡3
   መ. እግዚአብሔር እንኳ - ዕብ. 3፡9
   የእነዚህ ፈተናዎች ውጤት መልካም እንደሚሆን ይታሰባል (ሮሜ. 1:28፤ 14:22፤ 16:10፤ 2ቆሮ. 10:18፤ 13:3፤ ፊሊጵ. 2:27፤ 1ጴጥ. 1:7)። ስለዚህ፣ ቃሉ የሚያሳየው አንዱ የሚፈተሸውና የሚፈተንበት ሐሳብ
   ሀ. ጠቃሚ እንዲሆን
   ለ. መልካም እንዲሆን
   ሐ. ቅን እንዲሆን
   መ. ዋጋ ያለው እንዲሆን
   ሠ. የተከበረ እንዲሆን
2. *Peirazō፣ Peirasmus*
   ይህ ቃል ዘወትር ስህተትን የመፈለግ ወይም ያለመቀበልን ዓላማ የሚያሳይ ምርመራን የያዘ ፍች አለው። እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ከኢየሱስ የምድረ-በዳ ፈተና ጋር ተያይዞ ነው።
   ሀ. እሱም የሚያስረዳው ኢየሱስን ለማጥመድ የተሞከረውን (ማቴ. 4:1፤ 16:1፤ 19:3፤ 22:18፣ 35፤ ማርቆስ 1:13፤ ሉቃስ 4:38፤ ዕብ. 2:18)።
   ለ. ይህ ቃል (*peirazōn*) እንደ ሰይጣን መጠሪያ ጥቅም ላይ ውሏል ማቴ. 4፡3፤1ተሰ. 3፡5።
   ሐ. እሱም በኢየሱስ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እግዚአብሔርን እንዳንፈታተን (ማቴ. 14:7፤ ሉቃስ 4:12) [ወይም ክርስቶስ 1ቆሮ. 10:9]። እሱ ደግሞ የማይሰምር ነገር ለማድረግ መሞከርን መግለጫ ነው (ሐዋ. 9:20፤ 20:21፤ ዕብ.11:29)። እሱ ጥቅም ላይ የዋለው ከአማኞች ፈተና እና ምርመራ ጋር ተያይዞ ነው (1ቆሮ. 7:5፤ 10:9፣ 13፤ ገላ. 6:1፤ 1ተሰ. 3:5፤ ዕብ. 2:18፤ ያዕቆብ. 1:2፣ 13፣ 14፤ 1ጴጥ. 4:12፤ 1ጴጥ 2:9)። እግዚአብሔር ለሦስቱ የሰው ልጅ ጠላቶች ይፈቅዳል (ማለትም፣ ዓለም፣ ሥጋ፣ እና ሰይጣን) በተወሰነ ጊዜና ቦታ ይገለጡ ዘንድ።

◘ **"ራሳቸውን ሐዋርያት ነን ብለው የሚጠሩትን"** ይህ የ"ሐዋርያ" ቃል አጠቃቀም አስራ ሁለቱን አያመለክትም፣ ግን የቃሉን ሰፊ አጠቃቀም እንጂ (ሐዋ. 14:14፤ ሮሜ. 16:7፤ 1 ቆሮ. 15:7፤ ገላ. 1:19፤ ኤፌ. 4:11፤ 1 ተሰ. 2:6)። አኪ አዘውትሮ የሐሰተኛ ሐዋርያትን ወይም መምህራንን ጉዳይ ያመለክታል (ማቴ. 7:15-16፤ 24:24፤ ሐዋ. 20:29፤ 11ቆሮ. 11:13-15፤ 1ዮሐንስ 4:1 እንዲሁም በመጋቢያዊ መልእክቶች ሁሉ)። ይህች ቤተ-ክርስቲያን እነዚህን ሐሰተኛ ሐዋርያት በትክክል ለይታ አስወግዳቸዋለች።

**2፡3** ይህች ቤተ-ክርስቲያን ታማኝ ነች፣ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች መሐልና በስደትም ጭምር። ክርስቶስን አልካዱም ወይም መልካምን ከማድረግ አልዛሉም (ገላ. 6:9፤ ዕብ. 12:3፤ ያዕቆብ 5:7-8)። 2፡7 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**2፡4**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"የመጀመሪያውን ፍቅርህን ትተሃል"** |
| **አየተመት** | **"መጀመሪያ የነበረህን ፍቅር ትተሃል"** |
| **አእት** | **"ቀድሞ እንደምታፈቅረኝ አሁን አታፈቅረኝም"** |
| **አኢመቅ** | **"ቀድሞ ከነበረህ ፍቅር አሁን ያነሰ ነው ያለህ"** |

ይህ ምን ማለት እንደሆነ በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ።

1. አእት እና ቻርለስ ዊሊያምስ ትርጉሞች የሚሉት ለክርስቶስ ስላለ ፍቅር ነው።
2. ጀምስ ሞፋት የሚለው እርስ በርስ ስላለ ፍቅር ነው።
3. ሄርሼል ሆብስ በሐተታው ላይ የሚለው ለጠፉት ስላለ ፍቅር ነው።
4. ጄ.ቢ. ፊሊፕስ በትርጉሙ ላይ ከላይ ያሉትን ሁሉ ይደባልቃል።
5. አንዳንዶች የሚያስቡት እሱ የሚያያዘው ለሁለተኛው ትውልድ አማኞች ችግር ጋር እንደሚያያዝ ነው (መሳ. 2፡7-10)።
6. አንዳንዶች የሚመለከቱት ፍቅር የሌላት፣ ባለ ቀዘቀዘ-እምነት ቤተ-ክርስቲያን ነው (1 ቆሮንቶስ 13)።

**2፡5 "አስብ"** ይህ የአሁን የድርጊት ተተኳሪ ሲሆን ፍችውም "ዘወትር በአእምሮህ ጠብቀው" ማለት ነው።አማኞች ዘወትር ቀደም ሲል በኃጢአት የነበራቸውን ሁኔታ እና አዲሱን በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ያገኙትን ጸጋና ምሕረት እንዲያስቡ ይመከራሉ።

▣ **"ከወዴት እንደወደቅህ"** ይህ የተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች ነው። "የቀድሞ ፍቅራቸውን" መተው የችላ ባይነታቸው አመቺ ሁኔታ ነው!

▣ **"ንስሐ ግባ የቀድሞ *ሥራህንም* አድርግ"** እነዚህ ሁለት ያለፈ ድርጊት ተተኳሪዎች ናቸው። ቤተ-ክርስቲያን በጥቅሉ ወሳኝ የሆነ ንስሐ እንድትገባ እንደተጠራች አስታውሱ (2 ዜና. 7፡14) እና ለክርስቶስ ባላት ፍቅር ንቁ እንድትሆን፣ እርስ በርስም፣ ለጠፉትም።

ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር ላለ የእምነት ግንኙነት ዋነኛ ነገር ነው (ማቴ. 3:2፤ 4:17፤ ማርቆስ 1:15፤ 6:12፤ ሉቃስ 13:3፣5፤ ሐዋ. 2:38፤ 3:19፤ 20:21)። የዕብራይስጡ ቃል ፍችው የድርጊቶች ለውጥ ነው፣ በግሪክ ደግሞ የአስተሳሰብ ለውጥ። ንስሐ ከራስ-ወዳድነት ሕልውና ለመለወጥ ፍቃደኝነት ነው፣ ወደ እግዚአብሔር የሚነግረውና የሚመራው ሕይወት። እሱም ለራሳችን ቅድሚያ ከምንሰጠውና ከእስራት መመለስ ነው። በመሠረቱ እሱ አዲስ ዝንባሌ ነው፣ አዲስ የዓለም አተያይ፣ አዲስ ጌታ። ንስሐ የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፣ ለእያንዳንዱ የወደቀ የአዳም ልጅ፣ በአምሳሉ ለተሠራው (ሕዝ. 18:21፣23፣32 እና II ጴጥ. 3:9)።

የአኪ ምንባብ እሱም ለንስሐ የተለያዩ የግሪክ ቃላትን በተሻለ የሚያንጸባርቀው II ቆሮ. 7:8-12 ነው።

1. *lue*፣ "ምሬት" ወይም "ምሬት" ቁ.. 8 (ሁለቴ)፣ 9 (ሦስቴ)፣ 10 (ሁለቴ)፣ 11
2. *metamelomai*፣ "ከጥንቃቄ ኋላ፣" ቁ. 8 (ሁለቴ)፣ 9
3. *metanoeÔ*፣ "ንስሐ፣" "ማሰብ፣" ቁ. 9፣ 10

ተቃርኖው በውሸት ንስሐ (*metamelomai*፣ ይሁዳ፣ ማቴ. 27:3 እና ዔሳው፣ ዕብ. 12:16-17) እና በእውነተኛ ንስሐ መካከል ነው (*metanoeÔ*፣ *ጴጥሮስ*፣ ዮሐንስ 21:15-23፤ ማቴ 26:75፤ ማርቆስ 14:72፤ ሉቃስ 22:62)።

እውነተኛ ንስሐ ከሥነ-መለኮት አኳያ የሚያያዘው

1. የኢየሱስ ስብከት ከአዲስ ኪዳን ሁኔታዎች ጋር (ማቴ. 4:17፤ ማርቆስ 1:15፤ ሉቃስ 13:3፣5)
2. ሐዋርያዊ ስብከቶች፣ ሐዋርያት ሥራ ላይ (*kerygma*፣ ሐዋ. 3:16፣19፤ 20:21)
3. የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ስጦታ (ሐዋ. 5:31፤ 11:18 እና II ጢሞ. 2:25)
4. መጥፋት (II ጴጥ. 3:9)

ንስሐ አማራጭ አይደለም!

▣ **"አለበለዚያ እመጣብሃለሁ"** ይህ የተለመደ ጭብጥ ነው፣ በዚህ መጽሐፍ፤ ክርስቶስ ቶሎ ይመጣል (ዝከ. 1: 2፣3፤ 2: 5፣16፤ 25፤ 3:3፣11)። በብኪ የእግዚአብሔር መምጣት በረከትን ወይም ፍርድን ይዞ ይመጣ ነበር። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ክርስቶስ የመጣው ቤተ-ክርስቲያንን ሥርዓት ለማስያዝ ነው (1ጴጥ. 4፡17)! ስለዚህ፣ እሱ ጊዜያዊ፣ ደግሞም ፍጻሜያዊ ይዘት አለው።

▣ ***"መቅረዝህንም ከስፍራው እወስዳለሁ"*** መቅረዙ ተምሳሌት የሚሆነው ሙሉዋን ቤተ-ክርስቲያን ነው። ይህም ሊያካትት የሚችለው የክርስቶስን አለመኖርና የበረከቱን መወሰድ ነው። ሙሉው ማኅበር እምነቱን መጣል አልታየበትም፣ ግን መልካም አገልግሎታቸውን ግን ትተዋል። ይኸው ደግሞ በጴርጋሞን አብያተ-ክርስቲያናት ላይ ይሠራል (ዝከ. 2:16)፤ ትያጥራ (cf. 2:22-23)፤ ሰርዴስ (ዝከ. 3:3)፤ እና ሎዶቅያ (ዝከ. 3:19)። ሊሆን የሚችለው እነዚህ እያንዳንዱ ቤተ-ክርስቲያኖች በኒቆናውያን ዓይነት የሐሰት ትምህርት እንደተጎዱ ነው፣ ይኸውም ከጣዖት አምልኮ ባህል ጋር የሚቻቻሉት።

**2፡6 "የኒቆላውያንንም ሥራ ትጠላለህ"** እነዚህ ኒቆላውያን እነማን እንደነበሩና ምን እንደሚያምኑ በርካታ መላምቶች አሉ። ብቸኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንጫችን ራዕ. 2:6፣ 14-15 ነው። መላምቶች የጀመሩት ቀደም ብሎ በቤተ-ክርስቲያን አካባቢ በ180 ዓ.ም ኢሬኒዩስ እና ሂፖሊተስ እንደገመቱት እነዚህ በሐዋ. 6፡5 ከተመረጡት ከ"ሰባቱ" አንዱ ስሙ ኒቆላስ ተከታዮች ነበሩ የሚል ነው። ይህ ባጠቃላይ ተጨባጭነት የለውም። ኢሬኒዩስ፣ በመጽሐፉ *ተቃውሞ-መናፍቃን* 3፡11፡7፣ እንደሚገምተው እነርሱ የሲሪኒያን ግኖስቲሲስም ተከታዮች ነበሩ፣ የሁለተኛው ክፍለ-ዘመን። ኢዩሲቢዩስ፣ በመጽሐፉ *የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ*፣ 3፡29፡1፣ እንዳለው፣ ይህ የተለየ ወገን ብዙ አልቆየም።

በ2፡14-15፣ የበለዓም ትምህርትና የኒቆላውያን ትምህርት ተመሳሳይ ነው። ተመሳሳይ ሥርወ-ቃላዊ ግንኙነት በስሞቻቸው መሐል አለ፣ በግሪክ፤ ፍችውም "አሸናፊ" እና "ሕዝብ" (ከኒቆዲሞስ ስም ፍቺ ጋር እጅግ ተመሳሳይ)። ግልጽ የሆነው ነገር ሁለቱም አማኞች በጣዖት አምልኮ ሥርዓቶች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታቱ ነበር፣ እሱም አምልኳዊ የዝሙት ተግባርን የሚያካትት። በዚህ ስሜት ኒቆላውያንና በለዓማውያን (ዘኍ. 25:1-9፤ 31:16-18) እጅግ ተመሳሳይ ናቸው፣ ከኤልዛቤል ትምህርት ጋር (ዝከ. 2፡20)።

**2፡7 "መንፈስ ለአብያተ-ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ"** ይህ ማስጠንቀቂያ ለሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት ደብዳቤዎች ተደጋግሟል (ዝከ. 2:7፣11፣17፣29፤ 3:6፣13፣22)። እሱም ከኢየሱስ ቃል የመጣ ሐረግ ነው (ማቴ. 11:15፤ 13:9፣43)። መንፈሳዊ እውነት በአእምሮም በእጅም ምላሽ ማግኘት አለበት። ይህም ከዕብራይስጡ ቃል ከ*shema*፣ ጋር ተመሳሳይ ነው፣ "አድምጥ ታደርግ ዘንድ" (ዘዳ. 5:1፤ 6:4፤ 9:1፤ 20:3፤ 27:9-10)።

◘ **"ቤተ-ክርስቲያኖች"** ልዩ ርዕስ 1:4 ላይ ተመልከት።

◘ **"ድል ለሚነሣ ለእርሱ"** ቀጣይነት ያለው ሥነ-መለኮታዊ አጽንዖት በአማኞች ጽናት ላይ አለ (ዝከ. 2:7፣11፣17፣25-26፤ 3:4-5፣11-12፣21)። የትክክለኛው መለወጥ ተግባራዊ ማስረጃ ነው (ማቴ. 24:13፤ ገላ. 6:9)! ጆናታን ኤድዋርድስ እንደሚለው፣ "የመመረጥ ርግጠኛው ማረጋገጫ እስከ መጨረሻው ሲጸና ነው።" ደብልዩ. ቲ. ኮነር እንደሚለው፣ "ለመዳን የተመረጠ ሰው ደኅንነት፣ ከሁሉም ዘላለማዊነት በእግዚአብሔር ሥራና ሐሳብ ርግጠኛ ሲሆን ነው፣ እሱ ገናም በእምነት ሁኔታ ውስጥ ነው፣ እምነትም የሚታገሥና ድል የሚያደርግ።" ልዩ ርዕስ 2:2 ላይ ተመልከት።

◘ **"በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ"** ይህ የዔድን ገነት ዛፍ ጠቃሽ ነው፣ (ዘፍ. 2:9)። ሰዎች ከእግዚአብሔር እና በገነት ካሉት እንስሳት ጋር ወዳጅነት እንደጀመሩ፣ እንደዚያው ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ ያበቃል (ኢሳ. 11:6-9፤ ራዕ. 22:2፣14፣19)።

"ገነት" የሚለው ቃል የፋርስ ቃል ሲሆን የባላባት ባለ ግንብ የአትክልት ስፍራ ያመለክታል፣ እሱም በሴፕቱዋጂንት ጥቅም ላይ የዋለው የዔደንን ገነት ለመተርጎም ነው (ሕዝ. 28:13፤ 31:8)። እሱም ከብዙዎቹ አንደኛው ማጣቀሻ ነው ለመሲሐዊው ዘመን፣ እሱም በሰባቱ አብያተ-ክርስቲያናት መልእክቶች ሁሉ ላይ ያለ።

"ገነት" የሚለው ቃል በሁለት መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፡ (1) ሉቃስ 23:4 እሱም የሚጠቅሰው የሲዖልን/ገሃነምን የጻድቃን ክፍል ነው (1:8 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት)። ኢየሱስ ንስሐ የገባውን ሌባ ያን ቀን ከእርሱ ጋር እዚያ እንደሚሆን ነግሮታል (ኢየሱስ ለ40 ቀናት ወደ ሰማይ አልተመለሰም፣ ዮሐንስ 20:17) እና (2) II ቆሮ. 12:3፣ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን መገኘት ነው፣ የእግዚአብሔርን ሰማያዊ ዙፋን ክፍል ("ሦስተኛው ሰማይ")።

እግዚአብሔር በእርሱ አምሳልና መልክ ለተፈጠረው የሰው ልጅ ያለው ዓላማ (ዘፍ. 1:26-27)፣ ሁልጊዜ የዘላለም ሕይወት ነው። ዘፍጥረት 3 ላይ ያለው ውድቀትና ቀሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ሰነድ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ቁርጠኝነት መቤዠትና ዘላለማዊ ኅብረት ከእርሱ ጋር እንዲኖር ነው። ይህ የወደቀው ዓለም፣ ይህ በሙሉ ኅብረት መካከል ያለ ክፍተት የእግዚአብሐሔር ፍላጎት አይደለም፣ የሰው ልጅ አሳፋሪነት እንጂ። እግዘኢአብሔር ፍጥረቱን ለዓላማው ይመልሳል።

**ራዕይ፡ 2፡8-11**

**8በሰምርኔስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል። 9መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፥ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን የሚሉት የሚሳደቡትን ስድብ አውቃለሁ። 10ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ። 11መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም።**

**2፡8 "ፊተኛውና መጨረሻው"** ይህ ከኢየሱስ ተደጋጋሚ መጠሪያዎች አንዱ ነው፣ 1:17 እና 22:13 ላይ የሚገኘው። በመነሻው እሱ የሚያመለክተው ያህዌን ነው (ኢሳ. 41:4፤ 44:6፤ 48:12)። እሱም "አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ" ከሚለው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ነው (ዝከ. 1:8፤ 21:6፤ 27:13) እና "መጀመሪያና መጨረሻ" (ዝከ. 21:6፤ 22:13)። 1:8 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

◘ **"ሞቶ የነበረው፣ ሕያውም የሆነው"** ይህ ሳይቢሊ የፍጥረት አምልኮን ለመምታት ሊሆን ይችላል፣ እናት ጣዖት። አብዛኞቹ ጥንታዊ የመራባት ሃይማኖቶች አተያያቸውን የመሠረቱት ሰዋዊ በሆነ የተፈጥሮ ዑደት፣ ክረምት ሞት፣ እና ጸደይ ዳግም ልደት ላይ ነው። በዐውደ-ጽሑፍ ይህ የሚዛመደው፣ ከሥነ-መለኮት አኳያ ከ1:18፤ 5:6 ጋር ነው፣ እዚያም ኢየሱስ የታረደው በግ የሆነበት፣ አሁን ግን የተነሣው። እሱን አጽንዖት የሚሰጠው ኢየሱስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያደረገውን ተለዋጭ ሞትና ትንሣኤውን ነው (ዕብ. 7:27፤ 9:12፣28፤ 10:10)።

**2፡9 "መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ"** እነዚህ ሁለት ጠንከር ያሉ የግሪክ ቃላት ናቸው። እነርሱ ጠቃሚ ናቸው፣ የሰምርኔስ ከተማ ባለጠጋ ስለነበረች። ቤተ-ክርስቲያኒቷ ድሀ የነበረችበት ሐቅ የሚመስለው ኢኮኖሚያዊ መከራዋን ለማሳየት ይሆናል። እሱም ከሥነ-መለኮት አኳያ በቂ ነው፣ እንደ ራዕይ መጽሐፍ አማኞች ችግር "መከራ" የሚቀበሉት ከማያምኑትና ከክፉው ነው፣ የማያምኑት ግን የሚሣቀዩት "ከእግዚአብሔር ቁጣ" ነው። 7:14 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት። አማኞች ዘወትር ይጠበቃሉ (ታትመዋል፣ 7:2 ላይ ልዩ ርዕስ ተመልከት) ከመለኮታዊ ፍርድ።

## ልዩ ርዕስ፡ መከራ

*ሥነ-መለኮታዊ* ልዩነት ሊኖር ያስፈልጋል፣ በጳውሎስ የዚህ ቃል አጠቃቀም (*thlipsis*) መካከል እና በዮሐንስ።

*ሀ.* የጳውሎስ አጠቃቀም (እሱም የኢየሱስን አጠቃቀም የሚያንጸባርቅ)

1. ችግሮች፣ *መከራ፣* ክፉ በወደቀው ዓለም የገባ
   - *ሀ.* ማቴ. 13:21
   - ለ. ሮሜ. 5:3
   - ሐ. 1ቆሮ. 7:28
   - *መ.* 2ቆሮ. 7:4
   - *ሠ.* ኤፌ. 3:13
2. ችግሮች፣ *መከራዎች፣ መከራዎች* በማያምኑት የተፈጠሩ
   - *ሀ.* ሮሜ 5:3፤ 8:35፤ 12:12
   - ለ. 2ቆሮ. 1:4፣8፤ 6:4፤ 7:4፤ 8:2፣13
   - ሐ. ኤፌ. 3:13
   - *መ.* ፊሊጵ. 4:14
   - *ሠ.* 1ተሰ. 1:6
   - ረ. 2ተሰ. 1:4
3. ችግሮች፣ *መከራዎች፣* ክፉ የመጨረሻው ዘመን
   - *ሀ.* ማቴ. 24:21፣29
   - ለ. ማርቆስ 13:19፣24
   - ሐ. 2ተሰ. 1:6-9

ለ. የዮሐንስ አጠቃቀም

1. ዮሐንስ የተወሰነ ልዩነት አድርጓል፣ በ*thlipsis* እና *org'* ወይም *thumos* (ቁጣ) መካከል፣ በ*ራዕይ*። *Thlipsis* የማያምኑ በሚያምኑት ላይ የሚያደርጉት ሲሆን፣ እንዲሁም *org'* እና *thumos* እግዚአብሔር በማያምኑ ላት የሚያደርገው ነው።
   - *ሀ. thlipsis - ራዕ.* 1:9፤ 2:9-10፣22፤ 7:14
   - *ለ. org' - ራዕ.* 6:16-17፤ 11:18፤ 16:19፤ 19:15
   - *ሐ. thumos - ራዕ.* 12:12፤ 14:8፣10፣19፤ 15:2፣7፤ 16:1፤ 18:3
2. ዮሐንስ ደግሞ በወንጌሉ ላይ ቃሉን ተጠቅሟል፣ አማኞች በየዘመናቱ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለማንጸባረቅ - ዮሐንስ 16:33።

▣ **"(ግን ባለጠጋ ነህ)"** አማኞች በክርስቶስ መቆማቸውን በዓለማዊ መስፈርት መፍረድ አይችሉም (ማቴ. 6፡33)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ስድብ"** |
| **አየተመት፣ አኢመቅ** | **"የነውር ቃል"** |
| **አእት** | **"ባንተ ላይ የተባሉ ክፉ ነገሮች"** |

ይህ በጥሬው "ስድብ" የሚል ቃል ነው፣ እሱም የብኪ ፍቺ ያለው፣ "ክፉ ወሬ ማውራት" የሚል፣ እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ያህዌን በቃል ከማጥቃት ጋር በተያያዘ ነው (ሌዋ. 24፡13-23)። በብኪ ሁለቴ "መባረክ" (*barak*) የሚለው ቃል በተመሳሳይ ስድብ በሚል ጥቅም ላይ ውሏል (1 ነገሥ. 21፡10፣13)። ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ እነዚህ የአይሁድ ሃይማኖተኞች እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ ያስረግጣሉ ("እግዚአብሔርን ይባርካሉ")፣ ግን አይደሉም (ማቴ. 7፡21-23)።

▣ **"አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን የሚሉት"** ተመሳሳይ የሆነ ሐረግ 3፡9 ጥቅም ላይ ውሏል፤ ይህም በርግጠኝነት በዘራቸው አይሁድ የሆኑትን የእግዚአብሔር ሕዝብ ነን የሚሉትን ግን ያልሆኑትን ነው ( ዮሐንስ 8:44፤ ሮሜ. 2:28-29፤ ገላ. 3:29፤ 6:16)። ከሐዋርያት ሥራና ከገላትያ እንደምናውቀው አይሁድ ትልቅ ተቃውሞ አስነሥተዋል በወንጌል እወጃ ላይ (ሐዋ. 13:50፤ 14:2፣ 5፣ 19፤ 17:5)።

ራዕይ 2፡13 እንደሚለው ይህ የሚያመለክተው አጥቢያዊ የአጼአዊ የአምልኮ ሥርዓትን ነው፣ ኮንሲሊያ ተብሎ የሚጠራው፣ ይኸውም፣ ክርስቲያኖች ቄሳርን "ጌታ" እንዲሉ እና ለእሱ በዓመት አንዴ ዕጣን እንዲያጨሱ የሚጠይቀው።

▣ **"የሰይጣን ምኵራብ"** ዮሐንስ ዓለምን የሚያየው በሰላ ተቃርኖ ነው፣ እግዚአብሔር አልያም ሰይጣን። ሰይጣን (ልዩ ርዕስ፡ ሰይጣን 12፡3 ላይ ተመልከት) አዘውትሮ በመጽሐፉ ተጠቅሷል (cf. 2:9፣13፤ 3:9፤ 12:9፣10፤ 20:2፣7)። እሱ የአማኞችን ስም ያጠፋል፣ አሳዳጆችንም ያበረታል። ይህ በመንፈሳዊ ዓለም ያለ ተቃርኖ ወይም ምንታዌ የአፖካሊፕቲካዊ ጽሑፍ ባሕርይ ነው። የአዳምን ልጆች ልብ እና አዕምሮ ለመቆጣጠር ውጊያ አለ።

**2፡10 "አትፍራ"** ይህ የአሁን መካከለኛ ወይም ተገብሮ (አረጋጋጭ) ተተኳሪ ነው፣ ከአሉታዊ አንቀጽ ጋር እሱም ዘወትር ፍችው ቀደም ሲል በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ማቆም ነው። እነዚህ ቤተ-ክርስቲያኖች ፈርተዋል። ስደት የደኅንነታቸው ምልክትና የእግዚአብሔር በረከት ነበር (ማቴ. 5፡10-12)።

◘ **"ዲያብሎስ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊጥላችሁ ነው"** ከክፉው የሰው መሪዎች ጀርባ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ የክፉ አካላዊ ኃይል ያደፍጣል (ኤፌ. 6፡10-19)።

ሰይጣን የሚለው ቃል የብኪ መጠሪያና መግለጫ ነው። እሱ አምላክ የሰጠው ተግባር ዐመጸኛዊ፣ ግል-ተኮር አማራጭ ለሰው ልጆች መስጠት ነው፣ ከዚያም ለፈተና በሚሰጡበት ጊዜ መክሰስ ነው (ዘፍጥረት 3፤ ኢዮብ 1-2፤ ዘካርያስ 3)። በብኪ የክፉው መኀልበት አለ። ሰይጣን የተፈጠረው እንደ አገልጋይ ነበር ወደ ጠላትነት ተቀየረ (*የብሉይ ኪዳን ሥነ-መለኮት* በኤ.ቢ. ዴቪድሰን ገጽ 300-306)።

እሱ በርግጥ ግምት ነው፣ እጅግ ዘይቤአዊ የሆነው የኢሳይያስ 14 ቋንቋ፣ በቀጥታ የሚመለከተው ትዕቢተኛውን የባቢሎንን ንጉሥ ነው፣ ሕዝቅኤል 28፣ የጢሮስን ትዕቢተኛ ንጉሥ ነው፣ በመዳረሻው የሚመለከተው መንፈሳዊ ትዕቢትንና የሰይጣንን ውድቀት ነው። የሕዝቅኤል 28 ቋንቋ የተወሰደው ከዔድን ገነት መግለጫ ላይ ነው። ሰዋዊ፣ ታሪካዊ፣ ጣዖታዊ ንጉሥን፣ በመልአካዊ ቃላት ከዔድን የተወሰደውን ገለጻ ለመቀበል ያስቸግራል (ዘፍጥረት 3)። ሆኖም፣ ሕዝቅኤል ይህንኑ ተመሳሳይ ነገር ለግብጽ ንጉሥም ምዕራፍ 31 ላይ ያደርጋል። እሱም በዔድን ገነት እንደ ትልቅ ዛፍ ተገልጿል።

አማኞች ሁሉ ተጨማሪ መረጃ ይሻሉ፣ በተለይም ስለ እግዚአብሔር፣ መላእክት፣ ክፉው መገኛ። ንቁ መሆን ይጠበቅብናል፣ ዘይቤአዊና ትንቢታዊ ገለጻዎችን ወደ ቀኖናዊ ሥነ-መለኮት እንዳንለውጣቸው። አብዛኛው ዘመናዊ ሥነ-መለኮት የሚመጣው ከተለዩ፣ ዘይቤአዊ ጽሑፎች ነው፣ ከዘመናዊ ጽንሰ-ሐሳቦች ጋር በመደባለቅ፣ ሁለቱም ሥነ-መለኮታዊም ሆነ ጽሑፋዊ (ዳንቴ እና ሚልተን)።

በአኪ ዲያብሎስ ተብሎ ይጠራል (ዝኪ. 12፡9፣12፤ 20፡2፣10)፣ ይኸውም ድብልቅ የግሪክ ቃል የሆነ፣ ፍችውም "ወዲያ መጣል፣" "ስም ማጥፋት፣" ወይም "ክስ ማቅረብ" ነው። ይህም በድጋሚ የሚያንጸባርቀው የመክሰስና የመፈተን ሥራውን ነው። እነዚህ ቃላት ከራዕይ (ዝኪ. 12፡9፤ 20፡2) ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ልዩ ርዕስ፡ አካላዊው ክፉ 12፡9 ላይ ተመልከት።

◘ **"ትፈተኑ ዘንድ"** ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው በሁለት መልኩ ነው፡ (1) አማኞች የሚፈተኑት እውነተኛ እምነታቸውን ለማሳየት ነው፣ እንዲሁም እየጠነከሩ እንዲያድጉ (ዝኪ. 2፡10፤ ሐዋ. 14፡27፤ ሮሜ. 5፡3-4፤ 8፡17-19፤ ዕብ. 5፡8፤ ያዕቆብ 1፡2-4፤ 1ጴጥ. 4፡12-19) እና (2) የማያምኑት የሚፈተኑት አለማመናቸውን ለማሳየት ነው፣ እናም ፍርድ እንደሚገባቸው (ዝኪ. 3፡10)። በራዕይ የክርስቲያን ፈተና "መከራ" ሲባል (ልዩ ርዕስ 2፡9 ላይ ተመልከት)፣ የማያምኑት ግን "በእግዚአብሔር ቁጣ" ሥር ይሆናሉ።

ሁለት የግሪክ ቃላት ናቸው የተተረጎሙት "ፈተና፣" "ሙከራ፣" ወይም "ፈተና"። አንደኛው የሚኖረው ፍች "ለጥፋት መፈተን የሚል አተያይ" ነው (*peirasmos፣ peirasmo*)። ሌሎቹ ቃላት (*dokimos፣ dokimazo*) ጥቅም ላይ የዋሉበት ፍች "ወደ ማጽደቅ የሚያደርስ ፈተና የሚል አተያይ ነው።" ሰይጣን ለማጥፋት ይሞክራል፤ እግዚአብሔር ለማጠንከር ይፈትናል (1 ተሰ. 2፡4፤ 1ጴጥ. 1፡7፤ ዘፍ. 22፡1፤ ዘጸ. 16፡4፤ 20፡20፤ ዘዳ. 8፡2፣16፤ 13፡3፤ መሳ. 2፡22፤ 11 ዜና. 32፡31)። ልዩ ርዕስ 2.2 ላይ ተመልከት።

◘ **"አስር ቀናት"** "አስር ቀናት" በሚለው ሐረግ ላይ በርካታ ግምቶች አሉ፡

1. አንዳንዶች የሚሉት የሚያመለክተው በጥሬው የአስር ቀን ጊዜ ስደት ነው፣ በሰምርኔስ ከተማ በዮሐንስ ጊዜ
2. ሌሎች የሚሉት ቁጥር አስር የፍጽምና ቁጥር ከመሆኑ የተነሣ፣ እሱ እንዲያው የሚለው ፍጹም የሆነ ቁጥር ቀናት ስደት ነው
3. አንዳንዶች የሚሉት እሱ የሚያመለክተው ያለተለየ ጊዜ መከራ ነው

መልካሙ ዜና ወሰን ያለው መሆኑ ነው። መከራው ያበቃል!

ሆኖም፣ በአፖካሊፕቲካዊ መጽሐፍ አንዱ ፈጽሞ ርግጠኛ ሊሆን አይችልም፣ ቁጥሮቹ በፍካሬያዊ ወይም በእማሬያዊ ጥቅም ላይ ለመዋላቸው። ቁጥሩ አኪ እና በበይነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ላይ በተምሳሌታዊ ፍቺ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ከዋለ፣ ምናልባት ዘይቤአዊ ሊሆን ይችላል። እጅግ ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉት ተምሳሌታዊ ቁጥሮች 3፣ 4፣ 6፣ 7፣ 10፣ 12 እና የእነርሱ ብዜቶች ናቸው (ልዩ ርዕስ 1፡4 ላይ ተመልከት)።

◘ **"እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን"** ይህ የአሁን መካከለኛ ወይም ተገብሮ (አረጋጋጭ) ተተኳሪ ሲሆን፣ እሱም አጽንኦት የሚሰጠው አማኞች በእምነት እንዲቀጥሉ ነው፣ አካላዊ ሞት እንኳ ቢሆን (ማቴ. 2:13; 12:11; 10:22; 24:13; ሉቃስ 12:4; ገላ. 6:9)። አንዳንድ አማኞች ፊትም አሁንም ይገደላሉ። ይህ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና ከወደቀው ዓለም የሚደርስብን ነገር አያዎ (ፓራዶክስ) ነው።

◘ **"የሕይወት አክሊልን እሰጥሃለሁ"** ይህ የድል ነሽዎች አክሊል ነው "*stephanos*" (1 ቆሮ. 9:25)። እሱም የክርስቲያን ሰማዕታት ሽልማት ነው። ከኢዩሲቢስ የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ፣ 4፡15 እንደምንማረው፣ በርካታ ሰማዕታት መኖራቸውን ነው፣ የሰምርኔሱን ጳጳስ ፖሊክራፕን ጨምሮ። ሌሎች አክሊሎች (ሽልማቶች) ደግሞ አሉ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱ (2 ጢሞ. 4፡8፤ ያዕቆብ 1፡12፤ 1ጴጥ. 5፡4፤ ራዕ. 3፡11)።

ዮሐንስ ቃሉን የሚጠቀምበት ለሕይወት ነው፣ *zoē*፣ የዘላለም ሕይወትን ለማመልከት፣ የትንሣኤ ሕይወት (ዮሐንስ 1፡4፤ 3፡15፣36፤ 4፡14፣36፤ 5፡24፣26፣29፣39፣40፤ 6፡27፣33፣35፣40፣47፣48፣51፣53፣54፣63፣68፤ 8፡12፤ 10፡10፣28፤ 11፡25፤ 12፡25፣50፤ 14፡6፤ 17፡2፣3፤ 20፡31፤ ራዕ. 2፡7፣10፤ 3፡5፤ 13፡8፤ 17፡8፤ 20፡12፣15፤ 21፡6፣27፤ 22፡1፣2፣14፣17፣19)። እውነተኛው ሕይወት ከሥጋዊ ሕላዌ ይበልጣል!

**ልዩ ርዕስ፡ የሽልማቶች ደረጃና ቅጣት**

ሀ. ለእግዚአብሔር ተገቢ እና ተገቢ ያልሆነ ምላሽ መስጠት የተመሠረተው በእውቀት ላይ ነው። አነስተኛ እውቀት ያለው፣ አናሳ ምላሽ ይኖረዋል። በተቃራኒው ደግሞ እውነት ነው።

ለ. እግዚአብሔርን ማወቅ በሁለት መሠረታዊ መንገዶች ይመጣል
1. ተፈጥሮ (መዝሙር 19፤ ሮሜ 1-2
2. ቃሉ (መዝሙር 19፣ 119፤ ወንጌል)

ሐ. የብኪ ማስረጃ
1. ሽልማቶች
ሀ. ዘፍ. 15፡1 (ዘወትር የሚዘመደው ከምድራዊ ሽልማት ጋር ነው፣ መሬት እና ወንዶች ልጆች)
ለ. ዘዳግም 27-28 (የኪዳን ታዛዥነት በረከትን ያመጣል)
ሐ. ዳን. 12፡3
2. ቅጣት
ሀ. ዘዳግም 27-28 (ለኪዳን አለመታዘዝ ርግማንን ያመጣል)
3. የብኪ የሽልማት ዘርፍ ለግለሰባዊ፣ ኪዳናዊ ጽድቅ ተሻሽሏል፣ በሰዎች ኃጢአት ምክንያት። ይህ ማሻሻያ በኢዮብና በመዝሙር 73 ይታያል። አዲስ ኪዳን አትኩሮቱን ከዚህ ዓለም ወደ ቀጣዩ አዞሮታል (የተራራው ስብከት፣ ማቴዎስ 5፡7)።

መ. የአዲስ ኪዳን ማስረጃ

1. ሽልማቶች (ከደጎንነት በመለስ)
ሀ. ማርቆስ 9፡41
ለ. ማቴ. 5:12፣46፤ 6:1-4፣5-6፣6-18፤ 10:41-42፤ 16:27፤ 25:14-23
ሐ. ሉቃስ 6:23፣35፤ 19:11-19፣25-26
2. ቅጣት
ሀ. ማርቆስ 12:38-40
ለ. ሉቃስ 10:12፤ 12:47-48፤ 19:20-24፤ 20:47
ሐ. ማቴዎስ 5:22፣29፣30፤ 7:19፤ 10:15፣28፤ 11:22-24፤ 13:49-50፤ 18:6፤ 25:14-30
መ. ያዕቆብ 3:1

ሠ. ለእኔ ብቸኛው ምስያ፣ ትርጉም ሊሰጥ የሚችለው ከኦፔራ ነው። በኦፔራ ትርዒት ላይ ተገኝቼ አላውቅም፣ ስለዚህ ልረዳቸው አልችልም። አስቸጋሪነቱን እና የሴራውን ውስብስብነት፣ ዜማውን፣ እና ጭፈራውን ይበልጡን በተረዳሁት ቁጥር፣ ዝግጅቱን ይበልጥ አደንቃለሁ። መንግሥተ-ሰማይ ጽዋችንን እንደሚሞላ አምናለሁ፣ ነገር ግን ምድራዊ አገልግሎታችን የጽዋውን መጠን የሚወስነው ይመስለኛል።

ስለሆነም፣ እውቀትና ምላሽ ስለዛ እውቀት ውጤቱ በሽልማት እና ቅጣት ነው (ማቴ. 16:7፤ 1ቆሮ. 3:8፣14፤ 9:17፣ 18፤ ገላ. 6:7፤ 2ጢሞ. 4:14)። መንፈሳዊ መርሕ አለ— የዘራነውን እናጭዳለን! አንዳንዶች ብዙ ይዘራሉ እናም ብዙ ያጭዳሉ (ማቴ. 13፡8፣23)።

ረ. "የጽድቅ አክሊል" የእኛ ነው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠናቀቀ ሥራ (2ጢሞ. 4፡8)፣ ነገር ግን "የሕይወት አክሊል" የሚያያዘው በመከራ ለሚጸኑት ነው (ያዕቆብ 1:12፤ ራዕ. 2:10፤ 3:10-11)። "የክብር አክሊል" ለክርስቲያን መሪዎች፣ ከሕይወት ስልታቸው ጋር በተያያዘ (1ጴጥ. 5፡1-4)። ጳውሎስ የማይጠፋ አክሊል እንዳለው አውቋል፣ ግን ጽኑ የሆነ ራሱን መቆጣጠር ተለማምዷል (1ቆሮ. 9፡24-27)።

የክርስቲያን ሕይወት ምሥጢር፣ ወንጌል ሙሉ ለሙሉ ነጻና፣ በክርስቶስ የተፈጸመ ሥራ መሆኑ ነው፣ ነገር ግን በክርስቶስ ለሆነው ለእግዚአብሔር ስጦታ ምላሽ እንደምንሰጥ ሁሉ፣ እኛም የግድ ለክርስቲያን ሕይወት ለእግዚአብሔርን ሥልጣን ምላሽ መስጠት ይኖርብናል። የክርስቲያን ሕይወት ከተፈጥሮ በላይ ነው፣ እንደ ደጎንነት፣ ሆኖም እኛ የግድ መቀበል እና መያዝ ይኖርብናል። ነጻው ግን ሁሉም ዋጋ የተከፈለበት አያዎ (ፓራዶክስ) የሽልማት እና የመዝራት/ማጨድ ምሥጢር ነው።

በመልካም ሥራ አልዳንም፣ ግን ስለ መልካም ሥራ (ኤፌ. 2፡8-10)። መልካም ሥራዎች እሱን እንዳገኘነው ማስረጃዎች ናቸው (ማቴዎስ 7)። የሰው ሥራ በደጎንነት አካባቢ ወደ ጥፋት ያመራል፣ መልካም ኑሮ፣ እሱም ከደጎንነት የሚመነጭ ግን ይሸለማል።

**2፡11 "ድል የሚነሣ"** ይህም ደግሞ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ነው ስለ ታማኝነት (ዝከ. 2:7፣17፣26፤ 3:5፣12፣21፤ 21:7)። እሱ በርግጥ ትዕግሥት አጽንዖት ነው (ልዩ ርዕስ 2፡2 ተመልከት)።

▣ **"በሁለተኛው ሞት አይጎዳም"** ይህ ድርብ አሉታዊ አወቃቀር ነው ከድርጊት ተገብሮ ሊሆን ከሚችል ጋር፣ እሱም የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ክብካቤ ያሳያል፣ መሥዋዕት ለሆኑት (ዝከ. 12:11)። "ሁለተኛው ሞት" ሲያልን ያመለክታል (ልዩ ርዕስ 1፡8 ላይ ተመልከት) ወይም ከእግዚአብሔር ወዳጅነት ለዘላለም መለያየትን (ራዕ. 20:6፣14፤ 21:8).

▣ **"ጆሮ ያለው ይስማ"** ይህ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ነው፣ ለመንፈሳዊ ትኩረትና መረዳት (ዝከ. 2:7፣11፣ 17፣29፤ 3:6፣13፣22፤ 13:9)።

## *ራዕይ 2፡12-17*

**[12]በጴርጋሞንም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው እንዲህ ይላል። [13]የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን አውቃለሁ፤ ስሜንም ትጠብቃለህ፥ ሰይጣንም በሚኖርበት፥ በእናንተ ዘንድ የተገደለው የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ በነበረበት ዘመን እንኳ ሃይማኖቴን አልካድህም። [14]ዳሩ ግን ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበልዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ከአንተ ጋር ስላሉ፥ የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ። [15]እንዲሁ የኒቆላውያንን ትምህርት እንደ እነዚህ የሚጠብቁ ሰዎች ከአንተ ጋር ደግሞ አሉ። [16]እንግዲህ ንስሐ ግባ፤ አለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፥ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ። [17]መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፥ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፥ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል።**

**2፡12 "በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው"** ይህ ተመሳሳይ ማጣቀሻ ነው፣ ለከበረው ኢየሱስ፣ 1፡16 ላይ የሚገኘው። እሱም ለያህዌ የብኪ ዘይቤ ነበር (ኢሳ. 11፡4፤ 49፡2)። እሱም በአኪ ጥቅም ላይ የሚውለው ለእግዚአብሔር ቃል ዘልቆ የመግባት ኃይል ነው (ዝከ. 2፡16፤ II ተሰ. 2፡8፤ ዕብ. 4፡12)።

**2፡13 "የምትኖርበትን አውቃለሁ"** "መኖር" በብኪ አንድምታው "በቋሚነት አብሮ መኖር" ነው። እነዚህ አማኞች ጥንካሬ የሆነ አጥቢያዊ መንግሥታዊ እና ሰይጣናዊ ግፊት ገጥሟቸዋል። ኢየሱስ እነርሱንና ያሉበትን አደገኛ ሁኔታ አውቋል። እዛው ከእነርሱ ጋር ነበር።

▣ **"የሰይጣን ዙፋን ባለበት"** በርካታ የዚህ ሐረግ ታሳቢ ትርጉሞች ይኖራሉ፡

1. እሱም ትልቁን የዜውስን ዙፋን የሚያመለክት ይሆናል፣ በጴርጋሞን የነበረው።
2. እሱም የፈውስ ጣዖት ይሆናል፣ አስክሊፒኦስ፣ ምልክቱም እባብ የነበረ።
3. እሱም መላውን ከተማ እንደ ግዙፍ ዙፋን ተወስዶ ይሆናል፣ በአክሮፖሊስ ምክንያት፣ እሱም በሙቶዎች ጫማ ከራሱ ከከተማው በላይ ቆሞ የነበረው።
4. እሱም የኮንሲሊያ ጠቃሽ ይሆናል፣ አገራዊ ድርጅት የአጼ አምልኮን ለማስፋፋት፣ እሱም በጴርጋሞን እጅግ ኃይለኛ የነበረ።

ከታሪካዊ ዐውድ አኳያ ቁ. 1 ወይም ቁ. 4 የተሻለ ይመስላል።

▣ **"ስሜንም ትጠብቃለህ"** ይህ የአሁን የድርጊት አመላካች ነው። የሚያሳየውም የስሙን ጠቀሜታ ሲሆን፣ የግለሰቡን ባሕርይ እንደሚወክል ነው። አማኞች የሚያምኑት ስሙን በመጥራት ነው (ዮሐንስ 1፡12፤ 3፡18፤ ሮሜ. 10፡9-13) እና ስሙን በመጥራት በማምለክ (ዘፍ. 4፡26፤ 12፡8፤ 26፡25) እና ስሙን በመጥራት በመጽናት (ዮሐንስ 17፡11-12)።

### ልዩ ርዕስ፡ የጌታ ስም

ይህ የተለመደ የአዲስ ኪዳን ሐረግ ሲሆን እሱም የሥስቱ በአንዱ አምላክ (ሥላሴ) በቤተ-ክርስቲያን አካላዊ መገኘቱንና ንቁ ኃይል መሆኑን ያሳያል። ይህም አስማታዊ ቀመር አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ባሕርይ አስረጅ ነው።

ይህ ሐረግ ዘወትር የሚያመለክተው ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ ነው (ፊሊጵ. 2፡11)

1. አንዱ በኢየሱስ ላይ ላለው እምነት በጥምቀት ጊዜ መግለጫ (ሮሜ. 10፡9-13፤ ሐዋ. 2፡38፤ 8፡12፣16፤ 10፡48፤ 19፡5፤ 22፡16፤ I ቆሮ. 1፡13፣15፤ ያዕቆብ 2፡7)
2. ከርኩስ መንፈስ ነጻ ሲወጣ (ማቴ. 7፡22፤ ማርቆስ 9፡38፤ ሉቃስ 9፡49፤ 10፡17፤ ሐዋ.19፡13)
3. በፈውስ ጊዜ (ሐዋ. 3፡6፣16፤ 4፡10፤ 9፡34፤ ያዕቆብ 5፡14)
4. በአገልግሎት ጊዜ (ማቴ. 10፡42፤ 18፡5፤ ሉቃስ 9፡48)
5. በቤተ-ክርስቲያን ሥነ-ሥርዓት (ማቴ.18፡15-20)
6. ለአሕዛብ በሚሰበከበት ጊዜ (ሉቃስ 24፡47፤ ሐዋ. 9፡15፤ 15፡17፤ ሮሜ. 1፡5)
7. በጸሎት ጊዜ (ዮሐንስ 14፡13-14፤ 15፡2፣16፤ 16፡23፤ I ቆሮ. 1፡2)
8. ክርስትናን የማጣቀሻ መንገድ (ሐዋ. 26፡9፤ I ቆሮ. 1፡10፤ II ጢሞ. 2፡19፤ ያዕቆብ 2፡7፤ I ጴጥ. 4፡14)

ማንኛውንም ነገር፣ እንደ አዋጅ ነጋሪዎች፣ አገልጋዮች፣ ረጅዎች፣ ፈዋሾች፣ ከፉ መናፍስትን አውጭዎች ወዘተ… ብንሆን፣ የምናደርገው በእሱ ባሕርይ፣ በእሱ ኃይል፣ በእሱ ሰጪነት ነው— በእሱ ስም!

▣ **"ሃይማኖቴን አልካድክም"** ይህ የድርጊት መካከለኛ ነው (አረጋጋጭ) አመላካች። በእነዚህ የጥንት ክፍለ ዘመን ክርስትና፣ አሁንም እንኳ በአንዳንድ ማኅበረሰብ ተጨባጭ የሆነ ፈተና አለ፣ የአንዱን ሀብት ወይም ሕይወት ለማዳን በክርስቶስ ያለውን እምነት በመካድ፣ በሥጋዊ ወይም በፍርድ ሂደቶች ጊዜ። ቤተ ክርስቲያን ዘወትር እንደታገለች ነው ይሄንን ክህደት እንዴት መያዝ እንደሚገባ።

## ልዩ ርዕስ፡ እምነት (*PISTIS* [ስም]፣ *PISTEUÔ፣* [ግሥ]፣ *PISTOS* [ቅጽል])

ሀ. ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ ቃል ነው (ዕብ. 11፡1፣6)። እሱም የኢየሱስ ፊተኛ ስብከት ተያያዥ ነው (ማርቆስ 1፡15)። ቢያንስ ሁለት የኪዳን መማሚያ ቅድመ-ሁኔታዎች ነበሩ፡ ንስሐ መግባትና እምነት (ዝኪ. 1:15፤ ሐዋ. 3:16፣19፤ 20:21)።

ለ. ሥርወ ቃሉ

1. "እምነት" የሚለው ቃል በብኪ ፍችው ታማኝነት፣ ታማኝ፣ ወይም የሚታመኑት ነው፣ እናም የአምላክ ባሕርይ መግለጫ ነው፣ የእኛ ሳይሆን።
2. አሱም የመጣው ከዕብራይስጡ ቃል (*emun፣ emunah*፣ BDB 53)፣ ነው፣ ፍችውም "ርግጠኛ ወይም የጸና" መሆን ማለት ነው። የሚያድን እምነት የአእምሮ ስምምነት ነው (የእውነቶች ስብስብ)፣ የሞራል ሕይወት (የሕይወት ስልት) ነው፣ በቀዳሚነትም ግንኙነታዊ (ሰውን የመቀበል) እና ፍቃደኝነታዊ መሰጠት (ውሳኔ) ለእዛ ሰው።

ሐ. የብኪ አጠቃቀሙ

አጽንዖት የግድ መሰጠት ያለበት የአብርሃም እምነት በሚመጣው መሲሕ ላይ አልነበረም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ፣ እሱም ልጅና ዝርዮች እንደሚኖሩት (ዘፍ. 12:2፤ 15:2-5፤ 17:4-8፤ 18:14)። አብርሃም ለዚህ ተስፋ ምላሽ የሰጠው በእግዚአብሔር በማመን ነው። እሱ ገና ጥርጣሬና ሌሎች ችግሮች ስለዚህ ተስፋ ነበሩበት፣ ለመፈጸምም አስራ ሦስት ዓመት የወሰደበት። ሆኖም፣ ፍጹም ያልሆነው እምነቱ በእግዚአብሔር ተቀባይነት አግኝቷል። እግዚአብሔር እንከን ካላቸው የሰው ልጆች ጋር ለመሥራት ፍቃደኛ ሆኗል፣ ለእሱና ለተስፋው በእምነት ምላሽ ለሰጡት፣ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እንኳ ብትሆን (ማቴ. 17፡20)።

መ. የአኪ አጠቃቀሙ

"አመነ" የሚለው ቃል ከግሪክ ቃል (*pisteu*Ô) ነው። እሱም ደግሞ "ማመን" "እምነት" ወይም "መታመን" ተብሎ ሊተረጎም የሚችል። ለምሳሌ፣ ስሙ በዮሐንስ ወንጌል ላይ አልተከሰተም፣ ግሱ ግን ዘወትር ጥቅም ላይ ውሏል። በዮሐንስ 2፡23-25 ላይ ቅን የሆነ ርግጠኛ ያለ መሆን አለ፣ በሕዝቡ ቁርጠኝነት ላይ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስን እንደ መሲሕ መቀበል ላይ። ሌለኛው ትክክለኛ ያልሆነ "እምነት" የሚለው ቃል አጠቃቀም በዮሐንስ 8:31-59 እና ሐዋ. 8:13፣ 18-24 ላይ ይገኛል። እውነተኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ከመነሻው ምላሽ ላቅ ይላል። እሱም በደቀ መዝሙርነት ሂደት መከተል ይኖርበታል (ማቴ. 13:20-22፣31-32)።

ሠ. ከመስተጻምር ጋር ያለው አጠቃቀም

1. *eis* ማለት "በ-ላይ" ማለት ነው። ይህ የተለየ አወቃቀር አጽንዖት የሚሰጠው አማኞች እምነታቸውን/መታመናቸውን/አመኔታቸውን በኢየሱስ ላይ እንዲያደርጉ ነው
   ሀ. በስሙ (ዮሐንስ 1:12፤ 2:23፤ 3:18፤ 1 ዮሐንስ 5:13)
   ለ. በእርሱ (ዮሐንስ 2:11፤ 3:15፣18፤ 4:39፤ 6:40፤ 7:5፣31፣39፣48፤ 8:30፤ 9:36፤ 10:42፤ 11:45፣48፤ 17:37፣42፤ ማቴ. 18:6፤ ሐዋ. 10:43፤ ፊሊ. 1:29፤ 1 ጴጥ. 1:8)
   ሐ. በእኔ (ዮሐንስ 6:35፤ 7:38፤ 11:25፣26፤ 12:44፣46፤ 14:1፣12፤ 16:9፤ 17:20)
   መ. በወልድ (ዮሐንስ 3:36፤ 9:35፤ 1 ዮሐንስ 5:10)
   ሠ. በኢየሱስ (ዮሐንስ 12:11፤ ሐዋ. 19:4፤ ገላ. 2:16)
   ረ. በብርሃን (ዮሐንስ 12:36)
   ሰ. በእግዚአብሔር (ዮሐንስ 14:1)
2. *en* ማለት "በውስጥ" ማለት ነው እንደ ዮሐንስ 3:15፤ ማርቆስ 1:15፤ ሐዋ. 5:14
3. *epi* ማለት "ውስጥ""ወይም "በላይ" ማለት ነው፣ እንደ ማቴ. 27:42፤ ሐዋ. 9:42፤ 11:17፤ 16:31፤ 22:19፤ ሮሜ. 4:5፣ 24፤ 9:33፤ 10:11፤ 1 ጢሞ. 1:16፤ 1ጴጥ. 2:6
4. ከስም ጋር የተያያዘ ነው፣ ያለ ምንም መስተጻምር እንደ ገላ. 3:6፤ ሐዋ. 18:8፤ 27:25፤ 1 ዮሐንስ 3:23፤ 5:10
5. *hoti፣* ፍችውም "የታመኑት" ምን እንደታመኑ ይዘትን ይሰጣል
   ሀ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ነው (ዮሐንስ 6:69)
   ለ. ኢየሱስ ያለና የሚኖር ነው (ዮሐንስ 8:24)
   ሐ. ኢሱስ በአብ አለ አብም በእርሱ አለ (ዮሐንስ 10:38)
   መ. ኢየሱስ መሲሑ ነው (ዮሐንስ 11:27፤ 20:31)
   ሠ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ዮሐንስ 11:27፤ 20:31)
   ረ. ኢየሱስ በአብ ተልኳል (ዮሐንስ 11:42፤ 17:8፣21)
   ሰ. ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለው ነው (ዮሐንስ 14:10-11)
   ሸ. ኢየሱስ ከአብ መጥቷል (ዮሐንስ 16:27፣30)
   ቀ. ኢየሱስ ራሱን በአብ የኪዳን ስም ገልጿል። "እኔ ነኝ" (ዮሐንስ 8:24፤ 13:19)
   በ. ከእርሱ ጋር አንኖራለን (ሮሜ. 6:8)
   ተ. ኢየሱስ ሞቶ ዳግም ተነሥቷል (1 ተሰ. 4:14)

◘ **"አንቲጳስ ምስክሬ"** ስለዚህ ሰውዬ የምናውቀው ምንም የለም፡፡ የተሰጠው መጠርያ ለክርስቶስ ከተሰጠው ጋር ተመሳሳይ ነው፣ 5፡1 ላይ፡፡ "ምስክር" የሚለው ቃል "መሥዋዕት" ሊሆን ይችላል (ዝከ. 11፡3፤ 17፡6)፡፡ ተርቱሊያን የሚለው አንቲጳስ በሥጋ መቀቀያ ናስ ድስት ተጠብሷል፣ ይህ ግን ኋላ የመጣ ወግ ነው፡፡

**2፡14 "የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ"** ኢየሱስ አሉታዊ መግለጫ አለው፣ ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ለስድስቱ፡፡ የጽድቅ ኑሮ በአንዳንድ ስፍራዎች፣ በሌሎች ዘንድ ለኃጢአት ሰበብ ሊሆን አይችልም!

◘ **"እንዲሁ የኒቆላውያንን ትምህርት እንደ እነዚህ የሚጠብቁ ሰዎች ከአንተ ጋር ደግሞ አሉ"** በለዓም የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር (ዘኍ. 24፡2) የእስራኤል ልጆችን ለመቃወም ሌሎችን ለመርዳት የተነሣሣ (ዘኍ. 22-25 እና 31፡16)፡፡ እሱም በሁለቱም በብኪም እና በአኪ ተኮንኗል (ዘኍ. 31፡16፤ II ጴጥ. 2፡15፤ ይሁዳ 11)፡፡

በዕብራይስጥ በለዓም የሚለው ስም ፍችው "የሕዝብ አሸናፊ" ማለት ይሆናል፣ ኒቆላውያን የሚለው ስም ደግሞ በግሪክ ተመሳሳይነት አለው (ኒቆዲሞስ ከሚለው ዮሐንስ 3 ተመሳሳይ ፍች አለው)፡፡ ይኸም እነዚህን ሁለት ወገኖች ይለያቸዋል፣ ኢ-ሞራላዊ በሆነ ልምምዳቸው (ዝከ. ኤልዛቤል 2፡20)፡፡

◘ **"በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበልዓምን ትምህርት የሚጠብቁ"** በለዓም ለባላቅ፣ ለሞአብ ንጉሥ ያቀረበው ሐሳብ፣ የእስራኤል ልጆች በመራባት አምልኮ እንዲሳተፉ ነበር (ዘኍ. 25፡1-3)፡፡ ቀጣይነት ያለው ባህላዊ መፈታተን ነበር ነበር፣ የአንደኛው ክፍለ ዘመን ጣዖት፣ የግልሙትና አምልኮ፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ እስራኤል (ስሙ)

I. የስሙ ፍቺ ርግጠኝነት የለውም (ቢ.ዲ.ቢ. 975)፡፡
   ሀ. ኤል የዘላለም
   ለ. ኤል የዘላለም (ተጽዕኗዊ)
   ሐ. ኤል ጠባቂው
   መ. ኤል ይታገላል
   ሠ. ኤል እጅግ ይጥራል
   ረ. እሱም ከእግዚአብሔር ጋር ታግሏል (ዘፍ. 32፡28)

II. በብሉይ ኪዳን አጠቃቀሙ
   ሀ. የያዕቆብ ስም (ነጣቂ፣ ተረከዝ ያዥ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 784፣ ዝከ. ዘፍ. 25፡26) በያቦቅ ወንዝ ላይ ከመንፈሳዊ አካሉ ጋር ከታገለ በኋላ ተቀየረ (ዘፍ. 32፡22-32፤ ዘጸ. 32፡13)፡፡ የዕብራይስጥ ስሞች ፍቺ ዘወትር ድምፅን ተከትሎ የሚሄድ ነው፣ ሥርወ ቃልን ሳይሆን (ዝከ. 32፡28)፡፡ ስሙም እስራኤል ሆኗል (ምሳሌ፣ ዘፍ. 35፡10)፡፡
   ለ. እሱም ለአስራ ሁለት ልጆቹ የጥቅል ስም ሆኖ ያገለግላል (ምሳሌ፣ ዘፍ. 32:32፤ 49:16፤ ዘጸ.1:7፤ 4:22፤ 28:11፤ ዘዳ. 3:18፤ 10:6)፡፡
   ሐ. እሱም በአስራ ሁለቱ ነገዶች የሚመሠረተውን ሕዝብ የሚያመለክት ነው፣ ከዘጸዓት በፊት (ዘፍ. 47:27፤ ዘጸ. 4:22፤ 5:2) እና በኋላ (ዘዳ. 1:1፤ 18:6፤ 33:10)፡፡
   መ. ከሳኦል፣ ዳዊት፣ እና ሰለሞን አሀዳዊ ንጉሣዊ አገዛዝ በኋላ፣ ነገዶቹ ተከፍለዋል፣ በሮቦአም ሥር (1ኛ ነገሥ. 12)፡፡
      1. ልዩነት የተጀመረው ይፋዊ መከፋፈል በፊት ነው (ምሳሌ፣ 2ኛ ሳሙ. 3:10፤ 5:5፤ 20:1፤ 24:9፤ I ነገሥ. 1:35፤ 4:20)
      2. የሰሜኑ ነገዶች የሚታወቁበት፣ ሰማርያ ወደ ሶርያ እስከ ወደቀ ድረስ፣ በ722 ዓ.ዓ (2ኛ ነገሥ. 17)፡፡
   ሠ. ለይሁዳ በጥቂት ቦታዎች ጥቅም ላይ የዋለ (ምሳሌ፣ ኢሳይያስ 1፤ ሚክያስ 1፡15-16)፡፡
   ረ. ከሶርያና ከባቢሎን ስደት በኋላ እንደገና ለያዕቆብ ዝርዮች የጥቅል ስም ሆኗል (ምሳሌ፣ ኢሳ. 17:7፥9፤ ኤር. 2:4፤ 50:17፥19)፡፡
   ሰ. ምዕመኑን ከካህናት በአንጻራዊነት ለመለየት (1ኛ ዜና 9:2፤ ዕዝራ 10:25፤ ነህ. 11:3)፡፡

◘ **"ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ"** እነዚህ ሁለት ኃጢአቶች በጣዖት አምልኮ ልምምዶች ውስጥ ይካተታሉ (ዘኍ. 25፡1-3 እና 31፡16)፡፡ እዚያ የጣዖት መብል ብቻ አልነበረም፣ ለጣዖታት መሥዋዕት የተደረገ (1 ቆሮ. 8፡1-13)፣ ግን ደግሞ አዘውትሮ የዝሙት ርኩሰትም የተለመደና የሚጠበቅ የአምልኮ ሥርዓት ነበር፣ በእነዚህ የጣዖት ማኅበራት፡፡ የሰዎች ግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ ለከብቶች፣ ለአዝመራ፣ እና ለኅብረተሰቡ ጤንነትና መራባት አስፈላጊ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡

**2፡15 "እንዲሁ የኒቆላውያንን ትምህርት እንደ እነዚህ የሚጠብቁ ሰዎች ከአንተ ጋር ደግሞ አሉ"** በበለዓምና በኒቆላውያን ትምህርት መካከል ባለው መመሳሰል (ዝከ. 2፡6)፣ እና ኤልዛቤል (ዝከ. 2፡20)፣ እነዚህ ሦስቱም የሚያመለክቱት ጣዖትን፣ የግልሙትና አምልኮ ልምምዶችን ነው፡፡ አማኞች ወደ ጣዖት ባህል ወደ ኋላ መመለስ ወይም መቻቻል የለባቸውም፡፡

**2፡16 "ስለዚህ ንስሐ ግባ"** 2፡5 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

☒ **"አለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፥ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ"** ይህ የድርጊት የአሁን ተተኳሪ ነው። ቀጣይነት ያለው አጽንዖት አለ፣ ንስሐን በተመለከተ (ዝከ. 2:5፣16፣22፤ 3:3፣19)። መጪው የሚያመለክተው በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚሆን ጊዜያዊ ፍርድ ወይም የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ነው፣ በዓለም ላይ ሊፈርድ። ጠቃሚ የሚሆነው ቤተ ክርስቲያን በሙላቷ ለንስሐ መጠራቷ ነው (ዝከ. 3፡20፤ 2 ዜና. 7፡14) በአንዳንዶች ኃጢአት ምክንያት፤ እነርሱ ካላደረጉ መዘዙ አጠቃላይ ቅጣት ነው! ልዩ ርዕስ፡ ፈጽኖ መመለስ 1፡2 ላይ ተመልከት።

**2፡17 "ለእርሱ ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ"** መና ከአእምሮ በላይ የሆነ ስጦታ ነው፣ ለእስራኤል ልጆች፣ በምድረ በዳ ሲንከራተቱ በነበረበት ሰዓት (ዘጸ. 16፡14-15፣31፤ መዝ. 78፡17-33፣ በተለይ ቁ. 24)። በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች ተሰንዝረዋል፣ ይሄንን ምሥጢራዊ ሐረግ ለመተርጎም፡

1. እሱ የሚያመለክተው የኪዳኑን ታቦት ነው፣ ከተደበቀበት በኤርምያስ የወጣው፣ ከናባል ተራራ ላይ (2 መቃብያስ 2፡4-8) የእንስራ መና በመያዙ ምክንያት (ዘጸ. 16፡32-34፤ ዕብ. 9፡4).
2. እሱም የአዲሱ የጽድቅ ዘመን ምግብን የሚጠቅስ ሊሆን ይቸላል (II ባሮክ 29፡8)።

ትክክለኛ የሚያመለከተው ርግጠኛ አይደለም፣ ነገር ግን የአዲሱ የመንፈስ ዘመን ጠቃሽ ነው፣ በክርስቶስ የሚመረቀው። አንዳንዶች ይልቁንም የሚያስረግጡት፣ በዮሐንስ 6፡31-35 የተነሣ፣ የተሰወረው መና ራሱ ክርስቶስን የሚያመለክተ ነው። ይህም ደኅና ምሳሌ ነው፣ የዚህን መጽሐፍ የተለየ ዝርዝር መተርጎሙ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ፣ እሱንም የዛን ዘመን አድማጭ ሊረዳው የሚችል፣ ነገር ግን ትክክለኛው ማጣቀሻ የጠፋ።

☒ **"ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ"** ይህ ድንጋይ፣ ደግሞ *Tessera* ተብሎ ይጠራል፣ እናም በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ በርካታ አጠቃቀም አለው።

1. እሱም ለተለየ ግብዣ መግቢያ ትኬት ጥቅም ላይ ውሎ ይሆናል
2. እሱም ለመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ድምጽ ጥቅም ላይ ውሎ ሊሆን ይችላል
3. እሱም ለባለ ድል ስፖርተኛ ለድል ምልክት ጥቅም ላይ ውሎ ሊሆን ይችላል
4. እሱም የባርያን ነጻ መውጣት ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሎ ሊሆን ይችላል።

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ፣ ቁ.1 የተሻለ ይመስላል፣ መሲሐዊውን ግብዣ በመጥቀስ (በአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ የተለመደ ጭብጥ)።

☒ **"በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል"** ይህ አዲስ ስም የአዲሱ የጽድቅ ዘመን ሊሆን ይችላል፣ ወይም የመሲሑ መጠሪያ (ኢሳ. 56፡5፤ 62፡2፤ 65፡15፤ ልዩ ርዕስ፡ መሲሕ 1፡1 ላይ ተመልከት)። ይህ አዲስ ስም በራዕይ መጽሐፍ ላይ ተዘውትሮ ተጠቅሷል (ዝከ. 3፡12፤ 14፡1፤ 19፡12፣13፣16፤ 22፡4)።

### ራዕይ 2፡18-29

**[18]በትያጥሮንም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዓይኖች ያሉት በእቶንም የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ ይላል። [19]ሥራህንና ፍቅርህን እምነትህንም አገልግሎትህንም ትዕግሥትህንም ከፊተኛውም ሥራህ ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ። [20]ዳሩ ግን። ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ [21]ንስሐም እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋም ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም። [22]እነሆ፥ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ፥ ከእርስዋም ጋር የሚያመነዝሩትን ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ፤ [23]ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ፤ አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኵላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፥ ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ። [24]ዳሩ ግን ይህን ትምህርት ለማትይዙ ሁሉ የሰይጣንንም ጥልቅ ነገር እነርሱ እንደሚሉት ለማታውቁ ለእናንተ በትያጥሮን ለቀራችሁት እላለሁ፤ ሌላ ሸክም አልጭንባችሁም፥ [25]ነገር ግን እስክመጣ ድረስ ያላችሁን ጠብቁ። [26-27]ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፥ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ፤ [28]የንጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ። [29]መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።**

**2፡18 "የእግዚአብሔር ልጅ"** ኢየሱስን እንደ "ወልድ" መጥቀስ እጅግ የተለመደ ነው። እጅግ የተለመደው የዚህ ዘይቤ መጠሪያ "የሰው ልጅ" ነበር፣ እሱም ኢየሱስ ለራሱ የመረጠው መጠሪያ። ሌለኛው ቃል "የእግዚአብሔር ልጅ" ነበር፣ እሱም የተለመደው የኢየሱስ መጠሪያ ፣ በዮሐንስ ጽሑፎች (ዮሐንስ 1፡34፣49፤ 5፡25፤ 9፡35፤ 10፡36፤ 11፡4፣27፤ 19፡7፤ 20፡31፤ I ዮሐንስ 3፡8፤ 4፡15፤ 5፡5፣10፣12፣13፣20)። አንድ ሦስተኛው የ"ወልድ" አጠቃቀም በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ ይገኛል (ዝከ. 1፡2፤ 3፡6፤ 5፡8፤ 7፡28) እዚያም ኢየሱስ ከአገልጋይ ጋር በተቃርኖ የተገለጠበት (ማለትም፣ ሙሴ፣ ነቢያት)። እሱ ሙሉ የቤተሰብ አባል ነው፣ ከአብ ጋር።

ይህ በምዕራፍ 1 ላይ ካሉት ገላጭ ሐረጎች አንዱ አይደለም። ይህ ቃል፣ ልክ እንደ "ድንግል ትወልዳለች" በአኪ ደራስያን በመጠኑ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው፣ ምናልባትም በጣዖታዊ ሰሚዎች አዛብቶ መረዳት ሊሆን ይችላል፣ እነርሱም ወዲያውኑ

እነዚህን ቃላት ለራሳቸው አጠቃቀም ለጣዖት አማልክት ስለሚያውሉት። የሐሜር ጣዖታትና የሴት ጣዖታት ከሰዎች ጋር ተራክቦ ይፈጽሙ ነበር፣ ልዩ ዝርያ በመውለድ።

## ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ

ይህ ከኢየሱስ የአኪ መጠሪያዎች አንዱና ዋነኛው ነው። እሱም በርግጥ መለኮታዊ ፍችዎች አሉት። እሱም ኢየሱስን እንደ "ልጅ" ወይም "የእኔ ልጅ" ያካትታል፣ እግዚአብሔርም እንደ "አባት" ይገለጻል። እሱም በአኪ ከ124 ጊዜ በላይ ተከስቷል። የኢየሱስ የራሱ "የሰው ልጅ" ማለት እንኳ መለኮታዊ ፍች አለው ከዳን. 7፡13-13።

በብኪ "ወልድ" የሚለው መጠርያ አራት የተለዩ ቡድኖችን ያመለክታል።

1. መላእክት (ዘወትር በብዙ ቁጥር ዘፍ. 6:2፤ ኢዮብ 1:6፤ 2:1)
2. የእስራኤል ንጉሥ (II ሳሙ. 7:14፤ መዝ. 2:7፤ 89:26-27)
3. የእስራኤል ሕዝብ እንዳጠቃላይ (ዘጸ. 4:22-23፤ ዘዳ. 14:1፤ ሆሴ. 11:1፤ ሚል. 2:10)
4. እስራኤላውያን ፈራጆች (መዝ. 82:6)

ሁለተኛው አጠቃቀም ነው ከኢየሱስ ጋር የተያያዘው። በዚህ መልኩ "የዳዊት ልጅ" እና "የእግዚአብሔር ልጅ" ሁለቱም ይዛመዳሉ፣ ከ2 ሳሙኤል 7፤ መዝሙር 2 እና 89 ጋር። በብኪ "የእግዚአብሔር ልጅ" ተለይቶ ለመሲሕ ፈጽሞ ጥቅም ላይ አልዋለም፣ እንደ ፍጻሜ ዘመን ንጉሥ ካልሆነ በቀር፣ እንደ እስራኤል "የተቀቡት ሥልጣናት" እንዳንዱ። ሆኖም፣ በቀይ ባሕር ጥቅሎች መሲሐዊ አንድምታ ያላቸው ስሞች የተለመዱ ናቸው (የተለየ ማጣቀሻ፣ *የኢየሱስ እና የወንጌላት መዝገበ-ቃላት፣* ገጽ 770 ተመልከት)። ደግሞም "የእግዚአብሔር ልጅ" መሲሐዊ መጠሪያ ነው፣ በሁለት በይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአይሁድ አፖካሊፐቲካዊ ሥራዎች (II ኢስድራስ 7:28፤ 13:32፣37፣52፤ 14:9 እና I ሔኖክ 105:2)።

የአኪ ዳራው ለኢየሱስ የሚያመለክተው በተሻለ መልኩ ተጠቃሏል፣ በአንዳንድ ምድቦች።

1. ቅድመ-ሕላዌነቱ (ዮሐንስ 1:1-18)
2. የተለየ (የድንግል) ውልደቱ (ማቴ. 1:23፤ ሉቃስ 1:31-35)
3. ጥምቀቱ (ማቴ. 3:17፤ ማርቆስ 1:11፤ ሉቃስ 3:22. የእግዚአብሔር ድምጽ ከሰማይ፣ ከመንግሥታዊ ንጉሥነቱ፣ መዝሙር 2 ላይ ያለው ከመከራ ተቀባዩ አገልጋይ ጋር ኢሳይያስ 53 ያለውን አንድ ያደርገዋል)።
4. የሰይጣን ፈተናው (ማቴ. 4:1-11፤ ማርቆስ 1:12፣13፤ ሉቃስ 4:1-13። ልጅነቱን እንዲጠራጠር ተፈትኗል ወይም ቢያንስ ዓላማውን ከመስቀል በተለየ መንገድ እንዲቀዳጅ)።
5. የእሱ ማረጋገጫ ተቀባይነት በሌላቸው ተናጋሪዎች
   ሀ. አጋንንት (ማርቆስ 1:23-25፤ ሉቃስ 4:31-37፣41፤ ማርቆስ 3:11-12፤ 5:7)
   ለ. የማያምኑት (ማቴ. 27:43፤ ማርቆስ 14:61፤ ዮሐንስ 19:7)
6. በደቀ መዛሙርቱ መረጋገጡ
   ሀ. ማቴ. 14:33፤ 16:16
   ለ. ዮሐንስ 1:34፣49፤ 6:69፤ 11:27
7. የራሱ የግል ማረጋገጫ
   ሀ. ማቴዎስ 11:25-27
   ለ. ዮሐንስ 10:36
8. የእሱ በቤተሰባዊ ዘይቤ እግዚአብሔርን እንደ አባት መጠቀሙ
   ሀ. ለእግዚአብሔር "አባ"ን መጠቀሙ
      1) ማርቆስ 14:36
      2) ሮሜ 8:15
      3) ገላትያ 4:6
   ለ. የእሱ ተደጋጋሚ የአብ አጠቃቃቀም (*patēr*) ከመለኮት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ

ለማጠቃለል፣ "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው መጠርያ ታላቅ ሥነ-መለኮታዊ ትርጉም ይኖረዋል፣ ብኪን እና የእሱን ተስፋዎች እና ምድቦች ለሚያውቁ፣ ነገር ግን የአኪ ጸሐፍት ከአሕዛብ ጋር ባለው አጠቃቀም ይረበሻሉ፣ ጣዖታዊ ዳራ ባለው መልኩ "አማልክት" በማለት ሴቶቹን ወስደው "ቲታን" ወይም "ግዙፋን" ወልደዋል በሚል።

◘ **"እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዓይኖች ያሉት በእቶንም የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት"** ይህ ሌለኛው የኢየሱስ መጠሪያ ነው፣ ከ1፡14፣15 ላይ የተወሰደ። እሱም የዳን. 10፡6 ጠቃሽ ሲሆን የሚያሳየውም የኢየሱስን ሰማያዊ ስፍራ ነው። እሱም ከትያጥሮን ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ መዋሉ፣ ከተማዋ በናስ ሥራዎቿ የታወቀች ስለነበር ሊሆን ይችላል።

**2፡19** ቁጥሩ ኢየሱስ ለትያጥሮን አማኞች አገልግሎት የሰጠው እውቅና ነው። እነርሱ በመንግሥቱ ሥራ ንቁ ነበሩ፣ በንቃታቸው እየጨመሩ የሚሄዱ። ሆኖም፣ ይህ ማረጋገጫ ቁ. 20 ላይ ያለውን መናፍቅነት አያስቀረውም።

**2፡20 "ዳሩ ግን፣ ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤"** ይህ ጠቃሽ ነው፣ I ነገሥ.. 16:31-33፤ II ነገሥ. 9:21-22 ካለችው

ኤልዛቤል። አሌክሳንድሪነስ (ኤምኤስኤስ ሀ) "እርሳቸው" የሚል ከኤልዛቤል ፊት ይጨምራል፣ እሱም በአንድምታው የዚህ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሚስት ወይም ንቁ የቤተ-ክርስቲያን መሪ ልትሆን የምትችል። ይህ ግን የዝምብሎ ግምት ነው። የእሷ አስተምህሮት (ዝኪ. ቁ. 20ሐ) ከበለዓማውያን ጋር ተመሳሳይ ነው ቁ. 14ለ እና ከኒቆላውያን ቁ. 15።

ኤልዛቤል የሴት ነቢይት ስለነበረች አልተተወችም። በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ይኖራሉ፣ ለመልካም ሴት መሪዎች።

1. ማርያም፣ ዘጸ. 15፡20
2. ዲቦራ፣ መሳፍንት 4፡4
3. ሁልዳህ፣ 2 ነገሥት 22፡14
4. ሐና፣ ሉቃስ 2፡36
5. የፊሊጶስ ሴት ልጆች፣ ሐዋ. 21፡9
6. ፎቤ፣ ሮሜ 16፡

**ልዩ ርዕስ፡ ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

I. ብሉይ ኪዳን
ሀ. ከባህል አንጻር ሴቶች እንደ ንብረት ይታያሉ
1. በንብረት ዝርዝር ውስጥ ተካተዋል (ዘፀ 20÷17)
2. የባሪ ሴቶች አያያዝ (ዘፀ.21÷7-11)
3. የሴቶች መሃላዎች ወይም ቃል ኪዳኖች በማህበረሰቡ ኃላፊነት ባለባቸው ወንዶች ሊሻር ይችላል (ዘሑ.30)፡፡
4. ሴቶች በጦርነት ወቅት እንደ ዘረፋ ይቆጠሩ ነበር (ዘዳ.20÷10-14፤21÷10-14)
ለ. በተግባር የጋራ የሆኑ ባህርያት
1. ወንድና ሴት በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠሩ (ዘፍ.1÷26-27)
2. አባትና እናትን አክብር (ማክበር ዘፀ 20÷12 ዘዳ. 5÷16)
3. እናትንና አባትን መፍራት (ዘሌ. 19÷3፤20÷9)
4. ወንድና ሴት ናዝራውያን ሊሆኑ ይችላሉ ( ዘሑ. 6÷1-2)
5. ሴት ልጆች የመውረስ መብት አላቸው (ዘሑ.27÷1-11)
6. የቃል ኪዳን ሕዝብ ክፍል ናቸው (ዘዳ.29፡10-12)
7. የአባትንና የእናትን ትምህርት (ቃል መከተል (ምሳ.1÷8፤6÷20)
8. የሔዋን ወንድና ሴት ልጆች ‹የሌዊ ብተሰብ) በቤተመቅደስ ውስጥ አምልኮን ይመሩ ነበር (1ኛ ዜና 25÷5-6)
9. በመጨረሻው ዘመን ወንድና ሴት ልጆች ይተነብያሉ (ኢዮዔ.2÷28-29)፡፡
ሐ. ሴቶች በአመራር ቦታ/ሚና
1. ማርያም፣ የሙሴ እህት ነብይት ተብላ ነበር (ዘፀ. 15÷20-21) እንዲሁም ሚክ.6÷4ን ይመልከቱ፡፡
2. ለማደሪው ድንኳን የሚያገለግሉ ነገሮችን ለመሸመን እግዚአብሔር ሥጦታን ሰጥቷቸው ነበር (ዘፀ.35÷25-26)፡፡
3. ሁሉንም የእሥራኤል ነገዶች የመራች ዲቦራ የተባለች ሴት ነብይት ነበረች (መሳ.4÷4-5፤ 5÷7)
4. ጠፍቶ የነበረውን እና በኋላም የተገኘውን የ«ሕጉን መጽሐፍ» ታነበው እና ትተረጉመው ዘንድ ንጉሥ ኢዮሲያስ የለመናት ህልዳና ነብይት ነበረች (2ኛ ነገ.22÷14፤2ኛ ዜና 34÷22-27)፡፡
5. የእግዚአብሔር ሰው ንግሥት አስቴር በፋርስ የነበሩትን አይሁድ ከሞት ታደገች፡፡

II. አዲስ ኪዳን
ሀ. ከባህል አንጻር በአይሁድ እና በግሪኮ-ሮማን ዓለም ከተወሰኑ መብቶች ጋር እንደ ሁለተኛ ዜጎች ይቆጠሩ ነበር/ መቄዶንያ ግን በዚህ አትካከትም)/(ከመቄዶንያበስተቀር)
ለ. ሴቶች በአመራር ሚና
1. ኤልሳቤጥና ማርያም፤ ለእግዚአብሔር የተገኙ የእግዚአብሔር ሰዎች (ሉቃ.1፡2)
2. የእግዚአብሔር ሰው ሃና በቤተመቅደስ ታገለግል ነበር (ሉቃ.2፡36)
3. ሊዲያ አማኝና የቤት ውስጥ ቤተክርስቲያን መሪ (የሐዋ.16፡14-40)
4. የፊልጶስ አራት ደናግለ ሴቶች ነብያት ነበሩ (የሐዋ.21፡8-9)
5. ፌቨን በ ክንክራኦስ ላለቸው ቤተክርስቲያን የሴት ዲያቆን ነበረች (ሮሜ. 16÷1)፡፡
6. ጵርስቅላ ከውሎስ ጋር አብራ የምትሠራና የአጵሎስ አስተማሪ (የሐዋ.18፡26፤ ሮሜ 16፡3)
7. ማርያ፣ዩሊያን፣ብልያጦን፣ ስንጣክ፣የኔረስ እህት፣እና ከጳውሎስ ጋር ይሰሩ የነበሩ በርካታ ሴቶች ነበሩ(ሮሜ 16፤6-16)፡፡
8. ዩሊያ (KJV)፣ ምናልባትም የሴት የሴት ሐዋርያ ነበረች (ሮሜ. 16÷7)።
9. ኢዮዲያና ሊንጢኬ ከጳውሎስ ጋር አብረው የሚሰሩ (ፊልጵ.4÷2-3)፡፡

III. የዘመናችን አማኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን ሚዛናቸውን እንዴት ይጠብቃል?

ሀ. የመጀመሪያዎቹን የመልእክቱን ተቀባዮች ብቻ የሚመለከቱትን ታሪካዊና ባህላዊ እውነቶችን ከዘላለማዊእውነት አንፃር ለሁሉም ቤተክርስቲያናት በሁሉም ዘመንለሚገኙ ሁሉም አማኞች እውነቱን እንዴትማስተላለፍ ይቻላል?

1. በመንፈስ ቅዱስ መነዳት መልዕክቱን የጻፈውን የመጀጀመሪያውን ጸሐፊ ዋና ሃሳብ/ዓላማ በደንብ ማጤን አለብን፡፡
2. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ በመሆኑም ለእምነትና ለተግባር ብቻኛው ምንጭ ነው፡፡
3. ታሪክ ቀመስ የሆኑ እና በእግዚአብሔር መንፈስ መሪት የተፃፉትን ጽሑፎች ማጤን አለብን፡፡

   ሀ. የእስራኤል (የሐዋ.15፤ገላ.3፤ልማዶች (የቤተክርስቲያ ሥርዓት))

   ለ. የመጀመሪያውን ክፍለ ዘመን የአይሁድ ኃይማኖት የሚያመለክት

   ሐ. የ1ኛ ቆሮንጦስ ውስጥ የተጠቀሱትን ታሪክ ቀመስ የሆኑ የጳውሎስንጸሑፎች

   1) የአረማዊው የሮም መንግሥት የህግ ሥርዓት (1ኛ ቆሮ.6)
   2) ባሪ መሆን (1ኛ ቆሮ.7÷20-24)
   3) ጃንደረባነት (1ኛ ቆሮ.7÷1-35)
   4) ደናግል (1ኛ ቆሮ.7÷36-38)
   5) ለጣኦት የሚሰዋ ምግብ (1ኛ ቆሮ. 8፤ 10÷23-33)
   6) በጌታ ራት ላይ የሚከናወኑ ያልተገቡ ነገሮች /ድርጊቶች (1ኛ ቆሮ.11)

4. በተወሰነ ወቅትና በተወሰነ ባህል ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ገልጧል፡፡ እኛ ግን በትኩረት መቀበል ያለብን መገለጡን እንጂ ማንኛውንም ከመገለቱ ጋር የተቆራኙትን ታሪካዊ ሁነቶችን አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው በተወሰነ ወቅት በተወሰነ ባህል ውስጥ በሰው ቃል የተጻፈ ነው፡፡

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎም የመጀመሪው ጽሐፊ ዓላማ/ሐሳብ መፈለግ አለበት፡፡ በጊዜው ለማለት የፈለገው ምን ነበር? ለትክክለኛ አተረጓጎም ይህ ወሣኝናመሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህንእውነት እኛ ለዘመናችን ሥራ ላይልናውለው ይገባል፡፡ አሁን በዚህ ክፍል ላይ በአመራር ላይ ሰላሉት ሴቶች ላይችግር አለ (እውነተኛው የአተረጓጎም ችግር የሚከሰተው ቃሉን መተርጎሙ ላይነው፡፡ እንደመሪዎች ከሚለዩት መጋቢዎች ይልቅ ብዙ አገልግሎቶች ነበሩ ማለትነው? ወይስ ሴት ዲያቆናትና ሴት ነብያት እንደጨዋዎች ይታዩ ይሆን? ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንጦስ 14፡34-35 እና 1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡9-15 ላይ ሴቶች በጉባኤ አምልኮ ላይ መምራት እንዳሌለባቸው አስረግጦ መናገሩ በጣም የተገለጠ ነው! ይሁን እንጂ ያንን እውነትዛሬ እንዴት ነው ሥራ ላይ የማውለው? የጳውሎስም ሆነ የእኔ ባህል የእግዚአብሄርን ቃልና ፈቃዱን ዝም እንዲያሰኘው አልፈልግም፡፡ ምናልባት የጳውሎስ ዘመን ገደብ የበዛበት ሊሆን ይችላል፤ በአንፃሩም ደግሞ እኔ ያለሁበት ዘመን ደግሞ ገደብ የለበትም፡፡

የጳውሎስ ቃላትና አስተምሮዎች ሁኔታዊና የመጀመሪያው ክፍለዘመን እውነቶች ብቻ ናቸው ማለት ለእኔ አይመቸኝም፡፡ የእኔ አእምሮና የእኔ ባህል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የጻፈን ጸሐፊ መቃወም አለበት ለማለት እኔ ማነኝና?

ይሁን እንጂ የሴተር መሪዎችን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ሲኖሩ ታዲያ ምንድ ነው የማደርገው? (በጳውሎስ ጽሑፎች በሮሜ 16 እንኳ)? ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንጦስ ምዕ. 11-14 ላይ የሰጠው ትንታኔ ነው፡፡ በ11÷5 ላይ ሴቶች ራሳቸውን ሸፍነው በጉባኤ ላይ እንዲሰብኩና እንዲጸልዩ የሚፈቅድ ይመስላል፤ ይሁን እንጂ በ14÷34-35 ላይ ደግሞ ጸጥ እንዲሉ ይፈልጋል፡፡ ሴት ዲያቆናትና (ሮሜ. 16) እና ሴት ነብያት ነበሩ (የሐዋ.21÷9)፡፡ ይህ ልዩነት ነው እንግዲህ ጳውሎስ የሰጠው ማብራሪያ (በሴቶች ላይ ከሚደረገው ማዕቀብ ሰለሚገናኝ) በመጀመሪያው ክፍለመን ለነበሩ የቆሮንጦስና የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ብቻ የተወሰነ ነው እንድል ነፃነትን የሚሰጠኝ፡፡ በሁለቱም ቤተክርስቲያናት ውስጥ አዲስ የተመሰረተውን ነፃነት ሴቶች ለመጠቀም ችግሮች ነበሩ፤ ይህም በጊዜው የነበረችው ቤተክርስቲያን የጠፉትን በክርስቶሰ ወንጌል ለመድረስ ችግር በፈጠረ ነበር፤ ወንጌል ይስፋፋና ፍሬያማ ይሆን ዘንድ የነበራቸው ነፃነት መገደብ ነበረበት፡፡

እኔ ያለሁበት ዘመን ከጳውሎስ አንፃር ተቃራኒ ነው፡፡ እኔ ባለሁበት ዘመን ወንጌል ምናልባት ሊገደብ የሚችለው የሰለጠኑና የተማሩ ሴቶች ወንጌልን ካለሰሰበኩ እንጂ ካልመሩ አይደለም! የጉባኤ አምልኮ ዋነ ግብ ምንድ ነው? ወንጌልና ደቀመዝሙርነት አይደለም? እግዚአብሔር በሴት መሪዎች ሊከብርና ደስ ሊሰኝ ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅላላው «አዎን» የሚል ይመስላል፡፡

ለጳውሎስ ሐሳብ ራሴን ማስገዛት እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም የእኔ ሥነ-መለኮት ከመጀመሪው የጳውሎስ ነውና፡፡ አሁን በሚታየው የሴቶች እንቅስቃሴ ተፅዕኖ እንዲደርስብኝ ወይም ማሰመሰል አልፈልግም! ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያን በግል የሚታዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለምሳሌ የባርነትን ተገቢ አለመሆን፣ ዘረኝነትን፣ ልቅ ወሲብን እና አክራሪነት ላይ ምላሽ ለመስጠት ለዘብተኛ ናት፡፡ እንዲሁም ባለንበት ዘመን በሴቶች ላይ በሚደረገው ጥቃት ላይ ተገቢውን መላሽ ለመስጠት ቸልተኛ ናት፡፡ እግዚአብሔር ባሪያንም ሆነ ሴትን በክርስቶስ ነፃ አውጥቷል፡፡ በቤተክርስቲያን የተሠራ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንዲያሰራቸው አልፈቅድም፡፡

አንድ ሌላ ነጥብ ላንሳ፤ አንድ ተርጓሚ የቆሮንጦስ ቤተክርስቲያን በጣም የተበጠበጠች ቤክርስቲያን ነበረች፡፡ የካሪዝማቲክ ስጦታዎች (የጸጋ) ሽልማት ያሰጡና ያኮሩ ነበር፡፡ ምናልባትም ሴቶች በዚህ ሁኔታ ቴዘውም ሊሆን ይችላል፡፡ በኤፌሶን ባሉ የቤት ውስጥ ቤተክርስቲያናት ሴቶችን ለግል ጥቅማቸው መጠቀሚያ የሚያደርጉና ቅጥረኛ ሰባኪዎች አድርገው የሚጠቀሚቸው የሐሰት መምህራን በኤፌሶን ተጽእኖ እንደደረሰ ጭምር አምናለሁ፡፡

ሐ. ለተጨማሪ ምንባብ አስተያየት

*How to Read the Bible for All Its Worth* በጎርደን ሊ እና ዳግላስ ሰቱዋርት (ገጽ 61-77)
*Gospel aNd Spirit: Issues iNNew TestameNt HermeNeutics*በጎርደን ፊ.*Hard SayiNgs of the Bible* በ ዋልተር ሲ.ኬይዘር፤ ፒተር ኤች ዳቢድስ፤ ኤፍ ኤፍ ብሩስ እና ማንፍሬድ ቲ ብራንች (ገጽ 613-616፤ 665-667)፡፡

**2፡21** የእግዚአብሔር ምሕረት እና ትዕግሥት እንዲሁም ፍትሑ ተረጋግጧል ቁ. 21-23 (ሮሜ. 2:5)።

**2፡22 "እነሆ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ"** ይህ ከዝሙት አልጋዋ ጋር የተያያዘ ስላቅ ነው (ስለ ኢ-ሞራላዊነት ትምህርት)።

◘ **"ታላቁ መከራ"** ልዩ ርዕስ፡ መከራ 2፡9 ላይ እና ትልቁ የፍጻሜ ዘመኑ 7፡14 ላይ ተመልከት።

◘ **"ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ነው፣ እሱም ወደፊት የሚፈጸም ሁነኛ ድርጊትን ያመለክታል፣ ግን ከተጠባባቂ ነገሮች ጋር።

**2፡23 "ልጆቿንም እገድላለሁ"** ይህ ጥሬአዊ ልጆቿን አያመለክትም፣ ተከታዮቿን እንጂ (ዝከ. 2፡22፤ 2 ዮሐንስ ቁ. 1)።

◘ **"አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ያውቃሉ"** ይህ የሚያመለክተው ሰባቱም መልእክቶች በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እንደሚነበቡና እውነቱም በሁሉም እንደሚተገበር ነው፣ ከዚያ በኋላም ሆነ አሁን። ለ "ቤተ-ክርስቲያን" ልዩ ርዕስ 1፡4 ላይ ተመልከት።

◘ **"አዕምሮንና ልብን የምመረምር እኔ ነኝ"** መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስረግጠው እግዚአብሔር የሰዎችን ሁሉ የውስጥ ሐሳብና አስተሳሰብን ማወቁን ነው (መዝ. 7፡9፣ 26፡2፤ 39:1፤ ምሳ. 24:12፤ ኤር. 11:20፤ 17:10፤ ሉቃስ 16:15፤ ሐዋ. 1:24፤ ዕብ. 4:12-13፤ 8:27)።

## ልዩ ርዕስ፡- ልብ

"ካርዲያ" *Kardia* የሚለው የግሪኩ ቃል leb ልብ የሚለው የእብራይስጡን ቃል (BDB 523) ለማንጸባረቅ በሰብትዋጅንት እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ቃል በተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል (Bahuer፣ ArNdt፣ Giagrich aNd DaNker፣ *A Greek-ENglish lexicoN* pp.403-404)::

1. የተፈጥሮአዊ ሕይወት ማእከል፤ ለሰው የሚደረግ ተለዋዋጭ ዘይቤ (የሐዋ.14:17፤ 2ኛ ቆሮ.3:2-3፤ ያዕ. 5:5)
2. የመንፈሳዊ ሕይወት ማዕከል (ማለትም ሞራላዊ)
   ሀ. እግዚአብሔር ልብን ያውቃል (ሉቃ.16:15፤ሮሜ 8:27፤ 1ኛ ቆሮ. 14:25፤ 1ኛ ተሰሎ.2:4፤ ራዕ.2:23)
   ለ. የሰውን ልጅ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያመለክት (ማቴ.15:18-19፤ሮሜ.6:17፤ 1ኛ ጢሞ. 1:5፤ 2ኛ ጢሞ.2:22፤1ኛ ጴጥ. 1:22)
3. የአስተሳሰብ ሕይወት ማዕከል (እውቀት ማቴ.13:15፤24:48፤ የሐዋ.7:23፤16:14፤28:27፤ሮሜ.1:21፤10:6፤2ኛ ቆሮ.4:6፤ኤፌ. 1:18፤4:18፤ ያዕ.1:26፤ 2ኛ ጴጥ.1:19፤ራእ.18:7፤ ልብ ከአእምሮ ገር ተመሳሳይ ነው በ2ኛ ቆሮ.3:14-15 እና ፊልጵ 4:7)
4. የፈቃድ ማዕከል (ማለትም ፈቃድ የሐዋ.5:4፤11:23፤1ኛ ቆሮ. 4:5፤5:37፤2ኛ ቆሮ.9:7)፡፡
5. የስሜቶቻችን ማዕከል (ማቴ.5:28፤ የሐዋ. 2:26፡37፤7:54፤21:13፤ሮሜ 1:24፤ 2ኛ ቆሮ. 2:4፤7:3፤ኤፌ.6:22፤ ፊልጵ.1:7)፡፡
6. የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ልዩ ሥፍራ (ሮሜ 5:5፤ 2ኛ ቆሮ. 1:22፤ገላ.4:6/ክርስቶስ በልባችን፡-ኤፌ. 3:17/)
7. ልብ የአንድን ሰው ሁለንተና የሚያመለክት ተለዋዋጭ ዘይቤ ነው (ዘይቤያዊ ቋንቋ) ነው (ማቴ.22:37 ከዘዳ. 6:5 የተወሰደ)፡ ፡ ሃሳቦች፣ዓላማዎች፣ ድርጊቶች አንድ ላይ ተቀናጅተው የግለሰቡን ማንነት ያሳያሉ፡፡ ብሉይ ኪዳን ጎላ ያለ የቃሉ አጠቃቀም አለው፡፡
   ሀ. ዘፍ. 6:6፤8:21 "እግዚአብሔር በልቡ ተጸጸተ" ሆሴ. 11:8-9ንም አስታውል
   ለ. ዘዳ.4:29፤ 6:5 "በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ"
   ሐ. ዘዳ. 10:16 "ያልተገረዘ ልብ" እና ሮሜ 2:29፡፡
   መ. ሕዝ.12:31-32 "አዲስ ልብ"
   ሠ. ሕዝ 36:26 "አዲስ ልብ" እና "የድንጋይ ልብ"

◘ **"ለእያንዳንዳችሁ እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ"** ይህ መንፈሳዊ ሐቅ እጅግ ግልጽ ሆኖ ገላ. 6፡7 ላይ ቀርቧል። የዘራነውን እናጭዳለን። ይህ መርሕ አንድምታው ደኅንነት በሰው ጥረት አይደለም (ኤፌ. 2፡8-9)፣ ነገር ግን በክርስቶስ እግዚአብሔርን ያገኙ ሰዎች መልካም፣ ፍቅራዊ፣ ያገልግሎት ሕይወት ይኖራሉ ለማለት ነው (ዝከ. 3:12፤ ማቴ. 25:1-46፤ ኤፌ. 2:10)።

ይህ መንፈሳዊ መርሕ ነው። እግዚአብሔር ሥነ-ምግባራዊ—ሞራላዊ ነው፣ እንዲሁም የእሱ ፍጥረት። ሰዎች ራሳቸውን የሚያቋርጡት በእግዚአብሔር መለኪያዎች ነው። የዘራነውን እናጭዳለን። ይህ ለአማኞች እውነት ነው (ነገር ግን ደኅንነትን አይነካም) እና ለማያምኑት (ኢዮብ 34:11፤ መዝ. 28:4፤ 62:12፤ ምሳ. 24:12፤ መክ. 12:14፤ ኤር. 17:10፤ 32:19፤ ማቴ. 16:27፤ 25:31-46፤ ሮሜ. 2:6፤ 14:12፤ I ቆሮ. 3:8፤ II cor. 5:10፤ ገላ. 6:7-10፤ I ጢሞ. 4:14፤ I ጴጥ. 1:17፤ ራዕ. 2:23፤ 20:12፤ 22:12)።

**2፡24 "የሰይጣንን ጥልቅ ነገር"** ከዚህ ሐረግ ጋር በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች ይዛመዳሉ። እሱም የሚያመለክተው

1. ከኤልዛቤልና ከተከታዮቿ ጋር የተያያዘ ሐረግ
2. ከግኖስቲክ የሐሰት መምህራን፣ የእውቀት አጽንዖት
3. ከሮማ ኢምፓየር ምሥጢራዊ ሃይማኖቶች የማኅሣሻ አምልኮ ሥርዓቶች
4. ፍጹም ተቃርኗዊ በሆነ መንገድ፣ "የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገሮች" (ሮሜ. 11:33፤ 1 ቆሮ. 2:10፤ ኤፌ. 3:18)

▣ **"ሌላ ሸክም አልጭንባችሁም"** ይህ ለእውነተኛ አማኞች በትያጥሮን ከተማ ማረጋገጫ ነው። እነርሱ ንቁ የሆነ ቁርጠኛ እምነት ነበራቸው (ዝከ. ቁ. 19)።

**2፡25 "እስከመጣ ድረስ ያላችሁን ጠብቁ"** የክርስቶስ ተከታዮች መጠበቅ አለባቸው (ዝከ. ቁ. 20) በስደት፣ በመናፍቅነት፣ እና ተስፋ በመቁረጥ መሐል። ይህ ትእዛዝ ነው (የድርጊት ያሁን ተተኳሪ)። ኢየሱስ በመንገዱ ላይ ነው፤ በቅርብ ይመጣል (ዝከ. 2:16፤ 22:7፣ 20)። ይህ የሁሉም ትውልድ ክርስቲያኖች ተስፋ እና ማበረታቻ ነው።

**2፡26-27** ይህ የመዝሙር 2፡8-9 ጠቃሽ ነው፣ ከኢሳ. 30፡14 እና ኤር. 19፡11 ጋር፣ ተጨምሯል። ኢየሱስ መሲሐዊ ንጉሥ ነው። መንግሥቱም በመላው ዓለም ኃይልና ፍጻሜ የሚመጣ ነው። እሱም በሁሉም የሚገባው ይሆናል፣ አገልጋዮቹ ሲመለከቱት!

**2፡26 "ሕዝቦች"** የዚህ ቃል አጠቃቀም ከብኪ እንድምታው፣ እሱ የሚያመለክተው ከያህዌ ኪዳን ውጭ ያሉትን ነው (የተለየው 7፡9) ነው። እሱም መልካም የለሽ፣ ክፉ ሰዎችን ለማመልከት ነው (ዝከ. 2:26፤ 5:9፤ 10:11፤ 11:2፣9፣18፤ 12:5፤ 13:7፤ 14:6፣8፤ 16:19፤ 17:15፤ 18:3፣23፤ 19:15፤ 20:8)።

**2፡27 "እኔም ሥልጣን ከአባቴ እንደተቀበልኩ"** ኢየሱስ ገና ድሮ ሥልጣን ሁሉ ተሰጥቶታል (መዝሙር 2፤ ማቴ. 28:18፤ ፊሊ. 2: 9-11)። የኢየሱስ መንግሥት የአሁን ነው፣ ግን አልተቀዳጀነውም።

ከብኪ ቁጥር 27 ላይ የተጠቀሰው ከመዝ. 2፡8 ነው፣ እሱም በመነሻው መሲሕን የሚያመለክት (ዝከ. 12:5፤ 19:15)፣ እዚህ ግን ጥቅም ላይ የዋለው ለአማኞች ነው እምነታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባኖሩት። ከእርሱ ጋር ይገዛሉ። ልዩ ርዕስ 5፡10 ላይ ተመልከት።

**2፡28 "የንጋት ኮከብንም እሰጠዋለሁ"** በርካታ የዚህ ሐረግ ታሳቢ ትርጓሜዎች ነበሩ፡
1. እሱ የሚያመለክተው የክርስቶስን ዘይቤ ነው (ራዕ. 22፡16)
2. እሱ የሚያመለክተው ከክርስቶስ ጋር ቀረብ ያለ እውቀትና ወዳጅነት ነው (2 ጴጥ. 1፡19)
3. እሱ የሚያመለክተው ትንሣኤን ነው (ዳን. 12፡3)
4. እሱ የሚያመለክተው ወታደራዊውን መሲሕን ነው ዘኍ. 24፡17 ላይ የተጠቀሰውን
5. እሱ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ደስታ ነው (ኢዮብ 38፡7)
6. እሱ የሚያመለክተው ለሰይጣን ጥቅም ላይ የዋለውን ሐረግ ነው ኢሳ. 14፡12 ላይ፣ አሁን ግን ለክርስቶስ

**2፡29** 2፡7 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት

## ራዕይ 3፡1-6

**[1]በሰርዴስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲህ ይላል። ሥራህን አውቃለሁ ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህማል። [2]ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን፥ ሊሞቱም ያላቸውን የቀሩትን ነገሮች አጽና። [3]እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፥ ጠብቀውም ንስሐም ግባ። እንግዲያስ ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም። [4]ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋር አሉ፥ የተገባቸውም ስለ ሆኑ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ። [5]ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ። [6]መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።**

**3፡1 "ቤተ ክርስቲያን"** ልዩ ርዕስ 1፡4 ላይ ተመልከት።

▣ **"ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት እና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት"** ይህ ሐረግ ለከበረው ክርስቶስ ሌላ ጠቃሽ ነው (ዝከ. 1፡4፣16፣20)። ሰባቱ ከዋክብት የሚያመለክቱት ቤተ-ክርስቲያኖችንና 1፡20 ያሉትን መሪዎቿን ነው፤ ሰባቱ ከዋክብት ምናልባት ተጓዳኝ ዘይቤ ይሆናሉ፣ ምክንያቱም 4፡5 ላይ እነርሱ የሚዛመዱት ከሰባቱ መቅረዞች ጋር በመሆኑ፣ ደግሞም 1፡20 ላይ የተጠቀሱት፣ ቤተ ክርስቲያኖችን የሚያመለክቱት። እነዚህ ሰባት የእግዚአብሔር መናፍስት 5፡6 ላይ ደግሞ ተጠቅሰዋል፣ እንደ በጉ መግለጫ ክፍል። ልዩ ርዕስ፡ ሰባቱ መናፍስት 1፡4 ላይ ተመልከት።

▣ **"ሥራህን አውቃለሁ"** ኢየሱስ የቤተ-ክርስቲያኖቹን ጥንካሬና ድካም ያውቃል (ዝከ. 2:2፣19፤ 3:1፣8፣15)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ"** |
| **አየተመት** | **"ሕይወት እንዳለህ ስም አለህ"** |

**አእት** **"ሕይወት እንዳለህ ትጠራለህ"**
**አኢመቅ** **"ሕይወት እንዳለህ እንደምትጠራ"**

ይህ አጥፊ መገለጥ ነው። እነርሱ የሚያስቡት ከእግዚአብሔር ጋር ልክ እንደሆኑ ነው፣ በመንፈስ እሱን እንደሚያስደስቱ (ኢሳ. 29፡13፤ ሮሜ. 2፡19-20፤ ቆላ. 2፡16-23፤ II ጢሞ. 3፡5)፣ ግን አይደሉም!

**3፡2**
**አአመመቅ፣ አየተመት**
**አእት፣ አኢመቅ** **"ንቃ"**
**አኪጀት** **"ንቃ በል"**

ይህ የአሁን *መካከለኛ (አረጋጋጭ) ተተኳሪ* (ከአሁን የድርጊት አንቀጽ ጋር)፣ በጥሬው "ቀጣይነት ባለው መልኩ ንቃ" ነው። እሱም በቁጥር 2 እና 3 ከሚገኙት አምስት *የአሁን ተተኳሪዎች* አንደኛው ነው። ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ያዛል፣ እንድትነቃ!

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"የቀሩትን ነገሮች አጽና"**
**አየተመት** **"የቀሩትን አጽና"**
**አእት** **"አሁንም ያሉህን አጽና"**
**አኢመቅ** **"በቀረህ ጥቂት ኃይል ጥቂት ጽናትን ጨምር"**

ይህ የድርጊት የአሁን ተተኳሪ ነው። እነርሱ አሁን እንዲያደርጉ በቀጣይነትም በድርጊታቸው እንዲቀጥሉ፣ እየሞተ ባለው እምነታቸው በመጽናት።

▣ ***"ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና"*** የመጀመሪያው ግሥ የተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች ነው። እነርሱ መንፈሳውያን ይመስላሉ (ኢሳ. 29፡13)፣ ነገር ግን እነርሱ በእጅጉን ሃይማኖታዊ ሰዎችን ነው የሚመስሉት ማቴ. 7፡21-23 እና ቆላ. 2፡16-23 ላይ የተጠቀሱትን።

"ፍጹም" የሚለው ቃል የተጠናቀቀ ተገብሮ አንቀጽ ሲሆን፣ ፍችውም "የበሰለ፣ ፍጹም፣ ለሆነ ተግባር ብቁ የሆነ" ማለት ነው። እነርሱ፣ እግዚአብሔር እንዲያጠናቅቀው አልፈቀዱለትም፣ እምነት የጀመረውን (ፊሊ. 1፡6)።

**3፡3 "እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ"** ይህ የአሁን የድርጊት ተተኳሪ ነው፣ የተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች እና የድርጊት የአሁን አመላካች የሚከተለው። ይህ ከሰሙት እና በቀጣይም ከሚቀበሉት ወንጌል ጋር ይዛመዳል። ክርስትና ውሳኔ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን የሕይወት ስልት ግንኙነት እንጂ ነው። እሱም መልእክቱን ማመንና ሰውየውን መቀበልን ያካትታል። እሱም የተለወጠና የሚለወጥ የንስሐ ሕይወት ውጤት አለው (የድርጊት የአሁን ተተኳሪ፣ ቁ. 3ለ) እና ታዛዥነት (የአሁን የድርጊት ተተኳሪ፣ ቁ. 3ለ)።

▣ **"ጠብቀው"** ይህ የአሁን የድርጊት ተተኳሪ ነው እሱም ቀጣይነት ያለው ትእዛዝ።

▣ **"ንስሐ ግባ"** ይህ የድርጊት የአሁን ተተኳሪ ነው፣ ፍጹም የሆነ ንስሐን የሚያመለክት። 2፡5 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ስለሆነም ባትነቃ ግን"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ-ነገር ነው፣ እንደ 2፡22። ይህ ድርጊት የሚወሰነውና የሚያያዘው ለኢየሱስ ትእዛዝ በሚሰጡት ምላሽ ነው፣ ግን አልተረጋገጠም።

▣ **"እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ"** ይህ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ከዳግም ምጽአቱ ጋር ነው (ማቴ. 24፡43-44፤ ሉቃስ 12፡39-40፤ I ተሰ. 5፡2፣4፤ II ጴጥ.3፡10፤ ራዕ. 16፡15)። ሆኖም፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የሚመስለው የዚህ ቤተ ክርስቲያን ጊዜያዊ ፍርድ ነው።

**3፡4 "ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች"** ልብስን መልበስና ማውለቅ ለክርስትና ሕይወት እንደ ዘይቤ ጥቅም ላይ ይውል ነበር (ኤፌ. 4፡22፣24፣25፣31፤ ቆላ. 3፡8፣10፣12፣14፤ ዕብ. 12፡1፤ ያዕቆብ 1፡21፤ 1ጴጥ. 2፡1)። አንዳንድ አማኞች ከጣዖት ባህል ጋር አይደራደሩም።

▣ ***"ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ"*** ነጭ ልብስ እንደ ተምሳሌት ጥቅም ላይ የሚውለው ለንጽሕና ወይም ለድል ነው ቁ. 4፣ 5፣18፤ 6፡11፤ 7፡9፣13-14፤ 19፡14። "መራመድ" የሚለው ቃል ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለክርስትና ሕይወት ነው (ዝኪ. 3፡5፤ 21፡24፤ I ዮሐንስ 1፡6፣7፤ 2፡6፣11፤ III ዮሐንስ 3-4)።

**3፡5 "ድል የሚነሣ"** ድል ለሚነሣ አራት ነገሮች ይሰጡታል።

1. ከመሲሑ ጋር ይራመዳሉ፣ ቁ. 4
2. ነጭ ልብስ ይለብሳሉ
3. ስማቸው ከሕይወት መጽሐፍ አይደመሰስም
4. መሲሑ የራሱ እንደሆኑ ይመሰክርላቸዋል፣ በአብና በመላእክቱ ፊት

ልዩ ርዕስ ጽናት (ትዕግሥት) 2፡2 ላይ ተመልከት።

▣ **"ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም"** ይህ ጠንካራ ድርብ አሉታዊ ነው። ዜጎች ሲሞቱ ስማቸው ከከተማቸው መዝገብ ላይ ይሰረዛል፣ እግዚአብሔር ግን አማኞችን ከመዝገቡ አይሰርዛቸውም።

ይህ ዘይቤአዊ ሐረግ "የሕይወት መጽሐፍ" ደግሞ ራዕ. 20፡12-15 ላይ ይገኛል፣ እዚያም ሁለት መጽሐፍ የተጠቀሱበት፡

1. የሕይወት መጽሐፍ እሱም የእግዚአብሔር ሰዎች ስሞች ያሉበት (ዘጸ. 32:32-33፤ መዝ. 69:28፤ ኢሳ. 4:3፤ ዳን. 12:1፤ ሉቃስ 10:20፤ ፊሊ.. 4:3፤ ዕብ. 12:23፤ ራዕ. 13:8፤ 17:8፤ 20:12፣15፤ 21:27)
2. የድርጊቶች መጽሐፍ ወይም መታሰቢያዎች የሁለቱንም የክፉዎችንና የጻድቃንን ተግባራት የተመዘገቡበት (መዝ. 56:8፣ 139:16፤ ኢሳ. 65:6፤ ሚል. 3:16)

ስለ "መጽሐፍ" 5:1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

◘ **"በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ"** አማኞች ሁሉ ክርስቶስን ይመሰክራሉ ("ስሙን ይጠራሉ፣" ዝከ. ሮሜ 10፡ 9-13)፣ እሱም ደግሞ በአብ ፊት ይመሰክርላቸዋል (ማቴ. 10:32፤ ሉቃስ 12:8)።

"መመስከር" የግሪክ ቃል *exomulogeÔ* ነው። እሱም በሦስት መልኩ ጥቅም ላይ ይውል ነበር፡

1. በይፋ ኃጢአትን ለእግዚአብሔር መናዘዝ፣ ሌሎችም ባሉበት (ማቴ. 3:6፤ ማርቆስ 1:5፤ ሐዋ. 19:18፤ ያዕቆብ 5:16)
2. በክርስቶስ ያለን እምነት በይፋ መመስከር (ፊሊ.. 2:1፤ እና ሮሜ. 14:11)
3. እግዚአብሔርን በይፋ ማመስገን (ማቴ. 11:25፤ ሉቃስ 10:21፤ ሮሜ. 14:11 {ኢሳ. 45:23}፤ 15:9 [መዝ. 18:49])

ተጓዳኝ የግሪክ ቃል *homologeÔ* በተመሳሳይ መንገዶች ጥቅም ላይ ይውል ነበር፡

1. ኃጢአትን ለመናዘዝ (1 John 1:9)
2. በክርስቶስ ያለን እምነት ለማስታወቅ (ማቴ. 10:32፤ ሉቃስ 10:32፤ ዮሐንስ 9:22 [በአሉታ፣ ዮሐንስ 1:20፤ 12:42])
3. በአንድ ነገር ላይ ያለን እምነት ለማጽናት (ሐዋ. 23:8፤ 24:14፤ ዕብ. 11:13)

## ልዩ ርዕስ፡ መናዘዝ

ሀ. መናዘዝ ለሚለው የግሪኩ ስርወ ቃል ከሁለት ቃላት የተሰራ ነው፡፡ «ሆሞሎጀ እና ኤክሶሞሎጀ» ሆሞ የሚለው አንድ አይነት ሲሆን ሎጂ ደግሞ መናጋር እና ኤክሶ የሚለው ደግሞ መውጣት የሚል ፍቺ ይሰጣል፡፡ ስለዚህ የቃሉ ፍቺ አንድ አይነት ነገር ወይም መስማማት በተጨማሪም ኤክሶ ደግሞ በሰው ፊት መናገርን ያጠቃልላል፡፡

ለ. በእንግሊዘኛው ተመሳሳዮቹን ፍቺዎች እንመልከት

1. ማመስገን
2. መስማማት
3. ማወጅ
4. መናገር
5. መናዘዝ

ሐ. ቃሉ በሁለት ተቃራኒ አጠቃቀም ሊኖረው ይችላል፡፡

1. ማመስገን (እግዚአብሔርን)
2. ሐጢያትን ማመን

መ. በአዲስ ኪዳን መናዘዝ ማለት፡-

1. መሃላ ማድረግ (ማቴ 14፡7፣ሐዋ 7፡17)
2. መስማማት (ዮሐ 1፡20፣ ሉቃ 22፡6 ሐዋ24፡14፣ ዕብ 11፡19)
3. ማመስገን (ማቴ 11፡25፣ ሉቃ10፡21፣ሮሜ 14፡11፣ 15፡9)
4. ቃሉ የሚያመለክተው፡-
   ሀ. ለግለሰብ (ማቴ 10፡32፣ ሉቃ 12፡8፣ ዮሐ 9፡22)
   ለ. አእውነት (ሐዋ 23፡8፣ 2ቆሮ 11፡13፣ 1ዮሐ 4፡2)
5. በሰዎች ፊት ማወጅ (የራስን Eምነት ለመግለፅ) ሐዋ 24፡1 1ጢሞ 6፡13)
   ሀ. ከበደለኝነት ነፃ መሆን (1ጢሞ 6፡12፣ ዕብ 10፡23)
   ለ. ከመበደል ነፃ Aለመሆን (ማቴ 3፡6፣ ሐዋ 19፡18፣ ዕብ 4፡14፣ያዕ 5፡16 1ዮሐ 1፡9)

**3፡6** 2፡7 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

## ራዕይ 3፡7-13

**7በፊልድልፍያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። የዳዊት መክፈቻ ያለው፤ የሚከፍት፥ የሚዘጋም የሌለ፤ የሚዘጋ፥ የሚከፍትም የሌለ፤ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው እርሱ እንዲህ ይላል። 8ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ፥ በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፥ ስሜንም አልካድህምና። 9እነሆ፥ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን እሰጥሃለሁ እነሆ፥ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ። 10የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ። 11እነሆ፥ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ፤ ማንም አክሊልህን እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ። 12ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፥ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ። 13መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።**

**3፡7 *"ቅዱስና እውነተኛ የሆነ"*** ቁጥር 7 የአራት ገላጭ ሐረጎች ተለጣጣቂ ሲሆን የሚገልጸውም ኢየሱስን በያህዌ መጠሪያ ነው። "ቅዱስ" 30 ጊዜ በኢሳይያስ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ያህዌን ለመግለጽ። ዮሐንስ ዘወትር "ጻድቅ" የሚለውን ቃል ይተካዋል (ዝከ. 15:3፤ 16:7፤ 19:2)። "እውነት" ዘወትር ለያህዌ ጥቅም ላይ ይውላል (ኢሳ. 65:16፤ ኤር. 10:10፤ I ዮሐንስ 5:20፤ ራዕ. 15:3፤ 16:7፤ 19:2)። የፊተኞቹ ሁለቱ፣ "ቅዱስ" እና "እውነተኛ" በድጋሚ ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ራዕ. 6፡10 ላይ። "እውነት" የሚለው ቃል በግሪክ ፍችው "እውነተኛ ውሸትን በመቃወም፣" ሲሆን፣ በዕብራይስጥ ፍችው "የታመነ ወይም ታማኝ" ነው። ኢየሱስ በርግጥ ሁለቱንም ነው (ዝከ. 3:14፤ 19:11፤ 21:5፤ 22:6)።

▣ ***"የዳዊት መክፈቻ ያለው"*** ይህ የንጉሣዊው ዳዊታዊ መሲሕ ጠቃሽ ነው፣ የ2 ሳሙኤል 7፣ ነገር ግን በተለይ የኢሳ. 22፡22፣ ይህ ምስያ የተገኘበት ስፍራ።

▣ ***"የሚዘጋ የሚከፍትም የሌለ"*** ይህ የሚያመለክተው የወንጌልን ስብከት ነው (ቁ. 8 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

---

**ልዩ ርዕስ፡ "በር" የሚለው ቃል አጠቃቀም በአዲስ ኪዳን (አዲስ ኪዳን)**

አዲስ ኪዳን "በር"ን በተለያየ መልኩ ይጠቀማል።

1. ጥሬ ትርጉም
   - ሀ. የቤት፣ ማቴ. 6:6፤ ማርቆስ 1:33፤ 2:2፤ 11:7፣ የላይኛው ክፍል፣ ዮሐንስ 20:19፣26
   - ለ. የቤተ-መቅደስ፣ ሐዋ. 3:2፤ 21:30
   - ሐ. የእስር-ቤት፣ ሐዋ. 5:19፣23፤ 12:6፤ 16:26-27
   - መ. የመቃብር፣ ማቴ. 27:60፤ 28:2፤ ማርቆስ 15:46፤ 16:3
   - ሠ. የበረት፣ ዮሐንስ 10:1፣2
   - ረ. የፍርድ-ቤት፣ ዮሐንስ 18:16፤ ሐዋ. 12:13
2. ዘይቤአዊ
   - ሀ. የጊዜ ቅርበት፣ ማቴ. 24:33፤ ማርቆስ 13:29፤ ሐዋ. 5:9፤ ያዕቆብ 5:9
   - ለ. ወደ እውነተኛ እምነት ለመግባት ማገኛ፣ ማቴ. 7:13-14፤ ሉቃስ 13:24፤ ራዕ. 3:20
   - ሐ. የሚያድነው እምነት የመጥፋት ዕድል፣ ማቴ. 25:10፤ ሉቃስ 13:25፤ ራዕ. 3:7
   - መ. የሚያድነው እምነት ዕድል፣ ሐዋ. 14:27፤ ራዕ. 3:7
   - ሠ. የአገልግሎት ዕድል፣ 1ቆሮ. 16:9፤ 2ቆሮ. 2:12፤ ቆላ. 4:3፤ ራዕ. 3:8
   - ረ. ራዕይ፣ ራዕ. 4:1፤ 19:11
3. ለኢየሱስ መጠሪያ፣ ዮሐንስ 10:7፣9

---

**3፡8 *"በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቻለሁ ማንም አይዘጋውም"*** ይህ የተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች እና የአሁን ተገብሮ አንቀጽ ነው። ይህም የሚያመለክተው አንድም

1. የስብከት ዕድሎች (ቁልፎች፣ ማቴ. 16፡19)
2. ወደ በጉ ራት መግቢያ (ነጭ ልብስ ለብሰው፣ ዝከ. ቁ.4)
3. መለኮታዊ ዕድል ለአገልግሎት (ሐዋ. 14:27፤ I ቆሮ. 16:9፤ II ቆሮ. 2:12፤ ቆላ. 4:3)

▣ ***"ኃይልህ ጥቂት ቢሆንም"*** ይህ ከሦስቱ ምክንያቶች የመጀመሪያው ነው፣ ኢየሱስ ይሄንን አስደናቂ የዕድል በር የከፈተበት። ይሄ ከሰባቱ ቤተ ክርስቲያኖች ብቸኛው ነው፣ ኢየሱስ ምንም አሉታዊ ነገር ያላለበት።

▣ ***"ቃሌን ጠብቀሃልና"*** የግሡ ጊዜ (የድርጊት የአሁን አመላካች) የሚያመለክተው የተወሰነ ጊዜ ስደትን ወይም ወሳኝ የሆነ የመታዘዝ ድርጊትን ነው። እነርሱ "ትንሽ እምነት" አላቸው ግን ደኅና አድርገው ተጠቅመውበታል!

▣ ***"ስሜንም አልካድክምና"*** ይህ ምናልባት ስደት ይሆናል፣ በኮንሲሊያ ጥያቄ የተፈጠረ፣ የአጼ አምልኮ አጥቢያዊ ደጋፊዎች (ዝከ. 2፡13)።

**3፡9 *"ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን"*** ይህ ምናልባት የሚያመለክተው አይሁድ የወንጌል ተቃዋሚዎችን ነው። ቤተ ክርስቲያን እንጂ የማያምኑ አይሁድ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አይደሉም።

▣ ***"መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ"*** ይህ የኢሳ. 45:14፤ 49:23፤ 60:14 ጠቃሽ ነው፣ እሱም በመነሻው የሚናገረው አሕዛብ ወደ አይሁድ ሕዝብ እንደሚመጡ ነው፣ ነገር ግን ከዚህ አይሁድ መሲሑን አልተቀበሉትም ከሚለው የተነሣ፣ እነርሱ ወደ እነዚህ የአሕዛብ አማኞች መጥተው ይሰግዳሉ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለእነርሱ ለማሳየት (ኢሳ. 43፡4፣9)። ይህም ጥሩ ምሳሌ ነው አኪ ባጠቃላይ፣ እና በተለይም ዮሐንስ፣ ስለ እስራኤል የብኪ ትንቢቶችን እንዳሻሻሉት። ዮሐንስ ጽሑፉን ተጠቅሟል፣ ያም አሕዛብን በመጀመሪያ የተመለከቱትን፣ ወደ ታደሰችው ኢየሩሳሌም፣ ያህዌን ለማምለክ፣ ነገር ግን በአዲሱ የጽድቅ ዘመን ይህ

መልክዓ ምድራዊ የፖለቲካ ምስል የሚያምነውን ዓለም እስከሚያካትት ተስፋፍቷል (አይሁድ እና አሕዛብ) የማያምኑት አይሁድ መጥተው ይሰግዱላቸዋል! ይህ እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን ሁለንተናዊ ማድረግ የሚያሳየው፣ ራዕይ ከእማሬያዊ ፍጻሜ የራቀ ቁም-ነገር እንዳለው ነው፣ የብኪ ነቢያት ትንቢቶች ከአይሁድ ሕዝብ ባሻገር ተለውጧል (ኤፌ. 2፡11-3፡13)። ይህ ነው "ለዘመናት የተሰወረው የወንጌል ምሥጢር"!

**3፡10**

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ*** | ***"የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ"*** |
| ***አኪጀት፣ አኢመቅ*** | ***"ስለ ትዕግሥት ትዕዛዜን ስለጠበቅህ"*** |
| ***አየተመት*** | ***"የትዕግሥት ጽናት ቃሌን ስለጠበቅህ"*** |
| ***አእት*** | ***"እንድትታገሥ ትእዛዜን ስለ ጠበቅህ"*** |

ይህ ምናልባት የዮሐንስ 8፡51 ወይም 17፡6 ጠቃሽ ነው። ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ከስደት እንደሚጠብቅ ቃል አልገባም፣ ምክንያቱም ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በተጻፉት መልእክቶች ስደት፣ ሞትም ጭምር በመከሰቱ።

ቁጥር 10 የሚያመለክተው በመላው ዓለም የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው፣ በማያምኑት ላይ። "መከራውን" በእምነት በሚታገሡት አማኞች እና "የአግዚአብሔር ቁጣ" የሚወድቅበትን የማያምነውን ዓለም መካከል ያለውን ልዩነት ማየት ዋነኛ ነገር ነው።

ተርጓሚዎች በዚህ የፍጻሜ ዘመን መካከል ላይ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደምትሆን ይለያያሉ፡

1. አንዳንዶች የሚመለከቱት ቤተ-ክርስቲያን በዚህ ውስጥ እንደምታልፍ ነው፣ በእግዚአብሔር እየተጠበቀች (ዮሐንስ 17፡ 15)
2. ሌሎች የሚመለከቱት ከዚህ ጊዜ በፊት የሚሆነውን የአማኞች ምሥጢራዊ መነጠቅ ነው

እኔ ቁ. 1ን እመርጣለሁ። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከስደትና ከሞት አልተጠበቁም፣ በመጀመሪያዎች ጥቂት ክፍለ-ዘመናት፣ በግሪክ ሮሜ ባህል ወይም በቀጠለው ስደትና ሞት ወንጌል በተስፋፋ ቁጥር፣ እናም በፍጻሜው ዘመን በሚሆነው የአዲሱ ጊዜ የምጥ ሥቃይ አይጠበቁም። መከራ ዘወትር ቤተ-ክርስቲያንን ያጠራታል ያበረታታልም!

የምዕራፍ 2-3 ጽሑፋዊ ምድብ፣ ቤተ ክርስቲያን መከራ የምትቀበልበት፣ የመንግሥተ ሰማያት ጽሑፋዊ ምድብ ይከተለዋል፣ የተሠዉት ሰማዕታት ለበቀል የሚጸልዩበትን ይከተለዋል። ይህ "የአግዚአብሔር ቁጣ" የሚሆነው በከፉ ደረጃዎች ነው (ማኅተሞች-1/4፣ መለከቶች-1/3፣ ጽዋዎች- አጠቃላይ ጥፋት)፣ እያንዳንዱ ደረጃ የተሰጠው የጠፉትን ወደ ደኅንነት ለመጥራት ዓላማ ነው። የእግዚአብሔር አጠቃላይ ቁጣ፣ ሁለተኛው ሞት፣ የእሳት ባሕር (ራዕይ 20)፣ ከዚያ ወዲያ ለመዋጀት አይደለም፣ ነገር ግን አጠቃላይ ጥፋት ይሆናል።

የተሳደደችው ቤተ ክርስቲያን ድል አድራጊዋ ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች እንዲሁም የማያምኑት አሳዳጆች ስደትን ይቀምሳሉ! እግዚአብሔር ይቆጣጠራል! ልዩ ርዕስ፡ ትዕግሥት 2፡2 ላይ ተመልከት።

▣ **"በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ"** ይህ ሐረግ በተደጋጋሚ በየስፍራው ጥቅም ላይ የዋለው በማያምኑት የሚደረገውን የጸና ዐመጻ ለማመልከት ነው (ራዕ. 6፡10፤ 18፡13፤ 1፡10፤ 12፡12፤ 13፡8፣ 12፣ 14፤ 17፡8)። እግዚአብሔር ንስሐ እንዲገቡና እንዲያምኑ ይፈልጋል (1 ጢሞ. 2፡4፤ 2 ጴጥ. 3፡9)፣ እነርሱ ግን እሺ አይሉም፣ እየተስፋፋ በሚሄደው የማኅተሞቹ፣ የመለከቶቹ፣ እና የጽዋዎቹ ፍርድ መካከል እንኳ ቢሆኑም። ልዩ ርዕስ፡ ለፈተና የግሪክ ቃላት 2፡2 ላይ ተመልከት።

**3፡11 "ፈጥኜ እመጣለሁ"** ይህ ቀጣይነት ያለው አጽንዖት ነው፣ የጌታ ምጽአት ድንገተኝነት (ዝከ. 1፡1፣ 3፤ 2፡16፤ 22፡7፣12፣20)። ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን የጌታን ፈጣን መመለስ ተጠባብቃ ነበር። ይህ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ትውልድ ተስፋ ነው። ልዩ ርዕስ፡ ፈጥኖ መመለስ 1፡3 ላይ ተመልከት።

▣ **"ያለህን አጥብቀህ ያዝ"** ይህ የአሁን የድርጊት ተተኳሪ ነው፣ ፍችውም "አጥብቀህ መያዝህን ቀጥል" ነው፣ እንደ የድርጊት የአሁን ተተኳሪ 2፡25 ላይ ያለው፣ ወሳኝ የሆነ አጥብቆ የመያዝ ድርጊት ላይ ያተኮረ (ልዩ ርዕስ 2፡2 ላይ ተመልከት)። አማኞች በእግዚአብሔር እንደተያዙ፣ እሱ በእነርሱ ይያዛል (ገላ. 6፡9)። ይህ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ኪዳናዊ እና የሰው ልጅ የፈቃድ ምላሽ ግንኙነት ነው!

ደኅንነት የመነሻ ውሳኔ ነው ንስሐ የመግባትና የእምነት (ማርቆስ 1፡15፤ ሐዋ. 3፡16፣19፤ 20፡21) የሕይወት ስልት የሆነ ንስሐ እና እምነት፣ መታዘዝ፣ አገልግሎት፣ እና ትዕግሥት የሚከተለው። እነዚህ ሁሉ ዓይነቶች ለበሰለ ክርስትና አስፈላጊ ናቸው።

▣ **"አክሊል"** ይህ ሌለኛው ማጣቀሻ ነው ለ*stephanos* አክሊል፣ 2፡10 ላይ ለተጠቀሰው። እሱም ለታማኝነት የሆነ ሽልማት ነው።

**3፡12 "ድል የሚነሣ"** 2፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ"** ፊልድልፍያ በመሬት መንቀጥቀጥ ዘመን ነበር፤ የዓምዱ ዘይቤ የሚያስተላልፈው የመጽናትን ጽንሰ-ሐሳብ ነው። የዓይነተኛ ዜጎች ስሞች በፊልድልፍያ መቅደሶች አምዶች ላይ ተጽፏል። "መቅደስ" የሚለው ቃል እዚህ (*naos*) ሲሆን "መኖር" ከሚለው ግስ ነው፣ ጥቅም ላይ የሚውለውም ለመለኮት ማደሪያ መገኛ ስፍራ ነው። ድል ያደረጉ አማኞች ከአግዚአብሔር አጠገብ ፈጽሞ ዞር አይሉም (መዝ. 23፡6፤ 27፡4-6)።

ይህ ዘይቤ ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም በአዲሱ ዘመን ምንም መቅደስ አለመኖሩ ግልጽ ስለሆነ (ዝከ. 21፡22)።

◘ **"የአምላኬን ስም በእርሱ ላይ እጽፋለሁ"** አምስትዮሹን "የኔ" ድግግሞሽ አስተውል ቁ. 12። ይህ አስደናቂ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቅርበት እውቅና የሚሰጥ ነው። ስሙ ባለቤትነትን ተምሳሌት ያደርጋል (ዝክ. 7:3፤ 14:1፤ 22:4)።

◘ **"አዲሲቱን ኢየሩሳሌም... አዲሱን ስም"** ራዕይ የኢሳይያስን ትንቢቶች ይጠቅሳል።

1. አዲስ ነገሮች 42:9፤ 43:19፤ 48:6 (*ራዕ.* 21:5)
2. አዲስ *መዝሙር* 42:10 (*ራዕ.* 5:9፤ 14:3)
3. አዲስ ስም 62:2፤ 65:15 (*ራዕ.* 2:17)
4. አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፣ 65:17፤ 66:22 (*ራዕ.* 3:12፤ 21:1).

አዲሲቷ ሰማያዊ ኢየሩሳሌም፣ ደግሞ በኢሳይያስ ላይ ተተንብዮአል: 40:2፣9፤ 41:27፤ 44:20፣28፤ 52:1፣2፣9፤ 62:1፣6፣7፤ 65:18፣19፤ 66:10፣13፣20 (*ራዕ.* 21:2፣10)። እሱም የእግዚአብሔር ከሕዝቡ መሐል የመገኘቱ ዘይቤ ነው። የብኪ ትንቢቶች አጠቃላይ ሆነዋል። አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በፍልስጥኤም የምትሆን ከተማ አይደለችም፣ ነገር ግን የአዲሱ የጽድቅ ዘመን ተስፋ ነች።

**3፡13** 2፡6 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

## ራዕይ፡ 3፡14-22

**[14]በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። አሜን የሆነው፥ የታመነውና እውነተኛው ምስክር፥ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል። [15]በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ *ሥራህን* አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር። [16]እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው። [17]ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥ [18]ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኵል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ። [19]እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ። [20]እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል። [21]እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ። [22]መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።**

**3፡14 "አሜን የሆነው"** ይህ የያህዌ መጠሪያ ጠቃሽ ነው፣ "የአሜን አምላክ" ኢሳ. 65፡16። "አሜን" የሚለው ቃል የብኪ ቃል "ማመን" ወይም "እምነት" ዓይነት ነው (ዘፍ. 15:16፤ ዕን. 2:4)። እሱም ዘወትር አጽንዖት የሚሰጠው ታማኝነትን ወይም "የታመነ መሆንን" ነው (ዝክ. 1፡6፤ 2 ቆሮ. 1፡20)። ልዩ ርዕስ 1፡6 ተመልከት።

◘ **"የታመነውና እውነተኛው ምስክር፥"** ይህ ሌላው ሐረግ ሊሆን ይችላል ከምዕራፍ 1 (ዝክ. 1፡5)። በሴፕቱዋጀንት እነዚህ ሁለቱም ቅጽሎች ያህዌን ለመግለጽ ነው ጥቅም ላይ የሚውሉት። ማለት የሚቻለውም *emeth*፣እሱም የዕብራይስጥ ቃል "እምነት፣" "ማመን" ወይም "መታመን" የሆነው እንደ *pistos* (የታመነ) እና *alθeia* (እውነት) መተርጎሙ ነው። እነዚህ ሁለት የግሪክ ቃላት ዘወትር በራዕይ ለኢየሱስ ጥቅም ላይ ውለዋል (ዝክ. 3:14፤ 19:11፤ 21:5፤ 22:6)።

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ"** |
| **አየተመቅ** | **"የእግዚአብሔር ፍጥረት መነሻ"** |
| **አእት** | **"እግዚአብሔር የፈጠራቸው ሁሉ መነሻ"** |
| **አኢመቅ** | **"የእግዚአብሔር ፍጥረት መርሕ"** |

ይህ ለሁለቱም ጠቃሽ ነው ለዘፍ. 1፡1 እና ዮሐንስ 1፡1። "*መጀመሪያ*" (ዕብራይስጥ፣ *bereshith*) እና "መነሻ" (ግሪክ፣ *arch*) ሁለት ፍችዎች አሏቸው፡ (1) *መጀመር* ወይም (2) *መነሻ*፣ ምንጭ።

ይህ ሐረግ በአርዮስ/አትናትዮስ (ሥላሴያዊ) ውዝግብ በአራተኛው ክፍለ ዘመን ጥቅም ላይ ውሏል፣ እሱም የምሳ. 8፡22-31 ጠቃሽ ነው። ጥበብ የመጀመሪያው የያህዌ ፍጥረት ነበር፣ በጥበብ በኩልም ቀሪዎቹ ሁሉ ተፈጠሩ። ይህ ምናልባት የዮሐንስ የ"*logos*" አጠቃቀም መነሻ ሊሆን ይችላል፣ በወንጌሉ ላይ (ዮሐንስ1፡1)። ይህ አንደኛው ጠንካራ ምንባብ ነው በክርስቶስ ቅድመ-ሕላዌ ላይ (ዮሐንስ 1:1፤ 8:57-58፤ II ቆሮ. 8:4፤ ፊሊ.. 2:6-7፤ ቆላ. 1:17)። እና ደግሞ ክርስቶስ በፍጥረት ላይ ከአብ ጋር የሚሠራ ለመሆኑ (ዮሐንስ 1:3፤ I ቆሮ. 8:16፤ ቆላ. 1:15፣18፤ ዕብ. 1:2)።

## ልዩ ርዕስ፡ አሪኬ

"አሪኬ" የሚለው ቃል ትርጓሜ የአንድ ነገር "መጀመሪያ" ወይም "ምንጭ" ማት ነው፡፡

1. ፍጥረት ስርአት *መጀመሪያ* (ዮሐ 1፡1፤ 1 ዮሐ 1፡1፤ ዕብ 1፡10 *ጋር ያነጻጽሩ*)
2. የወንጌል *መጀመሪያ* (ማር 1፡1፤ ፊል 4፡15፤ 2 ተሰ 2፡13፤ ዕብ 2፡3 *ጋር ያነጻጽሩ*)
3. *የመጀመሪያ* የዐይን ምስክሮች (ሉቃ 1፡2 *ጋር ያነጻጽሩ*)
4. ከምልክቶቹ *የመጀመሪያው* (ተአምራ ዮሐ 2፡11 *ጋር ያነጻጽሩ*)

5. የመርሆዎቹ የመጀመሪያ (ከዕብ 5፡12 ጋር ያነጻጽሩ)
6. በወንጌል እውነት ላይ የተመሠረተ የመጀመሪያው መስተማመኛ (ዕብ 3፡14 ጋር ያነጻጽሩ)
7. የመጀመሪያ ቆላ 1፡18፤ ራዕ 3፡14

በኋላ ላይ ይህ ቃ "መግዛትን" ወይም "ስልጣንን" ማመልከት ጀመረ

1. የመንግስት በለስልጣናትን
   ሀ. ሉቃ 12፡11
   ለ. ሉቃ 20፡20
   ሐ. ሮሜ 13፡3፤ ቲቶ 3፡1
2. የመለአከትን ስልጣን
   ሀ. ሮሜ 8፡38
   ለ. 1 ቆሮ 15፡24
   ሐ. ኤፌ 1፡21፤ 3፡10፤ 6፡12
   መ. ቆላ 1፡16፤ 2፡10፤ 15
   ሠ. ይሁ ቁ.6

እነዚህ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በሰማይም በምድርም ያለውን ስልጣን ያጣጥላሉ፡፡ ጋጠወጣዊ ነጻነትን ይሻሉ፡፡ በእግዚአብሔር፣ በመለኣእከት፣ በመንግስት በለስልጣነት እና በቤተ ክርስቲያን ፊት እራሳቸውን እና የእነርሱን ፍላጎት ያስቀድማሉ፡፡

**3፡15 "በራድ ወይም ሞቃት አይደለህም"** ይህ ለስለስ ላለ ውኃ ጠቃሽ ይሆናል፣ ማለትም የዚህች ከተማ ሰዎች ይጠጡት የነበረ፣ በአካባቢው የሙቅ ውኃ ምንጭ ምክንያት። ተመሳሳይ ወቀሳ ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያንም ተደርጓል (ዝኪ. 3፡1)።

**3፡16 "ከአፌ ልተፋህ ነው"** የ2:5፤ 3:3፤16፤17 ማስጠንቀቂያዎች አስደንጋጭ ናቸው ወደ አንደኛው ክፍለ ዘመን የሚታዩ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሲያመለክቱ። ይህ ደኅንነትን ማጣት አይደለም፣ ግን ውጤታማ አገልግሎትን ማጣት እንጂ (ዝኪ. 3:19፤ ዕብ. 12:5-13)።

**3፡17 "ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ"** ቁጥር 17 እና 18 የሎዶቂያ ታሪካዊ ጠቃሽ ነው፣ ለባንክ ማዕከልነቷ፣ ለተቀለመ ሱፍ ማዕከልነቷ፣ ለዓይን ሕክምና ማዕከልነቷ። የብልጽግናቸው አሳዛኝነት ብዙ ያላቸው ሲመስላቸው ትንሽ ያላቸው መሆናቸው ነው (ዝኪ. 3፡1)።

## ልዩ ርዕስ፡ ሀብት

1. የብሉይ ኪዳን አጠቃላይ እይታ
   ሀ. እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ባለቤት ነው
      1. ዘፍጥረት 1-2
      2. 1ዜና 29፡11
      3. መዝሙር 24፡1፤ 50፡12፤ 89፡11
      4. ኢሳይያስ 66፡2
   ለ. ሰዎች የሀብት መጋቢዎች ናቸው ለእግዚአብሔር ዓላማ
      1. ዘዳግም 8፡11-20
      2. ሌዋውያን 19፡9-18
      3. ኢዮብ 31፡16-33
      4. ኢሳይያስ 58፡6-10

   ሐ. ሀብት የአምልኮ ክፍል ነው
      1. ሁለቱ መባዎች
         ሀ. ዘኍልቁ 18:21-29፤ ዘዳ. 12:6-7፤ 14:22-27
         ለ. ዘዳ. 14:28-29፤ 26:12-15
      2. ምሳሌ 3፡9
   መ. ሀብት የሚታየው ከእግዚአብሔር እንደሆነ ስጦታ ነው፣ ለኪዳን ታማኝነት
      1. ዘዳግም 27-28
      2. ምሳሌ 3:10፤ 8:20-21፤ 10:22፤ 15:6
   ሠ. በሀብት ላይ ማስጠንቀቂያ፣ በሌሎች ድካም በተገኘ
      1. ምሳሌ 21፡6
      2. ኤርምያስ 5፡26-29
      3. ሆሴዕ 12፡6-8
      4. ሚኪያስ 6፡9-12

ረ. ሀብት በራሱ ኃጢአት አይደለም ቀዳሚ እስካልሆነ ድረስ
1. መዝሙር 52:7፤ 62:10፤ 73:3-9
2. ምሳሌ 11:28፤ 23:4-5፤ 27:24፤ 28:20-22
3. ኢዮብ 31:24-28

II. የተለዩ የምሳሌዎች አስተሳሰብ

ሀ. በግል ጥረት የተከማቸ ሀብት ስፍራ
1. ሀኬተኝነትና ስንፍና ተኮንኗል— ምሳሌ 6:6-11፤ 10:4-5፣26፤ 12:24፣27፤ 13:4፤ 15:19፤ 18:9፤ 19:15፣24፤ 20:4፣13፤ 21:25፤ 22:13፤ 24:30-34፤ 26:13-16
2. ጠንክሮ መሥራት ተሞግሷል—ምሳሌ 12:11፣14፤ 13:11

ለ. ድህነት በተቃርኖ ሀብታምነት ጻድቅንነት በተቃርኖ ኃጢአተኝነትን ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል—ምሳሌ 10:1፤ 11:27-28፤ 13:7፤ 15:16-17፤ 28:6፣19-20

ሐ. ጥበብ (እግዚአብሔርንና ቃሉን ማወቅ እና በዚህ እውቀት መኖር)ከሀብት ይበልጣል—ምሳሌ 3:13-15፤ 8:9-11፣18-21፤ 13:18

መ. ማስጠንቀቂያዎች እና ጽኑ ምክሮች
1. ማስጠንቀቂያዎች
   ሀ. በባልንጀራህ ብድር ላይ ትርፎቻ እንዳታደርግ (ትርፍ)—ምሳሌ 6:1-5፤ 11:15፤ 17:18፤ 20:16፤ 22:26-27፤ 27:13
   ለ. በክፉ ሥራ ሀብት እንዳታፈራ ተጠንቀቅ— ምሳሌ 1:19፤ 10:2፣15፤ 11:1፤ 13:11፤ 16:11፤ 20:10፣23፤ 21:6፤ 22:16፣22፤ 28:8
   ሐ. በምታበድርበት ጊዜ ተጠንቀቅ— ምሳሌ 22፡7
   መ. በቶሎ ለሚያልቅ ሀብት ተጠንቀቅ— ምሳሌ 23፡4-5
   ሠ. ሀብት በፍርድ ቀን አይረዳም— ምሳሌ 11፡4
   ረ. ሀብት ብዙ "ጓደኞች" አሉት— ምሳሌ 14፡20፤ 19፡4
2. ተግሣጽ
   ሀ. ልግስና ሞገስ ትሆናለች— ምሳሌ 11:24-26፤ 14:31፤ 17:5፤ 19:17፤ 22:9፣22-23፤ 23:10-11፤ 28:27
   ለ. ጽድቅ ከሀብት ትበልጣለች—ምሳሌ 16:8፤ 28:6፣8፣20-22
   ሐ. ጸሎት ለሚያስፈልገው፣ ለተትረፈረፈ ሳይሆን— ምሳሌ 30፡7-9
   መ. ለደሀ መስጠት ለእግዚአብሔር መስጠት ነው— ምሳሌ 14፡31

III. የአዲስ ኪዳን እይታ

ሀ. ኢየሱስ
1. ሀብት በራሳችንና በሀብታችን እንድንመካ የተለየ ፈተና ሊሆንብን ይችላል ከእግዚአብሔርና ከሀብቱ ይልቅ
   ሀ. ማቴዎስ 6:24፤ 13:22፤ 19:23
   ለ. ማርቆስ 10:23-31
   ሐ. ሉቃስ 12:15-21፣33-34
   መ. ራዕይ 3:17-19
2. እግዚአብሔር ለሥጋዊ መሻታችን የሚያስፈልገንን ይሰጣል
   ሀ. ማቴዎስ 6:19-34
   ለ. ሉቃስ 12:29-32
3. መዝራት ከማጨድ ጋር ይዛመዳል (መንፈሳዊ ብሎም ሥጋዊ)
   ሀ. ማርቆስ 4፡24
   ለ. ሉቃስ 6፡36-38
   ሐ. ማቴዎስ 6፡14፤ 18፡35

4. ንስሐ በሀብት ላይ ተጽዕኖ አለው
   ሀ. ሉቃስ 19፡2-10
   ለ. ሌዋውያን 5፡16
5. ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ ተኮንኗል
   ሀ. ማቴዎስ 23፡25
   ለ. ማርቆስ 12፡38-40
6. የፍጻሜ ሰዓት ፍርድ ከሀብት አጠቃቀማችን ጋር ይዛመዳል— ማቴዎስ 25፡31-46

ለ. ጳውሎስ
1. ተግባራዊ እይታ ልክ እንደ ምሳሌ (ሥራ)
   ሀ. ኤፌሶን 4፡28
   ለ. 1ተሰሎንቄ 4፡11-12
   ሐ. 2ተሰሎንቄ 3፡8፣11-12

መ. 1ጢሞቴዎስ 5፡8
2. እንደ ኢየሱስ መንፈሳዊ አይታ (ነገሮች በቶሎ ያበቃሉ፣ ያላችሁ ይብቃችሁ)
ሀ. 1ጢሞቴዎስ 6፡6-10 (ባለው መርካት)
ለ. ፊሊጵስዩስ 4፡11-12 (ባለው መርካት)
ሐ. ዕብራውያን 13፡5 (ባለው መርካት)
መ. 1ጢሞቴዎስ 6፡17-19 (ልግስናና በእግዚአብሔር መታመን፣ በሀብት ሳይሆን)
ሠ. 1ቆሮንቶስ 7፡30-31 (የነገሮች መቀየር)

IV. ማጠቃለያ

ሀ. ሀብትን በተመለከተ ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-መለኮት የለም።
ለ. በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ሁነኛ አንቀጽ የለም፣ ስለዚህ ይዘቶች የሚሰበሰቡት ከተለያዩ አንቀጾች ነው። የራስህን አመለካከት በእነዚህ የተለዩ ጽሑፎች ውስጥ እንዳታነብ ተጠንቀቅ።
ሐ. ምሳሌዎች፣ በብልህ ሰዎች የተጻፉት (ጠቢባን)፣ ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ዘውጎች ይልቅ የተለያየ አመለካከት አላቸው። ምሳሌዎች ተግባራዊና ግለሰባዊ-ተኮር ናቸው። እሱም ሚዛኑ መጠበቅ ይኖርበታል እናም በሌሎቹ ቃሎች የግድ ሚዛኑ መጠበቅ ይኖርበታል (ኤር. 18፡18)።
መ. የእኛ ዘመን የእሱን አመለካከትና ድርጊት ሊተነትን ይሻል፣ ሀብትን በተመለከተ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ አኳያ። ቀዳሚ ነገሮቻችን ተዛብተው ይቀመጣሉ፣ ካፒታሊዝም ወይም ኮሚኒዝም ብቸኛ መመሪያዎቻችን ከሆኑ። አንዱ ለምን እና እንዴት ስኬታማ ሆነ የሚሉ ናቸው ዋነኞቹ ጥያቄዎች፣ ምን ያህል አከማቸ ከሚለው ይልቅ።
ሠ. ሀብት ማከማቸት ሚዛናዊ መሆን አለበት፣ ከእውነተኛ አምልኮና ኃላፊነት ከተሞላው መጋቢነት ጋር (2ቆሮንቶስ 8-9)።

**3፡18 "ከእኔ ግዛ"** ይህ የኢሳ. 55፡1-3 ጠቃሽ ይሆናል፣ የእግዚአብሔር የደኅንነት ስጦታ ነጻ ሆኖ፣ ግን ዋጋ እንዳለው ተገልጿል።

◘ **"ነጭ ልብስ"** 3፡4 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

◘ **"የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ"** በብኪ ራቁትነት የመሸነፍ፣ የፍርድ፣ እና የድህነት ምልክት ነው።

**3፡19 "እገሥጻለሁ"** ይህ የግሪክ ቃል *elegch*Ô ጥቅም ላይ የዋለው "ማጋለጥ እና ከዚያም መፈወስ ወይም ማረም" በሚል ስሜት ነው (ዮሐንስ 3፡20፤ ኤፌ. 5:11-14)።

◘ **"እቀጣለሁም"** በእግዚአብሔር መቀጣት የእሱ ቤተሰብ አባላት የመሆናችን ምልክት ነው (ኢዮብ 5:17፤ ምሳ. 3:12፤ መዝ. 94:12፤ ዕብ. 12:6)።

◘ **"ቅና"** ይህ የአሁን የድርጊት ተተኳሪ ነው። እሱም ከተመሳሳይ ሥርወ-ቃል ነው፣ እንደ "ሙቅ" "የፈላ" (*zestos*) 3፡15-16 ጥቅም ላይ የዋለ። እግዚአብሔርን ማወቅና ማገልገል የሚንቦገቦግ ስሜትና የሕይወት ስልት መሆን አለበት።

◘ **"ንስሐ ግባም"** ይህ የድርጊት የአሁን ተተኳሪ ነው። በእነዚህ ሰባት መልእክቶች ሁሉ ተደጋጋሚ ግፊት አለ፣ ክርስቲያኖች፣ የማያምኑት ሳይሆኑ፣ ወደ ክርስቶስ ንስሐ መግባት እና መመለስ፤ ለመብሰል፣ ለመጽናት፣ እና ለደስታ እንደሚኖርባቸው (ዝከ. 2:5፣ 16፣ 22፤ 3:3፣ 19)። ንስሐ መግባት የሕይወት ስልት ነው፣ የመነሻ ተግባር ብቻ ሳይሆን!

**3፡20 "እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ"** ይህ የተጠናቀቀ ድርጊት አመላካች ነው፣ "በር ላይ ቆሜአለሁ፣ በቀጣይነትም ቆሜአለሁ" የአሁን የድርጊት አመላካች ተከትሎት፣ "እና ማንኳኳቴን በመቀጠል።" ምንም እንኳ ይህች ቤተ ክርስቲያን ምንም የምስጋና ቃል ባትቀበልም፣ ሞቅ ያለ ግብዣ ተቀብላለች። ይህ ክርስቲያን ለመሆን የተደረገ ግብዣ አይደለም፣ ነገር ግን ይልቁንም የቤተ ክርስቲያን አባላት በክርስቶስ ወደ ሆነ ጠቃሚ ኅብረት እንዲመለሱ የቀረበ ግብዣ እንጂ። ይህ ቁጥር ከዐውደ ጽሑፉ ወጥቶ ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል፣ ወንጌላዊነትን ለመጥቀስ።

"በር" የሚለው ዘይቤ በወንጌላት ጥቅም ላይ ውሏል (ማርቆስ 13:28-29፤ ሉቃስ 12:36) የክርስቶስ ምጽአት ቅርብ መሆኑን እንደማመልከቻ መንገድ። ልዩ ርዕስ፡ በር 3፡7 ላይ ተመልከት።

◘ **"ማንም ድምጼን ቢሰማና በሩን ቢከፍትልኝ"** ይህ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፣ ዓይነተኛ ግን ርግጠኛ ያልሆነን ድርጊት የሚያመለክት። በበርካታ የዓለም ክፍሎች ማንኳኳት በንግግር ሰላምታ ይታጀባል። ፍቃዳዊውን ነገር ተገንዘብ፤ ግለሰቡ/ቤተ ክርስቲያን ምላሽ መስጠትና በር መክፈት ይኖርባቸዋል። ይህ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ኪዳናዊ ገጽታ ነው። መነሻውን ይወስዳል፣ አጀንዳውን ያስቀምጣል፣ ሰዎች ግን ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል። ደግሞም ንስሐ መነሻ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት እንዳለው ተገንዘብ። ደኅንነት ውጤት አይደለም፣ የሕይወተ ስልት ግንኙነት እንጂ። እሱም የራሱ ውጣ ውረድ አለው፣ ነገር ግን ቋሚው ኅብረት ርግጠኛ ነው!

◘ **"ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል"** ይህ የሰላም መሥዋዕት ጠቃሽ ነው (ሌዋውያን 3፣ እና 7)፣ የወዳጅነት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በተምሳሌት ከአቅራቢው ጋር ሲበላ። ሌሎች ይሄንን የሚመለከቱት እንደ ፍጻሜ ዘመኑ መሲሐዊ ግብዣ ነው።

እዚህጋ ለምግብ ጥቅም ላይ የዋለው ቃል በቀኑ ፍጻሜ ላይ የሚቀርበውን የምብል ዓይነት ነው፣ እሱም የቤተሰብ ኅብረት እና ጓደኝነት ዋነኛው ሰዓት። በምስራቅ መመገብ ዘወትር የኪዳን፣ የባልንጀርነት፣ እና የኅብረት ምልክት ነው።

**3፡21 "ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ"** ይህ ጠንከር ያለ ምስያ ነው፣ ከቀረበ ወዳጅነትና ኅብረት። በርካታ ጠቃሾች በአኪ አሉ፣ አማኞች ከክርስቶስ ጋር እንደሚገዙ (ዝከ. 2:26፣ 27፤ ሉቃስ 22:30፤ ማቴ. 19:28፤ I ቆሮ. 6:2፤ II ጢሞ. 2:12፤ ራዕ. 20:4)። ራዕይ 22:5 የሚያመለክተው የክርስቲያኖችን ዘላለማዊ ግዛት ነው፣ ከክርስቶስ ጋር። ልዩ ርዕስ በእግዚአብሔር መንግሥተ መግዛት 5፡10 ላይ ተመልከት።

▣ **"እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ"** ኢየሱስ ድሮውኑ ዓለምን ድል እንዳደረገ ማወቅ አስገራሚ ነው (ዮሐንስ 16:33፤ ኤፌ. 1:21-22) እናም እሱ ድሮውኑ በአብ ቀኝ ተቀምጧል (ኤፌ. 1:20፤ I ዮሐንስ 2:1 እና ራዕ. 22:1) እሱም በድሉ አብረነው እንድንሆን ይሻል!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>*መመሪያ*</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የዮሐንስ የፍጻሜ ዘመን ትንቢት ለምን በታናሹ እስያ ለነበሩ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በሆነ መልእክት ይጀምራል (ለሰባት ብቻ)?
2. እያንዳንዱ መልእክት ክርስቶስን ከምዕራፍ 1 በመግለጥ ለምን ይጀምራል?
3. እነዚህ መልእክቶች ካሁኒቷ ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?
4. ወደ እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች የተላኩትን እነዚህን ጠንካራ ማስጠንቀቂያዎች እንዴት ትተረጉማለህ?
5. "አንዴ የዳነ ሁሌም ድኗል" የሚለውን ዶክትሪን በእነዚህ ደብዳቤዎች ካሉት ማስጠንቀቂያዎችና የትዕግሥት ጥሪዎች ጋር እንዴት ታያይዛለህ?
6. 3፡20 ለምን የደኅንነት ተስፋ አይሆንም?
7. ቀጣዩ ጽሑፋዊ ምድብ ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መልእክት ጋር እንዴት ይዛመዳል? እግዚአብሔር የፍጻሜ ዘመን አማኞችን ከመከራ ይጠብቃቸዋልን፣ የአንደኛውን ክፍለ ዘመን አማኞች ሳይሆን?

# ራዕይ 4 – 5

# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ4 | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሰማያዊ አምልኮ | የሰማይ የዙፋኑ ክፍል | የእግዚአብሔርና የበጉ ክብር ራዕይ | አምልኮ በሰማይ | አምላክ የዓለምን መጻኢ በበጉ ጠብቆታል |
| 4:1-6ሀ | 4:1-11 | 4:1-6ሀ | 4:1-6ሀ | 4:1-11 |
| 4:6ለ-11 | | 4:6b-11 | 4:6ለ-8 | |
| | | | 4:9-11 | |
| ጥቅሉ እና በጉ | በጉ ጥቅሉን ወሰደ | | ጥቅሉ እና በጉ | |
| 5:1-14 | 5:1-7 | 5:1-5 | 5:1-5 | 5:1-5 |
| | በጉ ይገባዋል | 5:6-10 | 5:6-10 | 5:6-10 |
| | 5:8-14 | | | |
| | | 5:11-14 | 5:11-14 | 5:11-14 |

**የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ጽሑፋዊ ምድቡን ይመሠርታሉ፤ ምዕራፍ 4 የሚያሳየው እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ ነው (የ*Elohim* ፍቺ፣ እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ፣ ሰጪ፣ እና ሕይወትን ሁሉ እንደሚያኖር፣ መዝሙር 104) እና ምዕራፍ 5 የሚያሳየው የእግዚአብሔር በግ (ኢየሱስ) እንደ ተቤዢ ነው (የያህዌ ፍቺ፣ እግዚአብሔር እንደ አዳኝ፣ ተቤዢ፣ እና ኪዳንን የሚያደርግ አምላክ፣ መዝሙር 103)። ትልቁ ጽሑፋዊ ዐውደ-ጽሑፍ ሰባቱን ማኅተሞች በመክፈት ይቀጥላል። ሆኖም፣ ማኅተሞቹ ራሳቸው የሚጀምሩት ምዕራፍ 6 ላይ ጀምረው እስከ 8፡1 ይዘልቃሉ።

ለ. ምዕራፍ 4 ማዕከላዊውን ጭብጥ ያደራጃል (አስተማማኙ ክብር እና የያህዌ ግዛት) የራዕይን መጽሐፍ። ይህ የሰማያዊ ዙፋን ትዕይንት ዕብራውያን 8 እና 9 ላይ ካለው ሰማያዊ ቤተ መቅደስ ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ ይዘት (የእግዚአብሔር ሰማያዊ ክብር) የጥንታዊውን የአይሁድ ምሥጢራዊነት ማዕከላዊ ግብ ያደራጃል።

ሐ. የራዕይ መጽሐፍ ቀዳሚ የሚያደርገው የዳግም ምጽአቱን እንዴትና መቼ አይደለም፤ እሱ ቀዳሚ የሚያደርገው በሰዎች ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ነው። እነዚህ ሁለት ምዕራፎች የመጽሐፉን ቀሪ ክፍልና ዓላማውን ለመረዳት አስፈላጊ ናቸው!

መ. ከእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ግልጽ የሚሆነው ዮሐንስ አፖካሊፕቲካዊ ቋንቋ መጠቀሙን ነው፣ መንፈሳዊውን እውነት ለመግለጽ። ዮሐንስ ከብኪ አፖካሊፕቲካዊ ምንባቦች ምስያን ወስዷል፣ በተለይም ሕዝቅኤል ምዕራፍ 1 እና 10፤ እንዲሁም 2፡9፣10፤ ዳንኤል 4፤ 7፡13-14 እና ደግሞ በርካታ ማጣቀሻዎች ከአይሁድ በይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፎች ላይ ወስዷል፣ እንደ 1 ሔኖክ ካሉት። ይህ እውነት ከሆነ፣ እንግዲያውስ ራዕይን ጥሬአዊ፣ አጠቃላይ ታሪካዊ የትርጓሜ ፈርጅ አኳያ መቃኘት ፈጽሞ ተገቢ አይደለም፣ በተለይም የእኛን ዘመን ሁነቶች፣ ባህላችንን፣ መልክዓ ምድራዊ መቼትን ወስደን በጥንታዊው አፖካሊፕቲካዊ መጽሐፍ ዝርዝሮች አኳያ መቃኘት። ይህ ማለት በምንም መልኩ ራዕይ እውነት አይደለም የሚል አንድምታ ለማስተላለፍ አይደለም። እሱ እንደ ታሪካዊ ትርክት አልተተረጎመም ማለት አይደለም፤ የተሻለው ሥነ-ትርጓሜያዊ ሞዴል የኢየሱስ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ (ፊ እና ስቱዋርት፣ *መጽሐፍ ቅዱስን ከነ ሙሉ ጠቀሜታው ስለ ማንበብ*፣ ገጽ 256 ተመልከት)!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

### ራዕይ፡ 4፡1-11

**[1]ከዚያ በኋላም አየሁ፥ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ። ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ። [2]ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፤ እነሆም፥ ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ፤ [3]ተቀምጦም የነበረው በመልኩ የኢያስጲድንና የሰርዲኖን ዕንቍ ይመስል ነበር። በመልኩም መረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ። [4]በዙፋኑ ዙሪያም ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፥ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሀያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር። [5]ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፥ እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው። [6]በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ፥ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ። [7]ፊተኛውም እንስሳ አንበሳን ይመስላል፥ ሁለተኛውም እንስሳ ጥጃን ይመስላል፥ ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው፥ አራተኛውም እንስሳ የሚበረውን ንስር ይመስላል። [8]አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉአቸው፥ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፤ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የነበረውና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም። [9]እንስሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘላለምም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ፥ [10-11]ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ። ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።**

**4፡1**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ከእነዚህ ነገሮች በኋላ አየሁ"** |
| **አየተመቅ** | **"ከዚህም በኋላ አየሁ"** |
| **አእት** | **"በዚህ ነጥብ ላይ ሌላ ራዕይ አየሁ"** |
| **አኢመቅ** | **"ከዚያም በራዕይ አየሁ"** |

ይህ ሰዋሰዋዊ ቀመር፣ ባነስተኛ ልዩነት፣ 7፡1፣9፤ 15፡5፤ 18፡1 እና እንዲሁም 19፡1 ላይ ይገኛል። እነዚህ ተለጣጣቂ መገለጦች ናቸው። አብዛኞቹ የብኪ ትንቢታዊ መገለጦች በኪዳናዊ ሁኔታ የተቃኙ ናቸው፣ "እንዲህ ከሆነ... ከዚያም" ላይ አጽንኦት የሚሰጡ፣ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ባለው ኪዳን። የእስራኤል የወቅቱ እምነት የወደፊት ዕጣዋን ይወስናል። ይህም ደግሞ ራዕይ ላይ በዮሐንስ መገለጦች እውነት ነው።

1. የኢየሱስ ቃላት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታዊ ነው። ለማስጠንቀቂያው የሚሰጡት ምላሽ የወደፊታቸውን ይወስናል።
2. የማኅተሞቹ እና የመለከቶቹ ፍርዶች ሁኔታዊ ናቸው። እግዚአብሔር የማያምኑት ንስሐ እንዲገቡና ወደ እሱ እንዲመለሱ ይሻል። በብኪ የእግዚአብሔር ሁለንተናዊ የመዋጀት ዕቅድ (ዘፍ. 3፡15፤ 15፡12-2፤ 17፡1-8፣ ደግሞም ሐዋ. 2፡23፤ 3፡18፤ 4፡28፤ 13፡29 ማስታወሻ) ሁኔታዊ ባልሆነ መልኩ በእሱ ቃል ኪዳን ላይ እንደተመሠረተ ሁሉ፣ ግን ደግሞ ሁኔታዊ ነው (ዘፍ. 12፡1፤ ራዕይ 2-3) በሰዎች ኪዳናዊ ምላሽ። ይህ ሁለንተናዊ የመዋጀት ዕቅድ በሰማያዊ ትዕይንት ምዕራፍ 4 እና 5 ላይ ተገልጧል።

### ልዩ ርዕስ፡ የቡብ ወንጌላዊ ቅድመ-ዝንባሌዎች

ለእናንተ ለአንባቢዎች በዚህ ነጥብ ላይ ቅድመ-ግምቶች እንዳለብኝ የግድ መግለጽ እወዳለሁ። የእኔ ስልታዊ ሥነ-መለኮት ካልቫናዊ ወይም ነጻነታዊ አይደለም፣ ነገር ግን የታላቁ ተልዕኮ ወንጌላዊነት ነው (ማቴ. 28፡18-20፤ ሉቃስ 24፡46-47፤ ሐዋ. 1፡8)። እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁሉ ይቤዥ ዘንድ ዘላለማዊ ዕቅድ እንዳለው እንዳለሁ አምናለሁ (ምሳ. ዘፍ.

3:15፤ 12:3፤ ዘጸ. 19:5-6፤ ኤር. 31:31-34፤ ሕዝቅኤል 18፤ 36:22-39፤ ሐዋ. 2:23፤ 3:18፤ 4:28፤ 13:29፤ ሮሜ. 3:9-18፣19-20፣21-31)፣ በአምሳሉና በመልኩ ለተፈጠሩት ሁሉ (ዘፍ. 1:26-27)። ኪዳኖቹ በክርስቶስ ተዋህደዋል (ገላ. 3:28-29፤ ቆላ. 3:11)። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ምሥጢር ነው፣ ተሰውሮ የነበረ፣ አሁን ግን የተገለጠ (ኤፌ. 2:11-3:13)! የአዲስ ኪዳን ወንጌል፣ እስራኤል ሳይሆን፣ ለቃሉ ሳይሆን።

ይህ ቅድመ-መረዳት የእኔን የቃሉን ትርጓሜ ሁሉ አጥልቶበታል። ሁሉንም ጽሑፍ የማነበው በዚህ ውስጥ ነው! እሱ በርግጥ ቅድመ-ዝንባሌ ነው (ሁሉም ተርጓሚዎች ይኖሩባቸዋል!)፣ ነገር ግን እሱ በቃሉ መረዳት ያለ ቅድመ-ግምት ነው።

▣ **"በሰማይ የተከፈተ ደጅ"** ይህ የተጠናቀቀ ተገብሮ አንቀጽ ነው፣ ፍችውም በመለኮት የተከፈተ ደጅ (ተገብሮ ድምጸት) እናም ክፍት ሆኖ የሚቆይ (የተጠናቀቀ ጊዜ)። ይህም እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጅ የገለጠበትን መንገድ ማሳያ ሌለኛው መንገድ ነው። እሱም ከ19:11፤ ሕዝ. 1:1፤ ማቴ. 3:16፤ ዮሐንስ 1:51 እና ሐዋ. 7:55-56 ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው። ልዩ ርዕስ 3፡7 ላይ ተመልከት።

"ሰማይ" የሚለው ቃል በዮሐንስ ጽሑፎች ከ50 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ዘወትርም በነጠላ ነው፣ እንድ ጊዜ 12፡12 ላይ ካልሆነ በቀር። የዚህ ለውጥ ትክክለኛ ፍች፣ ከነጠላ ወደ ብዙ፣ ከሥነ-መለኮት አኳያ ርግጠኝነት የለውም። ራቢዎች የሚያብራሩት ሦስት ወይም ሰባት ሰማይ እንዳሉ ነው (2 ቆሮ. 12፡2)። ዮሐንስ የሚያተኩረው በአንድ ሰማይ ላይ ነው፣ እሱም አግዚአብሔር የሚኖርበት፤ እሱ የሚመርጠው ወደ እሱ ግዛት እንድንመለከት ነው። ምንም እንኳ በምድር ላይ ሁከት ቢኖርም፣ በሰማይ ግን ምንም አይኖርም።

## ልዩ ርዕስ፡ ሰማይ

በብሉይ ኪዳን ሰማይ ብዙ ቁጥር ነው፡፡ የዕብራይስጡ ቃል ትርጓሜ "ከፍታ" ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር በከፍታዎች ውስጥ ያድራል፡፡ ይህ ሀሳብ የሚያንጸባርቀው የእግዚብሔርን ቅድስና እና ምጡቅነት ነው፡፡

በዘፍ 1፡1 ብዙ ቁጥር የሆነው "ሰማይ እና ምድር" በእግዚአብሔር እንደተፈጠረ ተገጸዋል (1) ከዚህ ፒላኔት ውጭ ያለው ከባቢ ወይም (2) ለሁሉም ነበራዊ ሁኔታል ለማሳየት ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ መሰረታዊ ጥቅስ በመነሳት ሌሎች ጥቅሶች ይህንን በመውሰድ የሰማያትን ደረጃዎች ይናገራሉ "ሰማይ ሰማያት" ብለው ያወራሉ፡፡ (መዝ 68፡33)(ዘዳ 10፡14፣ 1ነገ 8፡27፤ ነህ 9፡6፤ መዝ 148፡4)፡፡ መምህራን ይህንን ስጠቀልሉት

1. ሁለት ሰማያት እዳሉ (አር. ይሁዳ፣ ሐጌ)
2. ሦስት ሰማያት
3. አምስት ሰማያት (3 ባሩክ)
4. ሰባት ሰማያት
5. አስር ሰማያት (2 ሄኖክ 20፡3፤ 22፡1)

እነዚህ ሁሉ ለማሳየት የታለሙት እግዚብሔር ከግኡዙ ዓለም የተለ መሆኑን እና ምጡቅ መሆኑን ነው፡፡ በአብዛኛዎቹ በይሁዳ የሚገኙ አይሁዳዊያን አመለካከት ሰማያት ሰባት መሆናቸው ነው፡፡

ጳውሎስ በ2 ቆሮ 12፡2 የእግዚአብሔርን ግላዊ፣ ንጉሣዊ ክብር ለማሳየት ስለ ሦስተኛ ሰማይ ጠቅሶዋል፡፡ ጳውሎስ በግሉ ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝቷል!

▣ ***"እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ"*** እንደ መለከት ያለ ድምፅ 1፡10 ላይ ተጠቅሷል (ማስታወሻ ተመልከት)። በመጀመሪያ ይሄ የሚያመለክተው ኢየሱስ ሲናገር ነው፣ ነገር ግን ምዕራፍ 4 እና 5 ጽሑፋዊ ምድብ ናቸው፣ ኢየሱስም እስከ 5፡5፣9-10፣12፣13 ድረስ አልተዋወቀም፣ ይህ ምናልባት የሚያመለክተው የተገለጠውን መልአክ ይሆናል (እሱም የአፖካሊፕቲካዊ ዓይነት ባሕርይ)። የመልአክ ድምፅ እና የመለኮት መነፋት ከጳውሎስ የዳግም ምጽአት ገለጻ ጋር ይዛመዳል (1 ተሰ. 4፡16)።

▣ ***"ወደዚህ ውጣና"*** ዲስፔንሴሽናሊስቶች እንደሚገምቱት ይህ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራዊ መነጠቅ ነው፣ በራዕይ መጽሐፍ ላይ ካላቸው ከእነርሱ ቅድመ-ግምታዊ መረዳት የተነሣ (ሁሉም የብኪ ትንቢቶች የግድ በጥሬው መፈጸም ይኖርባቸዋል፤ ቤተ ክርስቲያንና እስራኤል ፍጹም የተለያዩ ናቸው፤ ቤተ ክርስቲያን በምሥጢር ወደ ሰማይ ትነጠቃለች፣ ስለሆነም የብኪ ትንቢቶች በምድራዊቷ እስራኤል ላይ ሊፈጸሙ ይችላሉ)። ይህ ትርጉም ዘወትር በዝምታ ጊዜ ሙግት ይደገፋል፣ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል ከምዕራፍ 3 በኋላ በራዕይ ላይ ስለማይከሰት (ከ22፡10 በቀር)። ሆኖም፣ በጽሑፉ ውስጥ አመልካች ምንም የለም፣ ማንም ሳይሆን ዮሐንስ ነው ወደ ሰማይ የተጠራው።

ቁ. 5 ላይ ካለው "ከመብረቁ" እና "ነጎድጓዱ" የተነሣ ይህ ምናልባት የሙሴ ወደላይ መጠራት ጠቃሽ ነው (ዘጸ. 19፡20፣24) ወደ ሲና ተራራ የእግዚአብሔርን ራዕይ ለመቀበል (ዘጸአት 19-20፣ በተለይም፣ 19፡16፣19)።

ደግሞም የእግዚአብሔር ድምፅ እንደሚጮኽ መለከት ዘጸ. 19፡19 ላይ መጠቀሱን ተገንዘብ (ልዩ ርዕስ፡ በእስራኤል ጥቅም ላይ የዋሉት ቀንደ-መለከቶች 1፡10 ላይ ተመልከት)።

▣ ***"ከእነዚህ ነገሮች በኋላ የሚሆነውን"*** ይህ ሐረግ የዳን. 2፡29፣45 ጠቃሽ ይሆናል። እንደዛ ከሆነ እሱ የሚያመለክተው ተለጣጣቂ የሆኑ ታሪካዊ ሁነቶችን ነው፣ የወደፊት ሁነቶችን ሳይሆን። ራዕይ የአንደኛው ክፍለ ዘመን ነገሮች እና ወደፊት በርቀት ክፍለ-ዘመናት ነገሮች አይደለም፣ ነገር ግን ሁነቶቹ፡

1. በየዘመናቱ የሚከሰቱ (ማቴ. 24:4-14)

2. የሚያንጸባርቁት ከክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት እና በዳግም ምጽአቱ መካከል ያለውን ጊዜ በሙሉ ነው (የመጽሐፉ ሰባት ጽሑፋዊ ምድብ)

ይህ ሐረግ ከ1፡1 ጋር ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እና ፍቃድ (*dei*) የግድ መፈጸም ይኖርበታል። እዚህ የጊዜው ጉዳይ (ማለትም፣ በቶሎ) ወጥቷል፣ ነገር ግን ርግጠኝነቱ ይኖራል። እግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅዱን ይፈጽማል!

**4፡2 "ወዲያውኑ በመንፈስ ነበርኩ"** ዮሐንስ በመንፈስ እንደነበረ ተገልጿል 1:10፤ 17:3 እና 21:10 ላይ።ይኸም ተመሳሳይ የሚሆነው ሕዝቅኤል ላይ እንደሆነው ነው፣ ሕዝ. 8:1-4፤ 11:1፣ ኢየሱስ ማቴ.. 4:8፤ ፊሊጶስ ሐዋ. 8:39-40፣ እና ጳውሎስ II ቆሮ. 12:1-2። ይህ መንፈሳዊ መመሰጥ ይሁን ወይም አካላዊ መወሰድ ለመሆኑ ርግጠኝነት የለም።

▣ **"ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ፤"** "ዙፋን" (*thronos*) የሚለው ቃል በዚህ መጽሐፍ ላይ ከ47 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ ውሏል። የእግዚአብሔር ግዛት ማዕከላዊ ይዘት ነው፣ የዚህ ሰማያዊ ራዕይ (ምዕራፍ 4 እና 5)። ዙፋኑ ተምሳሌታዊ፣ አፖካሊፕቲካዊ መንገድ ነው፣ ያህዌ ታሪክን ሁሉ እንደሚቆጣጠር ለማሳያ። እግዚአብሔር መንፈሳዊ፣ ዘላለማዊ፣ አካላዊ መንፈስ ነው፤ በዙፋን ላይ አይቀመጥም (ልዩ ርዕስ 2፡1 ላይ ተመልከት)!

አንደኛው የትንቢትና የአፖካሊፕቲክ ዘውግ ዓላማ፣ እግዚአብሔር የወደፊቱን ሁነቶች ማወቁና መቆጣጠሩ ነው። ታሪክ ሁሉ ይታወቃል በዓላማም ነው (*telos*፣ ማቴ. 24:14፤ I ቆሮ. 15:24-28)።

ዙፋኑ የተገለጸው "ቆሞ ነበር" በሚል ነው። ያልተጠናቀቀ ጊዜ፣ ሁለት ፍችዎች ሊኖሩት ይችላሉ፡ (1) እሱ ዘወትር አንደቆመ ነው ወይም (2) ተዘጋጅቷል። ይህም ከዳንኤል 7፡9 "ዙፋኖች ተዘጋጅተዋል" ጋር ጠቃሽ ይሆናል።

**4፡3 "ተቀምጦም የነበረው…የመሰለ ነበር"** ዮሐንስ የእግዚአብሔርን ገጽታ መግለጽ ጀምሯል፣ ምክንያቱም በአይሁድ አስተሳሰብ፣ ይህ ፈጽሞ ተገቢ ስላልነበረ (*telos*፣ cf. ማቴ. 24:14፤ I ቆሮ. 15:24-28)። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ክብር ይገልጻል በሦስት የከበሩ ድንጋዮች። ደግሞም የከበሩ ድንጋዮች ሕዝ. 28፡13 ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል ሰማያዊውን (የእግዚአብሔር ገነት) ምስያ ለመግለጽ።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት**
**አየተመቅ፣ አእት** **"ኢያሰጲድ"**
**አኢመቅ** **"ዕንቍ"**

የከበሩ ድንጋዮቹ ትክክለኛ ቀለምና ስም በጣም ርግጠኛ አይደለም፣ በጥንታዊ ሥነ-ጽሑፍ። የከበሩት ድንጋዮች ቀለሞችና ስሞች ከአገር አገር እና ከዘመን ዘመን ይለዋወጡ ነበር። ኢያስጲድ የመጀመሪያው ድንጋይ ነበር፣ በሊቀ ካህኑ ደረትጌ ላይ የሚገኝ፣ እሱም ዘጸ. 28፡17-21 ላይ የተጠቀሰው። ይህ ድንጋይ የጠራ ድንጋይ ይመስላል። እሱም "ከብርጭቆ ባሕር" ጋር ይያያዛል (ዝከ. 4:6፤ 15:2፤ 21:11፣18፣21)። እሱም የእኛን አልማዝ ጠቃሽ ነው።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"ሳርድዮስ"**
**አየተመቅ፣ አእት** **"ካርኒሊያን"**
**አኢመቅ** **"ሩቢ"**

ሳርድዮስ ደም-ቀይ ድንጋይ ነበር። እሱም የመጨረሻው ድንጋይ ነው፣ በሊቀ ካህኑ ደረትጌ ላይ። ይህ ምናልባት ለእግዚአብሔር ጠቃሽ ነው፣ ፊተኛውና ኋለኛው የሆነ፣ የይሁዳ ነገዱ መሲሐዊ አጽንኦት የሚሰጥ (መረግድ (አረንጓዴ) ቀስተ-ደመና)። እነዚህ ሁለት ድንጋዮች በጥንታዊ ጽሑፎች ተዘርዝረዋል፣ ለሁሉም ጌጣጌጥ ማጣቃለያ።

▣ **"በመልኩም መረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ"** መረግድ ድንጋይ ነው፣ ለይሁዳ፣ በሊቀ ካህኑ ደረትጌ ላይ። የዚህ ቀስተ-ደመና አጽንዖት እጅግ አጠራጣሪነት ነበረው፣ ነገር ግን ሁለት ዋነኛ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ።

1. አንዳንዶች እሱን የሚመለከቱት ለዘፍ. 9፡16 ጠቃሽ ነው፣ እዚያም ቀስተ-ደመና ለእግዚአብሔር የጥበቃ ኪዳን ተምሳሌት ሆኖ የቀረበ፣ እና የማዕበሉ ማለፍ ምልክት፤ በፍርድ መካከል ተስፋና ምሕረት አለ።
2. ሌሎች የሚያዛምዱት ለሕዝ. 1፡28 ጋር ንው፣ የያህዌ ክብር ተምሳሌት።

ቀስተ ደመና የፍርድ ምልክት ይሁን የኪዳን አልለየም፣ ነገር ግን እሱ ያልተለመደው ቀስተ ደመና ነው፣ ምክንያቱም ቀለሙ አረንጓዴ ስለነበረና ከተለመደው ብርሃን የተለወጠ ስለሆነ።

**4፡4 "በዙፋኑ ዙሪያም ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፥"** የሃያ አራቱ ዙፋኖች ምክንያት አወዛግቧል።

1. አንዳንዶች የሚመለከቱት እንደ አሮናዊ ክህነት ቅደም ተከተል፣ በዳዊት ከተሰናዳው ጋር በማያያዝ ነው I ዜና. 24:7-19
2. ሌሎች የሚመለከቱት እንደ ሰማያዊ ጉባኤ ነው፣ እሱም I ነገሥ. 22:19፤ ኢሳ. 24:23፤ ዳን. 7:9-10፣26 ላይ እንደተጠቀሰው።

አስገራሚ የሚሆነው ይህ ቁጥር በአይሁድ በይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲክ ሥነ-ጽሑፍ አለመገኘቱ ነው።

▣ **"ሃያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው"** እነዚህን ሽማግሌዎች ማንነት በተመለከተ ብዙ ክርክሮች ተካሂደዋል። ሁለት ዋነኛ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ

1. እነርሱ አማኞችን ይወክላሉ፡
   ሀ. ነጭ እንደለበሱ መሳላቸው (I ቆሮ. 9:25፤ I ተሰ. 2:19፤ II ጢሞ. 4:8፤ ያዕቆብ 1:12፤ I ጴጥ. 5:4)
   ለ. መላእክት ፈጽሞ አክሊል ጭነው በዙፋን ላይ ይቀመጣሉ አልተባለም (ዝከ. ቁ. 4፣10)
   ሐ. እነርሱም በዝርዝሩ ውስጥ አሉ፣ መላእክትን በተለይ በሚያካትተው (ዝከ. 5፡11)

መ. 5፡9-10 በቫልጌት፣ ፔሺታ፣ እና ኋላ ላይ በቴክስተስ ሪሴፕተስ ሽማግሌዎች ተካትተዋል፣ በመዋጀት መዝሙሮች

2. እነርሱ መላእክትን ይወክላሉ፡
   ሀ. መላእክት መጭ ልብስ ይለብሳሉ (ማቴ. 28:3፤ ዮሐንስ 20:12፤ ማርቆስ 16:5፤ ሐዋ. 1:10፤ ራዕ. 15:6 እና ዳን. 10:5፣6)
   ለ. እነዚህ ሽማግሌዎች ዘወትር የሚገለጹት ከእንስሶቹ ጋር ነው፣ እንደ 5፡11፣14፣ እሱም ሦስት የተለያዩ የመላእክት ተራዎችን የሚዘረዝሩ
   ሐ. አንደኛው ሽማግሌ እንደ ገላጭ መልአክ ያደርግ ነበር (ዝከ. 5፡5)
   መ. ኢሳ. 24፡23 ላይ የእግዚአብሔር መላእክት ሰማያዊ ጉባኤ "ሽማግሌዎች" ይባላሉ
   ሠ. የ5፡10 ጽሑፋዊ ማስረጃ የሚያመለክተው ሽማግሌው ራሱን አላካተተም፣ ሰዎችን በመዋጀት መዝሙር ላይ

## ልዩ ርዕስ፡ ሽማግሌ

1. ለእግዚአብሔር መላእክት ጥቅም ላይ ይውላል፣ እነርሱም የመላእክት ጉባኤ ከሆኑት (ኢሳ. 24፡23)። ይኸው ተመሳሳይ ቃል ራዕይ ላይ ለመልአካዊ ፍጡራን ጥቅም ላይ ውሏል (ዝከ. 4፡4፣10፤ 5፡5፣6፣8፣11፣14፤ 7፡11፣13፤ 11:16፤ 14፡3፤ 19:4)።
2. ለነገድ አለቆች ጥቅም ላይ ውሏል (*zaqen*) በብኪ (ዘጸ. 3:16፤ ዘኍ. 11:16)። ኋላ ላይም በአኪ ይህ ቃል ለመሪዎች ቡድን ጥቅም ላይ ውሏል፣ ከኢየሩሳሌም፣ እነርሱም ከፍተኛውን የአይሁድ ሸንጎ (ሳንሄድሪን) የመሠረቱ (ማቴ. 21:23፤ 26:57)። በኢየሱስ ቀን ይህ ሰባ አባላት ያሉት አካል በተበላሸ የክህነት ሥርዓት ተይዞ ነበር።
3. ለአኪ ቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ መሪዎች ጥቅም ላይ ውሏል። እሱም ከሦስቱ ተመሳሳይ ቃላት አንዱ ነው (መጋቢ፣ መሪ፣ እና ሽማግሌ፣ ቲቶ 1:5፣7፤ ሐዋ. 20:17፣28)። ጴጥሮስና ዮሐንስ ተጠቅመውበታል፣ ራሳቸውን በአመራር ወገን ለማካተት (1 ጴጥሮስ 5:1፤ II ዮሐንስ 1፤ III ዮሐንስ 1)።
4. በቤተ ክርስቲያን ላሉ ሽማግሌ ሰዎች ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለአመራር ላይሆን ይችላል (1 ጢሞ. 5:1፤ ቲቶ 2:2)።

▣ **"የወርቅ አክሊሎች"** በቅዱስ ቃሉ የትኛውም ስፍራ መላእክት አክሊል እንደተጫኑ አልተባለም (ዳንኤል 10 ላይ ያለው ብርቱ መልአክ እንኳ ቢሆን)። ከጥልቁ የሆኑት ሰይጣናዊ ጭፍራዎች ከወርቅ አክሊል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነገር እንደደፉ ተገልጿል፣ 9፡7 ላይ።

**4፡5 "ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል፤"** ይህ የዘጸ. 19፡16-19 ተመሳሳይ ነው፣ እሱም አካላዊ ክስተቱን የሚገልጽ፣ በሲና ተራራ ላይ የእግዚአብሔርን መገኘት የሚከብብ። እነዚህ ሐረጎች የእግዚአብሔርን መገኘት ያመለክታሉ (ዝከ. 11፡19) ወይም የእርሱን ፍርድ (ዝከ. 8፡5፤ 16፡18)።

▣ **"ሰባት የእሳት መብራቶች"** እነዚህ የሚከሰቱት ሰባት የተለዩ መብራቶች ሆነው ነው (ችቦዎች)፣ አንድ ጽዋ ከሰባት ጧፎች (መብራት) ጋር ሳይሆን (ዘጸ. 25፡37፤ ዘካ. 4፡2)። እነርሱ የሚሠሩት ከሌሎቹ "ከሰባቱ" ሁሉ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ነው፣ የእግዚአብሔርን መገኘት የሚያመለክቱ።

▣ **"እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።"** ይኸው ተመሳሳይ ሐረግ 1:4፤ 3:1 እና 5:6 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። እሱም ዘወትር የሚተረጎመው መንፈስ ቅዱስን ለመጥቀስ ነው፣ 1፡4 ላይ በመመሥረት፣ ነገር ግን አንዳቸውም ሌሎች ማጣቀሻዎች ያንን ትርጓሜ አያስረግጡም። ይህ ሐረግ ከቤተ ክርስቲያኖቹ ጋር አቻ የተደረገ ይመስላል (ሰባት ከዋክብት፣ 3፡1፣ ሰባት መብራቶች፣ 4፡5) ወይም የበጉ ሁሉን ቻይነትና በሁሉን አዋቂነት (5፡6)። ልዩ ርዕስ፡ ሰባቱ መናፍስት 1፡4 ላይ ተመልከት።

**4፡6 "ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር"** ይህን ሐረግ በተመለከተ በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡
1. እሱ የሚያመለክተው በመቅደሱ ውስጥ ያለውን የመታጠቢያ ሳሕን ነው (1 ነገሥ. 7:23፤ II ዜና. 4:2-6)
2. እሱ የሚዛመደው የብርጭቆ ባሕር ጽንሰ-ሐሳብ ነው፣ ዘጸ. 24:9-10 የሚገኘውን
3. እሱም የእግዚአብሔር ተንቀሳቃሽ ሠረገላ ክፍል ነው ሕዝ. 1:22፣26፤ 10:1
4. እሱም ከእግዚአብሔር ቅድስና የመካፈል ተምሳሌት ነው (ዝከ. 15:2)

ይህ ባሕር ራዕ. 21፡1 ላይ ተወግዷል፣ ርግማኑን የሚያሳየው (ዘፍጥረት 3) የሰው ልጅ ኃጢአትና መለየት ተወግዷል። 21፡1 ላይ የሚገኘውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"አራቱ እንስሶች"** እነዚህ እንስሳት ቁ. 6-8 ላይ ተገልጸዋል። እነርሱ የሕዝ. 1:5-10 እና 10:1-17 *cherubim* (ኪሩቤል) እና የኢሳ. 6:2፣3 *seraphim* (ሱራፌል) ድብልቅ ናቸው። የክንፋቸውና የፊታቸው ቁጥር ይለያያል፣ ነገር ግን እነዚህ የሰው/እንስሳ/መላእክት ድብልቅ ስዕሎች ናቸው፣ የእግዚአብሔርን ዙፋን የከበቡ (ዝከ. 4:6፣8፣9፤ 5:6፣8፣11፣14፤ 6:1፣3፣5፣7፤ 7:11፤ 14:3፤ 15:7፤ 19:4)።

## ልዩ ርዕስ፡ ኪሩቤል

ሀ. ከብዙዎቹ መልአካዊ ሕላዌዎች አንዱ ነው። ይህ የተለየ ዓይነት ቅዱስ ቦታዎችን ይጠብቃል (ዘጸ. 25:18-22፤ 1 ነገሥ. 8:6-7)።
ለ. ሥርወ ቃሉ ርግጠኛ አይደለም፡
   1. ከአካድያን "ጣልቃ የሚገባ" ወይም "አማላጅ" በእግዚአብሔርና በሰው መሐል

2. ከዕብራይስጥ ይህ የቃላት አግባብ ነው፣ “ሠረገላ” እና ኪሩብ” (ሕዝ. 1፤10)

3. አንዳንዶች የሚሉት፣ እሱ የሚለው “ብሩኅ ገጽታ” ነው

ሐ. አካላዊ ቅርጹ— ይህን ለማረጋገጥ ያስቸግራል፤ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለ የተለያየ ገለጻ እና የተለያየ እንስሳ-ሰው

ቅርጽ፣ በጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ በሚገኙት። አንዳንዶች የሚያያይዟቸው

1. ከክንፋማ የሞሶፖታሚያ በሬዎች
2. ክንፋማ የግብፅ የአሞራ-አንበሶች፣ “ግሪፊንስ” ተብለው የሚጠሩት
3. የሂራም ክንፋማ ፍጥረታት፣ የጢሮስ ንጉሥ ዙፋን
4. የግብፅ ስፊኒክስ እና በንጉሥ አሃብ የዝኆን ጥርስ ሜተ መንግሥት በሰማሪያ የሚገኙት ተመሳሳይ ዓይነቶች

መ. አካላዊ ገጽታ

1. ኪሩቤል የሚለው ቅርጽ የሚያያዘው ከኢሳይያስ 6 ሱራፌል ጋር ነው
2. የተለያዩ ቅርጾች ምሳሌዎች

   ሀ. የፊታቸው ቁጥር

   1) ሁለት- ሕዝ. 41፡18

   2) አራት- ሕዝ. 1:6፣ 10፤ 10:14፣16፣21፣22

   3) አንድ- ራዕ. 4፡7

   ለ. የክንፎች ቁጥር

   1) ሁለት- 1ኛ ነገሥ. 6፡24

   2) አራት- ሕዝ. 1:6፣11፤ 2:23፤ 10:7፣8-21

   3) ስድስት (እንደ ኢሳ. 6፡2 ሱራፌልን የመሰለ)- ራዕ. 4፡8

3. ሌሎች ገጽታዎች

   ሀ. የሰው እጆች- ሕዝ. 1:8፤ 10:8፣21

   ለ. እግሮች

   1) ቀጥ ያለ፣ ጉልበት የሌለው- ሕዝ. 1፡7

   2) የጥጃ እግር- ሕዝ. 1፡7

3. ፍላቪየስ ጆሴፈስ ማንም ኪሩቤል ምን እንደሚመስሉ የሚያውቅ እንደሌለ ተቀብሏል *(የአይሁድ **አንቲኩቲስ*** VIII:3:3)።

ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ የተገኙ ቦታዎችና ተግባራት

1. የሕይወት ዛፍ ጠባቂዎች፣ ዘፍ. 3፡24 (ምናልባትም ለሰይጣን በዘይቤነት ጥቅም ላይ ውለዋል በሕዝ. 28፡14፣16)
2. የመቅደሱ ጠባቂዎች

   ሀ. በኪዳኑ ታቦት ላይ፤ ዘጸ. 25:18-20፤ ዘኍ. 7:89፤ I ሳሙ. 4:4

   ለ. በመሸፈኛና አመጋረጃ የሚከለል፤ ዘጸ. 26:1፣31፤ 36:8፣35

3. የሰሎሞን መቅደስ ጠባቂዎች

   ሀ. ሁለት ትላልቅ የሚያጥብቡ ኪሩቤል በቅድቅተ ቅዱሳን፤ I ነገሥ. 6:23-28፤ 8:6-7፤ II ዜና. 3:10-14፤ 5:7-9

   ለ. በውስጠኛው ሽሪን ግድግዳ ላይ፤ 1ኛ ነገሥ. 6:29,35፤ II ዜና. 3:7

   ሐ. ከብዙ ላቬርስ ጋር በሚገናኙ ከፈፎች ጋር፤ 1ኛ ነገሥ. 7:27-39

4. የሕዝቅኤል መቅደስ ጠባቂዎች

   ሀ. በግድግዳና በበር ላይ የተለበጡ፤ ሕዝ.41:18-20፣ 25

5. ከመለኮት መጓጓዣ ጋር የተያያዙ

   ሀ. የንፋስ ዘይቤ ሊሆን የሚችል፤ 2ኛ ሳሙ. 22:11፤ መዝ. 18:10፤ 104:3-4፤ ኢሳ. 19:1

   ለ. የእግዚአብሔር ዙፋን ጠባቂዎች፤ መዝ. 80:1፤ 99:1፤ ኢሳ. 37:16

   ሐ. የእግዚአብሔር ተንቀሳቃሽ ዙፋን ሠረገላ ጠባቂዎች፤ ሕዝ. 1:4-28፤ 10:3-22፤ I ዜና. 28:18

6. የሔሮድስ መቅደስ

   ሀ. በግድግዳዎች ላይ ተስሏል (ማለትም፣ የታልሙድ “ዮማ” ጠባቂ 54ሀ)

7. የራዕይ የዙፋን ትዕይንት (ማለትም፣ ጠባቂ ራዕ. 4-5)

◘ **“በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው”** ይህ ምናልባት የአራቱን ፊቶች የያንዳንዳቸውን ዓይኖች ይሆናል ወይም ለእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ዘይቤ ይሆናል (ዝከ. ቁ. 8፤ ሕዝ. 1:18፤ 10:12)።

**4፡7 “አንበሳ… ጥጃ… ሰው… ንስር”** ይህ የሕዝ. 1፡6፣10 ግልጽ ጠቃሽ ነው። በራቢያዊ ሥነ-ጽሑፍ እነዚህ የተዘረዘሩት እንደ ጠንካሮች የእግዚአብሔር ፍጥረታት የተለያዩ ቅደም ተከተሎች ነው። ኢሬነኡስ (120-202 ዓ. ም) እነዚህን አራት የተለያዩ ፊቶች አራቱን

የወንጌል ጸሐፍት ለማገለጽ ተጠቅሞበታል (የቤተ ክርስቲያን ልማድ በመጨረሻ የወሰነው ዮሐንስን፣ ንስር፤ ሉቃስን፣ ሰው፤ ማርቆስን፣ በሬ፤ ማቴዎስን፣ አንበሳ አድርጎ ነው) ይህ ግን እጅግ ግምታዊና አሊጎሪያዊ ነው። እነዚህ ድብልቅ ፍጥረታት ተምሳሌታዊ ናቸው፣ እማሬያዊ ሳይሆኑ። ብኪ የሚሰጠውን እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ቅደም ተከተል አጽንዖት በማወቅ፣ የሰውና የእንስሳ ድብልቅ ፍጥረት ከሌዋውያን አኳያ ንጹሕ ያልሆኑ ናቸው። ይህ የርግጠኛ ነገሮች እና ሁነቶች ታሪካዊ ትርክት አይደለም፣ ነገር ግን እጅግ ተምሳሌታዊ የሆነ ዘውግ ነው፣ የመዳረሻውን መንፈሳዊ እውነቶች ለማገለጽ የሚሻ፤ በዚህ ምክንያትም እግዚአብሔር ዘላለም እንደሚኖር (ቁ. 8፡9)፣ ቅዱሱ (ቁ. 8)፣ እና የሁሉም ነገር ፈጣሪ (ቁ. 11)።

**4፡8 "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ"** እነዚህ ፍጥረታት ኢሳ. 6፡2፣3 ላይ ያለውን የሱራፌልን መዝሙር ይደግማሉ። ይህ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት በርካታ ዝማሬዎች የመጀመሪያው ነው (ዝከ. 4:8፣11፤ 5:9-10፣12፣13፤ 7:12፤ 11:17-18፤ 12:10-12፤ 15:3-4፤ 16:5-7፤ 18:2-8፤ 19:1-3፣ 6-7)። ዝማሬዎቹ ዘወትር ራዕዩን መተርጎሚያ ናቸው። ሌላው ተምሳሌት፣ እንደ የብርጭቆ ባሕር፣ የሚያገለግለው እንደ ዕብራይስጥ ማወዳደሪያ፣ ለእግዚአብሔር ፍጹም ቅድስና ነው።

▣ **"ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ"** እነዚ ሦስቱ የብኪ የእግዚአብሔር ስሞች ነበሩ (ዝከ. 1፡8)፡

1. ጌታ = ያህዌ (ዘጸ. 3፡14፤ መዝሙር 103)
2. አምላክ = ኤሎሂም (መዝሙር 104)
3. ሁሉን የሚገዛ = ኤል ሻዳይ፣ የአባቶች የእግዚአብሔር ስም (ዘጸ. 6፡3)

ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞችን 1፡8 ላይ ተመልከት።

▣ **"የነበረውና ያለ የሚመጣውም"** ይህ ሐረግ ተደጋጋሚ መጠሪያ ነው (ዝከ. 1:4፤ 4:8፤ ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት፣ 1:4 ላይ)። ይህ የእግዚአብሔር የኪዳን ስም፣ ያህዌ መጠሪያ ነው፣ እሱም ከ"መሆን ግሥ" የመጣ። ይኸው ተመሳሳይ ጭብጥ ቁ. 9 እና 10 ላይ ተደግሟል፣ "ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ" በሚለው ሐረግ፣ (ዝከ. 10፡6፤ 15፡7)።

**4፡9-11** ይህ በግሪክ አንድ ዓረፍተ ነገር ነው፣ አምልኮ ሁሉ ለእርሱ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው እና ዘላለም ለሚኖረው እንደሚገባ የሚያሳየው (መዝሙር 47፤ ዳን. 4:34፤ 12:7)። ይህ ምናልባት ሰማያዊ ጉባኤ የሚባሉት የመላእክት ቋሚዎች ጠቃሽ ይሆናል (1 ነገሥ. 22:19፤ ኢዮብ 1:6፤ ዳን. 7:10) ወይም የአይሁድ "የመገኘቱ መላእክት" (ማለትም፣ ጦቢት 12:15)።

**4፡9 "እንስሶቹም"** እነዚህ መልአካዊ ፍጡራን በመጽሐፉ ተዘውትረው ተጠቅሰዋል (ዝከ. 5:6፣8፣14፤ 6:1፤ 7:11፤ 14:3፤ 15:7፤ 19:4)።

**4፡10 "በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።"** ይህ እውቅና የመስጠታቸው ተምሳሌት ነው፣ እግዚአብሔር ምስጋና ሁሉ እና ክብር እንደሚገባው! አክሊላቸውን ያገኙት በምንም ምክንያት ቢሆንም፣ ኃይሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ እውቅና ሰጥተዋል!

**4፡11 "አንተ ሁሉንም ነገር ፈጥረሃልና"** ሽማግሌዎቹና እንስሶቹ እግዚአብሔርን አመስግነዋል እንደ ፈጣሪ፣ ጠባቂ፣ እና ሰጪ፣ ሁሉንም ነገር። ይህ ሥነ-መለኮታዊ አጽንዖት ነው ኤሎሂም ለተባለው ስም (ዘፍጥረት 1፤ ኢዮብ 38-41፤ መዝሙር 104)። ይህ ምዕራፍ የእግዚአብሔርን እጅግ ተዘውታሪ ስሞች፣ እነርሱም የእሱን ድርጊት የሚገልጹትን፣ ሥነ-መለኮታዊ ፍችዎችን ተጠቅሟል። ቀጣይነት ያለው የአኪ መገለጥ ግልጽ ያደረገው ኢየሱስ በፍጥረት ላይ ከአብ ጋር መሥራቱን ነው (ዮሐንስ 1:3፤ 1 ቆሮ. 8:6፤ ቆላ. 1:16 እና ዕብ. 1:2)።

**ራዕይ፡ 5፡1-5**

**[1]በዙፋኑ ላይም በተቀመጠው በቀኝ እጁ ላይ በውስጥና በኋላ የተጻፈበት በሰባትም ማኅተም የተዘጋ መጽሐፍን አየሁ። [2]ብርቱም መልአክ። መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ማኅተሞቹንም ይፈታ ዘንድ የሚገባው ማን ነው? ብሎ በታላቅ ድምፅ ሲያውጅ አየሁ። [3]በሰማይም ቢሆን በምድርም ላይ ቢሆን ከምድርም በታች ቢሆን መጽሐፉን ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው ማንም አልተቻለውም። [4]መጽሐፉን ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው የሚገባው ማንም ስላልተገኘ እጅግ አለቀስሁ። [5]ከሽማግሌዎቹም አንዱ። አታልቅስ፤ እነሆ፥ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ሥር መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቶአል አለኝ።**

**5፡1 "በዙፋኑ ላይም በተቀመጠው በቀኝ እጁ ላይ አየሁ"** የዚህ ሐረግ የተሻለ ትርጉም የሚሆነው "በቀኝ እጁ ላይ" ነው (ፔሺታ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው በላምሳ ነው እንዲሁም የተብራራው መጽሐፍ ቅዱስ)። መጽሐፉን አጥብቆ መያዝ የእግዚአብሔር ሐሳብ አይደለም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ለማንም ይሰጠዋል፣ ወስዶ እንዲያነበው።

"በቀኝ እጁ ላይ" የሚለው ሐረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሰው አካላዊ ነው (አንትሮፖሞርፊዝም)፣ የእግዚአብሔርን ኃይል እና ሥልጣን ለማሳየት (ልዩ ርዕስ 2፡1 ላይ ተመልከት)። እግዚአብሔር ሥጋዊ አካል የለውም፤ እሱ መንፈሳዊ ሕላዌ ነው (ዮሐንስ 4፡ 24)፣ ያልተፈጠረና ዘላለማዊ።

▣ **"መጽሐፍ"** የግሪኩ ቃል "*biblion*" ነው፣ እሱም ኋላ ላይ ጥቅል-ጽሑፍን (መጽሐፍ) ለመጥቀስ ጥቅም ላይ ውሏል። አብዛኞቹ አታቾች የሚስማሙት፣ መጻሕፍት እስከ ሁለተኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ እንዳልነበሩ ነው፣ ስለሆነም፣ እዚህ ያለን ወረቀት (ፓፒረስ) ወይም የብራና ጥቅል ነው (አኪጀት፣ አየተመት፣ አእት፣ እና አኢመቅ)። የዚህን መጽሐፍ ፍቺ በተመለከተ በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ።

1. የዋይታ መጽሐፍ ሕዝ. 2:8-10፤ እና ራዕ. 10:8-11
2. ሰዎች ሊያነቡት የማይሹት መጽሐፍ፣ አምላክ ከመንፈሳዊነት አኳያ ስላሳወራቸው (ኢሳ. 29:11፤ ሮሜ. 11:8-10፣25)
3. የፍጻሜ ዘመን ሁነቶች (ዳን. 8፡26)

4. የሮሜ የፍጻሜ ፍቃድ ወይም መግለጫ፣ እሱም ከልማድ አኳያ በሰባት ማኅተሞች የሚታተም
5. የሕይወት መጽሐፍ (ዳን.7:10፤ 12:1)፣ እሱም በራዕይ መጽሐፍ ተዘውትሮ የሚጠቀስ (ዝከ. 3:5፤ 17:8፤ 20:12፣15)
6. ብሉይ ኪዳን (ቆላ. 2:14፤ ኤፌ. 2:15)
7. ሰማያዊ ጽላቶች (ጽሑፎች) 1 ሔኖክ 81:1፣2።

በእኔ አስተያየት፣ ቁ. 1፣ ቁ. 2፣ ወይም ቁ. 3 ገጽታዎች የተሻሉ ይመስላሉ፤ ጥቅሉ የሰው ልጅ መዳረሻ እና የእግዚአብሔር የታሪክ አጠቃላይነት መጽሐፍ ነው።

◘ **"በውስጥና በኋላ የተጻፈበት"** ይህ በጥንታዊው ዓለም ፍጹም ያልተለመደ ነው፣ ምክንያቱም ከፓፒረስ ጀርባ መጻፍ ስለሚያስቸግር፣ ምንም እንኳ ሕዝ. 2፡8-10 እና ዘካርያስ 5፡3 ላይ ቢጠቀስም። እሱም ተምሳሌትነቱ የእግዚአብሔርን ፍጹምና ሙሉ ተቆጣጣሪነት ነው፣ ታሪክንና የሰውን ፍጻሜ።

ሁለቱም አንቀጾች (የተጻፈ እና የታተመ) እነርሱም ይህንን ጥቅል የሚገልጹት የተጠናቀቁ ተገብሮዎች ናቸው። የመጀመሪያው ልዩ ሰዋሰዋዊ መልክ ነው፣ ቅዱስ ቃሉን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ተመስጦ ስለመሆኑ (ዮሐንስ 6:45፤ 8:17፤ 10:34፣ ወዘተ)። ሁለተኛው የመግለጫ መንገድ የሆነው ጥቅሉ በእግዚአብሔር እንደተጠበቀ፣ እንደተከለለ፣ እና እንደቆየ ነው።

◘ **"በሰባቱ ማኅተሞች የታተመ"** ሰባቱ ማኅተሞች ሁለት ታሳቢ መነሻ ይኖራቸዋል፡

1. ሰባት ፍጹም ቁጥር ነው፣ ከዘፍጥረት 1፣ ስለዚህ እሱ ፍጹም ሆኖ ታትሟል።
2. የሮሜ ፍቃዶች በሰባት ማኅተም ይታተሙ ነበር።

ማኅተሞች አነስተኛ የሰም ቅርጾች፣ እነርሱም የባለቤቱን አትም የያዙ ሆነው፣ መጽሐፉ ወይም ጥቅሉ የሚከፈትበት ስፍራ ይደረጋሉ (ልዩ ርዕስ 7፡2 ላይ ተመልከት)። 6፡1-8፡1 ላይ የእነዚህ ማኅተሞች መፈታት በምድር ላይ ዋይታን ሲያመጣ፣ ነገር ግን የጥቅሉ ይዘት በዚህ ጽሑፋዊ ምድብ አይገለጥም። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በመጽሐፉ መዋቅር፣ ሰባተኛው ማኅተም ሰባቱን መለከቶች ያስጀምራል፣ እሱም ሰባተኛው ማኅተም የሆነ።

**5፡2 "ብርቱ መልአክ አየሁ"** አንዳንዶች የሚመለከቱት ከሥርወ-ቃል አኳያ ገብርኤል ከሚለው ስም ጋር ያያይዙታል፣ ፍችውም "የእግዚአብሔር ብርቱ ሰው" የሚል። ሌለኛው ብርቱ መልአክ 10፡1 እና 18፡21 ላይ ተጠቅሷል። መልአካዊ ምልጃ በአይሁድ በይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፒቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ የተለመደ ነው።

◘ **"በታላቅ ድምጽ ሲያውጅ"** እሱም ለፍጥረት ሁሉ ይደርሳል።

◘ ***"መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ማኅተሞቹንም ይፈታ ዘንድ የሚገባው ማን ነው?"*** "የሚገባው" የሚለው ቃል የንግድ ቃል ነው፣ ጥንድ ሚዛኖችን ከመጠቀም ጋር የተያያዘ። እሱም፣ "እቻ የሚሆነው" ማለት ነው። አንድ ነገር በሚዛኑ አንደኛው በኩል ይቀመጣል፣ በሌለኛው በኩል የሚቀመጠውም እኩል ነው። እሱም በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። እዚህ፣ ሊወዳደሩት እንደማይቻል ዋጋ ነው፣ ኃጢአት የሌለበት አዳኝ። ኢየሱስ ብቻ ነው ከማዳኑ ሥራ ጋር እኩል የሆነ። ኢየሱስ ብቻ ነው ከመቀዳጀት ሥራ ጋር እኩል የሆነ። ኢየሱስ ብቻ ነው የሚገባው (ዝከ. 5:7፣ 9-10፣12)።

**5፡3 "በሰማይም ቢሆን በምድርም ላይ ቢሆን ከምድርም በታች ቢሆን መጽሐፉን ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው ማንም አልተቻለውም።"** ይህ የሚያሳየው የመላእክትንም ሆነ የሰዎችን ፈጽሞ አለመቻል ነው፣ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማምጣት! ዐመጻ ሁሉንም ነክቷቸዋል! ፍጥረት ራሱን ሊረዳ አይችልም! ማንም አይገባውም!

**5፡4 "እጅግ ማልቀስ ጀመርኩ"** ይህ ይህ ያልተጠናቀቀ የግስ ጊዜ ነው፣ እሱም የአንድን ድርጊት ወይም ተደጋጋሚ ድርጊት መጀመር የሚገልጽ፣ በአላፊ ጊዜ። ይህ ማለትም "ታላቅ ልቅሶ"፣ የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ባሕርይ።

**5፡5 "ከሽማግሌዎቹ አንዱ አለኝ"** እዚህ ከሽማግሌዎቹ አንዱ እንደ መልአካዊ ተርጓሚ ሲያደርግ እናገኘዋለን፣ እንደ ዳንኤል መጽሐፍ። ልዩ ርዕስ፡ ሽማግሌ 4፡4 ላይ ተመልከት።

◘ **"እታልቅስ"** ይህ የአሁን ተተኳሪ ነው በአሉታዊ አንቀጽ፣ እሱም ዘወትር ፍችው ቀደም ብሎ በሂደት ላይ ያለን ድርጊት ማቆም ነው።

◘ **"ከይሁዳ ነገድ የሆነ አንበሳ"** ይህ የዘፍ. 49:9-10 (II ኢስድራስ 12:31፣32)። መሲሑ አሸናፊ አንበሳ (ንጉሥ) ነው፣ ከይሁዳ ነገድ።

◘ **"የዳዊት ሥር"** ይህ II ሳሙኤል 7 እና በተለይ ኢሳ. 11:1-10 ጠቃሽ ነው። ይህ የንጉሣዊው ዳዊታዊ መሲሕ ተመሳሳይ ሐሳብ ነው፣ ኤር. 23:5፤ 33:5 እና ራዕ. 22:16 የሚገኘው።

◘ **"ድል ነሥቷል"** ይህ የድርጊት የአሁን አመላካች ነው፣ እሱም የሚያመለክተው የተቀዳጀን ሐቅ ነው (ማለትም፣ ቀራንዮ እና ባዶ መቃብር)። አንበሳው በራሱ ኃይል ድል አለማድረጉን ተገንዘብ፣ በራሱ መሥዋዕት እንጂ (ዝከ. ቁ. 6)።

### ራዕይ፡ 5፡6-10

**6በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልም በሽማግሌዎችም መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፥ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው። 7መጥቶም በዙፋን ላይ ከተቀመጠ ከዚያ ከቀኝ እጁ መጽሐፉን ወሰደው። 8መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፥ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ። 9-10መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥**

**ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ።**

**5፡6 "በግ ቆሟል"** የተሠዋ በግ ጽንሰ-ሐሳብ (ማለትም፣ የበግ ጠቦት፣ *arnion*) የኢየሱስ ክርስቶስን ተለዋጭ ዋጅ እና ትንሣኤ ያመለክታል። በጉ በራዕይ መጽሐፍ ሁሉ ተጠቅሷል (ዝከ. 5:6፣8፣12፣13፤ 6:1፣16፤ 7:9፣10፣14፣17፤ 12:11፤ 13:8፤ 14:1፣4(ሁለቴ)፣10፤ 15:3፤ 17:14፤ 19:7፣9፤ 21:9፣14፣22፣23፣27፤ 22:1፣3)። መሥዋዕታዊ ዘይቤው ከ

1. የፋሲካ በግ (ዘጸ. 12)
2. ቀኑ ጧትና ማታ ከሚሠዉት በጎች አንደኛው (ቀጣይነት ያለው፣ ዘጸ. 29:38-46፤ ዘኍ. 28:3፣6፣10፣23፣31፤ 29:11፣16፣ 19፣22፣25፣28፣31፣34፣38)
3. የታረደው በግ የኢሳ. 53:7 ወይም የዮሐንስ 1:7፣29

ይህ ዘይቤ ለኢየሱስ በሁለት የተለዩ መልኮች ጥቅም ላይ ውሏል: (ሀ) እንደ ንጹሕ መሥዋዕት እና (ለ) እንደ አሸናፊ ባለ-ድል (ደግሞም በአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍም ይገኛል፣ 1 ሔኖክ 90፡9፤ የዮሴፍ ምስክርነት 19፡8-9)። በአኪ. ዮሐንስ መጥምቁ ብቻ፣ ዮሐንስ 1፡29፣36 ላይ እና ዮሐንስ በራዕይ 5:6፣8፣12፣13፤ 61:1 ላይ ኢየሱስን እንደ "በግ" ገልጸውታል (ጳውሎስም ይሄንን ያስረግጣል፣ ነገር ግን ያለ ቃሉ፣ 1ክ ቆሮ. 5፡7)።

◘ **"እንደ ታረደ"** ሞቶ ነበር ግን አሁን በሕይወት አለ። የመሲሑ ትንሣኤ በባሕሩ አውሬ በስላቅ መልኩ ታይቷል (ዝከ. 13፡3)።

◘ **"ሰባት ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት"** የመጀመሪያው ቃል የሚያመለክተው ኃይልን ወይም ሁሉን ቻይነትን ነው (ዘጸ. 27:2፤ 29:12፤ ዘዳ. 33:17፤ 1I ዜና. 18:10፤ መዝ. 112:9፤ 132:17፤ ኤር. 48:25፤ ሕዝ. 29:21፤ ዘካ. 1:18-21)። ሁለተኛው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሁሉን አዋቂነት ነው (ዝከ. 4:6፣8፤ ሕዝ. 1:18፤ 10:12፤ ዘካ. 3:9 እና 4:10)። ይህ ተምሳሌታዊነት ከዳን. 7:13-14 ጋር ተመሳሳይ ነው።

◘ **"ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው"** ልዩ ርዕስ 1፡4 እና 4፡5 ላይ ማስታወሻውነ ተመልከት።

**5፡8 "መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፥"** ይህ የሚያሳየው ለበጉ የሚገባውን ስግደት ነው፣ ደግሞም ለእግዚአብሔር የሚገባውን ስግደት (ዝከ. ቁ. 13)፣ ይኸውም ራዕይ ላይ ማዕከላዊ ጭብጥ።

◘ **"የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ"** መላእክት ለእግዚአብሔር መደበኛ ጸሎት አድራሾች ናቸው፣ በበይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአይሁድ ሥነ-ጽሑፍ (ጦቢት 12:15፤ 1II ባሮክ 11)። የዕጣን ሐሳብ፣ እሱም ጸሎትን የሚወክለው በቅዱስ ቃሉ በርካታ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (ዝከ. 8:3-4፤ መዝ. 141:2፤ ሉቃስ 1:10)።

◘ **"ቅዱሳን"** ምንም እንኳ "ቤተ-ክርስቲያን" የሚለው ቃል ከምዕራፍ 3 በኋላ ባይከሰትም፣ የ"ቅዱሳን" ጽንሰ-ሐሳብ በመጽሐፉ ሁሉ ላይ ቀጥሏል፣ እሱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚጠቅስ። አማኞችን እንደ "ቅዱሳን" የሆነው ጽንሰ-ሐሳብ በራዕይ የተለመደ ነው (ዝከ. 8:3-4፤ 11:18፤ 13:7፣10፤ 14:12፤ 16:6፤ 17:6፤ 18:20፣24፤ 19:8 and 20:9)።

## ልዩ ርዕስ: "ቅዱሳን"

የዕብራይስጡ አቻ ቃሉ "ከዳሽ" ነው ትርጉሙ አንድን ቦታ፣ ሰውን፣ አንድ ነገርን ለያህዊ መለየት ማለት ነው፡፡ በእንግሊዘኛው ቃል "የተቀደሰ" ይህም ከፍጥረቱ የተለየ የሚያደርጉት ፈጣሪ መሆኑና መለኮታዊ ባህሪው ነው እርሱ ቅዱስ እና ብቻውን የሚኖር ነው፡፡

እግዚአብሔር ከሰው ጋር ሕብረት ማድረግ ይፈልጋል ነገር ግን በዙፋን የሰው ልጅ የሐጢያት ውድቀት ሰውን ከቅሉ እግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዳይኖረው አድርጓል፡፡ እግዚአብሔር ይህንን የፈረሰውን ሕብረት ለመመለስ ሕዝቡን ቅዱስ ሕዝብ በማለት ጠርቷቸዋል ዘሌ 11፡44 19፡2፣ 20፡7፣ 26፣ 21፡8) ሕዝቡ ለእግዚአብሔር የተለየ በመሆኑ ቅዱስ ተብሏል ነገር ግን በቅድስና እንዲኖር ታዟል ማቴ 5፡48

በቅድስና መኖር ይችላል ምክንያቱም አማኞች በክርስቶስ የመስቀል ስራ ሃጢያታቸው ይቅር ተደምስሷል የመንፈስ ቅዱስ ማደሪም ሆነዋል፡፡ ሁለት የሚጋጭ የሚመስል ሃሳብ እንመልከት

1. ክርስቶስ ፅድቃችን ነው
2. መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ስላደረ በቅድስና እንኑር

አማኞች "ቅዱሳን" በመባል ተጠርተዋል "hagios" ምክንያቱም፡- የቅዱሱ እግዚአብሔር ፈቃድ ህይወታችንን ስለሚመራው (2) ከቅዱስ

ከእግዚአብሔር ልጅ ስራ የተነሳ (3) ቅዱሱ መንፈስ ማደሪያ ስለሆንን ቅዱሳን መባል ችለናል፡፡

ከፊሊ. 4፡12 በስተቀር ቅዱሳን የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ተፅፎ ይገኛል መዳን ማለት አንድ ቤተሰብ አካል ወይም ህንፃ ውስጥ መጠለል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ የዳነ ሁሉ ስራ በአካሉ ውስጥ አለው 1ቆሮ 12፡11 ይህም ለአካሉ እድገትና ጤንነት ጠቃሚ ነው፡፡ 1ቆሮ 12፡7 የዳንነው ለማገልገል ነው ቅድስና የዚህ አካል የአኗኗር ዘይቤው ነው፡፡

**5፡9-10** በቂ የተለየ የግሪክ ጽሑፍ ይኖራል፣ ከ "እኛ" ተውላጠ ስም ጋር የሚዛመድ። አኪጀት "እኛ" የሚል ተውላጠ ስም አለው ቁ. 9 ላይ "እኛን ለእግዚአብሔር ዋጀን፣" እና ቁ. 10 ላይ "ለአምላካችንም የንጉሥ ካህናት አደረገን።" አብዛኞቹ ዘመናዊ ትርጉሞች (አአመመቅ፣ አየተመት፣ አእት፣ አኢመቅ) "እኛ"ን ገድፈዋል፣ በሁለቱም ቁጥሮች ላይ። "እኛ" በሁለቱም ቁጥሮች ላይ ካለ፣ እንግዲያውስ የኢየሱስ መሥዋዕታዊ ሞት ሃያ አራቱንም ሽማግሌዎች ያካትታል፣ እነርሱም መልአካዊ ፍጡራን የሚመስሉትን። በመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ የኢየሱስ ሞት ከመልአካዊ መቤዠት ጋር አይያያዝም። ደግሞም፣ የ"እነርሱም" (*autous*) መኖር ቁ. 10 ላይ ከሰዋሰው አኳያ የ"እኛ"ን በዋነኛነት የመኖር ዕድል አያካትትም። ዩናይት ባይብል ሶሳይቲ አራተኛ ዕትም የሁለቱን የብዙ ተውላጠ ስሞች መገደፍ እንደ "ርግጠኛ" ይወስደዋል።

**5፡9 "አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ"** በብኪ. በርካታ ጠቃሾች አሉ፣ ለአዲሱ ቅኔ (መዝ. 33፡3፤ 40፡3፤ 98፡1፤ 144፡9፤ 149፡1 እና ኢሳ. 42፡10)። በብኪ. በእያንዳንዱ ዋነኛ ሁነት፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያመሰግኑ አዲስን ቅኔ እንዲዘምሩ ይበረታቱ ነበር። ይህ የመዳረሻው መዝሙር ነው፣ እግዚአብሔር ራሱን በመሲሕ እና በመሲሑ የመዋጀት ሥራ የገለጠበት፣ በሁሉም አማኞች በኩል (ዝከ. ቁ. 9፣12፣13፤ 14፡3)።

የ"አዲስ" ነገሮች አጽንዖት የአዲሱ ዘመን ባሕርይ ነው፣ ኢሳይያስ 42-66 ላይ ያለው።

1. "አዲስ ነገሮች፣" 42፡9
2. "አዲስ ዝማሬ፣" 42፡10
3. "አዲስ ነገር ማድረግ፣" 43፡19
4. "አዲስ ነገሮች፣" 48፡6
5. "አዲስ ስም፣" 62፡6
6. "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፣" 65፡17፤ 66፡22.

በራዕይም ደግሞ ብዙ "አዲስ ነገሮች" አሉ።

1. "አዲሲቷ ኢየሩሳሌም፣" 3፡12፤ 21፡2
2. "አዲስ ስም፣" 2፡17፤ 3፡12
3. "አዲስ ዝማሬ፣" 5፡9፣10፣12፣13፤ 14፡3
4. "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፣" 21፡1

◘ ***"መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥"*** *ይህ አዲስ ቅኔ* (ቁ. 9-10) በጉ የሚገባው ለመሆኑ አምስትዮሽ ገለጻ ነው።

1. *ተቀያሪ ሞት* (ዝከ. 5፡6፣9፣12፤ 13፡8፤ I ጴጥ. 1፡18-19)
2. *የመዋጃው ዋጋ* ተከፍሏል (ዝከ. 5፡9፤ 14፡3-4፤ *ማርቆስ* 10፡45፤ I ቆሮ. 6፡19-20፤ 7፡23፤ I ጢሞ. 2፡6)
3. ከየአንዳንዱ ሕዝብ ሰዎችን ዋጅቷል (cf. 5፡9፤ 7፡9፤ 14፡6)
4. *አማኞችን የመንግሥት ካህናት* አድርጓል (ዝከ. 1፡6፤ 5፡10)
5. እነርሱም ከእርሱ ጋር ይነግሣሉ (ዝከ. 3፡21፤ 5፡10፤ 20፡4)

◘ **"ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ"** *ይህ ተደጋጋሚ ዘይቤ ነው፣* ስለ ሁሉን አቀፍነት (ዝከ. 7፡9፤ 11፡9፤ 13፡7፤ 14፡6)። እሱም የዳን. 3፡4፣7 ጠቃሽ ሊሆን ይችላል።

◘ **"በደምህም ለእግዚአብሔር ዋጅተሃ"** *ይህ* በርግጥ የእግዚአብሔር በግ ተለዋጭ ዋጀ ነው። ይህ የኢየሱስ እንደ *ኃጢአት መሥዋዕት* ጽንሰ-ሐሳብ በራዕይ ማዕከላዊ ሐሳብ ነው (ዝከ. 1፡5፤ 5፡9፣12፤ 7፡14፤ 12፡11፤ 13፡8፤ 14፡4፤ 15፡3፤ 19፡7፤ 21፡9፣23፤ 22፡3) እና ደግሞ በሁሉም አኪ (ማቴ. 20፡28፤ 26፡28፤ ማርቆስ 10፡45፤ ሮሜ. 3፡24-25፤ I ቆሮ. 6፡20፤ 7፡23፤ II ቆሮ. 5፡21፤ ገላ. 3፡13፤ 4፡5፤ ኤፌ. 1፡7፤ ፊሊ. 2፡8፤ I ጢሞ. 2፡6፤ ቲቶ 2፡14፤ ዕብ. 9፡28፤ እና I ጴጥ. 1፡18-10)።

## ልዩ ርዕስ፡ መዋጀት/መቤዠት

I. ብሉይ ኪዳን

ሀ. በቀዳሚነት ሁለት የዕብራይስጥ የሕግ ቃላት አሉ፣ ይሄንን ጽንሰ-ሐሳብ የሚገልጹ።

1. *ጋል Ga'al፣* እሱም በመሠረቱ "ነጻ ማውጣት" የሚል ፍቺ አለው፣ ዋጋ በመከፈል። ጎል የሚለው ቃል በቅርጹ ጽንሰ-ሐሳቡ ላይ ግላዊ ጣልቃ ገብነትን ይጨምራል፣ ዘወትር የቤተሰብ አባል (ማለትም፣ ተቤዢ ዘመድ)። ይህ ባህላዊ ገጽታ፣ ማለትም ዕቃዎችን፣ እንስሳትን፣ መሬትን መልሶ የመግዛት መብት (ሌዋውያን 25፣27)፣ ወይም ዘመዶችን (ሩት 4፡15፤ ኢሳ. 29፡22) ከሥነ መለኮት አኳያ የተሸጋገረው፣ የያህዌ እስራኤልን ከግብፅ መቤዠት ለማሳየት ነው (ዘጸ. 6፡6፤ 15፡13፤ መዝ. 74፡2፤ 77፣15፤ ኤር. 31፡11)። እሱም "ተቤዢ" ሆኗል (ኢዮብ 19፡25፤ መዝ. 19፡14፤ 78፡35፤ ምሳ. 23፡11፤ ኢሳ. 41፡14፤ 43፡14፤ 44፡6፣24፤ 47፡4፤ 48፡17፤ 49፡7፣26፤ 54፡5፣8፤ 59፡20፤ 60፡16፤ 63፡16፤ ኤር. 50፡34)።
2. *ፓዳህ Padah፣* እሱም በመሠረቱ ፍችው "መታደግ" ወይም "ማዳን" ነው
   ሀ. የበኩር ልጅ መቤዠት፣ ዘጸ. 13፡13፣14 እና ዘኁ. 18፡15-17
   ለ. ሥጋዊ መዋጀት ከመንፈሳዊ መዋጀት በተቃርኖ ነው፣ መዝ. 49፡7፣8፣15
   ሐ. ያህዌ እስራኤልን ከኃጢአታቸውና ከዐመጻቸው ይዋጃቸዋል፣ መዝ. 130፡7-8

ለ. ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቡ ሦስት ተያያዥ ነገሮችን ያካትታል።

1. ችግረኝነት፣ ባርነት፣ ኪሳራ፣ እስር ይኖራል።

ሀ. አካላዊ
ለ. ማኅበራዊ
ሐ. መንፈሳዊ (መዝ. 130፡8
2. ለነጻነት፣ ለመለቀቅ፣ እና ለመመለስ ዋጋ መከፈል ይኖርበታል።
ሀ. ለሕዝብ፣ እስራኤል (ዘዳ. 7፡8)
ለ. ለግለሰብ (ኢዮብ 19:25-27፤ 33:28)
3. አንዱ እንደ ጣልቃ ገቢ እና ረድኤት መሥራት አለበት። በጋል ይህ ዘወትር የሚሆነው በቤተሰብ አባል ወይም በቅርብ ዘመድ ነው (ማለትም ጎል)።
4. ያህዌ ዘወትር ራሱን የሚገልጸው በቤተሰባዊ ቃላት ነው።
ሀ. አባት
ለ. ባል
ሐ. የቅርብ ዘመድ ተቤዢ/ተበቃይ
መቤዠት የሚጸናው በያህዌ አካላዊ ወኪልነት በኩል ነው፤ ዋጋ ይከፈላል፣ እናም መቤዠቱ ይቀዳጃል!

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. ሥነ መለኮታዊውን ፅንሰ ሐሳብ ለመግለጽ በርካታ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል።
1. አጎራዞ *Agorazō* (1ኛ ቆሮ. 6:20፤ 7:23፤ II ጴጥ. 2:1፤ ራዕ. 5:9፤ 14:3-4) ይህ የንግድ ቃል ነው፣ እሱም ለአንድ ነገር የተመለከተውን ዋጋ የሚያንጸባርቅ። እኛ በደም የተገዛን ሕዝቦች ነን፣ የገዛ ራሳችንን ሕይወት መቆጣጠር የማንችል። የክርስቶስ ነን።
2. አክሳጎራዞ *Exagorazō* (ገላ. 3:13፤ 4:5፤ ኤፌ. 5:16፤ ቆላ. 4:5)። ይህም ደግሞ የንግድ ቃል ነው። እሱም የሚያንጸባርቀው
3. የኢየሱስን የምትክ ሞት ነው፣ በእኛ ፈንታ። ኢየሱስ እርግማንን ተሸከሟል፣ በሕግ ተግባር ላይ የተመሠረተውን (ማለትም፣ የሙሴ ሕግ፣ ኤፌ. 2:14-16፤ ቆላ. 2:14)፣ እሱንም ኃጢአተኞቹ የሰው ልጆች መፈጸም የማይችሉት። እሱ እርግማንን ተሸከመ (ዘዳ. 21፡23) ለሁላችንም (ማርቆስ 10:45፤ II ቆሮ. 5:21)! በኢየሱስ፣ የእግዚአብሔር ፍትሕና ፍቅር ወደ ሙሉ ምሕረት፣ ተቀባይነት፣ እና ቀረቤታ ይወጣል!
4. ሉ፣ *Luō* "ነጻ ማውጣት"
ሀ. ሉትሮን፣ *Lutron* "የተከፈለ ዋጋ" (ማቴ. 20፡28፤ ማርቆስ 10፡45)። እነዚህ ጠንካራ ቃላት ናቸው፣ ከኢየሱስ ከራሱ አንደበት የወጡ፣ የመምጣቱን ዓላማ በተመለከተ፣ የዓለም አዳኝ ለመሆን፣ የእሱ ያልሆነውን የኃጢአት ዕዳ ለመክፈል (ዮሐንስ 1፡29)።
ለ. ሉትሮ፣ *Lutroō* "መልቀቅ"
i. እስራኤልን መዋጀት፣ ሉቃስ 24፡21
ii. ሕዝቡን ለመዋጀትና ለማጥራት ራሱን ሰጠ፣ ቲቶ 2፡14
iii. ኃጢአት-የለሽ ምትክ መሆን፣ 1ኛ ጴጥ. 1፡18-19
ሐ. ሉትሮሲስ፣ *Lutr ōsis* "መቤዠት፣ ማዳን፣ ወይም ነጻ ማውጣት"
(1) የዘካርያስ ትንቢት፣ ስለ ኢየሱስ፣ ሉቃስ፣ 1፡68
(2) የሐና ለእግዚአብሔር ምስጋና፣ ስለ ኢየሱስ፣ ሉቃስ 2፡38
(3) የኢየሱስ የተሻለ፣ አንድ ጊዜ የቀረበ መሥዋዕት፣ ዕብ. 9፡12
5. አፖሊትሮሲስ *Apolytrōsis*
ሀ. መዋጀት በዳግም ምጽአቱ (ሐዋ. 3፡19-21)
(1) ሉቃስ 21፡28
(2) ሮሜ 8፡23
(3) ኤፌሶን 1፡14፤ 4፡30
(4) ዕብራውያን 9፡15
ለ. በክርስቶስ ሞት መቤዠት
(1) ሮሜ 3፡24
(2) 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30
(3) ኤፌሶን 1፡7
(4) ቆላስይስ 1፡14
6. አንቲሊትሮን *Antilytron* (1ኛ ጢሞ. 2፡6)። ይህ ወሳኝ የሆነ ጽሑፍ ነው (ቲቶ 2፡14 እንደሆነው)፣ መለቀቅን ከኢየሱስ የመስቀል ላይ ምትክ ሞት ጋር የሚያያይዘው። እሱ አንዱና ብቸኛ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ነው፤ ብቸኛው ስለ "ሁሉ" የሞተ (ዮሐንስ 1:29፤ 3:16-17፤ 4:42፤ I ጢሞ. 2:4፤ 4:10፤ ቲቶ 2:11፤ II ጴጥ. 3:9፤ I ዮሐንስ 2:2፤ 4:14)።

ለ. ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቡ በአዲስ ኪዳን የሚያመለክተው
1. የሰው ልጅ በኃጢአት ባርነት ተይዟል (ዮሐንስ 8፡34፤ ሮሜ. 3:10-18፤ 6:23)።
2. የሰው ልጅ የኃጢአት ባርነት በብሉይ የሙሴ ሕግ ተገልጧል (ገላትያ 3) እና በኢየሱስ የተራራው ስብከት (ማቴዎስ 5-7)። የሰዎች ድርጊት የሞት ፍርድ ሆነ (ቆላ. 2፡14)።

3. ኢየሱስ፣ ነውር የሌለው የእግዚአብሔር በግ፣ መጥቶ በእኛ ምትክ ሞተ (ዮሐንስ 1፡29፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)። ከኃጢአት የተገዛነው እግዚአብሔርን እንድናገለግል ነው (ሮሜ 6)።
4. በአንድምታ ያህዌም ሆነ ኢየሱስ "የቅርብ ዘመዶች" ናቸው፣ ለእኛ ብለው የሚሠሩ። ይህም ቤተሰባዊውን ዘይቤ ቀጣይ ያደርገዋል (ማለትም፣ አባት፣ ባል፣ ልጅ፣ ወንድም፣ የቅርብ ዘመድ)።
5. መቤዠት ለሰይጣን የተከፈለ ዋጋ አይደለም (ማለትም፣ መካከለኛው ሥነ-መለኮት)፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እና የእግዚአብሔር ፍትሕ ከእግዚአብሔር ፍቅርና ሙሉ ሰጭነት ጋር በክርስቶስ የታረቁበት ነው። በመስቀል ሰላም ተመልሷል፣ የሰዎች ዐመጸኝነት ይቅር ተብሏል፣ የእግዚአብሔር አምሳል በሰው ልጆች አሁን በመሥራት ላይ ይገኛል፣ በወዳጃዊ ኅብረት!
6. ወደፊትም ቢሆን የመቤዠት ገጽታ ይኖራል (ሮሜ. 8፡23፤ ኤፌ. 1፡14፤ 4፡30)፣ እሱም የእኛን የሥጋ ትንሣኤና አካላዊ ወዳጅነትን ከሥላሴ (አምላክ) ጋር ያካትታል። የተዋጀው አካላችን የእሱን ይመስላል (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)። እሱ አካል አለው፣ ነገር ግን ባለ ብዙ ኅብር ገጽታ። የ1ኛ ቆሮ. 15፡12-19 ከ 1 ቆሮ. 15፡35-59 ጋር ያለውን አያዎ (ፓራዶክስ) መግለጽ ያስቸግራል። ሥጋዊ፣ ምድራዊ አካል መኖሩ ግልጽ ነው፣ እንዲሁም፣ ሰማያዊ፣ መንፈሳዊ አካል ይኖራል። ኢየሱስ ሁለቱም አሉት!

**5፡10 *"መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው"*** ይህ የዘጸ. 19፡6 እና ኢሳ. 61፡6 ጠቃሽ ነው። ይህ ቃል አሁን ለቤተ-ክርስቲያን ነው ጥቅም ላይ የሚውለው፣ አዲሱ የታላቁ ተልእኮ ሕዝበ-እግዚአብሔር (ራዕ. 1፡6፤ 20፡6፤ 1 ጴጥ. 2፡5፣9)። 1፡6 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

⊡ **"በምድር ላይም ይነግሣሉ"** አንዳንድ ተርጓሚዎች ይሄንን የሚመለከቱት በመጻኢ መልኩ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ የሚመለከቱት በአሁን እውነታ ነው። የግሪክ ጸሑፎች ልዩነት አለ በትንቢት (መጻኢ) ጊዜ በMSS ℵ፣ P እና የአሁን ጊዜ በMS A (አሌክሳንድሪነስ)። እሱ በአሁን ጊዜ ከሆነ ከሮሜ. 5፡17 እና ኤፌ. 2፡6 ጋር ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከክርስቶስ ጋር ንግሥናው የወደፊት ጊዜ ከሆነ (ማቴ. 19፡28፤ ሉቃስ 22፡30፤ 1 ቆሮ. 4፡8፤ II ጢሞ. 2፡12፤ ራዕ. 3፡21፤ 5፡10)። ይህ የወደፊት ንግሥና እንኳ በሁለት መንገዶች ነው የሚታየው።

1. ራዕ. 20፡4 እና 6 ላይ እሱ የሚያመለክት የሚመስለው ሚሊኒየማዊ ንግሥና ነው
2. ራዕ. 22፡5 ላይ የሚያመለክት የሚመስለው ዘላለማዊ ንግሥና ነው (መዝ. 145፡13፤ ኢሳ. 9፡7፤ ዳን. 2፡44፤ 7፡14፣18፣27)
3. ሚሊኒየማዊው የዘላለማዊው ተምሳሌት ነው ሊሆን የሚችለው

ዩቢኤስ4 የሚሰጠው የትንቢት ጊዜ "ሀ" ደረጃ አለው (ርግጠኛ)።

## ልዩ ርዕስ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት መንገሥ

ከክርስቶስ ጋር የመንገሥ ጽንሰ-ሐሳብ "የእግዚአብሔር መንግሥት" የሚባለው ትልቅ ሥነ-መለኮታዊ ምድብ ክፍል ነው። ይህ በብኪ በኩል አልፎ የመጣ ነው፣ እግዚአብሔር እውነተኛው የእስራኤል ንጉሥ እንደሆነ (1 ሳሙ. 8፡7)። እሱ በተምሳሌታዊነት ነግሧል (1 ሳሙ. 8፡7፤ 10፡17-19)፣ ለትውልዶች ሁሉ ከይሁዳ ነገድ (ዘፍ. 49፡10) እና ከእሴይ ወገን (2 ሳሙኤል 7)።

ኢየሱስ መሲሕን በተመለከተ የብኪ ትንቢት የተስፋ ፍጻሜ ነው። እሱም የእግዚአብሔርን መንግሥት መርቋል በቤተ ልሔም ሥጋ በመልበሱ። የእግዚአብሔር መንግሥት፣ የኢየሱስ ስብከት ማዕከላዊው ዓምድ ነው። መንግሥቱ በእርሱ ፍጹም መጥቷል (ማቴ፡ 10፡7፤ 11፡12፤ 12፡28፤ ማርቆስ 1፡15፤ ሉቃስ 10፡9፣11፤ 11፡20፤ 16፡16፤ 17፡20-21)።
ሆኖም፣ መንግሥቱ ደግሞ የወደፊት ነው (የፍጻሜ ዘመን)። እሱ የአሁን ነው ግን አልተቀዳጀነውም (ማቴ. 6፡10፤ 8፡11፤ 16፡28፤ 22፡1-14፤ 26፡29፤ ሉቃስ 9፡27፤ 11፡2፤ 13፡29፤ 14፡10-24፤ 22፡16፣18)። ኢየሱስ በቅድሚያ የመጣው መከራን እንደሚቀበል አገልጋይ ሆኖ ነው (ኢሳ. 52፡13-53፡12)፤ እንደ ትሑት (ዘካ. 9፡9) ነገር ግን እንደ ነገሥታት ንጉሥ ይመለሳል (ማቴ. 2፡2፤ 21፡5፤ 27፡11-14)። የ"መንገሥ" ጽንሰ-ሐሳብ በርግጥ የ"መንግሥት" ሥነ-መለኮት ክፍል ነው። እግዚአብሔር መንግሥትን ለኢየሱስ ተከታዮች ሰጥቷል (ሉቃስ 12፡32 ተመልከት)።

ከክርስቶስ ጋር መንገሥ ጽንሰ-ሐሳብ በርካታ ገጽታዎችና ጥያቄዎች አሉት።

1. እግዚአብሔር ለአማኞች በክርስቶስ የሰጣቸውን "መንግሥት" የሚያስረግጡት ምንባቦች "መንገሥን" ያመለክታሉን (ማቴ. 5፡3፣10፤ ሉቃስ 12፡32)?
2. የኢየሱስ ቃላት ለዋነኞቹ ደቀ-መዛሙርት፣ በአንደኛው ክፍለ-ዘመን አይሁድ ዐውደ-ጽሑፍ፣ ሁሉንም አማኞች ያመለክታሉን (ማቴ. 19፡28፤ ሉቃስ 22፡28-30)?
3. የጳውሎስ አጽንዖት፣ አሁን በዚህ ዘመን ስለመንገሥ የሚለው ከላይኛው ጽሑፍ ጋር ይቃረናል ወይስ ተጨማሪ ነው (ሮሜ. 5፡17፤ 1 ቆሮ. 4፡8)?
4. መከራ መቀበልና መነገሥ እንዴት ይዛመዳሉ (ሮሜ. 8፡17፤ II ጢሞ. 2፡11-12፤ 1ጴጥ. 4፡13፤ ራዕ. 1፡9)?
5. የራዕይ ተደጋጋሚ ጭብጥ የክርስቶስን የከበረ መንግሥት መካፈል ነው፣ ያ ንግሥና ግን
   ሀ. ምድራዊ ነው፣ 5፡10
   ለ. ሚሊኒየማዊ፣ 20፡5፣6
   ሐ. ዘላለማዊ፣ 2፡26፤ 3፡21፤ 22፡5 እና ዳን. 7፡14፣18፣27?

**ራዕይ፡ 5፡11-14**

**[11]አየሁም፥ በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም እእላፋት ጊዜ**
**እእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር፥ [12]በታላቅም ድምፅ። የታረደው በግ ኃይልና ባለ ጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም**
**በረከትም ሊቀበል ይገባዋል አሉ። [13]በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ**
**ሁሉ። በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ። [14]አራቱም**
**እንስሶች። አሜን አሉ፥ ሽማግሌዎቹም ወድቀው ሰገዱ።**

**5፡11 "ብዙ መላእክት"** ይህ ቁጥር ባለ ሦስት ምድብ መላእክትን ይዘረዝራል፡ (1) ብዙ መላእክት (ሺህ ጊዜ ሺህ)፤ (2) እንስሶች (አራት)፤ ወይም (3) ሽማግሌዎች (ሃያ አራት)።

⊡ **"ቍጥራቸውም እእላፋት ጊዜ እእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር፥"** ይህ የሰማያዊው ችሎት፣ ዳን. 7፡10 ላይ ያለው ጠቃሽ ይመስላል። (5፡1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

**5፡12 "የታረደው በግ፣ ኃይል ሊቀበል"** ይህ የወልድ ማረጋገጫ ነው፣ ከመላእክት ሕላዌዎች። "የታረደው" የተጠናቀቀ ተገብሮ አንቀጽ ነው (ዝኪ. 5፡6፤ 13፡8)፣ አንድምታውም "ባለፈው የታረደ"፣ በመታረዱም ምልክቶችና ተጽዕኖዎች ያሉት ነው። ኢየሱስን ስንመለከተው፣ አሁንም ገና የስቅላቱ ምልክቶች አሉት። እነርሱም የክብር ምልክቶች ሆነውታል! ራዕይ ላይ የመስቀሉ ጽንሰ-ሐሳብ አካታችና ማዕከላዊ ነው። 5፡9 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

በዚህ ቁጥር ላይ ለበጉ ሰባት አስተዋጽዖዎች ተሰጥተዋል፣ በመላእክት ተራ፡

1. ኃይል
2. ብልጽግና
3. ጥበብ
4. ኃይል
5. ክብር
6. ገናናነት
7. ባርኮት

እነዚህ አስተዋጽዖዎች የመጡት ከ1 ዜና. 29፡10-12 ይሆናል፣ እሱም ደግሞ የብኪ. የጋራ አምልኮ ማጠቃለያ ምንጭ ይሆናል፣ የጌታ ጸሎት ማቴ. 6፡13 ላይ፣ በግሪክ የእጅ ጽሑፍ ደንብ መሠረት።

አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1855) ማስታወሻ ያክላል፣ የእግዚአብሔር አስተዋጽዖ በሦስት እንደሚጀምር 4፡11 ላይ፣ ከዚያም አራት 5፡13 ላይ፣ እና በመጨረሻ ሰባት 5፡12 እና 7፡12 ላይ። አፖካሎፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ እጅግ መዋቅራዊ ዘውግ እንደሆነ አስታውስ፣ ተምሳሌታዊ ቁጥሮችንም አዘውትሮ የሚጠቀም።

**5፡13** የሚያስብ ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ (ትልቁ የሰው የኅብረ-ዝማሬ ቡድን ሊሆን የሚችል)፣ ሰዎች (በሕይወት ያሉ እና የሞቱ) ቁ. 13 ላይ አብንና ወልድን ይባርካሉ፣ በአራትዮሽ ባርኮት (ዝኪ. ቁ. 14፤ መዝ. 103፡19-20፤ ፊሊ. 2፡8-11) እና የመላእክት ምድቦች (አራቱ እንስሶች እና ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች) ዙፋኑን ከበው ባርኮቱን ያጸናሉ (ዝኪ. ቁ. 14)።

**5፡14 "አሜን"** ይህ ከአራቱ ዙፋናዊ መላእክት ማረጋገጫ ነው (አራቱ እንስሳት)። ልዩ ርዕስ 1፡6 ላይ ተመልከት

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ምዕራፍ 4 እና 5 ከመጽሐፉ አጠቃላይ ጭብጥ ጋር እንዴት ይገጥማሉ?
2. የምዕራፍ 4 እና 5 ጽሑፋዊ ዘውግ ምንድነው?
3. ይሄንን ምስል ዮሐንስ ከየትኛው ምንጭ ወሰደው?
4. ሽማግሌዎቹ እነማን ናቸው?
5. እንስሳቱ 4፡7-10 ላይ ኪሩቤል ወይም ሱራፌል በሚል ተገልጸዋል?
6. ምዕራፍ 5 ላይ የሚገኙትን የመሲሑን የብኪ. መጠሪያዎች ዘርዝር።
7. 5፡9 እና 10 ላይ የሚገኘውን መሲሑ የሚገባው መሆኑን የሚጠቅሰውን አምስቶሽ ገለጻ ዘርዝር።

# ራዕይ 6፡ 1-7፡17
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ4 | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ማኅተሞች | አንደኛው ማኅተም፡ ድል አድራጊ | የመጀመሪያዎቹ ስድስት ማኅተሞች አከፋፈት | ማኅተሞች | በጉ ሰባቱን ማኅተሞች ፈታ |
| 6:1-2 | 6:1-2<br>ሁለተኛው ማኅተም፡ በምድር ላይ ውጊያ | 6:1-2 | 6:1-2 | 6:1-2 |
| 6:3-4 | 6:3-4<br>ሦስተኛው ማኅተም፡ እጥረት በምድር ላይ | 6:3-4 | 6:3-4 | 6:3-4 |
| 6:5-6 | 6:5-6<br>አራተኛው ማኅተም፡ በምድር የተስፋፋ ሞት | 6:5-6 | 6:5-6 | 6:5-6 |
| 6:7-8 | 6:7-8<br>አምስተኛው ማኅተም፡ የተሠዉት ጩኸት | 6:7-8 | 6:7-8 | 6:7-8 |
| 6:9-11 | 6:9-11<br>ስድስተኛው ማኅተም፡ የሰማይ ኃይላት ነውጥ | 6:9-11 | 6:9-11 | 6:9-11 |
| 6:12-17 | 6:12-17 | 6:12-17 | 6:12-17 | 6:12-17 |
| 144,000 ከእስራኤል የታተሙ<br>7:1-8<br>ከእያንዳንዱ ሕዝብ ብዛት<br>7:9-12<br>7:13-17 | ከእስራኤል የታተሙ<br>7:1-8<br>ከታላቁ መከራ የመጡ ብዙዎች<br>7:9-17 | ጣልቃ የገባ<br>7:1-8<br>7:9-12<br>7:13-17 | 144,000 የእስራኤል ሕዝብ<br>7:1-8<br>ብዙ ሕዝብ<br>7:9-12<br>7:13<br>7:14ሀ<br>7:14ለ-17 | የእግዚአብሔር ባሪያዎች ይጠበቃሉ<br>7:1-8<br>የቅዱሳን መሸለም<br>7:9-12<br>7:13-17 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ vii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

**ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት**

ሀ. ይህ ክፍል ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ከምዕራፍ 4 እና 5 ጋር ይዛመዳል። ምዕራፍ 4 እና 5 በሰማይ ያለ ሁነትን ሲገልጹ፣ 6፡1-8፡1 ደግሞ የማይታጠፈውን የእግዚአብሔርን ፍርድ በምድር ላይ ያሳያል። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ 4:1-16:21 አንድ ጽሑፋዊ ምድብ ይፈጥራሉ።

ለ. የመጀመሪያው ጋላቢ ማንነት (ዝከ. ቁ. 2) አስቸጋሪ ነው፣ ግን ሲገመት የክፉው ተምሳሌት ነው፣ አራቱ ፈረሰኞች፣ አማኞች የሚጋፈጧቸው ስደቶች ተምሳሌት ናቸው፣ በወደቀው፣ ባለጋራ ዓለም (ማቴ. 24፡6-7)። "መከራ" የሚለው ቃል (*thlipsis*) በቋሚነትና በግልጽ ጥቅም ላይ የሚውለው ስለ ክርስቲያኖች መከራ ነው፣ በማያምኑት።

ስድስተኛው ማኅተም ቁ. 12 ላይ የሚጀምረው የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ቁጣ በማያምኑት ላይ ነው። አማኞች ከእግዚአብሔር ቁጣ ተጠብቀዋል (*orgē*፣ ዝከ. ቁ. 16)፣ ነገር ግን ስደትና ቁጣ ከማያምነው ዓለም ይጠብቃቸዋል።

ሐ. በዚህ ክፍል ሦስት ዋነኛ የትርጓሜ ችግሮች ይገኛሉ።

1. ማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ እርስ በርሳቸው በታሪክ እንዴት ይዛመዳሉ
2. 7፡4 ላይ ያሉት 144000ዎች እነማን ናቸው፣ 7፡9 ላይ ካሉት ከሁለተኛቹ ምድቦች ጋር እንዴት ይዛመዳሉ
3. 7፡14 ላይ የተጠቀሰው ምድብ የትኛው የመከራው ጊዜ ነው እንዴትስ ያለ መከራ

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

**ራዕይ፡ 6፡1-2**

**[1]በጉም ከሰባቱ ማኅተም አንዱን በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ከአራቱም እንስሶች አንዱ ነጐድጓድ በሚመስል ድምፅ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ። [2]አየሁም፥ እነሆም፥ አምባላይ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ቀስት ነበረው፥ አክሊልም ተሰጠው፥ ድልም እየነሣ ወጣ ድል ለመንሣት።**

**6፡1 "በጉም ከሰባቱ ማኅተም አንዱን በፈታ ጊዜ"** ይህ ቁጥር የሚያሳየው በምዕራፍ 5 እና 6 መካከል ያለውን ግንኙነት ነው። እነዚህ ማኅተሞች የሚፈቱት መጽሐፉ ከመነበቡ በፊት ነው፣ እጅግ በርካታ ተርጓሚዎች የሚገምቱት እነርሱ በየዘመናቱ የሚከሰቱትን ችግሮች የሚወክሉ ናቸው (ማቴ. 24፡6-12)። ሆኖም፣ እየከፋ በሚመጣው የተጠናከረ ፍርድ ምክንያት፣ እነዚህ ለዘመናት ፍጻሜ ወዲያውኑ የሚያዘጋጁ ናቸው። በመንግሥቱ የአሁንነትና የወደፊትነት መካከል ያለው ተቃርኖ እዚህ ነው። በአኪ መዋለል አለ፣ "በገና ድሮ" እና "በገና" መካከል። የራዕይ መጽሐፍ ራሱ ይሄንን ተቃርኖ ያሳያል። እሱ የተጻፈው ለአንደኛው ክፍለ-ዘመን ተሳዳጅ ክርስቲያኖች ነው (እና በየዘመናቱ) እንዲሁም ከትንቢት አኳያ የመጨረሻውን የአማኞች ትውልድንም ይመለከታል። መከራዎች በየዘመናቱ የተለመዱ ናቸው!

ሰባተኛው ማኅተም ሰባቱ መለከቶች ነው፣ እንዲሁም ሰባተኛው መለከት ሰባቱ ጽዋዎች ነው። እንደተመዘገበው፣ እያንዳንዱ የተጠናከረ ነው፣ ከፊተኛው ይልቅ። ቀዳሚዎቹ ሁለቱ፣ በዓላማቸው የሚቤጁ ናቸው። እነርሱ በመሠረቱ የሚያሳዩት የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ መሆኑን ነው፣ ምክንያቱም የማያምኑት ንስሐ ስላልገቡ፣ ስለዚህ የመጨረሻው ዑደት (ማለትም፣ ጽዋዎች) ለንስሐ ዕድል የላቸውም፣ ፍርድ ብቻ! ለእኔ የሚመስለኝ ግን ሰባተኛው ማኅተም እና ሰባተኛው መለከት የዘመኑን ፍጻሜ ይገልጻሉ። ስለዚህ፣ እነዚህ በአፈጣጠራቸው በአንድ ጊዜ የሚሆኑ ናቸው፣ በቅደም ተከተል ተለጣጣቂ ሳይሆኑ።

አንዱ ዳግም ምጽአት ሦስት ጊዜ ተገልጿል፣ ከማኅተሞቹ መጨረሻ (ዝከ. 6:12-17) እና መለከቶች (ዝከ. 11:15-18)፣ እናም ልክ ከጽዋዎቹ መጨረሻ ሳይሆን 16፡17-21 እና በድጋሚም ምዕራፍ 19፡11-21።ይህ የመጽሐፉ መዋቅራዊ ፈርጅ ነው። እሱም አፖካሊፕቲካዊ ድራማ ነው፣ በበርካታ ድርጊቶች! የራዕይ መግቢያ ሐ ተመልከት።

▣ **"ከአራቱም እንስሶች አንዱ ነጎድጓድ በሚመስል ድምጽ አለ"** አራቱ እንስሶች፣ እንደ ሽማግሌዎቹ፣ የመልአካዊ ፍጥረት ደረጃዎች ናቸው። ይህ ድምጽ፣ እንደ ነጎድጓድ፣ 14፡2 እና 19፡6 ላይ ተጠቅሷል።

▣ **"'ና'"** ይህ ቃል ፍችው  አንድም "ና" ወይም "ወደፊት ሂድ" ማለት ነው። የጥንታዊው ግሪክ ክብ ትልቁ ፊደል ጽሑፍ ሲናይቲከስ (א) "ተመልከትም" የሚል ይጨምራል (ኪጀት፣ አኪጀት፣ እሱም ዮሐንስን ይጠቅሳል)፣ አሌክሳንድሪነስ ግን (ሀ) "ና" ብቻ ነው ያለው (እሱም አራቱን ፈረሶች የሚጠቅስ)። ዩቢኤስ[4] ትንሹን "ለ" ይመርጣል፣ ደረጃውም (ከሞላ ጎደል ርግጠኛ)። በዐውደ-ጽሑፍ ይህ ትእዛዝ (የአሁን ተተኳሪ) ዮሐንስን ወይም ቤተ-ክርስቲያንን አይጠቅስም፣ ወደ አራቱ ፈረሰኞች እንጂ (ዝከ. 6፡3፣5፣7)።

**6፡2 "አየሁም፣ እነሆም ነጭ ፈረስ"** ይህ ዐውደ-ጽሑፍ ለዘካ. 1፡8 ጠቃሽ ነው (አራቱ ፈረሶች) እና 6፡1-8 (አራቱ ሠረገላዎች)።  ስለ እነዚህ ፈረሰኞች ማንነት በርካታ ውይይት ተደርጓል። የትርጓሜዎቹ ደረጃ ከኢየሱስ አንሥቶ (ኢሪናዩስ) እስከ ክርስቶስ ተቃዋሚ ይደርሳል። በዛ ዓይነቱ ውኸንብር፣ ቀኖናዊነት ተገቢ አይደለም። አንዳንዶች የሚያምኑት፣ የሚጠቅሰው ክርስቶስን ነው በሚል ነው፣ 19፡11-21 በሚገኘው ተመሳሳይ ገለጻ ምክንያት፣ ብቸኛው ተመሳስሎ የሚመስለው ግን የፈረሱ ቀለም ነው። ሌሎች የሚመለከቱት ይህ የሚጠቅሰው ወንጌልን ስለማሰራጨት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት እነሱ ያዩት እነዚህ ምዕራፎች የኦሊቬት ንግግር ከሆነው ማቴ. 24፡ ማርቆስ 13፣ እና ሉቃስ 21 ትይዩ በመሆናቸው ነው። ስለዚህ፣ ይህ ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው የማቴዎስ 24፡14 እና ማርቆስ 13፡10 ጠቃሽ ነው።

እንዲያውም የሚባለው፣ ሕዝቅኤል 39 ላይ በመመሥረት፣ ይህ የሚያመለክተው ጎግን ነው፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሠራዊቱን እየመራ። ይህም ተምሳሌትነቱ የመጨረሻውን ዘመን የክርስቶስን ተቃዋሚ ነው (2 ተሰሎንቄ 2)። እሱም እጅግ ያልተለመደ ይመስላል፣ መልአክ ኢየሱስን እንዲመጣ ሲያዘው። ምንም እንኳ ኢየሱስ ምዕራፍ 6 እና 19 ላይ አክሊል ቢጭንም፣ እነዚህን አክሊሎች ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉት የግሪክ ቃላት የተለዩ ናቸው። እዚያ፣ ኢየሱስ፣ "የታመነና እውነተኛ" ተብሏል፣ እዚህ ግን የለም። የፈረሰኛው ድል አድራጊነት ፈጽሞ አልተጠቀሰም። ፈረሰኛው የተጠቀሰው ቀስት እንደያዘ ነው፣ ምዕራፍ 6 ላይ፣ ምዕራፍ 19 ላይ ክርስቶስ በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ በአፉ ላይ አለ፣ ስለዚህ ተመሳሳይነቱ የልዩነቶች ጥላ አጥልቶበታል። ይህ ምናልባት ከብኪ መቅሠፍቶች አንደኛው ነው። እነዚህ መቅሠፍቶች፣ እነርሱም የሌዋውያን 26 እና ሕዝ. 14፡21 ጠቃሾች ቁ. 8 ላይ ይታያሉ። ነጭ የጽድቅ ቀለማዊ ተምሳሌት ብቻ አይደለም፣ ግን ደግሞ ለወታደራዊ ድል የሮማ ተምሳሌት ነው። የሮሜ ጀነራሎች በውጊያ ላይ ድል ያደረጉ በሠረገላ ላይ ሆነው በሮም አደባባይ ይዞራሉ፣ በአራት ነጫጭ ፈረሶች እየተሳቡ።

▣ **"በእሱም ላይ የተቀመጠው ቀስት አለው"** ቀስት ተመራጭ መሣርያ ነበር፣ ለፓርቲያን ሆርደስ ቀስተኞች (በነጭ ፈረሶች ላይ የሚጋልቡ)። ቀሰት ዘወትር በብኪ ጥቅም ላይ የሚውለው ያህዌን እንደ ተዋጊ ለመግለጽ ነው (መዝ. 45:4-5፤ ኢሳ. 41:2፤ 49:2-3፤ ዕን. 3:9፤ ዘካ. 9:13 እና ዘፍ. 9:13)። ደግሞም የያህዌ ምሳሌዎች አሉ፣ በሌሎች ሕዝቦች ላይ ሲፈርድ፣ በዘይቤ መልኩ ቀስታቸውን በመስበር (መዝ. 46:9፤ ኤር. 51:56 እና ሆሴዕ 1:5)።

▣ **"አክሊልም ተሰጠው"** ይህ የ"*stephanos*" አክሊል ነው፣ ፍችውም የድል አድራጊ አክሊል፣ 19፡11 ላይ የተጠቀሰው ደግሞ የክርስቶስ ደግሞ "*diadema*፣" ንጉሣዊ አክሊል ነው።

▣ **"ድል እየነሣ ወጣ፣ ድል ለመንሣት"** ቁ. 1 ላይ ያሉት ተምሳሌቶች ጦርነትና ድል አድራጊነት ነው። የመጀመሪያውና ሁለተኛው ፈረሰኞች በተመሳሳይ ዓላማ በመጠቀሳቸው ምክንያት፣ አንዳንዶች ይሄንን የመጀመሪያውን የሚመለከቱት ድል እንደማድረግ ጦርነት ነው፣ ሁለተኛውን ደግሞ እንደ እርስ በርስ ጦርነት። ይህ ግምታዊ ነው፣ ነገር ግን ሁለቱ ፈረሶች ትይዩ ናቸው።

> *ራዕይ፡ 6:3-4*
>
> **[3]*ሁለተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ሁለተኛው እንስሳ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ።* [4]*ሌላም ዳማ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ ለተቀመጠው ሰላምን ከምድር ይወስድ ዘንድ ሰዎችም እርስ በርሳቸው እንዲተራረዱ ሥልጣን ተሰጠው፥ ታላቅም ሰይፍ ተሰጠው።***

**6፡4 "*ሌላም፣ ዳማ ፈረስ*"** ይህ ሌላው የወታደራዊ ግድያ ጠቃሽ ነው።

▣ **"*ታላቅም ሰይፍ ተሰጠው*"** ይህ አነስተኛ የሮሜ ሰይፍ ነው፣ "*machaira*" የሚባል። የሚገነደረውም በሮሜ ወታደር መታጠቂያ ላይ ነው፤ ለሮሜ ዜጎች የሞት ፍርድ ማስፈጸሚያ ይሆናል (ሮሜ. 13፡4)። "ሰዎችም እርስ በርሳቸው ይተራረዱ ዘንድ" የሚለው ሐረግ አስገራሚ ነው፣ ምክንያቱም በብኪ ይህ አንደኛው መንገድ ነው፣ ያህዌ የእሱን ሕዝብ ጠላቶች ለማሸነፍ ከሚጠቀምበት (መሳ. 7:22፤ I ሳሙ. 14:20፤ II ዜና. 20:22)።

> *ራዕይ፡ 6:5-6*
>
> **[5]*ሦስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ሦስተኛው እንስሳ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ። አየሁም፥ እነሆም፥ ጉራቻ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው በእጁ ሚዛን ያዘ።* [6]*በአራቱም እንስሶች መካከል ድምፅ። አንድ እርቦ ስንዴ በዲናር ሦስት እርቦ ገብስም በዲናር፥ ዘይትንና ወይንንም አትጒዳ ሲል ሰማሁ።***

**6፡5 "አየሁም፣ እነሆም ጉራቻ ፈረስ"** ይህ የራብ ምልክት ነው (ማቴ. 24፡7) ጦርነትን የሚከተል።

**6፡6 "አንድ እርቦ ስንዴ በዲናር"** ዲናር የቀን ዋጋ ነበር፣ ለወታደር ወይም ለሠራተኛ (ማቴ. 20፡2)። ከሔሮዱቱስ እንደምንማረው ይህ ለአንድ ሰው ለአንድ ቀን የሚበቃውን ምግብ መግዛት ይችላል። ይህም የራቡን አስከፊነት ያሳያል፡ አንድ ሰው ሙሉ ቀን ሠርቶ በቂ ምግብ ብቻ ለራሱ ያገኛል።

## ልዩ ርዕስ፡ በፍልስጥኤም በኢየሱስ ጊዜ ጥጭቅም ላይ የነበሩ ሳንቲሞች

I. የመዳብ ሳንቲሞች
- ሀ. *cherma* – ትንሽ ዋጋ (ዮሐንስ 2:15)
- ለ. *chalchos* – ትንሽ ዋጋ (ማቴ. 10:9፤ ማርቆስ 12:41)
- ሐ. *assarion* – የሮሜ የመዳብ ሳንቲም የዲናር 1/16 ዋጋ ያለው (ማቴ. 10:29)
- መ. *kodrantes* – የሮሜ የመዳብ ሳንቲም የዲናር 1/64 ዋጋ ያለው (ማቴ. 5:26)
- ሠ. *lepton* – የአይሁድ የመዳብ ሳንቲም የዲናር 1/128 ዋጋ ያለው (ማርቆስ 12:42፤ ሉቃስ 21:2)
- ረ. *quadrans/farthing* – የሮሜ የመዳብ ሳንቲም ትንሽ ዋጋ ያለው

II. የብር ሳንቲሞች
- ሀ. *arguros* ("የብር ሳንቲም") – ከመዳብ ወይም ከናስ ሳንቲሞች እጅግ ዋጋ ያለው (ማቴ. 10:9፤ 26:15)
- ለ. *dēnarius* – የሮሜ የብር ሳንቲም ለቀን ሥራ የሚከፈል (ማቴ. 18:28፤ ማርቆስ 6:37)

ሐ. *drachmē* – የግሪክ የብር ሳንቲም ከዲናር ዋጋ ጋር እኩል የሆነ (ሉቃስ 15:9)
መ. *di-drachmon* – እጥፉ *drachmas* ከአይሁድ ½ ሼክል ጋር እኩል ነው (ማቴ. 17:24)
ሠ. *statēr* – የብር ሳንቲም አራት ዲናር ያህል ዋጋ ያለው (ማቴ. 17:27)
III. የወርቅ ሳንቲሞች – *chrusos* ("የወርቅ ሳንቲሞች") – እጅግ ዋጋ ያላቸው ሳንቲሞች (ማቴ. 10:9)
IV. የክብደቶችና የብረቶች አጠቃላይ ቃላት
ሀ. *mnaa* – በላቲን *mina*፣ የክብደት መመዘኛ ብረት ከ100 *dēnarii* ጋር እኩል የሆነ (ሉቃስ 19:13)
ለ. *talanton* – የግሪክ የክብደት መመዘኛ (ማቴ. 18:24፤ 25:15፣16፣20፣24፣25፣28)
1. ብር 6፣000 *ዲናር ዋጋ አለው*
2. ወርቅ 180,000 *ዲናር ዋጋ አለው*
ሐ. *sheqel* – የአይሁድ የብኪ የብር *መመዘኛ* (ዘፍ. 23:15፤ 37:28፤ ዘጸ. 21:32)
1. *pΠm* – 2/3 ሰቅል
2. *beka* – ½ ሰቅል
3. *gerah* – 1/20 ሰቅል
ትልልቅ *መመዘኛዎች*
1. *maneh* – 50 ሰቅል
2. *kikkar* – 3,000 ሰቅል

▣ **"ሦስት እርቦ ገብስም በዲናር"** ገብስ ዋነኛ የደሀ ምግብ ነበር። የግሪኩ ቃል "quarts"፣ *"choinix* ነው፣ ከ1.92 pint (ኳርት) ጋር እኩል ነው።

▣ ***"ዘይትንና ወይንንም አትጉዳ"*** ይህን በተመለከተ ምን ያህል ትርጉሞች እንዳሉ የሚገርም ነው። ብዙዎች ብዙዎች ተመልሰው ወደ ቤተ-መቅደሱ ጥቅል ወደ ሙት ባሕር ጥቅሎች ለመሄድ ይሞክራሉ፣ አንዳንድ የአይሁድን *መሥዋዕት* ጠቃሽ ለመፈለግ። ዘይትና ወይን የሜዲትራኒያን ሕዝቦች ዋነኛ ምግብ ነበሩ። እነዚህ እንዳይጎዱ የሚለው ሐቅ የሚያሳየው ወሰን ያለው ራብን ነው። ይኸው ውስንነት ቁ. 8 ላይ ደግሞ ይታያል። እግዚአብሔር ፍርዱን ወሰን ያደርግለታል፣ የማያምኑት ንስሐ እንዲገቡ ጊዜ ለመስጠት (ዝከ. 16፡9)። ደግሞም እነዚህ ሁለቱ ለሕክምና አገልግሎት ይውሉ እንደነበር ማየት ይቻላል።

***ራዕይ፡ 6፡7-8***

**[7]*አራተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ የአራተኛው እንስሳ ድምፅ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ።* [8]*አየሁም፥ እነሆም፥ ሐመር ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ነበረ። ሲኦልም ተከተለው፤ በሰይፍና በራብም በሞትም በምድርም አራዊት ይገድሉ ዘንድ ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው።***

**6፡8**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"ሐመር ፈረስ"*** |
| **አኪጀት** | ***"የገረጣ ፈረስ"*** |
| **አየተመት** | ***"የገረጣ ሣርማ ፈረስ"*** |
| **አእት** | ***"የገረጣ ቀለም ያለው ፈረስ"*** |
| **አኢመቅ** | ***"ሙት የሚመስል ፈረስ"*** |

"የገረጣ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቢጫ-አረንጓዴ ወይም የገረጣ ነጭ ቀለምን ነው። በእንግሊዝኛ "ክሎሪን" የሚለውን ቃል ያገኘነው ከዚህ የግሪክ ቃል ነው። እሱም ሊሆን የሚችለው የሙት አካል ቀለም ነው። ሞት ማለት እንደሆነ ቁ. 8 ላይ በመጠቀሱ ምክንያት፣ ይህ የሚያመለክተው በዱር አራዊት የተገደሉትን ወይም የተበሉትን ነው፣ እሱም ከአኪ ርግማኖች አንዱ የሆነ (ሌዋ. 26:22፤ ኤር. 15:3፤ ሕዝ. 5:17፤ 14:21)።

▣ **"በእሱ ላይ የተቀመጠውም ስሙ ሞት ነው፤ ሲኦልም ተከተለው"** ይህ የብኪ ጠቃሽ ነው ምሳ. 5:5 ወይም ሆሴዕ 13:14። እሱም የሰውኛነት ቃላት ነው፣ ለሥጋዊ ሕይወት ማብቃት። እነዚህ ሁለት ቃላት አብረው ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ራዕይ ላይ (ዝከ. 1:18፤ 20:13-14)።

"*Hades*" የሚለው ቃል ለብኪ ቃል "*Sheol*" ተመሳሳይ ነው፣ ፍችውም "የሙታን ማቆያ ስፍራ" የሆነ። ልዩ ርዕስ፡ ሙታን የት ናቸው? 1:18 ላይ ተመልከት።

▣ **"ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው"** "እነርሱ" የሚለውን ተውላጠ ስም ተገንዘብ፣ ሁሉንም አራቱንም ፈረሶችና የተቀመጡባቸውን የሚመለከት ነው። በመለከቶቹ ላይ እየተጠናከረ የመጣ ፍርድ አለ (ማለትም፣ አንድ ሦስተኛ፣ ዝከ. 8:7፣8፣10፣ 12)፤ በጽዋዎቹ ፍጹም የሆነ ጥፋት አለ (ዝከ. 16:1-21)። እነዚህ ክፍልፋዮች ጽሑፋዊ ዘዴዎች ሲሆኑ፣ የሚያሳዩትም የእግዚአብሔር ፍርዶች የመቤዠት ዓላማ እንዳለው ነው (ዝከ. 9:20-21፤ 14:7፤ 16:9፣11)፣ ነገር ግን የወደቀው፣ ዐመጸኛው፣ የደነደነው የሰው ልጅ ምላሽ አልሰጠም (ምንም እንኳ ጥቂቶች ቢኖራቸውም፣ ዝከ. 11:13)።

▣ **"ለመግደል"** እነዚህ አራት ፈረሰኞች የብኪን ኪዳን ፍርዶች ይወክላሉ (ሌዋ. 26:21-26፤ ኤር. 15:2-3፤ 24:10፤ 27:8፤ 29:17-18፤ 32:24፣36፤ 34:17፤ ሕዝ. 5:12፣17፤ 14:21፤ ዐሞጽ 4:6-10)። "ሰይፍ" የሚለው ቃል ከቁ. 4 የተለየ ነው። ይህ የሚያመለክተው ረጅሙን የውጊያ ሰይፍ ነው፣ *hromphaia*። አራቱ ሁሉ የብኪ ፍርዶች ጦርነት፣ ራብ፣ መቅሠፍት እና የዱር አውሬዎች ሌዋ. 26:21-26 እና ሕዝ. 14:21 ላይ ተዘርዝረዋል። እነዚህ የኪዳን ፍርዶች ዘዳግም 27-29 ላይ በግልጽ ተብራርተዋል። ከመነሻ ዓላማቸው እስራኤል ንስሐ እንዲገባና ወደ ያህዌ እንዲመለስ ማድረግ እንደነበር አስታውስ። እዚህም በተመሳሳይ የመቤዠት መልክ ጥቅም ላይ ውለዋል (ዝከ. 9:20-21፤ 11:13፤ 14:7፤ 16:9፣11)።

**ራዕይ፡ 6፡9-11**

**[9]አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ። [10]በታላቅ ድምፅም እየጮኹ። ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ። [11]ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው።**

**6፡9 "ከመሠዊያ በታች አየሁ"** ይህ የትኛው መሠዊያ እንደሆነ ብዙ ውይይት ተካሂዷል። "መሠዊያ" የሚለው ቃል በራዕይ ላይ እጅግ ተዘውትሮ ጥቅም ላይ ውሏል (ዝከ. 8:3፣5፤ 9:13፤ 11:1፤ 14:18፤ 16:7)። አንዳንዶች የሚያምኑት ይህ የሚያመለክተው ሌዋ. 4:7 እና በጳውሎስ ፊሊ. 2:17 ላይ የተጠቀሰው ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ የሚያምኑት በመቅደሱ በቅዱስ ስፍራ ያለ የዕጣን መሠዊያ ነው ይላሉ (ዝከ. 8:3-5) ወይም የራዕ. 11:1 መቅደስ። እሱ ምናልባት የመሥዋዕት መሠዊያ ይሆናል፣ ምክንያቱም

1. ራቢዎች ይህንን የሚመለከቱት ታላቅ ክብር እንዳለው ስፍራ ነው
2. እሱም የሚያመለክተው ሞትን ነው (ማለትም፣ ደም) ሠማዕታት

አንዱ ሊጠይቅ ይችላል፣ "ሠማዕታት ከመሠዊያው በታች ለምን ይሰበሰባሉ?" በብኪ ደም የሕይወት ተምሳሌት እንደነበረ አስታውሱ (ዘፍ. 9:4፤ ሌዋ. 17:11፣14)። በእስራኤል መሥዋዕታዊ ሥርዓት ደሙ በመሥዋዕት ማቅረሚያው መሠዊያ ቀንድ ውስጥ አይቀመጥም ነበር፣ ግን ከሥር ይፈስሳል (ዘጸ. 29:12፤ ሌዋ. 4:7፣18፣25፤ 8:15፤ 9:9)። ስለዚህ፣ ሕይወት (ማለትም፣ ነፍሳት) የታረዱት ሰማዕታት ከመሠዊያው ሥር ነው።

▣ **"የታረዱትን ነፍሳት"** እነዚህ ነፍሳት፣ ከሥጋ የተለዩ ነፍሶች ናቸው (በሞትና በትንሣኤ መካከል) የተሠዉ አማኞች (ዝከ. 13:15፤ 18:24፤ 20:4)። ይህ የሚያስገርም ነው፣ ምክንያቱም እሱ የግሪክ አስተሳሰብ ነው፣ ከዕብራውያን ጽንሰ-ሐሳብ ይልቅ። ሁሉም ክርስቲያኖች ለመሥዋዕትነት ተጠርተዋል፣ ሁኔታው ከጠየቀ (ዝከ. 2:10፣13፤ ማቴ. 10:38-39፤ 16:24)።

በእነዚያ በአራቱ ፈረሰኞች በተገደሉት 6:1-8 እና በእነዚህ ሰማዕታት መካከል ምንም ግንኙነት የለም!

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ እና ከምስክርነታቸው የተነሣ"** |
| **አኪጀት** | **"ስለ እግዚአብሔር ቃል እና ስለ ምስክርነታቸው"** |
| **አየተመት** | **"ስለ እግዚአብሔር ቃል እና ስለ አደረጉት ምስክርነት"** |
| **አእት** | **"የእግዚአብሔርን ቃል በማወጃቸውና በምስክርነታቸው ታማኝ በመሆናቸው"** |
| **አኢመቅ** | **"ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ፣ እሱን በመመስከራቸው"** |

ይህ ሐረግ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ በራዕይ (ዝከ. 1:9፤ 12:11፣17፤ 19:10፤ 20:4)። እሱም በትርጉም እጅግ ተመሳሳይ ነው "ድል ለሚነሣ" ከሚለው ሐረግ ጋር (ዝከ. 2:6፣11፣17፣26፤ 3:5፣12፣21)።

**6፡10 "እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም፣ ደማችንንስ... አትበቀልም"** በርካታ አታቾች ይሄንን የሚመለከቱት ንፍቀ-ክርስቲያን እንደመሆን ነው። ይህ የሆነው ምናልባት እነዚህ አታቾች ራሳቸው በማያምኑት በከፋ ስደት ውስጥ ፈጽሞ ባለማለፋቸው ነው። እነዚህ ሰዎች በቀልን አይደለም የሚጠይቁት፣ ፍርድን እንጂ! ይህ የዘዳ. 32:43 (ራዕ. 19:2) ጠቃሽ ይሆናል። ይህ ጥያቄ የጳውሎስን ማስጠንቀቂያ ይከተላል፣ ሮሜ 12:19 ላይ።

▣ **"ጌታ ሆይ"** ይህ ቃል "ጌታ" (*despotēs*) ሙሉ ሥልጣንን ይገልጻል። የእንግሊዝኛውን ቃል "ዐምባ-ገነን" ያገኘነው ከዚህ የግሪክ ቃል ነው። እሱም ለያህዌ ጥቅም ላይ ውሏል ሉቃስ 2:29 እና ሐዋ. 4:24 ላይ እንዲሁም ለኢየሱስ 2 ጴጥ. 2:1 እና ይሁዳ ቁ.4 ላይ።

▣ **"በምድር በሚኖሩት ላይ"** ይህ ራዕይ ላይ የተለመደ ሐረግ ነው፤ እሱም ዘወትር የሚያመለክተው የማያምኑትን ነው (ዝከ. 3:10፤ 8:13፤ 11:10፤ 13:8፣12፣14፤ 17:2፣8)።

**6፡11 "ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው"** ይህ ዘይቤ ነው ለ "ዕረፍት፣" "መባረክ፣" ወይም "ድል።" ለአንዳንዶች እዚህ ያለው ሥነ-መለኮታዊ ችግር ከነፍስ የተለየ ሥጋ እንዴት ልብስ እንደሚለብስ ነው። ከተጋነነ ጥሬአዊነት ተጠንቀቁ፣ በተለይም አፖካሊፕቲካዊ ድራማ ሲተረጎም! አታቾች እንኳ ይህንን የሚገልጹበት ሐቅ የመጽሐፉን ዘውግ ባግባቡ እንዳልተረዱት ያሳያል! ራዕይ ላይ ዝርዝሩን አትግፉት!

▣ **"እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ፥"** የዚህ መጽሐፍ አንደኛው ዋነኛ ሐቅ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር መቆጣጠሩ ነው (ዝከ. ቁ. 8)፣ የክርስቲያን ሰማዕታትን ሞት እንኳ! ታሪክ

ሁሉ በእጁ ነው። እግዚአብሔር በአንዳችም ሁነቶች፣ ድርጊቶች፣ ወይም ውጤቶች አይደነቅም። ርግጥ ገና ሥቃይ፣ መከራ፣ እና ፍትሐዊ ያልሆነ ነገር በዚህ በወደቀ ዓለም ውስጥ ይኖራል። ለተሻለ የክፉው ችግር ማብራሪያ የጆን ደብልዩ. ዌንሃምን *የእግዚአብሔር መልካምነትን* ተመልከት።

ይህ የተጠናቀቀ የሠማዕታት ቁጥር ጽንሰ-ሐሳብ (ሔኖክ 47፡4) ተምሳሌታዊ የእግዚአብሔር እውቀት እና ዕቅድ፣ ለሰው ልጆች ያለውን ማመላከቻ ነው። ይህም ከጳውሎስ "የአሕዛብ ሙላት" ጽንሰ-ሐሳብ ጋር ይመሳሰላል (ሮሜ 11:12፣25) እሱም የሚጠቅሰው እግዚአብሔር የሚድኑትን አሕዛብ ሁሉ እንደሚያውቅ ለመግለጽ ነው።

**ራዕይ፡ 6፡12-17**

**[12]ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጕር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፥ [13]በለስም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ ቃርያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ፥ [14]ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ፥ ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ። [15]የምድርም ነገሥታትና መኳንንት ሻለቃዎችም ባለ ጠጋዎችም ኃይለኛዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች ዓለቶች ተሰወሩ፥ [16]ተራራዎችንና ዓለቶችንም። በላያችን ውደቁ በዙፋንም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቍጣ ሰውሩን፤ [17]ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው።**

**6፡12 "ስድስተኛውን ማኅተም ፈታ"** ይህ ቁጥር የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ቋንቋ ነው፣ ለዘመን መጨረሻ (ኢዩኤል 2:30-31፤ 3:15-16፤ ኢሳ. 13:9፣10፤ 34:4፤ ኤር. 4:23-28፤ ሐጌ 2:6፤ ማቴ. 24:29፤ እና *የሙሴ ቃል* 10:5)። ሰባቱን ዓይነቶች ቁ. 12-14 ላይ ተገንዘቡ። ቋንቋው በብኪ. ጥቅም ላይ የሚውለው ለጌታ ቀን ነው። እዚህ የእሱ አጠቃቀም በስድስተኛው ማኅተም እና ኋላም በስድስተኛው መለከት መሆኑ አንድ ምክንያት ነው፣ እኔ እንደማምነው፣ እነዚህ እያንዳንዳቸው ተለጣጣቂ ሰባቶች በዘመን ፍጻሜ ላይ ይጠናቀቃሉ፣ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት (ዝክ. 6:12-17፤ 11:15-18፤ 14:14-20፤ 16:17-21፤ 19:11-21፤ 22:6-16)። *ራዕይ* ቅደም ተከተላዊ ተለጣጣቂ <u>አይደለም</u>። እሱ ባለ ሰባት ገቢር ድራማ ነው።

▣ ***"ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ"*** በዚህ መጽሐፍ ላይ የተጠቀሱ በርካታ የምድር መናወጦች አሉ (ዝክ. 8:5፤ 11:13፣19፤ 16:18)። በዚህ በፍጻሜ ዘመን፣ አፖካሊፕቲካዊ ሁነት ሰባት ገጽታዎች እንዳሉ መገንዘቡ ያስገርማል። ደግሞም ሰባት የተለያዩ ምድቦች ቁ. 15 ላይ ተዘርዝረዋል (ልዩ ርዕስ፡ ተምሳሌታዊ ቁጥሮች በቅዱስ ቃሉ 1:4 ላይ ተመልከት)። ይህም ሌለኛው ምሳሌ ነው፣ እጅግ ለተዋቀረው፣ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ፣ ጽሑፋዊ ፈርጅ (ዝክ. 5፡12)።

▣ **"ፀሐይም ጠቆረች... ጨረቃም እንደ ደም መሰለች"** ይህ የብኪ ጠቃሽ ነው፣ ለፍጻሜ ቀን (ኢሳ. 13:10፤ 24:23፤ 50:3፤ ሕዝ. 32:7፤ ኢዩኤል 2:2፣10፣31፤ 3:15፤ ማቴ. 24:29፤ ማርቆስ 13:24-25፤ ሉቃስ 21:25)።

**6፡13 "የሰማይ ከዋክብትም ወደቁ"** ይህ ዘይቤ ሁለት መገኛዎች ይኖሩታል፡

1. እግዚአብሔር የፈጠረው ሥርዓት ጽኑዕነት (ኢዮብ 38:31-33፤ መዝ. 89:36-37፤ ኢሳ. 13:10፤ ኤር. 31:35-36፤ 37:20-26፤ ሔኖክ 2:1) በእግዚአብሔር ፍርድ መሐል ወደ ፍጻሜ ይመጣሉ (ማቴ. 24:29)
2. የከዋክብት መውደቅ የተለመደ የበይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ዘይቤ ነው (እርሱም ዘወትር መልአክትን የሚጠቅስ፣ ማለትም፣ 12፡4፤ ዳን. 8፡10)

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ቁ. 1 በተሻለ ይስማማል።

**6፡14 "ሰማይም ተጠቀለለ"** የጥንቶቹ ሰማይን የሚመለከቱት እንደ ጠጣር አጎበር ነው፣ እንደ ተዘረጋ ቆዳ (ኢዮብ 22:14፤ መዝ. 104:2፤ ምሳሌ. 8:27፤ ኢሳ. 40:22)። ይህ የመለኮት ዘይቤ ነው፣ የተፈጥሮን ሥርዓት መስበሩን (ኢሳ. 34፡4)።

▣ **"ተራሮችና ደሴቶች ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ"** በብኪ፣ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሲጎበኝ፣ ለበረከትም ሆነ ለፍርድ፣ ነውጥ ይሆናል። ገለጻው ዘወትር የሚሳለው በአፖካሊፕቲካዊ ቃላት ነው። ቁጥር 15-17 የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ቁጣ ነው፣ በማያምኑት አሳዳጆች ላይ (ዝክ. 16፡20)። እነዚህ ተመሳሳይ ገለጻዎች በብኪ. ጥቅም ላይ ውለዋል፣ እግዚአብሔር ወዳለበት አካላዊ ቅርርቦሽ ለማድረግ፣ አንድም ተራሮችን ዝቅ በማድረግ ዓይነት፣ ወንዞችንም በማድረቅ፣ ወዘተ. (ኢሳ. 40፡4)።

**6፡15 "በዋሻዎችና በተራሮች ዓለቶች መካከል ራሳቸውን ሸሸጉ"** እግዚአብሔር ያሳደዳቸው ሰዎች፣ ከማያምኑት እንደሆነው ስደት እንደሚሸሸጉ ሁሉ (ዕብ. 11፡38)፣ አሁንም እንዲሁ ሀብታሞችና ኃይለኞች (የመዝ. 2፡2 ጠቃሽ የሚሆን) ከእግዚአብሔር ቁጣ መጠጊያ ይፈልጋሉ (ኢሳ. 2:10፣19፣21)። ይህ ቁጥር የሚገልጸው የወደቀውን፣ የማያምነውን የሰው ልጅ ነው፣ በሰባት መንገዶች። ይህ የሰባቶች አጠቃቀም መሠረታዊ ፈርጅ ነው፣ በዮሐንስ መጽሐፍ (ልዩ ርዕስ 1፡4 ላይ ተመልከት)።

**6፡16 "በላያችን ውደቁ፣ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ከእርሱ ሰውሩን"** ይህ የሆሴዕ 10፡8 ጠቃሽ ነው (ኢሳ. 2:19፣21 እና ሉቃስ 23:30)። የአብና የወልድ ቁጣ መያያዙን ተገንዘብ፣ በእምነት ቤተሰባቸው ላይ ላይ የደረሰውን ሲቃወሙ። እነርሱ በታሪክ ላይ ሠርተዋል፣ ታማኙን ለመጠበቅ እና ዐመጸኞችን ለመቅጣት (ገላ. 6፡7)።

▣ **"የበጉ ቁጣ"** ይህ ኃይለኛ ድብልቅ ዘይቤ ነው። ይህ የድል አድራጊው በግ ተምሳሌት ከአይሁድ በይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-ጽሑፍ ነው። "ቁጣ" (*orgē*) 7፡14 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

**6፡17** ቁጥር 17 የኢዩኤል 2፡11 ወይም ሚል. 3፡2 ጠቃሽ ይመስላል። ብዙዎቹ አታቾች የሚያምኑት ቁ. 17 ምዕራፍ 7 ላይ ለሚገኘው ጥቂት የቆይታ ጊዜ ደረጃ እንደሚያመቻች ነው፣ እሱም "አማኞችስ እንዴት ይሆናሉ፣ በምድር ላይ ያሉት፣ በእነዚህ አፖካሊፒቲካዊ ሁነቶች እና ተለጣጣቂ ፍርዶች መካከል?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይሞክራል። በአታቾች መካከል ዘወትር ክርክር ይኖራል፣ ምዕራፍ 6 ላይ ያሉት ማኅተሞች ተቤዢ ወይም ፍርዳዊ ለመሆናቸው (ዝኪ. 9:20-21፤ 14:7-8፤ 16:9፣11)። ምዕራፍ 6 የሚያመለክተው በማያምኑት ላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው፣ እነርሱም ለማመን እምቢ ያሉ። እነዚህ ፍርዶች ¼ ዓለም መጉዳት ይጀምራሉ፣ ከዚያም 1/3፣ በመጨረሻም በጽዋዎቹ ባጠቃላይ የማያምነው ዓለም (ሶፎ. 1፡14-18)።

***ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ለ7፡1-17***

ሀ. ምዕራፍ 7 በስድስተኛው ማኅተም እና በሰባተኛው ማኅተም መከፈቻ መካከል ቆይታ ይፈጥራል (ዝኪ. 8:1፣ በስድስተኛውና በሰባተኛው መለከቶች መካከል 10:1-11:13 እንዳደረገ ሁሉ)። እሱም የሚገልጸው በአማኞች ላይ ምን ይሆናል፣ በእነዚህ የእግዚአብሔር ፍርድ ዑደቶች፣ በማያምኑት ላይ በሚሆኑት፣ የሚለውን ጥያቄ ነው። ሰባተኛው ማኅተም ሰባት መለከቶች ይሆናል።

ለ. ይህ ቆይታ ሁለት የአማኞች ቡድን ላይ ነው

1. 144,000 ከአስራ ሁለቱ ነገዶች በምድር (ዝኪ. ቁ. 1-8፣ በተለይም ቁ. 4)
2. የማይቆጠሩ ሰዎች ከሙሉው ምድር ነገዶች፣ አሁን በሰማይ ያሉ (ዝኪ. ቁ. 9-17፣ በተለይም ቁ. 9)

ሐ. እግዚአብሔር በኃይለኛ፣ በተከላካይነት፣ በተረጋገጡ መንገዶች በሕዝቡ በኩል ይሠራል። ይህ በራዕይ ላይ ልዩነት አይደለም፣ በአማኝ አይሁድና በአሕዛብ መካከል (ሮሜ. 2:28-29፤ 3:22፤ 1 ቆሮ. 12:13፤ ገላ. 3:28፤ ቆላ. 3:11)። የብኪ የዘር ልዩነቶች በሚያምኑትና በማያምኑት አጠቃሎሽነት ይዟል።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

***ራዕይ፡ 7፡1-3***

**[1]ከዚህም በኋላ በአራቱ በምድር ማዕዘን ቆመው አራት መላእክት አየሁ፥ እነርሱም ነፋስ በምድር ቢሆን ወይም በባሕር ወይም በማንም ዛፍ እንዳይነፍስ አራቱን የምድር ነፋሳት ያዙ። [2]የሕያው አምላክ ማኅተም ያለውም ሌላ መልአክ ከፀሐይ መውጫ ሲወጣ አየሁ፥ ምድርንና ባሕርንም ሊጐዱ ለተሰጣቸው ለአራቱ መላእክት በታላቅ ድምፅ እየጮኸ። [3]የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጉዱ አላቸው።**

**7፡1 "አራት መላእክት አየሁ በአራቱ በምድር ማዕዘን ቆመው... አራቱን የምድር ነፋሳት ይዘው"** በብኪ የቁጥር ተምሳሌታዊነት አራት የሚያመለክተው መላውን ዓለም ነው (ኢሳ. 11:12፤ ኤር. 49:36፤ ዳን. 7:2፤ ዘካ. 1:8፤ 6:1፣5፤ ማቴ. 24:31፣ ልዩ ርዕስ 1፡4 ላይ ተመልከት)።

እነዚህን አራት ነፋሳት በተመለከተ በርካታ ትርጉሞች አሉ።

1. ራቢዎች ባለ ሩብ ነፋሳትን የሚመለከቱት እንደ ክፉ ነው (ሐዋ. 27፡14)
2. አንዳንዶች የሚመለከቱት ክፉ ነፋሳትን ወይም የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው፣ ኤር. 49፡36 እና ዳን. 7፡2 ላይ ያለው
3. አንዳንዶች የሚመለከቱት ዘካ. 1:8 እና 6፡5 ላይ እንዳለው ቁጥር አራት ጥቅሻ ነው፣ አራቱ ፈረሰኞችና አራቱ ሠረገላዎች በመላው ዓለም የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑት (ማቴ. 24፡31)

▣ **"ነፋስም በምድር ላይ እንዳይነፍስ ወይም በባሕር ወይም በማንም ዛፍ"** ይህ እንደ 6፡6 እና 8 የተወሰነ ፍርድን ያሳያል (ዝኪ. 7፡3፤ 9፡4)።

**7፡2 "ሌላ መልአክ ከፀሐይ መውጫ ሲወጣ አየሁ"** ምስራቅ (ፀሐይ) የሕይወት፣ የጤና፣ ወይም የአዲስ ቀን ተምሳሌት ነው።

▣ **"የሕያው አምላክ ማኅተም ያለው"** የአምላክ ማኅተም በድጋሚ 9:4 እና 14:1 እና ምናልባትም 22:4 ላይ ተጠቅሷል። የሰይጣን ማኅተም 13:16፤ 14:9፤ እና 20:4 ላይ ተጠቅሷል። የዚህ ማኅተም ዓላማ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ለመለየትና የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳያገኛቸው ለማድረግ ነው። የሰይጣን ማኅተም የራሱን ሕዝቦች ይለያል፣ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚያገኛቸውን።

በራዕይ "መከራ" (ማለትም፣*thlipsis*) ዘወትር የሚሆነው የማያምኑት የሚያምኑትን ሲያሳድዷቸው ሲሆን፣ መዓት/ቁጣ (ማለትም፣ *orgē* ወይም *thumos*) ደግሞ ዘወትር የእግዚአብሔር ፍርድ በማያምኑት ላይ ሲሆን ነው፣ ስለሆነም እነሱ ምናልባት ተጸጽተው ወደ ኢየሱስ እምነት ይመለሱ ዘንድ። ይህ አዎንታዊ የፍርድ ዓላማ በዘዳግም 27-28 የርግማን/በረከት ኪዳን ላይ ይታያል።

"ሕያው አምላክ" የሚለው ሐረግ የያህዌ መጠሪያ ቃል ነው (ዘጸ. 3:14፤ መዝ. 42:4፤ 84:2፤ ማቴ. 16:16፣ ልዩ ርዕስ 1፡8 ላይ ተመልከት)። ይህን መሰሉ ቃል ዘወትር በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሐላዎች ላይ ይገኛል፣ "ሕያው እግዚአብሔርን።

## ልዩ ርዕስ፡ ማህተም

ማህተም በጥንት ጊዜ እነዚህን ነገሮች ለማመልከት ውሏል

1. እውነት (ዮሐ 3፡33)
2. ባለቤትነትን (ዮሐ 6፡27፤ 2ጢሞ 2፡19፤ ራዕ 7፡2-3)
3. ደንነትን ወይም ጥበቃን (ዘፍ 4፡15፤ ማቴ 27፡66፤ ሮሜ 15፡28፤ 2ቆሮ 1፡22፤ ኤፌ 1፡13፤ 4፡30)
4. የእግዚአብሔር የስጦታ ተስፋ ቃል እውነተኝነት ማረጋገጫ ምልክት ነው (ሮሜ 4፡11 እና 1ቆሮ 9፡2)

የዚህ ማህተም ጠቀሜታ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳያገኛቸው እግዚአብሔርን ሕዝች ለመለየት ነው፡፡ የሴጣን ምህተም የእርሱ የሆኑትን ለመለየት ሲያገለግል፤ እነዚህም የእግዚአብሔር ቁጣ የሚያርፋባቸው ናቸው፡፡ በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ "መከራ" (ትሊፕሲስ) ያላመኑት የሚያምኑትን ሲያሳድዱ ካለው ሃሳብ ጋር ሲገናኝ ፍርድ/ቁጣ *(ኦርጅ ወይም ቱምስ)* ሁል ጊዜ የሚገናኘው ያላመኑት በኃጢአታቸው ተፀተው ወደ ክርስቶስ በእምነት ዘወር ይሉ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሚመጣባቸው ፍርድ ነው፡፡ ይህ አዎንታዊ የሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ በዘዳ 27-28 ላይ ከተገለፁት የኪዳን እርግማኖች/በረከቶች ላይ የሚታይ ነው፡፡

▣ **"ምድርንና ባሕርንም ሊጎዱ ለተሰጣቸው ለአራቱ መላእክት"** ይህ የድርጊት ተገብሮ አመላካች ነው። እግዚአብሔር በምድር እና በማያምኑት ላይ የሚሆነውን ፍርድ ይቆጣጠራል። የእሱ በፍርዱ ላይ ያለው ወሰን ሁለት ዓላማዎች አሉት፡

1. አማኞች በእነርሱ እንዳይጎዱ
2. የማያምኑት ንስሐ እንዲገቡ፣ ስሙን እንዲጠሩ፣ እና ክብር እንዲሰጡት (ዝከ. 9:20-21፤ 14:6-7፤ 16:9፣11፤ 21:7፤ 22:17)

**7፡3 "የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ"** ይህ የሕዝ. 9:4፣6 (ራዕ. 9:4፤ 14:1) ጠቃሽ ነው። የዚህ ማኅተም ተቃራኒ የሰይጣን ማኅተም ነው፣ የአውሬው ምልክት (ዝከ. 13:16፣17፤ 14:9፣11፤ 16:2፤ 19:20፤ 20:4)።

## ራዕይ፡ 7፡4

**[4]የታተሙትንም ቍጥር ሰማሁ፤ ከእስራኤል ልጆች ነገድ ሁሉ የታተሙት መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።**

**7፡4 "አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ"** ተመሳሳይ ምሥጢራዊ ቡድን 14:1፣3 ላይ ተጠቅሷል። ይህን ቁጥር በተመለከተ በርካታ ውይይቶች ተካሂደዋል፣ ማንንም እንደሚወክል። ይህ ቁጥር ተምሳሌታዊ ነው፣ ጥሬአዊ ሳይሆን፣ በተከታዮቹ ምክንያት።

1. ቁጥሩ ራሱ ከብ ቁጥር ነው፣ ሁሉም ነገዶች እኩል ቁጥር አላቸው (ይኸውም በብኪ ፈጽሞ ያላደረጉት)
2. ቁጥሩ የአስራ ሁለት ብዜት ነው፣ እርሱም የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የድርጅት ቁጥር (ወይም የእግዚአብሔር ሕዝብ) እና አስር፣ እርሱም የመጽሐፍ ቅዱስ የፍጽምና ቁጥር (ልዩ ርዕስ 1:4 ላይ ተመልከት)
3. ምዕራፍ 7 በአፖካሊፕቲካዊ ቋንቋ ነው
4. የእስራኤል ነገዶች ዝርዝር በመጠኑ ተቀይሯል (ዳን ተገድፏል፣ ኤፍሬምም በዮሴፍ ተተክቷል)። አይሁድ በጥሬው የሚወሰድ እንዳልሆነ ያውቃሉ።

የዚህ ወገን ታሳቢ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት፡

1. እሱም በጥሬው፣ በመጨረሻው ዘመን የሚያምኑት እስራኤል (ዘካ. 12:10)
2. እሱም አዲስ ተለዋጭ አማኞች ናቸው፣ ከቤተ ክርስቲያን ምሥጢራዊ መነጠቅ በኋላ
3. እሱም የአማኝ አይሁድ ቅሬታዎች ናቸው (ሮሜ 11)
4. እሱም ለአኪ ቤተ ክርስቲያን መጠሪያ ነው (ዝከ. 1:6)

ማኅተሙ በራዕይ ለአንድ ቡድን ብቻ አልተወሰነም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ባለቤትነትና ለሕዝቡ ያለውን ጥበቃ ይወክላል (ዝከ. 2:20፤ 11:18፤ 19:2፣5፤ 22:36). ሰይጣን ተከታዮቹን ሁሉ አትሟቸዋል (ዝከ. 13:16፣17፤ 14:9፣11፤ 16:2፤ 19:20፤ 20:4)፣ ከእግዚአብሔር ኮርዡ (ዝከ. 3:12፤ 7:3፤ 14:1፤ 22:4)።

አኪ ዘወትር ቤተ ክርስቲያንን የሚገልጸው ለእስራኤል በሚውለው መልኩ ነው (ሮሜ. 2:28-29፤ 4:11፤ 9:6፣8፤ ገላ. 3:29፤ 6:16፤ ፊሊ. 3:3) እና በተለይ በራዕይ መጽሐፍ 1:6 ላይ ቤተ ክርስቲያን ለእስራኤል ጥቅም ላይ ይውል በነበረው መጠርያ ስትጠቀስ ዘጸ. 19:4-6 (cf. 1 ጴጥ. 2:5፣9)። በያዕቆብ መጻሕፍት (ዝከ. 1:1) እና 1 ጴጥሮስ (ዝከ. 1:1) ቤተ ክርስቲያን ደግሞ "ዳያስፖራ" በመባልም ትጠራ ነበር፣ ለተበተኑት አይሁድ በፍልስጥኤም ለማይኖሩት አይሁድ ስም።

ለእኔ የተሻለ የሚመስለኝ፣ ይሄንን መጽሐፍ በማጠናበት ጊዜ፣ 144,000 ቁ. 4 እና "እጅግ ብዙ ሕዝብ" ቁ. 9 ላይ ያለው፣ እንደ የአኪ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው—ክርስቶስን ያመኑ እነሱ፣ ነገር ግን በሁለት የተለያዩ መልኮች የሚታዩ (ያመኑ አይሁድ እና ያመኑ አሕዛብ)።

## ልዩ ርዕስ፡ አስራ ሁለት ቁጥር

ዐስራ ሁለት የሚለው ቁጥር ሁልጊዜ የመደራጀት ምሳሌያዊ ቁጥር ሆኖ ቆይቷል

ሀ. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጭ

1. ዐስራ ሁለት የዞዲክ ምልክት ነው
2. ዐስራ ሁለት የአንድ አመት ወራት

ለ. በብሉ ኪዳን ውስጥ
1. የያዕቆብ ልጆች (የአይሁድ ዘሮች)
2. ከዚህ በታች ባሉት ውስጥ ተንጸባርቋል
ሀ. በዘጸ 24፡4 ላይ በዐስራ ሁለቱ መሰዊያዎች
ለ. በዘጸ 28፡21 ላይ ካህናት በሙታጠቁት ዐስራ ሁለቱ መቀነቶች (እያንዳንዱ ለእስራኤላዊያን ብሔሮችን ያመለክታል)
ሐ. በዘሌ ውስጥ በመገናኛ ድንኳኑ ውስጥ ባለው ቅዱስ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ ያሉትን ዐስራ ሁለት ቅጣዎች
መ. በዘዳ 13 (ከእያንዳንዱ ነገድ) የተላኩ ዐስራ ሁለት ሰላዮች
ሠ በዘዳ 17፡2 ውስጠ በቆሬ አመጽ ወቅት (ዐስራ ሁለቱን ነገዶች ለማለከት ውሏል
ረ. በኢያ 4፡3፣ 9፣ 20 ውስጥ የኢየሱስን ዐስራ ሁለት ድንጋዮች
ሰ. በ1 ነገ 4፡7 ላይ በሰለሞን አመራር ውስጥ የነበሩ ዐስራ ሁለት አመራሮች
ሸ. በ1 ነገ 18፡31 ላይ የኤልያስ ለያሕዌ መሠዊያ ሲያዘጋጅ ያስቀመጣቸው ዐስራ ሁለት ድንጋዮች
ሐ. አዲስ ኪዳን
1. የተመረጡት ዐስራ ሁለት ሐዋርያት
2. በማቴ 14፡20 ዐስራ ሁለት መሶብ ዳቦ
3. በማቴ 19፡28 ላይ የተጠቀሰው ዐስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የሚቀመጡበት መቀመጫ
4. በ26፡53 ላይ የተጠቀሰው ኢየሱስን ለመታደግ ልላኩ የሚችሉ ዐስራ ሁለት ሌጌዎን የመላዕክት ሠራዊት
5. በራዕይ ውስጥ ያሉ ተምሳሌቶች
ሀ. በ4፡4 ላይ በዙፋን ላይ የተቀመጡ ዐስራ ሁለቱ ሽማግሌዎች
ለ. በ7፡4፤ 14፡1፣ 3 ላይ 144000 (12x12000)
ሐ. በ12፡1 ላይ ያለችው ሴት ዘውድ ዐስራ ሁለት ኮኮቦች
መ. በ21፡2 ላይ ዐስራሁለት መግቢያ በር፣ ዐስራ ሁለት ሁለቱን ነገዶች የሚያመለክቱ መላእክት
ሠ. በ21፡14 በዐስራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም ያለበት የኢየሩሳሌም ዐስራ ሁለት መሠረቶች
ረ. በ21፡16 ላይ ዐስራ ሁለት ሺህ ስታንዲያ
ሰ. በ21፡7 ላይ ያው 144 ክዩብ ግድግዳ
ሸ. በ21፡21 ላይ ዐስራ ሁለት መግቢያ መሰሶዎች
ቀ. በ22፡2 ላይ በአዲስቷ ኢየሩሳሌም ያለው ዛፍ ከዐስራ ሁለት ፍሬዎቹ ጋር

### *ራዕይ፡* 7፡5-8

***[5]ከይሁዳ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ታተሙ፥ ከሮቤል ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከጋድ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ [6]ከአሴር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከንፍታሌም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ [7]ከምናሴ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከስምዖን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከሌዊ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከይሳኮር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ [8]ከዛብሎን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከዮሴፍ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከብንያም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ታተሙ።***

**7፡5 "*ከይሁዳ ነገድ*"** የነገዶቹ ዝርዝር ከሃያ-በላይ ከሚሆኑት በብኪ ከሚገኙት ዝርዝሮች ጋር አይገጥምም። በተለይም ከሕዝ. 48፡2-7 ጋር አይገጥምም፣ እሱም የፍጻሜውን ዘመን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ዝርዝር የያዘ። ዳን ተደግፏል፣ ይሁዳ በመጀመሪያ ነው የተጻፈው፣ ኤፍሬም ወጥቷል፣ ዮሴፍ ግን በእርሱ ቦታ ተጽፏል፣ ሌዊም ከሌሎች ነገዶች ጋር ተካትቷል። ማንኛውም አይሁድ ይህ ዝርዝር የተዛባ እንደሆነ ያውቃል፣ እናም በተምሳሌትነት እንደሚወሰድ ይረዳል።

ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ፣ *ለጥያቄዎች መልሶች*፣ ገጽ 139 ላይ እንደጠቀሰው የዳን ነገድ ከዝርዝሩ የተገደፈበት ምክንያት፣ በቤተ ክርስቲያን ባህል ተመልሶ የሚሄደው ወደ ኢሪኑስ የኤር. 8፡16 ትርጓሜ ነው፣ በሴፕቱዋጂንት። እሱም ሲነበብ፡

> "የፈረሰኞቹ ድምጽ ከዳን ተሰማ ከአርበኞች ፈረሶች ማሽካካት የተነሣ ምድር ሁሉ ተንቀጠቀጠች መጡም ምድሪቱንና በእርስዋም ያለውን ሁሉ፥ ከተማይቱንና የተቀመጡባትንም በሉ።"

ኢሪኑስ የተመለከተው የሚመጣው የክርስቶስ ተቃዋሚ ከዳን ነገድ እንደሚመጣ ነው። ይህ የዝምብሎ ግምት ነው፣ ትርጉም ሳይሆን!

### *ራዕይ፡* 7፡9-12

***[9]ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤ [10]በታላቅም ድምፅ እየጮሁ። በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ። [11]መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ። [12]አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ።***

**7፡9** እዚህ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት እጅግ በርካታ ሰዎች በግልጽ እንደሚታየው ከመቶ አርባ አራት ሺው፣ ቁጥር 4 ላይ ከተጠቀሱት ይለያሉ። የመጀመሪያዎቹ ምድቦች ከእስራኤል የተለያዩ ነገዶች እንደመጡ፣ ይሄኛው ምድብ ከተለያዩ የምድር ነገዶች ነው የመጡት። የሚመስለውም እነዚህ ሁለት ወገኖች የሚወክሉት ተመሳሳይ ወደን ሕዝቦችን ነው፣ በሁለት በተለያዩ መልኮች። ቁ. 1-8 አማኝ አይሁድን የሚያመለክት ከሆነ፣ እንግዲያውስ ቁ.9 የሚያመለክተው ከሁሉም ወገን ሕዝቦች የሆኑ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ነው (ዝከ. 5:9፤ 11:9፤ 13:7፤ 14:6፤ 17:15)።

ሆኖም፣ እነርሱ የተባሉበት ሐቅ (1) ከታላቁ መከራ የወጡ ናቸው (ዝከ. ቁ. 14)፤ (2) በዙፋኑ ፊት የቆሙ (ዝከ. ቁ. 9)፤ እና (3) ነጭ ልብስ ለብሰዋል (ዝከ. 6፡11) የተጠናቀቀውን የሰማዕታት ቁጥር የሚጠቅሱ ይሆናሉ (ዝከ. 6:11፤ 17:6፤ 18:24፤ 19:2፤ 20:4)።

▣ ***"ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል"*** ይህ ጠቃሽ ይሆናል፣ ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ፣ ዘሩ እንደሚበዛ።

1. የምድር አሸዋ – ዘፍ. 13:16፤ 28:14፤ ዘኍ. 23:10
2. የሰማይ ከዋክብት – ዘፍ. 15:5፤ 22:17፤ 26:4፤ ዘዳ. 1:10
3. በባሕር ዳር ያለ አሸዋ – ዘፍ. 22:17፤ 32:12
4. አጠቃላይ ቃል – ዘፍ. 16:10

▣ ***"የዘንባባ ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው"*** አንዳንዶች ይሄንን ከሌዋ. 23፡40 ወይም ነህ. 8፡15 ጋር ሊያያይዙት ይሞክራሉ፣ እንደ ደስታና ድል ምልክት። ሌሎች የሚያዛምዱት ከፋሲካ በዓል የአምልኮ ሥርዓት ጋር ነው፣ ዮሐንስ 12፡13 ላይ እንዳለው ሌሎችም፣ ይህ ምንባብ ከምድረ በዳ የመንከራተት ጊዜ ጋር ስለሚያያዝ (ዝከ. ቁ. 15-16)፣ ከዳስ በዓል ጋር። የዘንባባ ዝንጣፊ የድል ተምሳሌት ሊሆን ይችላል።

**7፡10** ***"የአምላካችን ማዳን"*** ይህ የተለመደው የግሪክ ቃል "ደኅንነት" ነው (*sōteria* ከ*sōzō*)፣ ጥቅም ላይ የዋለው ግን በ "ድል" ስሜት ነው (አእመቅ) ወይም *"ሙሉ ለሙሉ ድል መንሣት።"* ስለዚህ፣ እሱ ሊያመለክት የሚችለው (1) በምድር ላይ ካሉ ችግሮች መታደግ ወይም (2) መንፈሳዊ፣ ዘላለማዊ ደኅንነት። የብኪ ቃል (*yasha*) ፍችው ሥጋዊ ትድግና ነው (ያዕቆብ 5፡15)። ይኸው ተመሳሳይ ቃል ተለጣጣቂ በሆኑት አምላክን መባረክ ሦስት ጊዜ ራዕይ (ዝከ. 7:10፤ 12:10፤ 19:1) ላይ ተጠቅሷል።

▣ ***"ለበጉም"*** መሲሑ፣ ያህዌ በተባረከበት መንገድ መባረኩን ተገንዘቡ። ይህም ለወልድ መለኮታዊ ባሕርይ አጽንዖት ይሰጣል።

**7፡11** በርካታ ቡድኖች እንደተለዩ ተገንዘብ።

1. መላእክት
2. ሽማግሌዎች
3. አራቱ እንስሳት

እነዚህ ቡድኖች ሁሉ በሰማይ ካለው ከእግዚአብሔር የዙፋኑ ክፍል ጋር ተያይዘዋል። እነርሱ ከ144,000 እና ከታላቅ ብዙ ሕዝቦች ተለይተዋል። ለ "ሽማግሌዎች" ልዩ ርዕስ፡ ሽማግሌ 4፡4 ላይ ተመልከት።

**7፡2** ***"እያሉ"*** ሰባት እጥፍ የሆነውን ለአምላክ የቀረበውን ባርኮት (እና መሲሕ፣ ዝከ. ቁ. 10) ተገንዘብ፣ እሱም ከሰባት እጥፍ ባርኮቶች፣ ለታረደው በግ ከሆነው ከ5፡12 ጋር ተመሳሳይ ነው።

▣ ***"አሜን"*** እሱ ባርኮቱን እንዴት እንደ ጀመረና እንዳጠናቀቀ ተገንዘብ። ልዩ ርዕስ 1፡6 ላይ ተመልከት።

### *ራዕይ፡ 7፡13-17*

**[13]ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ:- እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ። [14]እኔም። ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት። አለኝም። እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ። [15]ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል። [16]ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፥ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም፥ ፀሐይም ትኵሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም፤ [17]በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።**

**7፡14** ***"እኔም። ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት"*** ይህ የተለመደው የሰው ምላሽ ነው ለመልአካዊ መልእክተኞች (ዘካ. 4:5፣13፤ ዳን. 10:16)፣ እሱም የሽማግሌዎችን ማንነት የሚያጠናክር፣ ከመልአካዊ አካላት ቡድኖች ጋር።

አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ መልአካዊ ጣልቃ ገብነትንና ትርጓሜን ባሕርዩ ያደርጋል። እነዚህ ትርጓሜዎች ዓይነተኛ ሆነዋል (እንደ ኅብረ-ዝማሬዎች) ተምሳሌታዊውን ቋንቋ ለመግለጽና ለመረዳት።

▣ ***"እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው"*** ይህ የአሁን ያልተወሰነ አንቀጽ ሲሆን፣ በዮሐንስ ጊዜ የተሳደዱትን አብያተ-ክርስቲያናት የሚጠቅስ ነው (ዝከ. 1፡9፤ 2፡9፣10፣22)። ሆኖም፣ ታሪካዊው ጠቃሽ በራዕይ ላይ በግልጽ የሚያሳየው የቅዱሳንን ስደት ነው፣ በየዘመናቱ፣ እንዲሁም ደግሞ በፍጻሜው ዘመን የመከራውን እየተጠናከረ መምጣት (ዳን. 12፡1)። ይህም የሚዛመደው

1. የእግዚአብሔር ልጆች ስደት (ዝከ. 24:21-22፤ ማርቆስ 13:19፤ II ተሰ. 2:3፤ ራዕ. 2:10፤ ዳን. 12:1)

2. በማያምኑት ላይ የሚመጣ የእግዚአብሔር ቁጣ (II ተሰ. 1:6-9፤ ራዕ. 3:10፤ 6:17፤ 8:2፤ 16:1)
እነዚህ ችግሮች፣ በተወሰነ ደረጃ፣ ከየዘመናቱ ጋር ይያያዛሉ። ክርስቲያኖች በኢየሱስ ስም መከራ ይቀበላሉ (ዮሐንስ 16:33፤ ሐዋ. 14:22፤ ሮሜ. 5:3፤ I ጴጥ. 4:12-16)። እነዚህ ሁለቱም ሁነቶች ዘወትር የሚጠሩት የአዲሱ የጽድቅ ዘመን የምጥ ጣር በሚል ነው (ማርቆስ 13:8 እና አፖካሊፕቲካዊው መጽሐፍ 2 ባሮክ፣ ምዕራፍ 25-30)።

የግሪኩ ቃል *thlipsis* (መከራ) በራዕይ አዘውትሮ ጥቅም ላይ የሚውለው አማኞች በማያምኑት እጅ የሚደርስባቸውን መከራ ነው (ዝከ. 1:9፤ 2:9፣10፣22፤ 7:14)። የግሪኩ ቃላት *thumos* (ዝከ. 12:12፤ 14:8፣10፣19፤ 15:1፣7፤ 16:1፤ 18:3፤ 19:15) እና *orgē* (ዝከ. 6:16፣17፤ 11:18፤ 14:10፤ 16:19፤ 19:15) ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውሉት ለአብና ለወልድ ቁጣ ነው፣ በማያምኑት ዐመጸኞች፣ አስቸጋሪዎች ላይ።

እንደ ሥነ-መለኮታዊ ጎንታ፣ መጽሐፉ የተጻፈው በመከራ የሚያልፉትን አማኞች ለማበረታታት ከሆነ፣ አንዳንድ ተርጓሚዎች ከምሥጢራዊ መነጠቅ ጋር ለምን እንደሚያያዝ ያስረግጣሉ፣ አንዳንድ የቀጣይ ትውልድ አማኞችን መከራ እንዳልሆነ በማሳየት? ስደት የአብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዕጣ ፈንታ ነው፣ እንዲሁም የየትውልዱ አማኞች። ታዲያ ለምን አንድ ቀጣይ ትውልድ ብቻ ይጠበቃል?

▣ **"ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ"** ይህ በግልጽ የሚያመለክተው በታላቁ መከራ ጊዜ የሞቱትን ሰማዕታት ነው፣ በክርስቶስ ባላቸው እምነት። እንዴት ያለው አስደናቂ የመቤዠት ዘይቤ ነው (ዝከ. 22:14)! ይህ መሰሉ በክርስቶስ መሥዋዕታዊ ሞት የመንጻት ሐሳብ በሮሜ 3:25፤ 5:9፤ II ቆሮ. 5:21፤ ኤፌ. 1:7፤ ቆላ. 1:20፤ ዕብ. 9:14፤ I ጴጥ. 1:19፤ እና I ዮሐንስ 1:7 ላይ ይታያል። የመስቀሉ እውነት ዘወትር ራዕይ ላይ ይጠቀሳል (ዝከ. 1:5፤ 5:12፤ 7:14፤ 12:11፤ 13:8፤ 14:4፤ 15:3፤ 19:7፤ 21:9፣23፤ 22:3)።

የክርስቶስን ስጦታና የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ግብዣ የሚሰጠውን ምላሽ አስፈላጊነት ውህደት ተገንዘብ። የሁለቱም ኪዳናት፣ ኪዳናዊ ገጽታዎች የሚያስረግጠው የእግዚአብሔርን አነሣሽነትና ስጦታ ነው፣ ነገር ግን ሉዓላዊው እግዚአብሔር ያንን የወደቀ የሰው ልጅ መርጧል፣ የግድ ምላሽ ይሰጥ ዘንድ (ዮሐንስ 1:12፤ ማርቆስ 1:15፤ ሐዋ. 3:16፣19፤ 20:21፤ ሮሜ. 10:9-13)።

**7:15-16** የወደፊቱ የደስታና ሰማያዊ ሰላም በብኪ ቃላት ተገልጿል። ይህ በምድረ በዳ የመንከራተት ጊዜና የቤተ መቅደሱ ጠቃሽ ነው (ዘጸ. 40:34-38፤ ዘኁ. 9:15-23)። እሱም ተጨማሪ ጠቃሽ ነው፣ የ*Shekinah* ክብር ደመና፣ ይኸውም የእግዚአብሔርን ከሕዝቡ ጋር መገኘት ተምሳሌት የሚያደርግ (ኢሳ. 49:10፤ ማቴ. 5:6፤ ዮሐንስ 4:14፤ 6:35፤ 7:37)። ይህ የእስራኤል ታሪክ ዘመን በእውነታነቱ የፍርድ ጊዜ ነው። ሆኖም፣ ያህዌ እንደዚህ የፍርድ ጊዜ ቅርብ ሆኖ የተገኘበት ወቅት ፈጽሞ አልነበረም። እሱም ዘወትር በራቢዎች የሚጠቀሰው የያህዌና የእስራኤል ጫጉላ በሚል ነው።

**7:15 "ቀንና ሌሊት ያገለግሉታል"** በብኪ ይህ የሚጠቅሰው ሌዋውያን ካህናትን ነው (መዝ. 134:1፤ I ዜና. 9:33)። ወደ እግዚአብሔር መቅረብና እግዚአብሔርን ማገልገል እየተስፋፋ መጥቷል (1) የተሳደዱት አማኞች እና (2) ሁሉም አማኞች ከዚያም በኋላ የአይሁድ ሊቅ ክህነት አይኖርም! ሁሉም አማኞች ካህናት ናቸው (I ጴጥ. 2:5፣9፤ ራዕ. 1:6)።

"ቀንና ሌሊት" የሚለው ሐረግ ለቀጣይነት ዘይቤ ነው። እሱም ራዕይ ላይ በርካታ ጊዜ ይገኛል (ዝከ. 4:8፤ 7:15፤ 12:10፤ 14:11፤ 20:10)።

▣ **"በመቅደሱ"** ይሄንን ምንባብ ለማዛመድ ያስቸግራል (እና ሕዝቅኤል 40-48) ከራዕ. 21:22 በሰማይ መቅደስ አይኖርም ከሚለው። አንዳንዶች ልዩነት ለማድረግ ይሞክራሉ፣ በጊዜያዊው ሚሊኒየማዊ ግዛት እና ዘላለማዊ ግዛት መካከል። በርግጥ፣ ዘይቤዎቹና የጊዜው ቅንብብ በዚህ መጽሐፍ ተለዋዋጭ ናቸው። ይህም በሰማይ ያለውን መንፈሳዊ ቤተ መቅደስ ሊያመለክት ይችላል (ዕብ. 9:23)።

▣ **"በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል"** ይህ ቃላዊ ዘይቤ ነው፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በቅርበት ለመኖሩ። የእግዚአብሔር ድንኳን የሚወክለው ከአዲሱ ሕዝቡ ጋር በቋሚነት መገኘቱን ነው፣ ከየወገኑና ከየነገዱ ጋር። የዔድን ገነት መነሻው ዓላማ ተመልሷል። ሰው ተዋጅቷል (ዘፍ. 3:15)። የቅርብ ወዳጅነት ከእግዚአብሔር ጋር ድጋሚ ተችሏል (ማለትም፣ ዘፍ. 3:8)።

**7:16-17** እነዚህ በረከቶች ናቸው (ከብኪ) ለሁሉም አማኞች፣ ለሰማዕታት ብቻ ሳይሆን።

**7:16 "ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፥ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም"** ቁጥር 16 የኢሳ. 49:10-13 ጠቃሽ ነው። የእግዚአብሔር ለሥጋ የሚያስፈልገውን ሰጭነት፣ ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ ሰጭነት በተምሳሌትነት ጥቅም ላይ ውሏል (ማቴ. 5:6፤ ዮሐንስ 4:14፤ 6:35፤ 7:37)።

▣ **"ፀሐይም ትኩሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም"** ይህ ጠቃሽ ነው *በShekinah* የክብር ደመና የተሰጣቸው መጠለያ፣ በ38ቱ በምድረ በዳ የመንከራተት ዘመናት (መዝ. 121:5-7)።

**7:17 "በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና"** ይህ የብኪ ጠቃሽ ነው የሕዝ. 34:23። የታረደው ግን የተነሣው ተቤዢ የእግዚአብሔር የመቤዠት ሥራ ዋነኛ ነጥብ እንደሆነ ተገንዘብ። የዮሐንስ 10:11ዱ መልካም እረኛ አሁን የሁሉም በጎች እረኛ ነው (ዮሐንስ 10:16)።

▣ **"ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና"** ለበረሃ ሰዎች ውኃ ዘወትር ተምሳሌትነቱ የሙብዛትና የሕይወት ነው። ይኸም የኢሳ. 49:10 (መዝ. 23:2) ጠቃሽ ነው፣ ራዕይ መጽሐፍ መዝጊያ ላይ የተደገመ 21:6፤ 22:1።

▣ **"እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል"** ይህ የመሲሐዊ ግብዣ እና የአዲሲቷ የእግዚአብሔር ከተማ ጠቃሽ ነው ኢሳ. 25:6-9 (ራዕ. 21:4)። ይህ ምንኛ የሚያጽናና ነው፣ በስደት ላይ ላሉት አማኞች፣ በዮሐንስ ጊዜና በየዘመናቱ!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. 144,000 እነማን ናቸው? መልስህን ከራዕይ ጽሑፍ አስረዳ።
2. 144,000 ቁ. 9 ላይ ካሉት ብዙ ሰዎች ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?
3. እነዚህ ተምሳሌቶች ለመተርጎም ለምን እጅግ ጠነከሩብን?
4. የምዕራፍ 6 እና 7 ዋነኛው ሐሳብ ምንድነው?
5. ምዕራፍ 7 ጣልቃ የገባ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? በመጽሐፉ ላይ ሌሎች ጣልቃ ገቦች የት ይገኛሉ?

# ራዕይ 8፡1-9፡21
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ4 | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሰባተኛው ማኅተም እና የወርቁ ጥና | ሰባተኛው ማኅተም፡ የሰባቱ መለከቶች ቀዳሚ | ሰባተኛው ማኅተም | ሰባተኛው ማኅተም | ሰባተኛው ማኅተም |
| 8:1-2 | 8:1-6 | 8:1-2 | 8:1-2 | 8:1 የቅዱሳን ጸሎት የታላቁን ቀን ምጽአት ያቀርበዋል |
| 8:3-5 | | 8:3-5 | 8:3-5 | 8፡2-5 |
| መለከቶች | ፊተኞቹ ስድስት መለከቶች | ፊተኞቹ ስድስት መለከቶች | መለከቶች | |
| | 8:7 | | | ፊተኞቹ አራት መለከቶች |
| 8፡6 | ሁለተኛው መለከት፡ | 8፡6 | 8፡6 | |
| 8:7 | መኅተሙ ተመታ | 8:7 | 8:7 | 8፡6-12 |
| | 8:8-9 | | | |
| 8:8-9 | ሦስተኛው መለከት፡ ውኆች ተመቱ | 8:8-9 | 8:8-9 | |
| | 8:10-11 | | | |
| 8:10-11 | አራተኛው መለከት፡ ሰማያት ተመቱ | 8:10-11 | 8:10-11 | |
| | 8:12 | | | |
| 8:12 | 8:13 | 8:12 | 8:12 | |
| 8:13-9:6 | አምስተኛው መለከት፡ አንበጣዎች ከጥልቁ | 8:13 | 8:13 | |
| | | የዲያብሎሳዊ አንበጦች ቁጣ | | 8:13 አምስተኛው መለከት |
| | 9:1-12 | | | |
| | | 9:1-6 | 9:1-6 | |
| 9:7-11 | ስድስተኛው መለከት፡ መልአክ ከኤፍራጠስ | 9:7-11 | 9:7-11 | 9:1-6 |
| 9፡12 | | 9፡12 | 9፡12 | 9:7-11 |
| | 9:13-21 | | | 9፡12 |
| 9:13-19 | | 9:13-19 | 9:13-19 | |
| 9:20-21 | | 9:20-21 | 9:20-21 | 9:13-21 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ vii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

ሀ. ሰባቱ መለከቶች ከሰባተኛው ማኅተም እንደቀጠሉ፣ ጥያቄ የሚሆነው፣ "በመለከቶቹ፣ ማኅተሞቹ፣ እና ጽዋዎቹ መካከል ያለው ዝምድና ምንድነው?" የሚል ነው፡፡ ከፊል፣ ካልሆነም ሙሉ ማጠቃለያ አለ፡፡ እነሱም ተመሳሳይ ጊዜና ሰዓት ይሸፍናሉ፡፡ እነሱ የተዋቀሩት ከተመሳሳይ ፈርጅ ሲሆን አንዳቸው ካንዳቸው ይለጥቃሉ፡፡ ከፊል አጠቃሎሽ ንድፈ-ሐሳብ ቀድሞ የሆነ ይመስላል፣ በሦስተኛው ክፍለ-ዘመን፣ በፔታው ቪክቶሪየስ (*ቅድመ ኒቅያ አባቶች፣* ቅጽ. 7፣ ገጽ. 344-360 ተመልከት)፡፡ እሱ የሚጠቅሰው በመለከቶች እና በጽዋዎቹ መካከል ትይዩ ግንኙነትን ብቻ ነው፡፡ አንዱ ሦስቱን ሲያወዳድር፣ አፖካሊፕቲካዊ ይመስላሉ፣ እያደጉ የሚሄዱ የተለዩ ዘይቤዎች፣ የተመሳሳይ የፍጻሜ ዘመን ጊዜ፡፡ በርግጠኝነት ማለት የሚቻለው ስድስተኛው ማኅተም (ዝከ. 6፡12-17) ወደ ፍጻሜው ሲመጣ፣ ሰባቱ ማኅተሞች (ዝከ. 11፡ 15-19) እና ሰባቱ ጽዋዎች (ዝከ. 16፡17-21) የፍጻሜውን ሁነቶች ይገልጻሉ፡፡

ለ. ዮሐንስ ምናቡን ከየት ሳለው፣ ለእነዚህ አፖካሊፕቲካዊ ራዕዮች? በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡

1. ከበርካታ የብኪ ምንባቦች ጠቃሾች አሉ፣ በተለይም ምዕራፍ 8 እና 9፣ ለግብፅ መቅሠፍት እና ለኢዩኤል 2 ያንበጣ ወረራ፡፡ ዘወትር በራዕይ፣ በዳንኤል ምናብ፣ ሕዝቅኤልና ዘካርያስ ከመሠረታዊ ዳራ፡፡
2. የአይሁድ በይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፎች፣ እንደ 1 ሔኖክ፡፡ 1 ሔኖክ በስፋት የሚታወቀው በአንደኛ ክፍለ-ዘመን ይሁዲነት ነው፣ እንዲሁም በቤተ-ክርስቲያንና በአኪ ደራስያን ተጠቅሷል (2 ጴጥሮስ 2 እና ይሁዳ)፡፡
3. የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ታሪካዊ መቼት፣ በተለይም የሮሜ የአጼ አምልኮና አጥቢያዊ ስደቶች፡፡

እንደ ዋነኛ የምናብ ምንጭ የመረጥነው አማራጭ፣ እነዚህን ሁለት ምዕራፎች እንዴት እንደምንተረጉም ይወስናል፡፡ ይሄንን ከንጉሣዊ ሮም ዳራ ጋር አነጻጽረን ብንመለከተው፣ ከሮሜ ታሪክ (ራዕይ ቀድሞ ተፈጽሟል) ጋር ይገጥማል፡፡ ከአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ቋንቋ አንጻር ብንመለከተው፣ ከተምሳሌታዊ (ሐሳባዊነት) አኳያ እጅጉን እንተረጉመዋለን፡፡ ከብኪ ትንቢቶች ጋር ብናነጻጽረው፣ ከፍጻሜ ዘመን አይሁድ መቼት ጋር እናያይዘዋለን (ወደፊት የሚፈጸም)፡፡

ሐ. እነዚህ ሁለት ምዕራፎች እየጨመሩና እየተጠናኩ የሚሄዱ የማያምኑትን ፍርድ ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም፣ አጽንኦት መሰጠት ያለበት እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ፍርዱን የሚያመጣው ለራሳቸው የመቤዠት ዓላማ ነው (ዝከ. 9:20-21፤ 14:7፤ 16:9፣ 11)፡፡ ስለዚህ፣ እነርሱ የሚሠሩት እንደ ዘዳግም 27-29 ኪዳናዊ ርግማኖች ነው፡፡

መ. እንደ ፊተኞቹ ምዕራፎች፣ ተምሳሌትነቱ እጅግ አሻሚ ነው፣ አንዳንድ አታቾች ስለ ክርስቶስ ሲገልጹ፣ ሌሎች ስለ ሰይጣን ይገልጻሉ፡፡ በዛን ዓይነት ተምሳሌታዊ ተለዋዋጭነት፣ ቀኖናዊነት ሙሉ ለሙሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ተርጓሚዎች የተጠናቀቀውን ራዕይ በአንድ ማዕከላዊ እውነት ማጠቃለል ይኖርባቸዋል፡፡ ማዕከላዊው እውነት ዝርዝሩን ትርጓሜ መምራት ይኖርበታል፣ እናም ማዕከላዊው ሥነ-መለኮታዊው ጉዳይ አጽንኦት ተሰጥቶት መቀጠል አለበት!

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

### *ራዕይ፡ 8፡1-2*

***[1]ሰባተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ፡፡ [2]በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ፥ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው፡፡***

**8፡1 "በጉም ሰባተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ"** ኢየሱስ ነው ሰባተኛውን ማኅተም የፈታ፣ ነገር ግን ከዚህ ነጥብ በኋላ መላእክት ይካተታሉ፣ ሰባቱን መለከቶች በማወጅ እና ኋላም ሰባቱን ጽዋዎች፡፡

▣ **"እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ"** ከዚህ ዝምታ ጋር የተያያዙ በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡፡ ራቢዎች የሚያያይዙት የቅዱሳን ጸሎት ይሰማ ዘንድ ከሚኖረው የጸጥታ ጊዜ ጋር ነው

1. አንዳንዶች የሚያዛምዱት ከ 2 ኢስድራስ 7፡29-31 ጋር ነው፣ ዝምታው የአዲሱ ዘመን መጀመሪያ ከሆነው
2. ሌሎች እሱን የሚያዛምዱት ከበርካታ የብኪ ምንባቦች ጋር ነው፣ ሰዎች በሚመጣው አምላክ መገኘት ፊት ዝም እንደሚሉት (ዕንባ. 2:20፤ ሶፎ. 1:7፤ ዘካ. 2:13)
3. አንዳንዶች የሚያዛምዱት ተጠናክሮ ከሚመጣው በማያምኑት ላይ ከሚሆነው ፍርድ ድራማዊ ውጤት ጋር ነው
4. ቪክቶሪነስ የሚያዛምደው ከዘላለማዊነት መጀመር ጋር ነው

**8፡2 "በእግዚአብሔር ፊት የቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ"** የተወሰነ አንቀጽ መኖሩ የሚገርም ነው፣ "ሰባቱ መላእክት፡፡" በራቢያዊ ይሁዲነት የሰባቱ መላእክት መገኘታቸው ተሰይሟል፣ በጦቢት 12፡15፤ ጁቢለስ 1፡27፣29፤ 2፡1-2፣18፤ እና 1 ሔኖክ 20፡1-7፡፡ እነርሱም ዑራኤል፣ ሩፋኤል፣ ራጉኤል፣ ሚካኤል፣ ሳራቁል ወይም ሳርኤል፣ ገብርኤል፣ እና ረምኤል ናቸው፡፡ ሌሎች ይሄንን ሐረግ የሚመለከቱት ከመሲሕ ጋር በተያያዘ ነው ("የእርሱ መገኘት መልአክ" ትይዩ የሆነ) ኢሳ. 63፡9 ላይ ወይም በሚያምጹትና መንፈስ

ቅዱሳን በሚያሳዝኑት ላይ በሚሆነው ፍርድ (ኢሳ. 63፡10)። ከዘጸአት ጋር የተያያዘው ምናልባት ከመልአኩ ጋር ይታያል ዘጸ. 23:20-23፤ 33:12-16።

▣ **"ሰባት መለከቶች ለእነርሱ ተሰጣቸው"** ሰባት መላእክት ከሰባቱ መለከቶች ጋር ተያይዘው አሉ (ዝከ. ቁ. 6)። በብኪ መለከቶች ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውሉት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለመገናኘት ነው፣ በሃይማኖታዊም ሆነ በወታደራዊ (ዘጸ. 19:16፤ ዘኁ. 10:1-10፤ ኢሳ. 27:13፤ ኤር. 4:5-9፤ ኢዩኤል 2:1፤ ሶፎ. 1:16፤ ዘካ. 9:14፤ II ኢስድራስ 6:23፣ ልዩ ርዕስ 1:10 ላይ ተመልከት)። በአኪ መለከት የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ያውጃል (ማቴ. 24:31፤ I ቆሮ. 15:52-53፤ I ተሰ. 4:16)።

**ራዕይ፡ 8፡3-5**

**[3]ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሰዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሰዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። [4]የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ። [5]መልአኩም ጥናውን ይዞ የመሰዊያውን እሳት ሞላበት ወደ ምድርም ጣለው፤ ነጐድጓድና ድምፅም መብረቅም መናወጥም ሆነ።**

**8፡3 "ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ"** ይህ ጽሑፍና 5፡8 ራቢያዊ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብን፣ ይኸውም መላእክት ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ ናቸው የሚለውን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ውሏል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን መሰሉን ዝርዝር እንዴት መተርጎም እንደሚቻል ዝም ነው ያለው። እነዚህ ተምሳሌታዊ ምንባቦች ግምታዊ የሆኑ ሥነ-መለኮታዊ ዝርዝሮችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ መዋል አይኖርባቸውም። ይህ ራዕይ ነው እንጂ የተወሰኑ መላእክትን ሚና መግለጫ አይደለም። እሱ የሚያረጋግጠው የቅዱሳን ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ እንዳለው ነው።

መሠዊያው የተገለጸው አንድም የዕጣን መሠዊያ፣ ከመጋረጃው በፊት፣ በቅዱስ ስፍራ (ዘጸ. 30፡1-10) ወይም የመሥዋዕቱን መሠዊያ ነው (ዝከ. ቁ. 5፤ 9፡13)። ሆኖም፣ ራዕዩ ምድራዊ መሠዊያ ወይም በኢየሩሳሌም ያለ መቅደስ አይደለም፣ ነገር ግን በሰማይ ያለ የእግዚአብሔር ዙፋን ክፍል ነው (ዕብ. 8:2፤ 9:11፣24)። የዕጣኑ መሠዊያ ለዚህ ዐውደ-ጽሑፍ በተሻለ ይስማማል።

▣ **"ከቅዱሳን ጸሎት ሁሉ ጋር"** ይህ በትክክል የትኛውን የቅዱሳን ወገን እንደሆነ ርግጠኛ አይደለም፣ ነገር ግን ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር የሕዝቡን መሻት እንደሚያውቅና ምላሽ እንደሚሰጥ ነው (ዘጸ. 3፡7)። ዕጣን የጸሎት ተምሳሌት ነው (መዝ. 141:2፤ ራዕ. 5:8) ምክንያቱም ጢሱ ከሚታየው ዓለም ወደማይታየው ዓለም ሽቅብ ሄዶ ስለሚሰወር ነው።

ለ"ቅዱሳን" ልዩ ርዕስ፡ ቅዱሳን 5፡8 ላይ ተመልከት።

**8፡4** በሌዋውያን መጽሐፍ ሁሉ ዕጣን ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ ያሻቅባል፣ ስለዚህ፣ ዕጣን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይወክላል።

**8፡5 "መልአኩም ጥናውን ይዞ የመሰዊያውን እሳት ሞላበት ወደ ምድርም ጣለው"** ይህ የሕዝ. 10፡2 ጠቃሽ ነው። ፍም ለዕጣን መሠዊያ ከመጋረጃው በፊት በመጀመሪያ ይወሰድ የነበረው ከመሥዋዕቱ መሠዊያ ላይ ነው፣ ከመሠዊያው ፊት ለፊት (ዝከ. 9:13፤ ሌዋ. 16:11-13)። እነዚህ የመሠዊያው ተምሳሌቶች ናቸው፣ ትርጉማቸው ተለዋዋጭ የሆነ። ቁልፉ ሥነ-መለኮታዊ አስተሳሰብ፣ ይህ የሚሆነው በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት ነው።

▣ **"ከዚያም የነጎድጓድ ድምጽ ሆነ"** ይህ ዓይነቱ ሥጋዊ ክስተት ዘወትር የሚያያዘው ከያህዌ መገኘት ጋር ነው (ዝከ. 4:5፤ 11:19፤ 16:18፤ ዘጸ. 19:16-19፤ መዝ. 18:10-13)።

**ራዕይ፡ 8፡6**

**[6]ሰባቱንም መለከት የያዙ ሰባቱ መላእክት ሊነፉ ተዘጋጁ።**

**8፡1-6** እነዚህ ቁጥሮች በጸጥታው ጊዜ የሚሆኑትን ድርጊቶች ይወክላሉ።

**ራዕይ፡ 8፡7**

**[7]ፊተኛውም መልአክ ነፋ፤ ደምም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት ሆነ፥ ወደ ምድርም ተጣለ፤ የምድርም ሲሶው ተቃጠለ የዛፎችም ሲሶው ተቃጠለ የለመለመም ሣር ሁሉ ተቃጠለ።**

**8፡7 "ደምም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት ሆነ"** አብዛኞቹ ምስሎች የተወሰዱት ከግብፃውያን መቅሠፍት ነው። ይህ ምንባብ የዘጸ. 9፡ 24 ጠቃሽ ነው። እንዲሁም ደግሞ ይህ ከሕዝ. 38፡22 ተወስዷል ማለት ይቻላል፣ የጎግ ወራሪ ሠራዊት መገልበጡ።

▣ **"የምድርም ሢሶው ተቃጠለ"** ይህ የተወሰነ፣ ግን ዋነኝነት ያለው መቶኛ በቀጣዮቹ ጥቂት ምዕራፎች ተደጋግሞ ተጠቅሷል (ዝከ. 8:7-8፣9፣10፣11፣12፤ 9:15፣18፤ 12:4)። ሁለተኛው ተለጣጣቂ ፍርድ ከመጀመሪያው እጅግ የተጠናከረ ነው (ዝከ. 6፡8፣ እዚያም አንድ አራተኛው የተጠቀሰበት)። ያህዌ አሁንም ገና ኃጢአተኛውን የሰው ልጅ ለመድረስ እየሞከረ ነው፣ በሥጋዊ መቅሠፍት አማካኝነት (ዘጸአት 7-11፤ ዘዳግም 28-29)፣ እነርሱ ግን በንስሐና በእምነት ምላሽ አልሰጡም!

▣ **"የለመለመም ሣር ሁሉ ተቃጠለ"** ይህ የሚያመለክተው የለምለም ሣር ሁሉ መቃጠልን ነው፣ በሢሶ አካባቢ፣ የለመለመ ሣር 9፡4 ላይ በመጠበቁ።

**ራዕይ፡ 8፡8-9**

**[8]ሁለተኛውም መልአክ ነፋ፤ በእሳት የሚቃጠል ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባሕር ተጣለ፤ የባሕርም ሲሶው ደም ሆነ [9]በባሕርም ከሚኖሩ ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች ሲሶው ሞተ የመርከቦችም ሲሶው ጠፋ።**

**8፡8 "በእሳት የሚቃጠል ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባሕር ተጣለ"** አሁንም በድጋሚ ጉዳዩ የዮሐንስ ምናብ ምንጭ ነው—ሮሜ፣ አይሁድ በይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ወይም ብኪ።

1. ብኪ ቢሆን፣ እንግዲያውስ መዝ. 46፡2 ወይም ዘጸ. 7፡20-21 ማጣቀሻ ይሆናል።
2. የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ቢሆን፣ እንግዲያውስ ማጣቀሻው 1 ሔኖክ 18፡13-16 ወይም የሲቢሊኒ ንግርት 5፡158 ሊሆን ይችላል።
3. ሮሜ ከሆነ እንግዲያውስ ሊሆን የሚችለው የቬሱቪዩስ ተራራ ፍንዳታ ታሪካዊ ጠቃሽ ነው፣ እሱንም አይሁድ እንደ እግዚአብሔር ፍርድ፣ በሮም ላይ እንደሚሆን፣ ኢየሩሳሌምን ስላጠፉ አድርገው ይወስዱታል።

የዮሐንስ ዘይቤ ትክክለኛ ምንጭ በርግጠኝነት አይታወቅም፣ እነሱ ግን እንደ እግዚአብሔር ቁጣ ይወስዱታል፣ በዐመጸኞቹ ፍጡራን ላይ፣ የመዋጀትን ዓላማ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ።

▣ **"የባሕርም ሢሶው ደም ሆነ"** ይህም ሌለኛው ጠቃሽ ነው፣ ለግብፃውያን መቅሠፍት (ዘጸ. 7፡20-21)።
**8፡9 "...ከፍጥረቶች ሢሶው ሞተ"** ይህም የግብፃውያን መቅሠፍት ሌለኛው ጠቃሽ ነው (ዘጸ. 7፡21)።

▣ **"የመርከቦችም ሢሶው ጠፋ"** ይህ በብኪ ምንም ትይዩ የለውም፣ በአፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ፣ ወይም በአንደኛው ክፍለ-ዘመን የሮሜ ሥነ-ጽሑፍ። ግልጽ የሆነው ንግድ እንደሚስተጓጎልና የዕቃዎችና የምግብ እጥረት እንደሚኖር ነው። እሱም የእግዚአብሔርን የተወሰነ፣ እያደገ የሚሄድ ፍርድ ያረጋግጣል። ፍርዱ ይጠናከራል (1/4 በማኅተሞቹ፣ 1/3 በመለከቶቹ) እስከ ጽዋዎቹ ድረስ የንስሐ ጊዜ እስከሚያልፍ፣ እና አጠቃላይ፣ የተጠቃለለ ፍርድ ይሆናል።

**ራዕይ፡ 8፡10-11**

**[10]ሦስተኛውም መልአክ ነፋ፤ እንደ ችቦም የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ፥ በወንዞችና በውኃም ምንጮች ሲሶ ላይ ወደቀ። የኮከቡም ስም እሬቶ ይባላል። [11]የውኃውም ሲሶ መራራ ሆነ መራራም ስለተደረገ በውኃው ጠንቅ ብዙ ሰዎች ሞቱ።**

**8፡10 "ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ"** ይህ ምናልባት የኢሳ. 14፡12 ጠቃሽ ይሆናል። ብዙዎች ይሄንን ከራዕ. 6፡13 ወይም 9፡1 ጋር ሊያዛምዱት ሞክረዋል፣ ነገር ግን ይህ ምናልባት የዮሐንስን ምናብ እጅግ አጥብቆ መቀለፍ ይሆናል። እያንዳንዱን ዝርዝር ለመተርጎም ከመሞከር ተጠንቀቁ። ይህ ድራማዊ ምናብ ነው። ዘወትር በአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ የወደቀ ኮከብ የሚያመለክተው መልአክን ነው (ማለትም፣ 9፡1)።

**8፡11 "የኮከቡም ስም እሬቶ ይባላል"** በብኪ እሬቶ የሚያያዘው ከግልሙትና ጋር ነው (ዘዳ. 29፡17-18)። እሱም ደግሞ ከመርዝ ጋር ተደባልቆ ይታያል፣ እና ስለዚህ ገዳይ ነው (ኤር. 9፡15፤ 23፡15፤ አሞጽ 6፡12)። እሬቶ በራሱ (ዝኪ. አእት)፣ መራራ ነበር፣ ገዳይ ሳይሆን። እዚህ ለመለኮታዊ ፍርድ ዘይቤ ነው።

ዘመናዊዎቹ የራዕይን ዝርዝሮች ወደ ራሳቸው ቀን ለመግፋት ከሚሞክሩበት ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው፣ የሩሲያ ቼርኖቤል የኒኩሌር ተቋምን ማስረገጥ ነው፣ እሱም መቅለጥ የደረሰበትን፣ እንደ ተፈጸመ ትንቢት መውሰድ ነው፣ ምክንያቱም ስሙ በሩስያ እሬቶ ስለሆነ። ይህ መሰሉ መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም ልምምድ፣ በጧት ጋዜጦች ላይ በመንተራስ፣ ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት የተለመደ ነው፣ እኛም ተመሳሳይ አገባብ እንዳንከተል ያስጠነቅቀናል!

**ራዕይ፡ 8፡12**

**[12]አራተኛውም መልአክ ነፋ፤ የፀሐይ ሲሶና የጨረቃ ሲሶ የከዋክብትም ሲሶ ተመታ፥ የእነዚህ ሲሶ ይጨልም ዘንድ፥ የቀንም ሲሶው እንዳያበራ፥ እንዲሁም የሌሊት።**

**8፡12** ጨለማ ዘወትር የእግዚአብሔር ፍርድ ምልክት ነው (ዘጸ. 10፡21፤ ኢሳ. 13፡10፤ 34፡4፤ 50፡3፤ ሕዝ. 32፡7-8፤ ኢዩኤል 2፡2፣10፣31፤ 3፡15፤ አሞጽ 5፡18፤ ማርቆስ 13፡24)። ሰማያዊ አካላት እንደ መንፈሳዊ ኃይላት ዘወትር ይመለኩ ነበር። እግዚአብሔር ነው የፈጠራቸው (ዘፍ. 1፡14-19፤ ኢሳ. 40፡26)፤ ሰየማቸው (መዝ. 147፡4፤ ኢሳ. 40፡26)፤ ይቆጣጠራቸዋል (ኢሳ. 48፡13)፤ እነርሱም ያመሰግኑታል (መዝ. 148፡3)።

**ራዕይ፡ 8፡13**

**[13]አየሁም፥ አንድም ንስር በሰማይ መካከል እየበረረ በታላቅ ድምፅ። ሊነፉ ያላቸው የሦስቱ መላእክት መለከት ስለሚቀረው ድምፅ በምድር ላይ ለሚኖሩት ወዮላቸው፥ ወዮላቸው፥ ወዮላቸው ሲል ሰማሁ።**

**8፡13 "አየሁም፥ አንድም ንስር በሰማይ መካከል እየበረረ በታላቅ ድምፅ ሲል ሰማሁ..."** ኪጀት "መልአክ" አለው፣ በ "ንስር" ምትክ፣ ይህ ግን የመጣው በኋለኛው ዘጠነኛ ክፍለ-ዘመን የግሪክ እጅ ጽሑፍ ላይ ነው። ሁለቱም ሲናይቲከስ (ℵ) እና አሌክሳንድሪነስ (ሀ) "ንስር" አላቸው። ይህም ሊያመለክት የሚችለው ጥንብ አንሣ (ወይም ንስር) ነው፣ እሱም ዘወትር የአራጅ ተምሳሌት የሚሆነው (ሕዝ. 17:3፤ ዕን. 1:8፤ ማቴ. 24:28፤ ሉቃስ 17:37)

1. ለፍርድ ትዕይንት ጠቃሽ ነው ሕዝ. 39:17-20፤ ሆሴ. 8:1 ላይ
2. በይነ ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ለሆነው II ባሮክ 77:21-22 ጠቃሽ ነው፣ ይኸውም ጥንብ አንሣ መልእክት ይልካል፣ በአምላክ ለተጎዳ ሕዝብ
3. የሮሜ ሠራዊት ደረጃ በንስር ጫፍ ይደረግበት ነበር

"በሰማይ መካከል መብረር" ሌለኛው ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፣ ለነጣቂ ወፎች በምድር ላይ ለሚያንዣብቡት (ራዕ. 14:6፤ 19:17)።

▣ ***"ወዮላቸው፣ ወዮላቸው፣ ወዮላቸው"*** ይህ ምናልባት ከሚመጡት ሦስቱ የመጨረሻ መለከቶች ጋር ይያያዛል (ዝከ. 9:12፤ 11:14፤ 12:12)፤ እሰ ምናልባት የመጠናከር ተምሳሌት ሊሆን ይችላል (እንደ 4፡8ቱ "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ")። በዕብራይስጥ ሦስትዮሽ ድግግም የመጨረሻው ማወዳደሪያ ነው (እንደ ኢሳ. 6፡3 ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ)። በብኪ "ወየው" የሚያመለክተው የተወሰነ ቅኔያዊ ሙሾ ነው፣ ከሞትና ከፍርድ ጋር የሚዛመድ።

▣ ***"በምድር ለሚኖሩት"*** ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ያልተዋጁትን ነው (ዝከ. 3:10፤ 6:10፤ 11:10፤ 13:8፤ 17:2)።

***ራዕይ 9***

**ራዕይ፡ 9፡1-6**

**[1]አምስተኛውም መልአክ ነፋ፤ ከሰማይም ወደ ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ አየሁ፥ የጥልቁም ጉድጓድ መክፈቻ ተሰጠው። [2]የጥልቁንም ጉድጓድ ከፈተው፤ ጢስም ከታላቅ እቶን እንደሚወጣ ጢስ ሆኖ ከጉድጓዱ ወጣ ፀሐይና አየርም በጉድጓዱ ጢስ ጨለሙ። [3]ከጢሱም አንበጣዎች ወደ ምድር ወጡ፥ የምድርም ጊንጦች ሥልጣን እንዳላቸው ሥልጣን ተሰጣቸው። [4]የእግዚአብሔርም ማኅተም በግምባራቸው ከሌለባቸው ሰዎች በቀር በምድር ያለውን ሣር ቢሆንም ወይም ማናቸውንም የለመለመ ነገር ወይም ማናቸውንም ዛፍ እንዳይጐዱ ተባለላቸው። [5]አምስትም ወር ሊሣቅዩአቸው ተሰጣቸው እንጂ ሊገድሉአቸው አይደለም፤ እነርሱም የሚሣቅዩት ሥቃይ ጊንጥ ሰውን ነድፎ እንደሚሣቅይ ነው። [6]በዚያም ወራት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ አያገኙትምም፥ ሊሞቱም ይመኛሉ ሞትም ከእነርሱ ይሸሻል።**

**9፡1 "ከሰማይም ወደ ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ አየሁ"** በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች ነበሩ፣ ስለዚህ ሰውኛ ኮከብ ማንነት፣ እርሱም መልአክ ተብሎ የሚጠራ።

1. ግሡ የተጠናቀቀ ጊዜ በመሆኑ ምክንያት፣ እሱም ሰይጣንን ያመለክታል፣ ባለፈው ጊዜ የወደቀና በቀጣይም ከሰማይ የሚወድቅ (ኢሳ. 14:12፤ ሕዝ. 28:16፤ ሉቃስ 10:18፤ ራዕ. 12:9)
2. ከዐውደ ጽሑፉ አኳያ ሌለኛ አገልጋይ መልአክ በእግዚአብሔር ፍርድ ተካቶ ይሆናል (ዝከ. 20፡1)

መላእክት እንደሚወድቁ ከዋክብት በአይሁድ በይነ ኪዳናዊ ጽሑፍ ላይ ዘወትር ይገኛሉ።

▣ **"የጥልቁ መክፈቻ ተሰጠው"** "ቁልፍ" 1፡18 እና 20፡1 ላይ ተጠቅሷል። እሱም ተምሳሌት የሚያደርገው ሥልጣንን ነው። እግዚአብሔር በሰይጣን ሠራዊት ላይ ሥልጣናዊ ፍርዱን ይሰጣል።

ጥልቁ የግሪክ ቃል ሲሆን ፍችው "ጥልቅ" ነው፣ አሉታዊ የፊት-ቅጥያ ያለው።

1. እሱም በሴፕቱዋጂንት ጥቅም ላይ ውሏል (የብኪ የግሪክ ትርጉም) ዘፍ. 1:2፤ 7:11፤ Ps. 42:7፤ 107:26 ለፍጥረት ውኃዎች ጥልቀት።
2. መዝ. 71፡20 ላይ እሱ የሚያመለክተው የሙታን መቆያ ስፍራ ነው።
3. ይህም ደግሞ ሔኖክ 18:12-16፤ 21:7-10፤ 108:3-6፣ ላይ ትክክል ነው፣ እዚያም ሁለቱም ጊዜያዊ እና የመጨረሻ እስር ቤት ነው፣ የወደቁ መላእክት።
4. እሱም "*tartarus*" (እንጦርጦስ) ተመሳሳይ ይመስላል (II ጴጥ. 2:4 እና I ሔኖክ 21:7)፣ ክፉ መላእክት የሚታሰሩበት ስፍራ (ሉቃስ 8:31፤ ይሁዳ 6፤ ራዕ. 11:7፤ 17:8፤ 20:1-3፤ እና I ሔኖክ 10:4፤ 86:1፤ 88:1፤ ጁቢሊስ 5:6-11)።
5. ጳውሎስ ይሄን ቃል (ጥልቁ) ሮሜ. 10፡7 ላይ ተጠቅሞበታል፣ እንደ ሙታን ስፍራ (ኢሳ. 24:21-22)።
6. ኋላ ላይ ራቢዎች ያሉት እሱ *የሲኦል/ገሃነም* መልካም ያልሆነው ክፍል ነው (ልዩ ርዕስ 1፡18 ላይ ተመልከት)።

▣ **"ተሰጠው"** ተለጣጣቂ የሆኑ ተገብሯዊ ግሦች በሁለቱም ምዕራፍ 8 እና 9 ይገኛሉ፣ እነርሱም እግዚአብሔር ሁለቱንም ታሪክንና አጋንንታዊን መቆጣጠሩን (ዝከ. 8፡3፣7፣8፣11፣12፤ 9፡1፣3፣4፣5)። የአይሁድ ጸሐፍት ዘወትር ተገብሯዊ ድምጾትን ይጠቀማሉ፣ የመለኮትን ድርጊቶችን በተዘዋዋሪ ለማሳየት።

**9፡2 "ጢስም ከታላቅ እቶን እንደሚወጣ ጢስ ሆኖ ከጕድጓዱ ወጣ"** ይህ ቃል በብኪ በበርካታ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፡

1. እሱም ሰዶምና ገሞራ ላይ የነበረውን ፍርድ ይጎዳኛል (ዘፍ. 19፡28)
2. እሱም እግዚአብሔር በሕዝብ ላይ ያለውን ፍርድ ይጎዳኛል (ኢሳ. 34፡10)
3. እሱም በሲና ተራራ ላይ የእግዚአብሔርን መገኘት ይጎዳኛል (ዘጸ. 19፡18)

**9፡3 "አንበጣዎች"** እነዚህ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውሉት እንደ እግዚአብሔር ቁጣ ተምሳሌት ነው (ዘጸ. 10፡12-15፤ ኢዩኤል 1፡4፤ 2፡1) ወራሪ ሠራዊትን ተምሳሌት ከማድረጋቸው የተነሣ (ዝከ. ቁ. 7፤ ኢዩኤል. 2፡4-5፣ 7-9)።

**9፡4 "በምድር ያለውን ሣር ቢሆንም ወይም ማናቸውንም የለመለመ ነገር ወይም ማናቸውንም ዛፍ እንዳይጐዱ ተባለላቸው"** እነዚህ ሰይጣናዊ ኃይላት በቅጣታቸው የተወሰኑ ናቸው። እነርሱም ማንኛውንም ተክል ሊያጠፉ አይችሉም እንዲሁም የማያምኑትን ያሠቃያሉ እንጂ መግደል አይችሉም (ዝከ. ቁ. 5፤ 7፡4)፤ አማኞች በእግዚአብሔር ይጠበቃሉ (በግብፅ መቅሠፍት ላይ እንደነበሩት)።

▣ **"የእግዚአብሔር ማኅተም በግንባራቸው"** 7፡2 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት። እሱም ለሕዝ. 9፡4 ጠቃሽ ነው።

**9፡5 "አምስት ወራት"** አንዳንዶች ይሄን የጊዜ ወሰን የሚተረጕሙት ከአንበጣዎች በሕይወት የመቆያ ጊዜ ጋር ነው። ሆኖም፣ ሊሆን የሚችለው የቁጥር አስር ግማሽ ነው፣ ይኸውም ለተወሰነ ፍርድ ሌላ ዘይቤ (ዝከ. 6፡6፣8፤ 8፡7-12)።

▣ **"ጊንጥ እንደሚያሠቃይ"** የጊንጥ መውጊያ ሌለኛው የብኪ ዘይቤ ነው (II ዜና. 10፡11፣14)።

**9፡6** ይህ ለ6፡15-16 ቀጥተኛ ትይዩ ነው፣ እሱም ምናልባት ተጨማሪ የፍጻሜው ማጠቃለያ ንድፈ-ሐሳብ ማስረጃ ነው፣ በማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ መካከል። ይህ ምናልባት የእምነተ ቢሶቹ፣ አመንዝራ የኢየሩሳሌም አይሁዶች ፍርድ ጠቃሽ ነው የኤር. 8፡2-3።

## ራዕይ፡ 9፡7-11

**[7]የአንበጣዎቹም መልክ ለጦርነት እንደ ተዘጋጁ ፈረሶች ነው፥ በራሳቸውም ላይ ወርቅ እንደሚመስሉ አክሊሎች ነበሩአቸው፥ ፊታቸውም እንደ ሰው ፊት ነበረ፤ [8]የሴቶችን ጠጕር የሚመስል ጠጕር ነበራቸው፥ ጥርሳቸውም እንደ አንበሳ ጥርስ ነበረ፥ [9]የብረት ጥሩር የሚመስልም ጥሩር ነበራቸው፥ የክንፋቸውም ድምፅ ወደ ጦርነት እንደሚጋልቡ እንደ ብዙ ፈረሶች ሰረገላዎች ድምፅ ነበረ። [10]እንደ ጊንጥም ጅራት ያለ ጅራት አላቸው በጅራታቸውም መውጊያ አለ፥ ሰዎችንም አምስት ወር እንዲጐዱ ሥልጣን አላቸው። [11]በእነርሱም ላይ ንጉሥ አላቸው እርሱም የጥልቅ መልአክ ነው፥ስሙም በዕብራይስጥ አብዶን በግሪክም አጶልዮን ይባላል።**

**9፡7-9 "የአንበጦቹም መልክ"** የእነዚህ አንበጣዎች አካላዊ ገለጻ ኢዩኤል 2፡4-9 ላይ ካለው ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው እንዲሁም ደግሞ ከታወቀው የዓረብኛ ምሳሌ ጋር፣ "አንበጣዎች የፈረስን የመሰለ ራስ አላቸው፣ ያንበሳን የመሰለ ጡት፣ የግመልን የመሰሉ እግሮች፣ እባብን የመሰለ አካል፣ እና የሴት ፀጉርን የመሰለ አንቴና።"

ይህ በገሀድ የኢዩኤል መጽሐፍ ጠቃሽ ነው፣ ከእሱ ገለጻ ላይ:

1. የአንበሳ ጥርስ (ዝከ. ቁ. 8፤ ኢዩኤል 1፡6)
2. ወደ ውጊያ የሚሄዱ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሠረገሎችና ፈረሶች (ዝከ. ቁ. 9 እና ኢዩኤል 2፡5)

**9፡8** አንዳንዶች ይሄንን የሚመለከቱት ከፐርሺያ የፈረሰኛ ሠራዊት ነው፣ ረጅም ፀጉር ካላቸው። እነዚህም ፈረስ ላይ ሆኖ በቀስት በመዋጋት ጥበብ የታወቁ ነበሩ። ሮማውያን እነዚህን አረመኔያዊ ወራሪዎች ይፈሯቸው ነበር።

**9፡11 "በእነርሱም ላይ ንጉሥ አላቸው"** ምሳሌ 30፡27 አንበጣዎች ንጉሥ የላቸውም ይላል፣ ይህ ግን ለዲያብሎሳዊ ሠራዊት ነው፣ ለአካላዊ አንበጣ ሳይሆን።

▣ **"የጥልቁ መልአክ"** "ጥልቁ" የሚለው ቃል የሙታንን ስፍራ ያመለክታል (ዝከ. 9፡1፣2፣11፤ 11፡7፤ 17፡8፤ 20፡1፣3፤ እና ሮሜ. 10፡7)። 9፡1 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ስሙም በዕብራይስጥ አብዶን በግሪክም አጶልዮን ይባላል"** የዕብራይስጡ (አራማዊ) ቃል ፍችው "ጥፋት" ሲሆን የግሪኩ ቃል "አጥፊ" ነው። የዕብራይስጡ ቃል ሲኦል በመባል ይታወቃል፣ የሙታን ስፍራ (ኢዮብ 26፡6፤ 29:22፤ 31:12፤ መዝ. 88፡11 ምሳ. 15፡11፤ 27:20)።

ሮበርት ቢ ጊርድልስቶን ስለዚህ ቃል አስደናቂ አስተያየት አለው፣ *የብሉይ ኪዳን ተመሳስሎ* በሚለው መጽሐፉ: "ይህ ቃል "መጥፋት" ን ይሰጣል፤ ለመቶ ምንባቦች ያህል። ለግለሰቦች ጥቅም ላይ ሲውል እሱ የሚያጎላው ሞትን ነው፣ በመሬት ጥቅም ላይ ሲውል አንድምታው ጥፋት ነው (ገጽ 273)።

ኢዮብ 28፡22 ላይ ከሞት ጋር ሰውኛ ሆኗል። ይኸው ሰውኛነት ደግሞ የሙት ባሕር ጥቅሎች እና የበይነ-ኪዳናዊ አይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ባሕርይ ነው። ይህ ያልተለመደ ይመስላል ምክንያቱም በብኪ የሞት መልአክ የያህዌ አገልጋይ ነው (ዘጸ.

12:23፤ ኢዮብ 15:21) ወይም የያህዌ ሰውኛ (ዘጸ. 12:13፣29)። እዚህ ግን መልአኩ የሚመስለው የታሰሩ ኢጋንንታዊ ሠራዊት አለቃ ነው። ይህም ሌለኛው ማሳያ መንገድ ነው፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች እንደሚቆጣጠር።

አንዳንዶች እንዲያውም የሚያስረግጡት እንደ ንጉሥ ኔሮ እና ዶሚቲአን ነው፣ ሥጋ የለበሱ አፖሎ እንደሆኑ፣ እናም ይህ የግሪክ ስም የተበላሸ ቅርጽ ያለው ነው፣ ከአፖልዮንም ጋር ጠቃሽ የሆነ። ይህንን ለመደገፍ ሁለት አነስተኛ ማስረጃዎች አሉ፣

1. አንበጣዎች የአፖሎ ተምሳሌት ናቸው
2. አፖሎ የሚለው ቃልና አፖልዮን ሁለቱም የመጡት ከተመሳሳይ የግሪክ ሥር ነው

**ራዕይ፡ 9፡12**

[12]***ፊተኛው ወዮ አልፎአል፤ እነሆ፥ ከዚህ በኋላ ገና ሁለት ወዮ ይመጣል።***

**9፡12** ይህ ቁጥር ከ11፡14 እና 12፡2 ጋር ይያያዛል።

**ራዕይ፡ 9፡13-19**

[13]***ስድስተኛውም መልአክ ነፋ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ካለ በወርቅ ከተሠራ መሠዊያ ቀንዶች አንድ ድምፅ ሰማሁ፥*** [14]***መለከትም ያለውን ስድስተኛውን መልአክ። በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ የታሰሩትን አራቱን መላእክት ፍታቸው አለው።*** [15]***የሰዎችንም ሲሶ እንዲገድሉ ለሰዓቱና ለቀኑ ለወሩም ለዓመቱም ተዘጋጅተው የነበሩ አራቱ መላእክት ተፈቱ።*** [16]***የፈረሰኞችም ጭፍራ ቁጥር እልፍ ጊዜ እልፍ፥ እልፍ ጊዜ እልፍ ነበረ፤ ቁጥራቸውን ሰማሁ።*** [17]***ፈረሶቹንና በእነርሱም ላይ የተቀመጡትን እንዲሁ በራእይ አየሁ፤ እሳትና ያክንት ዲንም የሚመስል ጥሩር ነበራቸው፤ የፈረሶቹም ራስ እንደ አንበሳ ራስ ነበረ፥ ከአፋቸውም እሳትና ጢስ ዲንም ወጣ።*** [18]***ከአፋቸውም በወጡት በእሳቱና በጢሱ በዲኑም በእነዚህ ሦስት መቅሰፍቶች የሰዎቹ ሲሶ ተገደለ።*** [19]***የፈረሶቹ ሥልጣን በአፋቸውና በጅራታቸው ነውና፤ ጅራታቸው እባብን ይመስላልና፥ ራስም አላቸው በእርሱም ይጎዳሉ።***

**9፡13 "*በወርቅ ከተሠራ መሠዊያ ቀንዶች* ከአራቱም ማዕዘን አንድ ድምፅ ሰማሁ"** ይህ በመሠዊያው ላይ የዕጣን መሠዊያው ጠቃሽ ነው (ዘጸ. 30፡2፣3፣10)። በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ሁለት መሠዊያዎች አሉ፡ *መሥዋዕት ማቅረቢያው መሠዊያ*፣ እሱም የሠማዕታት ነፍሶች የሚገኙበት (ዝኪ. 6፡9-11)፣ እና *የዕጣን መሠዊያ* የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጸሎት የሚኖርበት (ዝኪ. 8፡3-5)። ቀንዶች የብኪ የኃይል ተምሳሌት ናቸው። ሁለቱም የዕጣኑ መሠዊያና የመሥዋዕቱ መሠዊያ ቀንዶች አሏቸው። 8፡3 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**9፡14 "'*በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ የታሰሩትን አራቱን መላእክት ፍታቸው*'"** የአንደኛውን ክፍለ ዘመን ታሪካዊ ጠቃሽ የሚፈልጉ ይሄንን የሚመለከቱት እንደ ፋርስ ሠራዊት ነው፣ ከኤፍራጥስ ወንዝ ባሻገር (ማለትም፣ የሮሜ ኢምፓየር ወሰን፣ ዝኪ. 1 ሔኖክ 56፡5-8። ሆኖም ሌሎች የሚመለከቱት እንደ ብኪ ጠቃሽ ነው፣ በዘካ. 1፡8 እና 6፡1-8 እንደሚገኙት አራት አፖካሊፐቲካዊ ፈረሶች፣ እነዚህ አራት መላእክት እግዚአብሔር ለሾማቸው አገልጋዮች ሌለኛ ዘይቤ ይመስላሉ፣ በወደቀው፣ ዐመጸኛው ዓለም ላይ ፍርድን የሚያመጡ (ዝኪ. 7፡1)። ሆኖም፣ እነዚህ መላእክት በመታሰራቸው ምክንያት፣ የክፉ መላእክት ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል (ይሁዳ ቁ. 6)። እነዚህ መላእክት በሰው ልጅ ሢሶ ላይ ሞትን ያመጣሉ (ዝኪ. ቁ. 18)።

የኤፍራጥስ ወንዝ ሰሜናዊው ክፍል፣ ከውኃው ጋን በስተ ሰሜናዊ ምስራቅ የተስፋይቱ ምድር ወሰን ነበር (ዘፍ.15፡18፤ ዘዳ. 1፡7፤ 11፡24፤ ኢያ. 1፡4)።

**9፡15 "ለሰዓቱና ለቀኑ ለወሩም ለዓመቱም ተዘጋጅተው የነበሩ አራቱ መላእክት ተፈቱ"** "ሰዓት" ከሚለው ቃል ጋር የተወሰነ አንቀጽ አለ፣ ይኸውም የዚህ የተጠናቀቀ ሐረግ መወሰንን ያመለክታል። ይህ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና ታሪክን እንደሚቆጣጠር ማጣቀሻ ነው (1 ሔኖክ 92፡2)። ይህ በመከራ ውስጥ ለሚያልፉት ትልቅ ዕርዳታ ነው።

**9፡16 "የፈረሰኞችም ጭፍራ ቁጥር እልፍ ጊዜ እልፍ፥ እልፍ ጊዜ እልፍ ነበረ (*ሁለት መቶ ሚሊዮን*)"** ይህ የዲያብሎሳዊ ጭፍራ ተምሳሌታዊ ቁጥር ነው፣ የተንሰራፋው ያልተዋጀ የሰው ልጅ። ይህ ቁጥር እግዚአብሔርን ከሚያገለግሉት አእላፍ መላእክት ጋር ሊወዳደር ይችላል (ዝኪ. 5፡11፤ ዘዳ. 33፡2፤ መዝ. 68፡17፤ ዳን. 7፡10፤ ዕብ. 12፡22፤ ይሁዳ ቁ. 14)።

እንደገናም፣ ይሄንን ከዘመናዊው የቻይና ሕዝብ ጋር ለማነጻጸር መሞከርም ሌለኛው ምሳሌ ነው፣ ዘይቤአዊ ጽሑፍን ከአሁኑ ታሪክ ጋር የማያያዝ። የክርስቲያኖች መጻኢውን የማወቅ ፍላጎት እና እርስ በርስ የተለየ እውቀት ለማግኘት መነሣሣት የአሁኑ ጊዜ ችግር ነው።

**9፡17-19 "*ፈረሶቹንና በእነርሱ ላይ የተቀመጡባቸው*"** ተከታዩ ገለጻ ፈረሶቹንና ጋላቢዎቹን እንደ አንድ ምድብ ነው የሚመለከቷቸው። ዋነኞቹ የሞትና የጥፋት ኃይላት ፈረሶቹ ራሳቸው ናቸው (ዝኪ. ቁ. 19)። የፈረሶቹ ቀለም— ቀይ (እሳት)፣ ሰማያዊ (ጭስማ) እና ቢጫ (ድኝ)— ይህንን የተለየ ሰይጣናዊ ጭፍራ ይገልጸዋል፣ እንደ ሦስቱ መቅሠፍቶች እሳት፣ ሰማያዊ ጭስ፣ እና ድኚ፣ ቁ. 18 ላይ የተጠቀሱት።

**ራዕይ፡ 9፡20-21**

[20]***በእነዚህም መቅሠፍቶች ያልተገደሉት የቀሩቱ ሰዎች ለኢጋንንትና ያዩ ወይም ይሰሙ ወይም ይሄዱ ዘንድ ለማይችሉ ከወርቅና***

**ከብር ከናስም ከድንጋይም ከእንጨትም ለተሠሩ ለጣዖቶች እንዳይሰግዱ ስለ እጃቸው ሥራ ንስሐ አልገቡም፤ [21]ስለ መግደላቸውም ቢሆን ወይም ስለ አስማታቸው ወይም ስለ ዝሙታቸው ወይም ስለ ስርቆታቸው ንስሐ አልገቡም።**

**9፡20 "በእነዚህም መቅሠፍቶች ያልተገደሉት የቀሩቱ ሰዎች... ስለ እጃቸው ሥራ ንስሐ አልገቡም"** ይህ ግልጽ የሆነ፣ የማያሻማ መግለጫ ነው፣ ስለእነዚህ መቅሠፍቶች የመዋጀት ዓላማ (ዝከ. ቁ. 21፤ 14:6-7፤ 16:9፣11፤ 21:7፤ 22:17)።

እግዚአብሔር በግብፅ መቅሠፍቶቹን ለማነሣሣት እንደተጠቀመበት (1) ግብፃውያን እሱን አምነው እንዲያገለግሉት እና (2) እስራኤላውያን ታማኝ ሆነው እንዲያገለግሉት (ዘዳግም 27-28)፣ እንዲሁ እነዚህ ተመሳሳይ መቅሠፍቶች የሚሆኑት የማያምነውን የሰው ልጅ ወደ ፈጣሪያቸው ለመመለስ ነው፣ እነርሱ ግን እምቢ ብለዋል። የእነርሱ እምቢተኝነት አለማመን ቋሚ የዐመጸኝነታቸው አቋም ሆነ (ሮሜ. 1፡24፣26)።

▣ **"ለእጃቸው ሥራ"** ይህ የግልሙትና ጠቃሽ ነው (ማለትም፣ የአጋንንት አምልኮ፣ ዘዳ. 32:17፤ መዝ. 106:37፤ 1 ቆሮ. 10:20) እሱም በብኪ ተዘውትሮ የተጠቀሰ (ዘዳ. 4:28፤ 28:36፣64፤ 29:17፤ 32:17፤ መዝ. 115:4-8፤ 135:15-18፤ ኢሳ. 2:8፤ 37:19፤ 40:19-20፤ 44:17፤ ኤር. 1:16፤ 10:3-5፤ ዳን. 5:23፤ ሚክ. 5:13)። በአኪ ግልሙትና የሚያያዘው ከሰይጣናዊ ጋር ነው (ዝከ. 16:14፤ 1 ቆሮ. 10:20፤ 1 ጢሞ. 4:1)።

**9፡21** እነዚህ አራት ነገሮች፣ (ግልሙትና፣ ግድያ፣ አስማተኝነት፣ ኢ-ሞራላዊነት) በብኪ የተኮነኑ ናቸው (ዘዳ. 18:10-11፣14፣20፤ ዘጸ. 22:18፤ ሌዋ. 20:6) እነርሱም ባሕርይ የሚያደርጉት የማያምኑትን ኢ-ሞራላዊ የሕይወት ስልት ነው (ሮሜ 1-2፤ 1 ጢሞ. 4:1፤ ራዕ. 18:23)። ይኸው ተመሳሳይ ንስሐ ያልገቡት አካታች ቡድን 13:15-17፤ 14:9፤ 16:2፣9፣11 ላይ ተጠቅሷል።

▣

**አአመመቅ፣አኪጀት**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | **"ጠንቋዮች"** |
| **አእት** | **"ጥንቆላ"** |
| **አኢመቅ** | **"ጥንቆላ"** |

የእንግሊዝኛውን ቃል "ፋርማሲ" ያገኘነው ከግሪኩ ቃል (*pharmakeia*፣ ነው፣ ገላ. 5:20)። ይህ ምናልባት መድኃኒት ወይም መመረዝ ሊሆን ይችላል፣ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው እሬቶ ያለ (ዝከ. 8፡11)። በጥንታዊው ዓለም መድኃኒቶች ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውሉት "ከሃይማኖታዊ" ልምምዶች ጋር በተያያዘ ነው።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የእነዚህን ምዕራፎች ምናብ ምንጭ ከየት ማግኘት እንችላለን፡ (1) ከብኪ፡ (2) ከአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ፡ ወይስ (3) ከሮማ ኢምፓየር ታሪካዊ ሁነቶች?
2. እነዚህ ሁነቶች የሚያመለክቱት (1) አንደኛውን ክፍለ-ዘመን (2) ሁሉንም ክፍለ-ዘመን፣ ወይስ (3) መጻኢውን?
3. እነዚህ ምዕራፎች መወሰድ ያለባቸው በጥሬው ነው ወይስ በአፖካሊፕቲካዊ?
4. የምዕራፍ 8-9 ዋነኛው ፍሬ ነገር ምንድነው?
5. ሰባቱ ማኅተሞችና ሰባቱ ጽዋዎች ምዕራፍ 8 እና 9 ላይ እንዴት ይዛመዳሉ?
6. ከዳግም ምጽአቱ በፊት የጨመረ መልአካዊና ሰይጣናዊ ድርጊት ለምን ይኖራል?

# ራዕይ 10፡1-11፡19
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ4 | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| መልአኩና ትንሹ ጥቅል | ታላቁ መልአክና ጥቅሉ | የቆይታ ጊዜ | መልአኩና ትንሹ ጥቅል | የመጨረሻው ቅጣት ጥኑነት |
| 10:1-7 | 10:1-7 | 10:1-7 | 10:1-4 | 10:1-7 |
| | ዮሐንስ ትንሿን መጽሐፍ በላ | | 10፡5-7 | ነቢዩ ትንሹን ጥቅል በላ |
| | 10:8-11 | | | 10:8-11 |
| 10:8-11 | | 10:8-10 | 10:8 | |
| | | | 10:9 | |
| | | | 10:10-11 | |
| | ሁለቱ ምስክሮች | 10:11 | | ሁለቱ ምስክሮች |
| ሁለቱ ምስክሮች | | የመቅደሱ መለካትና ሁለቱ ምስክሮች | ሁለቱ ምስክሮች | |
| | 11:1-6 | | | 11:1-10 |
| 11:1-13 | ምስክሮቹ ተገደሉ | 11:1-3 | 11:1-3 | |
| | 11:7-10 | 11:4-6 | 11:4-6 | |
| | ምስክሮቹ ተነሡ | 11:7-10 | 11:7-13 | |
| | 11:11-14 | | | 11:11-13 |
| | | 11:11-13 | | |
| | | ሰባተኛው መለከት | | 11:14 |
| 11:14 | ሰባተኛው መለከት፡ መንግሥት ታወጀ | 11:14 | 11:14 | ሰባተኛው መለከት |
| ሰባተኛው መለከት | | | ሰባተኛው መለከት | |
| | 11:15-19 | | | 11:15-18 |
| 11:15-19 | | 11:15-19 | 11:15-18 | 11:19 |
| | | | 11:19 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ vii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

ሀ. የመጀመሪያው የቆይታ ጊዜ (ምዕራፍ 7) የሚመጣው በስድስተኛውና ሰባተኛው ማኅተሞች መካከል ነው። ሁለተኛው የቆይታ ጊዜ (10፡1-11፡14) የሚመጣው በስድስተኛውና ሰባተኛው መለከቶች መካከል ነው። በስድስተኛውና ሰባተኛው ጽዋዎች መካከል ምንም የቆይታ ጊዜ የለም (ምዕራፍ 16)፣ ነገር ግን ሌላ የቆይታ ጊዜ ከእነርሱ ቀደም ብሎ አለ (ምዕራፍ 12-14)።

ለ. ይህ የቆይታ ጊዜ፣ እንደ ምዕራፍ 7፣ የብኪ ቃላትን ይጠቀማል (ቤተ-መቅደስ፣ መሠዊያ፣ ኢየሩሳሌም)። ሆኖም፣ ምዕራፍ 7 ላይ እንዳለው የአይሁድ ጠቃሽ ዘይቤ ወደ አኪ የእግዚአብሔር ሕዝብ ያመለክታል፣ ቤተ ክርስቲያን፣ በዚህ ምዕራፍም እንዲሁ። ጠቃሾቹ የተወሰዱት ከዳንኤል 9 ሲሆን፣ ነገር ግን ከግሪክ-ሮሜ አንደኛ ክፍለ-ዘመን መቼት አኳያ ተቃኝተዋል።

እዚህጋ ከአለን ጆንሰን *የራዕይ ሐተታ* ላይ አጭር ጥቅስ አለ፣ "የአይሁድ አተያይ ይሄንን ምዕራፍ ከምዕራፍ 10 ይዘት ጋር ከማዛመድ አኳያ የአለመቻል ድክመት አለበት፣ ከማኅተሙ የቆይታ ጊዜ ትይዩነት ጋር (ምዕ. 7)፣ ከሁለቱ ምስክሮች አገልግሎትና ጠቃሚነት ጋር፣ እንዲሁም ከቀጣዮቹ የራዕይ ምዕራፎች ጋር (በተለይም፣ ምዕራፍ 12-13)። ስለዚህ፣ ምዕራፍ 11ን መረዳቱ ይሻላል፣ ሞላውን ክርስቲያን ማኅበረሰብ እንደሚጠቅስ" (ገጽ 104)።

ሐ. አለን ጆንሰን ምዕራፍ 11ን ከምዕ. 7፣10፣ እና 12-13 ዝምድናውን እንደተመለከተው፣ ጆርጅ ላድ እሱን የሚመለከተው ራሱን እንደቻለ ጽሑፋዊ ምድብ ነው፣ ከአይሁድ ሕዝብ መጠበቅ እና ከመጨረሻ ደኅንነት ጋር በማያያዝ (ማቴ. 23:39፤ ሉቃስ 21:24፤ ሮሜ. 11:26)። የእሱን *የዮሐንስ ራዕይ ሐተታ* ገጽ 150-151 ተመልከት።

በእነዚህ ሁለት አተያዮች መካከል መወሰን አስቸጋሪ ነው። እኔ በርግጥ የሚሰማኝ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ካለው ቃል የተነሣ የፍጻሜ ዘመን መነቃቃት በዋናው ወይም በተለወጡት እስራኤል ላይ ይሆናል፣ ብዙዎች በክርስቶስ ወደ ሆነ እምነት ይመለሳሉ (ዘካ. 12፡10)፤ ይህ ሮሜ ላይ የጳውሎስ ሙግት ክፊል ነው (እሱም በርግጥ የሚቻለው ዘካ. 12፡10 ላይ የተጠቀሰው መነቃቃት በአንደኛው ክፍለ-ዘመን በፍልስጥኤም ቤተ ክርስቲያን ሆኗል ማለት ይቻላል)። ሆኖም፣ የራዕይ 7፣10፣ እና 12-13 ዐውደ-ጽሑፍ አንድምታው ሁለንተናዊ ደረጃ ያለው የሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ መጠበቅ እና በማያምኑት ላይ የሚሆነው ፍርድ ነው። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የአማኝ አይሁድ አጽንዖት ወይም የአይሁድ-አልያም-አሕዛብ አጽንዖት ቦታው አይደለም።

መ. ሁለት የፍጻሜ ዘመን ምስክሮች ይኖራሉን ወይስ ይህ የፍጻሜ ዘመን ምስክሮች ተምሳሌት ነው? የዚህን መጽሐፍ ተምሳሌቶች በርግጠኝነት ለመተርጎም እጅግ ይከብዳል። ዮሐንስ ጥሬአዊ አድርጓቸው ከሆነ፣ እሱ የተለየ ዘውግ በመረጠ ነበር በሁሉም ዘመናት ለሚገኙት አማኞች ይሄንን ለመግለጥ።

ይህ "የሁለቱ ምስክሮች" ማጣቀሻ ለአንደኛው ክፍለ-ዘመን መከራ ለሚቀበሉት አማኞች የተለየ ትርጉም ይኖረዋልን (ምናልባትም የአጼ አምልኮ ወገኖች)? ይህ በማጠቃለል ሊመለስ አይችልም። የዮሐንስ ምናብ የተቀዳው ከብዙ ምንጭ ነውና፡ ብሉይ ኪዳን፣ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ፣ የግሪክ-ሮማ ባህል እና የጊዜው የቅርብ ምስራቅ አፈ-ታሪክ (ምዕራፍ 12)። የመጀመሪያዎቹ ሰሚዎች በተጠናቀቀና በሙላት የእርሱን ምንጮችና ተምሳሌቶች ተረድተዋልን? ምናልባት ላይሆን ይችላል፣ በተለየ መንገድ ላይሆን ይችላል፣ ዘውጉን ግን አውቀዋል! እነርሱ ጥሬአዊ ታሪካዊ ፍጻሜን ለዝርዝሮቹ ሁሉ እንዲሆን ግፊት አላደረጉም።

የእኔ ብቸኛው ፍራቻ ይሄንን መግለጫ በማዘጋጀት፣ የብኪ ቀዳሚ ትንቢት በተመስጦአዊዎቹ የአኪ ደራስያን እንዴት እንደተተረጎመ ነው! እነርሱ ዘወትር የተመለከቱት ጥሬአዊ የብኪ ዝርዝሮች ፍጻሜን ነው፣ በክርስቶስ ሕይወት። አንዳንዶቹ እነዚህ ፍጻሜዎች ራቢያዊ የቃላት ጨዋታ ነበሩ፣ ወይም ዓይነተኛ/ዓይነተኛ ያልሆኑ ተምሳሌቶች። በመንፈስ መሪነት ሥር (ወይም በኢየሱስ ትምህርት፣ ሉቃስ 24፡13-35) የሐዋርያት የወቅቱ ታሪካዊ መቼት በብኪ ትንቢታዊ ጽሑፎች በኩል ይታያል። ይኸው ተመሳሳይ ነገር ለመጨረሻው ትውልድ ተሳዳጅ አማኞች ሊከሰት ይችላል። ሆኖም፣ ጣልቃ የሚገቡ ተርጓሚዎች ከእነዚህ ዝርዝሮች የትኞቹን በሥነ-መለኮት ወይም በሥነ-ትርጓሜ ቀድመው መተንበይ አልቻሉም! ዘመናውያኖቹ ተርጓሚዎች ማድረግ የሌለባቸው (1) የራሳቸውን ታሪክ በእነዚህ አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፎች ላይ መጫን አልያም (2) ለዚህ እጅግ ተምሳሌታዊ ዘውግ ዝርዝር ጥሬአዊ ፍጻሜ መሻት። ጊዜ ይናገራል!

ሠ. ጽሑፋዊ ፈርጆች እና የማኅተሞቹና መለከቶቹ ምስያ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም የሰውን ታሪክ ወደ ሁነኛው ፍጻሜ ያመጡታል (ዝከ. 6፡12-17 እና 11፡15-19)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ራዕይ፡ 10፡1-7**

**[1]ሌላም ብርቱ መልአክ ደመና ተጐናጽፎ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፤ በራሱም ላይ ቀስተ ደመና ነበረ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ እግሮቹም እንደ እሳት ዓምዶች ነበሩ፥ [2]የተከፈተችንም ታናሽ መጽሐፍ በእጁ ያዘ። ቀኝ እግሩንም በባሕር ላይ ግራውንም በምድር ላይ አኖረ፥ እንደሚያገሣም አንበሳ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። [3]በጮኸም ጊዜ ሰባቱ ነጐድጓድ በየድምፃቸው ተናገሩ። [4]ሰባቱ ነጐድጓድ በተናገሩ ጊዜ ልጽፍ አሰብሁ፤ ከሰማይም። ሰባቱ ነጐድጓድ የተናገሩትን ነገር በማኅተም ዝጋው አትጻፈውም የሚል ድምፅ ሰማሁ።**

[5]በባሕርና በምድርም ላይ ሲቆም ያየሁት መልአክ ቀኝ እጁን ወደ ሰማይ አሻቅቦ ዘረጋ፥ [6]ሰማይንና በእርሱም ያሉትን፥ ምድርንና በእርስዋም ያሉትን፥ ባሕርንና በእርሱም ያሉትን በፈጠረው፥ ከዘላለምም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ሆኖ በሚኖረው ምሎ። [7]ወደ ፊት አይዘገይም፥ዳሩ ግን ሰባተኛው መልአክ ሊነፋ ባለው ጊዜ ድምፁም በሚሰማበት ዘመን፥ ለባሪያዎቹ ለነቢያት የምስራች እንደ ሰበከላቸው የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል አለ።

**10፡1 "ሌላም ብርቱ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፤"** ዮሐንስ ከምዕራፍ 4-5 ራዕይ በኋላ ወደ ምድር መመለሱን አስተውል (ምዕ. 4 ላይ የዮሐንስ ወደ ሰማይ መጠራት የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከሆነ፣ ይህ የቤተ ክርስቲያን ውድቀት ነውን?)። ይህ መልአክ የተገለጸው በቢኪ ለያህዌ እና ለክርስቶስ በራዕ. 1፡12-20 በጥቅም ላይ በዋሉት ቃላት ነው። በዚህ ምክንያት፣ ብዙዎች የሚያስረግጡት ይህ ክርስቶስ ራሱ ነው። ሆኖም፣ ይህ በሚከተሉት ምክንያቶች አጠራጣሪ ነው፡

1. ክርስቶስ በራዕይ ላይ መልአክ ተብሎ ፈጽሞ አልተጠራም
2. በራዕይ ላይ ሌላ ብርቱ መልአክ የተመዘገበ አለ (ዝከ. 5፡2፤ 18፡21)
3. ይህ መልአክ በእግዚአብሔር ይምላል፣ ቁ. 6 ላይ፣ ይህም ለክርስቶስ የማይገባ
4. ዳንኤል 10 ላይ ሌላ መልአክ አለ፣ እሱም በተመሳሳይ ቃላት የተገለጸ።

ይህ የተብራራ ገለጻ ይሄንን የብርሃን መልአክ ከጥልቁ መልአክ ጋር ያቃርነዋል፣ ራዕይ 9 ላይ። ራዕይ 9 ላይ ያለው መልአክ እንደታዘዘ፣ ይህ መልአክ ራሱን የሚያዝ ነው። ይህ ምናልባት የዳን. 10፡5-6 ብርቱ መልአክ ጠቃሽ ነው፣ ወይም የሚካኤል፣ የእስራኤል ሊቀ መልአክ፣ ዳን. 10፡13 እና 12፡1።

▣ **"ደመና ተጎናጽፎ"** በብኪ ደመናት የተለዩ የመለኮት ማጓጓዣ ነበሩ (መዝ. 97፡2፤ 104፡3፤ ዳን. 7፡13፤ ሐዋ. 1፡9)።

▣ **"በራሱም ላይ ቀስተ ደመና ነበረ"** ብዙዎች ይሄንን የሚመለከቱት እንደ 4፡3 ጠቃሽ ነው፣ እና ስለዚህ ለመለኮት ኃይልና ሥልጣን ሌላ መጠሪያ መሆኑን የሚያስታውስ። ጠቃሹ ተመልሶ ወደ ዕዝ. 1፡28 ይሄዳል፣ እዚያም ቀስተ-ደመና የያህዌ ተንቀሳቃሽ ዙፋን/ሠረገላ የሆነበት።

▣ **"ፊቱም እንደ ፀሐይ ነበር"** ይህ የሚከተለው የክርስቶስን ገለጻ ነው 1፡16 (ማቴ. 17፡2) የሚገኘው።

▣ **"እግሮቹም እንደ እሳት ዓምዶች"** ይህ ገለጻ ደግሞ ለክርስቶስ ተመሳሳይ ነው፣ ራዕ. 1፡15 ላይ።

**10፡2 "የተከፈተችንም ታናሽ መጽሐፍ በእጁ ያዘ።"** ስለዚች ትንሽ መጽሐፍ በርካታ ውይይቶች ተካሂደዋል። አንዳንዶች የሚመለከቱት 5፡1 ላይ እንዳለችው ታናሽ መጽሐፍ ነው፣ አሁን ተከፍታለች፣ ነገር ግን ሁለት የተለያዩ የግሪክ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል (5፡1፣ *biblion*፤ 10፡2፣ *biblaridion*)። ሌሎች የሚመለከቱት ከሕዝቅኤል 2፡8-3፡14 ጋር በተያያዘ ነው። ይህ መልአክ እንጂ ክርስቶስ ስላልሆነ፣ ሕዝቅኤል እጅግ የተሻለው ጠቃሽ ነው።

▣ **"ቀኝ እግሩንም በባሕር ላይ ግራውንም በምድር ላይ አኖረ፥"** የመልአኩ መጠን ስለ ሁለንተናዊ መልእክት ይናገራል። ራቢዎች (በታልሙድ) ሳንድልፎን የተባለ መልአክ ያብራራሉ፣ የእሱም ትልቅ ከፍታ 500 ማይል ሆኖ ከሌሎቹ መላእክት የሚረዝም (ሀጊጋህ 13ለ)።

**10፡3 "እንደሚያገሣም አንበሳ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።"** "መጮኽ" የሚለው ቃል (*mukaomai*) ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለበሬዎች ድምጽ ነው (ዝቅተኛ ግሳት)። ሆኖም፣ ተገቢ የሚሆነው ይህ የብኪ ምንባቦች ጠቃሽ መሆኑ ነው፣ እግዚአብሔር እንደ አንበሳ የሚናገርበት (ኤር. 25፡30፤ ሆሴ. 11፡10፤ ኢዩኤል 3፡16፤ ዐሞጽ 3፡8)።

▣ **"ሰባቱ ነጐድጓድ በየድምፃቸው ተናገሩ"** የእነዚህ ነጎድጓዶች ማንነት አወዛጋቢ ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው፡

1. የሰባቱ የእግዚአብሔር ድምጾች ጠቃሽ ነው፣ መዝ. 29፡3-9 ያለው
2. ከሰባቱ ማኅተሞችና ሰባቱ መለከቶች ጋር ትይዩ፣ እሱም በማያምኑት ላይ የሚሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ ዑደት (ዝከ. 8፡5፤ 11፡19፤ 16፡18) ለመቤዠት ዓላማ
3. ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚመጣ ድምጽ (ዝከ. 4፡5)
4. እሱም ደግሞ ከሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ጋር ይዛመዳል (ዝከ.1፡4፤ 4፡5፤ 5፡6 ከኢሳ. 11፡22)

**10፡4 "በማኅተም ዝጋው"** በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ስፍራዎች አሉ፣ አንዱ ከእግዚአብሔር ራዕይ ተቀብሎ መግለጥ ግን ያልቻለው። ከእነዚህ ሁለቱ (1) ዳንኤል (ዳን. 8፡26፤ 12፡4፣9) እና (2) ጳውሎስ (II ቆሮ. 12፡4)። ሆኖም ይህ እጅግ አስገራሚ መግለጫ ነው። ዮሐንስ ያየውን እንዲጽፍ ተነግሮታልና (ዝከ. 1፡11፣19፤ 14፡13፤ 19፡9፤ 21፡5)። ዮሐንስ 22፡10 ላይ ያሉት የትንቢት ቃላት በማኅተም እንደማይዘጉ ተነግሮታል። ይሄንን መልእክት ብቻ በተመለከተ ይሆናል!

**10፡5 "ቀኝ እጁን ወደ ሰማይ አሻቅቦ ዘረጋ፥"** ይህ ለመሐላ የሚሆን የሰውነት አንቅስቃሴ ነው (ዘፍ. 14፡22፤ ዘጸ. 6፡8፤ ዘኍ. 14፡30፤ ዘዳ. 32፡40፤ ሕዝ. 20፡15፣28፤ ዳን. 12፡7)። የዚህ መሐላ መልክ በጣም የሚነካ ነው፣ ለእግዚአብሔር ከሰጠው ስም የተነሣ።

**10፡6 "ከዘላለምም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ሆኖ በሚኖረው"** ይህ የእግዚአብሔር ባሕርይ የሱን የብኪ በጣም የተለመዱ ሁለት ስሞችን ያስታውሳል፡

1. *ያህዌ* ከዕብራይስጡ ግስ *"መሆን"* (ዘጸ. 3፡14)። *"ያለና የሚኖር"* ለመለኮት የኪዳን ስም ነበር፤ እሱም ለእግዚአብሔር አጽንዖት ይሰጣል፣ እንደ አዳኝና ተቤዢ (ዘፍ. 14፡19፤ ዘጸ. 20፡11፤ ነህ. 9፡6፤ መዝ. 146፡6)።
2. *Elohim*፣ እሱም ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ የዋለ፣ ዘፍጥረት 1 ላይ እንደ ፈጣሪ፣ ጠባቂ፣ እና ሰጪ፣ በምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ (ዘፍ. 14፡19፤ ዘጸ. 20፡11፤ ነህ. 9፡6፤ መዝ. 146፡6)።

*ይህ መሐላ የመልአኩ መልእክት ታማኝ መሆኑን ማስረገጫ መንገድ ነው።*

▣ ***"ወደፊት አይዘገይም"*** ይህ ምላሽ ሊሆን ይችላል፣ 6፡10 ለቀረበው የሰማዕታት ጥያቄ። እሱም በጥሬው *"ያ ጊዜ* (*chronos*) ካሁን በኋላ አይሆንም ነው።" የጊዜ ጽንሰ-ሐሳብ በዚህ መጽሐፍ በብዙ ምክንያቶች እጅግ ተለዋዋጭ ነው።

1. ጊዜን የሚገልጹ ሁለት የተለያዩ የግሪክ ቃላት አሉ
   ሀ. *chronos*፣ የጊዜ ማለፍ (cf. 10፡6)
   ለ. *kairos*፣ ልዩ ሰዓት፣ ወቅት፣ ወይም ሁነት (ዝከ. 1፡3፤ 11፡18፤12፡12፣14).
2. በርካታ ፈሊጦች ጥቅም ላይ ውለዋል:
   ሀ. "በቅርቡ የግድ የሚሆኑ ነገሮች" (ዝከ. 1፡1፤ 22፡6)
   ለ. "ጊዜው ቅርብ ነው" (ዝከ. 1፡3፤ 3፡11፤ 22፡10)
   ሐ. "ፈጥኜ እመጣለሁ" (ዝከ. 2፡5፣16፤ 22፡7፣12፣20)
   መ. "እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ" (ዝከ. 3፡3፤ 16፡15)

እነዚህ ሁሉ የሚናገሩት ስለ ድንገተኝነቱ ነው (ልዩ ርዕስ 1፡3 ላይ ተመልከት)። ሆኖም፣ አንዳንድ ምንባቦች ስለ መዘግየቱ ይናገራሉ (ዝከ. 6፡11፤ 10፡6፤ 14፡13)። ሌለኛው ፈሊጥ፣ የፍርድና የሽልማት ቀን መድረሱ ነው፣ "ሆኗል" (ዝከ. 16፡17፤ 21፡6) ወይም "ሰዓቱ ደርሷል" (ዝከ. 11፡18፤ 20፡12)።

ይህ ተለዋዋጭነት የትርጓሜ ስልቶችን በመለየት ጥቅም ላይ ውሏል፣ የተወሰነ የጊዜ ገጽታን አጽንዖት በመስጠት (አንደኛ ክፍለ-ዘመን፣ ዘመናቱን ሁሉ፣ ወይም የመጨረሻውን ትውልድ)። የመልአኩ የምር መሐላ፣ የፍጻሜ ሰዓት ሁነቶች አሁን እንደሚጀምሩ ነው። የሰማዕታት ጸሎት ተሰምቷል! ራዕይ የግድ መተርጎም የሚኖርበት በመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ብርሃን ነው (የጆን ብሬይን፣ *የማቴዎስ 24 ፍጻሜን* ተመልከት)።

**10፡7**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል"** |
| **አኪጀት** | **"የእግዚአብሔር ምሥጢር ተፈጻሚ ይሆናል"** |
| **አየተመት** | **"የእግዚአብሔር ምሥጢር ተፈጻሚ ይሆናል"** |
| **አእት** | **"እግዚአብሔር የምሥጢር ዕቅዱን ይፈጽማል"** |
| **አኢመቅ** | **"የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል"** |

*ቃሉ* በርካታ ፍችዎች አሉት።

1. ጳውሎስ እሱን ዘወትር የሚጠቀምበት የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ ለማመልከት ነው፣ አይሁድንም ሆነ አሕዛብን በክርስቶስ ባለ እምነት (ኤፌ. 2፡11-3፡13፣ ልዩ ርዕስ 4፡1 ላይ ተመልከት)።
2. ራዕይ ዘወትር የሚያመለክተው ምሥጢርን ነው፣ ስለ ራዕዩ ክፋይ (ዝከ. 1፡20፤ 17፡5፣7)።
3. 10፡7 ላይ እሱ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ የመቤዠት ዕቅድ ነው፣ ጳውሎስ ሮሜ 16፡25-26 እና ኤፌ. 2፡11-3፡13 ላይ እንዳደረገው።

ማለት የሚቻለው ዮሐንስ ይሄን ቃል ከዳንኤል እንደወሰደው ነው፣ በተለይም ምዕራፍ 2 (ዝከ. 2፡18፣19፣27፣28፣29፣30፣ 47)። እንደዚያ ከሆነ፣ እሱ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ችሎታ ነው፣ ድርጊቶቹን ለመግለጥ። እግዚአብሔር የሚያውቅና ሁሉንም ታሪክ የሚቆጣጠር ነው።

**ልዩ ርዕስ፡ ምሥጢር በወንጌላት ውስጥ**

ሀ. ምሥጢር የሚለውን ቃል በሦስቱ ስኖፕቲክ ወንጌላት ውስጥ የኢየሱስ ምሳሌዎችን መንፈሳዊ መረዳት ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡
   1. ማርቆስ 4፡11
   2. ማቴ 13፡11
   3. ሉቃስ 8፡10

ለ. ጳውሎስ "ምሥጢር" የሚለውን ቃል ተጠቅሟል፣ ይህንን አጠቃላይ የመቤዠት ዕቅድ ለመግለጽ (1ቆሮ. 4፡1፤ ኤፌ. 6፡19፤ ቆላ. 4፡3፤ 1ጢሞ. 1፡9)። ሆኖም፣ በተለያዩ በርካታ አግባቦች ተጠቅሞበታል፡
   1. የእስራኤል ከፊል ልበ-ደንዳና መሆን፣ አሕዛብ ይጨመሩ ዘንድ ለመፍቀድ። ይህ የአሕዛብ መጉረፍ አይሁድ ኢየሱስን
   2. በትንቢቱ መሠረት እንደ ክርስቶስ ይቀበሉ ዘንድ እንደ ብልሃት ሆኖ አገልግሏል። (ሮሜ 11፡25-32)።
   3. ወንጌሉ ለሕዝቦች ሁሉ እንዲታወቅ ተደርጓል፣ እነሱ ሁሉም በክርስቶስ እና በክርስቶስ በኩል የተካተቱት ናቸው (ሮሜ 16፡25-27፤ ቆላ. 2፡2)።
   4. የአማኞች አዲስ አካላት በዳግም ምጽዓቱ (1ቆሮ. 15፡5-57፤ 1ተሰ. 4፡13-18)።
   5. የሁሉም ነገር በክርስቶስ መጠቅለል (ኤፌ. 1፡8-11)።
   6. አሕዛብና አይሁድ አብረው ወራሾች ናቸው (ኤፌ. 2፡11-3፡13)።

7. የክርስቶስና የቤተ-ክርስቲያን ወዳጃዊ ቅርበት በጋብቻ ቃላት ተገልጿል (ኤፌ. 5:22-33)።
8. አሕዛብ ከኪዳኑ ሕዝቦች ጋር ተካተዋል፣ እናም የክርስቶስ መንፈስ ያድርባቸው ዘንድ፣ ይህም ክርስቶስን የመምሰል ብስለት እንዲያፈሩ፣ ይህም የወደቀውን ሰው የእግዚአብሔርን መልክ ለመመለስ (ዘፍ. 6:5፣11-13፤ 8:21) እግዚአብሔርን በሰው ውስጥ (ዘፍ. 1:26-27፤ 5:1፤ 9:6፤ ቆላ. 1:26-28)።
9. የፍጻሜው ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ (2ተሰ. 2:1-11)።
10. የጥንታዊቷ ቤተ-ክርስቲያን የምሥጢር ማጠቃለያ በ1ጢሞ 3፡16 ላይ ይገኛል።

ሐ. በዮሃንስ ራዕይ ውስት ዮሐንስ ያያቸውን ራዕይ ምልክቶችን ትርጉም ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡
1. 1:20
2. 10:7
3. 17:5,6

መ. እነዚህ ሰዎች ሊረዱት የማይቻላቸው መገለጦች ናቸው፤ እግዚአብሔር ሊገልጥልን ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ መገለጦች የእግዚአብሔር ለሰው ልጆች ደህነነት ያለውን ዘላለማዊውን እቅድ ለመረዳት በጣም ወሳኞች ናቸው(ዘፍ. 3:15).

▣ "ነቢያት"

## ልዩ ርዕስ፡ መተንበይ

I. መግቢያ
 ሀ. የመክፈቻ መግለጫዎች
  1. አማኙ ማኅበረሰብ እንዴት አድርጎ ትንቢትን እንደሚተረጉም ስምምነት የለውም። ሌሎቹ ሐቆች ቀጥተኛ በሆነ አቋም ላይ ለዘመናት ሁሉ የተመሠረቱ ሲሆኑ፣ ይሄኛው ግን አይደለም።
  2. በርካታ በሚገባ የተገለጹ የብኪ ትንቢት ደረጃዎች አሉ
   ሀ. ቅድመ- ዘውዳዊ (ሞናርኪያዊ)
    (1) ነቢያት ተብለው የሚጠሩ ግለሰቦች
     (ሀ) አብርሃም — ዘፍ. 20፡7
     (ለ) ሙሴ — ዘኍ. 12:6-8፤ ዘዳ. 18:15፤ 34:10
     (ሐ) አሮን - ዘጸ. 7:1 (የሙሴ ቃል አቀባይ)
     (መ) ማርያም - ዘጸ. 15:20
     (ሠ) ሜዳድና ኤልዳድ - ዘኍ. 11:24-30
     (ረ) ዲቦራ - መሳ. 4:4
     (ሰ) ስሙ ያልተጠቀሰ - መሳ. 6:7-10
     (ሸ) ሳሙኤል - I ሳሙ. 3:20
    (2) ለነቢያት እንደ ምድብ ማጣቀሻ - ዘዳ. 13:1-5፤ 18:20-22
    (3) ትንቢታዊ ምድብ ወይም ተጓዳኞች - I ሳሙ. 10:5-13፤ 19:20፤ I ነገሥ. 20:35፣41፤ 22:6፣10-13፤ II ነገሥ. 2:3፣7፤ 4:1፣38፤ 5:22፤ 6:1፣ ወዘተ.
    (4) መሲሕ ነቢይ ይባላል - ዘዳ. 18:15-18
   ለ. ያልተጻፈ ዘውዳዊ (ሞናርኪያዊ) (እነሱም ንጉሥን ያመለክታሉ)
    (1) ጋድ — 1ኛ ሳሙ. 22:5; II Sam. 24:11; I Chr. 29:29
    (2) ናታን - II ሳሙ. 7:2፤ 12:25፤ I ነገሥ. 1:22
    (3) አሂጃ - I ነገሥ. 11:29
    (4) ጄሁ - I ነገሥ. 16:1፣7፣12
    (5) ስሙ ያልተጠቀሰ - I ነገሥ. 18:4፣13፤ 20:13፣22
    (6) ኤልያስ - I ነገሥ. 18-II ነገሥ. 2
    (7) ሚልክያስ - I ነገሥ. 22
    (8) ኤልሳ - II ነገሥ. 2:8፣13
   ሐ. የጥንታዊ ጽሑፍ ነቢያት (እነሱም ሕዝቡን እንዲሁም ንጉሡን ያመለክታሉ)፡ ከኢሳይያስ እስከ ሚልኪያስ (ከዳንኤል በቀር)
 ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት
  1. ሮህ = "ነቢይ፣" 1ኛ ሳሙ. 9፡9። ይህ ማጣቀሻ ራሱ የሚያሳየው ናቢ የሚለውነ ቃል ትርጉም ነው። ሮህ ከአጠቃላይ ቃል "ማየት"
  ከሚለው ነው። ይህ ሰው የእግዚአብሔርን መንገዶችና ዕቅዶች የተረዳ ሲሆን፣ በአንድ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማወቅ የሚያማክሩት ነው።
  2. ሆዚህ = "ነቢይ፣" 2ኛ ሳሙ. 24፡11። እሱም በመሠረቱ ከሮህ ጋር ተመሳሳይ ነው። እሱ ከማይዘወተረው ቃል ከ"ማየት"

ነው። የቦዝ አንቀጽ ዓይነቱ ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው ነቢያትን ለማመላከት ነው (ማለትም፣ "ተመልከቱ")።

3. ናቢ = "ነቢይ፣" ከአካድያን ግሥ ከናቡ ጋር ይያያዛል = "መጥራት" እና ዓረባዊ ናባ = "ማወጅ።" ይህ በብሉይ ኪዳን ነቢይን ለመግለጽ በእጅጉን የተለመደ ቃል ነው። እሱም ከ300 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ ውሏል። ትክክለኛው ሥርወ - ቃል አይወቅም፣ ግን "መጥራት" በአሁኑ ጊዜ የተሻለው አማራጭ ይሆናል። የተሻለው መረዳት ሊመጣ የሚችለው ያህዌ፣ ሙሴ ከፈርዖን ጋር ያለው ግንኙነት በአሮን በኩል ማድረጉን የገለጸበት ነው (ዘጸ. 4፡10-16፤ 7፡1፤ ዘዳ. 5፡5። ነቢይ ማለት ከእግዚአብሔር አኳያ ለሕዝቡ የሚናገር ነው (አሞጽ 3፡8፤ ኤር. 1፡7፣17፤ ሕዝ. 3፡4።)
4. ሦስቱም ቃላቶች ሁሉ በነቢያት ምድብ ጥቅም ላይ የዋሉት በ1ኛ ዜና. 29፡29፤ ሳሙኤል - ሮህ፤ ናታን - ናቢ እና ጋድ - ሆዜህ ላይ ነው።
5. ሐረጉ፣ ኢሻ - ኤሎሂም፣ "የእግዚአብሔር ሰው፣" ደግሞ ሰፋ ያለ መለያ ነው፣ ለእግዚአብሔር ለሚናገር። እሱም 76 ጊዜ ያህል በብኪ ጥቅም ላይ ውሏል፣ "ነቢይ" በሚል ስሜት።
6. "ነቢይ" የሚለው ቃል መነሻው ግሪክ ነው። እሱም የመጣው ከ፡ (1) ቅድመ = "በፊት" ወይም "ለ" እና (2) ፌሚ = "መናገር" ነው።

II. የትንቢት መግለጫ

ሀ. "ትንቢት" የሚለው ቃል ሰፋ ያለ የዕብራይስጥ የፍቺ መስክ አለው፣ ከእንግሊዝኛ ይልቅ። ከኢያሱ እስከ መጽሐፈ ነገሥት (ሩትን) ሳይጨምር ያሉት የታሪክ መጻሕፍት፣ በአይሁድ የሚለዩት እንደ "ቀደምት ነቢያት" ነው። ሁለቱም፣ አብርሃም (ዘፍ. 20፡7፤ መዝ. 105፡5) እና ሙሴ (ዘዳ. 18፡18) እንደ ነቢያት ይቆጠራሉ (ማርያም ጭምር፣ ዘጸ. 15፡20)። ስለዚህ፣ ግምታዊ ከሆነ የእንግሊዝኛ መግለጫ ተጠበቁ!

ለ. "ትንቢታዊነት በሕጋዊ መንገድ ሊገለጥ የሚቻለው እንደ ታሪክን መረዳት ነው፣ እሱም ትርጉምን ከመለኮታዊ አግባብ፣ መለኮታዊ ዓላማ፣ መለኮታዊ ተሳትፎ አኳያ ከሚቀበለው፣" የተርጓሚዎች የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ቅጽ 3፣ 896።

ሐ. "ነቢይ፣ ፈላስፋም ሆነ ስልታዊ የሥነ-መለኮት ሰው አይደለም፣ ነገር ግን በኪዳን መሐል ሆኖ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ሕዝቡ የሚያመጣ ሲሆን፣ መጪአቸውን መልክ በማስያስ አሁን ያሉበትን ለማደስ፣ "ነቢያትና ትንቢት፣" ኢንሳይክሎፔዲያ ጁዳይካ ቅጽ 13 ገጽ 1152።

III. የትንቢት ዓላማ

ሀ. ትንቢት፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚናገርበት መንገድ ነው፣ አሁን ላሉበት መቼት ምሪት የሚሰጥበት ነው፣ እንዲሁም ሕይወታቸውና የዓለም ሁነቶች በእሱ ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ተስፋ እንዲያደርጉ። የእነሱ መልዕክቶች በመሠረቱ የተደራጁ ናቸው። ማለትም፣ ለመገሠጽ፣ ለማበረታታት፣ እምነትን ለመፍጠር እና ለንስሐ፣ እናም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያስገነዝባል፣ ስለ ራሱም ሆነ ስለ እቅዱ። እነሱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይይዛሉ፣ ወደ እግዚአብሔር ኪዳናት ጽኑ ዕምነት። እዚህ ላይ የግድ መጨመር የሚኖርበት፣ እሱ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው የእግዚአብሔርን የቃል አቀባይ ምርጫ ለመግለጽ ነው (ዘዳ.13፡1-3፤ 18፡20-22)። ይህ፣ በድምዳሜ የሚወሰደው፣ መሲሑን ለማመላከት ነው።

ለ. ዘወትር፣ ነቢይ የሱን ዘመን ታሪካዊ ወይም ሥነመለኮታዊ ኪሳራዎችን ይወስዳል፣ እናም ይሄንን ወደ ፍጻሜያዊ የሆነ መቼት ይቀይሰዋል። ይህ የታሪክ የመጨረሻው ሰዓት የሆነ እይታ በእስራኤል የተለየ ነው፣ እናም የእሱ የመለኮታዊ ምርጫ እና የኪዳን ተስፋዎች እሳቤ የተለዩ ናቸው።

ሐ. የነቢያት ሹመት ለማመዛዘን የፈለገ የሚመስለው (ኤር. 18፡18) እና የሊቀ ካህናቱን ሹመት ሥልጣን መያዝ የእግዚአብሔርን ፍቃድ እንደማወቂያ መንገድ አድርጎ መውሰድን ነው። ኡሪምና ቱሚም ከእግዚአብሔር ቃል አቀባይ የመጣውን ወደ ቃል መልዕክት ያደገ ነው። የነቢያት ሹመት ከሚልክያስ በኋላ በእስራኤል ያከተመለከት ይመስላል። እሱም ከ400 ዓመት ቆይታ በኋላ እስከ መጥምቁ ዮሐንስ ድረስ አልተከሰተም። የአዲስ ኪዳን "የትንቢት" ስጦታ ከብሉይ ኪዳን ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ርግጠኝነት የለውም። የአዲስ ኪዳን ነቢያት (ሐዋ.11፡27-28፤ 13፡1፤ 14፡29፣32፣37፤ 15፡32፤ 1 ቆሮ. 12፡10፣28-29፤ ኤፌ. 4፡11) አዲስ ራዕይ ወይም ቃል ገላጮች አይደሉም፣ ነገር ግን በኪዳኑ ሁኔታዎች የእግዚአብሔርን ፍቃድ የሚነግሩ የሚተነብዩ ናቸው።

መ. ትንቢት በባሕርዩ ያልተጠቃለለ ወይም ቀደም ብሎ የሚታወቅ አይደለም። ትንበያ የእሱን ሹመት እና መልእክት የማረጋገጫ መንገድ ነው፣ ነገር ግን እሱ የግድ መመዝገብ ያለበት "የመሲሓዊ ትንቢት 2% ያነሰ ነው። ከ5% በታች በተለይ የሚገልጸው የአዲሱን ኪዳን ዘመን ነው። ከ1% ያነሰ ወደፊት የሚመጡትን ሁነቶች በተመለከተ ነው።" (ፊ እና ስቱዋርት፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣* ገጽ 166)።

ሠ. ነቢያት እግዚአብሔርን ለሕዝቡ ሲወክሉ፣ ካህናት ደግሞ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ፊት ይወክላሉ። ይህ አጠቃላይ መግለጫ ነው። የተለየነት ያላቸው ይኖራሉ፣ እንደ ዕንባቆም፣ ጥያቄውን ለእግዚአብሔር እንደሚያቀርበው ዓይነት።

ረ. ነቢያትን ያለመረዳት አንደኛው ምክንያት፣ መጽሐፎቻቸው እንዴት እንደተዋቀሩ አለማወቃችን ነው። ታሪክ ቅደም ተከተላዊ አይደሉም። ጭብጣዊ ይመስላሉ፣ ነገር ግን ዘወትር ማንም በሚጠብቀው መንገድ አይደለም። ዘወትር ግልጽ የሆነ ታሪካዊ መቼት፣ የጊዜ ቅንብብ ወይም ከመናፍስተኞች ጋር ግልጽ የሆነ ምድብ የለውም። እነዚህ መጻሕፍት አስቸጋሪዎች ናቸው (1) በአንድ ጊዜ ቅምጥ ለማንበብ፤ (2) በየርዕሱ ለመፈረጅ፤ እና (3) በእያንዳንዱ ትንበያ ላይ ማዕከላዊውን እውነት ወይም ሥልጣናዊ ሐሳብ ለማስረገጥ።

IV. የትንቢት ባሕርያት

ሀ. በብሉይ ኪዳን የ “ነቢይ” እና “ትንቢት” ጽንሰ-ሐሳብ እያደገ የመጣ ይመስላል። በጥንታዊ እስራኤል የነቢያት ኅብረት እየተጠናከረ መጥቶ ነበር፣ እሱም ይመራ ይነበረው እንደ ኤልያስና ኤልሳ በመሳሰሉ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ መሪዎች ነበር። አንዳንድ ጊዜ፣ “የነቢያት

ልጆች” የሚለው ሐረግ ጥቅም ላይ ይውል ነበር ይሄንን ቡድን ለመለየት (2ኛ ነገሥት 2)። ነቢያት ባሕርያቸው ይመደቡበት የነበረው መልክ ተመስጧዊነት ነው (1ኛ ሳሙ. 10:10-13፤ 19:18-24)።

ለ. ሆኖም፣ ይህ ጊዜ በፍጥነት ወደ ግለሰብ ነቢያት ተሸጋገሩ። እነዚያ የነበሩት ነቢያት (እውነተኞችም ሆነ ሐሰተኞች) በንጉሥ የሚታወቁት፣ እናም በቤተ-መንግሥት ይኖሩ ነበር (ጋድ፣ ናታን)። ደግሞም ነጻ የሆኑም ነበሩ፣ አንዳንድ ጊዜም ከእስራኤል ማኅበረሰብ አቋም ጋር ጨርሶ የማይገናኙ ነበሩ (አሞጽ)። እነሱም ወንድና ሴት ነበሩ (2ኛ ነገሥ. 22፡14።)

ሐ. ነቢይ ዘወትር መጻዒውን የሚተነብይ ነው፣ በሰዎች ፈጣን ምላሽ ላይ የተንተራሰ። የነቢያት ተግባር ዘወትር የነበረው እግዚአብሔር ለፍጡሩ ያለው የማይታጠፍ ሁለንተናዊ እቅድ ሲሆን፣ ፤ እሱም በሰዎች ምላሽ አይስተጓጎልም። ይህ ሁለንተናዊ ፍጻሜ-ተኮር እቅድ በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ነቢያት ዘንድ የተለየ ነበር። ትንበያና የኪዳን ትክክለኛነት ምንታዌ አትኩሮቶች ነበሩ፣ የትንቢታዊ መልዕክቱ (ዝከ. ፊ እና ስቱዋርት፣ ገጽ 150)። ይህ የሚያመለክተው ነቢያት በቅድሚያ ኅብረታዊ ላይ ነው የሚያተኩሩት። እነሱ ዘወትር፣ በአጠቃሎሽ ሳይሆን፣ ሕዝቡን የሚመለከቱ ናቸው።

መ. አብዛኛው ትንቢታዊ ነገር በቃል የሚቀርብ ነው። ኋላ ላይ ነው የተጠናቀረው፣ በጭብጥ፣ በታሪክ ቅደም ተከተል፣ ወይም በሌሎቹ የቅርብ ምስራቅ የሥነ-ጽሑፍ ፈርጆች ነበር፣ አሁን ግን አናገኘውም። እሱ ሥነ-ቃል ስለሆነ፣ እንደ ስድ ንባብ ጽሑፍ ያለ መዋቅር የለውም። ይህም መጻሕፍቱን በቀጥታ ለማንበብ አዳጋች ያደርገዋል፣ እንዲሁም ያለ ልዩ ታሪካዊ መቼት ለመረዳት አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ሠ. ነቢያት መልእክቶቻቸውን ለማስተላለፍ የተለያዩ ፈርጆችን ይጠቀማሉ።

1. የፍርድ ቤት ትዕይንት - እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ወደ ፍርድ ቤት ይወስዳል፣ ብዙ ጊዜ የፍቺ ጉዳይ፣ እሱም ያህዌ ሚስቱን አልቀበልም ሲል (እስራኤል) ታማኝ ሆና ስላልተገኘች (ሆሴዕ 4፤ ሚክያስ 6)።
2. የልቅሶ ሙሾ - ልዩ የሆነው የዚህ ዓይነት መልዕክት መለኪያና ባሕርዩ “ወዮ” ልዩ መልክ ይሰጠዋል (ኢሳይያስ 5፤ ዕንባቆም 2)።
3. የኪዳናዊ ባርኮት መግለጫ - የኪዳኑ ሁኔታዊ ተፈጥሮ አጽንዖት ተሰጥቶታል እንዲሁም የሚያስከትለው ውጤት፣ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ፣ ለቀጣዩ ጊዜ ይወጣል (ዘዳግም 27-28)።

V. ትንቢትን ለመተርጎም ረጂ መመሪያዎች

ሀ. የዋነኛውን ነቢይ (አዘጋጅ) ሐሳብ ፈልግ የእያንዳንዱን ትንቢት ጽሑፋዊ ይዘት ታሪካዊ መቼት በመመዝገብ። እሱም ዘወትር የሚያካትተው እስራኤል ሙሴያዊውን ኪዳን በዚህ መንገድ መስበሩን ነው።

ለ. ሁሉንም ትንቢት አንብበህ ተርጉም፣ ክፋዩን ብቻ አይደለም፤ እሱን እንደ ይዘት መድብ። እሱም ከአካባቢዎች ትንቢት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ተመልከት። የሞላውን መጽሐፍ ማውጫ ለማውጣት ሞክሩ።

ሐ. የአንቀጹን ጥሬ ትርጉም እየተመለከትክ ሂድ፣ ከራሱ ከጽሑፉ ውስጥ ተምሳሌታዊ አጠቃቀም እስከሚያሳይህ ድረስ፤ ከዚያም ተምሳሌታዊ ቋንቋውን በጽሑፍ አስፍረው።

መ. በታሪካዊ መቼት እና በትይዩአዊ አንቀጾች አመላካችነት ተምሳሌታዊ ድርጊቶችን ተንትን። እነዚህ ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ ሥነ ጽሑፎች ዘመናዊ የምዕራባውያን ሥነ-ጽሑፍ እንዳልሆኑ ግን አስታውስ።

ሠ. ትንቢቶችን በጥንቃቄ አስፍር

1. እነሱ የደራሲውን ጊዜ ብቻ በተናጠል የሚያዩ ናቸውን?
2. እነሱ በእስራኤል ታሪክ ኋላ ላይ ተፈጻሚ ሆነዋልን?
3. እነሱ የቀጣይ ሁነት ናቸውን?
4. እነሱ ተጓዳኝ የሆነ ፍጻሜ እና የወደፊት ፍጻሜ ይኖራቸዋልን?
5. ለጥያቄዎችህ ምሪት ይሆን ዘንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችን ተከተል፣ ዘመናዊዎቹን ጸሐፊዎች ትተህ።

ረ. ልዩ ትኩረቶች

1. ትንበያው ሁኔታዊ ምላሽ የሚያስፈልገው ነውን?
2. ትንቢቱ ለማን እንደሆነ በእርግጠኝነት ታውቋልን (ለምን)?
3. በሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እና/ወይም በታሪካዊነት አኳያ ድርብ ፍጻሜ የመኖር አጋጣሚ አለውን?
4. የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት በተመስጦ ሆነው መሲሑን በብሉ. በብዙ ስፍራ ለማየት ችለዋል፣ እሱም ለእኛ ግልጽ ያልሆነልን። እነሱም ምድቦችን ወይም የቃላት አግባቦችን የተጠቀሙ ይመስላል። እኛ ተመስጧዊ እስካልሆንን ድረስ ይሄንን አግባብ ለእነሱ ብንተወው የተሻለ ነው።

VI. ረጂ መጻሕፍት

ሀ. *ለመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መመሪያ* በካርል ኢ. አሜንዲንግ እና ደብሊዩ. ዋርድ ባስኩ

ለ. *መጽሐፍ ቅዱስ ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ* በጎርዶን ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት

ሐ. *ነቢያት የእኔ አገልጋዮች* በኤድዋርድ ጄ. ያንግ

መ. ፐላውሼርስ እና ፐሩኒንግሁክስ፡ *የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ቋንቋ እና የፍጻሜን (አፖካሊፕቲክ) ዳግመኛ መመርመር* በዲ. ብሬንት ሳንዲ

ሠ. *አዲሱ ዓለም አቀፍ የብሉይ ኪዳን ሥነ-መለኮትና ትርጓሜ መዝገበ ቃላት፣* ቅጽ 4 ገጽ 1067-1078

***ራዕይ፡ ፡ 10፡8-11***

**[8]ከሰማይም የሰማሁት ድምፅ እንደ ገና ሲናገረኝና። ሂድና በባሕርና በምድር ላይ ከሚቆመው መልአክ በእጁ ያለችውን የተከፈተችውን መጽሐፍ ውሰድ ሲል ሰማሁ። [9]ወደ መልአኩም ሄጄ። ታናሺቱን መጽሐፍ ስጠኝ አልሁት። እርሱም፡- ውሰድና ብላት፥ ሆድህንም መራራ ታደርገዋለች በአፍህ ግን እንደ ማር ትጣፍጣለች አለኝ። [10]ከመልአኩም እጅ ታናሺቱን መጽሐፍ ወስጄ በላኋት በአፌም እንደ ማር ጣፋጭ ሆነች፤ ከበላኋት በኋላም ሆዴ መራራ ሆነ። [11]በብዙ ወገኖችና በአሕዛብም በቋንቋዎችም በነገሥታትም ላይ እንደ ገና ትንቢት ትናገር ዘንድ ይገባሃል ተባለልኝ።**

**10፡8 "ከሰማይም የሰማሁት ድምፅ እንደገና ሲናገረኝ ሰማሁ"** በርካታ ግምቶች አሉ፣ ስለ ተናጋሪው ማንነት። አንዳንዶች የሚያስረግጡት እግዚአብሔር፣ ወይም ክርስቶስ፣ ወይም መንፈስ ቅዱስ፣ ወይም ከብርቱዎቹ መላእክት አንዱ እንደሆነ ነው።

ቁ. 11 ላይ ድምፁ የብዙ ነው፣ የሚያመለክተውም በሦስትነቱ አንድ የሆነውን አምላክ ይሆናል። የብዙ ቁጥሮች በብኪ ለመለኮት ነው ጥቅም ላይ የሚውሉት (*Elohim* የሚለው ስምና "እኛ" የሚለው ዘፍ. 1:26፤ 3:22፤ 7:11፤ ኢሳ. 6:8) ላይ ያለው በበርካታ መንገዶች ተብራርቷል።

1. ሰዋሰዋዊ መልክ "የግርማዊነቱ ብዙነት" ይባላል፣ ይህም ብዙነት ጽንሰ-ሐሳቡን ወይም ቃሉን ያጠናክራል
2. ያህዌ በጥቅሉ ነው የሚናገረው ለመላእክት ጉባኤ (1 ነገሥ. 22:19፤ ኢዮብ 1:6፤ 2:1፤ ኤር. 23:18፤ ዳን. 7:10)
3. በሦስትነቱ አንድ የሆነው አምላክ ወይም የሥላሴ ጽንሰ-ሐሳብ መነሻ መልክ (መዝ. 110:1፤ ዘካ. 2:8፤ 17:10)

ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች 1:8 ላይ ተመልከት።

**10፡9 "'ውሰድና ብላት'"** ይህ የሕዝ. 2:8-3:14 ወይም ኤር. 15:16-17 ጠቃሽ ነው። ይህ ተምሳሌታዊ አድርጎ የእግዚአብሔርን መልእክት የመናገር ተልዕኮ ነው። ትንሿ መጽሐፍ ተምሳሌትነቷ የእግዚአብሔር መልእክት እሱም ለአማኞች ዋስትናን የያዘ ነው (ማር፣ መዝ. 19:10-11፤ 119:103) እንዲሁም ለማያምኑትም ፍርድን (መራራ)። ይህ ጥቅል ኢየሱስ ምዕራፍ 6 ላይ እንደከፈተው ዓይነት አይደለም። ይህ የሚያመለክተው ከብርቱው መልአክ የሆነውን መልእክት ነው (ዝከ. ቁ. 7-11)።

**10፡11 "እነርሱም አሉኝ"** ብርቱው መልአክ ወይም በሦስትነቱ አንድ የሆነው አምላክ ዮሐንስን እንደ ትንቢት መዝጋቢና ተናጋሪ ያጸናዋል።

▣ **"በብዙ ወገኖችና በአሕዛብም በቋንቋዎችም በነገሥታትም"** ይህ ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ለሁለቱም የማያምኑት (ዝከ. 11:9፤ 13:7-8፤ 14:6፤ 17:15) እና አማኞች (ማለትም፣ ከፍርድ ቀን በፊት ዝከ. 7:9፤ 15:4 እና ከፍርድ ቀን በኋላ ዝከ. 21:24፣26፤ 22:2 ነው)። ይህ ቁጥር ወንጌልን መስበክ ያመለክታል (ዝከ. 10:11፤ 14:6) ለሕዝቦች ሁሉ (ማቴ. 24:14፤ ማርቆስ 13:10) ወይም ተጨማሪ ጊዜያዊ የእግዚአብሔር ቁጣ ፍርዶችን ይተነብያል።

***ራዕይ 11***

***ራዕይ፡ ፡ 11፡1-6***

**[1]በትር የሚመስል መለኪያ ለእኔ ተሰጠኝ፥ እንዲህም ተባለልኝ። ተነሥተህ የእግዚአብሔርን መቅደስና መሠዊያውን በዚያም የሚሰግዱትን ለካ። [2]በመቅደሱም ውጭ ያለው አደባ ለአሕዛብ ተሰጥቶአልና ተወው አትለካውም፤ እነርሱም አርባ ሁለት ወር የተቀደሰችውን ከተማ ይረግጡአታል። [3]ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ። [4]እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው። [5]ማንምም ሊጐዳቸው ቢወድ እሳት ከአፋቸው ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል፤ ማንም ሊጐዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል። [6]እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው፥ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው።**

**11፡1 "በትር የሚመስል መለኪያ"** ባለፉት ክፍሎች ዮሐንስ የተመለከተው መላእክት የሚሠሩትን ተግባራት ነበር። ነገር ግን ሰባተኛው መለከት ላይ ዮሐንስ በድርጊቱ ውስጥ ይገባል።

"የመለኪያ በትር" የሚለው ቃል (*kalamos*፣ በዚህ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለው እዚህ ብቻ ነው) ሊያመለክት የሚችለውም የብኪን የወንዝ ዳር ሸንበቆ ነው፣ የቁመት መለኪያ መሣሪያ የነበረውን (ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ 19፡11 ላይ ተመልከት)። እነርሱም ከስምንት እና ሃያ ጫማ መካካል ቁመት ነበራቸው (ሕዝ. 40:5-42:20)።

▣ ***"ተነሥተህ ለካ"*** መለካት ምልክት የነበረው (1) የተስፋ እድገትና ጥበቃ (ኤር. 31:38-40፤ *ራዕ.* 21:15)። ይህም የሕዝቅኤልን የፍጻሜ ሰዓት መቅደስ የሚያመለክት ይሆናል (ዝከ. 40-48) ወይም የዘካርያስን አዲሲቷን ኢየሩሳሌም (ዝከ. 1:16፤ 2:1-13)፤ ወይም (2) ፍርድ (II ሳሙ. 8:2፤ II ነገሥ. 21:13፤ ኢሳ. 28:17፤ ሰቆ. 2:8)። እዚህ፣ ምዕራፍ 7 ላይ እንዳለው ማኅተም፣ እግዚአብሔር ለአማኞች ያለውን ጥበቃ ምልክት ነው። ይህ የቆይታ ጊዜ ከምዕራፍ 7 ጋር ትይዩ ከሆነ እንግዲያውስ መቅደሱ ሞላው የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው (አማኝ አይሁድ እና አማኝ አሕዛብ)። እንግዲያውስ ይህ ከምዕራፍ 12 ጋር ትይዩ ነው።

▣ ***"የእግዚአብሔርን መቅደስና መሠዊያውን በዚያም የሚሰግዱትን"*** የመቅደሱ ማንነት የሚወሰነው አንዱ ባለው የትርጓሜ ቅድመ-ግምት ነው።

1. የዮሐንስ ምስያ ከሕዝቅኤል 40-48 ተወስዷል ብለን ብንገምት፣ እንግዲያውስ ይህ ጥሬአዊ የፍጻሜ ዘመን ቤተ-መቅደስ ነው፣ በኢየሩሳሌም ያለ (2 ተሰ. 2፡4)።
2. ሆኖም፣ ዘካርያስ 2 ነው ብለን ጠቃሹን ብናስብ፣ እንግዲያውስ ምስያው የእግዚአብሔር ከተማ ነች፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።
3. ሰማያዊውን ቤተ መቅደስ ብናስብ (ዝከ. 7:15፤ 11:19፤ 15:58፤ ዕብ. 9:23) እንግዲያውስ የ7፡9 ብዛት ያለው ሕዝብ (ቤተ ክርስቲያን፣ እና ምዕራፍ 12 ላይ ያለችው ሴት) ትኩረት ሊሆኑ ይችላሉ (21:15-16)።

ዮሐንስ እዛ የሚያመለኩትን ሰዎች እንዲለካ መነገሩን መገንዘብ አስደናቂ ነው። ይህ ያልተለመደ ቃል ነው። ይህ ምስያ ከሕንፃ ላቅ ያለ ነገርን ያመለክታል። ይህ ምስያ ነው የእምነትን ሰዎች ከማያምኑት መለያ ምልክት የሚሆነው፣ የእግዚአብሔርን ቁጣ በመቀበል። ስለዚህ፣ እሱ በአማኞች ግንባር ላይ ከሚሆነው ከእግዚአብሔር ምልክት ትይዩ ነው (ዝከ. 7፡3-4)።

**11፡2 "በመቅደሱም ውጭ ያለው እድሞ"** ይህ ከውጭ ያለ እድሞ ጽንሰ-ሐሳብ የሚያመለክተው ከታሪክ አኳያ የአሕዛብ ስፍራ ነው፣ በሔሮድስ ቤተ-መቅደስ። በርካታ የብኪ ጠቃሾች አሉ፣ ስለ ኢየሩሳሌም ሐሳብና በአሕዛብ ስለሚረገጠው ቤተ መቅደስ (መዝ. 79:1-7፤ ኢሳ. 63:18፤ ዳን. 8:13፤ ዘካ. 12:3 በሴፕቱዋጂንት)። ኢየሱስ ቀጥተኛ ጥቅሻ ያደረገ ይመስላል ዳን. 8፡13ን ሉቃስ 21፡24 ላይ።

▣ **"አሕዛብ"** 2፡26 እና 10፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ ***"አርባ ሁለት ወራት"*** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ አርባ ሁለት ወራት

አርባ ሁለት ወራት የሚለው ቁጥር ከትንቢት አኳያ ባሕርይ የሚሆነው የስደቱን ጊዜ ነው። እውጭ ያለው ስፍራ መረገጥ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በታሪክ የተለያዩ ጊዜያት በማያምኑት ሥር መሆኑን ምሳሌ ነው— አንቲከስ አፒፋነስ፣ ሮማውያን በ70 ዓ.ም፣ እና የፍጻሜው ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ።

አርባ ሁለት ወራት፣ ወይም የእሱ አቻ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። መነሻው የዳንኤል መጽሐፍ ይመስላል።

1. ዳንኤል 7፡25፤ 12፡7 "ዘመን፣ ዘመናት፣ የዘመናት እኩሌታ" ወይም 1277 ቀናት
   ("ጊዜ" ከዓመት እኩል አድርጎ በመገመት) ተጠቅሷል
2. ዳንኤል 8፡14 2300 ማታ እና ጠዋት ተጠቅሷል
3. ዳንኤል 12፡11 1290 ቀናት ተጠቅሷል
4. ዳንኤል 12፡12 1335 ቀናት ተጠቅሷል። ተመሳሳይ ሐረግ *ራዕ.* 12:6 (1260 ቀናት) እና 13:5 (42 ወራት) ተጠቅሷል።

እነዚህ ሁሉ ሁነቶች ግምት ውስጥ ሲገቡ፣ የእነርሱ ልዩነት ሊል የሚሻው የቁጥሮቹን ተምሳሌታዊ ተፈጥሮ ነው፣ የእነርሱ ለአርባ ሁለት ወራት ተቀራራቢነት ሊያሳይ የሚሻው ለስደቱ ጊዜ ተምሳሌታዊ ቁጥር ነው። ሦስት ከግማሽ የሰባት እኩሌታ እስከሆነ ድረስ፣ እሱ የሚመስለው የተጠናቀቀው የመከራ ጊዜ አመላካች ነው፣ እንዲያጥር የተደረገው (ማቴ. 24:22፤ ማርቆስ 13:20፤ ሉቃስ 21:24)። መከራ በእግዚአብሔር ፍቅር የተወሰነ ነው፣ ፍርዱ እንደሆነ ሁሉ።

▣ ***"ቅድስቲቱ ከተማ"*** ይህ ሊያመለክት የሚችለው ኢየሩሳሌምን ነው (ኢሳ. 52:1፤ ማቴ. 27:53)። ሆኖም፣ *ራዕ.* 3፡12 ላይ ያለውን መቅደስ ትርጓሜ ተከትሎ፣ የአኪ አማኞችን እንደሚጠቅስ፣ ተመሳሳይ ዘዴ ይህን ሐረግ መከተል ይኖርበታል። በራዕይ ኋለኞቹ ምዕራፎች እሱ የሚያመለክተው የአኪን የእግዚአብሔር ሕዝቦችን ነው (ዝከ. 20:9፤ 21:2፣10፤ 22:19)።

ዮሐንስ ዘይቤዎችን ከብኪ አምጥቶ ለአኪ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጥቅም ላይ አውሏቸዋል። ቤተ ክርስቲያን የተሠራችሁ ባመኑ አይሁድና አሕዛብ ነው። ራዕይ ላይ በአይሁድ ዘርም ሆነ በአሕዛብ ላይ ምንም ዓይነት አጽንዖት የለም። ከእንግዲህ ወዲያ አይሁድም ግሪክም የለም (1 ቆሮ. 12:13፤ ገላ. 3:28፤ ቆላ. 3:11)።

**11፡3 *"ለሁለቱ ምስክሮቼ ሥልጣን እሰጣለሁ"*** ይህ የሚያመለክት የሚመስለው የእግዚአብሔር አብን ንግግር ነው፣ ምክንያቱም ኢየሱስ ቁ. 8 ላይ ስለተጠቀሰ (ምንም እንኳ የግሪክ እጅ ጽሑፍ ችግር እዚህ ተውላጠ ስም ላይ ቢኖርም፣ እሱም ፒ[47] እና ℵ ላይ ስለተገደፈ)።

▣ ***"ሁለቱ ምስክሮቼ"*** ስለ እነዚህ ብርቱ ሰባክያን ማንነት በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡

1. ጠቃሹ (ዝከ. ቁ. 4) ከዘካ. 4:3፣11፣14። ይህ በዋነኝነት የሚያመለክተው የዳዊትን ዘር መመለስ ነው፣ ዘሩባቤል፣ እና የታላቁ ካህን ዘር መመለስ ነው፣ ኢያሱ፣ እነርሱም ሁለቱ መንፈስ-መር መሪዎች ነበሩ (ሁለቱ የወይራ ዛፎች) ከባቢሎን ግዞት መመለስን የመሩ (ማለትም፣ የተመለሰ የእግዚአብሔር ሕዝብ)።
2. ሁለቱ መቅረዞች (ዝከ. 1:20) የሚያመለክቱትም ሁለቱን ታማኝ ቤተ ክርስቲያኖችን ነው፣ ሰምርኔስ፣ 2:8-11 እና ፊልድልፍያ፣ 3:7-13።
3. ሁለቱ ምስክሮች የሚያመለክቱት በፍርድ ቤት የሚደረግን ምስክርነት ነው (ዘኍ. 35:30፤ ዘዳ. 17:6፤ 19:15)።
4. የእነዚህ ሁለት ምስክሮች ገለጻ የሚያመለክተው ኤልያስን (ሰማይን የዘጋ ከቁ. ቁ. 6፣ 1 ነገሥ. 17:1፤ 18:1፤ ሉቃስ 4:25፤ ያዕቆብ 5:17 እና እሳትን ማውረድ፣ ዝከ. 1 ነገሥ. 18:24፣38፤ 11 ነገሥ. 1:10፣12) እና ሙሴ (ውኃውን ወደ ደም የቀየረ ከቁ. 6፣ ዘጸ. 7:17-19)። እነዚህ ሁለቱ በመለወጥ ተራራ ላይ ከኢየሱስ ጋር ታይተዋል (ማቴ. 17:4)።
5. በይነ ኪዳናዊው አፖካሊፕቲካዊ መጽሐፍ 1 ሔኖክ 90:31 እና ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣ ተርቱሊያን እና ሂፖሊተስ እንደሚያስረግጡት እነርሱ ከብሊ ሁለቱ ሰዎች ናቸው፣ ተፈጥሯዊ ሞትን ያልሞቱት፣ ሔኖክ (ዘፍ. 5:21-24) ኤልያስ (11 ነገሥ. 2:11)።
6. የአኢሙቅ የግርጌ ማስታወሻ የሚያስረግጠው፣ እሱ የሚጠቅሰው ጴጥሮስንና ጳውሎስን ነው፣ ሁለቱም በሮም ሰማዕት ሆነዋል፣ በኔሮ አገዛዝ (ገጽ 435)።

እኔ በግሌ የምመለከታቸው እንደ መላው የእግዚአብሔር ሕዝብ ምስክርነት ተምሳሌት ነው፣ በሰባቱ ማኅተሞች ትይዩአዊ አወቃቀር የተነሣ እና በቆይታ ጊዜው እና ከሰባቱ መለከቶችና ከቆይታ ጊዜው የተነሣ። ስለዚህ፣ ሁለቱም 144,000 (አማኝ አይሁድ) እና ሊቆጠሩ የማይችሉ ወገኖች (አማኝ አሕዛብ)፣ እንዲሁም ሁለቱ ምስክሮች፣ ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታሉ።

▣ ***"ማቅ ለብሰው"*** ይህ ሊሆን የሚችለው አንድም (1) የኀዘንና የንስሐ ምልክት ነው (ዘፍ. 37:34፤ 11 ሳሙ. 3:31) ወይም (2) የነቢይ የተለመደው ልብስ (11 ነገሥ. 1:8፤ ኢሳ. 20:2፤ ዘካ. 13:4)።

▣ ***"ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ"*** እያንዳንዱ ሠላሳ ቀናት ያለው አርባ ሁለት ወር ከሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ቀናት ጋር እኩል ነው። ወንጌል በማያምኑት አሕዛብ በሚደረገው ስደት ጊዜ ይሰበካል (ማቴ. 24:8-14፣ 21-22)። ተምሳሌታዊ ቁጥሩ የሚመጣው ከዳን. 7:25፤ 12:7 ሲሆን በራዕይ (ዝከ. 12:6፤ 13:5) ተዘውትሮ ጥቅም ላይ ይውላል።

**11:4 *"ሁለቱ የወይራ ዛፎች"*** ይህ ጠቃሽነቱ ለዘሩባቤል ነው፣ ከግዞት የተመለሰው የዳዊት ዘር እና ኢያሱ፣ ከግዞት የተመለሰው የአሮን ዘር (ዘካ. 4:3፣11፣14)። ይህ ምናልባት የሚያመለክተው ወንጌል የሚመሰክረው የፍጻሜ ዘመን የሚወክለው ንጉሣዊ መሲሐዊ እና ካህናዊ መሲሐዊ አጽንዖት ነው (ኢየሱስ እንደ ንጉሥና ካህን፣ መዝሙር 110፤ ዕብ. 1:3)። እነዚህ ተመስጧዊ የንስሐ ሰባክያን የእግዚአብሔርን ብርሃን ያመጣሉ (ዘካርያስ 4) ለዐመጻኛው ዓለም (ዐመጻኛው እስራኤል አሁን ዐመጻኛው የሰው ዘር ሆኗል፣ ኢሳ. 6:9-11፤ 43:8-13፤ ኤር. 5:21-29፤ ሕዝ. 12:2)።

**11:5 *"ማንምም ሊጎዳቸው ቢወድ... ማንም ሊጎዳቸው ቢወድም"*** እነዚህ ሁለቱም አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፣ የሚታሰበውም ሊጎዷቸው የሚፈልጉ እንዳሉ ነው፣ ነገር ግን እነርሱ በመለኮታዊ ይጠበቃሉ፣ ተልእኳቸው እስከሚፈጸም ድረስ።

▣ ***"እሳትም ከአፋቸው ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል"*** የአፋቸው ኃይል እሱም የሚያውጁት መልእክት ኃይል እንደሆነ አስተውል። በራዕይ አፍ መሣርያ ነው፣ ምላስም ሰይፍ (ዝከ. 9:17፤ 19:15፤ ዕብ. 4:12)።

**11:6** እነዚህ የብሊ ድርጊቶች የኤልያስን (1 ነገሥ. 17:1) እና የሙሴን (ዘጸ. 7:17-19) ድርጊት ያስታውሳሉ።

***ራዕይ፡ ፡ 11:7-10***

**[7]ምስክራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፋቸውማል ይገድላቸውማል። [8]በድናቸውም በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይተኛል እርስዋም በመንፈሳዊ ምሳሌ ሰዶምና ግብጽ የተባለች ደግሞ ጌታቸው የተሰቀለባት ናት። [9]ከወገኖችና ከነገዶችም ከቋንቋዎችም ከአሕዛብም የሆኑ ሰዎች ሦስት ቀን ተኩል በድናቸውን ይመለከታሉ፥ በድናቸውም ወደ መቃብር ሊገባ አይፈቅዱም። [10]እነዚህም ሁለት ነቢያት በምድር የሚኖሩትን ስለ ሣቀዩ በምድር የሚኖሩት በእነርሱ ላይ ደስ ይላቸዋል በደስታም ይኖራሉ እርስ በርሳቸውም ስጦታ ይሰጣጣሉ።**

**11:7 *"ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ"*** ይህ የዳንኤል 7 ጠቃሽ ከሆነ፣ እንግዲያውስ አውሬው ዳንኤል ሰባት ላይ የተጠቀሱት አራት አውሬዎች ድብልቅ ዘይቤ ነው፣ የሚቆመውም ለመጻረሻው የፍጻሜ ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው (2 ተሰ. 2:3)።

"ጥልቁ" የሰይጣናዊ ቤት ነው (ዝከ. 9:1፤ 20:1)። ይህ የአውሬው ጽንሰ-ሐሳብ ምዕራፍ 13 እና 17 ላይ ዳብሯል።

▣ ***"ከእነርሱ ጋር ውጊያ ያደርጋል፣ ያሸንፋቸውማል፣ ይገድላቸውማል"*** ይህ የዳን. 7:21 ጠቃሽ ነው፣ እሱም እጅግ በሙላት ራዕይ 13 ላይ ተብራርቷል። እዚህ፣ ሐረጉ የሚያመለክተው ሁለቱ ምስክሮች ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ ተምሳሌታዊ መሆናቸውን ነው (ዝከ. 13:7 ማለትም፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ)። እነርሱ ከመከራና ከሞት አይጠበቁም።

**11:8 *"በድናቸውም አደባባይ ላይ ይተኛል"*** ይህ የሞቱ አካላት ውርደት የሚያሳየው ንቀትን ማመላከቻ መንገድ ነው (ዝከ. ቁ. 9; ዘዳ. 28:26; መዝ. 79:2; ኤር. 7:33; 8:2; 16:4; 19:7; 34:20)። ሆኖም፣ እግዚአብሔር የእነርሱን የሚታይ አካላት በኃይለኛ ትንሣኤ ተጠቅሞበታል፣ ለኃይሉ መገለጫና ለመልእክታቸው ማረጋገጫ።

▣ ***“ታላቂቱ ከተማ”*** ይህ የኢየሩሳሌም ገለጻ ይመስላል፤ ሆኖም፣ ዘይቤአዊ ቋንቋው የሚያመለክተው በምድራዊ መንግሥት እና በሰማያዊ መንግሥት መካከል ያለውን መንፈሳዊ ውጊያ ነው። የእኔ ምክንያቶች እነሆ፡

1. “ታላቂቱ ከተማ” የሚለው ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ለባቢሎን ወይም ለሮም ነው (ዝከ. 16፡19; 17፡18; 18፡10,16,18,19,21)።
2. ምንም እንኳ ኢየሩሳሌም ሕዝ. 16፡46-49 እና ኢሳ. 1፡9-10, ላይ ሰዶም ተብላ ብትጠራም፣ ግብፅ ተብላ ፈጽሞ አልተጠራችም፤ ሰዶምና ግብፅ የኃጢአትና የባርነት ዘይቤዎች ናቸው።
3. “እዚያም ጌታ የተሰቀለበት” ኢየሩሳሌምን የሚያመለክት ይመስላል፣ ነገር ግን የአምላክ ተቃዋሚ የሆኑት የዚህን ዓለም መንግሥታት የመግለጫ መንገድ ሊሆን ይችላል።
4. “ከወገኖችና ከነገዶችም ከቋንቋዎችም ከአሕዛብም” ቁ. 9 ላይ የሚያመለክተው
   ሀ. መላው ዓለም የሚገኝባት ቦታ፣ እሱም ከኢየሩሳሌም ይልቅ ለሮም የሚሰማማ
   ለ. “ከተማ” ለዐመጸኛው የሰው ልጅ ጥቅም ላይ የዋለ ዘይቤ ነው (ዘፍ. 4፡17; 10፡8-10)
5. “በምድር የሚኖሩት በእነርሱ ላይ ደስ ይላቸዋል በደስታም ይኖራሉ” ቁ. 10 የሚያመለክተው የእነዚህ ሁለት ምስክሮች መልእክት ለአይሁድ ብቻ አይደለም፣ በመላው ዓለም ላሉ ለማያምኑት ሁሉ እንጂ።

ይህም የሚገልጸው በዚህ ዓለም መንግሥት እና በመሲሐዊው መንግሥት መካከል ቀጣይነት ያለውን ውጊያ ነው (ዝከ. 11፡ 15)፣ በተለይም እንደ ዳንኤል 2 እና መዝሙር 2።

**11፡9 “ከወገኖችና ከነገዶችም ከቋንቋዎችም ከአሕዛብም”** 10፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ ***“ሦስት ቀን ተኩል”*** የቁ. 9 ጊዜ ከቁ. 11 ጋር ሲደባለቅ ከቁጥር ሰባት ጋር እኩል ይሆናል፣ እሱም በራዕይ እጅግ ተደጋግሞ ጥቅም ላይ የዋለ። ይህ ሁነት የእግዚአብሔር ፍጹም ሰዓት ነው።

**11፡9 “ደስ ይላቸዋል በደስታም ይኖራሉ እርስ በርሳቸውም ስጦታ ይሰጣጣሉ”** አንዳንዶች ይሄን የሚመለከቱት እንደ ፑሪም (የአይሁድ በዓል ግብዣ) ነው (አስቴር 9፡19፣22)። እሱም እጅግ የሚመሳሰለው ከዮሐንስ 16፡20 ጋር ነው (“ዓለም ደስ ይለዋል”)። ይህ የማያምነው ዓለም ደስታ የሁለቱን ምስክሮች መልእክት ኃይል ያመለክታል፣ የማያምኑት ግን ንስሐ አይገቡም (ዝከ. 9፡20-21; 16፡9,11)።

### ራዕይ፡ 11፡11-13

**[11]ከሦስቱ ቀን ተኩልም በኋላ ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው በእግሮቻቸውም ቆሙ፥ ታላቅም ፍርሃት በሚመለከቱት ላይ ወደቀባቸው። [12]በሰማይም። ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ፤ ጠላቶቻቸውም እየተመለከቱአቸው ወደ ሰማይ በደመና ወጡ። [13]በዚያም ሰዓት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፥ ከከተማይቱም አሥረኛው እጅ ወደቀ፥ በመናወጥም ሰባት ሺህ ሰዎች ተገደሉ፥ የቀሩትንም ፍርሃት ያዛቸው፥ ለሰማዩም አምላክ ክብር ሰጡ።**

**11፡11 *“ሦስቱ ቀን ተኩልም”*** ይህ ከዳንኤል የተጠቀሰ ነው፣ እሱም የስደቱ ተምሳሌታዊ ጊዜ የሆነ። 11፡9 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **“ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው”** ይህ የሕዝቅኤል 37 ጠቃሽ ነው፣ የደረቁ አጥንቶች ሸለቆ። ይህም የዕብራይስጥ ቃል “*ruach*” ዓይነት ነው፣ ፍችውም መተንፈስ፣ ነፋስ፣ እና መንፈስ (እንደ የግሪኩ ቃል *pneuma*)።

### ልዩ ርዕስ፡ መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ

I. የግሪክ ቃላት
   ሀ. *pneō*፣ መንፋት
   ለ. *pnoʹ*፣ ነፋስ፣ ትንፋሽ
   ሐ. *pneuma*፣ መንፈስ፣ ነፋስ
   መ. *pneumatikos*፣ በመንፈስ መወሰድ
   ሠ. *pneumatikōs*፣ መንፈሳዊነት
II. የግሪክ ፍልስፍናዊ ዳራ (*pneuma*)
   ሀ. አርስቶትል ቃሉን የተጠቀመበት እንደ የሕይወት ኃይል ነው፣ እሱም ከልደት ጀምሮ ራስን እስከመግዛት ድረስ እየዳበረ የሚሄድ
   ለ. ስቶይኮች ቃሉን የሚጠቀሙበት ከ*psuchʹ*፣ (ነፍስ) ጋር በተመሳሳይ ነው፣ *psuchʹ*፣ (አዕምሮ) ጭምር፣ ከአምስቱ የስሜት ሕዋሳት እና ከሰው አስተሳሰብ ጋር በተያያዘ።
   ሐ. የግሪክ አስተሳሰብ - ቃሉ ከመለኮታዊ ድርጊት ጋር አቻ ሆኗል (ማለትም፣ መናፍስት ጠሪነት፣ አስማት፣ መተት፣ ሟርት፣ ወዘተ...)
III. ብሉይ ኪዳን (*ruah*)
   ሀ. የአህዳዊው አምላክ ድርጊቶች (ማለትም፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በብኪ 90 ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ ውሏል)
      1. በአዎንታዊ፣ ዘፍጥረት 1፡2

2. በአሉታዊ፣ 1ሳሙ. 16:14-16፣23፤ 1ነገሥ. 22:21-22፤ ኢሳ. 29:10

ለ. እግዚአብሔር የሰጠው ሕይወት በሰው ውስጥ የሚሠራው (ማለትም፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ፣ ዘፍ. 2፡7)

ሐ. ሴፕቱዋጀንት *ruahን በ pneuma* ይተረጉመዋል (100 ጊዜ ያህል በLXX (ሰባው) ጥቅም ላይ ውሏል)

መ. በኋለኞቹ ራቢያዊ ጽሑፎች፣ የፍጻሜ ትንቢት ጽሑፎችና የሙት ባሕር ጥቅሎች፣ እነሱም የዞሮአስትሪያኒዝም ተጽዕኖ ያለባቸው፣

*pneuma* ጥቅም ላይ የዋለው ለመላእክት እና ለአጋንንት ነው

IV. አዲስ ኪዳን (*pneuma*)

ሀ. የእግዚአብሔር ልዩ መገኘት፣ ኃይል፣ እና ሰጭነት

ለ. መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የቤተ-ክርስቲያን ሥራ ጋር ይያያዛል

1. ትንቢት
2. ተአምራት
3. ወንጌልን በግልጽ ለማወጅ
4. ጥበብ (ማለትም፣ ወንጌል)
5. ደስታ
6. አዲሱን ዘመን የሚያመጣ
7. ዳግም ልደት (ማለትም፣ መቃተትና ማደር)
8. ክርስቶስን መምሰል
9. የአገልግሎት የተለያዩ ጸጋዎች
10. ለአማኞች መጸለይ

መንፈስ ቅዱስ የሰው ልጆችን ፍላጎት ያነቃል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ኅብረት፣ ይኸውም እነሱ ለተፈጠሩበት። ይህ ኅብረት ይቻላል፣ ምክንያቱም ከኢየሱስ፣ ከእግዚአብሔር መሲሕ አካልና ሥራ የተነሣ። አዲሱ መንፈሳዊ ንቃት ክርስቶስን ወደ መሰለ ሕይወት፣ አገልግሎት፣ እና መታመን ይመራል።

ሐ. የበለጠ የሚታወቀው እንደ መንፈሳዊ ቀጣይነት ባለው መንፈስ ቅዱስ በአንድ ዳርቻ በኩል፣ እና የሰው ልጅ እንደ ሥጋዊ የዚህ ዓለም ፍጡር፣ ግን ደግሞ በሌላው ዳርቻ የእግዚአብሔር አምሳል በሆነ መንፈሳዊ ፍጡር ነው።

መ. ጳውሎስ የአዲስ ኪዳን ደራሲ ነው፣ እሱም የመንፈስ ቅዱስን/መንፈስን ሥነ-መለኮት ያዳበረ ነው።

1. ጳውሎስ መንፈስን ይጠቀማል ሥጋን ለመቃረን (ማለትም፣ የኃጢአት ተፈጥሮ)
2. ጳውሎስ መንፈስን ይጠቀማል ሥጋዊነትን ለመቃረን
3. ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን/መንፈስን ይጠቀማል የሰዎችን አስተሳሰብ፣ እውቀት፣ እና ሕላዌ ለመቃረን

ሠ. ከ1ቆሮንቶስ ጥቂት ምሳሌዎች

1. መንፈስ ቅዱስ፣ 12፡3
2. የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ የሚገለጸው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው፣ 2፡4-5
3. የእግዚአብሔር ድርጊቶች በአማኝ ውስጥ
   ሀ. አዲስ አስተሳሰብ፣ 2:12፤ 14:14፣32
   ለ. አዲስ ቤተ-መቅደስ፣ 3:16፤ 6:19-20
   ሐ. አዲስ ሕይወት (ማለትም፣ ሞራላዊነት)፣ 6፡9-11
   መ. አዲስ ሕይወት፣ በጥምቀት ተምሳሌታዊ የሆነ፣ 12፡13
   ሠ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት (ማለትም፣ ዳግም ልደት)፣ 6፡17
   ረ. የእግዚአብሔር ጥበብ፣ የዓለም ጥበብ ሳይሆን፣ 2:12-15፤ 14:14፣32፣37
   ሰ. እያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያለው መሆኑ፣ ለአገልግሎት፣ ምዕራፍ 12 እና 14
4. መንፈሳዊው በተቃርኖ ከሥጋዊው ጋር፣ 9:11፤ 10:3፤ 15:44
5. መንፈሳዊው ዓለም በተቃርኖ ሥጋዊው ዓለም፣ 2:11፤ 5:5፤ 7:34፤ 15:45፤ 16:18
6. ወደ ሰዎች መንፈሳዊ/ውስጣዊ ሕይወት የማመላከቻ መንገድ፣ ከአንዱ ሥጋዊ አካል ልዩነት እንዳለው፣ 7፡34

ረ. ሰዎች በተፈጥሮ በሁለት ዓለማት ነው የሚኖሩት (ማለትም፣ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ)። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ከነበረው ወዳጅነት ወድቋል (ዘፍ. 3)። በክርስቶስ ሕይወት፣ ትምህርቶች፣ ሞት፣ ትንሣኤ፣ እና በመመለሱ ተስፋ በኩል፣ መንፈስ ቅዱስ የሰው ልጆችን ይማልዳል በወንጌል እምነትን እንዲለማመዱ፣ በዚሁም ነጥብ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ይኖራቸው ዘንድ የተመለሱ። መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ አካል ሲሆን እሱም አዲሱን የጽድቅ ዘመን ባሕርይ ያደረገ ነው። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር አብ ወኪል እና የወልድ ተጠሪ ነው፣ በዚህ "ዘመን"። ችግር የሚኖርበት ምክንያት አዲሱ ዘመን በጊዜው በመምጣቱና፣ የአሮጌው ዘመን ዐመጸ ገና ባለበት ጊዜ መሆኑ ነው። መንፈስ ቅዱስ አሮጌውን ወደ አዲስ ይለውጠዋል፣ ሁለቱም አንድ ላይ ቢኖሩም።

**11፡12 "በሰማይም። ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ፤"** አንዳንዶች የሚመለከቱት የቤተ ክርስቲያን ድንገተኛ መነጠቅ ነው፣ ቁ 4፡1 ላይ፣ ዮሐንስ ወደ ሰማይ የተወሰደበት፣ ሌሎች የሚመለከቱት በመከራው መካከል የሚሆን የቤተ-ክርስቲያን ምሥጢራዊ መነጠቅ ነው፣ እነዚህ ሁለት ምስክሮች ወደ ሰማይ የተጠሩበት፣ በዚህ ቁጥር ላይ። እዚህም ደግሞ የእኛ ቅድመ-ግምቶች እና ሥነ-መለኮታዊ አቋሞች፣ የተምሳሌታውያኑን፣ አሻሚዎቹን ጽሑፎች ትርጉሞች ያወጣሉ!

▣ **"ከዚያም እነርሱ ወደ ሰማይ በደመና ወጡ።"** ይህ መለኮታዊ መጓጓዣ ነው። መሲሑ በሰማይ ደመና ይጓጓዛል፣ ዳን. 7፡13 ላይ። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ያረገው በደመና ነው (ሐዋ. 1፡9)። ኢየሱስ በሰማይ ደመና ይመለሳል ማቴ. 24:30; 26:64; ማርቆስ 13:26; I ተሰ. 4:17; ራዕ. 1:7; 14:14)።

**11፡13 "በዚያም ሰዓት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፥ ከከተማይቱም አሥረኛው እጅ ወደቀ"** የመሬት መንቀጥቀጥን በተመለከተ ራዕይ ላይ ሰባት ማጣቀሻዎች አሉ (ዝከ. 6:12; 8:5; 11:13,19; 16:18)። ይህ የሚያሳየው በመከናወን ላይ ያለውን፣ ቀጣዩን፣ የተወሰነውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው፣ በማያምኑት ላይ። ይህም የሕዝ. 38፡17-23 ጠቃሽ ይሆናል።

▣ **"የቀሩትንም ፍርሃት ያዛቸው፥ ለሰማዩም አምላክ ክብር ሰጡ።"** በርካታ ውይይቶች "የተቀሩት" በሚለው ቃል ላይ ተካሂደዋል። እሱም ሊያመለክት የሚችለው

1. በጥሬው የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች (ዘካ. 12፡10) ወይም ሮም
2. በመከራው ሰዓት የዳኑት፣ ማለትም፣ በእውነት ንስሐ የገቡ
3. አማኝ አይሁድ፣ ከሮሜ 11
4. ሰዎች፣ እንደ ናቡከደነፆር እና ሲረስ የመሳሰሉት፣ በእግዚአብሔር ድርጊት የደነገጡት፣ ነገር ግን በእውነት ያልተለወጡት። በ9:20-21; 14:7-8 እና 16:10 ምክንያት፣ ቁ. 4 የተሻለ አማራጭ ነው።

ሆኖም፣ 16፡9 ላይ ክብር መስጠት ከንስሐ ጋር ይያያዛል። እሱም በርግጥ የሚቻለው እነዚህ (አይሁድ ወይም ጣዖት አምላኪዎች) አምነዋል! ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ዓይነተኛ ዓላማ ነው (ዝከ. 9:20-21; 16:9,11)

***ራዕይ፡* 11፡14**

[14]***ሁለተኛው ወዮ አልፎአል፤ እነሆ፥ ሦስተኛው ወዮ በቶሎ ይመጣል።***

**11፡14** ይህ የመሸጋገሪያ አገባብ (9፡12፤ 12፡12)።

***ራዕይ፡* 11፡15-16**

[15]***ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም። የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል*** [16]***የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ። በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ፣***

**11፡15 "የዓለም መንግሥት"** ኪጀት እና አኪጀት "የዚህ ዓለም መንግሥታት" የሚል አላቸው። የብዙ ቁጥሩ በማናቸውም በጥንታዊ የግሪክ ጽሑፎች ላይ የለም።

▣ **"ሆነች"** ይህ የድርጊት መካከለኛ (አረጋጋጭ) አመላካች ነው። ይህ የወደቀው የሰው ልጅ መንግሥታት አገዛዝ ፍጻሜና የአምላካችን አገዛዝ መጀመሪያ ነው (ዝከ. 12፡10)። አዲሱ የመንፈስ ዘመን በሙላት መጥቷል። ይህ የሚያረጋግጠውም የማጠቃለያው ንድፈ-ሐሳብ፣ እሱም፣ ዳግም ምጽአቱ የሚሆነው ከእያንዳንዱ ከሦስቱ የፍርድ ዑደቶች ፍጻሜ በኋላ ነው፡ ማኅተሞቹ (ዝከ. 6፡12-17)፣ መለከቶቹ (ዝከ. 11፡15-18)፣ እና ጽዋዎቹ (ዝከ. 19)። ራዕይ ዜና መዋዕላዊ፣ ቅደም ተከተላዊ ተራ ያለው አይደለም፣ ነገር ግን በሰባት ዑደቶች ድራማዊ አቅርቦት ነው፣ እያንዳንዱም ተመሳሳይ ጊዜን የሚመለከት፣ ነገር ግን ማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ በተከታታይ እና በተጠናከረ ደረጃ የሆኑ ፍርዶች ናቸው (1/4፣ 1/3፣ ሙሉ)።

▣ **"ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ"** አብና ወልድ እንዴት በቅርብ እንደተያያዙ ተገንዘብ (መዝሙር 2)። ደግሞም፣ የI ቆሮ. 15:24-28 እና ኤፌ. 5:5 አጽንዖት አሁን መፈጸሙን ተገንዘብ። አንዳንዶች ከዘካ. 14፡9 ጠቃሽ ይመለከታሉ፣ እሱም ሊሆን የሚችል፣ ምክንያቱም የዮሐንስ ተመራጭ የአፖካሊፕቲካዊ ምስያ ምንጭ ዳንኤል፣ ሕዝቅኤል፣ እና ዘካርያስ በመሆኑ።

▣ **"ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል"** ይህ የሚያመለክተው የአምላካችንን ዘላለማዊ ንግሥና ነው (ዘጸ. 15:18; መዝ. 10:16; 29:10; ኢሳ. 9:6-7; ዳን. 2:44; 4:34; 7:14,27; ዘካ. 14:9; ሉቃስ 1:33; I ተሰ. 4:17; II ጴጥ. 1:11), የሚሊኒየማዊ ንግሥና አይደለም (ራዕይ 20) የክርስቶስ። ይህ በርግጥ የማቴ. 6፡10 የኢየሱስ ጸሎት ፍጻሜ ነው፣ ይኸውም የእግዚአብሔር ፍቃድ በምድር ላይ ይሆናል፣ በሰማይ እንደሆነ ሁሉ።

የእግዚአብሔር መንግሥት ዋነኛ ጭብጥ ነው በወንጌላትና በራዕይ ላይ። ተለዋዋጭነትና ተቃርኖ አለው፣ በወቅቱ እውነታ (ድኅረ-ሚሊኒየማዊ እና በሚሊኒየማዊ) መካካል እና በወደፊቱ ቅድጅት (ታሪካዊ ቅድመ-ሚሊኒየማዊ እና ከፊል ቅድመ-ሚሊኒየማዊ)። ይኸው ተመሳሳይ ተለዋዋጭነት ደግሞ በምድራዊ ገጽታ (ሚሊኒየማዊ) እና በእርሱ ዘላለማዊ ገጽታ መካከል አለ። አንዳንድ አታቾች፣ አስተምህሮዎች፣ እና መሠረተ እምነቶች በተለዋዋጩ በአንደኛው ገጽታ ይኖራሉ፣ ነገር ግን ቀሪዎቹን ችላ ይሏቸዋል ወይም ይጠመዝዟቸዋል፣ ከራሳቸው ቅድመ-ግምት እና ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓት ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ።

ለምዕራባውያን ሰዎች እጅግ ጠጠር ይላል፣ የምስራቃዊ ሥነ-ጽሑፍን ተለዋዋጭነት፣ ዘይቤአዊነት፣ እና ተቃርኖ ለማጣጣም፣ በተለይም አፖካሊፕቲካዊ ዘውጉን። ጌታችንና የእርሱም ክርስቶስ ነግሠዋል፣ በንግሥና ላይ ናቸው፣ ይነግሣሉም፤ ዝርዝሩ እጅግም አስፈላጊ አይደለም! መሲሐዊ ንግሥና ለተወሰነ ጊዜ ሊኖር ይችላል (1 ቆሮ. 15:23-28); ብሔረ እስራኤል ጥቂት ክፍል ሊኖረው ይችላል (ሮሜ 11)። ሆኖም፣ የራዕይ ዘይቤዎችና ተምሳሌቶች ሁለንተናዊዋን ቤተ ክርስቲያንን እንጂ እስራኤልን አይመለከቱም (ዳን. 2:34-35,44)። እኔ በግሌ ክፍት ነው የምተወው፣ እስራኤል በፍጻሜ ዘመን ሁነቶች ላይ ድርሻ እንደሚኖረው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአብርሃም ዝርዮች ቃል ስለ ገባ (ኢሳ. 9:6-7; ዘካ. 12:10) በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ በመመሥረት (ሕዝ. 36:22-38)።

**11:16 *"ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች"*** ልዩ ርዕስ 4:4 ተመልከት።

### *ራዕይ፡ 11:17-18*

***[17]ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ። ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን፤ [18]አሕዛብም ተቈጡ፥ ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፥ ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ፥ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ።***

**11:17-18** ይህ የምስጋና ጸሎት በአኪጀት፣ አየተመት፣ እና አእት በቅኔ መልክ ነው የተጻፈው፣ በአአመመቅ እና አኢመቅ ደግሞ በስድ-ንባብ። እነዚህ ፈንቅለው የወጡ ጸሎትና ምስጋና የቀጣዩ መገለጥ የተሻሉ ተርጓሚዎች ናቸው (ከዝማሬዎች እና መልአካዊ ትርጓሜዎች ጋር)።

**11:17 *"ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥"*** ይህ የሚያመለክተው ሦስቱን ዋነኛ የብኪ የእግዚአብሔር መጠሪያዎችን ነው።

1. ያህዌ፣ የኪዳን አምላክ አንደ አዳኝ (ዘጸ. 3:14; መዝሙር 103)
2. *Elohim,* ፈጣሪ አምላክ እንደ ሰጪ እና ጠባቂ (ዘፍ. 1:1; መዝሙር 104)
3. *El Shaddai* (ዝኪ. 1:8), ብርቱና ርኅሩኅ አምላክ፣ እሱም ለመለኮት የአባቶች ስም የነበረ (ዘጸ. 6:3)

ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች 1:8 ላይ ተመልከት።

▣
***አአመመቅ*** **"ያለህና የነበርከ"**
***አኪጀት*** **"ያለው የነበረው የሚመጣውም"**
***አየተመት*** **"ያለና የነበረ"**
***አእት*** **"ያለና የነበረ"**
***አኢመቅ*** **"ያለ፣ የነበረ"**

ይህ የተለመደው የእግዚአብሔር ገለጻ የወደፊት ገጽታ (ከአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የግሪክ አናሳ ቅጥልጣይ ጽሑፎች በቀር) ተትቷል፣ እግዚአብሔር መንገሥ በመጀመሩ ምክንያት። የእነዚህ ቅደም ተከተላዊ ገጽታዎች፣ ከሦስቱ የመጨረሻው በራዕይ መጽሐፍ ፈጽሞ በድጋሚ አልተጠቀሱም። መንግሥቱ መጥቷል (ዝኪ. 11:15-16)! ይህም ለማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ ትይዩአዊ ግንኙነት ማጠቃለያ ንድፈ-ሐሳብ ማስረጃ ይሰጣል!

▣
***አአመመቅ*** **"ትልቁን ኃይልህን ስለያዝክ ስለነገሥህም"**
***አኪጀት*** **"ትልቁን ኃይልህን ስለያዝክ ስለነገሥህም"**
***አየተመት*** **"ትልቁን ኃይልህን ስለያዝክ እና ስለነገሥህ"**
***አእት*** **"ትልቁን ኃይልህን ስለያዝክ እና ስለገዛህ"**
***አኢመቅ*** **"ትልቁን ኃይልህን ስለያዝክ እና ስለነገሥህ"**

ይህ የተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች ነው፣ የድርጊት የአሁን አመላካች የተከተለው። ኃይሉ ሁልጊዜም የእርሱ ነው፣ ግን ንግሥናው አሁን ይጀምራል (የመግቢያ ድርጊት)።

**11:18 *"አሕዛብም ተቆጡ"*** ይህ ጠቃሽ ነው የመዝ. 2; 46:6; እና ሕዝቅኤል 38-39 (በሴፕቱዋጂንት የአስቴር አፖካሎፕቲካዊ መግቢያ ሊሆን ይችላል)። ይህ የአሕዛብ ቁጣ በሁለት መንገዶች ሊታይ ይችላል።

1. የወደቀው የዓለም ሥርዓት እግዚአብሔርን እና ዕቅዱን እና አገዛዙን እና ሕዝቡን ይጠላል
2. በእግዚአብሔር ላይ የፍጻሜ ዘመን ዐመጻ ይኖራል፣ በውጊያ የሚገለጥ (አርማጌዶን፣ ራዕይ 20)

▣ ***"ቁጣህም መጣ"*** ይህ የመዝ. 2 ወይም 110:5-6 ጠቃሽ ይሆናል። ይህ የግሪክ ቃል *orgē* ነው። ሙሉውን ማስታወሻ 7:14 ላይ ተመልከት።

▣ ***"ጊዜው መጣ"*** የጌታ ቀን ለአንዳንዶች የፍርድ ቀን ሲሆን ለሌሎች ደግሞ የሽልማት ነው። ይህ መንታ ገጽታ ማቴ. 25:31-46 እና ራዕ. 20:11-15 ላይ ይታያል። ሰዎች ሁሉ (ትንሾችም ትልቆችም) በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ፣ ስለ ሕይወታቸውም ምላሽ ይሰጣሉ (ገላ. 6:7; II ቆሮ. 5:10)።

### ልዩ ርዕስ፡ ያ ቀን

ይህ ሐረግ፣ "በዛ ቀን" ወይም "በዚያ ቀን፣" ለስምንተኛው ክፍለ ዘመን ነቢያት የእግዚአብሔርን ጉብኝት (መገኘት) የመናገሪያመንገድ ነው፣ ለፍርድም ሆነ ለመመለስ።

| **ሆሴዕ** | | **አሞጽ** | | **ሚክያስ** | |
|---|---|---|---|---|---|
| አዎንታዊ | አሉታዊ | አዎንታዊ | አሉታዊ | አዎንታዊ | አሉታዊ |
| 1:11 | 1:5 | | 1:14(2) | | 2:4 |
| | 2:3 | | 2:16 | | 3:6 |
| 2:15 | | | 3:14 | 4:6 | |
| 2:16 | | | 5:18(2) | | 5:10 |
| 2:21 | | | 5:20 | | 7:4 |
| | 5:9 | | 6:3 | 7:11(2) | |
| | 7:5 | | 8:3 | 7:12 | |
| | 9:5 | | 8:9(2) | | |
| | 10:14 | | 8:10 | | |
| | | 9:11 | 8:13 | | |

ይህ ፈርጅ የነቢያት ዓይነተኛ ነው። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ በጊዜው ርምጃ ሊወስድ ነው፣ ነገር ግን ለንስሐና ለይቅርታ ቀን ሰጥቷል፣ ልባቸውንና ድርጊታቸውን ለሚቀይሩ ለእነርሱ! የእግዚአብሔር የመዋጀትና የመመለስ ዕቅዱ ይፈጸማል! የእሱን ባሕርይ የሚያንጸባርቁ ሰዎች ይኖሩታል። የፍጥረት ዓላማ (እግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የሚሆን ኅብረት) ይፈጸማል!

▣ ***"በሙታንም ላይ ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ"*** የፍጻሜው ዘመን የእግዚአብሔር ፍርድ ማቴዎስ 25 እና ራዕይ 20 ላይ ተብራርቷል። ይህ ሐረግ የሚያጸናው የራዕይን ትርጓሜ በሰባት ገቢሮች (ትዕይንቶች) ነው፣ የፍጻሜ ዘመኑ የሚከሰተው በእያንዳንዱ ምድብ የሆነበት (በተለይም በማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ እና ጽዋዎቹ ላይ ግልጽ የሆነ)።

▣ ***"ለባሪያዎችህም ለነቢያት"*** ይኸው ሐረግ 10፡7 ላይ ይከሰታል። ዮሐንስ ራሱን የሚገልጸው እንደ ነቢይ ነው፣ መጽሐፉንም እንደ ትንቢት፣ ስለዚህ፣ ይህ ቃል ዘወትር በራዕይ መጽሐፍ ጥቅም ላይ ይውላል። ማለት የሚቻለው ይህ ቃል "ሐዋርያ" የሚለውን መጠሪያ መተካቱን ነው (ዝኪ. 10:7; 11:10,18; 16:6; 18:20,24; 22:6,9)። ልዩ ርዕስ፡ የአኪ ትንቢት 16፡6 ላይ ተመልከት።

▣ ***"ቅዱሳን"*** "ቅዱሳን" የሚለው ቃል አማኞች በክርስቶስ የሚኖራቸውን አቋም የሚያመለክት እንጂ፣ ኃጢአት የለሽነታቸውን አይደለም። እሱም ደግሞ ቀጣይነት ያለውን ክርስቶስን መምሰላቸውን መግለጽ ይኖርበታል። ቃሉ ዘወትር የብዙ ነው፣ ፊሊ. 4፡21 ላይ ካልሆነ በቀር። ሆኖም፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እንኳ የተጠቃለለ ነው። ክርስቲያን መሆን የማኅበረሰቡ፣ የቤተሰቡ፣ የአካሉ አባል መሆን ነው። ልዩ ርዕስ፡ ቅዱሳን 5፡8 ላይ ተመልከት። ይህ መጠሪያ በርግጥ የሚወክለው የአኪ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው፣ ቤተ ክርስቲያንን።

▣ ***"ለታናናሾችና ለታላላቆችም"*** ይህ የሚመስለው በዚህ ቁጥር ሁለት ወገኖች ብቻ መጠቀሳቸውን ነው፣ ነቢያትና ቅዱሳን። "ትንንሾችና ትልልቆች" የሚለው ይህ ሐረግ ቁ. 19፡5 ላይ ይገኛል። እሱም በዮሐንስ ወንጌል የተወደደ አገላለጽ ነበር (ዝኪ. 13:16; 19:5,18; 20:12; 19:5 የመዝ. 115፡13 ጠቃሽ የሆነ፣ ይኸውም ያሉትን ወገኖች ሁሉ የሚያካትት)።

▣ ***"ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ"*** ይህ የወደቀው ሰው ባሕርይ ዘፍጥረት 3 እና ሮሜ. 8፡18-22ን ያመለክታል። ክፉ ሰዎች በስግብግብነት እና በግለኝነት በመጠቀም፣ አዛብተው በመጠቀም፣ አላግባብ የእግዚአብሔርን ሥጋዊ ፍጥረት ይጠቀማሉ።

ይሄም ሊተረጎም የሚችለው፣ ክፉው የሰው ልጅ፣ እሱም እግዚአብሔር በምድር ላይ ፍርድ እንዲያመጣ እንደሚያስገድደው ነው (የጥፋት ውኃ፣ ዘፍጥረት 6-9፤ የግብፅ መቅሠፍቶች፣ ዘጸዓት 7-12፤ የኪዳን ርግማኖች፣ ዘዳግም 27-28፤ ወይም በእሳት የምትጠፋው ምድር፣ 2 ጴጥ. 3፡10)። ራዕይ ላይ፣ ማኅተሞቹ ¼፣ መለከቶቹ 1/3፣ እና ጽዋዎቹ አጠቃላይ ጥፋት በምድር ላይ ያደርሳሉ።

### *ራዕይ፡* 11፡19

**19በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።**

**11:19 “በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ”** ይህ ራዕይ የሚጀምረው በሰማይ በተከፈተ በር መሆኑን አስታውስ (ዝከ. 4:1፤ 15:5)። እንግዲህ፣ የእግዚአብሔር ሰማያዊ መቅደስ ውስጠኛው ክፍል ሊታይ ይችላል (ዕብ. 8:5; 9:23-28)።

ኢየሱስ ሲሞት የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች መቀደዱ የሚያመለክተው አሁን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ለሁሉም መቻሉን ነው፣ በክርስቶስ በኩል (ማቴ. 27:51; ማርቆስ 15:38; ሉቃስ 23:45; ከ ዕብ. 9:8; 10:20 ጠቃሽ ሆነዋል)። ይኸው ተመሳሳይ ተምሳሌት እዚህ ተደግሟል። እግዚአብሔር ለሁሉም ይገኛል። የሰማይ ውስጣዊ መቅደስ አሁን ሙሉ ለሙሉ ተከፍቶ ይታያል።

▣ **“የኪዳኑም ታቦት”** የኪዳኑ ታቦት በሆነ ጊዜ በባቢሎን ምርኮ ወቅት ጠፍቷል (ወይም ወደ ግብፅ ፈርዖን ሺሻክ፣ 1 ነገሥ. 14:25)። እሱም ተምሳሌት የሚሆነው ለእግዚአብሔር መገኘት ነው፣ እስራኤል የዮርዳኖስን ወንዝ ከተሻገሩ በኋላ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር። እሱም ደግሞ ተምሳሌት የሚያደርገው የእግዚአብሔርን የኪዳን ቃሎች ነው፣ እሱም ምሥጢርን የሚያመለክት (ዝከ. 10:7)፣ የእግዚአብሔር የመቤዠት ዓላማ ለሰው ልጆች ሁሉ (ሮሜ. 16:25-26)። በብሊ ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበር ይሄንን ቅዱስ ዕቃ የሚቀርበው፣ በዓመት አንድ ጊዜ በመቀደስ ቀን (ሌዋውያን 16)። እንግዲህ፣ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መገኘት መምጣት ይችላሉ።

▣ **“መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ”** ይህ ከ8:5 እና 16:18-21, እሱም ዘጸ. 9:24 and 19:16-19ን የሚያንጸባርቅ።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የዚህ የቆይታ ጊዜ ዓላማው ምንድነው?
2. እጅግ ብዙ ተርጓሚዎች ምዕራፍ 10 ላይ ያለውን መልአክ ለምን እንደ ክርስቶስ ለመውሰድ ሞከሩ?
3. ቁ. 10:7 ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ምሥጢር ምንድነው?
4. ዮሐንስ እንዲበላ የታዘዘው ትንሽ መጽሐፍ ምንድነው?
5. ሁለቱ ምስክሮች እነማን ናቸው? መልእክታቸው ምንድን ነበር?
6. 11:9 የኢየሩሳሌምን ከተማ ነው የሚገልጸው ወይስ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም መንግሥታት? ለምን?
7. በዚህ የቆይታ ጊዜ ላይ ያሉትን የብሉይ ኪዳን ጠቃሾች ዘርዝር?

# ራዕይ 12-14
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ[4] | አኪጆት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሴቲቱና ዘንዶው | ሴቲቱ፣ ሕፃኑ፣ እና ዘንዶው | የሴቲቱ፣ የሕፃኑ፣ እና የዘንዶው መገለጥ፣ | ሴቲቱ እና ዘንዶው | የሴቲቱ እና የዘንዶው መገለጥ |
| 12:1-6 | 12:1-6 | 12:1-6 | 12:1-2 | 12:1-6 |
| 12:3-6 | ሰይጣን ከሰማይ ተጣለ | | | |
| 12:7-12 | 12:7-12 | 12:7-9 | 12:7-9 | 12:7-12 |
| | ሴቲቱ ተሳደደች | 12:10-12 | 12:10-12 | |
| 12:13-17 | 12:13-17 | 12:13-17 | 12:13-18 | 12:13-17 |
| ሁለቱ አውሬዎች | የባሕሩ አውሬዎች | ሁለቱ አውሬዎች | ሁለቱ አውሬዎች | ዘንዶው ኃይሉን ለአውሬው ሰጠ |
| 12:18 | 12:18 | 12:18 | | 12:18-13:10 |
| 13:1-4 | 13:1-10 | 13:1-4 | 13:1-4 | |
| 13:5-8 | | 13:5-8 | 13:5-8 | |
| 13:9-10 | የምድሩ አውሬ | 13:9-10 | 13:9-10 | ሐሰተኛው ነቢይ እንደ አውሬው ባርያ |
| 13:11-18 | 13:11-18 | 13:11-18 | 13:11-17 | 13:11-17 |
| | | | 13:18 | 13:18 |
| የ144000 መዝሙር | በጉ እና 144000 | ጣልቃ የገባ | በጉና ሕዝቦቹ | የበጉ ባልንጀሮች |
| 14:1-5 | 14:1-5 | 14:1-5 | 14:1-5 | 14:1-5 |
| የሦስቱ መላእክት መልእክቶች | የሦስቱ መላእክት አዋጅ | | ሦስቱ መላእክት | መላእክት የፍርድ ቀንን አወጁ |
| 14:6-7 | | | | 14:6-7 |
| 14:8 | 14:6-13 | 14:6-7 | 14:6-7 | 14:8 |
| 14:9-12 | | 14:8 | 14:8 | 14:9-13 |
| | | 14:9-11 | 14:9-11 | |
| 14:13 | | 14:12 | 14:12 | |
| | | 14:13 | 14:13 | |
| የምድር መኸር | | | 14:13ለ | መኸሩ እና የአሕዛብ መኸር |
| | የምድርን መኸር መሰብሰብ | | የምድር መኸር | 14:14-16 |
| 14:14-16 | 14:14-16 | | | |
| | የቁጣውን ወይን መሰብሰብ | 14:14-16 | 14:14-16 | 14:17-20 |
| 14:17-20 | 14:17-20 | | | |
| | | 14:17-20 | 14:17 | |
| | | | 14:18-20 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው:: ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ viii):: ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ:: ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል:: እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል::

5. የመጀመሪያው አንቀጽ
6. ሁለተኛው አንቀጽ
7. ሦስተኛው አንቀጽ
8. ወዘተርፈ

**ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት**

ሀ. ሌለኛው የቆይታ ጊዜ የሚጀምረው 12፡1 ላይ ሲሆን እስከ 14፡20 ይቀጥላል። ብዙዎች የሚያስረግጡት ይህ በርግጥ ሌለኛው ተለጣጣቂ ሁነት ነው። ይህ ጽሑፋዊ ምድብ መንፈሳዊውን ውጊያ በመንታ ቃላት ይገልጻል
1. ሁለቱ መንግሥታት
2. ሁለቱ ከተሞች
3. ሁለቱ የታረዱት ምስክሮች እና የእነርሱ ገዳዮች

ለ. ቁጥር 1-6 የሚገልጸው አጠቃላዩን (ሰማያዊውን) በመልካምና በክፉ መካከል የሚካሄደውን ጦርነት ነው፣ በአፈ-ታሪካዊ ቃላት፣ ከጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ባህሎች የተወሰደ (ግራንት ኦስቦርን፣ *የሥነ-ትርጓሜ ሽክርክሪት* ገጽ 229)።
1. የባቢሎናውያን ሐተታ-ፍጥረት — ቲያማት (ቀውስ)፣ ባለ ሰባት ራስ አውሬ፣ እሱም የሰማይ ከዋክብትን ሢሶ የጣለ፣ በተቃርኖ ማርዱክ፣ የባቢሎን ከተማ አለቃ ጣዖት፣ እሱም እሷን ገድሎ የጣዖቱ ራስ የሆነ።
2. የግብፅ አፈ-ታሪክ — ሴት (ታይፎን)፣ ቀይ ዘንዶ በተቃርኖ አይሲስ (ሀዘር)፣ ሆርሩስን የምትወልድ። ኋላም ሴትን ይገድላል።
3. የዩጋሪቲክ በአል አፈ-ታሪክ — ያም (ውኃዎች) በተቃርኖ በአል። በአልም ያምን ይገድላል።
4. የፋርስ አፈ-ታሪክ — አዝሂ ዳባካ (ክፉ ዘንዶ) በተቃርኖ የአሁራ ማዝዳ ልጅ (ከፍተኛው መልካም ጣዖት)።
5. የግሪክ አፈ-ታሪክ — ፓይቶን (እባብ/ዘንዶ) በተቃርኖ ርጉዟ ሌቶ (አፖሎን ትወልዳለች፣ እሱም ፓይቶንን ይገድላል)።

ሐ. ይሄንን ምዕራፍ እንዴት መተርጎም እንደሚቻል ይቸግራል። አንዳንዶች ከታሪክ አኳያ ሊተረጉሙት ሞክረዋል፣ ለእኔ የሚመስለኝ ግን በዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ መንግሥታት እና በአዲሱ የክርስቶሳችን መንግሥት መካከል የሚደረገው ትግል ተምሳሌት ነው (ዝከ. 11፡18፤ መዝሙር 2)። ስለዚህ፣ ይህ ሁለቱንም፣ ለክርስቶስ መወለድ እና ለሚመጣው ለመሲሑ መንግሥት አጽንዖት የሚሰጥ ታሪካዊ ጠቃሽ ነው። ይህም የአንድ ግለሰብ ምንታዌነት ነው (መሲሕ) እና የቡድን (የእግዚአብሔር ሕዝብ) በተቃርኖ የአንድ ግለሰብ (ሰይጣን) እና የቡድን (ኢጋንንታዊ ተመስጦ ያላቸው ኢ-አማኒዎች)። ይኸው ተመሳሳይ ምንታዌነት በኢሳይያ የአገልጋይ መዝሙር ውስጥ ይገኛል። አገልጋዩ እስራኤል ነው (ኢሳ. 41-50), መሲሑም (ኢሳ. 52፡13-53፡12)።

መ. ጳውሎስ የክርስቶስን ሰማያዊ አመራር ተሰሎንቄ 1-2 ላይ አብራርቶታል (ዕብ. 1፡2-3 ተገንዘብ)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ራዕይ፡ 12፡1-6**

**1 ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች። 2 እርስዋም ፀንሳ ነበር፥ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጭንቃ ጮኸች። 3 ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥ 4 ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው። ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ። 5 አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ። 6 ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።**

**12፡1 "*ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ*"** ይህ ምናልባት የራዕይ "የሰባቱ ምልክቶች" መጀመሪያ ይሆናል። ይህ ልዩ ሥነ-መለኮታዊ ቃል ነው (*sēmeion*) በዮሐንስ ወንጌል ላይ ተዘውትሮ ጥቅም ላይ የዋለ (ዝከ. 2፡11,23; 3:2; 4:54; 6:2,14,30; 7:31; 9:16; 10:41; 11:47; 12:18,37; 20:30)። እሱም አሁን ሰባት ጊዜ ተከስቷል በ12፡1 እና 19:20 መካከል— ሦስት ጊዜ በሰማይ ምልክት (ዝከ. 12፡1,3; 15፡1) እና አራት ጊዜ እንደ ምድር ምልክት (ዝከ. 13፡13,14; 16፡14; 19:20)።

▣ **"በሰማይ"** ይህ ምናልባት የሚለው "በሰማይ" ነው፣ በመንግሥተ ሰማይ በራሱ ሳይሆን። ሰማይ(ያት) የሚለው ቃል በብኪ ሊያመለክት የሚችለው ከምድር በላይ ያለውን ከባቢ ዓየር ነው (ዘፍ. 1፡1,8-9,17,20; መዝ. 104፡2-3) ወይም እግዚአብሔር የሚኖርበት ስፍራ (መዝ. 11፡4; 103፡19; ኢሳ. 66፡1; 2 ቆሮንቶስ 12)። ይህ አሻሚነት ነው ራቢዎች የሰማያትን ቁጥር እንዲገምቱ ያደረጋቸው— ሦስት ወይም ሰባት።

ልዩ ርዕስ፡ ሰማያት 4፡1 ላይ ተመልከት።

◘ **"የተጎናጸፈች ሴት"** ይህች ሴት በተዋበ መልኩ ተገልጸለች፣ 17፡4 ላይ ካለችው ከታላቋ ጋለሞታ ፍጹም ተጻራሪ በሆነ መልኩ፣ እሷም የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ተምሳሌት የሆነች፣ የዓለም መንግሥት እንደ ባቢሎን፣ ሮም፣ እና የፍጻሜ ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓት። ለዮሐንስ ምስያ ምንጭ ሁለት ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡

1. ዘፍጥረት 3፣ ሴት፣ እባብና ሕፃን ልጅ ያሉበት
2. ሌላ ጠንከር ያለ ጠቃሽ "በወሊድ" ላይ ያለበት፣ በብኪ (ኢሳ. 26፡17-18 በሴፕቱዋጂንት እና ኢሳ. 66፡7-13)

እስራኤል፣ ልጅ እንደምትወልድ ሴት ተጠቅሷል (ሚክ. 4፡10)፣ ስለዚህ፣ ይህች ሴት የምትወክለው የእግዚአብሔርን እውነተኛ ሕዝቦች ነው (ዝኪ. ቁ. 1-6)፣ ነገር ግን ቁ. 13-17 ላይ እሷ የአኪ የእግዚአብሔር ሕዝብ ትሆናለች፣ ከዘንዶው ቁጣ የምትሸሸው። ለሌሎች ንድፈ-ሐሳቦች የአለን ጆንሰንን *ራዕይ*፣ ገጽ 117-119 ተመልከት።

በጥያቄና መልስ ላይ ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ እንዳለው፣ "ሴቷን የማስባት እንደ 'እስራኤል አምላክ' መሲሐዊ ማኅበረሰብ ነው፣ በተለይም በአካባቢው የተገለጠች የፍልስጥኤም ቤተ ክርስቲያን፣ የእናት ቤተ-ክርስቲያን አቻ ክብር ያላት፤... 'የእርሷ ዘር ቅሬታ' በሌላው የዓለም ክፍሎች ያሉት ክርስቲያኖች ይሆናሉ፣ 13፡7 ላይ ያለው ጥቃት ዒላማ" (ገጽ 140)።

በአዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ ጆርጅ አር. ቢስሌይ-ሙሬይ እንዳለው፣ "የጥንታዊው ዓለም ሃይማኖታዊ ሰዎች በምጥ ላይ ባለች ሴት ጣዖት፣ አስራ ሁለት የዞዲያክ ኮከቦች አክሊል ደፍታ ተመልክተዋል፤ አይሁድ እሷን የሚገነዘበው እንደ እናት ጽዮን ነው (ኢሳ. 26:16027:1; 49:14-25; 54:1-8; 66:7-9)፣ ለዮሐንስ ግን እሷ የምትወክለው የመሲሐዊው ማኅበረሰብ 'እናት' ነው፣ የሚያምኑ የእግዚአብሔር ሕዝቦች፣ የብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን" (ገጽ 1441)።

◘ **"አስራ ሁለት ከዋክብት"** እዚህም በድጋሚ የእኛ ቅድመ-ግምቶች ትርጓሜውን ያስኬዳሉ።

1. ብኪ ከሆነ እንግዲያውስ አስራ ሁለቱን የአይሁድ ነገዶች ነው የሚያመለክተው
2. በይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ከሆነ የዞዲያክ ምልክቶችን ነው የሚያመለክተው
3. አኪ ከሆነ እንግዲያውስ አስራ ሁለቱን ሐዋርያት ነው የሚያመለክተው

አስራ ሁለት መደበኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የድርጅት ተምሳሌት ቁጥር ነው። ልዩ ርዕስ፡ ቁጥር አስራ ሁለት 7፡4 ላይ ተመልከት።

ሆኖም፣ የምዕራፍ 12 ፍቺ የዮሐንስን ተምሳሌታዊነት በሚገባ በሚለይ ሁኔታ አይደለም፣ ነገር ግን የይዘቱን ማዕከላዊ እውነት እንጂ። ይህ መርሕ መያዝ ይኖርበታል። ማድረግ የማይኖርብን

1. ዝርዝሮቹን መግፋት
2. አንዳንድ ነገሮችን በጥሬው መምረጥ እና አንዳንድ ነገሮችን በተምሳሌታዊነት መምረጥ
3. የእኛን ትርጉም ወደራሳችን ታሪካዊ መቼት መግፋት

**12፡2** የምጥ ጣር በተምሳሌትነት ጥቅም ላይ የዋለው

1. የሚጠበቁ፣ ግን ድንገተኛ የሆኑ ሁነቶች
2. ከሚጠበቅ ሁነት ጋር የተያያዘ ሥቃይ ወይም ችግሮች
3. በትልቅ እምቅ-ኃይል የሚጀምር አዲስ ነገር

አይሁዶች የሚያምኑት "የአዲሱ ዘመን" መምጣት ስደትና ችግሮችን እንደሚያካትት ነው (ኢሳ. 13:8; 21:3; 26:17; 66:7-13; ማቴt. 24:8; ማርቆስ 13:8; 1 ተሰ. 5:3)። ዮሐንስ ይህን ጽንሰ-ሐሳብ የተጠቀመው በሰይጣንና በተከታዮቹ እና በእግዚአብሔርና በተከታዮቹ መካከል የሚኖረውን ግጭት ለመግለጽ ነው (ኢሳ. 66፡7-24)።

የዓለም ሁነቶች እየባሱ እየከፉ በመሄድ ላይ ናቸው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ታሪክን ይቆጣጠራል (ይህ የቅድመ-ሚሊኒየማዊ እና የሚሊኒየማዊነት አተያይ ሲሆን፣ ድኅረ-ሚሊኒየማዊነት እጅግ ተስፈኛ ነው ስለ ዓለም ታሪክ)። የእርሱ ተከታዮች በመከራ መሐል ይጠበቃሉ፣ እንዲሁም በጊዜያዊ ሽንፈት መካከል ባለ ድል ናቸው፣ ሥጋዊ ሞት እንኳ ቢሆን (ዮሐንስ 16፡20-21)። ጥያቄው፣ "እግዚአብሔር እንዴት ተከታዮቹን ይጠብቃል?" ነው። በግንባራቸው ላይ ያለው የእሱ ማኅተም "ከእግዚአብሔር ቁጣ" ይጠብቃቸዋል፣ ነገር ግን ከማያምኑ ከሚሆነው ስደት (መከራ) ሳይሆን። እግዚአብሔር ለእነርሱ፣ ከእነርሱ ነው፣ ይወዳቸዋልም፣ ግን ብዙዎች ይሞታሉ!

**12፡3 "እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ"** ይህ የክፉውና የታላቅ ኃይል መግለጫ ነው (ዝኪ. 13፡1 እና 17፡3)። ቀንዶቹና ራሶቹ ተምሳሌትነታቸው ፍጹም ኃይልን ሲሆን (ዳንኤል 7) እንዲሁም ዘውዶቹ የሚወክሉት፣ ክፉው የክርስቶስን የንግሥና ስፍራ ለመንጠቅ የሚያደርገውን ሙከራ።

"ዘንዶ" የሚለው ቃል ወደ ብኪ ተመልሶ ይሄዳል

1. የዘፍጥረት 3 እባብ
2. ሁለቱ የቀውስ ክፉ አውሬዎች
   ሀ. ራሀብ (መዝ. 89:10; ኢሳ. 51:9-10; ኢዮብ 26:12-13)
   ለ. ሌዋታን (መዝ. 74:13-14; 104:26; ኢዮብ 3:8; 7:12; 41:1; ኢሳ. 27:1; አሞጽ 9:3)

በርካታ መጠሪያዎች ለክፉው በአኪ ይገኛሉ

1. "ሰይጣን፣" 33 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
2. "ዲያብሎስ፣" 32 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
3. "ፈታኝ፣" (ማቴ. 4:3; 1 ተሰ. 3:5)
4. "ክፉው፣" (ማቴ. 6:13; 13:19; 1 ዮሐንስ 5:18)
5. "ጠላት፣" (ማቴ. 13:39)

6. “የጋንንት አለቃ፣” (ማቴ. 9:34; 12:24)
7. “የዚህ ዓለም ገዥ፣” (ዮሐንስ 12:31; 14:30; 16:11)
8. “በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ፣” (ኤፌ. 2:2)
9. “የዚህ ዓለም አምላክ፣” (II ቆሮ. 4:4)
10. “ቤልሆር፣” (II ቆሮ. 6:15)
11. “ብዔል ዜቡል፣” (ማርቆስ 3:22; ሉቃስ 11:15,18-19)
12. “ዘንዶው፣” (ራዕ. 12:3,4,7,9; 20:2)
13. “እባብ፣” (ራዕ. 12:9,15; 20:2)
14. “ከሳሽ፣” (ራዕ. 12:10,15)
15. “ባለጋራ፣” (1ጴጥ. 5:8)
16. “የሚያገሳ አንበሳ፣” (1ጴጥ. 5:8)

## ልዩ ርዕስ፡ ሰይጣን

በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ርዕስ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

1. ብሉይ ኪዳን ለደግነት ታላቅ ጠላት ብሎ አያስቀምጥም ነገር ግን የያህዊ አገልጋይና ለሰው ልጆች አማራጭ በመስጠት በፅድቅ ባለመሆኑ የሚከስ መሆኑን ነው፡፡
2. የክፋት ዋና ሃሳብ እየተስፋፋ የመጣው ኪዳን ባስነበረበት ዘመን ሥን ፅሁፍ ነበር፤ ይህም ሊስፋፋ የቻለው በፈሪሳዊያን ኃይማኖት (ዘራሽ ትራኒያንዝም) አማካኝነት ነበር፡፡ ይህም በተራው የረቢዎችን ኃይማኖት በከፍተኛ ሁኔታ ተፅዕኖ አሳድሮበታል፡፡
3. አዲስ ዲን የብሉይ ኪዳን ዋና ሐሳባችን የሚያስፋፋው በሙሉ በሙሉ ባይሆንም የተወሰኑትን መርጦ ነው፡፡

አንድ ሰው ከመፅሐፈ ቅዱስ አንፃር ክፋትን ለማጥናት ቢፈልግ፣ ስለክፋት የተለያዩ አመለካከቶኛ ወይም እሳቤዎተን ያገኛል፡

ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከመፅሐፍ ቅዱስ ውጪ ወይም ተጨማሪ ከሚመለከቱት ከዓለም ወይም ከምስራቅ ኃይማኖቶች አንፃር ክፋትን የሚመረምር ከሆነ አብዛኛው የአዲስ ዲን ትምህርት በፋሪሳዊያን እና በግሪኩ ሮማን የመናፍስት አምልኮ ይሸፈናል ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው በቅድሚያ ለመፅሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ስልጣን የሚገዛ ከሆነ የአዲስ ኪዳን መስፋፋት ሊታይ የሚገባው እንደ ቀጣይ መገለጥ ነው፡፡ ክርስትያኖች መፅሐፍ ቅዱሳዊውን ሐሳብ ለመለፅ ከአይሁድ ተረትና ምሳሌ መጠበቅ አለባቸው (ዳንቲ፣ ሚስተን)፡፡ በዚህ መረዳት ላይ ግራ መጋባትና ሚስጢራዊነት እንዳለ የማታመን ነው፡፡ እግዚአብሔር የመረጠው ሁሉንም የክፋት አቅጣጫዎች ለመግለጥ ብቻ አይደለም ነገር ግን የክፋትንም መሸነፍ ጥምር እንጂ፡-

በብሉይ ኪዳን አጠራር ሰይጣን ወይም ከሳሽ ከሶስት የተለያዩ ቡድኖች ጋር ይዛመዳል

1. የሰው ከሳሾች (1ሳሙ 29፡4፣ 2ሳሙ 19፡22፣ 1ነገ 11፡14-23-25፣ መዝ 109፡6)
2. የመላዕክት ከሳሾች (ዘሑል 22፡23፣ ዘካ 3፡1)
3. የክፊ መናፍስት ከሳሾች (ዜና 21፡1 22፡21 ዘካ 13፡2)

በዘፍ 3 ላይ የተጠቀሰው እባብ ሰይጣን መሆኑ የታወቀው በኃይለኛው የዝምታ ግዜ ነበር (የጥበብ መፅሐፍ 2፡23-24፣ 2ሔኖክ 31፡3) ከኋላም ቢሆን ይህ ሁኔታ በረቢዎች እንደአማራጭም አልታየም ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች (ዘፍ 6) በሔኖክ 54፡6 ላይ መላእክት ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡ ይህን የምገልፅው ሥን መለኮታዊ ትክክለኛነቱን ለመንገር ሳይሆን ዕድገቱን ለማሳየት ነው፡፡

በአዲስ ኪዳን እነዚህ የብሉይ ኪዳን እንቅስቃሴዎች ስብዕና ካለው መልዕክት ጋር ይዛመዳል (ሰይጣን) ፡- 2ቆሮ 11፡3፣ ራዕይ 12፡9

ስብዕና ያለውን ክፋት በብሉይ ኪዳን ለመወሰን አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ጉዳይ ነው (በአንተ እይታ በመመርኮዝ) ለዚህም አንድ ምክንያት የእስራኤል የአንድ አምላክ አምልኮ ነው፡፡ (1ነገ 22፡20-22፣ መክ 7፡14 ኢሳ 45፡7 አሞ 3፡6) ሁሉም መልካም ያልሆነ ነገር ከያህዊህ ጋር የተገናኘ ነበር፤ ልዩ እና ቀዳሚ መሆኑን ለማመልከት (ኡሳ 43፡11፣ 44፡6፣ 8፡24፣ 45፡56፣ 14፡18፣21፡22) የመረጃ ምንጨች እንደሚያመለክቱት (1) ኢዮብ 1-2 ሰይጣን ከእግዚአብሔር ልጆች አንዱ እንደሆነ (2) ኢሳ 24፣ ሕዝ 28 ትዕቢት የተሞሉትን የቅርብ ምስራቅ ነገስታት (ባቢሎን ጢሮስን) የሰይጣንን ትዕቢት ለማሳየት መጠቀሙ (1ጢሞ 3፡ 6)፡፡ ሕዝቅኤል የኤደን ገነትን የጢሮስን ንጉስ በሰይጣን ተምሳሌትነት ብቻ አልተጠቀመም (ሕዝ 28፡12-16) ነገር ግን የግብፅንም ንጉስ መልካሙንና ክፋውን እንደምታስታውቀው የእውቀት ዛፍ መስሏታል (ሕዝ 31) ይሁን እንጂ ኢሳ 14 በተለይም ቁ. 12-24 በትዕቢት ምክንያት የተነሳ የመላህክት አመፅን ለመግለፅ ይመስላል፡፡ እግዚአብሔር እያንዳንዱን የሳይጣን ባህሪ መግለፅ ቢፈልግ ኖሮ ይህ እንግዲህ በስራ ላይ ለማዋል በጣም ገዳዳ የሆነ አመለካከት ነው፡፡

አልፍሬድ ኢድርሻይም (The Life and Times of Jesus the Messiah፣ Vo. 2፤ ማውጫ 13 (ገፅ 748-763) እና ማውጫ 16 (ገፅ 770-776) እንደሚናገሩት የረቢዎች የአይሁድ ኃይማኖት በፋሪሳውያን የጣምራ ፍልስፍና እና ኢጋንታዊ ግምቶች በብዙ ተፅዕኖ እንደደረሰበት ነው፡፡ ረቢዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ጥሩ የመረጃ ምንጮች ሊሆኑ አይችሉም፡፡

ኢየሱስ በምኩራብ ከሚሰጠው ትምህርት ለየት ይላል፡፡

ሁለቱ የኢራናዊያን አማልዕክት (ዱዋሊዝም) Aukiman እና Ormaza መልካም እና ክፊ በተጨማሪም የረቢዎች ሐሳብ ተደምሮ ያቅዊና ሰይጣን የሚሉትን አመጣ የክፋትን ዕድገት በሚመለከት በአዲስ ኪዳን ቀጣይነት ያለው መገለጥ አለ ነገር ግን

ረቢዎች እንደሚያብራሩት አይደለም፡፡ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው "በሰማያት ላይ ያለው ጦርነት" የሚለው ነው የሰይጣን ውድቀት አስፈላጊ ነው ነገር ግን ዝርዝሮች አልተሰጡም፡፡ የተጠቀሰው እንኳን በታዩ ራዕዮች ምክንያት የተሸፈነ ይመስላል፡፡ (ራዕ 12፡4፡7፣ 12-13) ምንም እንኳን ሰይጣን የተሸነፈና የተጣለ ቢሆንም አሁንም የእግዚአብሔር ባሪያ ሆኖ ይሰራል (ማቴ 4፡1፣ ሉቃ 22፡31-32፣ 1ቆሮ 5፡5 1ጢሞ 1፡20)፡፡

በዚህ አቅጣጫ ላይ ያለንን መደነቅ ልንገታው ይገባል፡፡ በግላችን የሚገጥመን ክፋትና ፈተና አለ ነገር ግን ያለን አንድ አምላክ በቻ ስለሆነ የሰው ልጅ ለሚወስደው ማናቸውም ምርጫ ኃላፊነት አለበት፡፡ ከደህንነት በፊትም ሆነ በኋላ መንፈሳዊ ውግያ አለ፡፡ ድል ሊመጣና ሊጠበቅ የሚችለው በእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ክፋት ተሸንፏል ደግሞም ወደፊትም ይወገዳሉ፡፡

**12፡4 "ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው።"** "የሰማይ ከዋክብት" የሚለው ቃል ተዘውትሮ በብኪ ጥቅም ላይ የሚውለው የእግዚአብሔርን ቅዱሳን ለመጥቀስ ከመሆኑ የተነሣ (ዘፍ. 15:5; ኤር. 33:22; ዳን. 12:3), አንዳንዶች የሚገምቱት ይህ የሚጠቅሰው ቅዱሳንን ነው፣ ዐውደ-ጽሑፉ ግን መላእክትን ነው የሚያመለክተው (ዳን. 8:10; II ጴጥt. 2:4; ይሁዳ ቁ. 6)። የወደቁ መላእክት (ማለትም፣ የወደቁ ከዋክብት) የተለመደ ሐሳብ ነው፣ በአፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ (ማለትም፣ 1 ሔኖክ)።

ሰይጣን ከሰማይ መላእክት ጋር በእግዚአብሔር ፊት ይገኛል፣ ኢዮብ 1-2 እና ዘካርያስ 3። እሱ "የሚጋርድ ኪሩብ" ነበር (ሕዝ. 28:12-18)። ይህ ገለጻ፣ ከዔድን ገነት የሆነ ዘይቤ፣ ከጢሮስ ንጉሥ ጋር አይገጥምም፣ ነገር ግን የንጉሡ ኩራትና ትዕቢት ከሰይጣን የተኮረዥ ነው (እኔ ይህ አገባብ እጅግም አይመቸኝ፣ ምክንያቱም ሕዝቅኤል 31 ላይ የግብፅ ንጉሥ እንደ መልካሙንና ከፉውን እንደምትለየው ዛፍ ዓይነት ስለተገለጸ። ሕዝቅኤል በመደበኛነት የዔድንን ቃል የሚጠቀመው ነገሥታትን ለመግለጽ ነው)። በብኪ የእግዚአብሔር ጠላት አይደለም፣ የሰው ልጅ እንጂ (ዝከ. 12:10)። ሰይጣን ክፉ ሆኖ አልተፈጠረም ነገር ግን የሁሉም መልካምና ቅዱስ ነገሮች ዋነኛ ጠላት በመሆን እየጎለበተ መጣ (ኤ. ቢ. ዴቪድሰን *የብሉይ ኪዳን ሥነ-መለኮት*፣ ገጽ 300-306)። በርካታ ጊዜ ከሰማይ ስለ መጣሉ ተብሏል (ኢሳ. 14:12; ሕዝ. 28:16; ሉቃስ 10:18; ዮሐንስ 12:31; እና ራዕ. 12:9,12)። ችግሩ መቼ ነው። እሱ፡

1. በብኪ ጊዜ
   ሀ. ከሰው ፍጥረት በፊት
   ለ. ከኢዮብ በኋላ፣ በሆነ ጊዜ፣ ግን ከሕዝቅኤል 28 በፊት
   ሐ. በድኅረ-ግዞት ጊዜ፣ ግን ከዘካርያስ በኋላ
2. በአኪ ጊዜ
   ሀ. ከኢየሱስ ፈተና በኋላ (ማቴዎስ 4)
   ለ. በሰባው ሚሲዮናዊ ጉዞ ጊዜ (ሉቃስ 10:18)
   ሐ. በዐመጻው የመጨረሻ ጊዜ ላይ (ራዕ. 12፡9)። ልዩ ርዕስ 12፡7 ላይ ተመልከት።

አንዱ ሊደነቅ ይችላል የከዋክብት ሢሶ የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ላይ ያመጹትን መላእክት የሚጠቅስ በመሆኑ እና ሰይጣንን ሊከተሉ በፈለጉ። እንደዛ ከሆነ፣ ይህ ብቸኛው ቅዱስ ቃላዊ መሠረት ነው፣ በአኪ ከወደቁ መላእክት ጋር የተያያዘ (ዝከ. 12፡ 9፣12)። ቁጥሩ፣ ሢሶ፣ ምናልባት የሚዛመደው ከጥፋቱ ወሰን ጋር ነው፣ በመለከት ፍርድ ጊዜ (ዝከ. 8:7-12; 9:15,18) እና የተወሰነ ቁጥር አይደለም። ወይም እሱ የሰይጣንን ሽንፈት፣ ከመላእክቱ የተወሰኑትን፣ በውጊያ ላይ። እንዲሁም ደግሞ ሊሆን የሚችለው እሱ እንዲያው የሚያንጸባርቀው የባቢሎንን የጥንት አፈ-ታሪክ ነው። ለ.1 ላይ ያለውን ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት።

በዚህ ነጥብ ላይ ረጂ የሚሆነው ማስታወስ የሚገባው፣ ምንም እንኳ ይህ ጉዳይ አስገራሚ ቢሆንም፣ የደራሲው ዋነኛ ሐሳብ ላይሆን ይችላል፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ለማብራራት (1) የሰይጣናዊነት መነሻ፡ (2) የሰይጣን ውድቀት፤ ወይም (3) በሰማይ የሚሆን መልአካዊ ዐመጻ። በአፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ የራዕዩ ማዕከላዊ ጭብጥ ወሳኝ ነገር ነው፣ ነገር ግን የአቅርቦቱ እማሬያዊነት፣ ዝርዝሮቹ እና ምስሎቹ ድራማዊ ናቸው፣ ተምሳሌታዊ፣ ፈጠራዊ። ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለን ጥንቃቄና ክብር ነው የእኛን ዝርዝር፣ ሎጂካዊ፣ ዶክትሪናዊ ቀመሮች የሚያንቀሳቅሱት። ዝርዝሮችን ከመግፋት ተጠንቀቁ፤ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ዘወትር እውነተኛ ሥነ-መለኮት ነው፣ በምናባዊ ቅንብብ (ፍሬም) የቀረበ። እሱ እውነት ነው፣ ነገር ግን በተምሳሌታዊነት የቀረበ ነው!

◘ **"ሕፃኗን እንዲበላ"** ይህ ሕፃን የሚያመለክተው የተስፋውን መሲሕ ነው (ዝከ. 12፡5)። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ዕቅድ በየትኛውም ደረጃ ላይ ለመገዳደር ይፈልጋል፣ ሁለቱንም፣ ሁለንተናዊውን የመቤዠት ዕቅድ (ሁኔታዊ ያልሆኑ ኪዳናት) እና ግለሰባዊ የመቤዠት ዕቅድን (ሁኔታዊ ኪዳናት) ማቴ. 13:19; II ቆሮ. 4:4)።

**12፡5 "ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች"** ይህ የኢሳ. 66፡7-8 ጠቃሽ ይሆናል። ዮሐንስ እንዴት ከኢየሱስ ሥጋ መልበስ ወደ ወደ ፍጻሜ ግዛቱ እንዴት እንደተንቀሳቀሰ ተገንዘብ። በመካከሉ ያሉት ነገሮች ሁሉ በዮሐንስ ወንጌል ተገልጸዋል፣ በራዕይ ላይ ሳይሆን።

◘ **"አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን"** ይህ የመዝ. 2፡9 ጠቃሽ ሲሆን፣ እና ስለዚህ መሲሐዊ ነው። ራዕ. 19፡15 ላይ ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ለመሲሕ ሲሆን፣ ራዕ. 2፡26-27 ላይ ለቅዱሳን ነው ጥቅም ላይ የዋለው። በመሲሁ (ግለሰብ) እና በአማኙ ማኅበረሰብ (አጠቃላይ) መካከል እዚህጋ መለዋወጥ አለ፣ ኢሳይያስ የአገልጋይ መዝሙር ላይ እንዳለው (ማለትም፣ ብሔራዊው እስራኤል፣ ኢሳ. 42:1-9,19; 49:1-7; 50:4-11; 52:13-53:12)። አሁን ከፉው ሕዝቦችን እንደሚገዛ፣ አዲስ መሪ መጥቶ አንድ ቀን ባጠቃላይ ይገዛል።

◘ **"ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።"** አንዳንዶች ይሄንን የሚመለከቱት እንደ ክርስቶስ ዕርገት ነው፣ ነገር ግን የዚህን ጽሑፋዊ ምድብ ነጥብ እንስተዋለን፣ ለክርስቶስ ታሪካዊ ሕይወት እጅግ ጠንካራ ያደረግነው እንደሆነ። ዮሐንስ፣ በራዕይ መጽሐፍ ላይ የኢየሱስን ምድራዊ ሕይወት ወይም ሞት አልገለጸም። እሱ ከሥነ-መለኮት አኳያ ከሥጋዌነት ወደ መነጠቅ ነው

የተንቀሳቀሰው። የራዕይ ትኩረት የክርስቶስ መክበርና ልዕልና ነው (ዝከ. 1፡4-20)። የዮሐንስ የወንጌል አቅርቦት በራዕይ ላይ የሚያተኩረው ንስሐ እና ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ነው። ይህ ግን የኢየሱስን ማዕከላዊ ሚና ማንኳሰስ አይደለም (ዝከ. 5:9,12; 7:14; 12:11), ነገር ግን ዘላለማዊውን መንግሥት በማምጣት ላይ ባለው ሚና ለማተኮር ነው (1 ቆሮ. 15:25-28); የሁለቱም የአብና የወልድ መንግሥት!

**12፡6 "ሴቲቱም ወደ በረሀ ሸሸች"** ብዙዎች ይሄንን የሚመለከቱት ለዘጸአት ጠቃሽ ነው፣ እሱም በዐውደ-ጽሑፉ ላይ በየስፍራው የሚገኝ። የበረሀ መንከራተቱ ጊዜ በራቢዎች የሚታየው በያህዌና በእስራኤል መካከል እንደ መተጫጨት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሰጥቷቸዋል፣ እንዲሁም በቅርበት ከእነርሱ ጋር ነበር።

◘ **"በእግዚአብሔር ወደ ተዘጋጀው ስፍራ"** ምንም እንኳ አጠቃላይ ዐውደ-ጽሑፉ በምድረ በዳ የመንከራተቱን ጊዜ ቢያንጸባርቅም፣ ይህ ሐረግ ሌሎች ታሪካዊ ጠቃሾችንም ይዟል።

1. ኤልያስ በቄድሮን ፈፋ (1 ነገሥ. 17:1-7)
2. የኤልያስ ወደ ሲና ባሕረ-ሰላጤ መሸሽ (1 ነገሥ. 19:1-14)
3. ሰባት ሺህ የታመኑት (1 ነገሥ. 19:18)
4. ከኢየሩሳሌም ጥፋት የሸሹት በ70 ዓ. ም (ማቴ. 24:15-20; ማርቆስ 13:12-18)

◘ **"ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን"** ይህም በድጋሚ የሚመስለው ያልተቀረጠ፣ ነገር ግን የተወሰነ፣ የስደት ጊዜ ነው። ይኸው ተመሳሳይ ጊዜና ሰዓት በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ተጠቅሷል፣ እሱም ከሦስት ዓመት ተኩል ያህል ጋር እኩል የሆነ።

1. "ዘመን፣ ዘመናት፣ የዘመን እኩሌታ" (ዳን. 7:25; 12:7; ራዕ. 12:14)
2. "2,300 ማታ እና ጠዋት" (ዳን. 8:14)
3. "አርባ ሁለት ወራት" (ራዕ. 11:2; 13:5); "1,260 ቀናት" (ራዕ. 11:3; 12:6); "1,290 ቀናት" (ዳን. 12:11); እና "1,335 ቀናት" (ዳን. 12:12)።

ሰባት ፍጹም ቁጥር ነው፣ በዕብራይስጥ ሥነ-ቁጥር (ዘፍ. 1፡1-2፡3)። ከሰባት አንድ ሲቀነስ ስለ ሰው ፍጹም ያለመሆን ይናገራል እና 666 (ራዕ. 13፡17-18) የመጨረሻ ፍጹም ያልሆነ ሰው ነው፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ (2 ተሰሎንቄ 2)። በተመሳሳይ መልኩ፣ ሦስት ተኩል የተወሰነ፣ ነገር ግን ያልተቀረጠ የመከራ ጊዜ ተምሳሌት ነው። ልዩ ርዕስ፡ አርባ ሁለት ወራት 11፡2 ላይ ተመልከት።

***ራዕይ፡ 12፡7-10ሀ***

**[7]በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥ [8]ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም። [9]ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ። [10ሀ]ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦**

**12፡7 "በሰማይም ሰልፍ ሆነ"**

**ልዩ ርዕስ፡ ጦርነት በሰማይ**

የዚህን ግጥሚያ ጊዜ በተመለከተ ብዙ ውይይቶች ተካሂደዋል። ኢየሱስ ይህንን የጠቀሰ ይመስላል፣ ሉቃስ 10፡18 እና ዮሐንስ 12፡31 ላይ። ነገር ግን ለሁነቱ ቅደም ተከተላዊ ቀኑን ለማስቀመጥ እጅግ አዳጋች ነው፡

1. ከዘፍጥረት 1፡1 በፊት (ከፍጥረት በፊት)
2. ከዘፍጥረት 1፡1 እና 1፡2 መካከል (የክፍተት ንድፈ-ሐሳብ)
3. በብኪ ከኢዮብ 1-2 በኋላ (ሰይጣን በሰማይ)
4. በብኪ ከ1 ነገሥ. 22፡21 በኋላ (ሰይጣን በሰማያዊው ሸንጎ)
5. በብኪ ከዘካርያስ 3 በኋላ (ሰይጣን በሰማይ)
6. በብኪ እንደ ኢሳ. 14፡12፤ ሕዝ. 28፡15 እና 2 ሄኖክ 29፡4-5 (የምስራቅ ነገሥታት የተኮነኑበት)
7. በአኪ ከኢየሱስ ፈተና በኋላ (ማቴዎስ 4)
8. በአኪ በሰባዎቹ ተልእኮ ጊዜ (ሰይጣንም ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ፣ ሉቃስ 10፡18)
9. በአኪ ወደ ኢየሩሳሌም በድል ከመግባት በኋላ (የዚህ ዓለም ገዥ ተጣለ፣ ዮሐንስ 12፡31)
10. በአኪ ከኢየሱስ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ (ኤፌ. 4፡8፤ ቆላ. 2፡15)
11. በፍጻሜ ዘመን (ራዕ. 12፡7፣ ሰይጣን ሰማይን እንደወረረ፣ ሕፃኑን ፍለጋ)

እሱን እንዲያው ብንመለከተው ይሻላል፣ በእግዚአብሔርና በክፉው ሠራዊት መካከል እንደሚደረግ ዘላለማዊ ውጊያ፤ ይህ ግጭት የሚጠናቀቀው ከዘንዶውና ሠራዊቱ ሽንፈት በኋላ ይሆናል። ራዕይ 20 ላይ እነርሱ ይወገዳሉ ይለያሉም!

◘ **"ሚካኤል"** በመጽሐፍ ቅዱስ በስማቸው የተጠቀሱት ሁለት መላእክት ብቻ ናቸው (ማለትም፣ ሚካኤልና ገብርኤል)። ይህ መልአክ የእስራኤል ሕዝብ መልአክ በሚል ተሰይሟል ዳን. 10፡13፡21 እና 12፡1 ላይ። እሱም የመላእክት አለቃ በሚል ይሁዳ ቁ.9 ላይ ተጠርቷል። ስሙም "እንደ እግዚአብሔር ያለ" ማለት ነው። አንዳንዶች ይህንን የሚመለከቱት ለክርስቶስ እንደ ሌላ ስም ነው፣ ይህ ግን በጣም ሩቅ መሄድ ይመስላል። እግዚአብሔር በአመጸኛው ክፉ አይሞከርም። መጽሐፍ ቅዱስ ምንታዌ አይደለም፣ እንደ ፋርስ

ዞሮስትሪኒዝም። እግዚአብሔር ክፉውን አሸንፏል፣ መልአክን በመጠቀም (ምንም እንኳ በእውነታው የክርስቶስ የመቤዠት ሥራ ቢሆንም)።

በሕጋዊ ዘይቤ፣ ሚካኤል ተከላካይ ዐቃቤ-ሕግ ነው፣ ሰይጣን እንደ ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ሲሠራ፣ ያህዌም ዳኛ ነው! ሚካኤል በጉዳዩ የሚረታው

1. በክርስቶስ መሥዋዕታዊ ሞት፣ ትንሣኤ፣ እና ዕርገት በኩል ነው (ዝከ. 12፡16)
2. በቤተ ክርስቲያን ታማኝ ምስክር (ዝከ. 12፡11ለ)
3. በቤተ ክርስቲያን መጽናት (ዝከ. 12፡11ሐ)

▣ ***"ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ"*** በትክክል የሰይጣን መላእክት እነማን እንደሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ ለመግለጽ ያስቸግራል። ብዙዎች የሚመለከቷቸው እንደ አጋንንት ነው (ማቴ. 25:41; ኤፌ. 6:10)። ነገር ግን ዘወትር የሚደጋገም ጥያቄ አለ፣ በእንጦርጦስ ስላሉት መላእክት (2 ጴጥ. 2፡4)፣ እና ራዕ. 9፡14 ላይ ስለተጠቀሱት መላእክት፣ እነርሱም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር የሆኑት ግን ባጠቃላይ ክፉ መላእክት የሆኑት። አብዛኛው በመላእክት ዓለም ያለው ግጭት ያልተብራራ ነው (ዳንኤል 10)።

ደግሞም ቀጣይነት ያለው ውይይት አለ፣ በወደቁት የብኪ መላእክት እና በአኪ አጋንንት መካከል ባለው ዝምድና። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ዝም ነው ያለው። በይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ (በተለይ 1 ሔኖክ) የሚያስረግጠው ከፊል መልአክ፣ ከፊል ሰው የሆነው ፍጡር፣ የዘፍ. 6፡1-4 የአኪ አጋንንት ናቸው፣ የሰውን አካል ለዳግም መኖሪያነት የሚሹት። ይህ ግምታዊ ነው፣ ነገር ግን እሱ አንዳንድ የአንደኛው ክፍለ-ዘመን አይሁድ ስለዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ምን ያስቡ እንደነበር ይገልጻል።

*የድርጊት ያልተወሰነው* ለዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የሚገጥም አይመስልም። እሱ ሊሆን የሚችለው ሴማዊነት ነው፣ እናም ሊተረጎም የሚችለው "ተዋግቷል" በሚል ነው (የአብራሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣ ቅጽ 12፣ "ራዕይ" በአለን ጆንሰን፣ ገጽ 519፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 7። ይህ በራዕይ ላይ ከምወዳቸው ሐተታዎች አንዱ ነው)።

**12፡8** ይህ የመጀመሪያው ተለጣጣቂ አበረታች ቃል ነው፣ ለተሳደደችው ቤተ-ክርስቲያን። ቁጥር 8፣ 11፣ እና 14 ለእግዚአብሔር ሕዝብ ትልቅ መጽናኛ ይሰጣሉ፣ እነርሱም ቀጣይነት ባለው መከራ ውስጥ ለሚያልፉት በአንደኛው ክፍለ-ዘመንና በእያንዳንዱ ክፍለ-ዘመን። ሰይጣን ቀደም ብሎ ሁለት ጊዜ ተሸንፏል፡ አንድ ጊዜ ሕፃኑን ሊገድል ሲሞክር (ዝከ. ቁ. 4) እና አሁን ለእግዚአብሔርን ዙፋን ለመውረር ሲሞክር (ዝከ. ቁ. 7-9)፣ እሱም ደግሞ ይሸነፋል የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከምድር ላይ ሊያስወግድ ሲሞክር።

▣ ***"ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም"*** ይህ የሚያመለክተው ሰይጣን ለሆነ ጊዜ በሰማይ እንደነበረ ነው (ኢዮብ 1-2፤ ዘካርያስ 3፤ እና 1 ነገሥ. 22፡21)። የብዙ ተውላጠ ስሙን አስተውል፣ እሱም የሚያመለክተው ሌሎች መላእክት ከሰይጣን ጋር ኅብረት እንዳላቸው ነው።

**12፡9 "ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤"** እዚህና ራዕ. 20፡2 (ጥበበ ሰሎሞን 2፡24)፣ ናቸው ብቸኛ ስፍራዎች፣ ሰይጣን ተለይቶ የተጠቀሰው ከዘፍጥረት 3 እባብ ጋር፣ በተለየ መልኩም 2 ቆሮ. 11፡3። "ዲያብሎስ" የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን "ስም አጥፊ" ማለት ነው፣ "ሰይጣን" የሚለው ቃል ደግሞ የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን "ተቀናቃኝ" ማለት ነው (II ሳሙ. 19:22; I ነገሥ. 11:14)። እነርሱ ሁለቱም አጽንዖት የሚሰጡት ለክፉው ሥራ ነው፣ እንደ ወንድሞች ከሳሽ (ዝከ. ቁ. 10)። "ሰይጣን" የሚለው ቃል በብኪ (ልዩ ርዕስ 12፡3 ላይ ተመልከት) ዘወትር የተጸውዖ ስም አይደለም፣ ነገር ግን በሦስት የተለዩ ክስተቶች ነው፡ (1) ኢዮብ 1-2; (2) ዘካ. 3:1-3; እና (3) I ዜና. 21:1። ለ "የተጣለው" ሙሉ ማስታወሻውን 12፡4 እና 7 ላይ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ አካላዊው ክፉ

ይህ በብዙ ምክንያቶች አስቸጋሪ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡

1. ብሉይ ኪዳን አውራ ጠላት ለእግዚአብሔር መኖሩን አይገልጽም ነገር ግን የያህዌ አገልጋይ፣ እሱም ለሰው ልጅ አማራጭ የሚያቀርብ፣ ብሎም የሰው ልጅን ስል ጽድቅ የሚከስ።
2. የአካላዊ አውራ ጠላት ጽንሰ-ሐሳብ እያደገ የመጣው በአዋልድ መጻሕፍት ሥነ ጽሑፍ ነው (በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባልታቀፉት)፣ እሱም በፋርሳዊ ሃይማኖት (ዞሮአስትሪያኒዝም) ተጽዕኖ ነው። ይህ፣ በግልባጩ፣ ራቢያዊ ይሁዲነትን ተጽዕኖ አሳድሮበታል።
3. አዲስ ኪዳን የብኪን ጭብጦች እያሳደገ መጥቷል፣ በአስገራሚ መልኩ፣ ግን በተመረጡ ፈርጆች።

አንዱ የክፉውን ጥናት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ መለኮት አኳያ ለማየት ቢፈልግ (እያንዳንዱ መጽሐፍ ወይም ጸሐፊ ወይም ዘውግ የሚጠናውም ሆነ የሚከፋፈለው ለየብቻ ነው) ከዚያም በጣም የተለያዩ የክፉ እይታዎች ይገለጣሉ።

ሆኖም ግን፣ ማንም የክፉውን ጥናት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ ወይም ከተረፈ መጽሐፍ ቅዱስ አኳያ፣ ማለትም ከዓለም ሃይማኖቶች ወይም ከምስራቅ ሃይማኖቶች አንጻር ቢየየው፣ ከዚያም አብዛኛው የአዲስ ኪዳን እድገት በፋርስ ምንታዌነት እና በግሪክ ሮማ መንፈሳዊነት ንግር (ጥላ) ተደርጎበታል።

ማንም በቅድመ ግምታዊ ሁኔታ ተጠምዶ የመጽሐፍ ቅዱስን መለኮታዊ ሥልጣን ቢመለከት፣ ከዚያም የአዲስ ኪዳን እድገት የግድ የሚታየው በእድገታዊ መገለጥ ነው። ክርስቲያኖች የግድ መጠበቅ ያለባቸው የአይሁድ አፈ ታሪክ ወይም የእንግሊዝ ሥነ ጽሑፍ (ዳንቴ፣ ሚልተን) ጽንሰ ሐሳቡን በተጨማሪ ያብራሩ ዘንድ መፍቀድ አይኖርባቸውም። በራዕይ አካባቢ በርግጥ ምሥጢራዊነትና አሻሚነት ይኖራል። እግዚአብሔር አልመረጠም፣ ሁሉም የክፉው ገጽታዎች፣ የሱ መነሻ፣ ዓላማው፣ ይገለጹ ዘንድ፣ ነገር ግን መሸነፉን ገልጧል!

በብኪ ሰይጣን ወይም ከሳሽ የሚለው ቃል በሦስት የተለያዩ ምድቦች የሚዛመድ ይሆናል፡

1. የሰው ከሳሾች - 1ኛ ሳሙ. 29:4፤ II ሳሙ. 19:22፤ I ነገሥ. 11:14፣20፣29፤ መዝ. 109:6
2. የመላዕክት ከሳሾች - ዘኍ. 22:22-23፤ ዘካ. 3:1
3. የአጋንንት ከሳሾች - 1ኛ ዜና. 21:2፤ I ነገሥ. 22:21፤ ዘካ. 13:2

ኋላ ላይ በኪዳናት ጊዜ ነው የዘፍ. 3ቱ እባብ፣ ሰይጣን በመባል የሚታወቀው (መጽሐፈ ምሳሌ 2፡23-24፤ 2ኛ ሄኖክ 31፡ 3)፣ እናም ኋላ ላይ ይህ ራቢያዊ አማራጭ ሆነ (ሶት 9ለ እና ሳንሀ. 29ሀ)። በዘፍ. 6 ላይ ያሉት "የእግዚአብሔር ልጆች" በ1ኛ ሄኖክ 54፡6 ላይ መላዕክት ይሆናሉ። ይሄንን የጠቀስኩት፣ የሱን ሥነ መለኮታዊ ትክክለኛነት ለማጽናት አይደለም፣ ነገር ግን እድገቱን ለማሳየት ነው። በአዲስ ኪዳን እነዚህ የብኪ ተግባራት ለመላዕክት፣ ሰውኛ ለሆኑ ክፉ አካላት የተሰጡ ናቸው (I ቆሮ. 11:3፤ ራዕ. 12:9)።

ሰውኛ የሆነው የክፉ አካል መነሻው አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ነው (በራስህ አመለካከት የሚወሰን ነው) ከብኪ ለመወሰን። ለዚህ አንደኛው ምክንያት የእስራኤል የጸና አሀዳዊነት ነው (1ኛ ነገሥ. 22:20-22፤ መክብብ. 7:14፤ ኢሳ. 45:7፤ አሞጽ 3:6)። ሁሉም ምክንያቶች የሚያመላክቱት ወደ ያህዌ ነው፣ የሱን የተለየነትና ዋናነት ለማሳየት (ኢሳ. 43:11፤ 44:6፣8፣24፤ 45:5-6፣ 14፣18፣21፣22)።

አንደኛው ዓይነት መረጃ የማግኘት ጎዳና ያተኩር የነበረው (1) ኢዮብ 1-2 ነው፣ ሰይጣን አንደኛው "የእግዚአብሔር ልጆች" የሆነበት (ማለትም፣ መላዕክት) በእግዚአብሔር ፊት (ዘካ. 3) ወይም (2) ኢሳ. 14፤ ሕዝ. 28 ትዕቢተኛው በምስራቅ ነገሥታት አጠገብ በሆነበት (ባቢሎንና ጢሮስ)ጥቅም ላይ የዋሉት የሰይጣንን ትዕቢት ለማሳየት ነው (1ኛ ጢሞ. 3፡6)። በዚህ አግባብ ላይ ስሜታዊነትን ጨምሬበታለሁ። ሕዝቅኤል የኤደን ገነትን ዘይቤ የተጠቀመው የጢሮስን ንጉሥ እንደ ሰይጣን በማቅረብ ብቻ አይደለም (ሕዝ. 28:12-16)፣ ግን ደግሞ ለግብፅም ንጉሥ ነው፣ መልካምና ክፉውን እንደምታስታውቀው ዛፍ (ሕዝ. 31)። ሆኖም፣ ኢሳ. 14፣ በተለይም ቁ. 12-14፣ ለመግለጽ የሚሞክረው የመላዕክትን ዐመጽ ነው በኩራት የተነሣ። እግዚአብሔር የሰይጣንን የተለየ ተፈጥሮና መነሻ ለመግለጽ ቢፈልግ ይህ በእጅጉን ዘወርዋራ መንገድና ቦታ ነበር፣ ይህን ለማድረግ። ስልታዊ ከሆነ ሥነ መለኮት አዝማሚያ መጠበቅ ይኖርብናል፤ እሱም፣ ጥቂቱን፣ አሻሚ የሆነውን የተለያየ የቃሉን ክፍል፣ ጸሐፊዎችን፣ መጻሕፍትን፣ እንዲሁም ዘውጎችን በመውሰድና በመደባለቅ አንድ መለኮታዊ ዕንቆቅልሽ እንዳንፈጥር።

አልፍሬድ ኢደርሺም በእሱ፣ *የመሲሑ የኢየሱስ ሕይወትና ጊዜ*፣ ቅጽ 2 አዝል XIII (ገጽ 748-763) እና XVI (ገጽ 770-776) እንደሚለው ራቢያዊ ይሁዲነት በፋርስ ምንታዌነትና በአጋንንታዊ ትንተና ከመጠን በላይ ተጽዕኖ አርፎበታል። ራቢዎች በዚህ አካባቢ ላለው እውነት ጥሩ ምንጮች አይደሉም። ኢየሱስ በዚህ አካባቢ በምኩራብ ካለው ትምህርት ሥር ነቀል በሆነ መልኩ አፈንግጧል። እንደማስበው፣ የራቢያዊ ጽንሰ ሐሳብ የሆነው መልአካዊ ምልጃና ተቃውሞ፣ ለሙሴ ሕጉ በሲና ተራራ በተሰጠው ጊዜ ነው የሊቀ መላእክት ሕላዌ ያህዌንና የሰው ልጅን የመቃወማቸው ጽንሰ ሐሳብ በር የተከፈተለት። ሁለቱ የኢራናውያን ምንታዌ ታላቅ አማልክት፣ አሁራ ማዝዳ (መልካሙ አማልክት) ወይም አንግራ ሜንዩ (ክፉው አማልክት)፣ ለበላይነት በምድር ላይ ተዋግተዋል እንደ ጦር አውድማ። ከዚህ ውጊያ በኋላ በይሁዲነት ውስጥ ምንታዌነት እያደገ መጣ፣ በያህዌና በሰይጣን መካከል።

በርግጥ ቀጣይነት ያለው ራዕይ በአዲስ ኪዳን አለ፣ የክፉውን አካልነት በተመለከተ፤ ነገር ግን እንደ ራቢዎች የተብራራ አይደለም። ለዚህ ልዩነት ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው "በሰማይ የተደረገው ጦርነት" ነው። የሰይጣን መውደቅ አመክኖአዊ መሻት ነው፣ ግን በተናጠላዊ (በተለየ) መልኩ አልቀረበም። የተሰጠውም ቢሆን በተምሳሌታዊ ራዕይ ተሸፍኗል (ራዕ.12:4፣7፣12-13)። ምንም እንኳ ሰይጣን ቢሸነፍና ወደ ምድር ቢጋዝም፣ እሱ አሁንም ቢሆን እንደ ያህዌ አገልጋይ ይሠራል (ማቴ. 4:1፤ ሉቃ. 22:31-32፤ I ቆሮ. 5:5፤ I ጢሞ. 1:20)።

በዚህ አካባቢ ያለንን ትኩረት መገታት አለብን። ግለሰባዊ ግፊትና የክፉው ፈተኛ አለ፣ ግን አሁንም አንድ አምላክ አለ፣ እንዲሁም የሰው ልጅ ለራሱ/ራሷ ምርጫ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ። መንፈሳዊ ውጊያ አለ፣ በሁለቱም፣ ከመዳን በፊትም ሆነ ኋላ። ድል ሊገኝ እና ሊቀር የሚችለው በሦስትነቱ አንድ አምላክ ውስጥ ብቻ ነው። ክፉው ተሸንፏል፣ እናም ይወገዳል!

◘ ***"ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው"*** ይህ የሚገልጸው የክፉውን ተልዕኮ ነው። ወንጌል ሁለንተናዊ እንደመሆኑ (ማቴ. 28:18-20; ሉቃስ 24:47; ሐዋ. 1:8), የወንጌል ተቃዋሚም እንዲሁ ነው! እጅግ የተሻለው ያነበብኩት መጽሐፍ፣ በሰይጣን እድገት ላይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከአገልጋይነት ወደ ጠላትነት፣ የኤ.ቢ. ዴቪድሰን *የብሉይ ኪዳን ሥነ-መለኮት* ነው፣ ገጽ 300-306። የሰይጣን ተልዕኮ II ቆሮ. 4:4; I ጴጥ. 5:8; ራዕ. 13:14; 19:20; 20:3,8,10; II ዮሐንስ 7። ሰይጣንን እንደ እግዚአብሔር አጋልጋይ ማሰብ ያስቸግራል ነገር ግን II ሳሙ. 24:1ን ከ I ዜና. 21:1 ጋር አነጻጽሩ።

◘ ***"ወደ ምድርም ተጣለ"*** "ተጣለ" የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ፡ ሁለት ጊዜ ቁ. 9፤ ቁ. 10፣ እና ቁ. 13 ላይ። ደግሞም ጥቅም ላይ ውሏል 19:20; 20:3,10,14,15 እና እንዲሁም ጠቃሽ ነው ኢሳ. 14:12 ወይም ሉቃስ 10:18; እና እንዲሁም ዮሐንስ 12:31 ላይ። ምድር የሰይጣን ድርጊቶች ግዛት ሆናለች። ሙሉ ማስታወሻ በሰይጣን ውድቀት ላይ 12:4 እና 7 ላይ ተመልከት።

**ራዕይ፡ 12፡10ለ-12**

**[10ለ]አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው**

**የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። [11]እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም። [12]ስለዚህ፥ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ፤ ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።**

**12:10ለ-12** ይህ በሰማይ ያለ ትልቅ ድምፅ ያለው መልእክት ነው።

**12:10 *"አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥"*** ይህ ከ11:15-18 ጋር ጽሑፋዊ አቻ ነው። ፍጻሜው ገና ድሮ ቀርቧል፣ እግዚአብሔርም ባለ ድል ነው! ይህ እጅግ ረጂ ነው፣ ጽኑ መከራ፣ ሞትንም ጭምር ለሚቀበሉ አማኞች።

◘ **"የወንድሞቻችን ከሳሽ"** ይህ የሚያመለክተው ቁ. 10 ላይ ያለው ድምጽ መልአክ አለመሆኑን ነው፣ ነገር ግን ባጠቃላይ አማኞች፣ ይልቁንም የ6:9-11 ሰማዕታት።

የዕብራይስጡ ቃል ሰይጣን "ከሳሽ" ማለት ነው። ሰይጣንን በዚህ ሚናው ላይ ኢዮብ 1:9-11 እና ዘካ. 3:1 ላይ እናየዋለን።

◘ **"ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው"** ሰይጣን ከሰማይ ቢጣልም፣ አሁንም ታማኞችን በእግዚአብሔር ፊት ይከሳል። ይህ የዚህ ዘውግ ተለዋዋጭነት ነው። ኃይሉ ተሰብሯል፣ ነገር ግን አሁንም ንቁ ነው (ሆኖም፣ በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው፣ ኢዮብ 1-2)።

**12:11 "እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥"** ድሉ ቀደም ብሎ ሆኗል፣ በእግዚአብሔር መሲሕ ምትክ መሥዋዕትነት (ዝክ. 1:5; 7:14; I ጴጥ. 1:18-19; I ዮሐንስ 1:7)። ይህ የመቤዣ ዋጋ የሚያካትተው ሁለቱንም

1. የእግዚአብሔር ጸጋ፣ በክርስቶስ መሥዋዕታዊ ሞት (ማርቆስ 10:45; II ቆሮ. 5:21)
1. ከአማኞች የሚጠበቅ የእምነት ምላሽ (ዝክ. 6:9; ማርቆስ 1:15; ዮሐንስ 1:12; 3:16; ሐዋ. 3:16,19; 20:21) እና የእነርሱ ያንን እምነት ማካፈል (ማለትም፣ በሕይወት ስልት እና በቃል)

ይህ ሐረግ እጅግ 14:12ን ይመስላል። ትልቅ ተመሳሳይነት አለ፣ ቁ. 11 እና 17 መሐል። ቁጥር 11 ደኅንነትን የሚገልጽ ይመስላል፣ ቁ. 17 ደግሞ የክርስቲያንን ብስለትና ታጋሽነት። የክርስቶስ ድል የተገኘው ቀራንዮ እንደሆነ ተገንዘብ፣ ሚሊኒየም ላይ ሳይሆን።

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም"** |
| **አኪጀት** | **"ነፍሳቸውን እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም"** |
| **አየተመቅ** | **"በሕይወት መኖርን አልወደዱም እስከ ሞት ድረስ"** |
| **አእት** | **"ሕይወታቸውን እስከ መስጠትና እስከ ሞት ድረስ ፍቃደኛ ነበሩ"** |
| **አኢመቅ** | **"ሞትን እስከ መቅመስ ድረስ ሕይወትን አልወደዱም"** |

የአንደኛው ክፍለ-ዘመን አማኞች እና ቤተሰባቸው አስፈሪ ሞትን ቀምሰዋል (ብዙዎች በየዘመናቱ እንደሆኑት)። እነርሱ በእግዚአብሔር ታትመዋል፣ ተጠብቀዋልም፣ ነገር ግን አሁንም በማያምኑት ይሳደዳሉ። በክርስቶስ ያላቸው እምነት ከሞት ፍራቻቸው ይልቅ ጠንካራ ነበር (ዝክ. 2:10; ማርቆስ 8:35; 13:13; ሉቃስ 14:26; ዮሐንስ 12:25)።

**12:12 "ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ፤"** ይህ የአሁን መካከለኛ ተተኳሪ ነው (ዝክ. 18:20)። እሱም የመዝ. 96:11 ወይም ኢሳ. 49:13 ጠቃሽ ነው። ሰማይ ይደሰታል ምክንያቱም ሰይጣን ስለተጣለ፣ ነገር ግን ለምድር ወዮ!

"ሰማያት" የሚለው የብዙ ቁጥር በብኪ ጥቅም ላይ የዋለው (1) ከምድር በላይ ያለውን ከባቢ አየር ለመግለጽ ነው (ዘፍ. 1) እና (2) እግዚአብሔር የሚኖርበትን ስፍራ ለመግለጽ ነው። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ቁ. 2 ነው።

"መኖር" የሚለው ቃል (አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አየተመት) ወይም "እዚያ መኖር" (አእት፣ አኢመቅ) "መቅደስ" ከሚለው ስም የመጣ ነው። እሱ የሚያመለክተውም ከእግዚአብሔር ጋር ቋሚ መኖርያ ነው (ዝክ. 7:15; 12:12; 13:6; 21:3 እና ዮሐንስ 1:14 ክርስቶስ ከእኛ ጋር)።

◘ **"ቁጣ"** 7:14 ላይ ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት።

◘ **"ጥቂት ጊዜ እንዳለው አውቆ"** ይህ የሚያመለክተው ጊዜና ሰዓት በክርስቶስ ዕርገት (ሐዋ. 1:9-11) መካከል እና በዳግም ምጽአቱ፣ እሱም ዮሐንስ እና የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ክርስቲያኖች አጭር ጊዜ እንደሚሆን ያሰቡ እንደ ነበረ ነው። አሁን 2000 ዓመት ያህል ሆኖታል፤ እያንዳንዱ ትውልድ የጌታ በሆነ ጊዜ መመለስ ተስፋ አለው። አማኞች ይህ ዝግየታ ተስጠንቅቆላቸዋል፣ 2 ተሰሎንቄ እና ማቴዎስ 24:45-51። መዘግየቱ እምነትን እንደማይቀንስ ተጠንቀቁ (II ጴጥ. 3:3-4)።

## ልዩ ርዕስ፡ የኢየሱስ በሆነ ሰዓት መመለስ በተቃርኖ ገና ነው (የአዲስ ኪዳን ፓራዶክስ (ኢያዎ))

ሀ. የአዲስ ኪዳን የፍጻሜ አመላካች አንቀጾች የ ብሉይ ኪዳን ን ትንቢታዊ ውስጠት ያንጸባርቃሉ፣ እነሱም የፍጻሜ ጊዜን በወቅታዊ ክስተቶች ይመለከታሉ።

ለ. ማቴ. 24፣ ማርቆስ 13፣ እና ሉቃስ 21 ለመተርጎም በጣም አስቸጋሪ ናቸው፣ ምክንያቱም እነሱ በአንጻራዊው በርካታ ጥያቄዎችን ስለሚያስነሡ ነው።

1. መቅደሱ መቼ ይፈርሳል?
2. የመሲሑ መመለስ ምልክቱ ምን ይሆናል?
3. ይህ ዓለም መቼ ያልፋል (ማቴ. 24፡3)?

ሐ. የአዲስ ኪዳን የፍጻሜ ዘመን አንቀጾች ዘወትር የጥፋት እና የትንቢታዊ ቋንቋ አላቸው፣ እሱም ሆን ተብሎ አሻሚና ተምሳሌታዊ የተደረገ።

መ. በአዲስ ኪዳን በርካታ አንቀጾች (ማቴ. 24፣ ማርቆስ 13፣ ሉቃስ 17 እና 21፣ 1እና2 ተሰሎንቄ እና ራዕይ) ስለ ዳግም ምጽዓቱ ያወሳሉ። እነዚህ አንቀጾች አጽንዖት የሚሰጡት፡
1. የሁነቱ ትክክለኛ ሰዓት አይታወቅም፣ ሁነቱ ግን ርግጠኛ ነው
2. አጠቃላዩን ሰዓት ማወቅ እንችላለን፣ ነገር ግን የተለየ ጊዜውን አይደለም፣ የሁነቶቹን
3. እሱም በድንገት እና ሳይጠበቅ ይከሰታል
4. እኛ በጸሎት የተሞላን፣ ዝግጁ፣ እና ታማኝ መሆን ይጠበቅብናል፣ ለተሰጡን ተግባራት።

ሠ. እዚህ አያዎአዊ (ፓራዶክሲካል) ሥነ-መለኮታዊ ክርክር አለ (1) በማንኛውም ሰዓት ይመለሳል (ሉቃስ 12:40፣46፤ 21:36፤ ማቴ.24:27፣44) እና (2) ሐቁ አንዳንድ ሁነቶች በታሪክ የግድ መፈጠር አለባቸው በሚሉት መካከል።

ረ. አዲስ ኪዳን ከዳግም ምጽአቱ በፊት አንዳንድ ሁኔታዎች እንደሚፈጠሩ ያስቀምጣል፡
1. ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል (ማቴ. 24:14፤ ማርቆስ 13:10)
2. ታላቁ ክህደት (ማቴ. 24:10-13፣ 21፤ 1ጢሞ. 4:1፤ 2ጢሞ. 3:1፤ 2ተሰ. 2:3)
3. "የጥፋት ሰው" መገለጥ (ዳን. 7:23-26፤ 9:24-27፤ 2ተሰ. 2:3)
4. የሚያሰናክለው መወገድ (2ተሰ. 2:6-7)
5. የአይሁድ ተሐድሶ (ዘካ. 12:10፤ ሮሜ 11)

ሰ. ሉቃስ 17፡26-37 ከማርቆስ ጋር ትይዩ አልተደረገም። እሱም ከፊል አጠቃሎሻዊ ትይዩ በማቴ. 24፡37-44 አለው።

**ራዕይ፡ 12፡13-17**

**[13]ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት። [14]ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን፥ ዘመናትም፥ የዘመንም እኩሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት። [15]እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተ ኋላዋ አፈሰሰ። [16]ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፥ ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው። [17]ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤**

**12፡13 "ሴት"** በመነሻነት "ሴት" ሊጠቅስ የሚችለው የብኪን አማኝ ማኅበረሰብ ነው፤ አሁን እሱ የሚያመለክተው የአኪ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው (ዝከ. ቁ. 17፤ 13፡7)። *የአዲስ ኪዳን የቃል ስዕሎች* ላይ፣ ገጽ 6፣ ኤ. ቲ. ሮበርትሰን "እውነተኛዋ እስራኤል በምድር ላይ" በማለት ይጠራታል (ገጽ 395)።

**12፡14 "ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት።"** እነዚህ የንሥር ክንፎች የእግዚአብሔር ጥበቃና ሰጭነት ተምሳሌቶች ናቸው (ዘጸ. 19:4; ዘዳ. 32:11; መዝ. 36:7; 57:1; 63:7;90:1,4; እና ኢሳ. 40:31)። ይህም ሌለኛው ጠቃሽ ይሆናል፣ ለአዲሱ ዘጸአት።

◘ **"ወደ ስፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር"** በረሀ የሚታየው እንደ መለኮታዊ ጥበቃ ነው፣ በእስራኤል ታሪክ በበረሀ የመንከራተቻ ጊዜ (ዝከ. ቁ. 6)። ይህ ትልቅ ማበረታቻ ነው፣ ለተጎዳች ቤተ-ክርስቲያን።

◘ **"ለዘመን፣ ለዘመናትም ለዘመንም እኩሌታ"** ይህ የዳን. 7:25; 12:7 ጠቃሽ ነው። ለዚህ ሐረግ ሙሉ ማስታወሻ 11:2 እና 12:6 ላይ ተመልከት።

**12፡15 "እባቡም ውኃ አፈሰሰ"** ለዚህ ልከኛ የሆነ ትይዩ በብኪ የለም። እሱ ከእግዚአብሔር ቁጣ ጋር የተያያዘ ዘይቤ ሊሆን ይችላል፣ ሆሴዕ 5፡10 ላይ ወይም የጫናና የኀዘን ጊዜ ዘይቤ ይሆናል፣ እንደ መዝ. 18:4; 124:4-5። ነገር ግን ምዕራፍ 12 ከጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ የተፈጥሮ አፈ-ታሪክ ጋር እጅግ ምናባዊ ስለሆነ፣ እሱ ሊያመለክት የሚችለው የውኃ ነውጥን ነው፣ በመነሻው ላይ የነበረው የመልካም እና ክፉ፣ የሥርዓት እና የቀውስ ትግልን የሚያሳይ።

ተፈጥሮ ለባሮክና ለዲቦራ ተዋግቶላቸዋል፣ ከከነናዊቷ ከተማ እና ከእሷ ወታደራዊ ጀነራል ከሲሳራ ጋር፡ (1) ዝናቡ ሠረገሎቻቸውን አስቆመ (መሳ. 5፡4) እና (2) ከዋክብት እንኳ (መልአካዊ ኃይላት ተደርገው የሚታሰቡ) ከሲሳራ ጋር ተዋግተዋል (መሳ. 5፡20)።

**12፡17 "...ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤"** ክፉው መሲሐዊውን ማኅበረሰብ ሊያጠፋ ሞክሯል
1. መሲሑን በማጥፋት
2. እናት ቤተ-ክርስቲያንን በማጥፋት
3. ሁሉንም የመሲሑን ተከታዮች በማጥፋት።

"ጦርነትን ማካሄድ" የሚለው ሐረግ ለመንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ተቃዋሚዎች ዘይቤ ነው። ይህም የዳን. 7፡21 ጠቃሽ ነው (ዝከ. 11:7; 13:7)። ይህ ስደት ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ያገኘችው ድል ሁነኛ ማስረጃ ነው (ፊሊ. 1፡28)።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የሰባተኛውን መለከት ይዘት አብራራ።
2. የኪዳኑ ታቦት ራዕይ፣ እነዚህን የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ክርስቲያኖች እንዴት እጅግ የሚያበረታታቸው ሊሆን ቻለ?
3. ራዕይ 12 ላይ ያለችው ሴት ማናት?
4. ይህ የሰማይ ጦርነት የሚከፈተው መቼ ነው?
5. የዲያብሎስ መላእክት ከአጋንንታዊ ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?
6. "ለዘመን፣ ለዘመናት እና ለዘመን እኩሌታዕ የሚለው ሐረግ በዳንኤልና በራዕይ ምን ማለት ነው?
7. ይህ ምንባብ የአንደኛውን ክፍለ-ዘመን ተሳዳጅ ክርስቲያኖች እንዴት ያበረታል?

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ራዕይ 13፡1-18

ሀ. ምዕራፍ 13 ቀጣይ የዳበረ ምስያ ነው የ12፡13-17።

ለ. የዚህ መጽሐፍ የብኪ ዳራ ዳንኤል 7 ነው። ዳንኤል ላይ የተተነበዩት አራቱ የቅርብ ምስራቅ ኢምፓየሮች፣ በዚህ የተጠቃለለ፣ ሁለንተናዊ፣ የእግዚአብሔረ ተቃዋሚ፣ የፍጻሜው ዘመን መንግሥት ተጠቃለዋል።

ሐ. የአንደኛው ክፍለ-ዘመን የአጼ አምልኮ (በተለይም፣ በታናሹ እስያ) አንዱ ታሪካዊ ፍጻሜ ነው የአውሬው አምልኮ፣ የፍጻሜ ዘመኑ የኃጢአት ሰው እንደሚሆነው ሁሉ (2 ተሰሎንቄ 2)፣ እና የዳንኤል 7 (ዝኪ. ቁ. 8,11,20,25)፣ ትንሹ ቀንድ፣ እርሱም ከአራተኛው ሥርወ-መንግሥት ውጭ፣ ሮም።

መ. አውሬው በሁለት መንገዶች ተገልጧል

1. ቀጣይነት ያለው፣ የሐሰት ትምህርት/መምህር(ራን) (I ዮሐንስ 2:18,22; 4:3; II ዮሐንስ 7)። እሱም ሁለቱም የብዙና የነጠላ ቁጥር ነው፣ ሁለቱም የአሁንና የወደፊት።
2. እንደ አንድ ሁነኛ ሰው፣ ይልቁንም በክፉ ሰዎች ንግር የሆነ፣ በታሪክ ሁሉ ላይ (አንቲክስ፣ የሮም ነገሥታት፣ ሂትለር፣ ወዘተ…፣ ነገር ግን ባጠቃላይ እንደ ፍጻሜ ዘመን ሰው፣ ሰውኛ ሆኗል 2 ተሰ. 2፡1-10)።

ሠ. ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

### ልዩ ርዕስ፡ ሰዋዊ መንግሥት

I. መግቢያ
   ሀ. መግለጫ — መንግሥት በሰብዓዊነት ራሱን ያደራጀ ነው፣ አስፈላጊውን ነገሮች ለመስጠትና ለማስከበር (ማለትም፣ ዘፍጥረት 4 እና 11)። ሰዎች ማኅበራዊ ፍጡራን ናቸው፣ ከውድቀት በፊት እንኳ ዘፍ. 2፡18)። ቤተሰቦች፣ ነገዶች፣ ብሔሮች ማኅበረሰብን ያስገኙልናል።
   ለ. ዓላማ — የእግዚአብሔር ፍቃድ ከሥርዓተ-አልበኝነት ይልቅ ሥርዓትን ይመርጣል።
      1. የሙሴ ሕግጋት፣ በተለይም ተዕዛዛቱ ለሰው ማኅበረሰብ የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው። እሱም አምልኮንና ሕይወትን ያመዛዝናል።
      2. በቅዱስ ቃሉ የትኛውም ዓይነት መንግሥታዊ አወቃቀር ድጋፍ አላገኘም፣ ምንም እንኳ የጥንት የእስራኤላውያን መንግሥተ-መለኮት የሰማይ መልክ እንዳለው ቢጠበቅም። ዲሞክራሲም ሆነ ካፒታሊዝም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት አይደሉም። ክርስቲያኖች በአግባቡ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፣ በየትኛውም መንግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ ራሳቸውን ቢያገኙም። የክርስቲያን ዓላማ ወንጌላዊነት እና አገልግሎት ነው እንጂ አብዮት አይደለም። ሁሉም መንግሥታት ሀላፊ ናቸው!
   ሐ. የሰው መንግሥት መነሻ
      1. የሮሜ ካቶሊካዊነት የሚያስረግጠው የሰው መንግሥት ተፈጥሯዊ ፍላጎት ነው፣ ከውድቀት በፊት እንኳ። አርስቶትል ይህን ቅድመ-ሐሳብበመጀመሪያ ያስረገጠ ይመስላል። እሱ የሚለው፣ "ሰው ፖለቲካዊ እንስሳ ነው" እና በዚህ እሱ ማለት የሚሻውመንግሥት "የሚኖረው መልካም ሕይወትን ለማሳደግ ነው።"

2. ፕሮቴስታንታዊነት፣ በተለይም ማርቲን ሉተር የሚያስረግጠው የሰው መንግሥት ከውድቀት በኋላ የተገኘ መሆኑን ነው። እሱም "የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ መንግሥት" በማለት ይጠራዋል። እሱ የሚለው፣ "ክፉ ሰዎችን ለመቆጣጠር እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መንገድ፣ ክፉ ሰዎች እንዲቆጣጠሩት በማድረግ ነው።"
3. ካርል ማርክስ የሚያስረግጠው፣ መንግሥት ማለት ጥቂት አዋቂዎች ብዙኃኑን በቁጥጥራቸው ሥር የሚያደርጉበት መንገድ ነው። ለእርሱ መንግሥትና ሃይማኖት ተመሳሳይ ሚና ይጫወታሉ።

II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገሮች

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. እስራኤል በሰማይ ጥቅም ላይ የሚውል ፈርጅ ነው። በጥንታዊ እስራኤል ያህዌ ንጉሥ ነበር። ቴዎክራሲ (መንግሥት-መለኮት) የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ቀጥተኛ ገዥነት ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ነው (1 ሳሙ. 8:4-9)።
2. የእግዚአብሔር ሊዓላዊነት በሰዎች መንግሥት ላይ በግልጽ ይታያል፣ እነርሱን በመሾም
   ሀ. ነገሥታት ሁሉ ዳን. 2:21; 4:17,24-25
   ለ. የመሲሐዊ ንግሥና, ዳን. 2:44-45
   ሐ. ናቡከደነፆር (አዲሷ ባቢሎን), ኤር. 27:6; ዳን. 5:28
   መ. ሲረስ II (ፋርስ), II ዜና. 36:22; ዕዝራ 1:1; ኢሳ. 44:28; 45:1
3. የእግዚአብሔር ሰዎች ተገዢና አክባሪ ሊሆኑ ይገባል፣ ለወራሪና ለባዕድ መንግሥታት እንኳ ቢሆን፡
   ሀ. ዳንኤል 1-4፣ ናቡከደነፆር (አዲሷ ባቢሎን)
   ለ. ዳንኤል 5፣ ብልጣሶር (አዲሷ ባቢሎን)
   ሐ. ዳንኤል 6፣ ዳርዮስ (ፋርስ)
   መ. ዕዝራ እና ነህምያ (ፋርስ)
4. የተመለሰው ይሁዳ ለሲረስ እና ለእሱ ዝርዮች ግዛት እንዲጸልይ ታዟል
   ሀ. ዕዝራ 6፡10፤ 7፡23
   ለ. አይሁድ ለሲቪል ባለሥልጣናት አንዲጸልዩ ታዘዋል፣ ሚሽናህ፣ አቮት. 3፡2

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ኢየሱስ ለሰዎች መንግሥት አክብሮት አሳይቷል
   ሀ. ማቴዎስ 17:24-27፤ የመቅደሱን ታክስ ከፍሏል (ሃይማኖታዊና የሲቪል ባለሥልጣናት አንድ ማለት ናቸው 1 ጴጥ. 2፡17)
   ለ. ማቴዎስ 22:15-22; ማርቆስ 12:13-17; ሉቃስ 20:20-26, ለሮም ታክስ መክፈሉን ተቀብሏል በዚያውም ለሮሜ የሲቪል ባለሥልጣናት
   ሐ. ዮሐንስ 19፡11፣ እግዚአብሔር የሲቪል ባለሥልጣናት አንዲሠሩ ፈቅዷል
2. የጳውሎስ ቃላት፣ ከሰዎች መንግሥት ጋር የሚያያዙት
   ሀ. ሮሜ 13፡1-5፣ አማኞች ለሰዎች የሲቪል ባለሥልጣናት እንዲገዙ፣ በእግዚአብሔር የተሾሙ በመሆናቸው
   ለ. ሮሜ 13፡6-7፣ አማኞች ታክስ መክፈል አለባቸው እንዲሁም የሲቪል ባለሥልጣናትን ማክበር
   ሐ. 1 ጢሞቴዎስ 2፡1-3፣ አማኞች ለሲቪል ባለሥልጣናት መጸለይ አለባቸው
   መ. ቲቶ 3፡1፣ አማኞች ለሲቪል ባለሥልጣናት መታዘዝ አለባቸው
3. የጴጥሮስ ቃላት ከሰዎች መንግሥት ጋር የተያያዙት
   ሀ. ሐዋ. 4:1-31; 5:29, ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት (ይህ የሚያመለክተው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሲቪል ሕግ ነው ለሲቪል ስለአለመታዘዝ)
   ለ. I ጴጥሮስ 2:13-17, አማኞች ለሲቪል ባለሥልጣናት መገዛት ይኖርባቸዋል፣ ለኅብረተሰቡ ደኅንነትና ለወንጌላዊነት
4. የዮሐንስ ቃላት ከሰዎች መንግሥት ጋር የተያያዙት
   ሀ. ራዕይ 17፣ ጋለሞታዋ ባቢሎን የሰዎችን መንግሥት ነው የምትወክለው፣ ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀውንና የሚሠራውን
   ለ. ራዕይ 18፣ ጋለሞታዋ ባቢሎን ወደቀች

III. ማጠቃለያ

ሀ. የሰው መንግሥት (የወደቀው ዓለም) በእግዚአብሔር ትእዛዝ የቆመ ነው። ይህ "የነገሥታት መለኮታዊ መብት" አይደለም፣ ነገር ግን የመንግሥት መለኮታዊ ሥራ ነው። የትኛውም ዓይነት ቢሆን ከሌለኛው በላይ ሊሆን አይችልም።
ለ. ለአማኞች ሃይማኖታዊ ተግባር ነው፣ የሲቪል ባለሥልጣናትን ይታዘዙና ይጸልዩላቸው ዘንድ።
ሐ. አማኞች የሰዎችን መንግሥት ታክስ ይከፍሉ ዘንድ ተገቢ ነው፣ ከሁነኛ የአክብሮት ሁኔተታጋር።
መ. የሰዎች መንግሥት የሲቪል ሥርዓትን ለማስከበር ዓላማ ነው። እነርሱ ለዚህ ተግባር የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው።
ሠ. የሰዎች መንግሥት የመጨረሻ ግብ አይደለም። ሥልጣኑ የተገደበ ነው። አማኞች ለሕሊናቸው ሲሉ መሥራት ይኖርባቸዋል፣ የሲቪል ባለሥልጣናትን ባለመቀበል፣ መለኮታዊ ሹመት ወሰኑን በሚያልፍበት ጊዜ። አውግስቲን *በእግዚአብሔር ከተማ* እንዳስረገጠው፣ የሁለት ዓለም ዜጎች ነን አንደኛው ጊዜያዊ ሌላው ዘላለማዊ (ፊሊ. 3፡20)። ለሁለቱም ኃላፊነት አለብን፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግሥት የመጨረሻ ግብ ነው! ሁለቱም ዓይነት፣ ግለሰባዊም ሆነ የተጠቃለለ ትኩረት ለእግዚአብሔር ኃላፊነት አለብን።
ረ. አማኞችን ማበረታታት አለብን፣ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ በመንግሥት ሂደትና በትግበራው በንቃት ለመሳተፍ፣ ከተቻለም

በቅዱስ ቃሉ ትምህርቶች።

ሰ. ከማኅበራዊ ለውጥ በፊት የግለሰቦች መቀየር ይቀድማል። በመንግሥት ላይ ምንም ዓይነት ርግጠኛ የሆነ የፍጻሜ ዘመን ተስፋ የለም። ሁሉም የሰዎች መንግሥታት፣ በእግዚአብሔር የተፈቀዱና ጥቅም ላይ ቢውሉም ፣ የኃጢአት መገለጫ የሰው ድርጅቶች ናቸው፣ ከእግዚአብሔር የራቁ። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ በጆሀኒ "ዓለም" በሚለው ቃል አጠቃቀም ላይ ተገልጿል (1 ዮሐንስ 2:15-17)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ራዕይ፡ 13፡1-6**

***12:18 ዘንዶውም በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ። 13:1 አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ። 2 ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፥ እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች፥ አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበሩ። ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው። 3 ከራሶቹም ለሞት እንደ ታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ፥ ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰ። ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ፥ 4 ለዘንዶውም ሰገዱለት፥ ለአውሬው ሥልጣንን ስጥቶታልና፤ ለአውሬውም። አውሬውን ማን ይመስለዋል፥ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል? እያሉ ሰገዱለት። 5 ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፥ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው። 6 እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ።***

**13፡1 *"ዘንዶውም በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ"*** አአመመቅ፣ አኪጀት እና አኢመቅ ምዕራፍ 13ን የሚጀምሩት በዚህ ሐረግ ነው (ማለትም፣ 12፡18)፣ አእት ደግሞ የሚያጠቃልለው በምዕራፍ 12 ውስጥ አካቶት ነው።

የጽሑፍ ልዩነት አለ 12፡18/13፡1 ላይ ባለው "ቆሟል" ከሚለው ግሥ ጋር በተያያዘ

1. "ቆሟል" የሚያመለክተው አውሬውን/ዘንዶውን ነው፣ እሱም ከምዕራፍ 12 — ኤምኤስኤስ ፒ[47], ℵ, ኤ, ሲ, (አአመመቅ, አየተመት, አእት, የተእመቅ, አእት, አዓአት)
2. "ቆሜአለሁ" የሚያመለክተው ዮሐንስን ነው፣ እሱም ወደፊት ከምዕራፍ 13 ጋር የሚዛመድ — ኤምኤስኤስ ፒ፣ 046፣ 051 (አኪጀት፣ አኢመቅ)

ዩቢኤስ[4] አማራጭ ቁ. 1 "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል(ከሞላ ጎደል ርግጠኛ)

"ባሕሩ" ምናልባት የዳ. 7፡2-3 ጠቃሽ ይሆናል። እሱም ተምሳሌትነቱ

1. የሰው ልጆችን ባጠቃላይ (ኢሳ. 17:12-13; 57:20; ራዕ. 17:15)
2. የቀውስ ኃይላት (ዘፍ. 1; ኢሳ. 51:9-10)

▣ **"አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤"** የዱር አውሬ (ዝከ. 13:14,15; 15:2; 16:13; 15:8) በቅድሚያ ያለ እይታ የተጠቀሰው 11፡7 ላይ ከጥልቁ እንደሚወጣ (ዝከ. 17፡8) ነው። እሱም የሚጠቀሰው "የክርስቶስን ተቃዋሚ" ነው፣ የ1 ዮሐንስ 2:18ሀ,22; 4:3; II ዮሐንስ ቁ. 7, ደግሞም "የዓመጽ ሰው" በመባል ይታወቃል 2 ተሰ. 2፡3። የዚሁ አውሬ ተመሳሳይ መግለጫ 12፡3 እና 17፡3፣8 ላይ ይገኛል።

"ከባሕር ወጣ" የሚለው ሐረግ በብዙ መንገዶች ይተረጎማል።

1. በጥሬው፣ እንደ በይነ-ኪዳናዊ የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ጽነ-ጽሑፍ እንደ ሌዋታን እና ቁ. 11 ላይ እንደ ብሄሞት
2. እንደ ዳንኤል 7 ጠቃሽ፣ አውሬው ከባሕር የሚወጣበት፣ ቁ. 3 ላይ እና ከምድር ላይ የሚወጣበት ቁ. 17፣ ይኸውም ከዳንኤል 7 ጋር ተመሳሳይ የሚሆኑበት፣ ነገር ግን ዮሐንስ የመጨረሻውን አውሬዎች ለይቷቸዋል፣ ወደ ሁለት የተለያዩ የፍጻሜ ዘመን ክፉዎች ገጸ-ባሕርያት፡ የባሕሩ አውሬ፣ ቁ. 1 እና የምድሩ አውሬ ቁ. 11
3. የወደቀው ሰው ተምሳሌት (በተለይም ራዕ. 17:15, ግን ደግሞ ዳን. 7:2-3; ኢሳ. 17:12-13; 57:20)

ምዕራፍ 13 ላይ ሁለቱ አውሬዎች ከባሕርና ከምድር እንደሚወጡ የተጠቀሰበት ምክንያት (1) ይህ ምዕራፍ ዳንኤል 7ን እጅግ ስለሚከተል ነው፣ ወይም (2) እነርሱ ተደባልቀው ሙሉውን ዓለም ስለሚወክሉ ነው። ደግሞም ሊሆን የሚችለው እነዚህ ሁለት አውሬዎች እና ሰይጣን ታክሎበት የሦስትዮሽ (ሥላሴ) ክፉ ማስመሰል ያበጃሉ።

▣ **"አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች"** ይህ በርግጠኝነት ዘንዶው አይደለም (ዝከ. 12፡3) ነገር ግን እሱ እጅግ ይመሳሰላል (ዝከ. 17፡3፣7-12)። አስሩ ቀንዶች የሚናገሩት ፍጹም ለሆነ ኃይል ነው፤ ሰባቱ ራሶች የሚወክሉት የክፉውን ፍጹም መገለጫ ነው፣ እና አስሩ ዘውዶች የሚያስረግጡት ንግሥናን ነው። ክፉ ዘወትር የመልካም ተጻራሪ ነው። ይህ ከበርካታ ክርስቶስን ማስመሰያዎች የመጀመሪያው ነው።

▣ **"የስድብ ስሞች"** የግሪኮቹ ጽሑፎች እኩል ተከፍለዋል፣ በብዙ (ኤምኤስ ኤ) "ስሞች" (አየተመት፤ አኢመቅ) እና ነጠላ (ኤምኤስኤስ ፒ[47]፣ ℵ፣ ሲ፣ ፒ) "ስም" (አኪጀት፣ አእት)። ዩቢኤስ[4] የትኛው ዋነኛ እንደሆነ ሊወስን አልቻለም። የትኛውም እውነት ቢሆን፣ ይህ የዳን. 7:8,11,20,25 ወይም 11:36 ጠቃሽ መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህ የስድብ ስሞች የሚያያዙት (1) የመለኮትነት ይገባኛል ወይም (2) ክፉ መጠሪያዎች ነው (ዝከ. 17፡3)።

**13፡2 “ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር… ድብ… አንበሳ”** ይህ የበርካታ አውሬዎች ድብልቅ ነው፣ ሌላው ጠቃሽ፣ ከዳን 7፡4፣5፣6፣ እሱም ተለጣጣቂ ነገሥታትን የሚጠቅስ፣ እዚህ ግን ተምሳሌትነቱ ተቀይሯል፣ ወደ እግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓቶች ድብልቅ፣ እሱም በአንድ መሪ ሰውኛ የሆነ (ዳን. 7፡24)።

▣ **“ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው”** ይህ የ2 ተሰ. 2፡9 ትይዩ ነው፣ እሱም ስለ ሰይጣናዊ ተመስጦ ኃይል የሚናገር። አውሬው ሰይጣን አይደለም፣ ነገር ግን ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ኃይል የተሞላ የሰው መገለጫ ወይም የእሱው ሥጋ መልበስ ነው (ዝከ. ቁ. 4፣12)። ይህም ሌለኛው ክርስቶስን ማስመሰያ ነው ዝከ. 5፡6)።

**13፡3 “ከራሶቹም ለሞት እንደ ታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ፥”** ይህ የተጠናቀቀ ተገብሮ አንቀጽ ነው፣ እሱም ከሰዋሰው አንጻር ከበጉ 5፡6 ላይ ካለው ትይዩ የሆነ። ይህም ሌለኛው ለኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ማስመሰያ ነው።

▣ **“ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰ።”** ሰይጣን ይህንን ሰው ለማስነሣት ችሎታ ይኖረዋልን፣ ወይስ ይህ ማጭበርበር፣ ምትሐት፣ እና ማስመሰል ነው (ዝከ. 13፡15)? ሰይጣን የእግዚአብሔርን ኃይል ያስመስላል፣ ክርስቶስን እንዳስነሣው።

ይህ ታሪካዊ ጠቃሽ ይሆናል፣ ለ“ኔሮ አፈታሪክ” እሱም የሚያስረግጠው ኔሮ ተመልሶ ወደ ሕይወት እንደሚመጣ ነው፣ ብሎም ከታላቅ ምስራቃዊ ሠራዊት ጋር ተመልሶ ይመጣል። (ፋርሳውያን)፣ እና ሮምን ያጠቃል (የሲቢሊን ንግሮች፣ መጽሐፍ III-V)።

▣ **“ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ፥”** ሰይጣን ተአምራትን ይጠቀማል፣ የማያምነውን ዓለም ለማሳመን፣ እሱን እንዲከተል (ማቴ. 24:24; ማርቆስ 13:22; II ተሰ. 2:9; ራዕ. 13:5; 17:8)፣ ይኸውም ሌለኛው ክርስቶስን ማስመሰያ። ምድር በሁለቱ ምስክሮች ኃይል ተደንቋል፣ ራዕ. 11፡13 ላይ፤ አሁንም የእነርሱ አለመታመን ይታያል፣ አውሬውን በማምለካቸው።

**13፡4 “ለዘንዶውም ሰገዱለት… ለአውሬውም ሰገዱለት”** የክፉ ሐሳብ የፖለቲካ ሥልጣን ብቻ አይደለም፣ ግን ሃይማኖታዊ አምልኮትንም እንጂ (ዝከ. ቁ. 8)። ሰይጣን አምልኮ ይሻል (ዝከ. 13:12; 14:9,11; 16:2; 19:20; ማቴ. 4:8-9)። እንደ አምላክ መሆን ይሻል (ኢሳ. 14:12-15)። ያለ ምንም ጥርጥር ይህ የሚዛመደው ከእባቡ መዋሸት ጋር ነው ዘፍ. 3፡5 እና ማቴ. 4፡9፤ ሉቃስ 4፡5-7።

▣ **“አውሬውን ማን ይመስለዋል፥”** የዚህ ሐረግ ሦስት ታሳቢ መገኛዎች አሉ። አንዳንዶች የሚመለከቱት እንደ

1. የያህዌን መጠሪያ በማስመሰል ነው፣ ዘጸ. 15:11; መዝ. 35:10; 113:4
2. ያህዌን በማስመሰል ነው ኢሳ. 40:18-22;43:11; 44:6,8,9-20 45:6
3. የሌዋታንና የብሔሞት ጠቃሽ፣ በአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ(አንድ ምሳሌ ከብኪ ኢዮብ41፣በተለይም ቁ.33-34)

**13፡5** ቁጥር 5-7 እና 14-15 በርካታ ተገብሮ ግሦች አሉ፣ እነርሱም ፈቃድ የተሰጠው በሰይጣን እንደሆነ የሚያመለክቱ፣ ባጠቃላይም በእግዚአብሔር (ዝከ. ኢዮብ)። እግዚአብሔር ሰይጣንን ለገዛ ራሱ ዓላማ ይጠቀምበታል! ክፉው የገዛ ራሱን ሐሳብ በራሱ ቃላትና ድርጊት ይገልጣል።

▣ **“የትዕቢት ቃልን የሚናገር አፍ”** ይህ ጠቃሽነቱ፡

1. “አውሬው” ዳን. 7:8,11,20,25; 11:36
2. አንቲከስ IV ኢፒፋነስ ዳን. 8; I መቃብ. 1:24
3. “የኃጢአት ሰው” II ተሰ. 2:4
4. የጥፋት ርኩሰት ማቴ. 24:15, እሱም የኢየሩሳሌምን ወረራና ውድመት የሚጠቅስ ነው፣ በሮሜ ጀነራል፣ ኋላም ንጉሥ በሆነ፣ ቲቶ 70 ዓ.ም

ይህ መልካም ምሳሌ ነው፣ የእነዚህ ተምሳሌቶች ታሪካዊ ትኩረት ለመቀየሩ። ዳንኤል 8 ላይ የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን መደምሰስ ነው፣ በ70 ዓ.ም እና በዳንኤል 7 (እና እንዲሁም 11፡36-39) እሱ የሚያመለክተው የመጨረሻውን ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ ድርጊት ነው።

▣ **“በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ”** ይህ የዳን. 7፡25 ቀጥተኛ ጠቃሽ ነው። እሱም በቅድሚያ የተጠቀሰው 11፡2-3 ላይ ነው። እሱም የስደቱን ዘመን የሚያመላክት ዘይቤ ነው። ልዩ ርዕስ 11፡2 እና 12፡6 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**13፡6 “ሊሳደብም አፉን ከፈተ”** እዚህ ቁጥር ላይ ሁለት ወይም ሦስትዮሽ ስድብ በእግዚአብሔር ስም፣ በእግዚአብሔር መቅደስ፣ እና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ አለ። እሱን የሚወስነውም አንዱ ይህን የግሪክ ሐረግ እንዴት እንደሚተረጉመው ነው።

### ራዕይ፡ 13፡7-10

**7ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፥ በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው። 8ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል። 9ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ። 10ይማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል፤ በሰይፍ የሚገድል ማንም ቢኖር ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል። የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት በዚህ ነው።**

**13፡7 "ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፥"** ይህ የድርጊት ተገብሮ አመላካች እና የድርጊት የአሁን ያልተወሰነ ነው። የተገብሮ ድምጸቱ አንድምታ፣ እግዚአብሔር ይህ እንዲመጣ መፍቀዱ ነው። ከዚህ ጀርባ ያለውን ሁሉ አንረዳውም፣ ነገር ግን ከራዕይ መጽሐፍ ግልጽ እንደሆነው፣ እግዚአብሔርታሪክን ሁሉ እንደሚቆጣጠር ነው። ይህ በእርሱ ቅዱሳን ላይ የሚሆን ጦርነት ዳን. 7፡21፤25 ላይ ተጠቅሷል። እሱም የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ አካላዊ ሞት ነው። ጠላት ድል እንዳደረገ የሚመስበት ጊዜ አለ (እንደ ቀራንዮ)፣ ነገር ግን ራዕይና ዳንኤል የሚያስተምሩት ይህ ድል ለአጭር ጊዜ መሆኑን ነው! የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚጠበቁ ተገንዘብ፣ ግን ከአውሬው እና ከእርሱ ተከታዮች ቁጣ ሳይሆን። አምላክ፣ ክፉው አጠቃላይ ድል እንዲያገኝ ይፈቅዳል፣ እውነተኛ ሐሳቡንና ተፈጥሮውን ለመግለጽ።

▣ **"ቅዱሳን"** ልዩ ርዕስ 5፡8 ላይ ተመልከት።

▣ **"በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው።"** ይህ ሐረግ የሚያመለክተው (1) ራዕይ መተርጎም ያለበት ሰፋ ባለ መልኩ ነው፣ ከሮማ ኢምፓየር ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህ ሁለንተናዊ፣ አጠቃላይ ሐረግ የተነሣ ወይም (2) ይህ የሚያመለክተው ሰፊ ኢምፓየሩን ያካተተ ሁነት ነው።

**13፡8 "በምድር የሚኖሩ ሁሉ"** ይህ ተደጋጋሚ ሐረግ ነው፣ ራዕይ ላይ፣ ኢ-አማኒዎችን የሚያመለክት (ዝኪ. 3:10; 6:10; 8:13; 11:10; 13:8,12,14; 17:8)።

▣ **"ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ"** ከሰዋሰው አኳያ ርግጠኛ አይደለም፣ ይህ ሐረግ "ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ" ሊወሰድ የሚችለው (1) "ስማችን ተጽፏል" (ዝኪ. የተመት፣ አየተመት፣ አእት፣ አኢ.መቅ እና 17፡8፤ ኤፌ. 1፡4) ወይም (2) "በታረደው በግ" (ዝኪ. ኪጀት፣ አኪጀት እና 1 ጴጥ. 1፡19-20)። የዚህ ጽሑፍ እና የ17፡8 የቃል ቅደም ተከተል የሚያመለክተው ሐረጉ ምናልባት የሚገልጸው የአማኞች ስሞች በሕይወት መጽሐፍ ከፍጥረት በፊት መጻፉን ነው!

"ከምድር ፍጥረት ጀምሮ" የሚለው ሐረግ በርካታ ጊዜ በአኪ ጥቅም ላይ ውሏል (ማቴ. 25:34; ዮሐንስ 17:24; ኤፌ. 1:4; 1 ጴጥ. 1:19-20)። ደግሞም እጅግ ተመሳሳይ ሐረግ ማቴ. 13:35; ሉቃስ 11:50; ዕብ. 4:3; 9:26 እና ራዕ. 17:8። የእነዚህ ሐረጎች ድብልቅ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር የመቤዠት ድርጊት ከዓለም ፍጥረት በፊት ነው። አማኞች በክርስቶስ ተጠብቀዋል (ዝኪ. 7:4; 11:1; 13:8)። ክፉው በሉዓላዊው አምላክ ውስን ተደርጓል (በዚህ ምዕራፍ ያሉት ተገብሮ ግሦች ቁጥርና የጊዜ ውስንነት)። እሱም በአጭር ጊዜ እይታ መጥፎ ይመስላል፣ ነገር ግን ትልቁን ስዕል ተመልከት!

▣ **"የሕይወት መጽሐፍ"** ከዳን.7፡10 እና ራዕ. 20፡11-15 የምንረዳው ሁለት ዘይቤአዊ መጻሕፍት መኖራቸውን ነው፣ ከሰው ልጅ መዳረሻ ጋር በተያያዘ የተጠቀሱ፡

1. የሕይወት መጽሐፍ፣ እሱም በግላቸው እግዚአብሔርን ያወቁትን ስሞች የያዘ (ብኪ) እናም ክርስቶስን የተቀበሉት (አኪ) [ዘጸ. 32:32-33; መዝ. 69:28; ዳን. 12:1; ኢሳ. 4:3; 34:16; ሉቃስ 10:20; ፊሊ. 4:3; ዕብ. 12:23; ራዕ. 13:8; 17:8; 20:15; 21:27]
2. የሰው ልጅ ድርጊቶች መጽሐፍ፣ እሱም የሰዎችን ድርጊት የመዘገበ፣ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ (መዝ. 56:8; 139:16; ኢሳ. 65:6; ሚል. 3:16)

እነዚህ ዘይቤ መሆናቸው ግልጽ ነው፣ ነገር ግን በርግጠኝነት የማይገልጹት፣ እግዚአብሔር የእሱ የሆኑትን ማወቁንና እሱን ያልተቀበሉትን በተጠያቂነት ለመያዝ ነው (ገላ. 6፡7)።

▣ **"የታረደው"** 5፡12 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**13፡9 "ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ በዚህ መልእክት ላይ፣ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት (ዝኪ. 2:7,17; 3:6,13,22)። እሱ እንደ ሌሎቹ ሐረጎች፣ ቁ. 9-10 ላይ እንዳሉት፣ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፣ እሱም ከደራሲው ጽሑፋዊ ዓላማ አኳያ ትክክል ነው ተብሎ የሚገመት። እነዚህ ሐረጎች ከቤተ ክርስቲያናቱ ጋር የሚዛመዱበት ሐቅ የሚያመለክት የሚመስለው ቀጣዩ ሐረግ (ቁ. 10) ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማመልከቱን ነው።

**13፡10** ይህ ቁጥር የኤር. 15:2 ወይም 43:11, ጠቃሽ ይሆናል፣ እሱም ስለ እግዚአብሔር ፍርድ የሚናገር። በርካታ ልዩ ልዩ የግሪክ ጽሑፎች "መግደል" ከሚለው ግስ ጋር ይያያዛሉ። ይህ የዚህን ግስ የተለየ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች መያዝ ምክንያት ሆኗል።

1. ኪጀት እና አኪጀት እነዚህን ሁለቱንም ሐረጎች ከእግዚአብሔር ሕዝብ ስደት ጋር ያያይዟቸዋል።
2. የተመት እና አየተመት የመጀመሪያውን ሐረግ ከተሳዳጆች ክርስቲያኖች ጋር አያይዞ ሁለተኛውን ሐረግ ከእግዚአብሔር ተቃዋሚ አሳዳጆች ጋር ያያይዘዋል።
3. ሦስተኛው ታሳቢ ትርጓሜ (አእት እና አኢ.መቅ) ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ተሳዳጅ ክርስቲያኖችን ነው።

በትርጉም እጅግ ብዙ ልዩነት መኖሩን የሚያሳየው ሐቅ ርግጠኝነት አለመኖሩን ነው። እሱ በርግጥ መንፈሳዊ እውነት ነው፣ እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚቆጣጠር። ብቸኛው ጥያቄ ሐረጉ ለማን እንደተመለከተ ነው።

1. ክርስቲያኖችን ለማበረታታት፣ ታማኝ ሆነው እንዲገኙ (ማቴ. 26:52; ፊሊ. 1:28)

2. ለአሳዳጆች፣ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ስለ ምርጫቸውና ድርጊታቸው ምላሽ እንደሚሰጡ ሊያረጋግጥላቸው?

▣

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ*** | ***"የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት በዚህ ነው"*** |
| ***አኪጀት*** | ***"የቅዱሳን ትዕግሥና እምነት በዚህ ነው"*** |
| ***አየተመቅ*** | ***"የቅዱሳን መጠራት ትዕግሥት እና እምነት በዚህ ነው"*** |
| ***አእት*** | ***"የእግዚአብሔር ሕዝብ መጠራት ትዕግሥትና እምነት በዚህ ነው"*** |
| ***አኢመቅ*** | ***"ቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት የሚኖራቸው በዚህ ነው"*** |

ቁጥር 9 እና የቍጥር 10 መጨረሻ የሚያሳየው ይህ ሐረግ የግድ ማመልከት የሚኖርበት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው (ማቴ. 26፡52)። ይኸው ቁጥር ደግሞ የሚገልጸው እውነተኛ አማኞችን ነው (ዝኪ. 14:12; 12:11,17)። እስከመጨረሻው ድረስ ጠንክረው እንዲይዙ ይበረታታሉ (ዝኪ. 2:3,7,11,17,26; 3:5,12,21; 21፡7)። ትዕግሥት የእውነተኛ መዳን ማስረጃ ነው (1 ዮሐንስ 2፡19)። 2፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና ልዩ ርዕስ ተመልከት።

**ራዕይ፡ 13፡11-18**

**[11]ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር። [12]በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል። ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰለት ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል። [13]እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል። [14]በአውሬውም ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያስታል፤ የሰይፍም ቍስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል። [15]የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው። [16]ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፥ [17]የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቍጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ። [18]አእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ይቍጠረው፤ ቍጥሩ የሰው ቍጥር ነውና፥ ቍጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው።**

**13፡11 "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥"** ይህ የዳን. 7፡17 ጠቃሽ ነው። ብዙዎች የሚገምቱት እነዚህ ሁለት አውሬዎች የሁለቱ የእግዚአብሔር ምስክሮች ማስመሰያዎች ናቸው፣ 11:13-14 ላይ፣ ሌሎች ደግሞ የሚገምቱት ዘንዶውና ሁለቱ አውሬዎች የሥላሴ ማስመሰያ ናቸው።

ከባሕር የወጣው አውሬ የሌዋታን ጠቃሽ እንደሆነ (ኢዮብ 41፡1-34) የጥንቱ የውኃ ላይ ቀውስ ዋነኛ አለቃ፣ እንዲሁ ከመሬት የወጣው አውሬ የብሄሞት ጠቃሽ ነው (ኢዮብ 40፡15-24)፣ ተጓዳኝ የምድር አውሬ (ይህ በምንም መንገድ ዳይኖሰረስን አያመለክትም፣ ግን የጥንቱን የምስራቅ አፈ-ታሪክ እንጂ)።

እነዚህ አውሬዎች የክፉ (ቀውስ) ተምሳሌቶች ናቸው፣ እናም እግዚአብሔር በፈጠረው ሥርዓት ላይ ዐምጸዋል (መዝ. 74፡12-14; ኢዮብ. 3:8; ኢሳ. 51፡9-11; አሞጽ 9፡3)። አንዳንድ ጊዜ ሌዋታን፣ *ረዓብ* ተብሎ ይጠራል ("ጠማማው" ማለትም፣ እባቡ፣ ኢሳ. 51፡ 9)። በሌሎች ቦታዎች ረዓብ የግብፅ ስም ነው (ዐባይ፣ ማለትም ጠማማው ወንዝ፣ መዝ. 87፡4፤ ኢሳ. 30፡7 እና እንዲሁም ሕዝቅኤል 32፣ በተለይም ቁ. 2-3)።

▣ **"የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር።"** የበጉ መጠቀስ ግልጽ የሆነው የክርስቶስ ኩረጃ ነው (ዝኪ. 5፡6)። ድምጹ እና/ወይም መልእክቱ እውነተኛ ባሕርዩን ይገልጻል። ኋላ ላይ ራዕይ ላይ ሁለተኛው አውሬ አዘውትሮ ተሚጠቀሰው እንደ ሐሰተኛው ነቢይ ነው (ዝኪ. 16:13; 19:20; 20:10)። ለራሱ ክብርን አይፈልግም፣ ነገር ግን ዓለምን ይመለምላል፣ ለአውሬው እንዲሰግዱ (ዝኪ. ቁ. 12)። ይህም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ማስመሰል ነው (ዮሐንስ 14-16) ክርስቶስን በማስተዋወቅ። ስለዚህ ያልተቀደሰ ሦስትነት (ሥላሴ) አለን፡

1. ሰይጣን እንደ እግዚአብሔር አብ መሳይነት
2. የባሕሩ አውሬ እንደ አግዚአብሔር ወልድ መሳይነት
3. የምድሩ አውሬ አንደ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሳይነት

**13፡13 "*ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል።*"** ይህ የአሁን ጊዜ ግሥ ነው፣ ፍችውም ድንቆችን ማድረጉን ይቀጥላል። እሱም የሚጠበቀው፣ የፍጻሜ ዘመን ሐሰተኛ መምህራን ተአምራት መሥራት አንደሚችሉና የተመረጡትን አንኳ አንደሚያስቱ ሲሆን፣ *ያ የሚቻል ከሆነ* (ማቴ. 24:24; ማርቆስ 13:22; II ተሰ. 2:9-11; Didache 16:3,4)። ተአምራት የእግዚአብሔር የወዲያውኑ ምልክቶች አይደሉም (ዘጸ. 7:8-13)። ይህም የክርስቶስ አገልግሎትን ሌለኛው ማስመሰል ነው።

▣ **"እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ"** ይህ ከኤልያስ ጋር ተመሳሳይ ነው 1 ነገሥ. 18፡38፣ እሱም የሁለቱ ምስክሮች ገለጻ ምንጭ ሊሆን የሚችል፣ 11፡5 ላይ የሚገኘው። የሚያመለክተውም እንደ እግዚአብሔር ፍርድ የወደቀውን እሳት ለማመልከት ነው ሕዝ. 38፡22 ወይም 39፡6። ይህም ሌለኛው ማስመሰል ነው

1. የሁለቱን ምስክሮች
2. የእግዚአብሔርን የብኪ ድርጊቶች
3. የሐዋ. 2 ጰንጠቆስጤ

**13፡14 "የሰይፍም ቍስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው"** "ቍስል" የሚለው ቃል (*plēge,* ዝከ. 13:3,12,14) ዘወትር የሚተረጎመው "መቅሠፍት" በሚል ነው፣ ራዕይ ላይ (ዝከ. 9:18,20; 11:6; 15:1,6,8; 16:9,21; 18:4,8; 21:9; 22:18)። አየተመት የግርጌ ማስታወሻ የያዘው

1. ለቁ. 3 "ለሞቱ የሆነውም ቍስል"
2. ለቁ. 12 "ለሞቱ የሆነው ቍስል"
3. ለቁ. 14 "የደረሰበት የሰይፍ ቍስል"

የእነዚህ ትርጉሞች ሥነ-መለኮታዊ ሐሳብ የክርስቶስ ተቃዋሚ ሰው አለመሆኑን ነው፣ ነገር ግን የዓለም ሥርዓት እንጂ። ቃሉ በዘይቤነት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። "ያልታሰበ ምት" ወይም መቅሠፍት (BAGD, ገጽ. 674), ነገር ግን የእሱ መሠረታዊ ፍቺ ምት ወይም ቁስል ነው።

ተጓዳኙ ሐረግ "ወደ ሕይወት ተመለሰ" የሚያሳየው "መቅሠፍት" የተሻለ ትርጉም አለመሆኑን ነው፣ ለእነዚህ ቁጥሮች፣ ከአውሬው ጋር በተያያዘ። የፍጻሜው ዘመን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የክርስቶስ ተቃዋሚ ሐሳብ፣ ሕዝቦችን ለዓመጽ የሚመራው ተተንብዮአል፣ በብኪ ሕዝቅኤል 38-39፣ ዘካርያስ 14; ዳንኤል 7:21-27; 9:24-27; 11:36-39 እና በበይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ፣ የሲቢሊን ንግርቶች፣ መጽሐፍ III; IV ኢስድራስ 5.4,6 እና የባሮክ አፖካሊፕስ XL, እና በአኪ፣ II ተሰ. 2:3,8-9።

**13፡15 "ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው።"** ሌላ ስፍራ ይህ ከምድር የወጣው አውሬ ሐሰተኛው ነቢይ ተብሎ ይጠራል (ዝከ. 16:13; 19:20; 20:10)። ይህ ምናልባት ሕይወት የመስጠት ዘይቤ ሊሆን ይችላል (ማለትም፣ በዕብራይስጥ *ruah* (ሩሕ) = ትንፋሽ) ለንቅናቄ (ሕዝቅኤል 37)።

**13፡16 "በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፥"** ቅዱሳን በእግዚአብሔር ማኅተም እንደተደረገባቸው 7:3 (ዝከ. 13:16; 14:9), እዚህ ክፉው የእግዚአብሔርን ድርጊት በመኮረጅ የገዛ ራሱን ምልክት ያደርጋል። የግሪኩ ቃል የሚያመለክተው የእንስሳ ምልክት ወይም የታተመ የመንግሥት ሰነድን ነው። ከምልክቱ ስፍራ የተነሣ፣ አንዳንዶች የሚያስቡት፣ እሱ የነበረው

1. የአይሁድ ምልክት (ክታብ) (ዘዳ. 6፡8)
2. ከአንደኛው ክፍለ-ዘመን የሮሜ ባህል ጋር የሚያያዝ፣ ባሮች የአሳዳሪዎቻቸው ስም ምልክት ይደረግባቸው የነበረው
3. ወታደሮች ለጀነራላቸው ክብር የሚነቀሱበት

**13፡17** የአውሬው ምልክት የሚያያዘው ምግብ ከመግዛት፣ እና እንዲሁም ሥራ ከመቀጠር ጋር ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከዚህ ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ አይጠበቁም።

**13፡17-18 "የስሙ ቁጥር"** ጥንታዊ ቋንቋዎች የፊደሎቻቸውን ሆሄያት ለቁጥር አገልግሎትም ይጠቀሙባቸው ነበር። እንደ ዕብራይስጡ አናባቢ ለኢየሱስ ስም 888 ይጨምራሉ (የሲቢሊ ንግርቶች፣ 1324)፣ ስለዚህ የአውሬው ስም፣ የፍጻሜው ዘመን የሰይጣን ሥጋ መልበስ፣ 666 ይጨመርበታል። ስድስት ከፍጹሙ ቁጥር ከ7 በአንድ ያነሰ ነው (ዘፍ. 1፡1-2፡3፣ ሰባቱ የፍጥረት ቀናት)፤ ሦስት ጊዜ ሲደጋገም የዕብራይስጥ የላቀ ማወዳደሪያ ይፈጥራል (ኢሳ. 6:3; Jer. 7:4)።

ደግሞም ማለት የሚቻለው ስድስት የሰው ቁጥር እንደመሆኑ ሁሉ የሚያመለክተው የያንዳንዱን አካል ሰውኛ መሆን ነው፣ ቅዱስ ያልሆነውን ሦስትነት (ሥላሴ) — ዘንዶው (ሰይጣን)፣ የባሕሩ አውሬ (የክርስቶስ ተቃዋሚ) እና የምድሩ አውሬ (ሐሰተኛው ነቢይ)። ለእኔ የሚመስለኝ የመጀመሪያው አውሬ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ሰውኛ ነው፣ ሁለተኛው አውሬ ደግሞ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ሃይማኖታዊ ሥርዓተ ሰውኛ ነው። ከዚያም ወደ ታላቋ ጋለሞታ ምዕራፍ 17 እንንቀሳቀሳለን፤ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓት ማሳያ፣ ከዳንኤል 7። እሱም ጥንታዊ ባቢሎን፣ የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ሮም ቢሆን፣ ወይም የፍጻሜ ዘመን ድብልቅ የዓለም መንግሥት፣ የሚያመለክተው የሰው ታሪክ ወደ አጠቃላይ ግጭት ማምራቱን ነው፣ "በዚህ ዓለም አምላክ" (2 ቆሮ. 4፡4) መካከል እና በእርሱ ተከታዮች በተቃርኖ ከፍጥረት አምላክና ከእርሱም መሲሕ (መዝሙር 2)።

**13፡18 "ቁጥሩም ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ነው"** ይህ ቁጥር ማንን እንደሚጠቅስ መግባባት ላይ አልተደረሰም። ብዛት ያላቸው መላምቶች ተሰንዝረዋል፣ ነገር ግን አንዳቸውም ማጠቃለያ አልሆኑም። በእኔ አስተያየት ሦስት ምርጥ ንድፈ-ሐሳቦች እነሆ።

1. የጽሑፍ ልዩነት ከ666 እና 616 መካከል ከመኖሩ የተነሣ፣ ቄሳር ኔሮን መጠቀም ይቻላል። የግሪኩ ፊደላት የተተረጎመበት ወደ ዕብራይስ አቻ 666 ሲሆን የግሪኩ ፊደላት ወደ ላቲን አቻ የተተረጎሙት 616 ነው።
2. ሦስትዮሹ ድግግሞሽ የዕብራይስጡን ልዕለ ማወዳደሪያ ስለሚቆጥር፣ 666 እጅግ ክፉ ሰው ሊሆን ይችላል።
3. ዐውደ-ጽሑፉ ሥላሴን ማስመሰል በመጥቀሱ ምክንያት፣ ሦስቱ መለኮታዊ አካላት የተንጸባረቁት በ777 ነው፣ ሦስቱ ተጻራሪዎች በ666 እንደተጠቀሱ ሁሉ።

***ዐውደ ጽሑፋዊ ይዘት ራዕይ*** **14፡1-20**

ሀ. ማለት የሚቻለው ምዕራፍ 14 የምዕራፍ 12 እና 13 የክፉው የተጠናከረ ኃይል አቅራቦት ምላሽ መሆኑን ነው። ርግጠኛ ነኝ፣ አንባቢዎች እንደሚደነቁ፣ በቅዱሳን ላይ ምን እንደሚደርስባቸው፣ በፍጻሜው ዘመን አስከፊ ስደት ጊዜ።

ለ. አንዳንዶች ሌላ ጽሑፋዊ መዋቅር ተመልክተዋል ለ "ሰባት"፣ ቁ. 6-20። የሰባት መላእክት ተለጣጣቂነት አለ፣ ነገር ግን ይህ መዋቅር ከሥነ-መለኮት አኳያ ጠቃሚ አይመስልም"

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

***ራዕይ፡ 14፡1-5***

**[1]አየሁም፥ እነሆም፥ በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፥ ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም በግምባራቸው የተጻፈላቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ። [2]እንደ ብዙ ውኃም ድምፅና እንደ ታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፥ ደርዳሪዎችም በገና እንደሚደረድሩ ያለ ድምፅ ሰማሁ። [3]በዙፋኑም ፊት በአራቱም እንስሶችና በሽማግሌዎቹ ፊት አዲስ ቅኔ ዘመሩ፤ ከምድርም ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራት ሺህ በቀር ያን ቅኔ ሊማር ለማንም አልተቻለውም። [4]ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው፥ ድንግሎች ናቸውና። በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው። ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኵራት እንዲሆኑ ከሰዎች የተዋጁ እነዚህ ናቸው። [5]በአፋቸውም ውሸት አልተገኘም፤ ነውር የለባቸውም።**

**14፡1 "በጉ"** ይህ መሲሕ ጠቃሽ ነው (ዝኪ. 5:6,8,12-13; 13:8; ኢሳ. 53:7; ዮሐንስ 1:29,36; I ጴጥ. 1:18-19)።

▣ **"በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፥"** በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች ይህንን ሐረግ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውለዋል።

1. እሱ የሚወክለው የሞሪያ ተራራን እና የኢየሩሳሌምን የመቅደስ ስፍራ ነው (ኢሳ. 24:23; ኢዩኤል 2:32)
2. እሱ የሚወክለው ሰማያዊቷን ኢየሩሳሌም ነው (ዕብ. 11:10,16; 12:22-23; 13:14; ገላ. 4:26)
3. እሱ አፖካሊፕቲካዊ ተምሳሌት ነው፣ ካኖናዊ ካልሆኑ መጻሕፍት ላይ የሚገኝ II ኢስድራስ 2:42-47; 13:35,39-40
4. እሱ የሚያመለክተው የብኪ ምንባቦችን ነው፣ እነርሱም የፍጻሜ ዘመኑን የእግዚአብሔር ሕዝብ መሰብሰብ የሚናገሩትን (መዝሙር 48; ኢሳ. 24:23; ኢዩኤል 2:32; ሚክያስ 4:1,7; አብድዩ ቁ. 17,21)
5. ዳራው እንደ በርካቶች ሌሎች ምንባቦች በዚህ ክፍል፣ መዝሙር 2፣ በተለይም ቁ. 6 ነው።

አታቾች እነዚህን እያንዳንዳቸውን ራዕዮች እንደሚያያይዟቸው ተገንዘብ፣ አንድም

1. የብኪ ምንባቦች ከሆኑ የፍልስጥኤም ስፍራዎች ጋር
2. በይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ጋር
3. የአንደኛው ክፍለ-ዘመን የግሪክ-ሮማ ታሪክ ጋር

እንደ እኔ እነዚህ የብኪ የራዕይ ነገሮች፣ ምዕራፍ 6 ላይ የሚጀምሩት፣ የሚዘመዱት ከአኪ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር ነው (አማኝ አይሁድ እና አሕዛብ)፣ ቅዱሳን፣ ቤተ-ክርስቲያን። በዚህ ልዩ ጉዳይ ላይ፣ እሱ የሰማያዊው መቅደስ ጠቃሽ ነው (ዕብ. 8:2; 9:11,24)።

▣ **"ከእርሱም ጋር መቶ አርባ አራት ሺህ"** ይህ ተመሳሳይ የሆነ የተዋጁት ወገን ነው፣ 5፡9 ላይ እንዳለው፤ የታተሙት 7፡4-8 (7፡4 ላይ ሙሉ ማስታወሻውን ተመልከት)፤ በበጉ ደም የታጠቡ እነሱ (7፡14-17)። ስለዚህ፣ በእኔ አስተያየት፣ ይህ የሚወክለው ለአኪ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ነው፣ ቅዱሳን፣ ቤተ-ክርስቲያን። ለ144000 ማንነት ሙሉ ማስታወሻ 7፡4 ተመልከት። ቀደም ሲል ከነበሩት ማስታወሻዎች፣ እነሱ ታትመዋል ነገር ግን ይሳደዱ ነበር፣ እዚህ ግን ባለ ድል ናቸው!

▣ **"ስሙና የአባቱ ስም በግምባራቸው የተጻፈላቸው"** ይህ የሚጠቅሰው አንድ ስም ነው ሁለት? እሱ ምናልባት የሚያመለክተው የኢሳ. 9፡6 መጠሪያዎችን ነው፣ እሱም ከሁለቱም ከአብና ከወልድ ጋር የሚዛመድ። እነዚህም የታተሙት እና የእግዚአብሔር የሆኑት ናቸው (ራዕይ 7)። 7፡2 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

**14፡2 "ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፥ እንደ"** እነዚህ ገላጭ ሐረጎች ጥቅም ላይ ውለው የነበሩት ለእግዚአብሔር ድምጽ ሕዝ. 43፡2 ላይ፣ ለኢየሱስ ድምጽ 1፡15 ላይ፣ እና ለሰማያዊ ብዙ ድምጾች 19፡6 ላይ። እሱም ዘወትር የሚገልጸው ተናጋሪው ከሰማይ እንደሆነ ነው (ዝኪ. 4:5; 11:19; 16:8)።

**14፡3 "በዙፋኑም ፊት አዲስ ቅኔ ዘመሩ፤"** ይህ የራዕይ 5፡9 ጠቃሽ ነው። "እነርሱ" የሚያመለክተው (1) መልአካዊ ፍጥረታት እነርሱም 5፡9 ላይ ያለውን መዝሙር የሚዘምሩ ወይም (2) የአንድ መቶ አርባ አራት ሺው መዝሙር፣ ቁ. 3 እና 15፡2 ላይ ካለው የማጠቃለያ ክፍል ጋር። ይህ አዲስ ዝማሬ የኢሳ. 42፡10 ጠቃሽ ነው፣ እንዲሁም መዝ. 33:3; 40:3; 96:1; 98:1; 144:9; 149:1። ቃል የተገባው አዲሱ የመንፈስ ዘመን መጥቷል!

▣ **"ሽማግሌዎች"** 4፡4 ላይ ልዩ ርዕስ ተመልከት።

▣ **"ከምድርም ከተዋጁት"** ይህ የብኪ ጽንሰ-ሐሳብ ነው፣ የቅርብ ዘመድን መዋጀት፣ የተለቀቀ የቤተሰብ አባል (*go'el*, ማለትም፣ ሩትና ቦዔዝ)። እሱም ጥቅም ላይ የሚውለው ክርስቶስ ለሞተላቸው ነው (ዝኪ. 5፡9፡ 7፡14)። ልዩ ርዕስ፡ መዋጀት/መቤዠት 5፡9 ላይ ተመልከት።

**14፡4 "ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው፥"** በርካታ ውይይቶች በዚህ ቁጥር ላይ ተካሂደዋል፣ ምክንያቱም ይህ የተመረጡ፣ ድንግል ወንዶች ሰዎች ስለሚመስሉ፣ ከ14400 ውስጥ፣ ምዕራፍ 7 ላይ። ሆኖም፣ እኔ እንደማስበው እነዚህ ሐረጎች ሊብራሩ የሚችሉት በተምሳሌታዊ ነው፣ ወይም ቢያንስ በብኪ ቃላት፣ እናም በጥሬው ፈጽሞ የሚወሰዱ አይደሉም። "ከሴቶች ጋር ያልረከሱ" የሚለውን ሐረግ በብዙ መንገድ መረዳት ይቻላል።

1. እሱ የሚያመለክተው በጥሬው ስለ ድንግልና ነው
2. እሱ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ግልሙትና ነው፣ ከአውሬው ወይም ከታላቋ ጋለሞታ ጋር (ዝከ. 14:8; 17:2; 18:9)
3. እሱ የሚያመለክተው የተወሰኑ አስተያየቶችን ነው፣ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተደረጉትን (ዝከ. 2:14,20,22; 3:4)
4. እሱ የሚያመለክተው የብኪ የአምልኮ ሥርዓት መንጻትን ነው፣ ለአምልኮ ወይም ለጦርነት (ዘጸ. 19:14-15; ዘዳ. 23:9-10; I ሳሙ. 21:4-5; II ሳሙ. 11:6-13
5. እሱ ጠቃሽ ነው፣ በብኪ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መጠሪያ፣ "ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ" (II ነገሥ. 19:21; ኤር. 18:13; ሰቆ. 2:13; አሞጽ 5:2; II ቆሮ. 11:2; ኤፌ. 5:27)።

አጽንዖት መሰጠት ያለበት፣ ከትዳር ጓደኛ ጋር የሚከናወን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መንፈሳዊ ያልሆነ ተግባር አለመሆኑን ነው። የግብረ-ሥጋ ተራክቦ (ጋብቻ) የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው፣ የእሱ ምድርን የመሙላት መንገድ ነው፣ የእሱ ትዕዛዝ ነው (ዘፍ. 1፡28፤ 9፡ 1)። ድንግልና በርግጥ ለአገልግሎት መንፈሳዊ ስጦታ ነው (1 ቆሮንቶስ 7)፣ ነገር ግን እሱ የቅድስና አቋም አይደለም። የግሪክ ራስን የመካድ ፍልስፍና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም (ቅድመ-ጋብቻም ሆነ ብዙ በማግባት የሚፈጸም ግብረ-ሥጋዊ ግንኙነትም እንዲሁ)!

◘ **"በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው"** ይህ የሚናገረው ስለ ደቀ-መዛሙርትነትና አገልግሎት ነው ዮሐንስ 7፡17፤ 10፡4)።

◘ **"ከሰዎች ለእግዚአብሔር በኵራት እንዲሆኑ"** ይህ ቃል በብኪ ጥቅም ላይ የዋለው፣ እግዚአብሔር የአጠቃላይ መኸሩ ባለቤት መሆኑን ለማሳየት ነው (ዘጸ. 23:19; 34:76)። በአኪ እሱ የሚያመለክተው ቤተ-ክርስቲያንን ነው (ዕብ. 12፡23፤ ያዕቆብ 1፡18)፣ የኢየሱስን ሕዝቦች፣ እነርሱም የትንሣኤው በኩራት የሆኑትን (1 ቆሮ. 15:20,23; ራዕ. 1:5)።

**14፡5 "በአፋቸውም ውሸት አልተገኘም፤"** ለዚህ ዘይቤ በርካታ ታሳቢ መነሻዎች አሉት

1. እሱ የሚዛመደው ከራዕ. 21፡27 እና 22፡15 ተመሳሳይ ሐረግ ጋር ነው
2. እሱ የሚዛመደው ከአጼ አምልኮ ጋር ነው፣ ይኸውም ክርስቲያኖች የአሳዳጆችን ትእዛዝ ፈጽሞ የማያከብሩበት፣ "ቄሳር ጌታ ነው" ለማለት
3. እሱ ተምሳሌታዊ ነው፣ ለአኪ መርከስ (መዝ. 32፡2፤ ሶፎ. 3፡13)
4. እሱ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፣ ለአለማመን ሮሜ 1፡25፤ 1 ዮሐንስ 2፡22 ላይ እንዳለው

◘ **"ነውር የለባቸውም።"** ይህ በጥሬው፣ "ያለ ነውር" ማለት ነው (ፊሊ. 3፡6)። በዋነኛነት እሱ የሚያመለክተው ለመሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳትን ነው፣ ግን በዘይቤነት ለሰዎችም ጥቅም ላይ እየዋለ መጣ (ኖኅ፣ ዘፍ. 6፡9፣17 እና ኢዮብ፣ ኢዮብ 1፡1)። እሱ ለኢየሱስም ጥቅም ላይ ውሏል ዕብ. 9፡14 እና 1 ጴጥ. 1፡19። ይህም ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት መጥቀሻ ሌለኛው መንገድ ነው። ክርስቶስን መምሰል የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፣ ለሕዝቦቹ (ሌዋ. 19:2; ዘዳ. 18:13; ማቴ. 5:48; I ጴጥ. 1:16)።

## ልዩ ርዕስ፡ ነውር የሌለበት፣ ንጹሕ፣ ኃጢአት የሌለበት፣ ያለ ነቀፋ

*ሀ. የመክፈቻ መግለጫዎች*

1. ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ከሥነ-መለኮት አኳያ የሚገልጸው የሰው ልጅን መነሻ አቋም ነው (ማለትም፣ ዘፍጥረት 1፣ የዔድን ገነት)
2. ኃጢአትና ዐመጻ ይህን የመሰለውን ፍጹም ኅብረት አጠፉት (ማለትም፣ ዘፍጥረት 3)።
3. ሰዎች (ወንድ እና ሴት) ከእግዚአብሔር ጋር የሆነው ኅብረት እንዲመለስ ይናፍቃሉ፣ በእርሱ መልክና አምሳል ስለተፈጠሩ (ማለትም፣ ዘፍ. 1፡26-27)።
4. እግዚአብሔር ከኃጢአተኛ ሰው ጋር በብዙ መንገዶች ሊሠራ ይሻል
   ሀ. መልካም መሪዎች (ማለትም፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኢሳይያስ)
   ለ. መሥዋዕታዊ ሥርዓት (ማለትም፣ ሌዋውያን 1-7)
   ሐ. መልካም ምሳሌዎች (ማለትም፣ ኖኅ፣ ኢዮብ)
5. በመጨረሻም እግዚአብሔር መሲሑን ሰጠ
   ሀ. የራሱ ሙሉ መገለጫ
   ለ. ለኃጢአት ፍጹም መሥዋዕት
6. ክርስቲያኖች ያለ ነውር ሆነዋል
   ሀ. በሕጋዊነት በክርስቶስ በተደረገ ጽድቅ
   ለ. እየቀጠለ በሚሄደው በመንፈስ ሥራ በኩል
   ሐ. የክርስትና ግብ ክርስቶስን መምሰል ነው (ሮሜ. 8:28-29; ኤፌ. 1:4)፣ እርሱም በርግጥ የእግዚአብሔር አምሳል መመለስ ነው፣ በአዳም እና ሔዋን መውደቅ ሳቢያ ጠፍቶ የነበረ።

7. *መንግሥተ-ሰማይ* በዔድን ገነት የነበረው ፍጹም ወዳጅነት መመለስ ነው። *መንግሥተ ሰማይ* ከእግዚአብሔር መገኛ የምትወጣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ማለት ነው (*ራዕ.* 21፡2) ወደ ጠራችው ምድር (2 ጴጥ. 3፡10)። *መጽሐፍ ቅዱስ* የሚጀምረውና የሚጨርሰው በተመሳሳይ ጭብጦች ነው።
*ሀ.* የቅርብ፣ ግላዊ ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር
ለ. በገነት *መቼት* (ዘፍጥረት 1-2 እና *ራዕይ* 21-22)
ሐ. በትንቢታዊ *መግለጫ*፣ የእንስሳት *መኖርና* ጓደኝነት (ኢሳ. 11፡6-9

ለ. ብሉይ ኪዳን

1. በርካታ የተለያዩ የዕብራይስጥ ቃላት አሉ፣ የፍጽምናን፣ ያለ ነውር *መሆንን*፣ የንጽሕናን ጽንሰ-ሐሳብ የሚይዙ፣ ይህንንም ውስብስብ ዝምድና ለመሰየም እና ለማሳየት እጅግ አስቸጋሪ ነው።
2. የፍጽምናን፣ የኃጢአት የለሽነትን፣ ወይም የንጽሕናን ጽንሰ-ሐሳብ የሚይዙ ዋነኛ ቃላት (እንደ ሮበርት ቢ. *ግሪድልስቶን*፣ *የብሉይ ኪዳን ተመሳስሎ*፣ ገጽ 94-99) የሚሆኑት፡
*ሀ. shalom* (BDB1022)
*ለ. thamam* (BDB1070)
*ሐ. calah* (BDB478)
3. ሴፕቱዋጂንት (ማለትም፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን *መጽሐፍ ቅዱስ*) እነዚህን አብዛኞቹን ጽንሰ-ሐሳቦች የሚተረጉማቸው ወደ ቆኔ ግሪክ ቃላት ነው፣ በአኪ ጥቅም ላይ የዋሉትን።
4. ቁልፍ ጽንሰ-ሐሳቡ የተያያዘው ከ*መሥዋዕታዊ ሥርዓት* ጋር ነው።
*ሀ. amōmos* (ዘጸ. 29:1; ሌዋ. 1:3,10; 3:1,6; ዘኁ. 6:14)
*ለ. amiantos* እና *aspilus* ደግሞ የባዕድ አምልኮ ፍች አላቸው

ሐ. አዲስ ኪዳን

1. ሕጋዊ ጽንሰ-ሐሳብ
*ሀ.* የዕብራይስጥ ሕጋዊ ባዕድ አምልኳዊ ፍች የተተረጎመው በ *amōmos* (ኤፌ. 5:27; ፊሊ. 2:15; I ጴጥ. 1:19)
ለ. የግሪክ ሕጋዊ ፍች (1 ቆሮ. 1:8; ቆላ. 1:22)
2. ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት፣ ነውር የሌለበት፣ ንጹሕ ነው (*amōmos*, ዕብ. 9:14; I ጴጥ. 1:19)
3. የክርስቶስ ተከታዮች የግድ እሱን *መምሰል* ይኖርባቸዋል (*amōmos*, ኤፌ. 1:4; 5:27; ፊሊ. 2:15; ቆላ. 1:22; II ጴጥ. 3:14; ይሁዳ ቁ. 24; *ራዕ.* 14:5)
4. ይህ ጽንሰ ሐሳብ ለቤተ ክርስቲያን *መሪዎችም* ጥቅም ላይ ውሏል
*ሀ. anegkl tos*, "የማይከሰስ" (1 ጢሞ. 3:10; ቲቶ 1:6-7)
*ለ. anepilemptos*, "የማይወቀስ" ወይም "ነቀፌታ የሌለበት" (1 ጢሞ. 3:2; 5:7; 6:14; ቲቶ 2:8)
5. "ነውር የሌለበት" የሚለው ጽንሰ ሐሳብ (*amiantos*) ጥቅም ላይ የዋለው
*ሀ.* ለክርስቶስ ለራሱ (ዕብ. 7:26)
ለ. ለክርስቲያን ወራሾች (1 ጴጥ. 1:4)
6. የ "ፍጽምና" ወይም "ትክክለኝነት" ጽንሰ-ሐሳብ (*holoklēria*) (ሐዋ. 3:16; I ተሰ. 5:23; ያዕቆብ 1:4)
7. "ስሕተት የሌለበት" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ "ኃጢአት የሌለበት፣ ንጽሕና በ*amemptos* ታውቋል (ሉቃስ 1:6; ፊሊ. 2:15; 3:6; I ተሰ. 2:10; 3:13; 5:23)
8. "ነውር የማይገኝበት" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ በ*amōmētos* (II ጴጥ. 3:14)
9. "ነውር የሌለበት፣" "የማይነቀፍ" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ፣ ከላይ ከተጠቀሱት ቃላት አንዱን በያዙት ምንባቦች ዘወትር ጥቅም ላይ (1 ጢሞ. 6:14; ያዕቆብ 1:27; I ጴጥ. 1:19; II ጴጥ. 3:14)

መ. ይህን ጽንሰ-ሐሳብ ለማስረዳት ጥቅም ላይ የዋሉት ቃላት ቁጥር ጠቃሚነቱን ያሳያሉ። እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን በክርስቶስ በኩል ሰጥቶናል፣ አሁን ደግሞ እሱን እንድንመስል ጥሪ ያቀርባል።

አማኞች ከአቋም አኳያ፣ በማስረጃ "ትክክል፣" "ልክ፣" "ያለ ነውር" እንደሆኑ ታውጇል፣ በክርስቶስ *ሥራ*። እንግዲህ አማኞች ስፍራቸውን *መያዝ* ይጠበቅባቸዋል። "በብርሃን ተመላለሱ፣ እሱ በብርሃን እንደሆነ" (1 ዮሐንስ 1፡7)። "በተጠራችሁበት እንደሚገባ ተመላለሱ" (ኤፌ. 4:1,17; 5:2,15)። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን *መልክ መልሶታል*። የቅርብ ወዳጅነት አሁን ይቻላል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የእሱን ባሕርይ የሚያንጸባርቅ ሕዝብ እንደሚፈልግ አስታውሱ፣ ልጁ እንዳደረገው ሁሉ። ከቅድስና ላነሰ ነገር አልተጠራንም (ማቴ. 5:20,48; ኤፌ. 1:4; 1 ጴጥ. 1:13-16)። የእግዚአብሔር ቅድስና ከሕጋዊ ብቻ አይደለም፣ ግን ደግሞ ከሕላዌም ነው!

***ራዕይ*: 14፡6-7**

**[6]በምድርም ለሚኖሩ ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ [7]በታላቅ ድምፅም። የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት፤ ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው ስገዱለት አለ።**

**14፡6 "ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ"** 8፡13 ላይ አንድ ንስር በሰማይ ሲበር ታይቷል፣ እሱም አንዳች የሚታይን ነገር ለምድር ሊያውጅ እንዳለው።

▣ **"በምድርም ለሚኖሩ ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው"** ይህ ሐረግ፣ "የዘላለም ወንጌል" እዚህ ብቻ ነው የሚገኘው። ጠቃሚ የሚሆነው "ወንጌሉ" እዚህ በምድር ላሉት (ለሚኖሩት) መሆኑ ነው፣ ይህም ዘወትር በራዕይ ጥቅም ላይ የዋለው ለማያምኑት ነው። አንዳንዶች ይህን የሚመለከቱት እንደ ማቴዎስ 28:18-20 መፈጸም ነው፣ ወይም እጅግ በተለየ መልኩ ማቴ. 24:14 እና ማርቆስ 13:10። የዚህ ወንጌል ይዘት ባመዛኙ የዮሐንስ መጥምቁን መልእክት ይመስላል (ሉቃስ 3:3-14) ወይም የኢየሱስን ንግግር ለክፉው፣ ማቴ. 4፡10 ላይ። የፍርድ መልእክት በዚህ ወንጌል ላይ ዋነኛ ነገር ነው። ቁ. 6-7 ጠቃሚ ናቸው፣ እነዚህን እግዚአብሔር የላካቸውን ፍርዶች ስለሚያሳዩን፣ የጠፋውን የሰው ልጅ ለመዋጀት እንደሆነ (ዝከ. 9:20-21; 16:9,11)።

ቁ. 12 ላይ እውነተኛ አማኞች ባሕርያቸው (1) እንደሚጠብቁ (ማለትም፣ የአሁን አንቀጽ) የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እና (2) የሚጠብቁ (ማለትም፣ ተመሳሳይ የአሁን አንቀጽ) በኢየሱስ ያለውን እምነት።

▣ **"ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ"** 10፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**14፡7 "እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት"** ይህ ተገብሮ ድርጊት ነው (የተረጋገጠ) ተተኳሪ እና የድርጊት የአሁን ተተኳሪ። ሦስት የድርጊት ተተኳሪዎች አሉ፣ ቁ. 7 ላይ። የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ገቢውን ምላሽ በሥራና በእምነት ይሰጥ ዘንድ ታዟል (ዮሐንስ 1፡ 12፤ ሮሜ. 10:9-13)። 11:13 ላይ የወደቀው ሰው ለእግዚአብሔር ክብርን የሚሰጥ ይመስላል፣ ነገር ግን በፍጥነት በአውሬው ተአምራት ተስቦ ይወሰዳል፣ ምዕራፍ 13 ላይ ባለው (ተመሳሳይ የሆነ ሥነ-መለኮት ነው፣ ማቴዎስ 13፤ ማርቆስ 4፤ ሉቃስ 8) ለሚገኘው ለመሬቱ ምሳሌ።

▣ **"የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና"** "ሰዓት" የሚለው ቃል፣ በዮሐንስ ወንጌል ዋነኛ ነገር ነው (ዝከ. 2:4; 4:21,23; 5:25,28; 7:30; 8:20; 12:23,27; 13:1; 16:21,32; 17:1)። እሱም የአሁኑን ሁነት መለኮታዊ ሰዓት ይገልጻል (የጌታ ቀን ዝከ. 14:15 እና 9:15)።

### ልዩ ርዕስ፡ ሰዓቱ

"ሰዓቱ" የሚለው ቃል በወንጌላት በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል፣ እንደ

1. ሰዓት መጥቀሻ (ማቴ. 8:13; ሉቃስ 7:21; ዮሐንስ 11:9)
2. ለፈተናና ለምርመራ ሰዓት እንደ ዘይቤ (ማቴ. 10:19; ማርቆስ 13:11; ሉቃስ 12:12)
3. ኢየሱስ አገልግሎቱን መጀመሩን እንደሚያሳይ ዘይቤ (ዮሐንስ 2:4; 4:23)
4. ለፍርድ ቀን እንደ ዘይቤ (ማለትም፣ ዳግም ምጽአት፣ ማቴ. 24:36,44; 25:13; ማርቆስ 13:32; ዮሐንስ 5:25,28)
5. ለኢየሱስ መከራ ዘይቤ (ማቴ. 26:45; ማርቆስ 14:35,41; ዮሐንስ 7:30; 8:20; 12:23,27; 13:1; 16:32; 17:1)

▣ **"ስገዱለት"** ይህ ሌላው የድርጊት የአሁን ተተኳሪ ነው፣ እሱም ዋነኛ ትእዛዝ።

▣ **"ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው"** ይህ የሐዋ. 14፡15፣ እሱም ዘፍ. 14:19; ዘጸ. 20:11 ወይም መዝ. 146:6 የሚገኘው ማረጋገጫ ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ ተገልጿል፣ ኢዮብ 38፡41 ላይ እንዳለው። ብቸኛው ያልተለመደ ሐረግ "የውኃ ምንጮች" ነው፣ እሱንም አንዳንዶች የሚመለከቱት እንደ

1. ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የመልአኮቹ መቅሠፍቶች ጋር የተያያዙ (ዝከ. 8፡10)
2. ሊጠጣ ከማይችለው የባሕር ውኃ ጋር ተቃርኖ ያለው

### ራዕይ፡ 14፡8

**[8]ሌላም ሁለተኛ መልአክ። ሕዝብን ሁሉ የዝሙትዋን ቍጣ ወይን ጠጅ ያጠጣች ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች እያለ ተከተለው።**

**14፡8 "ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች"** ግሡ የተደገመ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን በግሪክ ዓረፍተ ነገር በቅድሚያ ነው የሚመጣው፣ ለዚህ የድርጊት የአሁን አመላካች አጽንዖት ለመስጠት። የራዕይ መጽሐፍን ለመተርጎም እጅግ አስቸጋሪ ነው፣ ምክንያቱም ጽንሰ-ሐሳቦቹ የተስፋፉት በተለያዩ ስፍራዎች ላይ በመሆኑ (አውሬው 11፡7 ላይ ባጭሩ ተጠቅሷል፣ ነገር ግን እስከ ምዕራፍ 13 ድረስ ሙሉ ለሙሉ አይብራራም)። የተሟላው የባቢሎን መውደቅ የሚገኘው (16:19 እና 17:1-18:24 ላይ ነው። እሱም የሚወክለው ሮምን ነው (1 ጴጥ. 5:13; II ባሮክ 11:1; 67:7; የሲቢሊን ንግርቶች 5:143, 159, 424), በመጨረሻ ግን የሚወክለው ከእግዚአብሔር ርቀው ለተደራጁትና ለሚሠሩት የሰው ማኅበረሰቦች ሁሉ ነው (ልዩ ርዕስ 13፣ ሠ ተመልከት)። ይህ የሰዎች የራስ ብቃት የውድቀት ቀጥተኛ ውጤት ነው (ዘፍጥረት 3) እናም እሱ በመጀመሪያ የተገለጸው በባብኤል ግንብ ላይ ነው (ዘፍጥረት 10-

11)። የዓለም መንግሥታት እጅግ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ እየሆኑ ይመጣሉ፣ እሱም በፍጻሜው ዘመን ከሚሆነው የክርስቶስ ተቃዋሚ አጠቃላይ የዓለም መንግሥት የሚወጣ ነው (ዳን. 2፡7-8)። ይህም የኢሳ. 21:9; ኤር. 51:8 ጠቃሽ ነው።

◘ **"አሕዛብን ሁሉ የዝሙትዋን ቍጣ ወይን ጠጅ ያጠጣች"** ጠቃሽነቱ ኤር. 51:7-8 (ዝከ. 17:2,4; 18:3) ነው። "ኃይለኛ ስሜት" የሚለው ቃል የግሪክ ቃል "*thumos,*" ሲሆን የሚዛመደውም ፈንቅሎ ከሚወጣ ስሜት ጋር ነው (7:14, ዝከ. 17:2,3; 18፡3 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት)። የባቢሎንን ወይን የጠጡ የያህዌን ወይን ይጠጣሉ (ዝከ. ቁ. 9)!

***ራዕይ፡ 14፡9-12***

**[9]ሦስተኛም መልአክ ተከተላቸው፥ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ። ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግምባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር፥ [10]እርሱ ደግሞ በቍጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቍጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፥ በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሳቀያል። [11]የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፥ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም። [12]የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው።**

**14፡9 "እንደ..."** ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ነው፣ በሁለት ግሦች፣ "ቢሰግዱ" እና "ቢቀበሉ።" አንዳንድ ሰዎች፣ ብዙ ሰዎች፣ እነዚህን የግልሙትና ድርጊቶች ይፈጽማሉ። ይህ ቀጥተኛ ተቃርኖ ነው፣ ቁ. 7 እና 12 ላይ ያለው የእግዚአብሔርን መሲሕ መቀበል። እንዲህ የሚያደርጉ የእግዚአብሔር ቍጣ ይደርስባቸዋል (ዝከ. ቁ.10)።

**14፡10 "እርሱ ደግሞ ከእግዚአብሔር ቍጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል"** ሰዎች ሁለት ብቻ መንፈሳዊ አማራጭ ይኖራቸዋል፣ እግዚአብሔር ወይም ክፉው። የግሪኩ ቃል ቁጣ *orgē* የሚያመለክተው "የተደራጀ ተቃዋሚ" ነው። 7፡14 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት። ጠቃሽነቱ ኢሳ. 51:17 ወይም ኤር. 25:15-16 (ራዕ.
16:19; 19:15) ነው። አማኞች የባቢሎንን ቁጣ መጋፈጥ ይኖርባቸዋል (ዝከ. ቁ. 8)፣ የማያምኑ ግን የእግዚአብሔር ቁጣ ያገኛቸዋል (ዝከ. ቁ. 10)።

ይህ ያልተለመደ የቃላት ድብልቅ (በጥሬው "የተደባለቀ ያልተደባለቀ") ማለት የእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ከሌሎች ነገሮች ጋር ተደባልቋል እጅግ አስካሪ ያደርገው ዘንድ፣ ነገር ግን ያልተደባለቀ ነው፣ እንደ ውኃ እስኪሆን ድረስ። "ጽዋ" የሚለው ቃል ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው በብኪ ዘወትር ለእግዚአብሔር ፍርድ ነው (ኢሳ. 51:17,22; ኤር. 25:15-17,27-29; መዝ. 75:8)። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የቁጣ ጽዋ ለሰው ልጆች ሁሉ ጠጣ (ማርቆስ 14፡36)። የማያምነው ዓለም ለእርሱ በእምነት ምላሽ አልሰጠውም፣ እና ስለዚህ፣ በራሳቸው ጽዋውን ይገጥሙታል!

## ልዩ ርዕስ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አዝማሚያ በአልኮል እና በአልኮለኝነት

I. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   1. ያይን - ይህ የወይን አጠቃላይ ቃል ነው (ቢዲቢ 406)፣ እሱም 141 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ።ሥርወ ቃሉ ርግጠኛ አይደለም፣ ምክንያቱም ከዕብራይስጥ ሥርወ ቃል ስላልሆነ። እሱም የሚሆነው የኮመጠጠ የፍራፍሬ ጭማቂ፣

      ባብዛኛውም ወይን ነው። ጥቂት ሁነኛ ምንባቦች፣ ዘፍ. 9፡21፤ ዘጸ. 29፡40፤ ዘኍ. 15፡5፣10።
   2. ቲሮሽ - ይህ "ጉሽ የወይን ጠጅ" ነው (ቢዲቢ 440)። በቅርብ ምስራቅ የዓየር ሁኔታ ምክንያት፣ ኩምጠጣ የሚጀምረው ጭማቂው ከተሰናዳ ከስድስት ሰዓት በኋላ ነው። ይህ ቃል የሚያመለክተው በመኮምጠጥ ሂደት ላይ ላለ ወይን ነው። ለሁነኛ ምንባቦች፣ ዘዳ. 12፡17፤ 18፡4፤ ኢሳ. 62፡8-9፤ ሆሴ. 4፡11 ተመልከት።
   3. አሲስ - ይህ የአልኮል መጠጥ ነው፣ ("ጣፋጭ ወይን" ቢዲቢ 7799፣ ምሳ. ኢዩኤል 1፡5፤ ኢሳ. 49፡26)።
   4. ሴካር - ይህ "ጠንካራ መጠጥ" ነው (ቢዲቢ 1016)። የዕብራይስጡ ሥር ጥቅም ላይ የሚውለው "ሰካራም" ወይም "ሰካር" በሚል ነው። እሱም አንዳች የተጨመረበት ይኖራል የበለጠ አስካሪ እንዲሆን። እሱም ከያይን ጋር ትይዩ ነው (ምሳ. 20፡1፤ 31፡6፤ ኢሳ. 28፡7)።
   ለ. አዲስ ኪዳን
   1. ኦዪኖስ - ከግሪኩ ያይን ጋር አቻ ነው
   2. ኒኦስ ኦዪኖስ (ጉሽ ወይን) የግሪኩ አቻ ቲሮሽ (ማርቆስ 2፡22)
   3. ግሊዩኮስ ቪኖስ (ጣፋጭ ወይን፣ ኤሲስ) - በአዲስነት መፍላት ላይ ያለ ወይን (ሐዋ. 2፡13)

II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀሙ
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ዘፍ. 27፡28፤ መዝ. 104፡14-15፤ መክ. 9፡7፤ ሆሴ. 2፡8-9፤ ኢዩ. 2፡19፣24፤ አሞጽ 9፡13፤ ዘካ. 10፡7)።
   2. ወይን የመሥዋዕታዊ ስጦታው አንደኛው አካል ነው (ዘጸ. 29፡40፤ ሌዋ. 23፡13፡ ዘኍ. 15፡7፣10፤ 28፡14፤ ዘዳ. 14፡26፤ መሳ  9፡13)።

3. ወይን እንደ መድኃኒት ያገለግላል (2ኛ ሳሙ. 16፡2፤ ምሳ. 31፡6-7)።
4. ወይን ተጨባጭ ችግር ሊሆን ይችላል (ኖህ - ዘፍ. 9፡21፤ ሎጥ- ዘፍ. 19፡33፣35፤ ሳምሶን- መሳ. 16፡19፤ ናባል- 1ኛ ሳሙ. 25፡36፤ ኦርዮ- 2ኛ ሳሙ. 11፡13፤ አምኖን- 2ኛ ሳሙ. 13፡28፤ ኢላህ- 1ኛ ነገሥ. 16፡9፤ ቤነሃዳድ- 1ኛ ነገሥ. 20፡12፤ ገዥዎች- አሞጽ 6፡6፤ እና ሴቶች- አሞጽ 4)።
5. ወይን ሊያዛባ ይችላል (ምሳ. 20፡1፤ 23፡29-35፤ 31፡4-5፤ ኢሳ. 5፡11፣22፤ 19፡14፤ 28፡7-8፤ ሆሴዕ 4፡11)።
6. ወይን ለተወሰኑ ወገኖች ክልክል ነው (ካህናት በሥራ ላይ፣ ሌዋ. 10፡9፤ ሕዝ. 44፡21፤ ናዝራውያን፣ ዘኁልቁ 6፤ እና ገዥዎች፣ ምሳ. 31፡4-5፤ ኢሳ.56፡11-12፤ ሆሴዕ 7፡5)።
7. ወይም እንደ የፍጻሜ መዳረሻነት መቼት ተደርጎ ተወስዷል፣ (አሞጽ 9፡13፤ አዩኤል 3፡18፤ ዘካ. 9፡17)።

ለ. ተረፈ መጽሐፍ ቅዱስ

1. ወይን በልኩ በጣም ይረዳል (መክብብ 31፡27-30)።
2. ራቢዎች የሚሉት፣ "ወይን ከመድኃኒት ሁሉ ታላቁ ነው፣ ወይን ሲያልቅ ነው ሌላ መድኃኒት የሚያስፈልገው።" (ባባ ባዝራ 58ለ)

ሐ. አዲስ ኪዳን

1. ኢየሱስ በርካታ ውኃ ወደ ወይን ቀይሯል (ዮሐንስ 2፡1-11)።
2. ኢየሱስ ወይን ጠጥቷል (ማቴ. 11፡18-19፤ ሉቃስ 7፡33-34፤ 22፡17)።
3. ጴጥሮስ በስካር ተከሷል፣ በጰንጠቆስጤ "ጉሽ ወይን"፣ (ሐዋ. 2፡13)።
4. ወይን እንደ መድኃኒት ያገለግላል (ማርቆስ15፡23፤ ሉቃስ 10፡34፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡23)።
5. 5. መሪዎች ጠጪ መሆን አይኖርባቸውም። ይህም ባጠቃላይ መጠጥን አለመቅመስ ማለት አይደለም (1ኛ ጢሞ. 3፡3፣8፤ ቲቶ 1፡7፤ 2፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡3)።

6. ወይን መንፈሳዊ ለሆነ መቼት ያገለግላል (ማቴ. 22፡1፤ ራዕ. 19፡9)።

7. ጠጪነት የተወገዘ ነው (ማቴ. 24፡49፤ ሉቃስ 12፡45፤ 21፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡11-13፤ 6፡10፤ ገላ. 5፡21፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡3፤ ሮሜ 13፡13- 14)።

III. ሥነ መለኮታዊ ይዘት

ሀ. ተቃርኗዊ ክርክር

1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።
2. ሰካራምነት ዋነኛው ችግር ነው።
3. አማኞች በአንዳንድ ባህሎች ነጻነታቸውን መገደብ ይኖርባቸዋል፣ ለወንጌል ብለው (ማቴ. 15፡1-20፤ ማርቆስ 7፡1-23፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 8-10፤ ሮሜ 14)።

ለ. ከተወሰነው ገደብ በላይ የመውጣት ዝንባሌ

1. እግዚአብሔር የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ነው።
2. የወደቀው የሰው ልጅ ሁሉንም የእግዚአብሔር ስጦታዎች እግዚአብሔር ካስቀመጠለት ገደብ በላይ በመውሰድ አበላሽቷቸዋል።

ሐ. ያላግባብ መጠቀሙ ከእኛ እንጂ ከነገሮች አይደለም። በሥጋዊ ተፈጥሮ ምንም ክፉ የለም (ማርቆስ 7፡18-23፤ ሮሜ 14፡14፣20፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡25-26፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡4፤ ቲቶ 1፡15)።

IV. የአንደኛው ክፍለ ዘመን የአይሁድ ባህልና አልኮል (ሆምጣጤ)

ሀ. መኮምጠጥ የሚጀምረው ወዲያው ነው፣ በግምት ከ6 ሰዓት በኋላ፣ ወይኑ ተረግጦ ሲያበቃ።

ለ. የአይሁድ ባህል እንደሚለው ከበስተላዩ ልከኛ አረፋ መታየት ሲጀምር (የመፍላት ምልክት)፣ የወይን መባ ለመስጠት ይደርሳል (ማአሴርዝ 1፡7)። እሱም "አዲስ ወይን" ወይም "ጣፋጭ ወይን" ይባላል።

ሐ. የመጀመሪያው አስካሪ ፍላት የሚያበቃው ከአንድ ሳምንት በኋላ ነው።

መ. ሁለተኛው ፍላት 40 ቀን ይወስዳል። በዚህ ጊዜ "ያረጀ ወይን" እንደ ሆነ ይቆጠራል፣ በመሠዊያው ላይም ለመሥዋዕትነት ይቀርባል (ኢድሁዮዝ 6፡1)።

ሠ. ሰፈፉ ላይ የረጋ ወይን (ያረጀ ወይን) መልካን እንደሆነ ይቆጠራል፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት መከለስ አለበት።

ረ. ወይን በተገቢው አረጀ የሚባለው ከፍላት ከአንድ ዓመት በኋላ ነው። ሦስት ዓመት ትልቁ ጊዜ ነው፣ ወይንን በተገቢው ለማስቀመጥ። እሱም "ያረጀ ወይን" ይባላል፣ ስለሆነም በውሀ መበረዝ ይኖርበታል።

ሰ. ባለፉት 100 ዓመታት በንጹሕ ቦታ እና ቅመም በመጨመር ኮምጣጥነቱን ማሻሻል ተችሏል። የጥንቱ ዓለም የኩምጠጣን ተፈጥሯዊ ሂደት ሊያስቀረው አልቻለም።

V. የመዝጊያ መግለጫ

ሀ. ያንተ ልምድ፣ ሥነ መለኮት፣ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የኢየሱስንና የአንደኛውን ክፍለ ዘመን አይሁድ/ወይም

ክርስቲያናዊ ባህል እንዳያንኳስስ ተጠንቀቅ! እነሱ ጨርሰው አልኮል የማይቀምሱ አልነበሩም።

ለ. እኔ የአልኮል ማህበራዊ ጠቀሜታ ተከራካሪ አይደለሁም። ሆኖም፣ ብዙዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስን አቋም ስለሚያጋንኑ እናም አሁን ልዕለ ጽድቅ የተመሠረተው በባህል/በመሠረተ እምነት ላይ ባለ አድሏዊነት በመሆኑ።

ሐ. ለእኔ፣ ሮሜ 14 እና 1ኛ ቆሮ. 8-10 በፍቅርና በአክብሮት ላይ የተመሠረተ ይዘትና መመሪያ ይሰጡኛል፣ ይህም ለአማኞችና ለወንጌል ስርጭት በሁሉም ባህል፣ ግለሰባዊ ነጻነት ወይም ፍርዳዊ ሂስ ሳይሆን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን የእምነትና የተግባር ምንጭ ከሆነ፣ እናም ሁላችንም ይሄንን ጉዳይ ዳግም ልናጤነው ይገባል።

መ. ጨርሶ መታቀብን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ብንወስደው፣ ስለ ኢየሱስ ምን እንላለን፣ እንዲሁም ስለ ዘመናዊዎቹ ባህሎች፣ በመደበኛነት ወይንን የሚጠቀሙ፣ (ለምሳሌ፣ አውሮጳ፣ እስራኤል፣ አርጀንቲና)?

◘ **"እርሱም በእሳትና በዲን ይሣቀያል።"** ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ጠቃሽ ነው፣ በሰዶምና ገሞራ ላይ ዘጸ. 19:24,28; ሉቃስ 17:29; ወይም ፍርድ ባጠቃላይ፣ መዝ. 11:6; ኢሳ. 34:8-11; ሕዝ. 38:22)። ሥቃይ የሁለቱ አውሬዎች የመጨረሻ ዕጣ ነው (ዝከ. 19:20)፣ የከፉው (ዝከ. 20:10)፣ እና ንስሐ ያልገባው የሰው ልጅ (ዝከ. 20:15፤ 21:8)።

እሳት (ልዩ ርዕስ 16:8 ላይ ተመልከት) ለእግዚአብሔር ቅድስና የብኪ ዘይቤ ነው (ዘኍ. 9:15-16, ወዘተ.) እሱም እንደ ማጥሪያ መሣርያ ጥቅም ላይ ውሏል (ሌዋ. 8:17,32; 9:11,24; 13:32,55,57, ወዘተ) እና ፍርድ (ሌዋ. 10:1-2; ዘኍ. 11:1-3, ወዘተ.)። ይህ ከፍርድ ጋር የተያያዘ ዝምድና የፍርዱንም ስፍራ እስከማሳየት ድረስ ተስፋፍቷል። ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ ያለውን የቆሻሻ መጣያ ስፍራ፣ የሄኖም ልጆች ሸለቆ (ገሃነም) ለዘላለማዊ ፍርድ በተምሳሌትነት ተጠቅሞበታል (ራዕ. 20:10, 14-15)።

**14:11 "የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፥"** እኔ ማመን የምሻው በአጠቃላይሽነት ነው ወይም ቢያንስ በሁለተኛ ዕድል፣ ለወንጌል ምላሽ ለመስጠት፣ ነገር ግን እንደ ቅዱስ ቃሉ ሰዎች ለእግዚአብሔር ስጦታ በእምነት ምላሽ የግድ መስጠት ይኖርባቸዋል (ማርቆስ 1:15፤ ሐዋ. 3:16,19; 20:21) በሕይወት እያሉ (ዕብ. 9:27); ምላሽ ከመስጠት እምቢ ካሉ፣ ውጤቱ የመጨረሻና ዘላለማዊ ነው (ማርቆስ 9:47-48; ማቴ. 25:46; ዮሐንስ 5:29; ሐዋ. 24:15; II ተሰ. 1:6-9)። በኃጢአተኞች ላይ የሚሆነው ቋሚ ቅጣት ከቅዱሳን ጊዜያዊ መከራ ጋር ይነጻጸራል። ይህም "ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም" በሚለው ሐረግ ድጋፍ ሲያገኝ፣ ቁ. 13 ላይ ቅዱሳን ያርፋሉ።

ይህ ለማብራራት ቀላል ርዕሰ-ጉዳይ አይደለም። የእግዚአብሔር ፍቅር እና የልቡም መቤዠት ከዘላለማዊ ቅጣቱ ጋር ይቃረናል። አብዛኞቹ ራዕይ ላይ ያሉት የእግዚአብሔር ፍርዶች ለመቤዠት ናቸው፣ እንደ ግብፅ መቅሠፍቶች እና ዘዳግም 27-29 የርግማን ኪዳን። እናም የእግዚአብሔር የመጨረሻ መተው ቋሚ ነው። ተግሣጻዊ አይደለም፣ ቅጣታዊ ነው! ይህን ለመረዳት እጅግ ይጠጥራል፣ በስሜት ለመያዝ። እሱም ለወንጌላዊነት አጽንዖት ይሰጣል!

ይህን ርዕሰ-ጉዳይ ከመተዌ በፊት በዚህ አካባቢ ያለኝን አስተሳሰብ ላካፍላችሁ። ለሰው ልጆች እንደ ሲኦል ከፉ እንደሆነ፣ ለእግዚአብሔር ደግሞ እጅግ የከፋ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን በአምሳሉ የፈጠረው ለኅብረት ነው። ፍጥረት ሁሉ ለእግዚአብሔር ደረጃ ነው፣ የሰው ልጆችን ለመገናኘትና ለማወቅ። እግዚአብሔር ሁሉንም የአዳም ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ይወዳል (ሕዝ. 18:32; I ጢሞ. 2:4; II ጴጥ. 3:9)። እነርሱን እጅግ ይወዳል፣ የገዛ ልጁን በእነርሱ ስፍራ እንዲሞት እስከ መላክ ድረስ (ዮሐንስ 3:16; II ቆሮ. 5:21)። ነገር ግን የመረጠው፣ ለእሱ የግድ ምላሽ እንዲሰጡ ነው፣ በነታመን፣ በእምነት፣ በንስሐ፣ በመታዘዝ፣ በአገልግሎት፣ በአምልኮ፣ እና በትዕግሥት። እግዚአብሔር ማንንም ወደ ገሃነም አይሰድም፣ የማያምኑ ግን ራሳቸውን ይሰዳሉ (ዮሐንስ 3:17-21)። ገሃነም ክፍት የሆነ፣ የሚደማ ቁስል ነው በእግዚአብሔር ልብ፣ እሱም ፈጽሞ የማይፈወስ! ርግጠኛ አይደለሁም፣ እግዚአብሔር "መልካም ቀን" እንደሚኖረው። አህ፣ የፈቃድ ዐመጻ፣ በመሥዋዕታዊው ፍቅር ፊት!

**14:12** ትዕግሥት ዋነኛ ጭብጥ ነው፣ በመጽሐፉ ሁሉ (ዝከ. 1:9; 2:7,11,17,19,26; 3:5,10,12,21; 13:10; 21:7)። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በመከራ ውስጥ እንኳ ቢሆን ታማኝ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ልዩ ርዕስ 2:2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

◘ **"ቅዱሳን"** ልዩ ርዕስ 5:8 ላይ ተመልከት።

◘ **"የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት"** ተመሳሳይ የሆነ የአማኞች ገለጻ 12:17 ላይ ይገኛል። አጽንዖቱ ከኢየሱስ ጋር የሚሆን ግላዊ የእምነት ግንኙነት እንደሆነ ተገንዘቡ፣ የሕይወት ስልት የሆነ መታዘዝ የሚከተለው (ዝከ. 12:17; ሉቃስ 6:46)።

የበሰለ ክርስትና የሚያካትተው

1. ሰውየውን መቀበል (ከክርስቶስ ጋር የሚሆን ወዳጅነት)
2. ያንን ሰው ለማመን ያሉት እውነቶች (የአኪ ዶክትሪናዊ እውነቶች)
3. ያንን ሰው የመሰለ ሕይወት መኖር (በየቀኑ ክርስቶስን መምሰል)

ሦስቱም ሁሉ ለበሰለ፣ ጤናማ፣ የሚያድግ እምነት ያስፈልጋሉ።

### ራዕይ፡ 14:13

[13]ከሰማይም። ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ። አዎን፥ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ፥ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።

**14፥13 "ብፁዓን"** ይህ በራዕይ መጽሐፍ ከሚገኙት ሰባት በረከቶች ሁለተኛው ነው (ዝከ. 1:3; 14:13; 16:15; 19:9; 20:6; 22:7,14)።

◘ **"በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው።"** ይህ ሰማዕታትን የሚጠቅስ ነው (በ144000 ላይ እንዳለው)፣ ነገር ግን የዚህ ሞት ትክክለኛ ጊዜ ርግጠኛ አይደለም። አንዳንድ ተንታኞች የሚያዛምዱት ከዮሐንስ ቀን ጋር ነው፣ አንዳንዶች ደግሞ ከመጨረሻው ዘመን ጋር። ምንም እንኳ የጊዜው ነገር ርግጠኛ ባይሆንም፣ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሞት በእርሱ ፊት የከበረ መሆኑን ማወቅ ጠቃሚ ነው (መዝ. 116፥15)።

ምንም እንኳ ይህ ወገን የክርስቲያን ሰማዕታት ቢሆንም፣ ይሄንን እንደ "ምስክሮች" መተርጎሙ እጅግ የተሻለ ነው፣ እንደ አማኞች አጠቃላይ መልክ። አማኞች ሁሉ በአንደኛው ክፍለ-ዘመን አልተገደሉም፣ በፍጻሜ ዘመኑም መከራ ሁሉም አማኞች አይገደሉም፣ ነገር ግን አማኞች ሁሉ በክርስቶስ የታመኑ ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል። ዘይቤው አጠቃላይ ነው፣ የማያካትት ሳይሆን።

◘ **"ሥራቸውም ይከተላቸዋል"** የክርስትና ፓራዶክስ (አያዎ) የሚሆነው እኛ እንደ አማኞች በመዳን በመንፈስ ጸጋ ተሰጥቶናል፣ ለውጤታማ አገልግሎት ለ እና በክርስቶስ አካል (1 ቆሮ. 12:7,11)። እግዚአብሔር ይጠራል፣ ያበቃል፣ የዘላለምም ፍሬ ያፈራል፣ ፍጹም ባልሆኑ አማኞች። የእርሱ ስጦታ ነው፣ የእርሱ መንፈስ ነው ኃይል የሚሞላ፣ ቅዱሳን ግን ስለ ታማኝነታቸው፣ መገኘታቸው፣ እና ትዕግሥታቸው ሽልማት ይቀበላሉ (ልዩ ርዕስ 2፥10 ላይ ተመልከት)። አማኞች በሥራ አልዳኑም (በራስ ጥረት)፣ ነገር ግን ለመልካም ሥራ ነው የዳኑት (ኤፌ. 2፥8-9፣10)። የእግዚአብሔር ፍቃድ ለእያንዳንዱ አማኝ ክርስቶስን የመሰለ አገልግሎት ነው (ሮሜ. 8:29; ገላ. 4:19; ኤፌ. 1:4)!

**ራዕይ፥ 14፥14-16**

**[14]አየሁም፥ እነሆም ነጭ ደመና፥ በደመናውም ላይ የሰውን ልጅ የሚመስል ተቀምጦአል፥ በራሱም ላይ የወርቅ አክሊል በእጁም ስለታም ማጭድ ነበረው። [15]ሌላ መልአክም ከመቅደሱ ወጥቶ በደመናው ላይ ለተቀመጠው። የማጨድ ሰዓት ስለ ደረሰ ማጭድህን ስደድና እጨድ፥ የምድሪቱ መከር ጠውልጓልና ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። [16]በደመናውም ላይ የተቀመጠው ማጭዱን ወደ ምድር ጣለው ምድርም ታጨደች።**

**14፥14-16** ሁለት የተለያዩ ዓይነት መከሮች አሉ (IV ዕዝራ 13፥10-11) ቁ. 14-16 እና 17-19 ላይ የተገለጹ። የመጀመሪያው የእህል አዝመራ ሲሆን ሁለተኛው የወይን አዝመራ ነው። ይህ ልዩነት የተጠበቀ ከሆነ (ኢዩኤል 3፥13 ላይ፣ ሁለቱም አዝመራዎች የሚታዩት እንደ አንድ ፍርድ ነው)፣ የመጀመሪያው የሚያመለክተው የጻድቅን መከር ሲሆን (ማቴ. 9:37-38; 13:30,38; ማርቆስ 4:26-29; ሉቃስ 10:2; ዮሐንስ 4:35-38), ሁለተኛው የወይን መከር ኢሳ. 63:2-6; ኤር. 51:33; ሰቆ. 1:15; ኢዩኤል 3:13 እና ራዕ. 19:15 ላይ የተጠቀሰው ኃጢአተኛን ነው የሚያመለክተው።

**14፥14 "እነሆም ነጭ ደመና፥ በደመናውም ላይ የሰውን ልጅ የሚመስል ተቀምጦአል፥ በራሱም ላይ የወርቅ አክሊል"** ተመሳሳይ የሆነ የማንነት ችግሮች ምዕራፍ 6 እና 10 ላይ ያሉት፣ በእነዚህም ቁጥሮች ላይ ይሠራሉ። ይህ የመለኮታዊው መሲሕ መግለጫ ነው (ዳን. 7፥13) ወይስ ሌላ መልአክ ነው በእርሱ በኩል የሚያገለግል? ሌላ ብርቱ መልአክ ይመስለኛል፣ ምክንያቱም

1. ይህ ተለጣጣቂ ከሆኑት መላእክት ነው (ዝከ. ቁ. 15፣17፣18)
2. ማቴ. 13:39, 41-42, 49-50 የሚለው መላእክት በመጨረሻው ዘመን ሰዎችን ሰብስበው ይለያሉ (አንዳንዶች ለበረከት እና አንዳንዶች ለፍርድ)
3. መልአክ ያዘዋል (ዝከ. ቁ. 15)

**14፥15** ይህ የኢዩኤል 3፥13 ጠቃሽ ነው።

**ራዕይ፥ 14፥17-20**

**[17]ሌላ መልአክም በሰማይ ካለው መቅደስ ወጣ፥ እርሱም ደግሞ ስለታም ማጭድ ነበረው። [18]በእሳትም ላይ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከመሠዊያው ወጥቶ ስለታም ማጭድ ያለውን። ዘለላዎቹ ፈጽመው በስለዋልና ስለታሙን ማጭድህን ስደድና በምድር ያለውን የወይን ዛፍ ዘለላዎች ቍረጥ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጠራ። [19]መልአኩም ማጭዱን ወደ ምድር ጣለው፥ በምድርም ካለው ከወይን ዛፍ ቈርጦ ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር ቍጣ መጥመቂያ ጣለ። [20]የወይኑም መጥመቂያ ከከተማ ውጭ ተረገጠ፥ እስከ ፈረሶች ልጓምም የሚደርስ ደም ርቀቱ ሺህ ስድስት መቶ ምዕራፍ ሆኖ ከመጥመቂያው ወጣ።**

**14፥17 "ሌላ መልአክም በሰማይ ካለው መቅደስ ወጣ፥"** ይህ የሚያመለክተው በሰማይ ያለውን መንፈሳዊ ቤተ መቅደስ ነው (ዕብ. 8:2; 9:11,23-24)።

**14፡18 "በእሳትም ላይ ሥልጣን ያለው"** መላእክት በነፋስ ላይ ሥልጣን አላቸው (ዝከ. 7፡1)፣ በእሳት ላይ (ዝከ. 14፡18)፣ እና በውኃ ላይ (ዝከ. 16፡5)። ይህ የሚያንጸባርቀውም የራቢያዊ ይሁዲነት ጽንሰ-ሐሳብ ሲሆን፣ መላእክት በተፈጥሮ ዓለም ውስጥ እንደሚገቡ የሚያንጸባርቅ ነው። ምንም እንኳ አኪ ለዚህ አጽንዖት ባይሰጥም፣ ያ ርግጠኛ አይደለም ማለት አይደለም (ዕብ. 1፡7፣14)።

**14፡20 "ከከተማ ውጭ"** አንዳንዶች ይህን የሚመለከቱት ክርስቶስ ከከተማ ውጭ መሰቀሉን ለመጥቀስ ነው (ዕብ. 13፡12)። ሌሎች የሚመለከቱት እንደ ብኪ የመንጻት ሕግጋት ነው፣ የረከሱት ከሰፈሩ ውጭ እንደሚወሰዱ (ሌዋ. 8:17; 9:11)። ሆኖም፣ እሱ የእግዚአብሔር ጠላቶች በፍጻሜ ዘመን በኢየሩሳሌም ከተማ ዙሪያ መሰብሰባቸውን የሚጠቅስ ይሆናል (መዝ. 2:2,6; ዳን. 11:45; ኢዩኤል 3:12-14; ዘካ. 14:1-4; እና በይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ መጽሐፍ 1 ሔኖክ 53:1)። እዚህ በድጋሚ፣ የትኛው እማሬያዊ፣ የትኛው ፍካሬያዊ የመሆኑ ችግር ዋነኛው የትርጓሜ ጉዳይ ይሆናል!

▣ **"እስከ ፈረሶች ልጓምም የሚደርስ ደም ርቀቱ ሺህ ስድስት መቶ ምዕራፍ ሆኖ ከመጥመቂያው ወጣ።"** ይህ የትልቁ ውጊያ ውጤት ይሆናል፣ ባለፉት ምዕራፎች የተገለጸ፣ ወይም እንዲያው ከወይን ጭማቂ ቀለም የተገኘ ዘይቤ ይሆናል። ርግጠኛው ጥያቄ እሱ እማሬያዊ ነው ተምሳሌታዊ የሚለው ነው። ይህም የሚገልጸው በጊዜ/በቦታ የሆነ ጦርነትን ነው ወይስ ተምሳሌታዊ ሰማያዊ ጦርነት፣ እሱም በመልካምና በክፉ መካከል የሚካሄድ? ዘውጉ የሚያመዝነው ወደ ኋለኛው ነው፣ ነገር ግን የኢየሱስ ቃላት፣ ማቴዎስ 24፡ ማርቆስ 13 እና ሉቃስ 21 የሚያመዝኑት ወደ ፊተኛው ነው።

ትክክለኛው ርቀት ርግጠኛ አይደለም። አንዳንዶች የሚሉት (1) 165 ማይል፤ (2) 184፤ ወይም (3) 200 ማይል ነው። ርግጠኛው ቃል 6600 ፈርሎንግ ነው። ይህም ያልተለመደ ተምሳሌታዊ ቁጥር ነው። አንዳንዶች የሚሉት እሱ የሚያመለክተው ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያለውን ርቀት ነው፣ ማለትም ፍርዱ በተምሳሌት ሙሉውን ቅዱስ ምድር ይሸፍናል።

"የወይን መርገጫ" የብኪ የፍርድ ዘይቤ ነው (ኢሳ. 63፡3፤ ሰቆ. 1፡15)። ይህም ምናልባት የቀይ ወይን ጭማቂ እና ደም ተመሳሳይነት በመካከላቸው ስላለ ይሆናል። እሱም 19፡15 ላይ ደግሞ ተጠቅሷል።

▣ **"የእግዚአብሔር ቁጣ"** 7፡14 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ምዕራፍ 7 እና 14 ላይ የሚገኘው 144000 ግንኙነቱ ምንድነው?
2. የጽዮን ተራራ ማንን ነው የሚያመለክተው?
3. 14፡4 ላይ የሚገኙት መለያዎች ለተመረጡ የድንግል ወገኖች ነው ወይስ ለሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝቦች?
4. የ14፡6 እና 7 ጠቀሜታ ምንድነው?
5. ባቢሎን ማን ወይም ምንድነው?
6. ገሃነም ዘላለማዊ ነውን?
7. 14፡14-16 ላይ ደመና ላይ የተቀመጠው ሰው ማነው፣ ለምን?

# ራዕይ 15-16
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| መላእክት ከመጨረሻው መቅሠፍት | ቅድመ-ጽዋ ፍርድ | ሰባቱ የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋዎች | መላእክት ከመጨረሻው መቅሠፍት | የሙሴና የበጉ መዝሙር |
| 15:1 | 15:1-16:1 | 15:1 | 15:1 | 15:1-4 |
| 15:2-4 | | 15:2-4 | 15:2-4 | ሰባቱ የቁጣ ጽዋዎች |
| 15:5-8 | | 15:5-16:1 | 15:5-8 | 15:5-8 |
| የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋዎች | | | የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋዎች | |
| 16:1 | | | 16:1 | |
| 16:2 | አንደኛው ጽዋ፡ ጽኑ ቁስል | | 16:2 | 16:1 |
| | 16:2 | 16:2 | | 16:2 |
| 16:3 | ሁለተኛው ጽዋ፡ ባሕሩ ወደ ደም ተቀየረ | | 16:3 | |
| | 16:3 | 16:3 | | 16:3 |
| 16:4-7 | ሦስተኛው ጽዋ፡ ውኆች ወደ ደም ተቀየሩ | | 16:4-7 | |
| | 16:4-7 | 16:4-7 | | 16:4-7 |
| 16:8-9 | አራተኛው ጽዋ፡ ሰዎች በሙቀት ተቃጠሉ | | 16:8-9 | |
| | 16:8-9 | 16:8-9 | | 16:8-9 |
| 16:10-11 | አምስተኛው ጽዋ፡ ጨለማና ሥቃይ | | 16:10-11 | |
| | 16:10-11 | 16:10-11 | | 16:10-11 |
| | ስድስተኛው ጽዋ፡ ኤፍራጥስ ደረቀ | | | |
| 16:12-16 | 16:12-16 | | 16:12-14 | |
| | ሰባተኛው ጽዋ፡ ምድር በሞላ ተንቀጠቀጠች | 16:12-16 | 16:15 | 16:12-16 |
| | | | 16:16 | |
| 16:17-21 | 16:17-21 | | 16:17-21 | |
| | | 16:17-21 | | 16:17-21 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ vii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

5. የመጀመሪያው አንቀጽ
6. ሁለተኛው አንቀጽ
7. ሦስተኛው አንቀጽ
8. ወዘተርፈ

**ጽሑፋዊ ይዘት** *ራዕይ* **15:1-16:21**

ሀ. ሰባቱ ጽዋዎች፣ እነርሱም ምዕራፍ 15 ላይ የተዋወቁት እና ምዕራፍ 16 ላይ የተብራሩት፣ ከሦስቱ የመለኮታዊ ቁጣ ዑደቶች፣ እነርሱም ለመቤዠት ዓላማ ከተላኩት ሦስተኞቹ ናቸው (ዝከ. 9:20-21፤ 14:6-7፤ 16:9፣11)። እያንዳንዱ ዑደት እየጨመረና እየከፋ ይሄዳል፡ 1/4፣ 1/3፣ እና አጠቃላይ ጥፋት (በክፉ ላይ የሚሆን ፍርድና መለየት)። ይህም ሊሆን የሚችለው በዘዳግም 27-28 "የርግማንና በረከት" ክፍል ላይ በመመሥረት ነው።

ለ. በእነዚህ ዑደቶች ላይ ጽሑፋዊ ዝምድና አለ። ሰባተኛው ማኅተም ሰባቱ መለከቶች ነው። የመጀመሪያዎቹ አራቱ መለከቶች ደግሞ ከመጀመሪያዎቹ አራቱ ጽዋዎች ጋር በቀጥታ ትይዩ ናቸው።

ሐ. ሰባተኛው ጽዋ የባቢሎን መውደቅ ነው፣ እሱም የሰው ማኅበረሰብ መውደቅ ተምሳሌት ነው፣ ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተደራጀና የሚሠራ። በዮሐንስ ጊዜ እሱ ሮም ነበር። ዳንኤል 2 ላይ እያንዳንዱ ቀጣይ የዓለም መንግሥት እጅግ እየጨመረ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ሆነ፣ በመላው ዓለም ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ መንግሥት፣ እሱም መሲሑ የተወለደበት፣ የሮም ግዛት (የዳንኤል 8ን መግቢያ www.freebiblecommentary.org) ላይ ተመልከት።

መ. ምዕራፍ 15 እና 16 ምስያቸውን የቀዱት ከዘጸአት የእስራኤል ተሞክሮ ነው (ምዕራፍ 12-14 ላይ እንደሆነው ሁሉ)። ይህ የፍጻሜ ዘመን ከክፉ ማዳን እንደ ዘጸአት አጠቃላይ ግብ ይታያል (ማለትም፣ መታደግ)።

ሠ. አውሬዎቹና የባቢሎኗ ጋለሞታ (ዓመጸኛው የሰው ኅብረተሰብ) በአርማጌዶን ተሸንፈዋል (16፡12-16)፣ ሰይጣንም ከጎግና ማጎግ ጋር ሲሸነፍ (ዐመጸኞች ሰዎች) በመጨረሻ ላይ (ዝከ. 20፡7-10)። የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምዕራፍ 19 ላይ የሰባተኛው ማኅተም እና የሰባተኛው መለከት እና የሰባተኛው ጽዋ ፍርዶች መስፋፊያና ፍጻሜ ነው። ይኸም የእግዚአብሔር ምላሽ ነው፣ 6፡9-11 ላለው የሰማዕታት ጥያቄ።

ረ. እነዚህን የፍጻሜ ዘመን ውጊያዎች የመተርጎም አስቸጋሪነት የሚሆኑት፡

1. የቀረቡበት የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት፣ አፖካሊፕቲካዊ/ትንቢታዊ።
2. እነርሱም የቀረቡት እያደጉ በሚሄዱ ደረጃዎች፣ ዑደቶች፣ ወይም ድራማዊ ድርጊቶች መሆኑ።
3. በቡድኖቹ እና በተምሳሌቶቹ መካከል ተለዋዋጭነት መኖሩ።
4. የመጀመሪያውን ክፍለ-ዘመን አፈጻጸም እና የፍጻሜውን ዘመን አፈጻጸም ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑ።

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

***ራዕይ፡ 15፡1-3ሀ***

**[1]ሌላም ታላቅና ድንቅ ምልክት በሰማይ አየሁ፤ የእግዚአብሔር ቍጣ በእነርሱ ስለሚፈጸም ኋለኛዎቹን ሰባት መቅሠፍቶች የያዙ ሰባት መላእክት ታዩ። [2]በእሳትም የተቀላቀለውን የብርጭቆ ባሕር የሚመስለውን አየሁ፥ በአውሬውና በምስሉም በስሙም ቍጥር ላይ ድል ነሥተው የነበሩት የእግዚአብሔርን በገና ይዘው በብርጭቆ ባሕር ላይ ሲቆሙ አየሁ። የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ።**

**15፡1 "በሰማይ"** ይህ ሦስተኛው ተለጣጣቂ ምልክት ነው፣ ዮሐንስ በሰማይ ያየው። ልዩ ርዕስ 12፡1 ላይ ተመልከት።

▣ **"ታላቅና ድንቅ"** ይህ ሐረግ እዚህ ብቻ ነው የሚገኘው፣ እናም ወደ ብኪ ጠቃሽ ያመለክታል፣ ቁ. 3 ላይ፣ እሱም ከበርካታ ስፍራዎች ከአንዱ የመጣ (ማለትም፣ ዘዳ. 32:3-4፤ መዝ. 111:2፤ 139:14፤ ወይም ሆሴ. 14:9)።

ቁጥር 3-4 አንድ ረጅም ጽሑፍ ጽሑፍ ያበጃል፣ የብኪ ጠቃሽ፣ ከበርካታ ታሳቢ ስፍራዎች።

▣ **"የእግዚአብሔር ቁጣ"** 7፡14 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ተፈጽሟል"** ይህ የድርጊት ተገብሮ አመላካች ነው፣ የ*teleō* መጨረስ ወይም መፈጸም። ጽዋዎቹ የተጠናቀቁና የመጨረሻ ፍርድ ናቸው፣ በአስቸጋሪ ኢ-አማኒዎች ላይ! በቀጣይ የሚሆን የንስሐና እምነት ተስፋ አይኖርም፣ ፍርድና መለየት ብቻ!

ከሥነ-መለኮት አኳያ ማለት የሚቻለው የማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና የጽዋዎቹ ቅደም ተከተል የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ መንገድ ነው፣ ሰዎች ንስሐ ይገቡ ዘንድ፣ በመጨረሻ ግን የእሱ በክፉ ላይ ያለ አጠቃላይ ፍርድ፣ ማስወገድ፣ እና መለየት ፍትሐዊ ነው! የቀረው ብቸኛ አማራጭ ገሃነም ነው።

**15፡2 "የብርጭቆ ባሕር የሚመስለውን አየሁ"** ይህ በመጀመሪያ ራዕ. 4፡6 ላይ ነው የተጠቀሰው። ራዕ. 21፡1 ላይ ባለው አጠቃቀም ምክንያት፣ ለእግዚአብሔር ቅድስና ዘይቤ ይመስላል፣ ኃጢአተኛው የሰው ልጅ ወደ እሱ እንዳይቀርብ የሚያግደው (ማለትም፣ ለሰማይ ውኆች ዘይቤ ሊሆን ይችላል)። አንድ ቀን ይህ ማገጃ ይወገዳል። የብኪ ጠቃሽ የሚሆነው አንድም ዘጸ. 24፡10 ወይም ሕዝ. 1፡22፤ 10፡1 ነው። 4፡6 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"እሳት የተቀላቀለ"** ይህ አዲስ ነገር ነው፣ 4፡6 ላይ የማይገኝ። ብዙ ንድፈ-ሐሳቦች ነበሩ።
1. እሱ የፀሐይ ነጸብራቅ ነው፣ በሰው ታሪክ
2. እሱ የሚወክለው እሳት ነው፣ ለእግዚአብሔር ፍርድ የሚቆመውን
3. እሱ የሰማዕታት ደም ነው
4. እሱ የሚያያዘው በቀይ ባሕር ላይ ከተገኘው ድል ጋር እና ከሙሴ መዝሙር ጋር ነው፣ ምዕራፍ 15 እና 16 የብኪ ዳራ ስላላቸው፣ ከዘጸአት መቅሠፍት ጋር (ዘጸ. 7-12፤ 15)

▣

**አአመመቅ** **"ድል ነሥተው"**
**አኪጀት** **"ድል የነሡ"**
**አየተመቅ** **"ድል የነሡ"**
**አእት** **"ድል የነሡት"**
**አኢመቅ** **"የተዋጉ"**

በመጀመሪያ ይሄ ሰማዕታትን የሚጠቅስ ይመስላል፣ ነገር ግን 12፡11 የሚያሳየው የተፈጥሮ ሞትን በሚያዩት ላይ የግድ መፈጸሙን ነው፣ ነገር ግን ለአውሬው ያልሰገዱ (ዝኪ. 20፡4)።

▣

**አአመመቅ** **"በአውሬውና በምስሉም በስሙም ቍጥር ላይ"**
**አኪጀት** **"በአውሬው ላይ፣ በምስሉም ላይ እና በምልክቱም ላይ"**
**አየተመቅ** **"አውሬውና ምስሉ እና የስሙም ቁጥር"**
**አእት** **"በአውሬው ላይና በምስሉም ላይ እና ስሙን በሚወክለው ቁጥር ላይ"**
**አኢመቅ** **"አውሬውና ሰው፣ እና የእሱንም አቋም በመቃወም እና ስሙ በሆነ ቁጥሩ ላይ"**

አውሬው በመጀመሪያ የተጠቀሰው 11፡7 ላይ ነው። ከምዕራፍ 13 መረዳት የሚቻለው ሁለት የዱር አውሬዎች መኖራቸውን ነው፤ አንደኛው የሰይጣን ሥጋ መልበስ (ማለትም፣ ክርስቶስን በመምሰል) እና ሌለኛው የእርሱ ሐሰተኛ ነቢይ ነው (ማለትም፣ መንፈስ ቅዱስን በመምሰል)። ከ13፡18 የምንረዳው ቁጥሩ 666 ነው፣ እሱም የግለሰብ ቁጥር ፈጽሞ የማይመስል፣ እንደ ወደቀና ብቁ አንደማይሆን የሰው ኅብረተሰብ (ማለትም፣ መንግሥት) ከእግዚአብሔር የራቀ።

▣ **"በብርጭቆ ባሕር ላይ ሲቆሙ"** አንዳንድ ትርጉሞች "ላይ" የሚል አላቸው (አአመመቅ፣ አኪጀት)፣ አንዳንዶችም "በጎን" የሚል አላቸው (አየተመቅ) ወይም "በኩል" (አኢመቅ፣ አእት)። የግሪኩ መስተጻምር መሠረታዊ ፍቺ "በላይ" ነው። ዘይቤው የሚናገረው ድል የሚነሡት ወደ እግዚአብሔር እንደሚቀርቡ ነው። "ባሕር" በራዕይ የሚወክለው በቅዱሱ እግዚአብሔር እና በኃጢአተኛ ፍጥረት መካከል እንደ መለያ ነው። ባሕር ሙሉ ለሙሉ ተወግዷል፣ 21፡1 ላይ ሙሉው ኅብረት በሚመለሰበት ጊዜ (ማለትም፣ የዔድን ገነት ወዳጅነት ተመልሷል)።

"ለብርጭቆ ባሕር" ፍች ትርጓሜአዊ አማራጮች 4፡6 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"የእግዚአብሔርን በገና ይዘው"** መላእክት በገና እንዳላቸው ነው የሚገለጹት፣ 5፡8 እና 14፡2 ላይ። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የሚያመለክተው አማኞችን ነው፣ እነርሱም ከ144000፣ ምዕራፍ 14 ላይ ካሉት ተመሳሳይ የሆነ። መላእክት የሰማይ አምላክን በዝማሬ እንደሚያመልኩ ሁሉ፣ አሁንም እንዲሁ፣ ድል ያደረጉት አማኞች!

**15፡3 "...የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ።"** ይህ የሚያሳየው የአሮጌውንና የአዲሱን ኪዳን አንድነት ነው፣ በዚህ የመቤዠት ዝማሬ። የሙሴ መዝሙር የዘጸ. 15፡1-9 ጠቃሽ ነው፣ እዚያም ሙሴ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት፣ ስለ ፈርዖን መሸነፍ፣ ቀይ ባሕር ላይ። ሆኖም፣ ሊሆን የሚችለው ዮሐንስ ዘዳግም 32ን በሐሳቡ እንደያዘ ነው፣ ምክንያቱም የመጀመሪያው ሐረግ ከዘዳ. 32፡3-4 ስለተጠቀሰ። የበጉ ዝማሬ ቀደም ሲል 5፡9 እና 14፡3 ላይ ተመልክቷል። የተጠቃለለ መዝሙር እንደሆነ ተገንዘብ፣ የግለሰብ ሳይሆን፣ የደኅንነት (ዘፍ. 3፡15)።

▣ **"የእግዚአብሔርን ባርያ"** ይህ የክብር መጠሪያ ነው፣ እንደ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ እና ዳዊት ለመሳሰሉት ገጸ-ባሕርያት። እሱ የጳውሎስ "የክርስቶስ ባርያ" መነሻ ሊሆን ይችላል።

### ራዕይ፡ 15፡3ለ-4

***[3ለ-4]ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፤ ጌታ ሆይ፥ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥ የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ።***

▣ ***"ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው"*** ይህ ድብልቅ ጠቃሽ ነው የመዝ. 40፡5፤ 92፡5፤ 111፡2፤ 139፡14 እና ሆሴ. 14፡9።

▣ ***"ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ"*** ይህ በብኪ. በብዛት ጥቅም ላይ ከሚውሉት ሦስት የእግዚአብሔር መጠሪያዎች ጠቃሽ ነው (ዝከ. 1:8፤ 4:8፤ 11:7፤ 16:7)።

1. *"ጌታ"* ያህዌን የሚጠቅስ ነው፣ አዳኝ፣ ተቤዢ፣ የኪዳን አምላክ።
2. *"አምላክ" Elohim* (ኤሎሂምን) የሚጠቅስ ነው፣ ፈጣሪ፣ ሰጪ፣ እና ጠባቂ፣ በምድር ላይ የሚኖረውን ሕይወት ሁሉ።
3. *"ሁሉን የሚገዛ" El Shaddai* (ኤልሻዳይን) የሚያመለክት ነው፣ የአባቶች ስም፣ ለአብርሃም፣ ይስሐቅ፣ እና ያዕቆብ አምላክ (ዘጸ. 6፡3)።

ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች 1፡8 ላይ ተመልከት።

▣ ***"መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው"*** በቅዱሳን መከራ መካከል፣ ይህ አጽንዖት እጅግ ጠቃሚ ነው (ዝከ. 16፡7)። ይህ የሆሴዕ 14፡9 ጠቃሽ ይሆናል።

▣

***አአመመቅ፣ አየተመት***

***አእት፣ አኢመቅ*** ***"አንተ የአሕዛብ ንጉሥ"***

***አኪጀት*** ***"የቅዱሳን ንጉሥ ሆይ"***

ሦስት ዓይነት የተለያዩ የዚህ ቁጥር ትርጉሞች በዘመናዊ እንግሊዝኛ ይገኛሉ።

1. "የዘመናት ንጉሥ" (አመት፣ አዓት፣ የተእመቅ) እሱም በጥንታዊ ግሪክ የሚገኝ MSS ፒ[47]፣ ℵ*፣[2]፣ እና ሲ (1 ጢሞ. 1:17፤ 1 ሔኖክ 9፡4)
2. "የአሕዛብ ንጉሥ" (አየተመት፣ አእት፣ አኢመቅ) እሱም MSS ℵ[a]፣ ኤ፣ ፒ፣ እና አብዛኞቹ ቅጥልጣይ ጽሑፎች (ዝከ. ቁ. 4፤ ኤር. 10፡7)
3. "የቅዱሳን ንጉሥ" (አኪጀት) MSS 296፣ 2049 (ሜቲዝተር፣ ጽሑፋዊ ሐተታ፣ ገጽ 753) እሱም የቀድሞውን የላቲን ጽሑፍ ካለመረዳት የመጣ ነው

አማራጭ ቁ. 2 ዋነኛ ሊሆን ይችላል። ዩቢኤስ[4] "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (ከሞላ ጎደል ትክክል)።

**15፡4 "ጌታ ሆይ፥ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው?"** ይህ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ቅዱሱ ነው (ዝከ. 14፡7፤ ኤር. 10፡7-10)። እሱም ደኅንነትን ይሰጣል፣ ለማንም እና ለሁሉም፣ ለሚፈሩትና ስሙን ለሚያከብሩት።

▣ **"አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ።"** በብኪ. ትንቢት አሕዛብ ሁሉ አንድ ቀን ወደ ኢየሩሳሌም ይጎርፋሉ (መዝ. 22:27፤ 66:4፤ 86:9፤ ኢሳ. 2:2-4፤ 19:19-24፤ 27:13፤ 56:7፤ 66:19-24፤ ሚል. 1:11)። ዮሐንስ የብኪ. ትንቢትንና ምስያን ተጠቅሟል፣ ሁለንተናዊ ደኅንነትን ለመግለጽ። የብኪዋ ኢየሩሳሌም ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ሆናለች፣ የአማኝ አይሁድና አሕዛብ። ይህ መጽሐፍ በአይሁድ አልያም በአሕዛብ ላይ አያተኩርም፣ ብኪ. እንዳደረገው፣ ነገር ግን በአማኞች አልያም በማያምኑት ላይ ነው (ኢሳ. 45፡23ን ከፊሊ. 2፡9-11 ጋር አነጻጽር)። በሐተታው መጀመሪያ ላይ ያለውን ዋነኛ መግቢያ ተመልከት።

---

## *ራዕይ፡ 15፡5-8*

**[5]ከዚህም በኋላ አየሁ፥ የምስክርም ድንኳን መቅደስ በሰማይ ተከፈተ፥ [6]ሰባቱንም መቅሠፍት የያዙ ሰባቱ መላእክት ከመቅደሱ ወጡ፤ ከተልባ እግርም የተሠራ ጥሩ የጌጥ ልብስ ለበሱ ደረታቸውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጠቁ። [7]ከአራቱም እንስሶች አንዱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ የሚኖር የእግዚአብሔር ቍጣ የሞላባቸውን ሰባት የወርቅ ጽዋዎች ለሰባቱ መላእክት ሰጣቸው። [8]ከእግዚአብሔርም ክብርና ከኃይሉ ጢስ በመቅደሱ ሞላበት፥ የሰባቱ መላእክት ሰባቱ መቅሠፍት እስኪፈጸሙ ድረስ አንድ እንኳ ወደ መቅደሱ ይገባ ዘንድ አልቻለም።**

---

**15፡5 "የምስክርም ድንኳን መቅደስ በሰማይ ተከፈተ፥"** 4፡1 ላይ በሰማይ ደጅ ለዮሐንስ ተከፍቷል፣ 11፡19 ላይ የኪዳኑ ታቦት በመቅደሱ ተከስቷል፣ አማኞች ያዩት ዘንድ። አሁን ሞላው ሰማያዊ መቅደስ ተከስቷል (ዘጸ. 25፡9፣40፤ 38፡21፤ ዘኍ. 10:11፤ 17:7፤ ሐዋ. 7:44)። ይህ የብኪ. ጠቃሽ ዕብ. 8፡5 እና 9፡23 ላይ ዳብሯል። ይህ ጽሑፋዊ ምድብ ዘጸአትንና በበረሀ የመንከራተትን ጊዜ ይጠቀማል፣ እንደ ኋለኛ መቼት። ይህም ተምሳሌትነቱ ለሁለተኛውና ለመዳረሻው ዘጸአት ነው፣ ከባርነት ለመውጣት፣ (ከኃጢአት ባርነት)።

**15፡6 "ከተልባ እግርም የተሠራ ጥሩ የጌጥ ልብስ ለበሱ"** እነዚህ ሰባት መልአካዊ ሕላዌዎች የመጡት ከሰማያዊው መቅደስ ውስጠኛ ክፍል ነው፣ ይህም ሥልጣናቸውን ያሳያል፣ ከራሱ ከእግዚአብሔር መገኛ በመምጣታቸው። በራቢያዊ ይሁዲነት ሰባት ብርቱ መላእክት አሉ፣ የእግዚአብሔርን ዙፋን የሚከቡ፣ "የክብሩ መላእክት" ተብለው ይጠራሉ።

ልብሳቸውም የተገለጸው (1) "የተልባ እግር" (*linon* ወይም *linoun* [P[47]]) እሱም በካህናት የሚለበስ ዘጸ. 28፡4 (ዩቢኤስ[4]፣ "ለ" ደረጃ) ወይም (2) አመት ይህንን የሚተረጉመው በዔድን ገነት የመላእክት ልብስ በሚል ነው።

የጽሑፋዊ ትንተናው ሁለቱ መሠረታዊ ቅድመ ግምቶች (ዕዝል ተመልከት)፡ (1) እጅግ አስቸጋሪው ምንባብ ምናልባት ዋነኛው ነው እንዲሁም (2) የተለያዩትን የሚያብራራው ምንባብ ምናልባት ዋነኛው ሊሆን ይችላል፣ ከዚያም "ድንጋይ" ታሳቢ ምርጫ ነው።

▣ **"ደረታቸውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጠቁ"** ይህ ዳን. 10፡5 ላይ ከሚገኘው መልአክ ጋር ተመሳሳይ ነው ወይም ከራሱ ከክርስቶስ ጋር ራዕ. 1፡18 ላይ። እነዚህ በግልጽ እጅግ ኃይለኛ መላእክት ናቸው፣ እግዚአብሔርን ወይም ክርስቶስን የሚወክሉ።

**15፡7 "የእግዚአብሔር ቍጣ የሞላባቸውን ሰባት የወርቅ ጽዋዎች"** እነዚህ ዝርግ የወርቅ ጽዋዎች 5፡8 ላይ ተጠቅሰዋል፣ እዚያም የቅዱሳንን ጸሎት የያዙበት። በሙሉው ራዕይ ላይ መያያዝ አለ፣ በተሰደዱ ልጆቹ ጸሎት እና በማያምኑት ላይ በሚሆነው የእግዚአብሔር ቁጣ (7፡14 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

▣ **"ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ የሚኖር"** ይህ መሐላ ነው፣ ያህዌ በሚለው ቃል የሥር ፍቺ ላይ የተመሠረተ (ዘጸ. 3፡14)። ያህዌ ብቸኛው ሕያው ነው፤ የተቀሩት ሁሉ ከእርሱ ነው ሕይወት ያገኙት። ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች 1፡8 ላይ ተመልከት።
ለ"ከዘላለም እስከ ዘላለም" ልዩ ርዕስ 1፡6 ላይ ተመልከት።

**15፡8 "ከእግዚአብሔርም ክብርና ከኃይሉ ጢስ በመቅደሱ ሞላበት፥"** ይህ የተለመደው የብኪ ገለጻ ነው፣ ለእግዚአብሔር መገኘት (ዘጸ. 19:18፤ 40:34፤ 1 ነገሥ. 8:10-11፤ II ዜና. 5:13-14፤ ኢሳ. 6:4)። ይህ ለ*Shekinah* የክብር ደመና ጠቃሽ ነው፣ እሱም ለእስራኤል የእግዚአብሔርን መገኘት ይወክላል፣ በዘጸአት ጊዜ። ነገር ግን ከጽዋዎቹ ጋር ካለው ዐውደ-ጽሑፋዊ ትስስር፣ እሱ ሊያመለክት የሚችለው የዕጣንን መትረፍረፍ ነው፣ እሱም የእግዚአብሔርን ልጆች የፍትሕ ጥየቃ ጸሎት ይወክላል።

## ልዩ ርዕስ፡ ክብር

የመጽሐፍ ቅዱሳዊው የ "ክብር" ጽንሰ ሐሳብ ለመግለጽ ያስቸግራል። የአማኞች ክብር፣ ከእግዚአብሔር የሆነውን የክብር ወንጌል ማወቅ ነው እንጂ በራሳቸው አይደለም (ዝከ. 1፡29-31፤ ኤር. 9፡23-24)።

በብኪ በጣም የተለመደው ለዕብራይስጥ ቃል ለ "ክብር" (ከብድ kbd) በዋነኛነት ከጥንድ ሚዛኖች ጋር የተያያዘ የንግድ ቃል ነው ("ከባድ መሆን")። ከበድ የሚል ዋጋ ያለውና የሚጠቅም ነው። የብሩኅነት ጽንሰ ሐሳብ በቃሉ ላይ ይታከልበታል የእግዚአብሔርን ግርማ ለማሳየት (ዘጸ. 19፡16-18፤ 24፡17፤ ኢሳ. 60፡1-2)። እሱ ብቻውን ጠቃሚና የሚከበር ነው። እሱ ለወደቀው የሰው ልጅ ለመድረስ ግሩም ነው (ዘጸ. 19፡16-18፤ 24፡17፤ ኢሳ. 6፡5)። ያህዌ በእውነት ሊታወቅ የሚችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው (ኤር. 1፡14፤ ማቴ. 17፡2፤ ዕብ. 1፡3፤ ያዕ. 2፡1)።

"ክብር" የሚለው ቃል አሻሚነትም አለው፡

1. ከ"የእግዚአብሔር ጽድቅ" ጋር ተነጻጻሪ ነው፤
2. እሱም ምናልባትም የሚያጣቅሰው ከእግዚአብሔር ቅድስና ወይም "ፍጹምነት" ጋር ነው፤ ወይም
3. የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ከእግዚአብሔር አምሳል ጋር ያመላክታል (ዘፍ. 1፡26-27፤ 5፡1፤ 9፡6)፣ ነገር ግን ቆይቶ በዐመጽ ምክንያት ወደቀ (ዘፍ. 3፡1-22)። በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው በያህዌ መገኘት ከሕዝቡ ጋር በምድረ በዳ በሚዞሩበት ጊዜ፣ በዘጸ. 16፡7፣10፤ ሌዋ. 9፡23፤ እና ዘኍ. 14፡10።

▣ **"የሰባቱ መላእክት ሰባቱ መቅሠፍት እስኪፈጸሙ ድረስ አንድ እንኳ ወደ መቅደሱ ይገባ ዘንድ አልቻለም።"** ይህ ማለት የሚሆነው የእግዚአብሔር ቁጣ አንዴ ከተጀመረ እንደማያቆም ነው። ይህ ቁጣ ከሥነ-መለኮት አኳያ ከ16፡9 እና 11 ጋር ለማዛመድ አስቸጋሪ ነው፣ እሱም አንድምታው መቤዠት አሁንም ቢሆን ግቡ ነው፣ በጽዋዎቹ ላይ እንኳ ቢሆን ተስፋና ሐሳብ አለ፣ የወደቀው የሰው ልጅ፣ እሱም በእግዚአብሔር አምሳል የተሠራ፣ ተጸጽቶ ወደ እርሱ እንደሚመለስ!

**ራዕይ፡ 16፡1**

**[1]ለሰባቱም መላእክት። ሄዳችሁ የእግዚአብሔርን ቁጣ ጽዋዎች በምድር ውስጥ አፍስሱ የሚል ታላቅ ድምፅ ከመቅደሱ ሰማሁ።**

**16፡1 "ለሰባቱም መላእክት የሚል፣ ታላቅ ድምፅ ከመቅደሱ ሰማሁ።"** ራዕይ 15፡8 የሚያመለክተው ይህ ድምጽ የራሱ የእግዚአብሔር መሆኑን ነው። ይህ የመጨረሻው የመላእክት ምድብ የመጨረሻ ሥልጣን አለው፣ የእግዚአብሔርን ምድር ለማጥፋት። በብኪ የሞት መልአክና የጥፋት መልአክ የእግዚአብሔር አጋልጋዮች ናቸው የሰይጣን ሳይሆኑ።

▣ **"ሄዳችሁ የእግዚአብሔርን ቁጣ ጽዋዎች በምድር ውስጥ አፍስሱ"** ይህ የብኪ ተምሳሌት ነው ለእግዚአብሔር ፍርድ፣ በማያምኑ ሕዝቦች ላይ (መዝ. 79:6፤ ኤር 10:25፤ ሕዝ. 22:31፤ ሶፎ. 3:8)። ይህ ቃል ተዘውትሮ ጥቅም ላይ ውሏል፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ፣ ለእግዚአብሔር ቍጣ በማያምኑት ላይ (7:14፣ ዝከ. ቁ. 1፣2፣3፣4፣8፣10፣12፣17 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት) ምክንያቱም

1. በመሳደባቸው )ዝከ. ቁ. 9)
2. አማኞችን በማሳደዳቸው (ዝከ. ቁ. 6)
3. በአስቸጋሪነታቸው፣ ለንስሐ እምቢ በማለታቸው (ዝከ. 9:20-21፤ 16:9-12)

ለ"እግዚአብሔር ቍጣ" 7፡14 ላይ ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት።

**ራዕይ፡ 16፡2**

**[2]ፊተኛውም ሄዶ ጽዋውን በምድር ውስጥ አፈሰሰ፤ የአውሬውም ምልክት ባለባቸው ለምስሉም በሚሰግዱ ሰዎች ክፉኛ የሚነዘንዝ ቍስል ሆነባቸው።**

**16፡2** ይህ የመጀመሪያ ጽዋ ከአንደኛው የግብፃውያን ቁጣ ጋር እጅግ ይመሳሰላል (ዘጸ. 9፡10-11)። አንዳንዶች ይህንን የሚመለከቱት ከዘዳ. 28፡35 ጋር እንደሚዛመድ ነው፣ ይኸውም በሙሴ ኪዳን መታደሻ ላይ በርግማንና በበረከት ክፍል ያለ። እንደ ግብፃውያን መቅሠፍት እነዚህ የማያምኑትን እንደሚጎዱ ማስተዋል ይገባል።

**ራዕይ፡ 16፡3**

**[3]ሁለተኛውም ጽዋውን በባሕር ውስጥ አፈሰሰ፤ እንደ ሞተም ሰው ደም ሆነ፥ በባሕርም ከሚኖሩት ሕይወት ያለበት ነፍስ ሁሉ ሞተ።**

**16፡3-4** ሁለተኛውና ሦስተኛው ጽዋዎች ከሁለተኛውና ሦስተኛው መለከቶች ጋር ትይዩ ናቸው (ራዕ. 8፡8-11) እና ደግሞ የዘጸአትን መቅሠፍቶች ያንጸባርቃሉ፣ ዘጸ. 7፡17-21፤ መዝ. 78፡44።

**ራዕይ፡ 16፡4-7**

**[4]ሦስተኛውም ጽዋውን በወንዞችና በውኃ ምንጮች ውስጥ አፈሰሰ፤ እነርሱም ደም ሆኑ። [5]የውኃውም መልአክ። ያለህና የነበርህ ጌታ ሆይ፥ ቅዱስ ሆይ፥ እንዲህ ስለፈረድህ ጻድቅ ነህ፤ [6]የቅዱሳንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ ደምን ደግሞ አጠጥተሃቸዋል፥ የሚገባቸው ነውና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። [7]ከመሰዊያውም። አዎን፥ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው ብሎ ሲናገር ሰማሁ።**

**16፡5 "የውኃውም መልአክ።"** ይህ ሊያንጸባርቅ የሚችለው በይነ-ኪዳናዊ አይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ቃልን ነው፣ 1 ሔኖክ 66፡2። ራዕይ ላይ ነፋስን በሚመለከት አንድ መልአክ አለ (ዝከ. 7፡1) እና አንድ መልአክ ደግሞ እሳትን በሚመለከት (ዝከ. 14፡8)፣ ስለዚህ ውኃን በተመለከተ አንድ መልአክ መመልከት ያልተለመደ አይሆንም። እንደገናም፣ መልአካዊ ጣልቃ ገብነትና ድርጊቶች በበይነ-ኪዳናዊ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ የተለመዱ ናቸው። ራዕይን መተርጎም የሚኖርብን በገዛ ራሱ ብርሃን ነው፣ በራሱ ቀን፣ በእኛ ዘመናዊ ምዕራባዊ ሥነ-መለኮታዊ የፍጻሜ ዘመን ሥርዓቶች ሳይሆን።

▣ **"ጻድቅ ነህ"** ይህ ዘዳ. 32 (በተለይም ቁ. 5) ላይ ያለው የሙሴ መዝሙር ጠቃሽ ነው ወይም መዝ. 119፡137።

▣ **"ያለህና የነበርህ"** እንደ 1፡4፣8፤ 4፡8 የመጻኢ ነገር እንደሌለው ተገንዘብ፣ የወደፊት ጊ ባለመኖሩ ምክንያት (ዝከ. 11፡17)። ይህ መጨረሻው ነው! ይህ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው፤ ሦስትዮሹን መጠርያ ተገንዘብ የ1፡4ን። ከዚያም በኋላ ጊዜ አይኖርም! ፍጻሜ (ማለትም፣ *Parousia*) ራዕይ ላይ ብዙ ጊዜ ተገልጿል፣ ምዕራፍ 19 ሳይሆን። እያንዳንዳቸው ማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ የሚያበቁት በዳግም ምጽአቱና በታሪክ መዘጋት ነው። እኔ እንደማስበው የማጠቃለያ ንድፈ-ሐሳብ ራዕይን ለመተርጎም እጅግ የተሻለ ነው!

**16፡6 "ቅዱሳን"** ልዩ ርዕስ 5፡8 ላይ ተመልከት።

▣ **"ነቢያት"** ለብኪ ትንቢት ልዩ ርዕስ 10፡7 ላይ ተመልከት። ከሥር ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ የአዲስ ኪዳን ትንቢት

I. እሱ እንደ ብሉይ ኪዳን ትንቢት የመሰለ አይደለም (BDB 611)፣ እሱም ራቢያዊ ፍች እንዳለው ተመስጧዊ መገለጥ፣ ከያህዌ (ሐዋ. 3፡18፣21፤ ሮሜ 16፡26)። ቅዱስ ቃሉን ሊጽፉ የሚችሉት ነቢያት ብቻ ናቸው።
   ሀ. ሙሴ ለነቢይነት ተጠርቷል (ዘዳ. 18፡15-21)
   ለ. የታሪክ መጻሕፍት (ኢያሱ-ነገሥት [ከሩት በቀር] "ቀዳሚ ነቢያት" ተብለው ይጠራሉ (ሐዋ. 3፡24)።
   ሐ. ነቢያት የሊቀ-ካህኑን ስፍራ ይይዛሉ፣ ከእግዚአብሔር ለሚመጣ መልዕክት ምንጭነት (ኢሳይያስ-ሚልኪያስ)
   መ. ለዕብራውያን ቅዱስ ቃል ሁለተኛው ምድብ "ነቢያት" ናቸው (ማቴ. 5፡17፤ 22፡40፤ ሉቃስ 16፡16፤ 24፡25፣27፤ ሮሜ 3፡21)።

II. በአዲስ ኪዳን ጽንሰ-ሐሳብ በተለያዩ በርካታ መንገዶች ጥቅም ላይ ይውላል።
   ሀ. ወደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት እና ወደ ተመስጧዊ መልእክታቸው ማመልከት (ማቴ. 2፡23፤ 5፡12፤ 11፡13፤ 13፡14፤ ሮሜ. 1፡2)

ለ. ወደ አንድ ግለሰብ የሚያመለክት መልዕክት ከተጠቃለለው ቡድን ይልቅ (ማለትም፣ የብኪ ነቢያት በቅድሚያ ለእስራኤል ይናገራሉ

ሐ. ወደ ሁለቱም በማመልከት፣ ወደ መጥምቁ ዮሐንስ (ማቴ. 11:9፤ 14:5፤ 21:26፤ ሉቃስ 1:76) እና ኢየሱስ፣ እንደ እግዚአብሔር መንግሥት አዋጅ ነጋሪዎች (ማቴ. 13:57፤ 21:11፣46፤ ሉቃስ 4:24፤ 7:16፤ 13:33፤ 24:19)። ኢየሱስ ከነቢያት እንደሚልቅ ገልጿል (ማቴ. 11:9፤ 12:41፤ ሉቃስ 7:26)።

መ. ሌሎች ነቢያት በአኪ

1. የኢየሱስ የቀድሞ ሕይወት፣ በሉቃስ ወንጌል እንደተመዘገበው (ማለትም፣ የማርያም ማስታወሻዎች)
   ሀ. ኤልሳቤጥ (ሉቃስ 1:41-42)
   ለ. ዘካርያስ(ሉቃስ 1:67-79)
   ሐ. ስምዖን (ሉቃስ 2:25-35)
   መ. ሐና (ሉቃስ 2:36)
2. ውስጠ ወይራዊ ትንቢቶች (ቀያፋ፣ ዮሐንስ11:51)

ሠ. ወንጌልን ለሚያውጀው ለአንዱ የሚያመለክቱት (የማወጅ ጸጋ ዝርዝሮች በ1ቆሮ. 12:28-29፤ ኤፌ. 4:11)

ረ. በቤተ-ክርስቲያን እየተከናወነ ያለ ጸጋ አመላካች (ማቴ. 23:34፤ ሐዋ. 13:1፤ 15:32፤ ሮሜ 12:6፤ 1ቆሮ. 12:10፣28-29፤ 13:2፤ ኤፌ. 4:11)። ይህ አንዳንዴ ሴቶችን ሊያመለክት ይችላል (ሉቃስ 2:36፤ ሐዋ. 2:17፤ 21:9፤ 1ቆሮ. 11:4-5)።

ሰ. የፍጻሜውን ዘመን የራዕይ መጽሐፍ የሚያመለክት (ራዕ. 1:3፤ 22:7፣10፣18፣19)

III. የአዲስ ኪዳን ነቢያት

ሀ. እነሱ ተመስጧዊ ራዕዮችን አይተነብዩም፣ የብኪ ነቢያት ያደርጉ በነበረው ስሜት (ማለትም፣ ቅዱስ ቃሉ)። ይህ መግለጫ የሚሆን ነው፣ "እምነት" ለሚለው ሐረግ የተነሣ (ማለትም፣ በተጠናቀቀው ወንጌል እሳቤ) ጥቅም ላይ የዋለውም በሐዋ. 6:7፤ 13:8፤ 14:22፤ ገላ. 1:23፤ 3:23፤ 6:10፤ ፊሊጵ. 1:27፤ ይሁዳ 3፣20 ነው።

ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ግልጽ ነው፣ በይሁዳ 3 ጥቅም ላይ በዋለው ሙሉ ሐረግ፣ "ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ለአጠቃላይ ስለ ተሰጠ እምነት።" "አንድ ጊዜ ለአጠቃላይ" የተሰጠ እምነት የሚያመለክተው ወደ እውነቶች፣ ዶክትሪኖች (የእምነት መግለጫዎች)፣ ጽንሰ-ሐሳቦች፣ የክርስቲያን ርዕዮተ-ዓለም ትምህርቶችን ነው። ይህ ለአንድ ጊዜ የተሰጠ አጽንዖት ከሥነ-መለኮት አኳያ ለአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ያለውን ተመስጦ የሚወስን መጽሐፍ-ቅዱሳዊ መሠረት ሲሆን፣ እንዲሁም ኋለኛም ሆነ ሌሎች ጽሑፎች ራቢያዊ ተደርገው እንዲወሰዱ አይፈቅድም። በአዲስ ኪዳን በርካታ አሻሚ፣ ርግጠኛ ያልሆኑ፣ ጥርት ያላሉ ቦታዎች ይኖራሉ፣ ነገር ግን በእምነት የሚያጸኑት ለእምነትና ለተግባር "የሚያስፈልጉት" ማንኛውም ነገሮች ጥርት ባለ መልኩ በአዲስ ኪዳን መካተታቸውን ነው። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ "የመገለጥ ሦስት ማዕዘኖች" ተብሎ የሚታወቀው ጥርት ባለ መልኩ ተገልጿል።

1. እግዚአብሔር ራሱን በታሪክ ጊዜና ቦታ ገልጿል (ራዕይ)
2. እሱም የተወሰኑ ጸሐፊ ሰዎችን መርጧል፣ የእሱን ድርጊቶች ይመዘግቡና ያብራሩ ዘንድ (ተመስጦ)
3. እሱም የሰዎችን አእምሮና ልብ ለመክፈት መንፈሱን ሰጥቷል፣ እነዚህን ጽሑፎች ይገነዘቡ ዘንድ፣ በተወሰነ መልኩ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለደኅንነትና ለስኬታማ ክርስቶስን ለመምሰል ሕይወት በሚበቃ መጠን (ማብራሪያ)። የዚህ ነጥብ የሚሆነው ተመስጦ ለቃሉ ጸሐፊዎች መወሰኑን ነው። ሌሎች ሥልጣናዊ ጽሑፎች፣ ራዕዮች፣ ወይም መገለጦች አይኖሩም። ቅዱስ ቃሉ ታትሟል (ተዘግቷል)። ለእግዚአብሔር ተገቢውን ምላሽ እንሰጥ ዘንድ አስፈላጊ የሆነው እውነት አለን። ይህ እውነት በተሻለ የሚታየው በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች መስማማት ወይም በቅንና መልካም አማኞች ያለመግባባት ነው። ማንም ዘመናዊ ጸሐፊ ወይም ተናጋሪ ከቅዱስ ቃሉ ጸሐፊዎች በተሻለ ደረጃ መለኮታዊ መሪነት የለውም።

ለ. በአንዳንድ መንገዶች የአዲስ ኪዳን ነቢያት ከብኪ ነቢያት ጋር ይመሳሰላሉ።

1. መጭውን እውነቶች በመተንበይ (ጳውሎስ፣ ሐዋ. 27:22፤ አጋቦስ፣ ሐዋ. 11:27-28፤ 21:10-11፤ ሌሎችም በስም ያልተጠቀሱ ነቢያት፣ ሐዋ. 20፡23)
2. ፍርድን ያስታውቃሉ (ጳውሎስ፣ ሐዋ. 13:11፤ 28:25-28)
3. ተምሳሌታዊ ድርጊቶች፣ እነሱም አንድን ሁነት በጉልህ ያሳያሉ (ዝኪ. አጋቦስ፣ ሐዋ. 21፡11)

ሐ. እነሱ አንዳንድ ጊዜ በትንቢታዊ መንገድ የወንጌልን እውነት ያውጃሉ (ሐዋ. 11:27-28፤ 20:23፤ 21:10-11)፣ ይህ ግን ቀዳሚ ትኩረት አይደለም። ትንበያ በ1ቆሮንቶስ በመሠረቱ ወንጌልን ማካፈል ነው (ዝኪ. 14፡24፣39)።

መ. እነሱ የመንፈስ ወቅታዊ አግባቦች ናቸው፣ የእግዚአብሔርን እውነት ከወቅታዊውና ተግባራዊው አተገባበር ጋር፣ ስለ አዲሱ ሁኔታ፣ ባህል፣ ወይም ጊዜና ሰዓት የሚያመላክቱ (1ቆሮ. 14፡3)።

ሠ. እነሱም በጥንታዊው ጳውሎሳዊ አብያተ-ክርስቲያናት በንቃት ይፈጸሙ ነበር (1ቆሮ. 11:4-5፤ 12:28፣29፤ 13:29፤ 14:1፣3፣4፣5፣6፣22፣24፣29፣31፣32፣37፣39፣ ኤፌ. 2:20፤ 3:5፤ 4:11፤ 1ተሰ. 5:20) እንዲሁም በ*Didache* ተጠቅሰዋል (በኋለኞቹ አንደኛ ክፍለ-ዘመን ወይም በሁለተኛው ክፍለ-ዘመን፣ ቀኑ ርግጠኛ አይደለም) እናም በሁለተኛው እና ሦስተኛው ክፍለ-ዘመን በሰሜን አፍሪካ ሞንታኒዝም።

IV. የአዲስ ኪዳን ጸጋዎች አቁመዋልን?

ሀ. ይህን ጥያቄ መመለስ ያስቸግራል። ጉዳዩን ማብራራት ይበጃል፣ የጸጋን ዓላማ በመግለጽ። እነሱ የሚሉት የመነሻውን የወንጌል ስብከት ለማጽናት ነውን ወይስ ቀጣይነት ባለው መንገድ ለቤተ-ክርስቲያን አገልግሎትና ለጠፋው ዓለም ናቸውን?

ለ. አንዱ ጥያቄውን ለመመለስ መመልከት ያለበት የቤተ-ክርስቲያንን ታሪክ ነውን ወይስ አኪን ራሱን? የአዲስ ኪዳን መንፈሳዊ ስጦታዎች ጊዜያዊ ለመሆናቸው አመላካች ነገር የለም። 1ቆሮ. 13፡8-13ን ለመጠቀም የሚሞክሩት እነሱ፣ ይህንን ጉዳይ ለመመለስ የአንቀጹን ሥልጣናዊ ሐሳብ ያዛቡታል፣ ይኼውም፣ ሁሉም ነገር ከፍቅር በስተቀር ማለፉን የሚያስረግጠውን።

ሐ. እኔ ለመናገር የምፈተነው፣ ከአዲስ ኪዳን ወዲህ፣ የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ሳይሆን፣ ሥልጣን ያለው፣ አማኞች የግድ ማጽናት የሚኖርባቸው ጸጋዎቹ ቀጣይ መሆናቸውን ነው። ሆኖም፣ ባህል ትርጓሜ ላይ ተጽዕኖ እንዳለው አምናለሁ። አንዳንድ በጣም ግልጽ የሆኑ ጽሑፎች ከእንግዲህ ተግባራዊ አይሆኑም (ማለትም፣ ቅዱስ አሳሳም፣ የሴቶች መሸፋፈኛ መልበስ፣ የቤተ-ክርስቲያን ስብሰባዎች በቤት፣ ወዘተ...)። ባህል ጽሑፎች ላይ ተጽዕኖ ካለው፣ የቤተ-ክርስቲያን ታሪክስ እንዴ.ታ?

መ. ይህ እንዲያው ጥያቄ ነው፣ እሱም በትክክል መመለስ የማይቻል። አንዳንድ አማኞች ለ "መቋረጡ" ይወግናሉ፣ ሌሎች ደግሞ ለ"አለመቋረጡ"። በዚህ አካባቢ፣ እንደ ብዙዎቹ ትርጓሜያዊ ጉዳዮች፣ የአማኙ ልብ ቁልፍ ነው። አዲስ ኪዳን አሻሚና ባህላዊ ነው። አስቸጋሪ የሚሆነው የትኛው ጽሑፍ የባህል/ታሪክ ተጽዕኖ እንዳለበት እና የትኞቹ ለሁሉም ጊዜ እና ባህሎች እንደሆኑ መወሰን መቻሉ ላይ ነው (Fee እና Stuart's *How to Read the Bible for All Its Worth*፣ (መጽሐፍ ቅዱስን ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት ማንበብ እንደሚቻል) ገጽ 14-19 እና 69-77)። እዚህጋ ነው የነጻነት እና ኃላፊነት ማብራሪያዎች የሚሆኑት፣ እነሱም በሮሜ. 14:1-15:13 እና 1ቆሮንቶስ 8-10 የሚገኙና ወሳኞች ናቸው። እንዴት ጥያቄውን እንደምንመልስ በሁለት መንገድ ይጠቅማል።

1. እያንዳንዱ አማኝ ባለው ብርሃን በእምነት የግድ መጓዝ ይኖርበታል። እግዚአብሔር ልባችንንና የውስጥ ሐሳባችንን ይመለከታል።
2. እያንዳንዱ አማኝ ሌሎች አማኞች በራሳቸው የእምነት መረዳት እንዲራመዱ የግድ መፍቀድ ይኖርበታል። መቻቻል የግድ መኖር ይኖርበታል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ወሰኖች ውስጥ። እግዚአብሔር እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ይፈልጋል፣ እሱ እንዳደረገው ሁሉ።

ሠ. ጉዳዩን ለመጠቅለል፣ ክርስትና የእምነትና የፍቅር ሕይወት ነው፣ ፍጹም የሆነ ሥነ-መለኮት ሳይሆን። ከእሱ ጋር የሚኖር ግንኙነት፣ ይኸውም ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ተጽዕኖ የሚያሳድረው፣ ከተወሰነ መረጃ ወይም የእምነት መርሕ ከሆነ ፍጽምና ይልቅ እጅግ ጠቃሚ ነው።

**16፡7 "ከመሠዊያውም ሲናገር ሰማሁ"** የመሠዊያው ቀንዶች ቀደም ብለው ተናግረዋል፣ 9፡13 ላይ። ይህም የሚጠቅሰው (1) ከመሠዊያው በታች የነበሩትን ነፍሳት (ዝኪ. 6:9፤ 14:18) ወይም (2) የእግዚአብሔርን ልጆች ጸሎት (ዝኪ. 8፡3-5)። እሱም እንዲያው ዘወር ያለ ሰውኛ አጽንዖት ይሆናል።

▣ **"ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ"** 15፡3ለ ላይ ያለውን ማስታወሻ እና ልዩ ርዕስ 1፡8 ተመልከት።

▣ **"ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው"** ይህ የመዝ. 19:9፤ 119:137 ጠቃሽ ነው። ይህ ረጂ ማስገንዘቢያ ነው፣ በዚህ መሰሉ አስከፊ ስደት ውስጥ ላሉ ክርስቲያኖች (ዝኪ. 15፡4 እና 19፡2)። እግዚአብሔር አንድ ቀን ሁሉንም ነገር ያስተካክላል!

***ራዕይ፡ 16፡8-9***

**[8]አራተኛውም ጽዋውን በፀሐይ ላይ አፈሰሰ፤ ሰዎችንም በእሳት ልታቃጥል ተሰጣት። [9]ሰዎችም በታላቅ ትኵሳት ተቃጠሉ፥ በነዚህም መቅሠፍቶች ላይ ሥልጣን ያለውን የእግዚአብሔርን ስም ተሳደቡ፥ ክብርንም እንዲሰጡት ንስሐ አልገቡም።**

**16፡8** ይህ አራተኛ ጽዋ 6፡12 ላይ ካለው ከስድስተኛው ማኅተም ጋር ተመሳሳይ ነው እንዲሁም 8፡12 ላይ ካለው ከአራተኛው መለከት ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው።

▣ **"ሰዎችንም በእሳት ልታቃጥል ተሰጣት።"** ፀሐይ ሰውኛ ተደርጋለች፣ መዝ. 19:1-6 እንደተደረገችው። እግዚአብሔር ሰማያዊ አካላትን ይቆጣጠራል (ዘፍ. 1:14-19)። አማልክት አይደሉም። እነርሱ የሚሠሩት እንደ መልእክተኛ ነው (ተፈጥሮአዊ መገለጥ) እና ለወቅቶች ምልክቶች (ለአምልኮ)።

## ልዩ ርዕስ፡ እሳት (ቢዲቢ 77)

እሳት ሁለቱንም፣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ፍችዎች አሉት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ።

ሀ. አዎንታዊ/Positive

1. ያሞቃል (ኢሳ. 44:15፤ ዮሐንስ 18:18)
2. ብርሃን (ኢሳ.50:11፤ ማቴ. 25:1-13)
3. ያበስላል (ዘጸ. 12:8፤ ኢሳ. 44:15-16፤ ዮሐንስ 21:9)

4. ያጠራል (ዘኍ. 31:22-23፤ ምሳ. 17:3፤ ኢሳ. 1:25፤ 6:6-8፤ ኤር. 6:29፤ ሚል. 3:2-3)
5. ቅድስና (ዘፍ. 15:17፤ ዘጸ. 3:2፤ 19:18፤ ሕዝ. 1:27፤ ዕብ. 12:29)
6. የእግዚአበሔር አመራር(ዘጸ. 13:21፤ ዘኍ. 14:14፤ 1 ነገሥ. 18:24)
7. የእግዚአብሔር ኃይል ማስታጠቅ (ሐዋ. 2:3)
8. ጥበቃ (ዘካ 2፡5)

ለ. አሉታዊ / Negative
1. ያቃጥላል (ኢያ.6:24፤ 8:8፤ 11:11፤ ማቴ. 22:7)
2. ያጠፋል (ዘፍ. 19:24፤ ሌዋ. 10:1-2)
3. ቁጣ (ዘኍ. 21:28፤ ኢሳ. 10:16፤ ዘካ. 12:6)
4. ቅጣት (ዘፍ. 38:24፤ ሌዋ. 20:14፤ 21:9፤ ኢያ. 7:15)
5. የተሳሳተ መናፍስትነት ምልክት (የፍጻሜ) (ራዕ. 13:13)

ሐ. የእግዚአብሔር ቁጣ በኃጢአት ላይ የሚገለጠው በእሳት ዘይቤዎች ነው
1. የእሱ ቁጣ ይነዳል (ሆሴ. 8፡5፤ ሶፎ. 3፡8)
2. እሱም እሳትን ያወጣል (ነህ. 1፡6)
3. ዘላለማዊ እሳት (ኤር. 15:14፤ 17:4)
4. የመጨረሻው ፍርድ (ማቴ. 3:10፤ 13:40፤ ዮሐንስ 15:6፤ II ተሰ. 1:7፤ II ጴጥ. 3:7-10፤ ራዕ. 8:7፤ 16:8)

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳሉ በርካታ ዘይቤዎች (ማለትም፣ እርሾ፣ አንበሳ) እሳትም በረከት ወይም መርገም ሊሆን ይችላል፣ በዐውደ ጽሑፉ ላይ በመመሥረት ፡፡

**16፡9 "ክብርንም እንዲሰጡት ንስሐ አልገቡም።"** የእግዚአብሔር ቁጣ በማኅተሞቹና በመለከቶቹ ለመዋጀት ዓላማ ነው (ዝከ. 9:20-21፤ 14:6-7፤ 16:9፣11)፣ ምንም እንኳ አስቸጋሪው፣ ዐመጸኛው የሰው ልጅ ንስሐ ለመግባት እምቢ ቢልም። በጽዋዎቹ ላይ ንስሐ የመግባቱ ተስፋ አልፏል፣ ፍርድ ብቻ ነው የሚቀረው!

**ራዕይ፡ 16፡10-11**

**[10]አምስተኛውም ጽዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤ መንግሥቱም ጨለማ ሆነች ከስቃይም የተነሳ መላሶቻቸውን ያኝኩ ነበር፥ [11]ከስቃያቸውና ከቍስላቸውም የተነሳ የሰማይን አምላክ ተሳደቡ፥ ከስራቸውም ንስሐ አልገቡም።**

**16፡10 "አምስተኛውም ጽዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤"** የሰይጣን ዙፋን ለአውሬው ተሰጥቷል 11፡7 ላይ። ኃይሉም 13፡2 ላይ ተገልጿል። ይህ የሚያመለክተው የፍጻሜ ሰዓቱን ዋና ከተማ ነው፣ የአንድ መንግሥት ዓለም።

▣ ***"መንግሥቱ"*** ሰይጣን እግዚአብሔርን ያስመስላል። እግዚአብሔር መንግሥት እንዳለው ሁሉ፣ ሰይጣንም መንግሥት አለው። በእነዚህ በሚቀሩት ምዕራፎች ሁሉ እግዚአብሔር በክርስቶስ ያለው አገልግሎት በክፉው ሦስትዮሽ ማስመሰል ተደርጎበታል። የሰይጣን መንግሥት፣ በአውሬው በኩል ዓለም አቀፋዊ ሆኗል (ዝከ. 13፡14-17)።

▣ **"ጨለማ ሆነች"** ይህ የግብፃውያን መቅሠፍት ሌለኛው ጠቃሽ ነው (ዘጸ. 10:21-23)። እግዚአብሔር ብርሃንን ይቆጣጠራል (ዝከ. 8:12፤ 9:2፤ ዘፍ. 1:5፣14-18)።

**16፡11 "የሰማይን አምላክ ተሳደቡ፥"** እነዚህ ኢ-አማኒዎች የሥቃያቸውን ምንጭና ምክንያት ተገንዝበዋል፣ ነገር ግን ተጸጽተው ወደ ክርስቶስ አልተመለሱም! በግብፅ ላይ የነበሩት መቅሠፍቶች የተላኩት ሐሰተኞቹን የግብፅ ጣዖታት ለማጋለጥ ነበር፣ ግብፃውያንም የእስራኤልን አምላክ እንዲያምኑ ለማድረግ። ዘዳግም 27-28 ላይ ያሉት "ርግማኖች" የተላኩት የማያምኑትን አይሁድ ለመመለስ ነበር፣ ወደ እምነትና መታዘዝ። ፍርድ የመቤዠት ግብ አለው (ከመጨረሻው በስተቀር)!

"የሰማይ አምላክ" የሚለው መጠሪያ ቀደም ሲል 11፡13 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል የሚያንጸባርቀውም የባቢሎናውያንንና የፋርስን የመለኮት መጥሪያ ነው፣ እሱም በዳንኤል ተዘውትሮ ጥቅም ላይ የዋለ (ዝከ. በዳንኤል ላይ ሐተታዬን 2:18 www.freebiblecommentary.org ላይ ተመልከት)።

**ራዕይ፡ 16፡12-16**

**[12]ስድስተኛውም ጽዋውን በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤ ከፀሐይም መውጫ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሰናዳላቸው ውኃው ደረቀ። [13]ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጕንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኵሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤ [14]ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፥ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ። [15]እነሆ፥ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው። [16]በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ስፍራ አስከተቱአቸው።**

**16፡12 "ስድስተኛውም ጽዋውን በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤"** ይህ ወንዝ 9፡13-19 ላይ ተጠቅሷል፣ አጋንንታዊው ሠራዊት ወሰኖቹን ሲያቋርጥ፣ የሰው ልጅን ሊያሣቀይ። የኤፍራጥስ የውኃ ጋኖች የተስፋይቱ ምድር ሰማያዊ አዋሳኝ ላይ ነው፣ እንዲሁም የሮሜ ግዛት ውጫዊ ዳርቻ። የዚህ ዘይቤአዊ አጋንንታዊ ሠራዊት ታሳቢ ታሪካዊ መሠረት ፋርሳዊው የሥቃይ ስፍራ ነው። እነዚህ ኃይለኛ ጸረ-ሮማ ወራሪዎች ለሮማ ሠራዊት ሽብር ነበሩ።

▣ **"ውኃው ደረቀ"** በብኪ ተዘውትሮ የውኃ መድረቅ ታይቷል፣ እንደ እግዚአብሔር ድርጊት፣ እንደታየው

1. ቀይ ባሕር (ዘጸ. 14፡21)
2. ዮርዳኖስ ወንዝ (ኢያ. 3፡17)
3. በትንቢታዊ ጽሑፎች በብዙ ስፍራ (ኢሳ. 11፡15-16፤ 44፡27፤ ኤር. 51፡36፤ ዘካ. 10፡11)

ይህ ሥጋዊ ድርጊት ተምሳሌት የሚሆነው፣ እግዚአብሔር የፍጻሜ ዘመኑ ግጭት ከፍጻሜ እንዲደርስ መፍቀዱን ነው። እሱም ከሥነ-መለኮት አኳያ ከ2 ተሰ. 2፡6-7 ጋር ትይዩ ነው፣ "ምን/ማን ወሰን እንዳለው።"

▣ **"ከፀሐይም መውጫ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሰናዳላቸው"** በርካታ ውይይቶች ተካሂደዋል፣ "የፀሐይ መውጫ ነገሥታት" ቁ. 12 ላይ ያሉት ከ "የሞላው ዓለም መንግሥታት" ቁ. 14 ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ፡

1. አንድ ናቸው
2. ባላንጣዎች ናቸው (የኔሮ ዳግም መምጣት አፈታሪክ እና የፋርስ ሠራዊት)
3. የፀሐይ መውጫ ነገሥታት የሚያመለክቱት የእግዚአብሔርን ሠራዊት ነው

እንደዚያ ከሆነ፣ እሱ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባቢሎን ለመጥራቱ ጠቃሽ ዘይቤ ነው (ኢሳ. 41፡2፣25፤ 45፡1-3፤ 46፡11)። ከዐውደ-ጽሑፉ ማለት የሚቻለው የፀሐይ መውጫ መንግሥታት የእግዚአብሔር መሣርያ ናቸው፣ የአውሬውን ሠራዊት ያጠቁ ዘንድ (ማለትም፣ ታሪካዊ ጠቃሽ፣ ፋርሳውያን ሮምን እንዳጠቁ)። ሆኖም፣ ቁ.14 እና ምዕራፍ 19 እና 20 የሚያመለክቱት አንድ ብቻ የሰው ሠራዊት መኖሩን ነው፣ እግዚአብሔርን ለመቃወም የሚተባበር (መዝሙር 2፤ ኤር. 25፡15-26)።

**16፡13 "ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ"** ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው ሁለተኛው አውሬ (ዝከ. 13፡11) "ሐሰተኛ ነቢይ" ተብሎ የተጠራበት፣ ነገር ግን ከአሁን በኋላ በዚህ ስም ነው በየጊዜው የሚጠቀሰው (ዝከ. 16፡13፤ 19፡20፤ 21፡10)።

እነዚህ ሦስቱ የሚያመለክቱት ሰይጣናዊውን ሥሉስነት ነው፣ እሱም በሦስት ደረጃዎች የሚሸነፍ፡ ሁለቱ አውሬዎች በአርማጌዶን ሸለቆ (ዝከ. ቁ. 12-16) እና ሰይጣን በክርስቶስ የምድር ንግሥና መጨረሻ ላይ (ዝከ. 20፡7-10)።

▣ **"ጓጉንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት"** "ርኵስ" የሚለው ቃል በአኪ ወንጌላት ጥቅም ላይ የዋለው አጋንንትን ለማመልከት ነው። ለምን ጓጉንቸሮች እንደመሰሉ እጅግ አወዛግቧል፡

1. ይህ የግብፅ መቅሠፍቶች ሌለኛው ጠቃሽ ነው (ዘጸ. 8፡6)
2. በዞሮስትሬናዊነት ጓጉንቸሮች ወሰን ለሌለው ክፉ ተምሳሌቶች ናቸው
3. እነርሱም ንጹሕ ላልሆኑ እንስሳት አመላካች ናቸው (ሌዋ. 11፡10፣31)

## ልዩ ርዕስ፡ አጋንታዊ (ርኩስ መንፈስ)

ሀ. የጥንት ሰዎች ፍጥረት ሁሉ መንፈስ አለው ብለው ያምኑ ነበር፡፡ የሰውን የስብዕና ባህሪይ ከተፈጥሮ፣ የእንስሳት፣ እና የተፈጥሮአዊ ነገሮች ኃይላት ውጤት (ጋር ያዛምዱ/ያቆራኙ) ነበር፡፡ ሕይወት የሚገለጠው እነዚህ መንፈሳዊ አካላት ከሰው ልጅ ጋር ባላቸው ግንኙነት ነበር፡፡

ለ. ይህ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን በሰውኛ የመግለጽ ልማድ ሰዎችን ብዙ አማልክትን ወደ ማምለከት አመጣቸው፡፡ በተለምዶ አጋንንት (ጂኒ) አነስ ያሉ አማልክት ወይም በሥልጣን ተዋረድ ከሌሎች አማልክት አነስ ያሉ (ደግ ወይም ክፉ) በግለሰቦች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ተጽዕኖ አላቸው፡፡

1. መስጴጦሚያ፣ ብጥብጥ እና ግጭት
2. ግብፅ፣ ሥርዓትና ተግባር
3. ከነዓን፣ W. F. Albright's *Archaeology and the Religion of Israel*፣ Fifth Edition፣ ገጽ. 67-92 ይመልከቱ፡፡

ሐ. ብሉይ ኪዳን የአነስተኛ አማልክትን፣መላእክትን፣ ወይም አጋንንትን ትምህርት ይቃወማል፣ ምናልባት ምክንያቱ አንድ አምላክ ብቻ ከሚል ጠንካራ አቋሙ የተነሳ ነው (ዘፀ.8÷10፤9÷14፤15፡11፤ ዘዳ.4÷35፣39፤6፡4፤ 33÷26፤መዝ.35÷10፤71÷19፤86፡6፤ ኢሳ.46÷9፤ ኤር.10÷6-7፤ ሚክ. 7÷18)፡፡ የአህዛብን የውሸት አምላኮችን ይጠቅሳሉ (*Shedim*፣) ዘዳ 32፡17፣ መዝ 106፡37 ጥቂቶቹንም ይጠቅሳቸዋል፡፡

1. *Se'im* ሴኢም (ጣኦታት ወይም ጸጉራማ አጋንንት፣ ዘሌ.17÷7፤ 2ኛ ዜና 11÷15)
2. *Lilith* ሊሊስ (ሴት፣ የምትዳራ አጋንንት፣ ኢሳ.34÷14)
3. *Mavet* ማቬት (ለሞት የእብራውያን ቃል ሆኖ የከነዓንን አምላክ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሎአል፣ *Mot (ሞት)*፣ ኢሳ.28÷15፣18፤ ኤር. 9÷21፤ እና ምናልባትም ዘዳ.28÷22)፡፡

4. *Resheph* ሬሼፍ (መቅሰፍት፣ ዘዳ. 33÷29፤መዝ.78÷48፤ ዕብ.3÷5)
5. *Dever* ዴቨር (ቸነፈር፣ መዝ.91÷5-6፤ ዕብ.3÷5)
6. *Az'azel* አዛዜል (ስሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም፣ ነገር ግን ምናልባት የበረሃ አጋንንት ወይም የቦታ ስም ሊሆን ይችላል፣ ዘሌ.16÷8፣10፣26)

(እነዚህ ምሳሌዎች የተወሰዱት ከኢንሳይክሎፒዲያ ጁዳካ፣ ቮልዩም 5፣ ገጽ.1523 ነው፡፡)

ሆኖም በብ.ኪ. ከእግዚአብሔር ዘንድ ሁለትዮሽ ወይም መልአካዊ ነጻነት የለም፡፡ ሠይጣን የእግዚአብሔር (ያሕዌ) ባሪያ ነው (ኢዮብ 1-3፤ ዘካርያስ 3)፣ ነፃ አይደለም፣ ራሱን በራሱ የሚመራ ጠላት እንጂ (A.B. Davidson፣ *A Theology of the Old Testament*፣ pp.300-306)፡፡

መ. አይሁዳዊነት ያደገው በባቢሎኒያን ምርኮ ጊዜ (ቅ.ክ. 586-537) ነው፡፡ ሁኔታው በሥነ መለኮት ረገድ በፋርስ በሰው ምሳሌ በተመሰለ ሁለትዮሽን በሚያራምድ ዞሮአስቴሪያኒዝም በተባለ የፋርስ ኃይማኖት፣ ማዘዳ ወይም ኦረማዝድ የተባለ ከፍ ያለ መልካም አምላክ እና አሀሪማን በተባለ ክፉ ተቃዋሚ ተጽዕኖ ውስጥ ወድቋል፡፡ ይህ ከድህረ ምርኮ በኋላ በአይሁዳውያን ውስጥ በያህዌ እና በመልአክቱ እና በሰይጣን እና መልአክቶቹ ወይም አጋንንት መካከል በሰው ምሳሌ የሆነ ሁለትዮሽ አስተሳሰብ እንዲኖር አድርጓል፡፡

በአይሁዳውያን ሥነ መለኮት የክፋት ሰውኛ አገላለጽ ዘ ላይፍ ኤንድ ታይምስ ኦፍ ጂሰስ ዘ መሳያ በሚለው የበአልፍሬድ ኤዴረሼይም ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተብራራ እና የተያዘ ነው (Alfred Edersheim፣ *The Life and Times of Jesus the Messiah*፣ vol. 2፣ appendix XIII፣ pp.749-863 and XVI፣ pp.770-776)። አይሁዳውያን ክፋትን በሦስት መንገዶች በሰውኛ አገላለጽ ይገልጹታል፡፡

1. ሰይጣን
2. ክፉ አሳብ ((*yetzer hara*) የተዜር ሃራ በሰው ልጅ ውስጥ
3. የሞት መልአክ

ኤዴርሼይም እነዚህን ነገሮች እንደዚህ ይገልጻቸዋል (1) ከሳሽ፤ (2) ፈታኝ፤ እና (3) የሚያሰቃይ (vol.2፣p.756)፡፡ በድህረ ምርኮ አይሁዳዊነት ሥነ መለኮት እና በአ.ኪ. ጽሑፎች መካከል ክፋትን በተመለከተ ልዩነቶች አሉ፡፡

ሠ. የክፋት መንፈሰዊ ፍጥረቶች በሰው ላይ እና በእግዚአብሔር/ያህዌ (በአይሁዳዊነት ሰይጣን የሰው ልጆች ጠላት ነበረ፤ ለእግዚአብሔር ግን አይደለም) ላይ ያለቸውን የተቃውሞ ሕልውና በተመለከተ አ.ኪ.፣በተለይ ወንጌሎች፣ያረጋግጣሉ፡፡ እነርሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ፣ ሕግ እና መንግሥቱን ይቃወማሉ፡፡ ኢየሱስ እነዚህን አጋንንታዊ ፍጡራንን ደግሞም (1) ርኩስ መናፍስት (ሉቃስ 4÷36፤6÷18) ወይም (2) ክፉ መናፍስት (ሉቃስ 7÷21፤8÷2) ተጋፍጠአል ደግሞም ከሰዎች ውስጥ አስወጥቶአቸዋል፡፡ ኢየሱስ በሕመም (አካላዊ እና አእምሮዋዊ) እና

በአጋንንታዊ ሥራ መካከል ያለውን ልዩነት ግልጽ አድርጎአል፡፡ እርሱ በእውቀቱና እነዚህን ክፉ መናፍት ከሰዎች በማስወጣ ኃይሉንና መንፈሳዊ እውቀቱን አሳይቷል፡፡ እነርሱ ኢየሱስን ያውቁታል ስለእርሱም ለመናገር ይሞክራሉ፣ ነገር ግን እርሱ የእነርሱን ምስክርነት አይቀበልም ነበር፣ ዝም እንዲሉም ያዛቸው ነበር፣ ከሰዎችም ያባርራቸው ነበር፡፡ አጋንንት ከሰዎች እየወጡ ሲሄድ የሠይጣን መንግሥት መሸነፉን ያመለክታል፡፡

በጣም የሚያስደንቀው ነገር በዚህ ጉዳይ ላይ የአ.ኪ. ሐዋሪያዊ ደብዳቤዎች/ጽሑፎች ብዙ የሚሉት ነገር የላቸውም፡፡ አጋንንትን ማስወጣን በፍጹም እንደ ጸጋ ሥጦታ አልተቆጠረም፣ ወጥ የሆነ ዘዴ ወይም አሠራር ለወደፊቱ የአገልጋዮች ትውልዶች ወይም አማኞች አልተሰጠም፡፡

ረ. ክፋት መኖሩ እውነት ነው፤ ክፉ አካላዊ ነው፤ ክፉ አለ፡፡ የክፋት መነሻውም ሆነ ዓላማው አልተገለጠም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የክፋትን መኖር ያረጋግጥ እና ተጽእኖውን በቁጣ ይቃወማል፡፡ በእውነት ውስጥ የመጨረሻ ሁለትነት (ultimate dualism) የለም፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ተቆጣጣሪ ነው፤ ክፉ ተሸንፎአል ተፈርዶበታልም እናም ከፍጥረት ይወገዳል፡፡

ሰ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ክፉውን መቃወም አለበት (ያዕ.4፡7)፡፡ በክፉ ቁጥጥር ውስጥ ሊሆኑ አይችሉም (1ኛ ዮሐ. 5፡18)፣ ነገር ግን በክፉ ሊፈተኑና ምስክርነታቸው እና ተጽዕኖአቸው ሊበላሽ ይችላል (ኤፌ.6፡10-18)፡፡ ክፋት በክርስቲያን ንጽረተ ዓለም ውስጥ የተገለጠ ነው፡፡ ዘመናዊ ክርስቲያኖች ክፋትን እንደገና ለመግለጽ መብት የላቸውም (የሩዶልፍ ቡልትማን ክፋትን እንደፈለጉ የመተርጎም ትምህርት-ዴሚቴዎሎጂይዚንግ)፤ ክፋትን የማንነት ክፍል አርጎ በመውሰድ ጤናማውን የሰውነት ባሕሪ የሚያሳጣ ትምህርት (የፓውል ቲሊክ የማህበረሰብ አካላት ትምህርት)፣ ሥነ ልቦናዊ በሆኑ ቃልት ጨርሶ ለመተርጎም ያዳግታል (ሲግመንደ ፍሪውድ)፡፡ ትጽዕኖው ይኖራል፣ ግን ተሸንፎአል፡፡ አማኞች በክርስቶስ ድል ውስጥ መመላለስ አለባቸው!

**16፡14 "ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና"** እነዚህ ምልክቶችና ድንቆች የማያምኑትን ሁሉ እንዳሳቷቸው መገንዘብ እጅግ አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን አንዳንዶቹን የእግዚአብሔርን ልጆች እንኳ (ዝክ. 13፡13፤ ማቴ. 24፡24፤ ማርቆስ 13፡22፤ 11 ተሰ. 2፡9-11)። ይህ የመጨረሻ ጽሑፋዊ ምድብ (ጽዋዎቹ) በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ምን እንደሚሆን እና በምድር በሚኖሩት ላይ ምን እንደሚሆን ማወዳደሪያ ነው። ክርስቶስ የእውነትን፣ የጽድቅን፣ እና የምሕረትን ቃል ይናገራል፣ በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት፣ ነገር ግን አጋንንታዊው የጓኍንቸር መናፍስት ውሸትን ይናገራሉ፣ እንዲሁም አሕዛብን ለጦርነት ይሰበስባሉ።

▣ ***"ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ"*** ይህ ሊሆን የሚችለው የመዝ. 2፡2 ጠቃሽ ነው፣ እሱም የእነዚህ የራዕይ የመጨረሻ ምዕራፎችን ምስያ ያዋቀረ፡፡

▣ ***"በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው"*** የመጨረሻው ቀን ገለጻ የሚገኘው 6፡2-8፤ 11:7-10፤ 12:17፤ 16:14፤ 17:14፤ 19:19 እና 20:8 ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚወክሉት አንድን ጦርነት ከተለያየ አተያይ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል (ማለትም፣ ትይዩነት)፡፡

**16፡15** ይህ ቅንፋዊ ሐረግ የክርስቶስን ቃል ይዟል፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማበረታታትና ለማስጠንቀቅ የታቀደ፡፡ ይህ ለአማኞች ከሚሆኑ ሰባት በረከቶች ሦስተኛው ነው (ዝክ. 1:3፤ 14:13፤ 16:15፤ 19:9፤ 20:6፤ 22:7፣14)፡፡

▣ ***"እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ"*** እነዚህ የኢየሱስ ቃላት (ማቴ. 24:43-44፤ ሉቃስ 12:39-40) ቀደም ሲል ራዕ. 3፡3 ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል፣ እንዲሁም 1 ተሰ. 5፡2 እና 2 ጴጥ. 3፡10 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ እሱም የሚያመለክተው በማናቸውም ጊዜ፣ በድንገት ክርስቶስ ለፍርድ እንደሚመጣ ነው በ*Parousia* (ዳግም ምጽአት)፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ዳግም ምጽአቱ

ይህ በጥሬው "እስከ ዳግም ምጽአት" ፍችው "መገኘት" ነው፣ ጥቅም ላይ የሚውለውም ለንጉሣዊ ጉብኝት ነው፡፡ ሌሎቹ የአኪ ቃላት፣ ለዳግም ምጽአቱ ጥቅም ላይ የሚውሉት (1) *epiphaneia፣ "ፊት ለፊት መከሰት"*፤ (2) *apokalupis*፡ *"ያለ መጋረጃ"*፤ እና (3) "የጌታ ቀን" እና የዚህ ሐረግ መለያየት፡፡

አኪ የተጻፈው በብኪ የዓለም አተያይ ውስጥ ነው፣ የሚያስረግጠውም

1. የአሁኑን ክፉ፣ ዓመጸኛ ዘመን
2. የሚመጣውን የጽድቅ ዘመን
3. ይህም የሚመጣው በመንፈስ በኩል በመሲሑ ሥራ ነው (የተቀባው)

ቀጣይነት ያለው መገለጥ ሥነ-መለኮታዊ ግምት ያስፈልጋል፣ ምክንያቱም የአኪ ደራስያን የእስራኤልን ተስፋ በመጠኑ ስላሻሻሉት፡፡ ከወታደራዊው፣ ብሔር-ተኮር (እስራኤል) የመሲሑ መምጣት ምትክ ሁለት ምጽአቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ምጽአት የመለኮት ሥጋ መልበስ ነው፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ መጸነስና መወለድ፡፡ እሱ የመጣውም ወታደራዊ ባልሆነ፣ ፍርዳዊ ባልሆነ "መከራን የሚቀበል አገልጋይ" ሆኖ ነው፣ የኢሳይያስ 53፤ ደግሞም በአህያ ውርንጫ ላይ የሚቀመጥ (የጦር ፈረስ ወይም የንጉሥ በቅሎ ሳይሆን)፣ የዘካ. 9፡9፡፡ የመጀመሪያው ምጽአቱ አዲሱን መሲሐዊ ዘመን አስመርቋል፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር፡፡ በአንድ መልኩ መንግሥቱ እዚህ ነው፣ ግን ደግሞ በሌላ መልኩ አሁንም ሩቅ ነው፡፡ ይህ ተቃርኖ ነው በሁለቱ የመሲሑ ምጽአቶች፣ በሆነ መልኩ ሁለቱን የአይሁድ ዘመናት፣ ያልታዩትን የሚያነባብሩት፣ ወይም ቢያንስ ከብኪ ግልጽ አይደሉም፡፡ በእውነታው፣ ይህ ድርብ ምጽአት አጽንዖት የሚሰጠው የያህዌን ቁርጠኝነት ነው፣ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን (ዘፍ. 3:15፤ 12:3፤ ዘጸ. 19:5 እና የነቢያት ስብከት፣ በተለይም ኢሳይያስ እና ዮናስ)፡፡

ቤተ ክርስቲያን የብኪን ትንቢት መፈጸም አትጠባበቅም፣ ምክንያቱም አብዛኞቹ ትንቢቶች የመጀመሪያ ምጽአቱን ስለሚጠቅሱ *(መጽሐፍ ቅዱስን ከነሙሉ ጠቀሜታው ስለማንበብ፡ ገጽ* 165-166)፡፡ አማኞች ተስፋ የሚያደርጉት የትንሣኤውን የነገሥታት ንጉሥ እና የጌቶች ጌታ፣ ተስፋ የተደረገበትን የአዲሱን የጽድቅ ዘመን ታሪካዊ ፍጻሜ በምድር ላይ ነው፣ በሰማይ እንደሆነ (ማቴ. 6፡10)፡፡ የብኪ መግለጫዎች ትክክለኛ ያልነበሩ አልነበሩም፣ ነገር ግን ያልተጠናቀቁ እንጂ፡፡ እሱ ተመልሶ ይመጣል ነቢያት እንደተነበዩት፣ በያህዌ ኃይልና ሥልጣን፡፡

ዳግም ምጽአት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም፣ ነገር ግን ጽንሰ-ሐሳቡ ርዕዮተ-ዓለሙንና የሙሉውን አኪ ቅንብብ (ፍሬም ወርክ) ይቀርጸዋል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም በትክክል ያስቀምጠዋል፡፡ በእግዚአብሔርና በአምሳሉ በተፈጠረው መካከል ያለው ወዳጅነት ይመለሳል፡፡ ክፋው ይፈረድበታል ይወገዳልም፡፡ የእግዚአብሔር ዓላማ የሚወድቅ አይሆንም፣ አይችልምም!

▣ ***"ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው"*** ይህ ከሰባቱ በረከቶች ሦስተኛው ነው፣ ለታማኝ አማኞች የተሰጠ (ዝክ. 1:3፤ 14:13፤ 16:15፤ 19:9፤ 20:6፤ 22:7፣14)፡፡ ይህም ከሞላ ጎደል የፍጻሜ ዘመን ማስጠንቀቂያ ማጠቃለያ ነው ማርቆስ 13:33-37፤ ሉቃስ 12:37 ላይ የሚገኝ፡፡ ይህ ቁጥር ከስፍራው ውጭ መሆን ይገባዋል፣ የቤተ-ክርስቲያን ምሥጢራዊ መነጠቅ ንድፈ-ሐሳብ፣ ከስደቱ ጊዜ በፊት መሆኑ ከተረጋገጠ፡፡ እንግዲያስ ኢየሱስ ስለ ማን ነው የሚናገረው? ማቴ. 24፡37-42 በዌብ ሳይት ተመልከት www.freebiblecommentary.org ላይ፡፡

▣ ***"ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ"*** ይህ የራዕ. 3፡18 ጠቃሽ ይሆናል፡፡ በብኪ ራቁትነት የፍርድ ተምሳሌት ነው (ሕዝ. 23:29፤ ሆሴ. 2:3፤ አሞጽ 2:16፤ ሚክ. 1:8)፡፡ ሆኖም፣ እሱ ደኅንነት ማጣትን አያመለክትም፣ ነገር ግን በድርጊታቸውና በኢየሱስ ዳግም ምጽአት የሕይወት ስልታቸው እምነት ጉድለት ላለባቸውና ለሚያፍሩ ክርስቲያኖች ነው፡፡ የኢየሱስ እንደ ፈራጅና ድል አድራጊ ሆኖ መምጣት፣ እሱንም አይሁድ የመሲሑን መመለስ በትክክል እንደሚጠብቁት፣ 19፡ 11-16 ላይ ተገልጿል፡፡

**16፡16 "እነርሱንም አንድ ላይ አስከተቷቸው"** ይህ 20፡8 ላይ ተደግሟል፡፡

▣
**አአመመቅ** **"በዕብራይስጥም ሐርማጌዶን ይባላል"**
**አኪጀት፣ አኢመቅ** **"በዕብራይስጥ አርማጌዶን"**
**አየተመት** **"በዕብራይስጥ ሐርማጌዶን ይባላል"**
**አእት** **"በዕብራይስጥ አርማጌዶን"**

ይህ ቃል በተለያዩ ፊደላት ነው በበርካታ የግሪክ ጽሑፎች ላይ የተጻፈው። ይህንን ስም ለመግለጽ በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ (እሱም በዕብራይስጥም ሆነ በግሪክ ሥነ-ጽሑፍ የትም ቦታ የማይገኝ)።

1. እሱ የሚጠቅሰውም "የሜጊዶ ተራራን" ነው፣ በምናሴ ነገድ ስፍራ በስተሰሜን ያለች ከተማ፣ በኮረብታ ላይ የተገነባች
2. እሱ የሚያመለክተው "የሜጊዶ ከተማን" ነው፣ ችግሩ ግን ይህ በትክክል የከተማዋ መጠሪያ ፊደል አለመሆኑ ነው
3. እሱ "የጉባኤ ተራራ" ተብሎ ይተረጎማል፣ ኢሳ. 14፡13 ላይ ያለው፣ የሚጠቅሰውም የመለኮት የመዳረሻ ተራራ ነው፣ ሰይጣን የሚያጠቃው
4. እሱ የሚጠቅሰው ሞላውን የተስፋ ምድር ነው ("የእስራኤል ተራራ" ሕዝ. 38፡8፣20፣21፤ 39፡2፣4፣17)
5. እሱ የሚጠቅሰው "ፍሬአማውን ተራራ" ነው፣ እሱም ኢየሩሳሌምን ተምሳሌታዊ የሚያደርግ፣ የእነዚህ የመጨረሻው ዘመን የበርካታ የፍጻሜ ውጊያዎች ስፍራ፣ በመልካምና በክፉ መካከል የሚደረጉ ((የኢዩኤል ትንቢት)
6. "የሜጊዶ" የሥር ፍቺ "መቁረጥ ወይም ማጥቃት" ሊሆን ይችላል፣ ይህንንም "የማጥፊያ ተራራ" ብሎ በመጥቀስ፣ ኤር. 51፡25፣ የሮም መውደቅ ተምሳሌት።

ዮሐንስ ታዋቂ ከተማ መርጦ ፊደላቱን በመጠኑ ለውጦታል (ሜቲዝገር፣ *ጽሑፋዊ ሐተታ*፣ ገጽ 755)። ይህም 7፡5-8 ላይ ካለው ትክክል ያልሆነ የአስራ ሁለቱ ነገዶች አገላለጹ ጋር ተመሳሳይ ነው፣ ተምሳሌታዊ ተፈጥሯቸውን ለማሳየት። ይህ ተምሳሌታዊ ትርጓሜ በተጨማሪ ይታያል፣ "በዕብራይስጥ" በሚለው ሐረግ አጠቃቀም፣ እሱም ተምሳሌታዊነትን የሚያመለክት፣ እንደ 9፡11። ርግጥ ነው፣ የኢዝራኤል ሸለቆ ወይም የኢስድራሎን ሜዳ የአብዛኞቹ የብኪ ውጊያዎች ስፍራ ነበር (መሳ. 5፡19-21፤ II ነገሥ. 9፡27፤ 23፡29-30፤ II ዜና. 35፡22፤ ዘካ. 12፡11)። ይህ የሜሶፖታሚያ ኃይላት ሰሜናዊ የመውረሪያ መስመር የክፉው ባህላዊ ተምሳሌት ሆኗል (ኢሳ. 14፡31፤ ኤር. 1፡13-14፤ 4፡6፤ 10፡22፤ 46፡20-24፤ 47፡2-7፤ 50፡3፣9፣41፤ 51፡48፤ ሕዝ. 38፡6፣15፤ 39፡2)።

## ራዕይ፡ 16፡17-21

**[17]ሰባተኛውም ጽዋውን በአየር ውስጥ አፈሰሰ፤ ከመቅደሱም ውስጥ። ተፈጽሞአል የሚል ታላቅ ድምጽ ከዙፋኑ ወጣ። [18]መብረቅና ድምጽም ነጎድጓድም ሆኑ፥ ትልቅም የምድር መናወጥ ሆነ፤ ሰው በምድር ከተፈጠረ ጀምሮ እንዲህ ያለ ታላቅ መናውጥ ከቶ አልነበረም፤ ከሁሉ በለጠ። [19]ታላቂቱም ከተማ በሦስት ተከፋፈለች፥ የአሕዛብም ከተማዎች ወደቁ። ታላቂቱም ባቢሎን የብርቱ ቍጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች። [20]ደሴቶችም ሁሉ ሸሹ ተራራዎችም አልተገኙም። [21]በሚዛንም አንድ ታላንት*ፍ1* የሚያህል ታላቅ በረዶ በሰዎች ላይ ከሰማይ ወረደባቸው፤ ሰዎቹም ከበረዶው መቅሰፍት የተነሳ እግዚአብሔርን ተሳደቡ፥ መቅሰፍቱ እጅግ ታላቅ ነውና።** (አንድ ታላንት ሦስት ፈለሱላ የሚያህል ነው)

**16፡17 "ሰባተኛውም መልአክ ጽዋውን በአየር ውስጥ አፈሰሰ"** ይህ የሰይጣንን መንግሥት አመላካች ይሆናል፣ ኤፌ. 2፡2 ላይ እንደተመለከተው። ከምድር በላይ ያለው ዓየር የክፉ ግዛት ተደርጎ ይወሰድ ነበር፣ በአንደኛው ክፍለ-ዘመን ዓለም። ከክፉው ጋር የሚደረገው ጦርነት ተጠናቋል (ዝከ. 17ሐ-21)።

**16፡18** ይህ ምስያ በርካታ ጊዜ ራዕይ ላይ ተገልጿል (ዝከ. 4፡5፤ 8፡5፤ 11፡19፤ 16፡18)።

**16፡19 "ታላቂቱ ከተማ"** አንዳንዶች ይህንን የሚመለከቱት ለኢየሩሳሌም ማጣቀሻ ነው በ11፡8 ምክንያት። ሆኖም፣ እኔ እንደማስበው 11፡8 እንኳ የሮም ተምሳሌት ነው (ዝከ. 11፡8፤ 16፡19፤ 17፡18፤ 18፡10፣18-19፣21)። ሮም የምትወሰደው እንደ ታላቂቱ ባቢሎን ጋለሞታ ነው (ዝከ. 14፡8) እሷም የጥንቱ አምልኮ የማያውቀው ማኅበረሰብ መቀመጫ። በዮሐንስ ጊዜ ሮም የዛ የአጼ አምልኮ ማዕከል ነበረች፣ ቤተ ክርስቲያንን የምታሳድድ። በፍጻሜ ዘመን ጊዜ የክርስቶስ ተቃዋሚ ሌላዋ የዓለም ከተማ ልትሆን ትችላለች። ዮሐንስ መግለጹን ቀጥሏል የወደቀውን ሰው፣ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ መንግሥት መቀመጫ ጥፋትን፣ ምዕራፍ 17-18 ላይ።

▣ **"በሦስት ተከፋፈለች"** ይህ ሊሆን የሚችለው የሕዝቅኤል 5 ጠቃሽ ነው፣ እሱም ፍጹም ሽንፈትን የሚገልጽ።

▣ **"የአሕዛብ ከተማዎች ወደቁ"** ይህ የሚያሳየው የወደቀው ሰው መንግሥታት ያልሰመረ ኅብረትን ነው፣ እነርሱም በእግዚአብሔርና በመሲሑ ላይ የተነሡ (መዝሙር 2)። 10፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ታላቂቱም ባቢሎን በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች"** "እግዚአብሔርም አሰበ" የሚለው ሐረግ ዘወትር የእግዚአብሔር ፍርድ ነው (ዝከ. 18፡5፤ 19፡15)። ይህ የተለየ የፍርድ ጽዋ ቀደም ሲል 14፡10 ላይ ተገልጿል።

▣ **"የብርቱ ቍጣው ወይን ጠጅ"** ስካር የብኪ ዘይቤ ነው፣ ለእግዚአብሔር ፍርድ (መዝ. 60፡3፤ 75፡8፤ ኢሳ. 51፡17፣22፤ ኤር. 25፡15-16፣ 27-28፤ ልዩ ርዕስ 14፡10 ላይ ተመልከት)።

"ቁጣ" *orgē* የሚለው ቃል ነው። 7፡14 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

**16፡20 "ደሴቶችም ሁሉ ሸሹ"** ይህ ከስድስተኛው ማኅተም ጋር ተመሳሳይ ነው (ዝከ. 6፡14)።

▣ **"ተራራዎችም አልተገኙም"** እነዚህ የብኪ ተምሳሌታዊ ሐረጎች ናቸው፣ ጽኑ ቁጣ ላለባቸው የፍጻሜ ዘመን ሁነቶች (መዝ. 97፡5፤ ሚከ. 1፡4፤ ናሆ. 1፡5)።

**16፡21 "ታላቅ በረዶ"** በረዶ ዘወትር የእግዚአብሔር ፍርድ ነው (ኢያ. 10፡11፤ ኢሳ. 28፡2)። ይህም ሌለኛው የግብፅ መቅሠፍት ዓይነት ነው (ዘጸ. 9፡23-24)። ሕዝ. 38፡22 ላይ በረዶ በፍጻሜ ዘመን የእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። የበረዶው ክብደት ይለያያል።

▣ **"አንድ ታላንት የሚያህል"** ይህ በጥሬው "የታላንት ክብደት" ነው። የታላንት ክብደቶች በጥንት ቅርብ ምስራቅ ከ45 እስከ 138 ፓውንድ ይለያያሉ። ትክክለኛ ክብደታቸው አይታወቅም፣ እነዚህ ግን በግልጽ የተጋነኑ ክብደቶች ናቸው፣ ሊፈጥሩ የሚችሉትን ጥፋትና ሞት ለማሳየት።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወስን አይደለም።

1. "የብርጭቆ ባሕር" ምንን የሚያሳይ ተምሳሌት ነው?
2. እግዚአብሔር ለዮሐንስ ሰማያዊውን መቅደስ ለምን አሳየው?
3. በማኅተሞቹ፣ በመለከቶቹ፣ በጽዋዎቹ፣ እና በግብፅ መቅሠፍቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎ ዘርዝር።
4. 6፡12 ላይ ያሉት የምስራቅ ነገሥታት 6፡14 ላይ ካሉት ከመላው ዓለም መንግሥታት ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?
5. አርማጌዶን ምን ወይስ የት ነው? (16፡16)
6. "ታላቂቱ ከተማ" ማንን ነው የሚያመለክተው? (16፡19)

# ራዕይ 17-18
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ[4] | አኪጆት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ታላቂቱ ጋለሞታና አውሬው | ቀይዋ ሴትና ቀዩ አውሬ | የባቢሎን መውደቅ | የታወቀችው ጋለሞታ | ታላቂቱ ጋለሞታ |
| 17:1-6ሀ | 17:1-6 | 17:1-6ሀ | 17:1-2 | 17:1-7 |
| | የሴቲቱና የአውሬው ትርጉም | | 17:3-6ሀ | |
| 17:6ለ-14 | 17:7-18 | 17:6ለ-8 | 17:6ለ-8 | |
| | | | | የአውሬውና የጋለሞታዋ ተምሳሌት<br>17፡8 |
| | | 17:9-14 | 17:9-11 | 17:9-11 |
| | | | 17:12-14 | 17:12-14 |
| 17:15-18 | | 17:15-18 | 17:15-17 | 17:15-18 |
| | የታላቂቷ ባቢሎን ውድቀት | | 17:18 | |
| የባቢሎን ውድቀት | 18:1-8 | ሙሾ ለወደቀችው ከተማ | የባቢሎን ውድቀት | መልአኩ የባቢሎንን ውድቀት አወጀ |
| 18:1-3 | | 18:1-3 | 18:1-3 | 18:1-3 |
| | ዓለም በባቢሎን ውድቀት አዘነ<br>18:9-20 | | | የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመሸሽ ተሰባሰበ |
| 18፡4-8 | | 18፡4-8 | 18፡4-8 | 18፡4-8 |
| 18:9-10 | | 18:9-10 | 18:9-10 | 18:9-13 |
| 18:11-20 | | 18:11-20 | 18:11-17ሀ | |
| | የባቢሎን ውድቀት ፍጻሜ | | | 18:14 |
| | 18:21-24 | | | 18:15-17ሀ |
| | | | 18:17b-19 | 18:17b-20 |
| | | | 18:20 | |
| 18:21-19:4 | | 18:21-24 | 18:21-23 | 18:21-24 |
| | | | 18:24-19:4 | |

## የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ vii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ጽሑፋዊ ይዘት ራዕይ 17:1-18:24

ሀ. እነዚህ ሁለት ምዕራፎች በዝርዝር የሚገልጹትየባቢሎንን ጥፋት ነው፣ ውድቀቷ ቀደም ሲል 14:8 እና 16:19፣ ብሎም 18:2፣21 ላይ የተጠቀሰውን። እነዚህ እያንዳንዳቸው የሚከሰቱት በተለያየ ጽሑፋዊ ምድብ ነው (12-14)፣ (15-16)፣ እና (17-19)። ይህም ሌለኛው የትይዩአዊነት ወይም የማጠቃለያ ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

ለ. የእነዚህ ሁለት ምዕራፎች የብሉይ ኪዳን ዳራ የሚገኘው በቀብር ሙሾ ላይ ነው፣ የጥንቱን አምላክ-የለሽ ከተማዎች ውድቀት ለማድነቅ የተጻፈ፡

1. ባቢሎን (ኢሳ. 13፣14፣21 እና ኤር. 50-51)
2. ጢሮስ (ኢሳይያስ 23 እና ሕዝቅኤል 26-28)
3. ነነዌ (ናሆም)
4. ኃጢአተኛይቷ ኢየሩሳሌም (ኢሳ. 1:1-26፤ ሕዝ. 16:51-52)

ሐ. ይህ የወደቀው ዓለም ሥርዓት ጽንሰ-ሐሳብ፣ እሱም ከእግዚአብሔር ጋር ተጻራሪ የሆነ መዝሙር 2፣ ዳንኤል 2፤ 7፤ 9:24-27፤ ማቴዎስ 24: ማርቆስ 13፤ ሉቃስ 21፤ እና 1 ዮሐንስ 2:15-20 ላይ ተገልጿል።

መ. ራዕይ የቀብር ሙሾን ይጠቀማል፣ የሮምን አወዳደቅ ለመግለጽ፣ የዮሐንስ ዘመን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ዓለም። ሆኖም፣ ይኸው ተመሳሳይ ነጻ የሆነ፣ ትዕቢተኛ፣ ቁሳዊ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓት በየዘመኑ ላይ ላይ ይኖራል (1 ዮሐንስ 2፡18)። እሱም ደግሞ በመዳረሻው ላይ ራሱን ይገልጣል፣ እንደ ፍጻሜ ዘመን ገዥ እና የዓለም መንግሥት (2 ተሰሎንቄ 2)። የዮሐንስን የመጨረሻ ትውልድ አንባብያን የሚረዳው ዝርዝር፣ እሱም የፍጻሜ ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ በመጨረሻውም ዘመን ሊከሰት ይችላል። ችግሩ የሚሆነው እያንዳንዱ የአማኞች ትውልድ ራዕይን ወደየራሱ ቀን ገፋፍቶ ለማምጣት መሞከሩ ነው!

ይህ መጽሐፍ የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ጠቀሜታ አለው፣ የሁሉም ክፍለ-ዘመን ጠቀሜታ፣ እና የመጨረሻው ዘመን ጠቀሜታ። ዝርዝሮቹን አለመግፋት እጅግ የተሻለ ነው። እነርሱ ፍች አላቸው (የመጀመሪያዎች ሰሚዎች)፤ እነርሱ በድጋሚ ፍቺ አላቸው (የመጨረሻው ትውልድ)። ነገር ግን እጅግ ለአብዛኛው የአማኞች ትውልድ ምሥጢራዊ ናቸው። ማስረገጡ የተሻለ ነው የሰባቱን ጽሑፋዊ ምድቦች ማዕከላዊ እውነቶች። እነዚህ ከዘላለማዊነት አኳያ ጠቃሚ ናቸው! ዝርዝሮቹ በጠበቀ መልኩ እማሬያዊ (በጥሬው) ከሆኑ፣ ለመጨረሻው ትውልድ ተሳዳጅ አማኞች፣ የሚነግራቸው አታች አያስፈልጋቸውም!

ሠ. ዊሊያም ሄንድሪክሰን፣ *ከአሸናፊዎች በላይ*፣ የሚያስረግጠው የራዕይ የሰባቱም ምድቦችን ትይዩነት ነው (ማስታወሻ ሐ ተመልከት፣ ገጽ 10)። ይህን በማድረጉም እሱ የሚያስረግጠው የአማኞችን ጠላቶች መውደቅ ትይዩ ነው (ሰይጣን፤ ሁለቱ አውሬዎች፤ እና ባቢሎን፣ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓት)። ምንም እንኳ ጥፋታቸው ለየብቻ ቢሆንም (ሰይጣን፣ 20፡7-10፤ ሁለቱ አውሬዎች፣ 19፡17-21፤ እና ባቢሎን፣ 18፡1-19፡4)፣ እነርሱ በርግጥ አንጻራዊ ናቸው፣ ልክ እንደ ማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ።

በብዙ መንገዶች ይህ ማራኪ የትርጓሜ አወቃቀር ነው፣ እሱም ግልጽ የሆነውን የማኅተሞቹን ትይዩነት የሚያሰፋ (4-7)፣ የመለከቶች (8-11)፣ እና የጽዋዎች (15-16) ወደ ምዕራፍ 17-19 እና 20-22።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ራዕይ፡ 17፡1-7**

**[1]ሰባቱንም ጽዋዎች ከያዙ ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ። ና በብዙም ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ፤ [2]የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ በምድርም የሚኖሩ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ሰከሩ ብሎ ተናገረኝ። [3]በመንፈስም ወደ በረሀ ወሰደኝ፤ የስድብም ስሞች በሞሉበት፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ። [4]ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቁችም ተሸልማ ነበር፥ በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኵሰት የሞላባትን የወርቅ ጽዋ ያዘች፤ [5]በግምባርዋም ምስጢር የሆነ ስም። ታላቂቱ ባቢሎን፥ የጋለሞታዎችና የምድር ርኵሰት እናት ተብሎ ተጻፈ። [6]ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት። ባየኋትም ጊዜ እጅግ ታላቅ ድንቅ አደነቅሁ። [7]መልአኩም አለኝ። የምትደነቅ ስለ ምንድር ነው? የሴቲቱን ምስጢርና የሚሸከማትን፥ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ያሉትን የአውሬውን ምስጢር እኔ እነግርሃለሁ።**

**17፡1 "ከሰባቱ መላእክት አንዱ"** ሌላ መልአክ በተመሳሳይ መንገድ 21፡9 ላይ ተገልጿል። ቅደም ተከተላዊ ግንኙነት በምዕራፍ 17 እና 18 መካከልና የጽዋዎቹ መፍሰስ ምዕራፍ 16 ላይ

1. የጽዋዎቹን መፍሰስ ቀደም ይላል
2. እሱም ተጨማሪ ገለጻ ይሆናል፣ የጽዋዎቹ ውጤት

▣ **"የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ"** ይህ መንፈሳዊ ግልሙትና ቁጥር 5 ላይ ተገልጿል "ታላቂቷ ባቢሎን፣ የጋለሞቶች እናት፣" በሚል፣ እና 18፡10 ላይ "ታላቂቱ ከተማ፣ ባቢሎን" በሚል። እንደ ቀዳሚዎቹ ምዕራፎች ከሆነ ይህ መጠሪያ የሚያመለክተው የወደቀውን የዓለም ሥርዓት ነው፣ እሱም ምሳሌነቱ

1. የዳንኤል ባቢሎን
2. የዳንኤል በይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንቲከስ IV
3. የዮሐንስ የሮሜ አጼ፣ መለኮት ነኝ የሚለው።

ምዕራፍ 17 ላይ ያለው የግልሙትና የቅንጦት ኃይል እና ስግብግብነት ከምዕራፍ 18 የንግድ ኃይል ጋር ይገጥማል። በብኪ ሦስት ከተማዎች ጋለሞቶች ተብለዋል።

1. ጢሮስ (ፍንቄ) ኢሳ. 23:15-16
2. ነነዌ (ሶርያ) ናሆም 3:4
3. ኢየሩሳሌም (ፍሬ-አልባዋ ይሁዳ) ኢሳ. 1:21፤ ሕዝ. 16:31፣35፤ 23።

▣ **"የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ"** የብኪ ጠቃሹ ኤር. 51፡11-14 ነው፣ እሱም ጥንዊቷን የባቢሎንን ከተማ የሚያመለክት፣ በኤፍራጥስ ስፍራ የነበረውን (ነነዌ በጤግሮስ ወንዝ እንደ ስፍራ እንደነበረች) እናም የተጠናከረ ሰው-ሠራሽ መስኖ እና የመጓጓዣ ቦይ የነበራት። ሆኖም፣ በቁ. 15 እይታ ይህ ሐረግ የሚተረጎመው እንደ ዓለም አቀፋዊ መንግሥት ነው (ዳን. 7፡2፤3)።

**17፡2**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"የምድርም ነገሥታት ከእርሷ ጋር ሴሰኑ"*** |
| **አኪጀት፣ አየተመት** | ***"የምድርም ነገሥታት ከእርሷ ጋር ዝሙትን ፈጸሙ"*** |
| **አእት** | ***"የምድርም ነገሥታት ዝሙትን ፈጸሙ"*** |
| **አኢመቅ** | ***"የምድርም ነገሥታት ሁሉ ከእርሷ ጋር አመንዝራነትን ፈጸሙ"*** |

ይህ ሴሰኝነት ሁለት ቀዳሚ ገጽታዎች አሉት፡

1. የንግድ ኅብረት (ጢሮስ፣ ኢሳ. 23፡13-18፤ እና ነነዌ፣ ናሆም 3፡4)
2. ፖለቲካዊ ኅብረት፣ እሱም የአሕዛብን ጣኦት የማምለክ ውልን የሚያካትቱ ክብረ-በአሎችን በሕግ ማጽደቅ (ኢየሩሳሌምም ጋለሞታ ተብላ ተጠርታለች፣ ኢሳ. 1፡21 እና ኤርምያስ 3)
3. የሮምን አጼ እንደ መለኮት ማምለክ

▣ **"በምድርም የሚኖሩ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ሰከሩ"** ይህ የኤር. 51፡7 ጠቃሽ ነው። እሱም 14፡8 ላይ ተዋውቋል። "በምድር ላይ የሚኖሩት" የሚለው ሐረግ በራዕይ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ ንስሐ ያልገባውን፣ የወደቀውን፣ ከእግዚአብሔር የራቀውን የሰው ልጅ የሚያመለክት (ዝክ. 3፡10፤ 6፡10፤ 8፡13፤ 11፡10፤ 13፡8፣14፤ 17፡8)።

"መጠጥ" የብኪ ዘይቤ ነው፣ ለፍርድ (መዝ. 75፡6-8)።

**17፡3 "በመንፈስም ወሰደኝ"** ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የዮሐንስን ራዕይ ለማመልከት ነው (ዝክ. 1፡10፤ 4፡2፤ 17፡3፤ 21፡10)። ብዙ አታቾች የራዕይ መዋቅር መረዳታቸውን የመሠረቱት በእነዚህ ራዕዮች ላይ ነው። አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ እጅግ መዋቅራዊ ዘውግ እንደሆነ አስታውሱ። መዋቅር በትርጓሜ ላይ ቁልፍ ነው።

▣ **"ወደ በረሀ"** ይህ ሊሆን የሚችለው

1. የደኅንነት ቦታ ዘይቤ (ዝክ. 12፡6፣14፣ እሱም የእስራኤል በበረሀ የመንከራተት ዘመን ጠቃሽ)
2. ክፉውና አጋንንት የሚኖሩበት ስፍራ (ማለትም፣ ሌዋ. 16፡8፤ 17፡7)
3. የጥንታዊቷ ከተማ የባቢሎን ጠቃሽ፣ ኢሳ. 21፡1-10 ላይ የሚገኘው፣ እሱም የፍርድ ዘይቤ የሆነ

የዮሐንስ ምስያ እጅግ ተለዋዋጭ ነው። ቁ. 1 ላይ ሴቲቱ በብዙ ውኃዎች ላይ ተቀምጣለች (የኤፍራጥስ ወንዝ) እና ቁ. 3 ላይ ቀይ አውሬ ላይ ተቀምጣለች፣ በበረሀ።

▣ **"በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ"** "ቀይ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው

1. ግድያ፣ ዝክ. 17፡6-7
2. ቅንጦት፣ 18፡12-16
3. ሰይጣን እንደ ቀይ ዘንዶ፣ ዝክ. 12፡3

አውሬው በዝርዝር ተገልጿል፣ 13፡1-10 ላይ። እሱም የሚያመለክተው የፍጻሜ ዘመኑን የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው (ዳንኤል 7፡9-14፤ 9፡24-27፤ 11፡36-45፤ II ተሰሎንቄ 2፤ I ዮሐንስ 2፡18)።

▣ **"የስድብም ስሞች በሞሉበት፥"** ይህ ከ13፡1፣5-6 ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ ማዕርግ ከታሪክ አኳያ የሚዛመደው ከሮማው አጼ የራስ ጣኦት ጋር ነው። ለገዛ ራሳቸው ማዕርግ ያወጣሉ፣ እንደ "መለኮት፣" "አዳኝ፣" "ጌታ" የመሳሰለ። የአውሬው የመዳረሻ ግብ የዓለም ፖለቲካዊ ኃይል አይደለም፣ ነገር ግን ሃይማኖታዊ አምልኮ እንጂ (ዳን. 7፡8፣20፤ 8፡11፣25፤ 9፡36፣37) እንደ ሰይጣን ተወካይ ወይም ሥጋ መልበስ (ሊወከል ይችላል ኢሳ. 14፡13-14 እና ሕዝ. 28፡16-17)።

▣ **"ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት"** ይህ ገለጻ ከቀዩ አውሬ ጋር ተመሳሳይ ነው (ዝክ. 12፡3) እና የባሕሩ አውሬ (ዝክ. 13፡1)። ተመሳሳይነቱ የሚያሳየው የእነዚህን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ አካላት ኅብረትን ነው።

ከቁጥር ተምሳሌታዊነት አኳያ (1) ሰባት ራሶች የሚዛመዱት "ፍጹም" እውቀትን ወይም የፍጻሜ ዘመን መዳረሻ የዓለም መሪ ነው፣ (2) አስሩ ቀንዶች የሚዛመዱት የተጠናቀቀ ኃይል ወይም የዓለም ሥልጣንን ነው (ዝክ. 17፡7፣9፣12፣16)።

**17፡4 "ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፋ ነበር"** እነዚህ ቀለሞች የሚያመለክቱት ንጉሣዊነት (ቀይ) አጸያፊነት (ሐምራዊ) ወይም ለቅንጦት፣ ለብልጥግና፣ እና ለሀብታምነት ዘይቤ ነው (ዝክ. 18፡12፣16)።

▣ **"በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቁችም ተሸልማ"** ይህ የምድራዊና የመንፈሳዊ ኃይል እና ሥልጣን ተምሳሌት ነው (በሕዝቅኤል ጥቅም ላይ የዋለ፣ ለዔደናዊ ዘይቤ፣ ለጢሮስ ንጉሥ ኩራት፣ ሕዝ. 28፡13)።

▣ **"የወርቅ ጽዋ"** ይህ ለባቢሎን ከተማ ጠቃሽ ነው (ኤር. 51፡7)።

**17፡5 "በግንባሯም ላይ ስም ተጽፏል"** የሴኔካ *Controversies* 1:2 እና የጁቬናል *Satires* 6:122-123 እንደመዘገቡት የሮም ጋለሞቶች ክብ ጌጥ ያደርጋሉ፣ የገዛ ራሳቸው ወይም የጌታቸው ስም ያለበት፣ በግንባራቸው ላይ። ይህ ታሪካዊ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፣ ለዮሐንስ ጊዜ፣ ወይም በራዕይ ዐውደ-ጽሑፍ፤ እሱም የማያምኑት ምልክት ማጣቀሻ ይሆናል (ዝከ. 13:16-17፤ 14:9፣11፤ 15:2፤ 16:2፤ 19:20፤ 20:4) እሱም እግዚአብሔር አማኞችን ማኅተም እንዳደረገው የተኮረጀ (ዝከ. 7:2፤ 9:4)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ምሥጢራዊ፣ 'ታላቂቱ ባቢሎን"** |
| **አኪጀት** | **"የምሥጢር፣ ታላቂቱ ባቢሎን"** |
| **አየተመት** | **"ምሥጢራዊ፡ 'ታላቂቱ ባቢሎን"** |
| **አእት** | **"ምሥጢራዊ ፍቺ፡ 'ታላቂቱ ባቢሎን"** |
| **አኢመቅ** | **"ስም፣ ምሥጢራዊ ስም፡ 'ታላቂቱ ባቢሎን"** |

እዚህጋ አለመግባባት አለ፣ "ምሥጢራዊ" የሚለው ስም፣ የመጠሪያው ክፍል እንደሆነ ወይም የመጠሪያው ተምሳሌታዊ ባሕርይ መጥቀሻ መንገድ (ዝከ. ቁ. 7)። ባቢሎን መነሻዋን ያገኘችው በመጀመሪያው ሥልጣኔ ላይ ነው፣ በናምሩድ የተጀመረው (ባብኤል)፣ በእግዚአብሔር ላይ ያመጹት፣ ብሎም ዘፍጥረት 11 ላይ የተበታተኑት። ከዚህ አጠቃቀምና ባቢሎን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለግዞት ከመውሰዱ የተነሣ (ይሁዳ)፣ እሱ ለክፉው ተመሳሳይ ሆኗል፣ ንጉሣዊ የዓለም ኃይል። በዮሐንስ ጊዜ፣ ይህ ኃይል ሮም ነበር (1 ጴጥ. 5፡13)።

**17፡6** ይህ ቁጥር የሚናገረው ስለ አማኞች ስደትና *መሥዋዕትነት* ነው (ዝከ. 11:7፤ 13:7፤ ዳን. 7:21)።

▣ **"እጅግ ተደነቅሁ"** ኪጀት ይህን የሚተረጉመው "እጅግ ታላቅ ድንቅ" በሚል ሲሆን፣ አኪጀት ግን "እጅግ ታላቅ ድንቅ አደነቅሁ" የሚል አለው። ዮሐንስ እሷን አላደነቃትም፣ ነገር ግን በእርሷ ድርጊት ፍጹም ተደንቋል። የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንድታሳድድና እንድትገድል ተፈቅዶላታል (ዝከ. 13:5፣7፣15፤ 11:7)።

### ራዕይ፡ 17፡8-14

**[8]ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ፥ አሁንም የለም፥ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው፥ ወደ ጥፋትም ይሄዳል፤ ስሞቻቸውም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ አውሬው አስቀድሞ እንደነበረ አሁንም እንደሌለ፥ ነገር ግን እንዳለ ሲያዩ ያደንቃሉ። [9]ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው። ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች ናቸው፥ [10]ሰባት ነገሥታት ደግሞ ናቸው፤ አምስቱ ወድቀዋል አንዱም አለ፥ የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም፥ ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል። [11]የነበረውና የሌለውም አውሬ ራሱ ደግሞ ስምንተኛው ነው ከሰባቱም አንዱ ነው፥ ወደ ጥፋትም ይሄዳል። [12]ያየሃቸውም አስሩ ቀንዶች ገና መንግሥትን ያልተቀበሉ አስር ነገሥታት ናቸው፥ ዳሩ ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት እንደ ነገሥታት ሥልጣንን ይቀበላሉ። [13]እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው፥ ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ። [14]እነዚህ በጉን ይወጋሉ፤ በጉም የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ስለ ሆነ እነርሱን ድል ይነሣል፥ ከእርሱም ጋር ያሉ የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም ደግሞ ድል ይነሣሉ።**

**17፡8 "ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ፥ አሁንም የለም፥ ይመጣ ዘንድ አለው፥"** ይህ ቅደም ተከተላዊ ገለጻ በአታቾች መካከል ትልቅ ድንጋጤ ፈጥሯል።

1. አንዳንዶች የሚመለከቱት ከታሪካዊ መልኩ ነው፣ እሱም በተለይ ተግባራዊ የሚሆነው ከኔሮ መመለስ አፈ-ታሪክ ጋር ነው።
2. ሌሎች ቀጣይነት እንዳለው የዓለም መንግሥት ነው፣ ከዳንኤል 2 ጋር በተያያዘ፣ በፍጻሜ ዘመን የሚሆን የመጨረሻው የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓት።
3. ሌሎች የሚመለከቱት ከፍጻሜው ዘመን የአውሬው ድርጊት ጋር በተያያዘ ነው፣ 13:3፣12፣14፣ ላይ የተገለጸው፣ እሱም ከክርስቶስ አገልግሎት ጋር የተመሳሰለ ወይም የተኮረጀ።
4. እሱም ከ1 ዮሐንስ፣ በየዘመኑ ካለው የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ጽንሰ-ሐሳብ ይዛመዳል፣ በፍጻሜው ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚያበቃ (ዝከ. 1 ዮሐንስ 2:18፣22፤ 4:3፤ II ዮሐንስ 7)።

እሱም ሌለኛው የያህዌን ስም ማስመሰያ ነው (ዝከ. 1፡4፣8)።

▣ **"ጥልቁ"** ይህ የግሪክ ቃል "ጥልቅ" ነው፣ ከአሉታዊ ምእላድ (ተጨማሪ) ጋር። እሱ መጀመሪያ የተጠቀሰው 9፡1 እና 11፡7 ላይ ነው። እሱም ለክፉውና ለኢጋንንት መኖርያ ስፍራ ነው። 9፡1 ተመልከት።

▣ **"የሕይወት መጽሐፍ"** 5፡1 እና 13፡8 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ"** 3፡5 እና 13፡8 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

**17:9**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጆት** | **"ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው"** |
| **አየተመት** | **"ይህ ጥበብ ያለውን አእምሮ ያመለክታል"** |
| **አእት** | **"ይህ ጥበብንና ማስተዋልን ያሳያል"** |
| **አኢመቅ** | **"ይህ ጥበበኝነትን ያሳያል"** |

ይህ ሐረግ ከ13:18 ጋር ተመሳሳይ ነው፣ እሱም ከአውሬው ስም ቁጥር ጋር የሚያያዝ። ይህ አነስ ያለ ሐሳብን የሚወስድ የቅዱስ ቃል ክፍል እያንዳንዱ ሰው የየራሱን ንድፈ ሐሳብ እንዲሰነዝር ምክንያት ሆኗል! ሆኖም፣ ይህ በርካታ ትርጓሜዎች እንዲኖሩ ያደረገው እውነታ የሚያሳየው በመካከላችን በርካታ ጥበበኞች አለመኖራቸውን አመላካች ነው! (1 ቆሮ. 1:26-31)። ለእኔ፣ ዮሐንስ የጽሑፉን ምሥጢራዊነት፣ ተምሳሌታዊነት፣ እንቆቅልሻዊነት ያሳየበት ሌላው መንገድ ነው (ፍራንክ ስታግ፣ *የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት*፣ ገጽ 317)።

▣ **"ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች"** ይህ የሮም ጠቃሽ ነው። ሮም፣ እንደ ኢየሩሳሌም፣በሰባት ተራሮች ላይ ነው የተገነባችው። ይህ ሐረግ በበርካታ ጥንታዊ ጽሑፎች ላይ ይገኛል የሮም ከተማን ለመግለጽ። ስለዚህ፣ የተርጓሚዎች ኃላፊነት ነው፣ ይሄንን ቢያንስ ከሮማ ኢምፓየር አኳያ መመልከት፣ ምንም እንኳ የምዕራፍ 17 እና 18 ሙሉው ጠቃሽ በእግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓት ላይ ቢሆንም፣ እሱም የፍጻሜው ዘመን ሆኖ በእውነታው ግን ለየዘመናቱ እንደሆነ።

**17:10-11** አንዳንድ ተንታኞች ይህን የሚመለከቱት እንደ ተለጣጣቂ የሮሜ ነገሥታት ነው፡ አውግስጦስ፣ ጢባርዮስ፣ ካሊጉላ፣ ክላውዲዮስ፣ እና ኔሮ "እንደ ወደቁት እንደ አምስቱ።" ቬስፓስያን "አሁን እንዳለው ነው" እና ቲቶ፣ "ጥቂት ቆይቶ የሚመጣ" (ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ፣ *መልሶች ለጥያቄዎች*፣ ገጽ 141)። ይህ ትርጓሜ ይልቁን አሻሚ ነው፤ ሦስቱ በአንጻራዊነቱ አናሳ ነገሥታት (ጋልባ፣ ኦቶ፣ እና ቪቲሊዩስ) እነርሱም ለዘውዱ የተፎካከሩት፣ በ68-69 ዓ. ም ተገድፈዋል። ሆኖም፣ ከእነ ችግሩም ቢሆን፣ ይህ ሊሆን የሚችለው፣ የቁ. 10 እና 11 ተተኳሪ ነው፣ ይኸውም ከኔሮ ተሐድሶና መመለስ አፈ-ታሪክ ጋር፣ ከፋርስ ሠራዊት ጋር፣ ሮምን ለመውጋት (ይህም የሚያስረዳው ቁ. 16ን ይሆናል፣ የሲቢሊያን ንግርት፣ 5:361-368)።

ሌሎች ይሄንን ትንቢት የሚመለከቱት እንደ ዶሚቲያን ስደት ፍጻሜ ነው። በዚህ ትርጓሜ ላይ አንዳንድ ዋነኛ የሚይዙ ነገሮች አሉ፡

1. ራዕይ በቬስፓስያን አገዛዝ ጊዜ መጻፍ ይኖርበታል፣ ይኸውም ከጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን ባህል ጋር የተለያየ፣ ዮሐንስ በዶሚቲያን አገዛዝ ጊዜ በመጻፉ
2. በሙሉ መጽሐፉ ያለው ተምሳሌታዊ አጠቃቀም

ይህን ከታሪክ አኳያ እማሬያዊ (ጥሬ) ያደረገው ምንድነው? እንደገናም፣ ዮሐንስ ይህንን ሆን ብሎ ያደረገው ይሆን፣ የራዕዩን ተምሳሌታዊ ባሕርይ ለማሳየት፣ ይኸውም ባጠቃላይ ከማንኛውም ታሪካዊ ጊዜ ጋር የተቆለፈ ማለት ያልሆነ።

ሌላው ታሳቢ ትርጓሜ፣ ይህ የሚያመለክተው ተለጣጣቂ የሆኑትን የብኪ ኢምፓየሮችን ነው፣ እነርሱም የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት የሆኑ፡ ግብፅ፣ ሶርያ፣ ባቢሎን፣ ፋርስ፣ ግሪክ ("አምስቱ ወድቀዋል")፣ ሮም ("አንዱ አለ")፣ የፍጻሜ ዘመን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ኢምፓየር ("ሌለኛው ገና አልመጣም")። ይህ ትርጓሜ ከአጠቃላይ ተለጣጣቂ ከሆኑት የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም መንግሥታት ጋር ይስማማል፣ ከዳን. 2:1-8 (ጆርጅ ላድ፣ ራዕይ፣ ገጽ 227-231)።

አሁንም ሌለኛው ጥንታዊ ትርጓሜ ተምሳሌታዊ ባሕርዩ ነው፣ ለቁጥሮቹ ሁሉ እና ራዕይ ውስጥ ለሚገኙት ዝርዝሮች፣ ይኸውም ይህንን ምዕራፍ ወደ ሌላው፣ በእግዚአብሔርና በክፉው መካከል ለሚደረገው የመጨረሻ ግጭት ምሳሌ ነው ( አለን ጆንሰን ራዕይ፣ ገጽ 152-153፣ 157-161)።

ይህ የተሻለ ምሳሌ ነው፣ እንደ ተርጓሚ ለእኔ ውስጣዊ ግጭቶች። እጅግ በርካታ የተለያዩ ትርጓሜዎች አሉ፣ በምታመናቸው መልካም ሊቃውንት። የመጀመሪያው ንድፈ-ሐሳብ በምወደው ጸሐፊ በኤፍ. ኤፍ ብሩስ ነው። ቀጣዮቹ ሁለቱ በምወዳቸው የራዕይ ተንታኞች፣ ጆርጅ ላድ እና አለን ጆንሰን ነው። ሁሉም አይስማሙም! ዋነኛው ጉዳይ፣ ጽሑፉ የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ሮም ጠቃሽ ይሆን፣ (ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ)፣ ብኪ (ጆርጅ ላድ)፣ ወይም አፖካሊፕቲካዊ ምስያነት (አለን ጆንሰን) መሆኑ ነው። በዚህ ነጥብ ላይ የእኔ ግላዊ ጥናት፣ እንደማስበው የጆንሰን አተያይ የተሻለ ይመስለኛል።

**17:12 "ያየሃቸውም አስሩ ቀንዶች አስር ነገሥታት ናቸው፥"** ይህ የዳን. 7:7፤23-24 ጠቃሽ ነው። ዳንኤል 7 የፍጻሜ ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ ገለጻ ነው። አንዳንዶች ይህንን የሚመለከቱት ከታሪክ አኳያ ለአስሩ የሮም ነገሥታት ታማኝ እንደሆኑ አገልጋዮች ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ የሚመለከቱት እንደ አጋንንታዊ ሠራዊት ነው፣ ራዕይ 9 ላይ እንዳሉት። ለብዙዎች፣ በራዕይ መጽሐፍ የቁጥሮች ተምሳሌታዊ ባሕርይ፣ ቁ. 12 የሚያመለክተው የፍጻሜ ዘመንን የዓለም መሪዎችን ነው፣ ነገር ግን ለይቶ ሳይሆን።

ብዙዎች የራዕይን መጽሐፍ እማሬያዊ ፍቺ የሚያብራሩት ቁ. 10-12 ባሉት የተለዩ ዝርዝሮች ላይ በመመሥረት ነው። እነዚህ ትንቢቶች እጅግ ተናጠላዊ ናቸው፣ የፍጻሜውን ዘመን እማሬያዊ ፍቺ ፍጻሜ የሚያስገኙ። ሆኖም፣ የጽሑፋዊ ዘውጉ ባሕርይ የሚያመለክተው ወደ እነዚህ ቁጥሮች እና ዝርዝሮች ተምሳሌታዊ ፍቺ ነው (ቢያንስ ለእኛ፣ የመጨረሻው ትውልድ ተሳዳጅ አማኞች ላልሆንነው)።

**17:13** ይህ ቁጥር የሚያሳየው የክፉውን ኅብረት ሲሆን፣ ቁ. 15-16 ደግሞ የሚያሳየው የክፉውን አንድ አለመሆን ነው። ክፉው በመዳረሻ ላይ ራሱን ይቃረናል፣ 16:12 ላይ እንዳለው።

**17:13 "እነዚህ በጉን ይወጋሉ"** በጉ ከሕዝቦቹ ጋር ተገልጿል (ማቴ. 25:35-40፤ Acts 9:4)።

▣ **"በጉም ድል ይነሣል... ከእርሱም ጋር ያሉ"** በክርስቶስ ድልና በሕዝቡ ድል መካከል ያለውን የቀረበ መለያ ተገንዘቡ።

▣ ***"እሱም የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው"*** ይኸው ተመሳሳይ መጠሪያ 19፡16 ላይ ተጠቅሷል፣ እንደሚመለሰው መሲሕ ባሕርይ። የእርሱ ስፍራ የሚገኘውም (1) የያህዌ መግለጫ ነው ዘዳ. 10፡17፤ መዝ. 136፡2-3 ላይ ወይም (2) ባቢሎናዊ መጠሪያ ለናቡከደነፆር ጥቅም ላይ የዋለ ዳን. 2፡37፣47። የዚህ ሐረግ የቁጥር ዋጋ ከ777 ጋር እኩል ነው፣ በአራምኛ፣ ምንም እንኳ ይህ በጽሑፉ ላይ ባይጠቀስም።

▣ **"የተጠሩ የተመረጡ እና የታመኑ"** በ "የተመረጡ" እና "በተጠሩ" በሚሉት ቃላት ያለውን የቅድመ መዳረሻ ጠቃሽ ተገንዘብ፣ ግን ደግሞ እነርሱ እንዲጸኑ ተጠርተዋል፣ "የታመኑ" ከሚለው ጋር የተያያዘውን ተገንዘብ። እኛ የእርሱ ነን፣ በመጠራትና በእምነት (በሁለቱም፣ በመነሻና በቀጣይነት)። ልዩ ርዕስ መጽናት 2፡2 ላይ ተመልከት።

## ራዕይ፡ 17፡15-18

***[15]አለኝም። ጋለሞታይቱ የተቀመጠችባቸው ያየሃቸው ውኃዎች፥ ወገኖችና ብዙ ሰዎች አሕዛብም ቋንቋዎችም ናቸው። [16]ያየኃቸውም አስር ቀንዶችና አውሬው ጋለሞታይቱን ይጣላሉ፤ ባዶዋንና ራቁትዋንም ያደርጓታል፥ ሥጋዋንም ይበላሉ፥ በእሳትም ያቃጥሉአታል። [17]እግዚአብሔር አሳቡን እንዲያደርጉ አንድንም አሳብ እንዲያደርጉ የእግዚአብሔርም ቃል እስኪፈጸም ድረስ መንግሥታቸውን ለአውሬው እንዲሰጡ በልባቸው አግብቶአልና። [18]ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት።***

**17፡15** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው የፍጻሜ ዘመኑን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ መሪ እና ግዛቱን ሁለንተናዊ አገዛዝ ነው። 10፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**17፡16** ይህ የሕዝ. 16፡39-40፤ 23፡25-27፤ 28፡18 ጠቃሽ ነው። እሱም የሚያመለክተው በክፉ ኃይላት መካከል ያለውን ውስጣዊ ግጭት ነው፣ 16፡12 ላይ እንዳለው። ይህ የርስ በርስ ግጭት የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው (ዝከ. ቁ. 17)።

**17፡17 "በልባቸው"** ልዩ ርዕስ 2፡23 ላይ ተመልከት።

**17፡18** ይህች ታላቅ ከተማ 11፡8 እና 16፡19 ላይ ተጠቅሳለች፣ አንድም ለኢየሩሳሌም (ነጻ አስተሳሰቦች) ወይም ሮም (ቀድሞ ተፈጽሟል ባዮች)። የጽሑፋዊ ምድቡ ዐውደ-ጽሑፍ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ኃይል መዋቅር እንደ ከተማ ተምሳሌታዊ ሆኗል። የትኛዋ ከተማ አይደለም ጉዳዩ፤ ነጥቡ የሚሆነው ከእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ የተለየ መንግሥታዊ ሥርዓት መኖር ነው፣ የገዛ ራሳቸውን መሻት ለማሟላት የሚሞክሩ ሰዎች (ኢ-አማኒ ሰብአዊነት)።

## ራዕይ፡ 18፡1-3

**[1]ከዚህ በኋላ ታላቅ ስልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች። [2]በብርቱም ድምፅ። *ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤* [3]አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቍጣ ወይን ጠጅ የተነሳ ወድቀዋልና፥ የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ የምድርም ነጋዴዎች ከቅምጥልነትዋ ኃይል የተነሳ ባለ ጠጋዎች ሆኑ ብሎ ጮኸ።**

**18፡1 *"ታላቅ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች።"*** ይህ እጅግ ኃይለኛ መልአክ ነበር። "ሥልጣን" (*exousia*) የሚለው ቃል በመጽሐፉ ላይ ለማንም መልአክ ጥቅም ላይ አልዋለም። ዮሐንስ 5፡27 ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ለእግዚአብሔር ሥልጣን ነው፣ ለኢየሱስ የተሰጠው። 22፡16 ላይ ኢየሱስ እንዳለው፣ አንድ መልአክ ልኳል እሱን ወክሎ እንዲናገር።

**18፡2 *"ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፣ ወደቀች!"*** ይህ አንደኛው ምሳሌ ነው የራዕይ መጽሐፍን ለመተርጎም ካሉት ችግሮች። በራዕይ ላይ አንዳች መረጃ በሆነ ነጥብ ላይ ይገኛል፣ በከፊልም በሌለኛው ነጥብ ላይ ይዳብራል፣ እናም ሙሉ ለሙሉ በሌላ ራዕይ ይዳብራል (ምሳ. ዝከ. 11፡8፤ 14፡8፤ እና 16፡19-20 ወይም ይህ ሌለኛ ምሳሌ ይሆናል፣ በሰባቱ ጽሑፋዊ ምድቦች መካከል ባለው አጠቃሎሽ)። ይህ ሌለኛ ጠቃሽ ነው የኢሳ. 21፡9 እና/ወይም ኤር. 51፡8።

▣ ***"የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤"*** ይህ ጠቃሽ ነው፣ ከጥንታዊ ከተሞች ፍርስራሽ፡

1. ባቢሎን (ኢሳ. 13፡21-22፤ 14፡23፤ ኤር. 50፡39፤ 51፡37)
2. ኤዶም (ኢሳ. 34፡10-15)
3. ነነዌ (ሶፎ. 2፡14)

በብኪ እንስሳት በፈረሱ ከተማዎች ውስጥ ይዘዋወራሉ ይባላል። ይህ የሁለቱም ተምሳሌት ነው፣ የጥፋትና የክፉ መናፍስት መገኘት (አእመቅ)። አብዛኞቹ እነዚህ ወፎች ኢጋንንትን ይወክላሉ።

የዮሐንስ ጽሑፎች እጅግ ተለዋዋጭ ናቸው። ቁጥሩ የሚገልጸው ከተማዋን ነው፣ እንደ ባድማና የኢጋንንት መኖርያ፣ 19፡3 የሚገልጸው እንደ ተቃጠለችና እንደምትነድ ነው።

**18፡3 "አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቍጣ ወይን ጠጅ ጠጥተዋልና"** ይህ ሐረግ ለባቢሎን ጥፋት የብኪ ትንቢት ጠቃሽ ነው (ኤር. 51፡7)። ኤርምያስ ለይቶ ሰካርነትን ይጠቀማል (ማለትም፣ "የወርቅ ጽዋ") ለሀብት እንደመሴሰን ተምሳሌት።

▣ **"ጽኑ ስሜት"** ይህ በጥሬው "ቁጣ" (*thumos*) ነው። 7፡14 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"የምድርም ነጋዴዎች ከቅምጥልነትዋ ኃይል የተነሳ ባለ ጠጋዎች ሆኑ"** ይህ የወደቀው የሰው ልጅ፣ እሱም በራስ ወዳድነት እና በፍጻሜ ዘመን ቁሳዊነት የተያዘው፣ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓት፣ ዋነኛ ችግር ጠቃሽ ነው። ሦስት ዓይነት ሰዎች አሉ፣ ለወደቀችው ታላቂቱ ጋለሞታ የሚያዝኑ፡

1. ነጋዴዎች (ዝከ. ቁ. 3፤11-16)
2. የምድር ነገሥታት (ዝከ. ቁ. 3፤9-10)
3. የባሕር ነጋዴዎች (ዝከ. ቁ. 3፤17-19)

እነዚህ ሦስቱ የመላው ዓለምን የሰው ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች ያመለክታሉ።

**ራዕይ፡ 18፡4-8**

**[4]ከሰማይም ሌላ ድምፅ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦ ሕዝቤ ሆይ፥ በኃጢአትዋ እንዳትተባበሩ ከመቅሠፍትዋም እንዳትቀበሉ ከእርስዋ ዘንድ ውጡ፤ [5]ኃጢአትዋ እስከ ሰማይ ድረስ ደርሶአልና፥ እግዚአብሔርም ዓመፃዋን አሰበ። [6]እርስዋ እንደ ሰጠች መጠን ብድራት መልሱላት፥ እንደ ሥራዋም ሁለት እጥፍ ደርቡባት፤ በቀላቀለችው ጽዋ ሁለት እጥፍ አድርጋችሁ ቀላቅሉባት፤ [7]ራስዋን እንደ አከበረችና እንደ ተቀማጠለች ልክ ሥቃይና ኀዘን ስጡአት። በልብዋ። ንግሥት ሆኜ እቀመጣለሁ ባልቴትም አልሆንም ኀዘንም ከቶ አላይም ስላለች፥ [8]ስለዚህ በአንድ ቀን ሞትና ኀዘን ራብም የሆኑ መቅሰፍቶችዋ ይመጣሉ፥ በእሳትም ትቃጠላለች፤ የሚፈርድባት እግዚአብሔር ብርቱ ነውና።**

**18፡4 "ሕዝቤ ሆይ፥ በኃጢአትዋ እንዳትተባበሩ ከመቅሠፍትዋም እንዳትቀበሉ ከእርስዋ ዘንድ ውጡ"** ይህ የብኪ ጠቃሽ ነው ኢሳ. 48:20፤ 52:11፤ ኤር. 50:8፤28፤ 51:6፤9፤45 ወይም ዘካ. 2:6-7። እሱም የድርጊት የአሁን ተተኳሪ ነው፣ እሱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚጎተጉት፣ በዚህ በወደቀ የዓለም ሥርዓት እንዳይያዝ።

**18፡5 "ኃጢአትዋ እስከ ሰማይ ድረስ ደርሶአልና፥"** ይህ የዘፍ. 18:20-21 ወይም ኤር. 51:9 ጠቃሽ ነው። የእግዚአብሔር ትዕግሥት ብዙ ኃጢአት ለመሥራት እንደ ምክንያት ተወስዷል፣ ንስሐ ከመግባት ይልቅ (ዝከ. 2፡21፤ ሮሜ. 2፡4)።

▣ **"እግዚአብሔርም አሰበ"** በመጽሐፍ ቅዱስ ዘወትር፣ እግዚአብሔር የክፉን ሥራ በሚያስብበት ጊዜ ውጤቱ ፍርድ ነው (ዝከ. 16:19፤ መዝ. 79:8፤ ኢሳ. 64:9፤ ኤር. 14:10፤ 17:1-4፤ 44:21-23፤ ሆሴ. 7:2፤ 8:13፤ 9:9፤ አሞጽ 8:7)።

**18፡6 "እርስዋ እንደ ሰጠች መጠን ብድራት መልሱላት፥"** ይህ የዘራነውን እንደምናጭድ ላለው እውነታ ጠቃሽ ነው (ገላ. 6፡7፤ ለተሟላ ዝርዝር www.freecommentary.org ተመልከት)። ይህ እውነት የሚቀርበው በመጽሐፍ ቅዱስ በበርካታ የተለያዩ መልኮች ነው (መዝ. 137:8፤ ኤር. 50:15፤29፤ ማቴ. 7:2፤ ራዕ. 13:10)።

▣ **"እንደ ሥራዋም ሁለት እጥፍ ደርቡባት፤"** ይህ የኤር. 16፡18 እና 17፡18 ጠቃሽ ነው፣ እውነቱ ግን በበርካታ ጽሑፎች ተገልጿል (ዘጸ. 22:4-9፤ መዝ. 75:7-8፤ ኢሳ. 40:2)። ይህ ፈሊጥ ስለ ፍጹምና የተሟላ ፍርድ ይናገራል፣ ቀጣዩ ሐረግ እንደሚያደርገው። ይህ ቁጥር ለተሳዳጅ ክርስቲያኖች እጅግ የሚያበረታታ ነው።

▣ **"በቀላቀለችው ጽዋ ሁለት እጥፍ አድርጋችሁ ቀላቅሉባት"** "ጽዋ" የብኪ ዘይቤ ነው፣ ለእግዚአብሔር ፍርድ (መዝ. 11:6፤ 60:3፤ 75:6-8፤ ኢሳ. 51:17፤22፤ ኤር. 25:15-16፤27-28)።

**18፡7 "በልብዋ። ንግሥት ሆኜ እቀመጣለሁ ባልቴትም አልሆንም ኀዘንም ከቶ አላይም ስላለች፥"** ይህ በተለይ የሚዛመደው ከሶፎ. 2:15 እና ኢሳ. 47:7-8 ጋር ነው። እሱ የሚጠቅሰው የራስ ብቃትንና ኩራትን ነው፣ ይኸውም የሰይጣን የውድቀት ምንጭ የነበረ (ሊጠቀስ የሚችለውም ኢሳይያስ 14 እና ሕዝቅኤል 28 ነው)፣ የሰው ልጅ መውደቅ (ዘፍጥረት 3)፣ እና ይህ የፍጻሜ ዘመን የዓለም ሥርዓት። ችግሩ የትዕቢት ነጻነት ነው!

ለ"ልብ" ልዩ ርዕስ 2፡23 ላይ ተመልከት።

**18፡8 "ስለዚህ በአንድ ቀን መቅሠፍቶችዋ ይመጣሉ"** ይህ የኢሳ. 47፡9 የተለየ ጠቃሽ ነው። በአንድ ቀን ኀዘን ላይ የመውደቋ ጽንሰ-ሐሳብ ቁ. 17-19 ላይ ተደግሟል፣ እዚያም ዮሐንሳዊው ቃል "ሰዓት" ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ለተሳዳጅ ክርስቲያኖች ዋነኛ ማበረታቻ ነው።

▣ **"በእሳትም ትቃጠላለች"** ይህ የሌዋ. 21፡9 ጠቃሽ ይሆናል። ልዩ ርዕስ፡ "እሳት" 16፡8 ላይ ተመልከት።

▣ **"የሚፈርድባት እግዚአብሔር ብርቱ ነውና።"** ይህ የኤር. 50፡34 ጠቃሽ ነው።

> ***ራዕይ፡ 18፡9-10***
> ***[9]ከእርስዋም ጋር የሴሰኑና የተቀማጠሉ የምድር ነገሥታት የመቃጠልዋን ጢስ ሲያዩ ስለ እርስዋ ዋይ ዋይ እያሉ ያለቅሳሉ፤ [10]ሥቃይዋንም ከመፍራት የተነሣ በሩቅ ቆመው። አንቺ ታላቂቱ ከተማ፥ ብርቱይቱ ከተማ ባቢሎን፥ ወዮልሽ፥ ወዮልሽ፥ በአንድ ሰዓት ፍርድሽ ደርሶአልና እያሉ ይናገራሉ።***

**18፡9-10 "*የምድር ነገሥታት*"** ይህ 17፡12፣16፣ ላይ ከተጠቀሱት ነገሥታት የተለየ መሆን አለበት፣ እነርሱም በታላቋ ጋለሞታ ጥፋትና ውድቀት ላይ ከተሳተፉ። እነዚህ ነገሥታት ባጠቃላይ ነጋዴ ሕዝቦች ናቸው፣ ከንግድ የሚጠቀሙ፣ በእግዚአብሔር ተቃዋሚ ሥርዓት። ይህም የጠንካራዋ የንግድ ከተማ የጢሮስ እና የትዕቢተኛ ንጉሢ ጠቃሽ ነው፣ ሕዝቅኤል 26-28 ላይ። ምዕራፍ 18 የሚያስታውሰው በንግድ ኃይል የሰከሩ፣ ከወደቀው የዓለም ሥርዓት ጋር የሚተባበሩትን ነው።

> ***ራዕይ፡ 18፡11-20***
> ***[11]የመርከባቸውንም ጭነት ከእንግዲህ ወዲህ የሚገዛ የለምና የምድር ነጋዴዎች ያለቅሱላታል ያዝኑላትማል፤ [12]ጭነትም ወርቅና ብር የከበረም ድንጋይ ዕንቁም፥ ቀጭንም ተልባ እግር ቀይም ሐርም ሐምራዊም ልብስ የሚሸትም እንጨት ሁሉ፥ ከዝሆን ጥርስም የተሰራ ዕቃ ሁሉ፥ እጅግም ከከበረ እንጨት ከናስም ከብረትም ከዕብነ በረድም የተሰራ ዕቃ ሁሉ፥ [13]ቀረፋም ቅመምም የሚቃጠልም ሽቱ ቅባትም ዕጣንም የወይን ጠጅም ዘይትም የተሰለቀ ዱቄትም ስንዴም ከብትም በግም ፈረስም ሰረገላም ባሪያዎችም የሰዎችም ነፍሳት ነው። [14]ነፍስሽም የጎመጀችው ፍሬ ከአንቺ ዘንድ አልፎአል፥ የሚቀማጠልና የሚያጌጥም ነገር ሁሉ ጠፍቶብሻል፥ ሰዎችም ከእንግዲህ ወዲህ ከቶ አያገኙአቸውም። [15-17]እነዚህን የነገዱ በእርስዋም ባለ ጠጋዎች የሆኑት እያለቀሱና እያዘኑ። በቀጭን ተልባ እግርና በቀይ ሐምራዊም ልብስ ለተጐናጸፈች በወርቅና በከበረ ድንጋይም በዕንቁም ለተሸለመች ለታላቂቱ ከተማ ወዮላት፥ ወዮላት፥ ይህን የሚያህል ታላቅ ባለ ጠግነት በአንድ ሰዓት ጠፍቶአልና እያሉ ስቃይዋን ከመፍራት የተነሣ በሩቅ ይቆማሉ። የመርከብም መሪ ሁሉ በመርከብም ወደ ማናቸውም ስፍራ የሚሄድ ሁሉ መርከበኞችም ከባሕርም የሚጠቀሙ ሁሉ በሩቅ ቆሙ፥ [18]የመቃጠልዋንም ጢስ ባዩ ጊዜ። ታላቂቱን ከተማ የምትመስላት ምን ከተማ ነበረች? እያሉ ጮኹ። [19]በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነስንሰው እያለቀሱና እያዘኑ። በባሕር መርከቦች ያሉአቸውን ሁሉ ከባለ ጠግነትዋ የተነሣ ባለ ጠጋዎች ላደረገች ለታላቂቱ ከተማ ወዮላት፥ ወዮላት፥ በአንድ ሰዓት ጠፍታለችና እያሉ ጮኹ። [20]ሰማይ ሆይ፥ ቅዱሳን ሐዋርያት ነቢያትም ሆይ፥ በእርስዋ ላይ ደስ ይበላችሁ፥ እግዚአብሔር ፈርዶላችኋልና።***

**18፡11-19 "*የምድር ነጋዴዎች ያለቅሱላታል ያዝኑላትማል*"** ይህ የሕዝቅኤል 27 ተመሳሳይ ነው፡

1. ቁ. 11 - ሕዝ. 27:31፣36
2. ቁ. 12-13 – ሕዝ. 27:12፣13፣22
3. ቁ. 15 – ሕዝ 27:31፣36
4. ቁ. 17 – ሕዝ. 27:26-30
5. ቁ. 18 – ሕዝ. 27:32
6. ቁ. 19 – ሕዝ. 27:30-34

እሱም የሚገልጸው ዓለም አቀፋዊውን ንግድ ነው፡

1. ብር ከእስፔን
2. የተልባ እግር ከግብጽ
3. ሐር ከቻይና
4. እንጨት ከሰሜን አፍሪካ
5. የዝኆን ጥርስ ከአፍሪካ
6. ብረት ከእስፔን ወይም ከጥቁር ባሕር
7. ቀረፋ ከሕንድ
8. ዓለም አቀፋዊው የባርያ ንግድ

**18፡13**

***አአመመቅ፣ አኪጀት***
***አየተመት፣ አኢመቅ "ሠረገላዎች"***
***አእት "ሠረገላዎች"***

ይህ የሚያመለክተው የግል፣ ባለ አራት እግር፣ የቅንጦት ሠረገላ ነው፣ የጦርነት ሠረገላ ሳይሆን።

**18፡14 "የሚቀማጠልና የሚያጌጥ"** ይህ የቃላት ጨዋታ ነው፣ ለግሪኩ ቃላት *lipara* (ቅንጦት) እና *lampra* (ያጌጠ)።

**18፡17** ይህ የሕዝቅኤል 26-28 (ጢሮስ ከተማ) ጠቃሽ ነው፣ እነርሱ በዚህ የቅንጦት ማጓጓዣ ላይ የሚሠሩ ያዝናሉ፣ የገዛ ኑሯቸው ከመጎዳቱ የተነሣ።

**18፡19 "በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነስንሰው"** ልዩ ርዕስ፡ የኀዘን ሥርዓቶች 1፡7 ላይ ተመልከት።

**18፡20 "በእርስዋ ላይ ደስ ይበላችሁ፥"** ይህ የኤር. 51፡48 ጠቃሽ ነው፣ ምንም እንኳ አንዳንዶች እሱን ዘዳ. 32፡43 (በሴፕቱዋጂንት) እንደሚጠቅስ ቢመለከቱትም፣ እንደ ኢኮኖሚያዊ አጋር፣ ለባቢሎን መውደቅ እንደሚያለቅሱ፣ አማኞችም እንዲሁ ይደሰታሉ!

▣ **"እግዚአብሔር በእርሷ ላይ ፈርዶላችኋልና"** በመጽሐፉ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ከልጆቹ ጸሎት ጋር ይያያዛል (ዝከ. 6፡10)።

> *ራዕይ፡ 18፡21-24*
>
> **[21]አንድም ብርቱ መልአክ ትልቅን ወፍጮ የሚመስልን ድንጋይ አንስቶ ወደ ባሕር ወረወረው እንዲህ ሲል፦ ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን እንዲህ ተገፍታ ትወድቃለች ከእንግዲህም ወዲህ ከቶ አትገኝም። [22]በገና የሚመቱና የሚዘምሩም ድምፅ እንቢልታንና መለከትንም የሚነፉ ድምፅ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም፥ የእጅ ጥበብም ሁሉ አንድ ብልሃተኛ እንኳ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይገኝም፥ የወፍጮ ድምጽም ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም፥ [23]የመብራትም ብርሃን ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይበራም፥ የሙሽራና የሙሽራይቱም ድምጽ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም፤ ነጋዴዎችሽ የምድር መኳንንት ነበሩና፥ በአስማትሽም አሕዛብ ሁሉ ስተዋልና። [24]በእርስዋም ውስጥ የነቢያትና የቅዱሳን ደም በምድርም የታረዱ ሁሉ ደም ተገኘባት።**

**18፡21 "አንድም ብርቱ መልአክ ትልቅን ወፍጮ የሚመስልን ድንጋይ አንስቶ ወደ ባሕር ወረወረው"** ይህ የኤር. 51፡63-64 ጠቃሽ ነው። እሱም ጠንካራ ምንባብ ነው፣ ባቢሎን ፈጽሞ፣ ፈጽሞ በድጋሚ እንደማትነሣ የሚያሳይ። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ቁ. 21-33 ስድስት ድርብ አሉታዎች አሉ፣ "በርግጥ አይሆንም" "በምንም ሁኔታ አይሆንም" እና "ፈጽሞ፣ አይሆንም፣ ፈጽሞ።"

▣ **"ከእንግዲህም ወዲህ ከቶ አትገኝም"** ይህ የሚያሳየው አጠቃላይ የጸና ጥፋትን ነው (ሕዝ. 26፡21)።

**18፡22-23** እነዚህ በጥንታዊው ቅርብ ምስራቅ የዕለት ተ'ለት ሕይወት ጽምፆች ናቸው። የእግዚአብሔር ፍርድ፣ አምላክ የለሹን ማኅበረሰብ ወደ ፍጻሜ ያመጣዋል (ኢሳ. 24፡8፤ ኤር. 7፡34፤ 25፡10፤ ሕዝ. 26፡13)።

**18፡23 "በአስማትሽም አሕዛብ ሁሉ ስተዋልና"** ይህ የናሆም 3፡4 ጠቃሽ ነው። ቁ. 23-24 ላይ ለታላቂቱ ከተማ መውደቅ ሦስት ምክንያቶች መዘርዘራቸውን ተገንዘብ።

1. ኩራትና ብልጥግና (ኢሳ. 23፡8)
2. ጣኦት አምላኪነትና አስማት (ሌዋ. 19፡26፣33፤ ዘዳ. 18፡9-12)
3. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማሳደድ (ዝከ. 16፡6፣ 17፡6)።

**18፡24** ይህ የኤር. 51፡49 ጠቃሽ ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ምዕራፍ 17 እና 18 ጽሑፋዊ ምድቦች ናቸውን? ከሆኑስ፣ ለምን?
2. ባቢሎን ስትወድቅ ለመተርጎም እጅግ አስቸጋሪ የሆነው ስለምንድነው?
3. በዮሐንስ ቀን ታላቂቱ ጋለሞታ ባቢሎን ማን ነው የምታመለክተው? በእኛ ቀንስ? በፍጻሜ ዘመንስ?
4. 14፡8፤ 17፡2፤ 18፡3 ላይ የተጠቀሱት ኢ-ሞራላዊነት እና ወይን ምንን ያመለክታሉ፣ ከዚህ ዓለም ሥርዓት ጋር በተያያዘ?
5. 17፡10-11 ያንተን ትርጉም እባክህን ግለጽ።
6. አብዛኞቹ የዮሐንስ ጠቃሾች ከየትኛው የብኪ መጽሐፍ ነው የተወሰዱት?

# ራዕይ 19
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| (18፡21-19፡4)<br>የበጉ የጋብቻ ራት<br>19:5-8<br>19:9-10 | ሰማይ በባቢሎን ተደሰተ<br>19፡1-10 | በሰማይ ምስጋና<br>19፡1-4<br>19:5-8<br>19:9-10 | (18፡24-19፡4)<br>የበጉ ሰርግ ግብዣ<br>19:5-8<br>19:9<br>19:10ሀ-ለ<br>19:10ሐ | የድል ዝማሬ በሰማይ<br>19፡1-4<br>19:5-10 |
| በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው<br>19:11-16 | ክርስቶስ በነጭ ፈረስ ላይ<br>19:11-16<br>አውሬውና ሠራዊቱ ድል ተነሡ<br>19:17-21 | የክርስቶስ ድልና ሰማያዊ ሠራዊቱ<br>19:11-16 | በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው<br>19:11-16 | የመጨረሻው የፍጻሜ ዘመን ውጊያ<br>19:11-16 |
| 19:17-21 | | 19:17-21 | 19:17-18<br>19:19-21 | 19:17-18<br>19:19-21 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ vii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

**ጽሑፋዊ ይዘት ራዕይ 19:1-21**

ሀ. በዚህ የራዕይ ክፍል የምዕራፍ ምድብ ሁነኛ ባልሆነ ስፍራ ነው የተደረገው (የምዕራፍ ምድቦች፣ የአንቀጽ ምድቦች፣ የቁጥር ምድቦች፣ ጉልህ ፊደላት፣ እና ሥርዓተ-ነጥብ የዋነኛው ተመስጧዊ ግሪክ ጽሑፍ ክፍል አይደለም)። ራዕይ 19፡1-10 በግልጽ የማጠቃለያ ነጥብ ነው፣ ለታላቋ ጋለሞታ ጥፋት፣ 17፡1-18፡24 ለተጠቀሰው። ሰዎች በሶርያና በባቢሎን መውደቅ በብኪ እንደተደሰቱ፣ አሁን ቅዱሳን መላእክት (ዝከ. ቁ. 4) በጋለሞታዋ በባቢሎን ውድቀት ይደሰታሉ (ማለትም፣ ከእግዚአብሔር የራቀ የሰው መንግሥት)፣ አማኞች 18፡20 ላይ እንዳደረጉት።

ለ. 19፡1-10 ያለው ተለጣጣቂ ምስጋና ለ18፡20 ምላሽ ነው።

ሐ. ይህ ባጠቃላይ ግንዛቤ የተያዘው የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እንደሚያስረዳ ምዕራፍ ነው (ዝከ. 19፡11-16)። ነገር ግን መታየት የሚኖርበት ይህ ምዕራፍ ሌለኛውን የፍርድ ዑደት እንደሚዘጋ ነው። የክርስቶስ ምጽአት በዚህ ምዕራፍ ተገልጿል፣ በሁነኛ የአይሁድ ቃላት፣ ይኸውም ባጠቃላይ 1 ተሰ. 4፡14-18 ላይ ካለው ከጳውሎሳዊው ገለጻ የተለየ የሆነ። አይሁድ መሲሑ የሚመለስበትን ሁኔታ ተስፋ ያደረጉበት የተገለጸበት፣ ቁ. 11-16 ላይ። አኪ ዳግም ምጽአቱን የሚገልጸው በበርካታ የተለያዩ ነገር ግን በተዛመዱ መንገዶች ነው። አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የፍጻሜውን ዘመን የሚመለከቱት

ከኢየሱስ የደብረዘይት ተራራ ገለጻ አኳያ ነው (ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ ሉቃስ 21) እና በጳውሎስ "የዐመጽ ሰው" ገለጻ አኳያ (2 ተሰሎንቄ 2)።

መ. ለሚሣቀዩና ለሚሳደዱ፣ ኢየሱስ እንደ ተዋጊ፣ ተከላካይ፣ እና ፈራጅ መሆኑ የሚያበረታታ ነው።

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

**ራዕይ፡ 19፡1-5ሀ**

**[1-2]ከዚህ በኋላ በሰማይ። ሃሌ ሉያ፤ በዝሙትዋ ምድርን ያጠፋችይቱን ታላቂቱን ጋለሞታ ስለ ፈረደባት፥ የባሪያዎቹንም ደም ከእጅዋ ስለ ተበቀለ፥ ፍርዶቹ እውነትና ጽድቅ ናቸውና ማዳንና ክብር ኃይልም የአምላካችን ነው ብሎ ሲናገር እንደ ብዙ ሕዝብ ታላቅ ድምፅ ያለ ድምፅን ሰማሁ። [3]ደግመውም። ሃሌ ሉያ አሉ፤ ጢስዋም ለዘላለም እስከ ዘላለም ይወጣል። [4]ሀያ አራቱም ሽማግሌዎችና አራቱ እንስሶች በፊታቸው ተደፍተው በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለእግዚአብሔር፦ አሜን፥ ሃሌ ሉያ እያሉ ሰገዱለት። [5]ድምፅም። ባሪያዎቹ ሁሉ እርሱንም የምትፈሩት ታናናሾችና ታላላቆች ሆይ፥ አምላካችንን አመስግኑ**

**19፡1 "እንደ ብዙ ሕዝብ ታላቅ ድምፅ ያለ ድምፅን በሰማይ ሰማሁ።"** ይህ የኤር. 51፡48 ጠቃሽ ነው። ምዕራፍ 17-18 በእጅጉን ከኤርምያስ 50-51 የተቀዳ ነው (የባቢሎን ውድቀት) ለምስያቸው። ይኸው ተመሳሳይ ሐረግ ወይም ጽንሰ-ሐሳብ ደግሞ ራዕ. 11፡15 ላይ ይገኛል (ዳግም ምጽአቱ፣ ከሰባተኛው መለከት በኋላ) እና 19፡6። ሕዝቦቹ እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ብዙ ውይይት ተደርጓል፣ ግን እሱ ታማኝ የሆኑት የመላእክት ሠራዊት ይሁን፣ የተዋጁት ሰዎች፣ ወይም ሁለቱም ይሁን ግምት ነው።

▣ **"ሃሌሉያ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ፍቹ "ያህዌ ይመስገን" ነው (ቢ.ዲ.ቢ 237 II እና 219)። ይህ ብቸኛው የዚህ ቃል መከሰቻ ነው፣ በአኪ። እሱም በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ አራት ጊዜ ተከስቷል፡ ቁ. 1፣3፣4፣ እና 6። የብኪ ዳራ ለዚህ የሚገኘው በምስጋና መዝሙሮች ላይ ነው፣ በሁለቱም በፋሲካና በዳስ በዓላት ላይ (ዝኪ. 104፡35፤ 105፡45፤ 106፡48፤ 111፡1፤ 112፡1፤ 113፡1፤ 116፡19፤ 117፡2፤ 125፡1፣21፤ 146፡1፣10፤ 147፡1፤148፡1፣14፤ 149፡1፣9፤ 150፡1፣6)። ትይዩ ሐረግ ቁ. 5ለ ላይ ይገኛል።

▣ **"መዳን"** ይህ ባሕርይ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ሐሳብ ነው፣ ለሰው ልጆች ሁሉ ያለውን (ዝኪ. 9፡20-21፤ 14፡6-7፤ 16፡9፣11፤ 21፡7፤ 22፡17፤ ሕዝ. 18፡23፣30-32፤ ዮሐንስ 3፡16፤ 4፡42፤ I ጢሞ. 2፡4፤ 4፡10፤ II ጴጥ. 3፡9፤ I ዮሐንስ 4፡14)። እሱም ሊጠቅስ የሚችለው የብኪ ጽንሰ-ሐሳብን ነው፣ አካላዊ ትድግና፣ ነገር ግን ከአጠቃላይ፣ ዘላለማዊ፣ ፍጥረታዊ ደኅንነት ጋር ሊዛመድ ይችላል፣ ለሚያምኑ ግለሰቦች፣ እና ለሁሉም ሥጋዊ ፍጥረት (ሐዋ. 3፡21፤ ሮሜ. 8፡18-25፤ ቆላ. 1፡19)።

▣ **"ክብርና ኃይል"** በመጽሐፉ ሁሉ ሰማያዊ መዘምራን ለእግዚአብሔር በምስጋና ይዘምራሉ። እነዚህ የምስጋና ዝማሬዎች ዘወትር የዐውደ-ጽሑፉን የወዲያውነት ለመተርጎም ቁልፍ ናቸው።

**19፡2 "ፍርዶቹ እውነትና ጽድቅ ናቸውና"** ይህ ጠቃሽነቱ መዝ. 19፡9፤ 119፡138 እና 142 ይሆናል። የእግዚአብሔር ፍርዶች ተገቢና ፍትሐዊ ናቸው (በሦስቱ የፍርድ ዑደቶች ታይተዋል)። ይህም በመከራ ውስጥ ለሚያልፉ ክርስቲያን ወገኖች የሚያበረታታ ነበር (ዝኪ. ቁ. 11፤ 15፡3፣4፤ 16፡7)።

▣ **"ታላቂቱ ጋለሞታ"** ይህ የወደቀ፣ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የዓለም ሥርዓት በብዙ ስሞች ይጠራል፡

1. ታላቂቱ ከተማ
2. ባቢሎን
3. ጋለሞታዋ (ዝኪ. 14፡8፤ 16፡19-21፤ 17፡1-18፡24)

ቁጥር 1-4 ከምዕራፍ 17 እና 18 ዐውደ-ጽሑፉን የሚቀጥሉ ናቸው።

▣ **"በዝሙትዋ ምድርን ያጠፋችይቱን"** ይህ የሚያመለክተው ቁሳዊነትን፣ አመንዝራነትን፣ ወይም ኢ-ሞራላዊ የሆነ የጣዖት የመራባት አምልኮት፣ ወይም የአጼ አምልኮ ነው (ዝኪ. 2፡14፣20፣21፤ 9፡21፤ 14፡8፤ 17፡2፣4፤ 18፡3)።

**ልዩ ርዕስ፡ ማውደም፣ ማበላሸት፣ ማጥፋት (PHTHEIRō)**

የዚህ ቃል መሠረታዊ ፍች *phtheirō* ማውደም፣ ማበላሸት፣ ማጥፋት ወይም መጉዳት ነው። እሱም ጥቅም ላይ የሚውለው

1. ገንዘብን ማጥፋት (ምናልባት 2 ቆሮ. 7፡2)
2. አካላዊ ጉዳት (1ቆሮ. 3፡17ሀ)
3. የሞራል መበላሸት (ሮሜ.1፡23፤ 8፡21፤ 1ቆሮ. 15፡33፣42፣50፤ ገላ. 6፡8፤ ራዕ. 19፡2)
4. ወሲባዊ ጥቃት (2ቆሮ. 11፡3)
5. ዘላለማዊ ጥፋት (2ጴጥ. 2፡12፣19)
6. የሰዎችን ወጎች ማጥፋት (ቆላ. 2፡22፤ 1ቆሮ. 3፡17ለ)

ይህ ቃል ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው በተመሳሳይ ዐውደ-ጽሑፍ እንደ አሉታዊ ተቃራኒ ሆኖ (ሮሜ 1፡23፤ 1ቆሮ. 9፡25፤ 15፡50፣53)። ትይዩአዊ ተቃርኖዎቹ በእኛ ምድራዊ ሥጋዊ አካላትና በእኛ ሰማያዊ ዘላለማዊ አካላት መካከል እንደሆኑ ተገንዘብ።

1. የሚበላሽ በተቃርኖ የማይበላሽ፣ 1ቆሮ. 15፡42፣50
2. ውርደት በተቃርኖ ክብር፣ 1ቆሮ. 15፡43
3. ድካም በተቃርኖ ብርታት፣ 1ቆሮ. 15፡43
4. የተፈጥሮ አካል በተቃርኖ፣ መንፈሳዊ አካል፣ 1ቆሮ. 15፡44
5. ፊተኛው አዳም በተቃርኖ ኋለኛው አዳም፣ 1ቆሮ. 15፡45
6. የምድራዊ መልክ በተቃርኖ የሰማያዊ መልክ፣ 1ቆሮ. 15፡49

▣ **"የባሪያዎቹንም ደም ከእጅዋ ስለ ተበቀለ፥"** ይህ የዘዳ. 32:43 ወይም II ነገ. 9:7 (ሮሜ. 12:19) ጠቃሽ ነው። እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ጸሎት በኩል ይሠራል (ዝከ. 6:9-11፤ ማቴ. 7:7-8፤ 21:22፤ ዮሐንስ 21:22፤ 14:13-14፤ 15:7፣16፤ 16:23-24፣ 26፤ ያዕቆብ 4:2፤ I ዮሐንስ 3:22፤ 5:14-16)።

የእግዚአብሔር ተቃዋሚው የዓለም ሥርዓት ዘወትር የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዳሳደደና እንደገደለ ነው። እግዚአብሔር ለክፉ ይፈቅዳል፣ እውነተኛ ሐሳቡ እንዲታወቅ (ዝከ. 13፡5፣7፣15)።

**19፡3 "ጢስዋም ለዘላለም እስከ ዘላለም ይወጣል"** ይህ የኢሳ. 34፡10 ጠቃሽ ነው፣ እሱም ሁለንተናዊውን ፍርድ የሚያመለክት። ማስታወስ ያለብን ይህ ጽሑፋዊ ዘውግ (አፖካሊፕቲካዊ) እውነትን ለማሳየት ተምሳሌትን መጠቀሙን ነው። እዚህ እውነቱ ሊሆን የሚችለው ከሁለት አንዱ ታሳቢ ማዕከላዊ ነጥብ ነው፡

1. ዘላለማዊ ቅጣት (ዝከ. 6:10፤ ማቴ. 3:12፤ 25:41፤ ሉቃስ 3:17፤ ማርቆስ 9:43፣48)
2. አጠቃላይ ጥፋት (ኢሳ. 34:8-10)። ይኸው ተመሳሳይ እውነት ራዕ. 14:11 ላይ ይገኛል

**19፡4 "ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች"** ልዩ ርዕስ 4፡4 ላይ ተመልከት።

▣ **"አሜን"** ይህ ቃል 1:6፣7፤ 3:14፤ 5:14 እና 7:12፤ 19:4፤ 22:20፤ እና 22:21 ጥቅም ላይ ውሏል። እሱም የብኪ ዕብራይስጥ ቃል ሲሆን "ለእምነት" (*emeth*፣ ዕን. 2:4)። የእሱ ዋና ሥርወ-ቃል "መጽናት" ወይም "ርግጠኛ መሆን" ነው። እሱም በብኪ ጥቅም ላይ የሚውለው ለእግዚአብሔር ታማኝነት ነው። ሆኖም፣ በአኪ የእሱ አጠቃቀም በቅድሚያ ከጌታ ራት ጋር ነው፣ "ተስማምቻለው" ወይም "አጽንቻለሁ" በሚል መልኩ ነው። ልዩ ርዕስ፡ አሜን 1፡6 ላይ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ እና ታማኝነት በብሉይ ኪዳን (rma )

I. የመክፈቻ መግለጫ

የዚህን ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ አጠቃቀም መቀመጥ የሚኖርበት፣ ለአዲስ ኪዳን በጣም ወሳኝ እንደሆነ ነው፣ በብኪ በግልጽ እንደ ተቀመጠው ሳይሆን። እሱ በርግጥ እዚያ ነው፣ ነገር ግን የተገለጠው በተመረጡ ቁልፍ አንቀጾችና ሰዎች ነው።
ብኪ የሚቀይጠው

ሀ. ግለሰብን እና ማኅበረሰቡን
ለ. የግለሰብን ገጠመኝ እና ኪዳናዊ መታዘዝን
እምነት ግለሰባዊ ገጠመኝና የየቀኑ የአኗኗር ስልት ነው! እሱም በግለሰብ ማስረዳት ይቀላል፣ በቃላታዊ መልኩ ከመግለጽ ይልቅ (ማለት፣ የቃላት ጥናት)። ይህ ግለሰባዊ ገጽታ በተሻለ የተገለጠው
ሀ. አብርሃምና ዘሩ
ለ. ዳዊትና እስራኤል

እነዚህ ሰዎች የተገናኙት/ያጋጠማቸው እግዚአብሔር ነው እንዲሁም ሕይወታቸው በቋሚነት ተለውጧል (የፍጽምና ሕይወት አይደለም፣ ግን ቀጣይነት ያለው እምነት)። ፈተና የእምነታቸውን ድካምና ጥንካሬ ይገልጣል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት፣ ግን ጓደኛዊ፣ መተማመን ያለበት ግንኙነት በጊዜ ሁሉ ይቀጥላል! እሱም ተፈትኗል ጠርቷልም፣ ግን እሱ ይቀጥላል እንደ መሰጠታቸውና የሕይወት ስልታቸው ማስረጃ።

II. ዋናው ሥርወ ቃል አጠቃቀሙ

ሀ. אמן (ቢዲቢ 52)

1. ግሥ VERB

ሀ. *Qal* stem ግንድ — ለመደገፍ፣ ለመንከባከብ (ማለትም፣ 2ኛ ነገሥ. 10:1፣5፤ አስቴር 2:7፣ ሥነ-መለኮታዊ ያልሆነ አጠቃቀም)

ለ. *Niphal* stem ኒፋል ግንድ — ርግጠኛ ለመሆን ወይም ለማጽናት፣ ለማቆም፣ ለማረጋገጥ፣ ታማኝ ለመሆን ወይም የሚታመኑት

(1) ለሰዎች፣ ኢሳ. 8:2፤ 53:1፤ ኤር. 40፤14
(2) ለነገሮች፣ ኢሳ. 22፡23
(3) ለእግዚአብሔር፣ ዘዳ. 7:9፣12፤ ኢሳ. 49:7፤ ኤር. 42:5

ሐ. *Hiphil* stem ሂፊል ግንድ — ጸንቶ መቆም፣ ማመን፣ መታመን

(1) አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ፣ ዘፍ. 15፡6
(2) እስራኤላውያን በግብፅ አመኑ፣ ዘጸ. 4:31፤ 14:31 (ከዘዳ. 1:32 የሚቃረን)
(3) እስራኤላውያን ያህዌን አመኑ፣ በሙሴ በኩል የተናገራቸውን፣ ዘጸ. 19:9፤ መዝ. 106:12፣24
(4) አካዝ በእግዚአብሔር አላመነም፣ ኢሳ. 7፡9
(5) በእሱ የሚያምን ሁሉ፣ ኢሳ. 28፡16
(6) ስለ እግዚአብሔር የሚታመኑ ሐቆች፣ ኢሳ. 43፡10-12

2. ስም (ተባዕታይ) — ታማኝነት (ማለትም፣ ዘዳ. 32:20፤ ኢሳ. 25:1፤ 26:2)
3. ተውሳከ ግሥ — በእውነቱ፣ በጣሙን፣ እስማማለሁ፣ እንዲህ ሊሆን ይችላል (ዘዳ.27:15-26፤ 1 ነገሥ. 1:36፤ 1 ዜና. 16:36፤ ኢሳ. 65:16፤ ኤር. 11:5፤ 28:6)። ይህ የ "አሜን" የኅብረት አምልኳዊ አጠቃቀም ነው፣ በብኪ እና በአኪ።

ለ. (תמא ቢዲቢ 54) አንስታይ ስም፣ ጽናት፣ ታማኝነት፣ እውነት
1. ለሰዎች፣ ኢሳ. 10:20፤ 42:3፤ 48:1
2. ለእግዚአብሔር፣ ዘጸ. 34:6፤ መዝ. 117:2፤ ኢሳ. 38:18፣19፤ 61:8
3. ለእውነት፣ ዘዳ. 32:4፤ 1 ነገሥ. 22:16፤ መዝ. 33:4፤ 98:3፤ 100:5፤ 119:30፤ ኤር. 9:4፤ ዘካ. 8:16

ሐ. תנומא (ቢዲቢ 53)፣ ጽናት፣ ጽኑዕነት፣ አማኝነት
1. ለእጆች፣ ዘጸ. 17፡12
2. ለጊዜ፣ ኢሳ. 33፡6
3. ለሰዎች፣ ኤር.5:3፤ 7:28፤ 9:2
4. ለእግዚአብሔር፣ መዝ. 40:11፤ 88:12፤ 89:2፣3፣6፣9፤ 119:138

III. የጳውሎስ የብኪ ጽንሰ-ሐሳብ አጠቃቀም ךמא

ሀ. ጳውሎስ የያህዌንም ሆነ የብኪ አዲሱን መረዳቱን መሠረት ያደረገው በራሱ ግላዊ ድንገተኛ ግንኙነት ነው፣ ከኢየሱስ ጋር በደማስቆ መንገድ (ሐዋ. 9፤ 22፤ 26)።

ለ. እሱም የብኪን ድጋፍ ፈልጓል ለአዲሱ መረዳቱ በሁለት የብኪ ቁልፍ አንቀጾች ላይ፣ እነሱም ሥርን የሚጠቀሙ
1. ዘፍ. 15፡6 — የአብራም ግለሰባዊ ግንኙነቱ የተነሣሣው በእግዚአብሔር ነው (ዘፍጥረት 12) ውጤቱም በእምነት የመታዘዝ ሕይወት የሆነ (ዘፍጥረት 12-22)። ጳውሎስ ይሄንን በሮሜ 4 እና ገላትያ 3 ላይ ጠቅሶታል።

2. ኢሳ. 28፡16 — በእሱ የሚያምኑ ሁሉ (ማለትም፣ እግዚአብሔር የፈተነው እና ያስቀመጠው የማዕዘን ድንጋይ) ፈጽሞ
ሀ. ሮሜ 9፡33፣ "አያፍርም" ወይም "ቅር አይሰኝም"
ለ. ሮሜ 10፡11፣ እንደ ላይኛው የሆነ
3. ዕንባ. 2፡4 — እነሱ ታማኙን እግዚአብሔርን የሚያውቁ የመታመን ሕይወት መኖር ይኖርባቸዋል (ኤር. 7፡28)።
ጳውሎስ ይሄንን ጽሑፍ በሮሜ 1:17 እና ገላ. 3፡11 (ዕብ. 10፡38 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

IV. የጴጥሮስ የብሉይ ኪዳንን ጽንሰ ሐሳብ አጠቃቀም

ሀ. ጴጥሮስ የደባለቀው
1. ኢሳ. 8:14 – 1 ጴጥ. 2:8 (የማሰናከያ ድንጋይ)
2. ኢሳ. 28:16 – 1 ጴጥ. 2:6 (የማዕዘን ድንጋይ)
3. መዝ. 111፡22– 1 ጴጥ. 2:7 (የተናቀ ድንጋይ)

ለ. እስራኤልን የሚገልጸውን የተለየ ቋንቋ ገለበጠው፣ "የተመረጠ ዘር፣ የንጉሥ ክህነት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለእግዚአብሔር ርስት የሆነ ሕዝብ" ሀ. ዘዳ.10:15፤ ኢሳ. 43:21
ለ. ኢሳ. 61:6፤ 66:21
ሐ. ዘጸ. 19:6፤ ዘዳ. 7:6
እና አሁን የተጠቀመው በክርስቶስ ባለ የቤተ-ክርስቲያን እምነት ነው

V. የዮሐንስ የጽንሰ-ሐሳቡ አጠቃቀም

ሀ. የእሱ የአዲስ ኪዳን አጠቃቀም
"አመነ" የሚለው ቃል ከግሪክ ቃል (*pisteuō*) ሲሆን፣ እሱም ደግሞ የሚተረጎመው "ማመን፣" "እምነት፣" ወይም "መታመን" በሚል ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ስሙ በዮሐንስ ወንጌል ላይ አልተከሰተም፣ ግሡ ግን ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል። በዮሐንስ 2፡23-25 የሕዝቡ ቅንነት የተሞላው መሰጠት መኖሩ ርግጠኛ አይደለም፣ የናዝሬቱን ኢየሱስ እንደ መሲሕ ለመቀበል። ሌለኛው ምሳሌ፣ የዚህ ቃል "ማመን" ጥራዝ ነጠቃዊ አጠቃቀም የሚገኘው በዮሐንስ 8፡31-59 እና ሐዋ. 8:13፣ 18-24. ላይ ነው። እውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ከመነሻው ምላሽ ላቅ ይላል። እሱም መከተል ያለበት ወደ ደቀመዝሙራዊ ሂደት ነው (ማቴ. 13:20-22፣31-32)።

ለ. የእሱ አጠቃቀም ከመስተፃምር ጋር
1. *eis* ማለት "ወደ... ውስጥ (በ)" ማለት ነው። ይህ የተለየ ዓይነት አወቃቀር አጽንዖት የሚሰጠው አማኞች እምነታቸውን/መታመናቸውን ማድረግ ያለባቸው በኢየሱስ ላይ ነው
ሀ. በስሙ (ዮሐንስ 1:12፤ 2:23፤ 3:18፤ 1 ዮሐንስ 5:13)

ለ. በእሱ (ዮሐንስ 2፡11፤ 3፡15፣18፤ 4፡39፤ 6፡40፤ 7፡5፣31፣39፣48፤ 8፡30፤ 9፡36፤ 10፡42፤ 11፡45፣ 48፤ 17፡37፣42፤ ማቴ. 18፡6፤ ሐዋ 10፡43፤ ፊሊጵ. 1፡29፤ 1 ጴጥ. 1፡8)

ሐ. በእኔ (ዮሐንስ 6፡35፤ 7፡38፤ 11፡25፣26፤ 12፡44፣46፤ 14፡1፣12፤ 16፡9፤ 17፡20)

መ. በልጁ (ዮሐንስ 3፡36፤ 9፡35፤ 1 ዮሐንስ 5፡10)

ሠ. በኢየሱስ (ዮሐንስ 12፡11፤ ሐዋ. 19፡4፤ ገላ. 2፡16)

ረ. በብርሃኑ (ዮሐንስ 12፡36)

ሰ. በእግዚአብሔር (የሐንስ 14፡1)

2. *en* ኢን ማለት "ውስጥ" ነው፣ እንደ ዮሐንስ 3፡15፤ ማርቆስ 1፡15፤ ሐዋ. 5፡14
3. *epi* ኢፒ ማለት "ውስጥ" ወይም "በላይ፣" ነው፣ እንደ ማቴ. 27፡42፤ ሐዋ. 9፡42፤ 11፡17፤ 16፡31፤ 22፡19፤ ሮሜ. 4፡5፣ 24፤ 9፡33፤ 10፡11፤ 1 ጢሞ. 1፡16፤ 1 ጴጥ. 2፡6
4. ቀጥተኛ ያልሆነ የግሥ ተሳቢ፣ ያለ መስተጻምር እንደ ገላ. 3፡6፤ ሐዋ. 18፡8 27፡25፤ 1 ዮሐንስ 3፡23፤ 5፡10
5. *hoti* ሆቲ፣ ፍችውም "ያመነው" ምን እንዳመነ ይዘቱን ያመለክታል

ሀ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱሱ መሆኑን (ዮሐንስ 6፡69)

ለ. ኢየሱስ ያለና የሚኖር ነው (ዮሐንስ 8፡24)

ሐ. ኢየሱስ በአብ አለ፣ አብም በእሱ አለ (ዮሐንስ 10፡38)

መ. ኢየሱስ መሲሕ ነው (ዮሐንስ 11፡27፤ 20፡31)

ሠ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ዮሐንስ 11፡27፤ 20፡31)

ረ. ኢየሱስ የተላከው በአብ ነው (ዮሐንስ 11፡42፤ 17፡8፣21)

ሰ. ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለው ነው (ዮሐንስ 14፡10-11)

ሸ. ኢየሱስ ከአብ የመጣው ነው (ዮሐንስ 16፡27፣30)

ቀ. ኢየሱስ ራሱን በአብ የኪዳን ስም፣ "እኔ ነኝ" በሚል ገልጿል (ዮሐንስ 8፡24፤ 13፡19)

በ. እኛም ከእሱ ጋር እንኖራለን (ሮሜ 6፡8)

ተ. ኢየሱስ ሞቶ ዳግም ተነሥቷል (1ኛ ተሰ. 4፡14)

VI. *መደምደሚያ*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ለመለኮታዊ ቃል/ተስፋ የሰዎች ምላሽ ነው። እግዚአብሔር ዘወትር መነሻውን ይወስዳል (ማለትም፣ ዮሐንስ 6፡44፣65)፣ ነገር ግን የዚህ መለኮታዊ ግንኙነት ክፋይ ለሰዎች ምላሽ ተትቷል።*

*ሀ. ማመን*

*ለ. ኪዳናዊ መታዘዝ*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት*

1. *ግለሰባዊ ግንኙነት ነው (መነሻ እምነት)*
2. *የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት መተማመኛ ነው (በእግዚአብሔር መገለጥ ማመን)*
3. *ለእሱም ምላሽ በሚሆን ተገቢ ምላሽ (የየዕለቱ እምነት)*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ለመንግሥተ ሰማያት ትኬት አይደለም ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲ። እሱ ግለሰባዊ ግንኙነት ነው። ይህ የፍጥረት እና የሰው ልጆች ዓላማ ነው፣ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ለተፈጠሩት (ዘፍ. 1፡26-27)። ፍሬ ነገሩ "መቀራረብ" ነው። እግዚአብሔር ኅብረትን ይሻል፣ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ አቋም ሳይሆን! ነገር ግን ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር የሚሆን ኅብረት፣ ልጆች "የቤተሰባቸውን" ባሕርይ እንደሚያንጸባርቁት ያለውን ይጠይቃል (ማለትም፣ ቅድስና፣ ሌዋ. 19፡2፤ ማቴ. 5፡48፤ 1 ጴጥ. 1፡15-16)።*

*ውድቀት (ዘፍጥረት 3) ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ችሎታችንን ጎዳው። ስለሆነም፣ እግዚአብሔር በእኛ ፈንታ አደረገ (ሕዝ. 36፡27-38)፣ "አዲስን ልብ" በመስጠት፣ እንዲሁም "አዲስ መንፈስ፣" እሱም በእምነት እና ንስሐ በመግባት በኩል ከእሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረንና እንድንታዘዘው የሚያስችለንን!*

*እነዚህ ሦስቱም ዋነኞች ናቸው። ሦስቱም ሁሉ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ግቡም እግዚብሔርን ለማወቅ ነው (በዕብራውያንና በግሪክ አግባቦች) እንዲሁም በሕይወታችን የእሱን ባሕርይ ማንጸባረቅ። የእምነት ግብ አንድ ቀን የሚገኝ መንግሥተ ሰማይ አይደለም፣ ነገር ግን በእየቀኑ ክርስቶስን መምሰል ነው!*

*የሰዎች ታማኝነት ውጤቱ ነው (አኪ)፣ መሠረቱ ሳይሆን (ብኪ) ከእግዚብሔር ጋር ላለ ግንኙነት፡ የሰዎች እምነት በእሱ ታማኝነት፤ የሰዎች መታመን በአሱየታ መነ መሆን ላይ። አንኳሩ የአዲስ ኪዳን አመለካከት በደኅንነት ላይ የሚሆነው፣ ሰዎች የግድ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል ከመነሻውም ሆነ በቀጣይነት፣ መነሻ ለሆነው ጸጋ እና የእግዚአብሔር ምሕረት፣ በክርስቶስ ለተገለጠው። እሱ ወዷል፣ እሱ ልኳል፣ እሱ ሰጥቷል፤ እኛም በእምነትና በታማኝነት ምላሹን ልንሰጥ ይገባል (ኤፌ. 2፡8-9 እና 10)!*

*ታማኙ እግዚአብሔር ታማኝ የሆነ ሕዝብ ይሻል፣ ራሱን ለእምነተ ቢሱ ዓለም ለመግለጽና በእሱ ላይ ለሚሆን ግላዊ እምነት ለማምጣት።*

**19፡5 “ከዙፋኑም ድምጽ መጣ፤ እንዲህ ሲል”** “አምላካችን” ከሚለው ሐረግ የተነሣ (ቁ. 5ለ)፣ ይህ መልአክ መሆን አለበት፣ መለኮት ሳይሆን። ኢየሱስ እግዚአብሔርን ፈጽሞ “አምላካችን” ብሎ ጠርቶ አያውቅም (ሚካኤል ማጊል፣ *NT Transline*፣ ገጽ 1011)።

> ***ራዕይ፡ 19፡5ለ-6ሀ***
> **[5ለ]ድምፅም። ባሪያዎቹ ሁሉ እርሱንም የምትፈሩት ታናናሾችና ታላላቆች ሆይ፥ አምላካችንን አመስግኑ [6ሀ]ሲል ከዙፋኑ ወጣ። እንደ ብዙ ሕዝብም ድምፅ፥ እንደ ብዙ ውኃዎችም ድምፅ፥ እንደ ብርቱም ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ድምፅ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦**

▣ **“አምላካችንን አመስግኑ”** ይህ የመዝ. 115፡13፤ 134፡1፤ 135፡1 ጠቃሽ ነው። ቃሉ የአሁን የድርጊት ተተኳሪ ነው፣ እሱ ግን ከ “ሃሌሉያ” ይልቅ የተለየ ነው፣ ቁ. 1፣3፣4 እና 6 ላይ ከሚገኘው። እሱ ከሥነ-መለኮት አኳያ ያልተለመደ ነው፣ ይኸውም መልአክ “አምላካችን” የሚል ቃል መጠቀሙ፣ ነገር ግን ቁ. 10 የሚያሳየው መላእክት ራሳቸውን የሚያስተዋውቁት ከቅዱሳን ጋር በአገልግሎት ብቻ አይደለም፣ ግን ደግሞ ከቅዱሳን ጋር ከምስክርነታቸው ጋር ነው፣ ኢየሱስን በተመለከተ።

▣ **“ባሪያዎቹ ሁሉ እርሱንም የምትፈሩት ታናናሾችና ታላላቆች”** ይህ የመዝ. 115፡13 ጠቃሽ ነው (እሱም ቀደም ብሎ ራዕ. 11፡18 ላይ የተጠቀሰ)።

**19፡6** እነዚህ ገላጭ የሆኑ ሐረጎች ጥቅም ላይ የዋሉት
1. ለእግዚአብሔር ሕዝ. 43፡2
2. ለብርቱው መልአክ ዳን. 10፡6
3. ለክርስቶስ ራዕ. 1፡15
4. ለተዋጀው ማኅበረሰብ ራዕ. 14፡2
5. ከዐውደ-ጽሑፉ መልአካዊ ኅብረ-ዘማርያን ይመስላል

> ***ራዕይ፡ 19፡6ለ-8***
> **[6]*ሃሌ ሉያ፤ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሦአልና።* [7]የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ። [8]ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጐናጸፍ ተሰጥቶአታል። ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና።**

▣ **“ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን”** ይህ ሦስትዮሽ የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው፣ ከብኪ (ያህዌ፣ *ኤሎሒም*፣ እና *ኤል ሻዳይ።* ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች 4፡8 ላይ ተመልከት) በተለያየ መንገድ ይከሰታል 1፡8፤ 4፡8፤11፡7፣ 15፡3፣ 16፡7፣14፤ 19፡15፤ እና 21፡22 ላይ።

“የእኛ” የሚለው ተውላጠ ስም እጅግ ያልተለመደ ነው፣ በመልአክ በመነገሩ ሳቢያ። እሱም በሌላ በማናቸውም ስፍራ አልተከሰተም፣ በእዚህ ሦስትዮሽ መጠሪያ። ሆኖም፣ ጽሑፋዊ ማስረጃው፣ ለእሱ አጠቃላይነት ጠንካራ ነው።
1. “ጌታ አምላካችን” በጥንታዊ ማስተካከያ ከMS ℵ[2] (UBS[4] ይህን በጽሑፉ ያስቀምጠዋል፣ ግን “ሐ” ደረጃ ነው የሚሰጠው)
2. “አምላካችን፣ የእኛ ጌታ” ከዋናው MS የ ℵ[2]
3. በአንዳንድ ኋለኛ ቅጥልጥል የግሪክ ጽሑፎች፣ “አምላካችን” (MSS 051፣ 209)
4. “ጌታ እግዚአብሔር” (MS A)
5. “ጌታ” (ፔሺታ እና የኮፕቲክ ቅጅዎች)

▣ **“የሚገዛ”** በርካታ ውይይቶች ተካሂደዋል፣ በድርጊት ግሥ ጊዜ ምክንያት (ዝኪ. 11፡17)። አንዳንዶች እሱን የሚመለከቱት፣ እግዚአብሔር መግዛት መጀመሩን ነው (መግባት ወይም የድርጊት መጀመር፣ መዝ. 93፡1፤ 97፡1፣ አኢ.መቅ)። ሆኖም፣ እግዚአብሔር ዘወትር እንደ ገዛ ነው (ቋሚ ወይም የድርጊት እውነታ፣ መዝ. 99፡1)። አንዳንዶች እሱን የሚመለከቱት እግዚአብሔር አሁን በምድር ላይ መንገሡን ነው፣ እንደ ሰማዩ (የመጨረሻው ወይም ብቃት ያለው ድርጊት፣ ማቴ. 6፡10)። የዘመኑ ፍጻሜ እና የእግዚአብሔር መንግሥት ቅድጅት በርካታ ጊዜ ራዕይ ላይ ተከስቷል፣ በተለያዩት የፍርድ ዑደቶች መጨረሻ ላይ (ማኅተሞች፣ መለከቶች፣ ጽዋዎች)። ይህም ከ11፡15 ጋር ትይዩ ይመስላል። እሱም የኢሳ. 24፡23፤ 52፡7 ወይም ሚክያስ 4፡7 ጠቃሽ ነው። ልዩ ርዕስ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት መንገሥ 5፡10 ላይ ተመልከት።

**19፡7** የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ግሦች ቁ. 7 ላይ ሁኔታ ገላጭ ናቸው።
1. እንደሰት — የአሁን የድርጊት
2. ደስ ይበለን — የአሁን የድርጊት

ሦስተኛው ግሥ በርካታ ልዩነቶች አሉት።
1. *dÔsÔmen* (ኢ-መደበኛ የድርጊት የአሁን ሁኔታ ገላጭ) – MS P
2. *dÔsomen* (የወደፊት)፣ “ክብር እንሰጣዋለን” – MSS ℵ[2]፣ A
3. *dÔmen* (የድርጊት የአሁን ሁኔታ ገላጭ) – MS ℵ*

ቁጥር 1 እና 3 እንደ ፊተኞቹ ሁለት ግሦች ሊተረጎሙ ይችላሉ፣ “ክብር እንስጠው።” ቁጥር 2 “ክብር እንሰጠዋለን” በሚል ሊተረጎም ይችላል (የተመት)። ዩቢኤስ[4] ለቁ. 1 “ሐ” ደረጃ ይሰጣል፤ ዩቢኤስ[3] “መ” ደረጃ ይሰጠዋል። ኮሚቴው የትኛው ዋነኛ እንደሆነ መወሰን አልቻለም።

▣ **“ክብርን ስጡት”** ይህ ዘይቤአዊ ሐረግ ይሆናል ለመታመን፣ ለማመን፣ ወይም እምነትን በክርስቶስ ላይ ለመጣል። 11፡13 ላይ የእሱ ፍቺ የተደገመና የአማኞች የሆነ ነው፣ ከእግዚአብሔር የፍርድ ድርጊት የተነሣ። ይህ ሐረግ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጥቅም ላይ ውሏል 14፡7 ላይ፣ እንዲሁም የማያምኑት መከራ ተቀባዮች እግዚአብሔርን ለማምለክ እምቢ ማለታቸው 16፡9።

▣ **“የበጉ ሰርግ”** “በግ” የብኪ *መሥዋዕታዊ* ፍቺ አለው (ሌዋ. 1፡7)። *ይህ ሐረግ የመሥዋዕቱን ነገርና የኅብረት ማዕድን (የሰላም መሥዋዕት) ያያይዛል።* ለዚህ የሰርግ ግብዣ ጠቃሽ አለ፣ ማቴ. 8፡11፤ 26፡29፤ ሉቃስ 14፡15፤ 22፡16 ላይ። የሚያተኩረውም በአይሁድ የሰርግ ወግ የመታጫ ጊዜ፣ የመጠበቂያ ጊዜ፣ እና የሰባት ቀን የሰርግ ግብዣ ላይ ነው። አስገራሚ የሚሆነው ከጥቂት ምንባብ በኋላ ዘይቤው ይቀየራል፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ሙሽራ ሳይሆን፣ እንደ ሰርግ ታዳሚ ሆኖ (ዝኪ. ቁ. 9 እና ማቴ. 22፡1-14)። ዘይቤው እንደገና ደግሞ ይቀየራል 21፡2፣9 ላይ፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ “አዲሲቷ ኢየሩሳሌም።” በእግዚአብሔርና በቤተ-ክርስቲያኑ የሚኖረው የጋብቻ ጽንሰ-ሐሳብ በብኪ ኢሳ. 54፡4-8፤ 62፡5፤ ኤር. 31፡32፤ ሕዝቅኤል 16፤ እና ሆሴዕ 2፡14-19 ላይ ይገኛል። ዘይቤው በአኪ II ቆሮ. 11፡2፤ ኤፌ. 5፡21-31፤ ራዕ. 19፡9፤ 21፡2፣9፤ 22፡17 ላይ ይታያል። ደግሞም ኢየሱስ እንደ ሙሽራ ተወክሏል (ማቴ. 9፡15፤ ማርቆስ 2፡19-20፤ ሉቃስ 5፡34-35፤ ዮሐንስ 3፡29)። በርካታ ምሳሌዎች ይሄንን ጭብጥ ያሳያሉ (ማቴ. 22፡1-14፤ 25፡1-13)። ጋብቻ እጅግ የተሻለው ሰዋዊ ምሳሌ ነው፣ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ኪዳን ጽንሰ-ሐሳብ።

▣ **“ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች”** ይህ የድርጊት የአሁን አመላካች ነው። አንዳንዶች ይሄንን የሚተረጉሙት ሸልማት እንዳለው የሰው *ሥራ* ነው። የቁ. 8 የድርጊት ተገብሮ የሚያሳየው ይህ ትርጓሜ እውነት ሊሆን እንደማይችል ነው። ይህ *ዐውደ-ጽሑፍ* የሚያጸናው በእግዚአብሔር የመነሻ ድርጊት (ዮሐንስ 6፡44፣65)፣ ቁ. 9 ላይ ባለው ግብዣ የሚታየው፣ ይኸውም፣ የተጠናቀቀ ተገብሮ አንቀጽ እና በሰው ልጅ የእምነት ምላሽ አስፈላጊነት (ማርቆስ 1፡15፤ ሐዋ. 3፡16፣19፤ 20፡21) መካከል ያለውን ፓራዶክሳዊ (አያዎ) ግንኙነት ነው። ይህ ፓራዶክሳዊ ግንኙነት ፊሊ. 2፡12-13 ላይ ሊታይ ይችላል። እሱም ድጋፍ ያገኛል፣ ቁ. 8 ላይ ባለው ሐቅ፣ እግዚአብሔር፣ ለመልበስ ፍቃድ በመስጠቱ፣ ልብሱ ግን የሚያመለክተው መልካም *ሥራ* ነው (የጽድቅ *ሥራ*) የእግዚአብሔር ሕዝብ (ዝኪ. 14፡13፤ ኤፌ. 2፡10፤ I ጢሞ. 5፡25)።

*የአዲስ ኪዳን ስዕላዊ ቃላት* ላይ ኤ. ቲ. ሮበርትሰን ቁ. 7 ላይ አስደናቂ አስተያየት አለው። “*ሦስት የሴቶች ዘይቤዎች* በአፖካሊስ ይገኛሉ (እናት ምዕራፍ 12 ላይ፣ ጋለሞታ ከ13 እስከ 19 ላይ፣ እንዲሁም የክርስቶስ ሙሽራ ከዚህ እስከመጨረሻ)። ‘አንደኛውና ሦስተኛው በቤተ ክርስቲያን ይገኛሉ፣ በተለያዩ የሕይወት ገጽታዎቿ፣ ሁለተኛው መልስ የሚሆነው ለእሷ ታላቅ ባላንጣና ጠላት ነው (ስዌቲ)’” (ገጽ 449)።

**19፡8 “የቅዱሳን ጽድቅ *ሥራ*”** “ጽድቅ *ሥራ*” የሚለው ቃል (*dikaiōma*) በአኪ በርካታ አጠቃቀሞች አሉት።

1. እሱ የሚጠቅሰው የእግዚአብሔርን የፍትሕ ድርጊቶች ነው (ዝኪ. 15፡4)
2. እሱ የሚጠቅሰው የኢየሱስን ድርጊት ነው፣ በሰው ልጅ ምትክ መሞቱን (ሮሜ. 5፡16፣18)
3. እሱ የሚያመለክተው የአማኞችን ተገቢ ኑሮ ነው (ዝኪ. 19፡8)
4. እሱ የሚያመለክተው አዋጅ፣ ሕግ፣ ወይም ደንብ ነው፣ ዘወትር የሙሴ ሕግ (ሉቃስ 1፡6፤ ሮሜ. 1፡32፤ 2፡26፤ 8፡4፤ ዕብ. 9፡1፣10)።

ከእነዚህ የግሪክ ቃላት ቤተሰብ ጋር የተዛመደው ዋናው የሥነ-መለኮት ጉዳይ (*dikaioÔ*፣ *dikaiÔsis*፣ *dikaios*፣ *dikaiosune*)፣ የወደቀው የሰው ልጅ እንዴት ትክክል፣ ጻድቅ፣ ልክ፣ የጸደቀ እንደሆነ ሊገልጽ እንደሚችል ነው። በአጽንዖት መቀመጥ የሚኖርበት ይህ መንፈሳዊ ሁኔታ በሰዎች ጥረት ለመቀዳጀት አለመቻሉ ነው (ሮሜ. 3፡21-30፤ ኤፌ. 2፡8-9)፣ ግን በመለኮት ምርጫ (አብ)፣ በመለኮት ድርጊት በኩል (ወልድ)፣ እና በመለኮት መሳብ፣ በመንፈስ ቅዱስ (ዮሐንስ 6፡44፣65)። የሰው ልጅ የተጠናቀቀውን ውጤት ብቻ ነው ሊቀበል የሚችለው (ሮሜ. 5፤ II ቆሮ. 5፡21)።

የትክክለኛ አቋም ግብ ትክክለኛ ኑሮ ነው፣ ክርስቶስን የመሰለ ሕይወት (ሮሜ. 9፡29፤ ገላ 4፡19፤ ኤፌ. 1፡4፤ 2፡10)። የጽድቅ ኑሮ ከእግዚአብሔር ጋር ላለ ሕይወት ማስረጃ ነው (ዝኪ. 14፡13)፣ የእዛ ግንኙነት መሠረት ሳይሆን (ገላ. 3፡1-3)! ልዩ ርዕስ 19፡11 ተመልከት።

***ራዕይ፡ 19፡9-10***

[9]**እርሱም፡- ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ አለኝ። ደግሞም፡- ይህ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ነው አለኝ። [10]ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ። እርሱም፡- እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ።**

**19፡9 “ብፁአን ናቸው”** ይህ ለተዋጁት ከሰባቱ በረከቶች አራተኛው ነው፣ በራዕይ ላይ (ዝኪ. 1፡3፤ 14፡13፤ 16፡15፤ 19፡9፤ 20፡6፤ 22፡7፣ 14)።

▣ **“የተጠሩ”** ይህ የተጠናቀቀ ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ነው፣ እሱም ለእግዚአብሔርን የደኅንነት ጥሪ አጽንዖት ይሰጣል (ዝኪ. 17፡14፤ ዮሐንስ 6፡44፣65)።

▣ **"ይህ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ነው"** ይህ ሐረግ ለመልአኩ መልእክት ታማኝነት አጽንዖት ይሰጣል (ዝከ. 21:5፤ 22:6)።

**19፡10 "ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ"** በርካታ ውይይቶች ተደርገዋል፣ ዮሐንስ ለመልአኩ ለመስገድ በመሞከሩ (ዝከ. 22፡8)። ዮሐንስ ሆን ብሎ ያካተተው ሊሆን ይችላል፣ የመላእክት አምልኮቶት እንደሚቃወም ቃል (ዝከ. 22:9፤ ቆላ. 2:18)። ዮሐንስ በዚህ ብርቱ መልአካዊ አካል ተደናግጧል፣ እና ምናልባት መለኮታዊ አካል መስሎት ሊሆን ይችላል (ዘፍ. 16:7-13፤ 22:11-15፤ 31:11፣13፤ 48:15-16፤ ዘጸ. 32፣4፤ 13:21፤ 14:19፤ መሳ. 2:1፤ 6:22-23፤ 13:3-22፤ ዘካ. 3:1-2፤ ሉቃስ 24:5) ወይም የመንፈስ አካላዊ መገለጥ (ዝከ. 22፡8-9)።

▣ **"ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ"** ዮሐንስ በዚህ ተመሳሳይ ቃል ራሱን ጠርቷል፣ 1፡1 ላይ። መልአኩ ራሱን ያስተዋወቀው እንደ እግዚአብሔር ባሪያ ብቻ አይደለም (ዘዳ. 33:2፤ መዝ. 103:21፤ ዳን. 17:10)፣ ግን ደግሞ ለሚዋጁ የሰው ልጆች ነው (ዕብ. 1፡14)። ይህ መልአክ ደግሞም ራሱን ያስተዋውቃል፣ ከኢየሱስ ምስክር ጋር፣ ይህ በመሠረቱ የተባለው ለቅዱሳን ነው፣ ከመልአክ ይልቅ (ዝከ. 12፡17)።

▣ **"የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ።"** ይህ እጅግ ያልተለመደ ሐረግ ነው፣ እናም በስፋት ተተርጉሟል። እሱም ሊያመለክት የሚችለው አንድም

1. ኢየሱስ እንደ ትንቢት ተተኳሪ
2. ትንቢት እንደ ምልክት የመቀየሩ ሐቅ፣ ያም ኢየሱስ በአዲሱ የመንፈስ ዘመን ያመጣው (ዝከ. 1:2፤ 6:9፤ 12:17 እና 14:12 ለዚህ ሐረግ ተመሳሳይ ጠቀሜታ)
3. ኢየሱስ ዋናው የትንቢት ትንፋሽ ነው ("ከአምላክ ትንፋሽ" ጋር ተመሳሳይ 2 ጢሞ. 3፡16)

ዐውደ-ጽሑፉ የሚያሳየው፣ በክርስቶስ የሚያምኑ በመንፈስ ይመራሉ። ማንም ወደ ክርስቶስ ሊመጣ አይችልም

1. መንፈስ ካልሳበው በቀር (ዮሐንስ 6፡44፣65)
2. የወንጌልን መልእክት እንዲገነዘብ ካልረዳው
3. በክርስቶስ እንዲያምን ካላበረታታው
4. በክርስቶስ ካላጠመቀው
5. ክርስቶስን በውስጡ ካልሳለ (ዮሐንስ 16፡8-11)

የመንፈስ አገልግሎት ክርስቶስን መግለጥ ነው!

> *ራዕይ፡ 19፡11-16*
>
> **[11]ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፥ እነሆም አምባላይ ፈረስ፥ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፥ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም። [12]ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፥ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ፥ ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው፤ [13]በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል፥ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል። [14]በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር። [15]አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፤ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል። [16]በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት። የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው።**

**19፡11 "ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፥"** ይህ የተጠናቀቀ ተገብሮ ግሥ መልክ ሲሆን የሚዘመደውም ከሕዝ. 1፡1 ጋር ነው። በራዕይ በርካታ ጊዜ ሰማይ ተከፍቷል (በከፊል መንገዶች) ለዮሐንስ እውነትን ለመግለጽ፣ እያደጉ በሚሄዱ ደረጃዎች (ዝከ. 4:1;11:19; 15:5)። ልዩ ርዕስ 3፡7 ላይ ተመልከት።

▣ **"ነጭ ፈረስ"** ሙሽራው ባለፈው አንቀጽ የተገለጠው ሁሉንም ድል እንደሚያደርግ ተዋጊ ነው። ይህ የሚገልጸው የኢየሱስ ምጽአት አይሁድ ተስፋ እንደሚያደርጉት ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ብርቱ የጦር መሪ ነው። ይህም በመጠኑ ከጳውሎስ የዳግም ምጽአት ገለጻ ይለያል (ዳግም ምጽአት)፣ ይኸውም 1 ተሰ. 4:13-18 ላይ ይገኛል። በመሳደድ ላይ ላሉ ክርስቲያኖች ይህ እጅግ የሚያበረታታ ዘይቤ ነው። ተርጓሚዎች ማስታወስ የሚኖርባቸው

1. ይህ የተሟላና የተጠናቀቀ የዳግም ምጽአቱ ማብራሪያ አለመሆኑን
2. ተምሳሌታዊ፣ አፖካሊፕቲካዊ ቋንቋ መልበሱን
3. እሱ እውነት ነው፤ አምላካችን፣ በክርስቶስ የገዛ ራሱን ለመቀበል ዳግም እንደሚመጣ (ዮሐንስ 14፡2-3) እና በሰው ልጆች ሁሉ ላይ እንደየሥራቸው እንደሚፈርድ (ገላ. 6፡7)

▣ **"በእሱ ላይ የተቀመጠ"** ምንም እንኳ 6፡2 ላይ ነጭ ፈረስ ቢኖርም፣ ይህ የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው።

▣ **"የታመነና እውነተኛ ይባላል፥"** "የታመነና እውነተኛ" የሚሉት ቃላት በዕብራይስጥ ታማኝነትን ያስተላልፋሉ (ራዕ. 3:14 እንዲሁም 1:5; 3:7)።

## ልዩ ርዕስ፡ “እውነታ” (ጽንሰ-ሐሳብ) በዮሐንስ ጽሑፎች

ዮሐንስ የዕብራይስጥ ዳራን እና የግሪክ ዳራን ደባልቋል *alētheia* “እውነት” *logos* ላይ እንዳደረገው (ዝከ. 1:1-14)። በዕብራይስጥ *emeth* (BDB 53) የሚገልጸው የትኛው እውነት፣ ወይም የታመነ መሆኑን ነው (እሱም ዘወትር በሴፕቱዋጂንት *hpisteuÔ* ጋር ይያያዛል)። በግሪክ እሱ የሚያያዘው ከፐላቶ እውነታ በተቃርኖ እውነታ ያልሆነ፣ ከሰማያዊ በተቃርኖ ምድራዊ ጋር ነው። ይህ ከዮሐንስ ምንታዌነት ጋር ይሰማማል። እግዚአብሔር በግልጽ ይፋ አድርጓል (*palētheia* ሥርወ ቃል፣ መግለጥ፣ ማሳየት፣ በግልጽ ይፋ ማድረግ ነው) ራሱን በልጁ በኩል። ይህም በበርካታ መንገዶች ተገልጿል።

1. ስም፣ *alētheia*፣ እውነት
   - ሀ. ኢየሱስ ሙሉ ጸጋና እውነት ነው (ዝከ. 1፡14፣17 — የብኪ የኪዳን ቃላት)
   - ለ. ኢየሱስ የዮሐንስ መጥምቁ ምስክርነት ተተኳሪ ነው (ዝከ. 1:32-34; 18:37 – የመጨረሻው የብኪ ነቢይ)
   - ሐ. ኢየሱስ እውነትን ይናገራል (ዝከ. 8:4,44,45,46 – ራዕይ አረጋጋጭ እና ግላዊ ነው)
   - መ. ኢየሱስ መንገድ፣ እውነት፣ እና ሕይወት ነው (ዝከ. 14፡6)
   - ሠ. ኢየሱስ በእውነት ይቀድሳቸዋል
   - ረ. ኢየሱስ (ሎጎስ፣ 1:1-3) እውነት ነው (ዝከ. 17፡17)
2. ቅጽል፣ *alēthēs*, እውነት የታመነ
   - ሀ. የኢየሱስ ምስክርነት (ዝከ. 5:31-32; 7:18; 8:13-14)
   - ለ. የኢየሱስ ፍርድ (ዝከ. 8፡16)
3. ቅጽል፣ *alēthinus* ርግጥ
   - ሀ. ኢየሱስ እውነተኛ ብርሃን ነው (ዝከ. 1፡9)
   - ለ. ኢየሱስ እውነተኛ እንጀራ ነው (ዝከ. 6፡32)
   - ሐ. ኢየሱስ እውነተኛ ወይን ነው (ዝከ. 15፡1)
   - መ. ኢየሱስ እውነተኛ ምስክር ነው (ዝከ. 19፡35)
4. ተውሳከ ግስ፣ *alēthÔs*፣ በርግጥ
   - ሀ. ሳምራዊ ምስክር ለኢየሱስ፣ እንደ ዓለም አዳኝ (ዝከ. 4፡42)
   - ለ. ኢየሱስ እውነተኛ ምግብና መጠጥ ነው፣ በሙሴ ጊዜ የነበረውን መና በተቃርሞ (ዝከ. 6፡55)

እውነት የሚለው ቃልና የእሱ ርቢዎች ደግሞ የሌሎችን ምስክርነት ይገልጻሉ፣ ለኢየሱስ፣ *alēthēs,*

- ሀ. የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክር እውነት ነበር (ዝከ. 10፡41)
- ለ. የዮሐንስ (የወንጌሉ ደራሲ) ምስክርነት እውነት ነው (ዝከ. 19:35; 21:24)
- ሐ. ኢየሱስ እንደ እውነተኛ ነቢይ ታይቷል (ዝከ. 6:14; 7:40)

ለአኪና ብኪ እውነት መልካም ማብራሪያ የጆርጅ ኢ. ላድን የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት፣ ገጽ 263-269 ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ “እውነት” (ቃሉ) በዮሐንስ ጽሑፎች

1. እግዚአብሔር አብ
   - ሀ. እግዚአብሔር እውነት/የታመነ ነው (ዮሐንስ 3:33; 7:18,28; 8:26; 17:3; ሮሜ. 3:4; 1 ተሰ. 1:9; 1 ዮሐንስ 5:20; ራዕ. 6:10)
   - ለ. የእግዚአብሔር መንገድ እውነት ነው (ራዕ. 15:3)
   - ሐ. የእግዚአብሔር ፍርድ እውነት ነው (ራዕ. 16:7; 19:2)
   - መ. የእግዚአብሔር ንግግር እውነት ነው (ራዕ. 19:11)
2. እግዚአብሔር ወልድ
   - ሀ. ወልድ እውነት/እውነታ ነው
     1) እውነተኛ ብርሃን (ዮሐንስ 1:9; 1 ዮሐንስ 2:8)
     2) እውነተኛ ወይን (ዮሐንስ 15:1)
     3) ጸጋና እውነት የተሞላ (ዮሐንስ 1:14,17)
     4) እሱ እውነታ ነው (ዮሐንስ 14:6; 8:32)
     5) እሱ እውነት ነው (ራዕ. 3:7,14; 19:11)
   - ለ. የወልድ ምስክርነት/እማኝነት እውነት ነው (ዮሐንስ 18፡37)
3. ተነጻጻሪ መልክ ሊኖረው ይችላል
   - ሀ. የሙሴ ሕግ አልያም የኢየሱስ ጸጋና እውነት (ዮሐንስ 1፡17)
   - ለ. በበረሀ የነበረው የማደሪያ ድንኳን አልያም ሰማያዊ ቤተ መቅደስ (ዕብ. 8፡2፤ 9፡1)
4. በዮሐንስ እንደሆነ ሁሉ ይህ ቃል በርካታ ፍችዎች አሉት (ዕብራይስጥ እና ግሪክ)። ዮሐንስ የተጠቀመባቸው አብና ወልድን ለመግለጽ ነው፣ እንደ አካላት፣ እንደ ተናጋሪዎች፣ እንደ እነርሱ መልእክት፣ ይኸውም ወደ ተከታዮቻቸው እንደሚያልፍ (ዮሐንስ 4:13; 19:35; ዕብ. 10:22; ራዕ. 22:6)።

5. ለዮሐንስ እነዚህ ቅጽሎች የሚገልጹት አብን ነው፣ እንደ አንድና ብቸኛ የታመነ መለኮት (ዝኪ. 5፡44፤ 1 ዮሐንስ 5፡20) እና ኢየሱስ እንደ የእሱ እውነት እና ፍጹም መገለጥ፣ ለመዋጀት ዓላማ፣ የሚዛመድ ሳይሆን፣ ሐቅ!

▣ ***"በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም"*** ይህ የኢሳ. 11:3-5 (ኢሳ. 9:7; 16:5; 32:1; መዝ. 96:13) ጠቃሽ ነው፣ ይኸውም አዲሱን የጽድቅ ዘመን የሚገልጽ፣ አዲሱን የመንፈስ ዘመን። ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ

"ጽድቅ" የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የግድ ተከታታይ የሆነ የግል ጥናት በጽንሰ ሐሳቡ ላይ ማድረግ ያለበት ወሳኝ ርዕስ ነው።

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚገለጸው "ትክክለኛ" ወይም "ጻድቅ" በሚል ነው። ሜሶፖታሚያዊው ቃል ራሱ የመጣው ከወንዝ ዳር ሸንበቆ ሲሆን፣ የግድግዳና የአጥርን አግድሞሽ ቀጥተኛነት መለኪያ የሚሆን የግንባታ መሣርያ ነው። እግዚአብሔር ቃሉን በዘይቤነት ለራሱ ባሕርይ መጠሪያ እንዲሆን መርጦታል። እሱ ቀጥተኛ የሆነ (የማስመሪያ) ጫፍ ነው፣ በእሱም ሁሉም ነገር የሚመዘንበት። ይህ ጽንሰ ሐሳብ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ይገልጻል፣ እንዲሁም ለመፍረድም ሥልጣን እንዳለው።

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው (ዘፍ. 1፡26-27፤ 5፡1፣3፤ 9፡6)። የሰው ልጅ የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረው ነው። ሁሉም ፍጥረታት የተዘጋጀውና ያለው ለእግዚአብሔር እና ለሰው ልጆች መስተጋብር ተብሎ ነው። እግዚአብሔር ልዕለ ፍጡሩን ይፈልገዋል፣ የሰው ልጅ፣ እንዲያውቀው፣ እንዲወደው፣ እንዲያገለግለው፣ እንዲሁም እሱን እንዲመስል! የሰው ልጅ ታማኝነት ተፈትኗል (ዘፍ. 3)፣ እናም ሁለቱ ዋነኛ ጥንዶች ፈተናውን ወድቀዋል። ይህም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት አበላሽቶታል (ዘፍ. 3፤ ሮሜ 5፡12-21)።

እግዚአብሔር ኅብረቱን ለማደስና ለመመለስ ቃል ገብቷል (ዘፍ. 3፡15)። ይህንንም ያደረገው በራሱ ፍቃድና በራሱ ልጅ ነው። ሰዎች የተጣሰውን ሊመልሱት አልቻሉም (ሮሜ 1፡18-3፡20)።

ከውድቀት በኋላ፣ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ርምጃ፣ ለተሐድሶው የኪዳናዊ ጽንሰ-ሐሳብ የተመሠረተው በእሱ ግብዣና በሰው ልጅ የንስሐ፣ የእምነት፣ የመታዘዝ ምላሽ ነው። በውድቀት ምክንያት፣ ሰዎች ተገቢ ድርጊት ለመፈጸም አልቻሉም (ሮሜ 3፡21-31፤ ገላትያ 3)። እግዚአብሔር ራሱ መነሻውን ወስዷል፣ ኪዳን አፍራሽ የሆኑትን የሰው ልጆች ለመመለስ። ይሄንንም ያደረገው

1. ኃጢአተኛውን ሰው በክርስቶስ ሥራ በኩል ጻድቅ አድርጎ <u>ማወጅ</u> (የፍርድ ጽድቅና)
2. <u>በነጻ የተሰጠ</u> የሰው ልጅ ጽድቅ በክርስቶስ ሥራ በኩል (የተሰጠ ጽድቅ)
3. <u>የተሰጠ</u> የሚያድረው መንፈስ ጽድቅን ይፈጥራል (ሥነ ምግባራዊ ጽድቅ) በሰው ልጆች።
4. <u>መመለስ</u> የኤደን ገነት ኅብረት በክርስቶስ የእግዚአብሔርን አምሳል መለሰ (ዘፍ. 1፡26-27) በአማኞች (ግንኙነታዊ ጽድቅ)።

ሆኖም፣ እግዚአብሔር ኪዳናዊ ምላሽ ይፈልጋል። እግዚአብሔር አውጇል (በነጻ ሰጥቷል) እናም ይሰጣል፣ የሰው ልጆች ግን <u>የግድ</u> ምላሽ መስጠት አለባቸው እንዲሁም በምላሻቸው መቀጠል

1. ንስሐ
2. እምነት
3. በሕይወት ኑሮ መታዘዝ
4. መጽናት

ጽድቅ፣ ስለዚህ ኪዳናዊ ነው፣ በእግዚአብሔርና በልዕለ ፍጡሩ መካከል ያለ ሁለትዮሽ ድርጊት። እሱም የተመሠረተው በእግዚአብሔር ባሕርይ፣ በክርስቶስ ሥራ፣ በመንፈስ አስቻይነት፣ ይህም እያንዳንዱ ሰው በግሉ እና በቀጣይነት በተገቢው ምላሽ መስጠት ያለበት ነው። ጽንሰ ሐሳቡም "በእምነት መጽደቅ" ይባላል። ጽንሰ ሐሳቡ በወንጌላት ተገልጿል፣ ነገር ግን በእነዚህ ቃልት አይደለም። እሱም በመጀመሪያ የተገለጠው በጳውሎስ ሲሆን እሱም የግሪኩን ቃል "ጽድቅ" ን በተለያየ መልኩ ከ100 ጊዜ በላይ ተጠቅሟል።

ጳውሎስ የሠለጠነ ራቢ እንደ መሆኑ መጠን፣ ዲካዮሱኔ (dikaiosunē) የሚለውን ቃል በዕብራይስጥ አገባቡ SDQ በሴፕቱዋጂንት ጥቅም ላይ የዋለውን፣ ከግሪክ ሥነ ጽሑፍ ሳይሆን። በግሪክ ጽሑፎች ቃሉ የሚያያዘው፣ ለአንዱ የመለኮት ተስፋ በኅብረተሰቡ ዘንድ ለማረጋገጥ ነው። በዕብራይስጥ አግባቡ ዘወትር የሚያያዘው ከኪዳናዊ ቃላት ጋር ነው። ያህዌ ፍትሐዊ፣ ሥነምግባራዊ፣ ግብረገባዊ አምላክ ነው። እሱም ሕዝቦቹ የሱን ባሕርይ እንዲያንጸባርቁ ይሻል። የተቤዠ የሰው ልጅ አዲስ ፍጥረት ሆኗል። ይህ አዲስነት ውጤቱ አዲስ የመልካምነት የሕይወት ስልት ያሳያል (የሮማን ካቶሊክ የጽድቅ ትኩረት)። እስራኤል ቲዎክራሲያዊ (የአምላክ መንግሥት) እንደመሆኑ መጠን በሥጋዊ (የኅብረተሰቡ ደንቦች) እና በተቀደሰው (የእግዚአብሔር ፍቃድ) መካከል እንዲሁም "በጽድቅ" (ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ) ግልጽ የሆነ መለያ የለውም። ይህ ልዩነት የሚገለጠው በዕብራይስጥና በግሪክ ቃላት ነው፣ እነርሱም ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎሙ "ፍትሕ" (ከኅብረተሰቡ ጋር በተያያዘ) እንዲሁም "ጽድቅ" (ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ)።

ወንጌል (መልካም የምስራች) የኢየሱስ፣ የወደቀው የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ኅብረት መመለሱን ነው። የጳውሎስ አያዎ (ፓራዶክስ) የሚሆነው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በደልን ማስወገዱ ነው። ይህም ሊገኝ የሚችለው በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ምሕረት፣ እና ጸጋ ሲሆን፣ የልጁ ሕይወት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ፤ እንዲሁም የመንፈስ መቃትትና ወደ ወንጌል መሳብ ነው። ጽድቅ የእግዚአብሔር ነጻ ድርጊት ነው፣ ነገር ግን መልካምነትን ሊያመነጭ ይገባል (የአውግስጢኖስ አቋም፣ እሱም የሚያሳየው ሁለቱንም፣ የተሐድሶ አጽንኦት በነጻ ወንጌል ላይ እና የሮማን ካቶሊክ አጽንኦት በተለወጠ ሕይወት በፍቅርና በታማኝነት ላይ ነው)። ለባለ ተሐድሶዎች ቃሉ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" ተጨባጭ ባለ መብትነትን ሲያሳይ (ማለትም፣ ኃጢአተኛውን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር

ተቀባይነት እንዲያገኝ የማድረግ *ሥራ* [አቋማዊ ቅድስና])፣ ለካቶሊክ ደግሞ የተሳቢ ባለሙብትነት ነው፣ ይህም እግዚአብሔርን የመምሰል ሂደት ነው፣ (ተሞክሯዊ ተራማጅ ቅድስና ነው)። በተጨባጭ ግን ሁለቱም ነው!!

በእኔ አስተያየት መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ከዘፍ. 4-ራዕይ 20 የተመዘገበው እግዚአብሔር የኤደንን ኅብረት እንደሚመልስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ ኅብረት በምድራዊ መቼት ይጀምራል፣ (ዘፍ. 1-2) እናም መጽሐፍ ቅዱስ በተመሳሳይ መቼት ነው የሚያበቃው (ራዕ. 21-22)። የእግዚአብሔር አምሳልና ዓላማ ይመለሳል!

የላይኛውን ማብራሪያ ለማጠቃለል የሚከተሉትን የተመረጡ የአዲስ ኪዳን ምንባቦችን የግሪኩ ቃለት ምድብ የሚያመላክቱትን እይ።

1. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው (ዘወትር የሚያያዘው እግዚአብሔር እንደ ፈራጅ ነው)
   ሀ. ሮሜ 3፡26
   ለ. 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡5-6
   ሐ. 2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡8
   መ. ራዕይ 16፡5
2. ኢየሱስ ጻድቅ ነው
   ሀ. ሐዋርያት *ሥራ* 3፡14፤ 7፡52፤ 22፡14 (የመሲሕ ማዕርግ)
   ለ. ማቲዎስ 27፡19
   ሐ. 1ኛ ዮሐንስ 2፡1፣29፤ 3፡7
3. የእግዚአብሔር ሐሳብ ለፍጥረቱ ጽድቅ ነው
   ሀ. ሌዋውያን 19፡2
   ለ. ማቲዎስ 5፡48 (ዝከ 5፡17-20)
4. የእግዚአብሔር ጽድቅን የመስጠትና የመፍጠር አግባብ
   ሀ. ሮሜ 3፡21-31
   ለ. ሮሜ 4
   ሐ. ሮሜ 5፡6-11
   መ. ገላትያ 3፡6-14
   ሠ. በእግዚአብሔር የተሰጠ
      1. ሮሜ 3፡24፤6፡23
      2. 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30
      3. ኤፌሶን 2፡8-9
   ረ. በእምነት የሚቀበሉት
      1) ሮሜ 1፡17፤3፡22፣26፤ 4፡3፣5፣13፤ 9፡30፤ 10፡4፣6፣10
      2) 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡21
   ሰ. በልጁ *ሥራ* በኩል
      1. ሮሜ 5፡21-31
      2. 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14
      3. ፊሊፕስዩስ 2፡6-11
5. የእግዚአብሔር ፍቃድ ተከታዮቹ ጻድቅ እንዲሆኑ ነው
   ሀ. ማቴዎስ 5፡3-48፤ 7፡24-27
   ለ. ሮሜ 2፡13፤ 5፡1-5፤ 6፡1-23
   ሐ. 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14
   መ. 1ኛ ጢሞቲዎስ 6፡11
   ሠ. 2ኛ ጢሞቲዎስ 2፡22፤ 3፡16
   ረ. 1ኛ ዮሐንስ 3፡7
   ሰ. 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24
6. እግዚአብሔር ዓለምን በጽድቅ ይፈርዳል
   1. ሐዋ. 17፡31
   2. 2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡8

ጽድቅ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፣ በክርስቶስ በኩል ለኃጢአተኛው የሰው ልጅ በነጻ የተሰጠ። እሱም

ሀ. የእግዚአብሔር ደንብ

ለ. የእግዚአብሔር ስጦታ

ሐ. የክርስቶስ ድርጊት ነው።

ነገር ግን እሱ ደግሞ ጻድቅ የመሆን ሂደት፣ ያም በጽናት እና በብርታት መያዝ ያለበት ነው፤ አንድ ቀን በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የምንቀዳጀው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት በደኅንነት ይመለሳል፣ ነገር ግን ሂደቱ በሕይወት ዘመን ሁሉ ፊት ለፊት ይገኛል በሞት ወይም በፓሮሲያ!

እዚህ መልካም ጥቅስ አለ፣ *ከጳውሎስና ጽሑፎቹ መዝገበ ቃላት* የተጠቀሰ አይ ቪ ፒ

“ካልቪን፣ ከሉተር ከፍ ባለ መልኩ አጽንዖት የሚሰጠው ግንኙነታዊ በሆነው የእግዚአብሔር ጽድቅ ገጽታ ላይ ነው። የሉተር አተያይ በእግዚአብሔር ጽድቅ ላይ፣ ከጥፋተኝነት ነጻ መሆንን ገጽታ የያዘ ይመስላል። ካልቪን አጽንዖት የሚሰጠው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለእኛ ያለውን አስደናቂ አፈጣጠር ከግንኙነት ወይም ከተካፋይነት አኳያ ነው” (ገጽ 834)።
እንደ እኔ የአማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ሦስት ገጽታዎች አሉት።
1. ወንጌል አካል ነው (የምስራቅ ቤተ ክርስቲያንና የካልቪን አጽንዖት)
2. ወንጌል እውነት ነው (የአውግስጢኖስና የሉተር አጽንዖት)
3. ወንጌል የተለወጠ ሕይወት ነው (የካቶሊክ አጽንዖት)

ሁሉም እውነት ናቸው እናም አንድ ላይ መያዝ ይኖርባቸዋል፣ ለጤናማ፣ ትርጉም ላለው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና። ማንም በጣም አጽንዖት ከሰጠ ወይም ካንኳሰሰ ችግሮች ይፈጠራሉ።

ኢየሱስን መቀበል ይኖርብናል!
ወንጌልን ማመን ይኖርብናል!
ኢየሱስን መምሰል ይኖርብናል!

**19:12 “ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፥”** ይህ የኢየሱስ ገለጻ ነው፣ ከ1:14 እና 2:18። እሱም የብኪ መልአካዊ ዳራ አለው፣ ዳን. 10:6።

▣ **“በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ፥”** ይህ የሚያመለክተው የንጉሥ አክሊሎችን ነው። ኢየሱስ በርካታ አክሊሎች አሉት፣ ከሌሎቹ ይልቅ

1. በነጭ ፈረስ ላይ ከተቀመጠው፣ 6:2 ላይ (እሱም ስኬታማ የሆነ ጦርነት ተምሳሌት)
2. ሰይጣን (ቀይ ዘንዶ፣ 12:3 ላይ ያለው)
3. አውሬው 13:1

▣ **“ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው፤”** ይህ የራዕ. 2:17 ጠቃሽ ይሆናል፣ ነገር ግን ግን ቢሆን እንኳ ፍችው አሁንም ርግጠኛ አይደለም። አንዳንዶች የሚመለከቱት እንደ ጥንታዊ እምነት ጠቃሽ ነው፣ ይኸውም የአማልክትን ስም ማወቅ በእነርሱ ላይ ሥልጣን እንዳለው ነው። ሌሎች የሚያምኑት፣ እሱ የሚወክለው ሐቅ ማንም ቢሆን የክርስቶስን ባሕርይ ሙሉ ለሙሉ እንደማያውቅ ነው። መጠሪያው ባለመታወቁ፣ በማንኛውም የኢየሱስ መጠሪያ አይጠቀስም (“የታመነና እውነተኛ” ቁ. 11፣ እና “የእግዚአብሔር ቃል” ቁ. 13) በምንባቡ ላይ ይገኛል (ወይም በመጽሐፉ) “የነገሥታት ንጉሥንና የጌቶችን ጌታ” ጨምሮ፣ ቁ. 16።

**19:13 “በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል”** ለያህዌ ፍርድ የሚሆን ግጥም ጠቃሽ ነው፣ ከኢሳ. 63:3፣ ይኸውም ደግሞ ቁ. 15 ላይ የተጠቀሰ። “የተነከረ” የሚለው ቃል (MS A, ዩቢኤስ[4] ለ ደረጃ ይሰጠዋል) ወይም “የተረጨ” (MSS ℵ*, P ከኢሳ. 63:3) በተጠናቀቀ ግሥ ነው፣ ተንታኞች ምንን እንደሚያመለክት አልተግባቡም

1. የጠላቶቹ ደም፣ ይኸውም የአንቀጹ ተተኳሪ ይመስላል፣ እናም ታርጉም (Targum) ላይ ተንጸባርቋል፣ ዘፍ. 49:10-11 (ሆኖም፣ በዐውደ-ጽሑፍ፣ ውጊያው አልተከሰተም)
2. የገዛ ራሱ የሚዋጅ፣ መሥዋዕታዊ ደም በእርሱም ቅዱሳን የራሳቸውን ልብስ አንጥነው ያጠቡበት (ዝከ. 7:14)
3. እንዲሁም ሊሆን የሚችለው የምስክሮቹ ደም ነው፣ ለእርሱ ውድ የሆኑት

ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ አማራጭ ቁ. 1 እጅግ የተሻለ ይመስላል።

▣ **“የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።”** ይህ *ሎጎስ* የሚለው ቃል ነው፣ ይኸውም የራዕይን መጽሐፍ ከሐዋርያው ዮሐንስ ጋር የሚያያይዝ፣ እሱም ብቸኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ ነው፣ ይህንን መጠሪያ ለኢየሱስ መጠሪያ የተጠቀመበት (ዮሐንስ 1:1,14; 1 ዮሐንስ 1:1)።

ወንጌል ሁለቱንም ነው፣ አካል (የአምላክ ሕያው ቃል፣ ኢየሱስ) እና መልእክት (የተጻፈ የአምላክ ቃል፣ መጽሐፍ ቅዱስ)። ይኸው ተመሳሳይ መንታ ገጽታ “እምነት” በሚለው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃቀም ይንጸባረቃል፣ ይኸውም ሁለቱም በግለሰባዊ ድርጊት ኢየሱስን መቀበል እና ተያያዥ በሆነ ድርጊት ዶክትሪናዊ እውነታዎችን መቀበል (“እምነት፣” ይሁዳ ቁ. 3፤20)።

## ልዩ ርዕስ፡ የዕብራይስጥ እና ግሪክ የሎጎስ ዳራ

ሎጎስ የሚለው ቃል ዳራ

1. የዕብራይስጥ ዳራ
   ሀ. የንግግር ቃል ኃይል (ኢሳ. 55:11; መዝ. 33:6; 107:20; 147:15,18), እንደ ፍጥረት (ዘፍ. 1:3,6,9,11,14,20,24, 26,29) እና የአባቶች ባርኮት (ዘፍ. 27:1; 49:1)
   ለ. ምሳሌዎች 8:12-23 “ጥበብን” እንደ እግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያና የሁሉም ፍጥረታት ወኪል ሰውኛ ያደርገዋል (መዝ. 33:6 እና ካኖናዊ ያልሆነው ጥበበ ሰሎሞን፣ 9:9)
   ሐ. ታርጉም (አራማዊ ትርጉሞች እና ሐተታዎች) “የእግዚአብሔር ቃል” የሚለውን ሐረግ ወደ ሎጎስ ይቀይሩታል፣ አንትሮፖሞርፊማዊ ቃላት ስለማይመቻቸው
2. የግሪክ ዳራ
   ሀ. ሔራክሊተስ — ምድር በለውጥ ላይ ነች፤ ሰው ያልሆነው መለኮትና የማይለወጠው ሎጎስ አንድ ላይ ይዘዋታል፣

ብሎም የለውጡን ሂደት ይመራሉ
ለ. ፕላቶ — ሰው ያልሆነውና የማይለወጠው ሎጎስ የፕላኔቶችን ሂደት ይመራሉ፣ ወቅቶችንም ይወስናሉ
ሐ. ስቶይክስ — ሎጎስ "ዓለም ምክንያት" ነበር ወይም አመራር፣ ግን ከፊል ሰዋዊ
መ. ፊሎ — እሱ የሎጎስን ጽንሰ-ሐሳብ ሰዋዊ አድርጎታል እንደ "ሊቀ ካህን እሱም የሰውን ነፍስ በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርብ፣" ወይም "በእግዚአብሔርና በሰው መሐል ያለ ድልድይ፣" ወይም "መዘውር ነው፣ ይኸውም የዩኒቨርሱ ፓይለት ሁለን ነገር የሚመራበት" (*kosmocrater*)

**19:14 "በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች"** ይህ በሁለት መንገድ ተተርጉሟል።

1. በ17:14 እና በዚሁ የወዲያው ዐውደ-ጽሑፍ ባለው በቁ. 8 የቅዱሳን ገለጻ ምክንያት፣ ብዙዎች የሚገምቱት ይህ ቅዱሳንን የሚጠቅስ ነው።
2. በብሉ ዳራ ዘዳ. 33:2; መዝ. 68:17; እና ዘካ. 14:5 እንዲሁም በአኪ ምንባቦች ማቴ. 13:41; 16:27; ማርቆስ 8:38; 13:27; ሉቃስ 9:26; I ተሰ. 3:13; II ተሰ. 1:7 ምክንያት፣ ብዙዎች የሚያምኑት እሱ የሚያመለክተው መላእክትን ነው።

ይኸው ተመሳሳይ አሻሚነት በብዙ ምንባቦች ላይ ይገኛል።

**19:15 "ከአፉም"** ይህ የኢሳ. 11:4 እና ራዕ. 1:16 እና 2:16 ጠቃሽ ነው። ይኸው ተመሳሳይ የፍርድ ዘይቤ በአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ይገኛል (ኢስድራስ 12:6፤ የሰሎሞን መዝሙራት 17:10፣45፣49፤ እና መጽሐፈ-ሔኖክ I 62:6)።

▣ **"ስለታም ሰይፍ"** ይህ የወንጌል ወይም እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ኃይል ዘይቤ ነው (ዘፍ. 1; ኢሳ. 55:11; ዮሐንስ 1:1; II ተሰ. 7:8)፣ ጥሬያዊ ትርጉም ሳይሆን።

የፍጻሜው ዘመን የዐመጸኞቹ የሰው ልጆች ሠራዊት ውድመት ሕዝ. 38-39 ላይ ተገልጿል። ይኸው ውድመት ተፈጽሟል በ (1) ሰይፉ (ሕዝ. 38:21 እና ራዕ. 19:15,21) ወይም (2) እሳት ከሰማይ, ሕዝ. 38:22; 39:6; እና ራዕ. 20:9። ይህ በራዕይ 19 እና 20 መካከል ያለ ትይዩነት (ማለትም፣ የአሕዛብን ሠራዊት የማጥፊያ የተለያዩ መንገዶች)፣ ሁለቱም የሚያንጸባርቁት ሕዝቅኤል 38-39 ሲሆን እንድምታውም ማጠቃለል ነው። 19 ላይ ያለው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በተለየ አገላለጽ 20:1-10 ላይ ተደግሟል። ድግግሞሹ ቀደም ሲልም በማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ መካከል ታይቷል።

▣ **"አሕዛብ"** የእነዚህ ሠራዊት የብኪ መነሻ አምላክ የሌላቸው ሕዝቦች፣ እነርሱም ሕዝቅኤል 38 ላይ የተዘረዘሩት ናቸው፣ ከጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ሁሉ (ዝከ. ቁ. 2፣5፣6፣13)። ዮሐንስ የሕዝቅኤል 38-39 (ወይም መዝሙር 2) የፍጻሜ ዘመን ጦርነት ተጠቅሟል፣ እንደ ምናቡ ምንጭነት፣ በመልካምና በክፉ መካከል ስለሚደረገው የፍጻሜ ዘመን ጦርነት! ኢየሱስ ትልቁ ሰይፍ አለው! 2:26 እና 10: 11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፤"** ይህ ከሦስቱ ገለጻዎች ሁለተኛው ነው፣ በነጭ ፈረስ ላይ ስለተቀመጠው። ይህ የፍርድ ገለጻ የመጣው ከመዝ. 2:9 እና 110:5-6 (ራዕ. 2:27; 12:5) ነው።

▣ **"እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል"** ይህ ሦስተኛው የፍርድ ገለጻ የኢሳ. 63:2-3; ኤር. 51:33; ሰቈ. 1:15; ኢዩኤል 3:13 (ራዕ. 14:19-20) ጠቃሽ ነው። የተረገጠው ወይን ቀለም የጥንታዊዎቹን ደም፣ ሞት፣ እና ውጊያ ያስታውሳል!

ለ"እግዚአብሔር ቁጣ" 7:14 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**19:16 "በጭኑም የተጻፈበት ስም"** "ጭኑም" ስለሚለው ቃል በርካታ ውይይቶች ተካሂደዋል፡

1. ይህ ሰይፍ የሚደረግበት ስፍራ በመሆኑ
2. ይህ ስፍራ፣ ልብሱ በፈረሱ ጀርባ ላይ በግልጽ የታየበት ነው
3. እሱም የአካሉ ጠንካራው ጡንቻ ነው፣ እናም የኃይሉ ተምሳሌት

▣ **"የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ"** ይህ የሚጠቅሰው አንድ ስም ነው ሁለት? ራዕይ 17:14 የሚያሳየው አንድ ስም እንደሚያመለክት ነው (1 ጢሞ. 6:15)። እሱም ሁለት ታሳቢ የብኪ ዳራዎች አሉት፡

1. የያህዌ መግለጫ (ዘዳ. 10:17 እና ሔኖክ 9:4)
2. የባቢሎናውያንና የኋለኞቹ ፋርሶች የመለኮት መጠሪያ፣ እርሱም ወደ ያህዌ የተተረጎመ (ዳን. 2:37)

አስገራሚ የሚሆነው ይህ ሐረግ በአራምኛ እስከ 777 መጨመሩ ነው፣ ለአውሬው ቁጥር 666 ተቃርኗዊ መለያ። የላቀ ፍጽምና አልያም የከፋ ፍጹም አለመሆን።

## ራዕይ፡ 19:17-18

**[17-18]አንድም መልአክ በፀሐይ ውስጥ ቆሞ አየሁ፥ በሰማይም መካከል ለሚበሩ ወፎች ሁሉ። መጥታችሁ የነገሥታትን ሥጋና የሻለቃዎችን ሥጋ የብርቱዎችንም ሥጋ የፈረሶችንም በእነርሱም የተቀመጡትን ሥጋ የጌታዎችንና የባሪያዎችንም የታናናሾችንና የታላላቆችንም ሁሉ ሥጋ እንድትበሉ ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር እራት ተከማቹ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።**

**19:17 "ለወፎች ሁሉ"** ይህ አስፈሪ አንቀጽ የሁለቱ የብኪ ምንባቦች ጠቃሽ ነው፣ ይኸውም የጦርነትን ትዕይንቶች የሚያሳዩት። ይህ ዐውደ-ጽሑፍ ተመሳሳዩ ጦርነት ነው 16:12-16 ላይ የተብራራው፣ አርማጌዶን የሚባለው። ነጣቂዎቹ ወፎች ወደ ጦርነት እንደሚሄዱ

ተገልጸዋል እንደ 1 ሳሙ. 17:46 (ማቴ. 24:28; ሉቃስ 17:37) እና ሕዝ. 39:17-20፣ እሱም የጎግ እና ማጎግ የፍጻሜ ጦርነት። ዮሐንስ ዘወትር የብኪን ምስያ በአዲስ መንገድ ይጠቀማል። ምዕራፍ 20 ላይ የጎግ እና ማጎግ ጦርነት ከሰይጣን ጋር ይያያዛል፣ ከሚሊኒየም በኋላ፣ እንዲሁም ምዕራፍ 19 ላይ ያለው ጦርነት ከሚሊኒየም በፊት የሚከሰት ነው፣ እናም ከዱር አውሬውና ከሐሰተኛው ነቢይ ጋር የሚደረግ ነው።

▣ **"ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር እራት ኑ፣ ተከማቹ"** "ኑ" የሚለው ቃል የተተረጎመው ተውሳከ *ግሥ* ነው፣ እናም ጥቅም ላይ የዋለው እንደ የድርጊት የአሁን ተተኳሪ የብዙ ቁጥር ሆኖ ነው፣ እሱም ከሁለተኛው ቃል ከ"ተከማቹ" ጋር የሚገጥም፣ ይኸውም የድርጊት ተገብሮ ተተኳሪ የብዙ የሆነ። ይህ ቁ. 7 እና 9 ላይ ለተጠቀሰው ለበጉ ራት ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው። በጉ የጠፉትን ሰዎች ይጋብዛል፣ መጥተው እንዲድኑና በሰርጉ ግብዣ ላይ እንዲገኙ። መልአኩ ግን ነጣቂ ወፎችን ይጋብዛል፣ ወደ ሙት አካላት ግብዣ (እና የሞቱ ነፍሳት) በታላቁ የፍጻሜ ጊዜ ጦርነት (ኤር. 12፡9፤ ሕዝ. 39፡17)። የእግዚአብሔር ቁጣ ርግጥ ነው፣ በግብዣ ተመስሏል፣ በጠላቶቹ *ሥጋ* ላይ (ኢሳ. 34:6; ኤር. 12:12; 46:10; ሶፎ. 1:7)።

**19፡18** ይህ ተመልሶ ወደ 6፡15 ይሄዳል፣ ይኸውም ደግሞ የፍጻሜ ዘመን መቼት፣ እነዚሁ አጠቃላይ የሰው ልጅ ምድቦች ደግሞ የተጠቀሱበት። ሳይቀበሩ የመቅረት ፍርሃት በተለይ ለጥንት የቅርብ ምስራቅ ሕዝቦች አስደንጋጭ ነበር።

የኢየሱስ በድል አድራጊነት መመለስ በእያንዳንዱ የፍርድ ዑደት ፍጻሜ ላይ ይታያል፡ ማኅተሞች፣ 6፡12-17፤ መለከቶች፣ 11፡ 15-18፤ እና ጽዋዎች፣ 19፡1-21።

*ራዕይ፡* **19፡19-21**

**[19]በፈረሱም የተቀመጠውን ጭፍራዎቹንም ይወጉ ዘንድ አውሬውና የምድር ነገሥታት ጭፍራዎቻቸውም ተከማችተው አየሁ። [20]አውሬውም ተያዘ በእርሱም ፊት ተአምራትን እያደረገ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉትን ለምስሉም የሰገዱትን ያሳተ ሐሰተኛው ነቢይ ከእርሱ ጋር ተያዘ፤ ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ። [21]የቀሩትም በፈረስ ላይ ከተቀመጠው ከአፉ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ፤ ወፎችም ሁሉ ከሥጋቸው ጠገቡ።**

**19፡19** *ሁነኛው ጦርነት ተጀመረ።* ይህ የመዝ. 2 ጠቃሽ ነው። ይህ የሚያመለክተው የተለየ፣ በጥሬው የሚሆን የፍጻሜ ዘመን ጦርነትን ነው፣ ወይስ በመልካምና በክፉ መካከል ለሚካሄደው ትግል ተምሳሌት ነው? የራዕይ ዘውግ ተምሳሌትነትን ያመለክታል፤ ትይዩ ምንባቦቹ ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ ሉቃስ 21፤ እና 2 ተሰሎንቄ 2 ጥሬአዊነትን ያመለክታሉ። ይህ አሻሚነት የታላቅ አለመግባባት ምንጭ ነው፣ ራዕይን በመተርጎም ረገድ፣ በመልካም ሰዎች። ቀኖናዊነት በርግጥ ተገቢ አይደለም!

**19፡20 "ሐሰተኛው ነቢይ ምልክትን ያደረገ"** እሱ ሁለተኛው አውሬ ነው (ዝከ. 13:11-18; 16:13)። ይህም ወደ 13:12-13 ተመልሶ ይሄዳል፣ ሐሰተኛው ነቢይ እና የባሕሩ አውሬ ወዳላቸው ግንኙነት፣ ይህም መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር ካለው ግንኙነት የተኮረጀ ነው።

▣ **"የአውሬውን ምልክት የተቀበሉ"** (ዝከ. 13፡16-17)።

▣ **"ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ"** "የእሳት ባሕር" የሚለው ሐረግ ለራዕይ መጽሐፍ የተለየ ነው፣ ነገር ግን *ገሃነም* ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ነው (ልዩ ርዕስ 1፡18 ላይ ተመልከት)፣ እሱንም ኢየሱስ አዘውትሮ የሚጠቀምበት፣ ገሃነምን ለመግለጽ። የተለየ የብኪ ጠቃሽ ሊሆን የሚችለው ኢሳ. 30:23-33 እና ዳን. 7:11 ነው። በርካታ የትንቢት ምንባቦች አሉ፣ ፍርድን ከእሳት ወይም ከመቃጠል ጋር የሚያያይዙ። ይህ የዘላለም እሳት ጭብጥ በአፖካሊፕቲካዊ ይሁዲነት እየጎለበተ መጥቷል (ሔኖክ 27:1; 54:1; 56:3; 90:26; IV *ዕዝራ* 7:36; *አፖ*ካ. ባሮክ 59:10; 85:13 [ከጆርጅ ኢ. ላድ፣ *ራዕይ*፣ *ገጽ* 258 የተወሰደ])። ይህ ሐረግ *ራዕይ* 20:10,14; 21:8 ጥቅም ላይ ውሏል። እሱ ለሰይጣንና ለመላእክቱ የተዘጋጀ ቦታ ነበር፣ ነገር ግን ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያመጹ ደግሞ ይህንን ስፍራ ለመዳረሻ መኖርያቸው ያገኙታል። እሱ የሰይጣን የመጨረሻ መኖርያ ስፍራ ነው። እሱ በእግዚአብሔር ላይ የማመጽ ፍጻሜ ነው፣ እናም የጥልቁ ቋሚ መልክ (ማቴ. 25:46; *ራዕ*. 9:11; 11:7; 17:8; 20:1,3)።

**19፡21** ያንን የአውሬ ምልክት የሚቀበሉ (ዝከ. 13:16; 14:9,11), እነርሱም አማኞችን ያሳደዱት ናቸው፣ አሁን በክርስቶስ ቃል ይገደላሉ (የባሕሩ አውሬ እንደሚሆነው፣ 2 ተሰ. 2፡8)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ የተለያዩ ቡድኖችን ዘርዝር፣ ቁ. 1-8 እና የምስጋናቸውን ምክንያት።
2. የበጉ ሰርግ ግብዣ ጽንሰ-ሐሳብ ከየት መጣ፣ አንድምታውስ ምንድነው?
3. ቁ. 10 ስለ መላእክት ምን አንድምታ አለው?
4. የቁጥር 11-16 ጠቀሜታን አስረዳ፣ ለክርስቶስ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ።
5. ቁ. 17-21 ምን ዓይነት ጦርነት ነው የተገለጸው? በፍጻሜ ጊዜ ምን ያህል ጦርነቶች ይኖራሉ?

# ራዕይ 20
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሺህ ዓመት<br>20:1-3 | ሰይጣን ለሺህ ዓመት ታሰረ<br>20:1-3<br>ቅዱሳን ከክርስቶስ ጋር 1000 ዓመት ይነግሣሉ | የሰይጣን መታሰርና የሰማዕታት ንግሥና<br>20:1-3 | ሺህ ዓመት<br>20:1-3 | የሺህ ዓመት ንግሥና<br>20:1-3 |
| 20:4-6<br>የሰይጣን መሸነፍ | 20:4-6<br>የሰይጣን ዐመጽ ተደመሰሰ | 20:4-6<br>የሰይጣን መፈታትና የፍጻሜው ውጊያ<br>20:7-10 | 20:4-6<br>የሰይጣን መሸነፍ | 20:4-6 |
| 20:7-10<br>ፍርድ በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት<br>20:11-15 | 20:7-10<br>የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ | የመጨረሻው ፍርድ | 20:7-10<br>የመጨረሻው ፍርድ | 20:7-10<br>የመጨረሻው ፍርድ |
| | 20:11-15 | 20:11-15 | 20:11-15 | 20:11-12<br>20:13-15 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ viii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

**ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ራዕይ 20፡1-15**

ሀ. ምዕራፍ 20 ከሥነ-መለኮት አኳያ ከምዕራፍ 19 ጋር መያያዝ ይኖርበታል (ዳግም ምጽአት) እና 21-22 (ዘላለማዊው መንግሥት)። የትርጓሜው ጥያቄ የሚሆነው፣ ዳግም ምጽአቱ ከክርስቶስ የሺህ ዓመት ንግሥና የሚቀድም ከሆነ፣ ከዚያም አንዳንድ የቅድመ-ሚሊኒየም መልኮች ተመራጭ ናቸው (ይህም እንደ ታሪካዊ ትርክት የሚተረጎም ከሆነ)። ነገር ግን ምዕራፍ 20-22 አዲስ ምድብ ከሆኑ፣ እነርሱም 17-19ን የሚደግሙ ከሆኑ እንዴት ሊሆን ነው (ደብልዩ. ሄንድሪክሰን፣ *ካሸናፊዎች የበለጠ*)? ይህ ለውጥ ተመሳሳይነት አለው፣ በማኅተሞቹ፣ መለከቶቹ፣ እና ጽዋዎቹ መካከል ካለው ተደጋጋሚነት ጋር፣ እንግዲያውስ አንድ ዓይነት ሐሳባዊነት ወይም ሚሊኒየማዊነት በተሻለ ይገጥመዋል።

ለ. ምዕራፍ 20 በርካታ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቦችን ያስተዋውቃል፣ በሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያልተገለጠ፡

1. ባለ ሁለት ደረጃ ትንሣኤ
2. የተወሰነ ጊዜያዊ የሰማዕታት ንግሥና
3. መሲሐዊ ምድራዊ የአንድ ሺህ ዓመት ንግሥና
4. የመሲሑ ከፊል ንግሥና (የሰው ልጅ እንደገና ማመጽ በሰይጣን ዐመጻ ምክንያት፣ ከክርስቶስ 1000 ዓመት ንግሥና በኋላ)
5. ከማያምኑት ጋር ሌላ ጦርነት፣ ከታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ በኋላ

ሐ. በትርጓሜ ላይ ችግሮች የሚኖሩበት ምክንያት

1. በምዕራፍ 20 ሥነ-መለኮታዊ ልዩነቶች
2. በበርካታ ቁልፍ ስፍራዎች አሻሚነት
   ሀ. የሰይጣን መታሰር፣ ቁ.2

ለ. የቡድኖች ቁጥር፣ ቁ. 4 ላይ
ሐ. በመጀመሪያው ትንሣኤ እነማን ናቸው የሚካተቱት፣ ቁ. 5
መ. ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡት፣ ማን፣ የት፣ እንዴት ናቸው፣ ቁ. 6
ሠ. ቁ. 8 ላይ ያሉት "ሕዝቦች" ከየት መጡ
ረ. "የተወደደችው ከተማ" ፍችና ስፍራ፣ ቁ. 9
ሰ. ቁ. 11-15 ላይ ካለው ከነጩ ዙፋን ፍርድ የሚካተቱት እነማን ናቸው፣ እሱስ ከማቴ. 25፡31 ጋር እንዴት ይዛመዳል

3. ትልቅ ያለመስማማት ችግር አለ፣ በመልካም፣ አማኝ ተንታኞች መካከል፣ በተመሳሳይ ሚሊኒየማዊ ንድፈ-ሐሳበኞች እንኳ ቢሆን። የአንዱ ሚኒኒየማዊ ንድፈ-ሐሳብ የአካላዊውን፣ እማሬያዊውን (ጥሬ) ዳግም ምጽአት እውነታ ላይ ተጽኖ ማሳረፍ አይኖርበትም፣ ይኸውም በአኪ በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው።
4. አንዳንድ መልካም ጥቅሶች ከማምናቸው ሰዎች
ሀ. በሐተታው ላይ፣ *ራዕይ*፣ ጆርጅ ኢ. ላድ እንደሚለው "የአሜሪካ ወንጌላዊነት በሚሊኒየማዊ ዶክትሪን ላይ በማስረጃ ያልተደገፈ አጽንዖት አኑሯል... አንድ ነገር ግልጽ ነው፣ እሱ (ኢየሱስ) ስለ ጊዜያዊ ምድራዊ መንግሥት ለማስተማር አይገደውም፣ ከዘላለማዊው ሥርዓት በሚመጣው ዘመን ፊት።"
ለ. *በአዲስ ኪዳን የስዕል ቃላት*፣ ኤ. ቲ. ሮበርትሰን እንደሚለው፣ "ይህ አስደናቂ መጽሐፍ የተጻፈው ቅዱሳንን ለማበረታታት ነው፣ በታላቅ መከራ ወቅት፣ በመካከላቸው አለመግባባትን ለመፍጠር ሳይሆን" (ገጽ 457-458)።
ሐ. በጉ ይገባዋል ላይ፣ ሬይ ሰመርስ እንደሚለው፣ "ይህ ምዕራፍ በታላቅ የመንፈስ ትሕትና መቀረብ ያስፈልገዋል፣ ለአስቸጋሪነቶቹ እውቅና በመስጠት፣ ቀኖናዊ መግለጫዎችን በማስወገድ፣ እና ለሌሎች ትርጓሜ ክብር በመስጠት። ይህ ምዕራፍ ለክርስቲያኖች የመረረ የመከራከሪያ መስክ ሆኗል፣ ለብዙ ዘመናት" (ገጽ 202)።
መ. በሐተታው ላይ *የራዕይ መጽሐፍ፣ አዲሱ ዓለም አቀፍ ሐተታ ተከታታይ*፣ ሮበርት ኤች. ሞኡንስ እንደሚለው፣ "ለምዕራፍ 20 የመጀመሪያዎቹ አስር ቁጥሮች በብዙ ጸሐፍት የተሰጡትን አትኩሮቶች በመያዝ መፍረድ፣ አንዱ የሚፈርደው ተናጠላዊ እጅግ ጠቃሚ የራዕይ መጽሐፍ ክፋይ አድርጎ ነው። በዚህ ነጥብ ላይ የብዙ ተርጓሚዎች አዝማሚያ በተወሰነ የሚሊኒየም አተያይ ላይ ልክ እንደሆኑ ማቅረብ ነው። የዚህን ጠቃሚ ምንባብ ጠቀሜታ ባለመካድ፣ ከዚህ መሠረታዊ ጭብጥ ከፍ ሳያደርጉ፣ ከክርስቶስ መመለስ፣ ከመጨረሻው ፍርድ እና ከሁሉም ከፉዎች መወገድ፣ እንዲሁም ድንቅ ስለሆነው ከዘላለም አቋም። የሚሊኒየሙ ምንባብ ጥንቁቅ ንባብ (ቁ. 1-10) የሚያሳየው ምናልባት በተወሰነ መልኩ ስለ ሰማዕታት ትንሣኤ ብቻ ነው፣ እናም እሱ የተለየ አመላካች አልያዘም፣ ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡበት በምድር ላይ ለመሆኑ ወይም ዳግም ምጽአቱን ስለመከተሉ" (ገጽ 351)።

መ.ሚሊኒየማዊው ንግሥና አንድ ዓይነት አይደለም፣ እንደ
1. መሲሐዊው ዘመን፣ ወይም
2. የእግዚአብሔር መንግሥት (ሁለቱም ቁ.1 እና ቁ.2 ዘላለማዊ ናቸው፣ ዳን. 7:14,27; ኢሳ. 9:7; ሉቃስ 1:33; II ጴጥ. 1:11; *ራዕ.* 11:15; 22:5)

ሠ. የ1000 ዓመት ከክርስቶስ ጋር የደስታ ንግሥና ጽንሰ-ሐሳብ የመጣው ከ6000 ዓመት ታሪክ ነው፣ እና ከዚያም የሰንበት የብልጽግና ዕረፍት፣ ከዘፍጥረት 1። ይህ የሚመስለው (ታሪካዊ ቅድመ-ሚሊኒየም) የቀድሞ ክርስቲያን ጽሑፎች ክፍል እንደነበረ ነው (የበርናባስ መልእክት 15 እና 2 ሔኖክ 33)።

ረ. ይህ ምዕራፍ ተመስጧዊ መገለጥ እንደሆነና መለኮታዊ ዓላማ እንዳለው ግልጽ ነው። ሆኖም፣ ያ ዓላማ ምንድነው፡ (1) የፍጻሜ ዘመን ሁነቶችን ዝርዝር ማሳየት ወይስ (2) በየዘመናቱ ለሚሆነው መንፈሳዊ ውጊያ መንፈሳዊ ይዘትን መስጠት?

ተርጓሚዎች መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል፣ የዮሐንስን ሳይሆን የራሳቸውን አጀንዳ ከመግፋት። የተለየነት፣ እኔ ብቻነት፣ ወይም የሥነ-መለኮታዊ አቋም ወይም መምህር ታማኝነት በርካታ ትርጉሞችንና መጥፎ አዝማሚያን ፈጥሯል። የዮሐንስ አጀንዳ/ዓላማ የሚገለጸው በዘውግ ምርጫውና በአኪ ሳይሆን በብኪ ምስያ አመራረጡ ነው! አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፍን በጥሬው መውሰድ የወግ አጥባቂነት ምልክት አይደለም፣ ግን የተሳሳተ ምሪት ያለው ስሜት እንጂ! ዘመናውያን ተርጓሚዎች አንዳንድ የዮሐንስ ተምሳሌቶችን ለምን እማሬያዊ (ጥሬ) ሌሎችንም ፍካሬያዊ (ዘይቤአዊ) ያደርጋሉ? ሁሉም ዘይቤአዊ ናቸው (ይህ ማለት ትክክል አይደሉም ማለት አይደለም)! የዮሐንስ የፍጻሜ ሰዓት አቅርቦት በቀዳሚነት የብኪ መዋቅር ነው። እሱ ሆን ብሎ የኢየሱስንና የጳውሎስን የፍጻሜ ዘመን ትምህርቶች ችላ ያላቸው ይመስላል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጸሐፍት፣ በሁለቱም በብኪም ሆነ በአኪ፣ ስልታዊ የፍጻሜ ዘመን አተያይን አልገለጹም። እነርሱ በርግጥ እውነትን አቅርበዋል፣ ነገር ግን ሎጂካዊ፣ ቅደም ተከተላዊ፣ ስልታዊ ባልሆነ መንገድ! የራዕዮቹን ማዕከላዊ እውነቶች እናጽና ስለ ዝርዝሮቹ ቀኖናዊ ሳንሆን።

ሰ. ይህ ምዕራፍ ሥነ-መለኮታዊ ከብደት እንዲይዝ ተደርጓል፣ ተዋረዳዊ በሆነ መልኩ ባለው ስፍራ፣ ከሙሉው መጽሐፍ መዋቅርና መልእክት አኳያ! ይህ የደራሲው ዋነኛ አጽንዖት አይደለም! ሚሊኒየም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ንግሥና ቀዳሚ ነው። ራዕይ ብቻ ነው ይህን ጊዜያዊ መሲሐዊ አገዛዝ ለመጥቀስ የመረጠው። እሱም የሚከሰትነት ዘውግ እውነትን በተግባቦት የሚያቀርበው በተምሳሌታዊ ቋንቋ ነው። በግሌ፣ የሚያስደንቀኝ የሚሊኒየማዊ ንግሥና አይደለም (ከብኪ ጽሑፎች አኳያ)፣ ግን

1. ባለ ሁለት ደረጃው ፍርድ
2. ከሙታን የተነሡ ቅዱሳን እና ሌሎች ሰዎች አንድ ላይ መደባለቅ፣ በምድራዊ መቼት
3. ከረጅሙ የመሲሐዊ ንግሥና በኋላ የዐመጽ መኖር
   የክርስቶስ አካላዊ ንግሥና ውጤት የማይኖረው ይሆናልን፣ የሰው ልጅን ወደ ጽድቅና ለማምጣት፣ ሰይጣን እንኳ በሌለበት? ወይስ ይህ ተምሳሌታዊ መንገድ ነውን የሰውን ልጅ የብልሹነት ደረጃ በግልጽ ለማሳየት?

ሽ. እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን በ22፡18-19 ብርሃን! ሁላችንም በኃጢአተኛ ተፈጥሯችን፣ በዘመናችን፣ በልምዳችን፣ እና በመምህራናችን ተጎድተናል!

**ረጂ ጸሐፍት**

ሀ. አለን ጆንሰን፣ "ራዕይ፣" የተንታኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣ ቅጽ 12
ለ. ጆርጅ ላድ፣ የዮሐንስ ራዕይ
ሐ. ሊዮን ሞሪስ፣ "የቅዱስ ዮሐንስ ራዕይ፣" ቲንዳሌ የአዲስ ኪዳን ሐተታ፣ ቅጽ 20
መ. ሮበርት ሞኡንስ፣ "የራዕይ መጽሐፍ፣" አዲሱ ዓለም አቀፍ ሐተታ
ሠ. ሬይ ሰመርስ፣ በጉ ይገባዋል
ረ. ክሬግ ብሌሲንግ እና ዳረል ቦክ፣ ቀጣይነት ያለው ነጻነታዊነት
ሰ. ዲ. ብሬንት ሳንዲ፣ የማረሻ ጫፍ እና የመግረዣ ሜንጦ

**የቃል እና የሐረግ ጥናት**

**ራዕይ፡ 20፡1-3**

**[1]የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። [2]የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፥ [3]ሺህ ዓመትም አሰረው፥ ወደ ጥልቅም ጣለው አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።**

**20፡1 "የጥልቁንም መክፈቻ በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ"** ይህ 9፡1-2፣11 ላይ ካለው የጥልቁ መክፈቻ ካለው መልአክ ጋር ተመሳሳይ ነው። ሰይጣን፣ ስሙ ባልተጠቀሰ መልአክ መታሰሩ አስገራሚ ነው።

▣ **"የጥልቁንም መክፈቻ"** ራዕይ ላይ ሁለት "ቁልፎች" አይተናል። ኢየሱስ የሞትና የሲኦል ቁልፍ አለው፣ 1፡18 ላይ እና ስሙ ያልተጠቀሰው መልአክ የጥልቁ መክፈቻ አለው፣ 9፡1 ላይ። "መክፈቻ" የሚለው ቃል ዘይቤአዊ ነው፣ "ለሥልጣን።"

"ጥልቁ" የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ለጥልቀት ነው፣ በአሉታዊ ቅጥያ (ጥልቅ ጉድጓድ)፣ 9፡1 ላይ ተብራርቷል። እሱም ለአጋንንታዊ መናፍስት ማሰሪያ ስፍራ ነው። ሆኖም፣ ይህ ፍጹም የሆነ ትርጓሜ ሊሆን አይችልም፣ በጳውሎስ የእሱ አጠቃቀም ምክንያት ሮሜ. 10፡7 ላይ። እሱም "ከእንጦርጦስ" ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፣ እንደ ሁሉም ርኩሳን መናፍስት ማሰሪያ ስፍራ (ሉቃስ 8፡31፤ ይሁዳ ቁ. 6፤ 2 ጴጥ. 2፡4)። በራቢያዊ ይሁዲነት፣ በ2ኛ እና 3ኛ ክፍለ ዘመን እሱን የሚረዱት እንደ ሲኦል የኩነኔ ክፍል ነው።

**20፡2 "የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን"** እነዚህ አራትዮሽ የክፉው መጠሪያዎች፣ 12፡9 ላይ የተብራሩት፣ ማን እንደሚታሰርና ማን ኋላ ላይ ወደ እሳት ባሕር እንደሚጣል አጽንዖት በመስጠት በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው (ዝከ. ቁ. 10)። ይህም መጀመሪያውን (ዘፍጥረት 3) እና መጨረሻውን (ራዕይ 20-22) ያያይዘዋል።

"ዘንዶ" የሚለው ቃል ምናልባት
1. "ከእባቡ" ጋር ትይዩ ይሆናል። በብኪ የዕብራይስጡ ቃል *tannin* ሊያመለክት የሚችለው
   ሀ. የምድር እባብ (ዘጸ. 7፡9,10,12; ዘዳ. 32:33; እንዲሁም መዝ. 91፡13)
   ለ. የባሕር እባብ (ዘፍ. 1፡21; መዝ. 148፡7)
2. ከአፈ-ታሪካዊው የባሕር አውሬ፣ ሌዋታን ጋር ትይዩ፣ (ኢዮብ 7፡12; መዝ. 74፡13-14; ኢሳ. 27፡1), እሱም አንዱን የእግዚአብሔርን ፍጡር ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ (ኢዮብ 41; መዝ. 104፡24-26), ወይም እንደ ክፉ ተምሳሌት (እንደ ረዓብ ኢሳ. 51፡9)
3. ለእስራኤል ጠላቶች መሪዎች በተምሳሌትነት ጥቅም ላይ የዋለ
   ሀ. ግብፅ (መዝ. 87፡4; ረዓብ; ሕዝ. 29፡3)
   ለ. ባቢሎን (ኤር. 51፡34)
4. ለሚሶፖታሚያ አፈ-ታሪክ ጥቅም ላይ የዋለ፣ እንደ አዋኪ አውሬ (የራዕይ 12 መግቢያ ቁ. ለ እና በተለይም 12፡3)

የኪንግ ጀምስ ትርጉም ሁለቱንም *tannin* እና *tannim* ይተረጉማቸዋል (ቀበሮ ወይም ተኩላ, ኢዮብ 30፡29; መዝ. 44፡19; ኢሳ. 13፡22; 34፡13; 35፡7; 43፡20; ኤር. 9፡11; 10፡22; 49፡33; 51፡37; ሕዝ. 29፡3 እና ሚኪ. 1፡8) እንደ "ዘንዶዎች" ነገር ግን እነርሱ የሚዛመዱ ቃላት አይደሉም። ተኩላዎች የ*tan* የብዙ ቁጥር ናቸው።

▣ **"ሺህ ዓመትም አሰረው"** ሰዎች ዘወትር የሚሰማቸው በአዳምና ሔዋን ምርጫ ምክንያት አጠቃላይ ኩነኔ መሆኑ ፍትሐዊ እንዳልሆነ ነው። ይህ የክፉውና የፈተናው መወገድ ከሥነ-መለኮት አኳያ ከዔድን ገነት ጋር ተመሳሳይ የሆነ መቼት ይሰጣል። የሰው

ልጅ ከሰይጣን የሚመጣውን ፈተና ብቻ አይደለም የሚገላገለው፣ በከበረው መሲሕ መገኘት ይደሰታሉ፣ ረዘም ላለ ጊዜ። አሳዛኙ ነገር የሰው ልጅ እንደገና በእግዚአብሔር የክርስቶስ ንግሥና ላይ ማመጹ ነው (ዝከ. 20፡7-9)!

የብኪ ጽንሰ-ሐሳብ የሆነው ሁለቱ የአይሁድ ዘመናት በመልካምና በክፉ መካከል የሚሆነው ግጭት ማሳያ መንገድ ነው (የተወሰነ ምንታዌነት)። አይሁድ ይህንን ሁለንተናዊ ግጭት የሚስሉት በፍጻሜ ዘመን በሚሆን ጦርነት እንደሚቃለል ነው (መዝሙር 2)። ዮሐንስ ይሄንን ምስያ የተጠቀመው በእሱ ዘመን የነበሩትንና በየዘመናቱ ያሉትን ተሳዳጅ ክርስቲያኖች ለመርዳት ነው። በዚህ መሰሉ ግልጽ ተምሳሌታዊ መጽሐፍ፣ እና እጅግ በተለየ ራዕይ እና እንደ 1000 ዓመት ንግሥና ያልተደገመ፣ እንዴት አንዱ ይሄንን በጥሬው ለመተርጎም ይፈልጋል? መልሱ የሚያርፈው በተርጓሚው ቅድመ-ግምት ነው፣ በሥነ-ትርጓሜ ሳይሆን። እሱ መጽሐፍ ቅዱስን የማመን ጉዳይ አይደለም፤ እሱ ተገቢ የሆነ፣ ቋሚ የአፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ትርጓሜ ነው። አማኞች ስለ ፍጻሜ ዘመን ተጨማሪ መረጃ መፈለጋቸው የሚወስዳቸው (1) ይሄንን መጽሐፍ ወደ ቅደም ተከተላዊ አቅርቦት መቀየር፣ ለዳግም ምጽአቱ እና (2) ዝርዝሮቹ ከገዛ ራስ ታሪክ፣ ባህል፣ እና ትርጓሜ፣ ሥነ-መለኮታዊ አቋም ጋር እንዲስማሙ ማስገደድ። ይህም በጥሬው ከተወሰደ፣ በዚህ ጊዜ ብቻ የኖሩና የሞቱ ክርስቲያኖች ብቻ ከክርስቶስ ጋር ይነግሣሉ (ዝከ. ቁ. 4-5)!

**20:3 "ወደ ጥልቅም ጣለው፣ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት፤"** ለሰይጣን ባልታወቀ መልአክ መታሰር ጋር በተያያዘ አምስት ግሦች አሉ፡ (1) "የያዘው"፤ (2) "አሰረው"፤ (3) "ጣለው"፤ (4) "ዘጋበት"፡ እና (5) "ማኅተም አደረገበት።" እነዚህ ሁሉ የድርጊት የአሁን አመላካች ናቸው። ይህም የሚያመለክተው የሰይጣን ተጽዕኖ ሙሉ ለሙሉ መወገዱን ነው። ይህም የኢሳ. 24፡22 ጠቃሽ ነው።

▣ **"አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት"** ማሳት ዘወትር የክፉውና የእሱው ወኪሎች ተግባር ነው (ዝከ. 12:9 13:11-14; 16:14; 19:19; 20:8)። የእሱ ጊዜ አጭር መሆኑን ከማወቁ የተነሣ (ዝከ. 12፡12)፣ የእግዚአብሔርን ተወዳጅ ፍጡሮች፣ ወንዶችና ሴቶች፣ የቻለውን ያህል ከእሱ ነጥቆ ወደ ዐመጻና አለማመን ለመውሰድ ይሞክራል። እሱም ደግሞ አምልኮን ይሻል፣ በኢየሱስ ፈተና ሰዓት እንደታየው፣ ማቴ. 4፡9 እና 13፡4 ላይ።

እጅግ ዋነኛው ጥያቄ፣ "አሕዛብ" ማንን እንደሚያመለክት ነው? የማያምኑት አሕዛብ ቀደም ሲል ጠፍተዋል 17:2; 18:3 እና 19:18-21። አንዳንዶች የሚሉት እሱ የሚያመለክተው ተመሳሳይ አሕዛብን ነው፣ ግን የእነርሱ ቅሬታዎች ናቸው፣ የተሸነፈ ሠራዊታቸው ሳይሆን። ሌሎች የሚሉት እነርሱ የተለዩ አሕዛብ ናቸው በእግዚአብሔር ተቃዋሚነት፣ በክርስቶስ ተቃዋሚነት ሴራ ላይ ያልተሳተፉ። "የአሕዛብ" ተምሳሌት እጅግ አስቸጋሪ ነው (2፡26 እና 10፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት) እንደገና ራዕ. 22፡2 ላይ በመታየታቸው ምክንያት፣ ከሰይጣን እና ከማያምኑት ሁሉ መጥፋት በኋላ እንኳ።

ሊሆን የሚችለው 19:11-21 (ማለትም፣ ምዕራፍ 17-19) ተደግሟል፣ 20:1-10 ላይ (ማለትም፣ ምዕራፍ 20-22)። ይህም ጥያቄውን ሊያቃልል ይችላል፣ የ"አሕዛብ" ከአጠቃላይና ከመጨረሻው ፍርድ በኋላ የመኖራቸውን፣ ምዕራፍ 19 ላይ። "አሕዛብ" ዘወትር የሚያመለክተው፣ ኃጢአተኛ፣ አምላክ-የለሽ ሕዝቦችን ነው (2፡26 እና 10፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ እና የጴቭ ማቲውሰንን ዘገባ ተመልከት፣ "ሚሊኒየምን ዳግም መመርመር 20:1-6 ላይ፡ መቀዳጀት እና ማጠቃለል፣" ጄኢቲኤስ፣ ቅጽ 44 ቁ.2፣ ሰኔ 2001፣ ገጽ 237-251)። የሰይጣን መገኘት 20:1-10 ላይ ከሉቃስ 10:17-20 ጋር አቻ ነው (ሰይጣን ከሰማይ ወደቀ)፤ ማቴ. 12:26-29 (የሰይጣን መንግሥት ድል ተነሣ፣ በክርስቶስ ከክፉ መንፈስ የማንጻት ሥራ)፤ ቆላ. 2:10፣15 (ኀይሎችንና ሥልጣናትን ትጥቅ አስፈታ)። ራዕይ 20:1-10 የክርስቶስን ድል ነው የሚያሳየው፣ በመጀመሪያ ምጽአቱ፣ ውጤቱም እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ ይኖራል፣ ጥቂት ቀደም ብሎ (ሚሊኒየማዊነት)።

ይህ ማጠቃለያ እውነት ከሆነ እንግዲያውስ ዮሐንስ እንዴት ተጽዕኖ እንዳደረበት ያሳያል፣ በሕዝቅኤል 38-39 (እና መዝሙር 2)፣ በነጠላ የፍጻሜ ዘመን ጦርነት ሐሳብ። ዮሐንስ የተንሹን እስያ አምላክ የለሽ ሕዝቦች ግጥሚያ ወስዶ ሁሉን አቀፍ አደረገው፣ ወደ ፍጻሜው ዘመን ጦርነት፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ እና በሰይጣን ተጽዕኖ እና ባለማመን በተያዙ መካከል።

▣ **"ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።"** በርካታ ውይይቶች ተካሂደዋል፣ ሰይጣን ለምን ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ እንደ"ሚገባው" (*dei*) ። አንዳንዶች የሚመለከቱት፣ እግዚአብሔር ፍትሐዊነቱን ለማሳየት ነው፣ ዓመጸኞቹን ሰዎች መኮነኑን፤ ሌሎች የሚመለከቱት እንደ አንድ ተጨማሪ የመዋጀት ዕድል ነው፣ 9:20-21; 14:6-7; 16:9,11 ላይ እንዳለው።

ደግሞም ሊሆን የሚችለው የሰይጣን መታሰር የክፉው የመጨረሻ ሽንፈት ተምሳሌት ነው፣ የአይሁድን አፖካሊፕቲካዊ ምስያዎች ከ1 ሔኖክ 10:4-6,11-13 በመጠቀም፣ እዚያም አዛዜል (የበረሀው ጋኔን፣ የሌዋ. 16፡8፣10፣26) በመልአክ ታስሯል፣ ሰዎችን እንዳያስት። እስሩ ክፉ መላእክትን የመያዣ መንገድ ነው፣ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ኢሳ. 24:21-22; IIጴጥ. 2:4; እና ይሁዳ ቁ. 6።

እንዲሁም ደግሞ ሊሆን የሚችለው የእርሱ መፈታት የፍጻሜ ዘመኑን ያመጣል፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በእግዚአብሔር፣ መሲሕ፣ መንፈስ እና በተከታዮቻቸው እና በሰይጣን፣ በባሕሩ አውሬ፣ በምድሩ አውሬ እና በተከታዮቻቸው መካከል ግጥሚያ ይካሄዳል። ፍጥረት ከክፉው ነጻ ይወጣል። ታሪክ የጦር አውድማ ሆኗል፣ ታሪክ የፍጻሜው ግጥሚያ ትዕይንት ይሆናል። የብኪ ሐሳብ ከመዝሙር 2 እና ሕዝቅኤል 38-39 ነው። ይኸው ተመሳሳይ የፍጻሜ ዘመን ፍርድ 19:19-21 ላይ ይታያል። ይህ እውን ከሆነ እንግዲያውስ ምዕራፍ 17-19 እና 20 ትይዩ ናቸው፣ እናም ተመሳሳይ ጊዜ ይሸፍናሉ፣ ከክርስቶስ የመጀመሪያው ምጽአት እስከ ሁለተኛው ምጽአት ድረስ።

**ራዕይ፡ 20፡4-6**

**[4]ዙፋኖችንም አየሁ፥ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፥ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም**

**ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ። [5]የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም። ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው። [6]በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።**

**20:4 "ዙፋኖችንም አየሁ"** ይህ የዳን. 7፡9 ጠቃሽ ነው። በርካታ ዙፋኖች ራዕይ ላይ ተጠቅሰዋል፡ (1) የእግዚአብሔር ዙፋን (ዝከ. 5:1,1,17; 6:16; 7:10,15; 19:4; 21:5); (2) የሰይጣን ዙፋን (ዝከ. 2:13); እና (3) የአውሬው ዙፋን (ዝከ. 13:2; 16:10)። እሱም የሥልጣንና ኃይል ተምሳሌት ነው።

▣ **"በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት"** ይህ የዳን. 7፡22 ጠቃሽ ነው። ጥያቄው፣ "እነርሱ" የሚጠቅሰው ማንን ነው? ዳንኤል ላይ እሱ መልአካዊ ጭፍራ ወይም ቅዱሳን ሊሆኑ ይችላሉ። በርከት ያሉ ውይይቶች በተንታኞች መሐል ተካሂዷል፣ ምን ያህል ቡድኖች በዚህ ቁጥር እንተጠቀሱ።

1. አንዳንዶች ሦስት ቡድኖችን ያያሉ (በዙፋኖቹ ላይ ያሉ፣ ክርስቲያን ሰማዕታት፣ እና ሌሎች ክርስቲያኖች፣ ለአውሬው ያልሰገዱ)
2. አንዳንዶች ሁለት ቡድኖች ያያሉ
3. አንዳንዶች አንድ ቡድን ያያሉ

አንድ ቡድን ከሆነ፣ የሚያመለክተው ክርስቲያን ሰማዕታትን ነው። ሆኖም፣ ሌላ ቅዱስ ቃላዊ ትይዩ የለም፣ የሰማዕታትን ንግሥና ለመወሰን። መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚገባው የቅዱሳንን ሁሉ ንግሥና ነው (ራዕ. 3:21; 5:10; 22:5; ማቴ. 19:28; ሉቃስ 22:29-30; II ጢሞ. 2:12)። ልዩ ርዕስ 5፡10 ላይ ተመልከት።

ሌሎች አተያያቸውን የመሠረቱት በሁለት ቡድን ላይ ነው፣ በትንሹ ሐረግ፣ በቁ. 4 ኋለኛ ክፍል ላይ በሚገኘው፣ "ለአውሬውም ያልሰገዱትን፡" እነርሱ ይህንን የሚመለከቱት እንደ ሁለተኞቹ የክርስቲያን ቡድኖች ነው፣ በተፈጥሮ ሞት የሞቱት አማኞች ሁሉ፣ ግን ለአውሬው አንሰግድም ያሉ። ምዕራፍ 19 ላይ ባለው በዳግም ምጽአቱ እይታ እና 20:11 ላይ በሚገኘው በታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ፣ ይህ እጅግ የተሻለ ትርጓሜ ይሆናል። ይህ ትርጉም እውነት ከሆነ፣ እንግዲያውስ ቁ. 11 ላይ ያለው የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ የሚጠቅሰው የጠፉትን ብቻ ነው፣ እናም ከማቴ. 25፡31 ጋር ቀጥተኛ ትይዩ አይደለም።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ዳኝነትም ተሰጣቸው"** |
| **አኪጀት** | **"ዳኝነትም የደረገላቸው** |
| **አየተመት** | **"እንዲዳኙ ሥልጣን ተሰጣቸው"** |
| **አእት** | **"የዳኝነት ሥልጣን ተሰጣቸው"** |
| **አኢመቅ** | **"ዳኝነት ይሰጡ ዘንድ ሥልጣን ተሰጣቸው"** |

የግሪኩ ሐረግ ማመልከት የሚችለው አንድም፣ (1) የእነርሱን ከክርስቶስ ጋር መንገሥ ነው (ዝከ. 2:26-27; I ቆሮ. 6:2, ልዩ ርዕስ 5፡10 ላይ ተመልከት) ወይም (2) የእነርሱን ፍትሕ መቀበል (ዝከ. 2:26-27; I ቆሮ. 6:2።

▣ **"ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት"** አንዳንዶች ይህንን የሚተረጉሙት ከሥጋ የተለዩትን ነፍሳት ነው (ዝከ. 6፡9)። "ራሶቻቸው የተቆረጡ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባለ ሁለት ስለት መጥረቢያ ነው፣ የሞት ቅጣትን ለመፈጸም ጥቅም ላይ ይውል የነበረ፣ በሮሜ ግዛት (ሮሜ. 13፡4 እና ጆሴፈስ፣ የአይሁድ ጥንታዊ ቅርሶች፣ 14፡9፡4)። ይህ የሚያመለክተው ክርስቲያን ሰማዕታትን ነው።

▣ **"ለአውሬውም ያልሰገዱትን"** የላይኛው ሐረግ ሰማዕታትን የሚጠቅስ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ሌሎችን ነው፣ በዚህ ጊዜና ሰዓት የሞቱትን (ዝከ. 13፡15)። እንግዲህ ይህ በክርስቶስ ሁለት ምጽአቶች መካከል ያለ ስዕል ከሆነ፣ እንግዲያውስ እሱ የሚያመለክተው አማኞችን ሁሉ ነው። ይህን የመጨረሻ ጊዜ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ያንን ትውልድ ብቻ ነው።

▣ **"ምልክቱንም ያልተቀበሉት"** 13፡16-17 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት። ምልክቱ፣ "ለአውሬው ወይም ለምስሉ ያልሰገዱ" ለሚለው ትይዩ ነው።

▣ **"በሕይወት ኖሩ"** ይህ ቃል (zÔē) ዘወትር የሚጠቅሰው ለሥጋ ትንሣኤ ነው (ማቴ. 9:18; ዮሐንስ 4:25; ሐዋ. 1:3, 9-11; ሮሜ.14:9; ራዕ. 1:18; 2:8; 13:14)። ተርጓሚዎች አንደኛውን የቃሉን አጠቃቀም ሊተረጉሙ አይችሉም፣ ቁ. 4 ላይ፣ እንደ መንፈሳዊ ትንሣኤ እና ሁለተኛው አጠቃቀሙ ቁ. 5 ላይ እንደ የሥጋ ትንሣኤ። ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡት ሰማዕታት የትንሣኤ አካል ነው ያላቸው ወይስ ሥጋዊ አካል፣ እሱም የሚበሰብስ? እነርሱ የትንሣኤ አካል ካላቸው፣ "አሕዛብስ" እንዴት ይሆናሉ?

▣ **"ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ነገሡ"** የኢየሱስ ንግሥና ጽንሰ-ሐሳብ ራዕ. 12:5; 19:5 ላይ የተጠቀሰው፣ ይኸውም ከመዝ. 2፡8-9 ላይ የተጠቀሰ ይመስላል፤ ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡት ቅዱሳን ማቴ. 19:28; ሉቃስ 22:28-30; II ጢሞ. 2:12; ራዕ. 3:21; 5:10; 20:4,6 እና 22:5 ላይ ተጠቅሰዋል። ንግሥናው ሚሊኒየማዊ ነው ዘላለማዊ (ዳን. 7:14,18,27 እና ራዕ. 22:5)? ንግሥናው ምድራዊ ነውን (ዝከ. 5፡10) በፍልስጥኤም ዐውድ ወይስ በዓለም አቀፍ ዐውድ? ልዩ ርዕስ በእግዚአብሔር መንግሥት መግዛት 5፡10 ላይ ተመልከት። የተለያዩ ሚሊኒየማዊ አተያዮችን ዕዝል አምስት ላይ ተመልከት።

1000 ዓመት ለቤተ ክርስቲያን ዕድሜ ተምሳሌት ከሆነ (ከሥጋ መልበስ እስከ ዳግም ምጽአቱ)፣ ከዚያም ይህ 1000 ዓመት (10x10x10 — የዕብራይስጥ የላቀ ማወዳደርያ መልክ ፣ ፍጹም ለሆነው ቁጥር) ዘላለማዊነትን ያመለክታል።

ሆኖም፣ ይህ ማሳያ ከቁ. 5-6 ጋር ደኅና አድርጎ አይገጥምም። ይህም ጥሩ ምሳሌ ነው፣ አንዱ የትርጓሜ አገባብ ለአንዳንድ ጽሑፎች በሚገባ ምላሽ ሲሰጥ፣ ግን ለሁሉም ላለመሆኑ። እነዚህ የተለያዩ የትርጓሜ ብልሃቶች እየጎለበቱ የመጡት የተለያዩ ተርጓሚዎች ለተለያዩ ጽሑፎች አጽንዖት ስለሚሰጡ ነው፣ እንዲሁም ሙሉውን የአኪ ጽሑፍ በተወሰኑ የተመረጡ "ቁልፍ" ጽሑፎች አኳያ ስለሚያነቡ። እዚህ ጋ ተለዋዋጭነት አለ፣ አሻሚነት አለ፣ ምሥጢራዊነት አለ። ችግሩን ከማያካትትነት እና ከቀኖናዊነት ጋር አናደበላልቀው!

**20:5** አየተመት እና አእት ትርጉሞች ቁ. 5ን በቅንፍ ውስጥ ያስገቡታል። በዚህ በአንደኛው ትንሣኤ የሚካተተው ማን በአጠቃላዩ ፍርድ እንደሚካተት ይወስነዋል፣ 20፡11 ላይ ባለው። እዚህ አማራጮች አሉ፣ "ለተቀሩቱ ሙታን።"

1. የጠፉት (ዝከ. ቁ. 6፤ ዳን. 12፡2)
2. ቀደም ሲል ከነበሩት ጊዜያት ክርስቲያኖች (ዝከ. ቁ. 6፤ 2 ጢሞ. 2፡12)
3. ከዚህ ዘመን ክርስቲያኖች፣ ግን የተፈጥሮ ሞት የሞቱ (ዝከ. ቁ. 4ሐ)

◘ **"የፊተኛው ትንሣኤ"** በአኪ ሁሉ ለሙታን ትንሣኤ አጽንዖት ተሰጥቶታል (ዮሐንስ 5:28-29; ሉቃስ 14:14; ሐዋ. 24:15; I ቆሮ. 15:52; ፊሊ.. 3:3; I ተሰ. 4:16; II ተሰ. 1:7-10)። ሆኖም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም ትይዩ የለም፣ ስለ ሁለቱ ተናጠላዊ የአማኞች ትንሣኤዎች፣ ስለ ድርብ ትንሣኤ፣ ዳን. 12፡2 ላይ ካለው ጠቃሽ በቀር፣ (የጠፉት እና የዳኑት)፣ ምንም እንኳ ጆርጅ ላድ፣ ዮሐንስ 5:29 እና I ቆሮ. 15:24-25ን እንደ ታሳቢ ትይዩ ቢመለከታቸውም። ሁሉም ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓቶች፣ የአንድ ሺህ ዓመቱን ንግሥና በጥሬው እንደሚሆን የሚያምኑት እንኳ ቢሆኑ፣ በዚህ የተሰነጠቀ ትንሣኤ ዋነኛ የትርጓሜ ችግር አለባቸው። የተነጠቁት ክርስቲያኖች (1 ተሰ. 4:13-18; ራዕ. 4:11 ወይም 11:12) በሺው ዓመት ንግሥና ይካተታሉን፣ የብኪ አማኞች በሺው ዓመት ንግሥና ይካተታሉን? ይህ የብኪ ሰማዕታትን ይጨምራል፣ ወይስ በመጨረሻው ዘመን መከራ ጊዜ ሰማዕት የሆኑትን?

◘ **"የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ"** ይህ የዘጸ. 19፡5-6 ጠቃሽ ነው። ይህ ቃል፣ እስራኤልን እንደ እግዚአብሔር መሣርያ የሚያመለክተው፣ ለአሕዛብ መገለጥና መዋጀት፣ በአኪ ሰፊ ሆኖአል፣ ሁሉንም በቤተ ክርስቲያን ለማካተት (1ጴጥ. 2:5,9 እና ራዕ. 1:6; 5:10)። በፊልድልፍያ መልእክት፣ አንድ ጠቃሽ ለቅዱሳን ተደርጓል፣ ከመቅደስ ጋር በተያያዘ (ዝከ. 3፡12)። ዘይቤው ተቀይሯል፣ ከእግዚአብሔር ባርያዎች፣ ይህን ዓለምን በተመለከተ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ኅብረት እስከማድረግ ድረስ።

**20፡6** ይህ ቁጥር የትርጓሜ ችግሩ ላይ ተጨማሪ ነው። ማንኛውም አማኝ ለሁለተኛው ሞት ለምን ይገዛል፣ እሱም ለገሃነም ዘይቤ የሆነ (ዝከ. ቁ. 6) ? ሰማዕታት ብቻ ናቸው የእግዚአብሔር ካህናት የሚሆኑት ወይስ ቅዱሳን ሁሉ (ዝከ. 1:6; 5:10; IIጴጥ. 2,5,9)? የአንደኛው ክፍለ ዘመን ሰማዕታት ብቻ ናቸው የሚነግሡት ወይስ የብኪ ሰማዕታት ይካተታሉ፣ የየዘመኑ ሰማዕታት ይካተታሉ ወይስ ታማኝ ሆነው የቀሩት ሁሉም ክርስቲያኖች ይካተታሉ?

**ራዕይ፡ 20፡7-10**

**[7]ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፥ [8]በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን፥ እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው። [9]ወደ ምድርም ስፋት ወጡ የቅዱሳንንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው። [10]ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።**

**20:7 "ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፥"** ሕዝቅኤል 36-39 የዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ዳራ ነው። ሕዝቅኤል ላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ በደኅንነት ዐርፏል፣ በፍጻሜ ዘመን መቼት ላይ (ይሁዳ ወይም ኢየሩሳሌም ወይም የተስፋይቱ ምድር)፣ ግን አሁንም በክፉ ሕዝቦች ይጠቃሉ (ጎግ እና ማጎግ)። በራቢያዊ ይሁዲነት እነዚህ ሁለት ጠላቶች ጥቅም ላይ የሚውሉት እንደ ሁሉም የመሲሑንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጠላቶች ለመግለጽ ነው። በመነሻው፣ ጎግ ሰው ነው፣ ከማጎግ ምድር፣ ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ ቃላቱ ሰውኛ ሆነዋል፣ ለመንታ ጠላቶች። ዮሐንስ ዘወትር የብኪ ጠቃሹን ደግሞ ይሠራዋል፣ ለአንደኛው ክፍለ ዘመን አንባቢዎቹ እንዲስማማ።

**20:8 "እንዲያስታቸውይወጣል፤"** አስገራሚ የሚሆነው የሰው ልጅ ከ1000 ዓመት የክርስቶስ ግዛት በኋላ ወደ ዐመጽ ለማምራት መቻሉ ነው! እነዚህ ሕዝቦች "የማያምኑ" ወይም "በመነሻ ያመኑ" ናቸውን? የክርስቶስ መገኘትና ንግሥና በሰው ኅብረተሰብ ዘንድ ቋሚ ለውጥ የሚያመጣ ተጽዕኖ ማሳደር አልቻለምን?

◘ **"ጎግና ማጎግ"** ይህ የማያምኑት ሕዝቦች ቀጣይነት ያለው ዐመጻ ጠቃሽ ነው። እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ከተመለሰች በኋላ (ሕዝቅኤል 37)፣ በእግዚአብሔር ድርጊቶች ላይ በመመሥረት (ሕዝቅኤል 36)፣ እሷ ገና ችግሮች አሉባት በድኃሚ ከሚወሯት ሕዝቦች ጋር ("በጎግ ላይና በማጎግ ምድር ላይ፥ በሞሳሕና በቶቤል ዋነኛ አለቃ" ሕዝ. 38፡2)። ይህም የሚገልጸው የመሪዎችን ስም ወይም የክልሎችን ስም ነው፣ የወራሪውን ሠራዊት፤ ሕዝ. 38፡5-6፣13 ዓለም አቀፍ ሠራዊት ያደርገዋል። ሕዝቅኤል 38-39 የፍጻሜ ዘመን መቼት አለው (ዝከ. 38:8,10,14,16,18; 39:11)። እነዚህ ምዕራፎች የአብዛኞቹ የዮሐንስ የብኪ የፍጻሜ ዘመን ጠቃሽ ምንጮች ናቸው። ነገሮች እየከፉ ይሄዳሉ (የአዲሱ ዘመን የምጥ ሕመም) የተሻለ እስኪሆንላቸው ድረስ (አዲሲቷ ኢየሩሳሌም)።

የሐንስ የብኪ ጽሑፎችን ወስዶ በአንደኛው ክፍለ-ዘመን የግሪክ-ሮማ ባህል መሠረት እንዴት ደግሞ እንደሠራው ተገንዘብ። ጎግ፣ ማጎግ፣ እና ባቢሎን ከሜሶፖታሚያ ወይም ከቱርክ ጋር ጠላትነት የላቸውም፣ ከሮም አንጂ።

◘ **"በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥"** ይህ በግልጽ ዓለም አቀፍ መሳትና ዐመጻ ነው (ዝከ. 7፡1)። ቁጥር "አራት" ተምሳሌታዊ ጠቀሜታ አለው፣ ሞላው ዓለምን በመወከል።

◘ **"እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል"** ይህ ሐረግ በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው ለአብርሃም ዘር ነው (ዘፍ. 15:5; 22:17; 32:12 እና ዕብ. 11:12)። ይህም ሌለኛው ምሳሌ ይሆናል፣ ክፉው ቃላትን የኮረዠበት፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚገልጸውን። ሆኖም፣ ከመጀመሪያው ሐረግ ከቁ. 9 የተነሣ፣ ይህ ሌለኛው መግለጫ ነው፣ እጅግ ትልቅ የሆነውን ሠራዊት የሚገልጽ።

**20:9** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው እማሬያዊ (በጥሬው) የሆነ ጦርነትን ነውን፣ በመጌዶን ሜዳ ላይ፣ አንደ ፍጻሜ ዘመን ሠራዊት ወደ ፍልስጥኤም ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የሚንቀሳቀስ? በርካታ ጠቃሾች አሉ፣ በዚህ ትዕይንት ላይ፣ በብኪ (መዝሙር 2; ሕዝቅኤል 38-39; ዳን. 9:24-27; ዘካ. 13-14)። ሆኖም፣ ኢየሩሳሌም ከመጊዶ ብዙ ማይል ርቀት ላይ ነች።

ራዕይ ላይ "ከተማ" ዘወትር (1) የሰዎች ማኅበረሰብ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ተደራጅቶ የሚሠራ፣ እንደ ባቢሎን ሰውኛ የሆነ እና (2) ከታሪክ አኳያ ሮምን የሚያመለክት፣ በዮሐንስ ጊዜ (ዝከ. 14:8; 16:19; 17:18; 18:2,10,16,18,19,21)። ሆኖም፣ የኢየሩሳሌም ከተማ የተጠቀሰችው 11:8 እና እዚህ ነው።

የአኪ ደራስያን ባጠቃላይ፣ እና ዮሐንስ በተለይ፣ የብኪን ምስያ ወስደው ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር እንዲዛመድ ሁለንተናዊ ያደርጉታል። ራዕይ ላይ ያለው ጉዳይ አይሁድ በተቃርኖ አሕዛብ አይደለም፣ ነገር ግን አማኝ በተቃርኖ የማያምን ነው። ይህም ተመሳሳይ የፍጻሜ ዘመን ጦርነት ነው እንደ 6:15-16; 11:18; 16:12,14,16; 19:19 (ትይዩነት)።

◘ **"እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው"** ይህ የሕዝ. 38፡22 እና 39፡6 ጠቃሽ ነው። ድሉ የእግዚአብሔር ነው!

**20:10 "ያሳታቸውም ዲያብሎስ ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ"** ይህ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ የተጣሉበት ነው 19፡20 ላይ። ይህም ሞትና ሲኦል የሚጣሉበት ነው 20፡14 ላይ፣ እንዲሁም በክርስቶስ ያላመኑ ሁሉ ይጣሉበታል 20፡15 ላይ። እሱም ከገሃነም (ሲኦል) ጋር ተመሳሳይ ነው፣ እናም ዘላለማዊ መለያየት ነው ከእግዚአብሔርና ከክርስቶስ ጋር ካለ ኅብረት (ማርቆስ 9፡43፣48)።

◘ **"ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።"** ይህ ከራዕ. 14:10-11 እና 19:5 ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው። የቋሚ መለያየት ጽንሰ-ሐሳብ ማቴ. 25፡46 ላይ ተጠቅሷል፣ ተመሳሳይ የሆነ ቃል (*aiÔnios*), ለመንግሥተ ሰማይ ጥቅም ላይ የዋለው፣ ከገሃነምም ውሏል።

አብዛኞቹ የእግዚአብሔር ፍርዶች የመዋጀት ዓላማ አላቸው፤ ያም በብኪም እና በአኪ እውነት ነው። ገሃነም የታወቀ የመዋጀት ዓላማ የለውም። እሱ የእግዚአብሔርን ተስፋ ይፈጽማል፣ ፍትሕና ጽድቅን ለመመለስ። ገሃነም የክፉ መለየት ነው፣ ከእግዚአብሔር መልካም ፍጥረት። እንደ ገሃነም አስፈሪው ለሰው ልጅ ነው፣ ለእግዚአብሔር ግን ከዚያ ይከፋል። ታላቁን ፍጡሩን፣ ሰውን፣ ምርጫ እንዲኖረው በመፍቀዱ (አንደኛውን የእግዚአብሔር መልክ ገጽታ፣ በሰው)፣ እግዚአብሔር ያውቃል በርካታ መቶኛዎች ግለኝነትንና ኃጢአትን እንደሚመርጡ። ገሃነም ክፍት፣ የሚደማ ቁስል ያለበት ነው፣ በእግዚአብሔር ልብ፣ እሱም ፈጽሞ የማይድን። ገሃነም አሳዛኝ ምሥጢራዊ አያዎ ነው፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅርና ፍትሕ!

### ራዕይ፡ 20፡11-15

**[11]ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም። [12]ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ። [13]ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፥ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ። [14]ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው። [15]በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።**

**20:11 "ታላቅና ነጭ ዙፋንን አየሁ፥"** ይህ የዳን. 7፡9 ጠቃሽ ነው። ታላቁ ነጭ ዙፋን የማቴ. 25፡31-46 ትይዩ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ይህ ለጠፉት ፍርድ ብቻ ከሆነ ከማቴዎስ 25 ጋር ትይዩ ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም እዚያ በጎች (የዳኑት) እና ፍየሎች (የጠፉት) አንድ ላይ በመቅረባቸው።

◘ **"በእርሱም ላይ የተቀመጠውን"** ይህ የዳን. 7፡9 ጠቃሽ ነው፣ በአኪ እግዚአብሔር ክርስቶስን ፈራጅ አድርጓል (ዮሐንስ 5:22,27; 9:39; ሐዋ. 10:42; 17:31; II ቆሮ. 5:10; II ጢሞ. 4:1 እና I ጴጥ. 4:5)። ሆኖም፣ በአንዳንድ ምንባቦች ክርስቶስ ብሏል፣ ልፍርድ እንዳልመጣ (ዮሐንስ 3:17-21; 12:47-48)። ክርስቶስ ለፍርድ አልመጣም፣ ግን ለማዳን እንጂ፣ ሆኖም፣ ሰዎች እሱን የማይቀበሉበት እውነት በገዛ ራሳቸው ላይ ፍርድን ያመጣል። ስለዚህ፣ ማነው በዚህ ዙፋን ላይ የተቀመጠው? ኢየሱስ ነውን? ይህ ሊሆን ይችላል በማቴ. 25:31-46 ምክንያት በተለይም በዮሐንስ 5:22 እና II ቆሮ. 5:10፣ ሆኖም፣ ብዙውን ጊዜ በአኪ፣ በተለይም በራዕይ መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አብ ነው በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው (ሮሜ. 14:10; ራዕ. 5:1,7,13; 6:16; 7:10,15; 19:4 እና 21:5)።

◘ **"ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ"** አንዳንዶች ይህንን የሚመለከቱት የርግማን መወገድ ነው፣ እሱም በሥጋዊ ፍጥረት ላይ የተቀመጠ፣ አዳምና ሔዋን ሲያምጹና ሲወድቁ (ዘፍ. 3:17-19 እና ሮሜ. 8:19-22)። ሌሎች ይህንን የሚመለከቱት ለአሁኑ የሥጋ ሥርዓት አጠቃላይ ጥፋት ዘይቤ ነው፣ IIጴጥ. 3:10,12 (ሐዋ. 3:21; ሮሜ. 8:21) ላይ እንደተመለከተው።

ይህ የብኪ ቋንቋ የሚያመለክተው፡ (1) የእግዚአብሔርን ወደ ፍጥረቱ መምጣት፣ መዝ. 114:3-6; ኢሳ. 13:10; 24:19-20,23; ኢዩኤል 2:10,30-31; 3:15; ዘካ. 14:6) ወይም (2) እግዚአብሔር ካሁን በኋላ ሁለቱን ዘላለማዊ ምስክሮቹን አለመፈለጉን ነው፣ ዘኍ. 35:30; ዘዳ. 17:6; 19:15። እሱ ይነግሣል!

ሰማይ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የእግዚአብሔርን ዙፋን አያመለክትም፣ግን ከምድር በላይ ያለውን ከባቢ አየር እንጂ፣ እንደ ዘፍ.1፡1።

**20:12 *"ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፥"*** የዚህ ታላቅ ወገን ስብስብ ርግጠኛ አይደለም፣ እና ዘወትር በአንዱ ቅድመ-ግምት ላይ የተመሠረተ ነው፣ እንደ አብዛኞቹ የራዕይ መጽሐፍ ዝርዝር ራዕዮች ትርጉሞች።

*"ታላላቆችንና ታናናሾችን"* የሚለው ሐረግ ሊያመለክት የሚችለው (1) አማኞች (መዝ. 115:13; ራዕ. 11:18; 19:5) ወይም (2) የማያምኑ (ዝከ. 13:16; 19:18)። በዚህ ዐውደ ጽሑፍ ከ"በጎች እና ፍየሎች" ጋር ትይዩ ነው፣ የማቴ. 25፡31-46 ወይም "በሰማይ ያሉ፣ እና በምድር፣ እና ከምድርም በታች" ፊሊ.. 2፡10-11።

▣ ***"መጻሕፍትም ተከፈቱ፤"*** ይህ የዳን. 7፡10 ጠቃሽ ነው። ሁለት መጻሕፍት ተጠቅሰዋል፡ የድርጊቶች ወይም የመታሰቢያ መጽሐፍ እና የሕይወት መጽሐፍ (ዝከ. 3:5; እና 13:8)። የሕይወት መጽሐፍ ዘጸ. 32:32-33; መዝ. 69:28; ኢሳ. 4:3; ዳን. 12:1; ሉቃስ 10:20; ፊሊ.. 4:3; ዕብ. 12:23; ራዕ. 3:5; 13:8; 17:8; 20:15; 21:27 ላይ ተገልጿል። የድርጊት ወይም የመታሰቢያ መጽሐፍ መዝ. 56:8; 139:16; ኢሳ. 65:6; ሚል. 3:16 እና ራዕ. 20:12-13 ላይ ተገልጿል። እነዚህ ለእግዚአብሔር ማስታወስ ዘይቤዎች ናቸው። እግዚአብሔር ከፍጡሩ ጋር ባግባቡ ይሠራል፣ ሰዎች ለድርጊታቸውና ለሐሳባቸው ኃላፊነት አለባቸው፣ እናም ለእግዚአብሔር ተጠያቂነት አለባቸው (ገላ. 6፡7)። አንድ ፍርድ ብቻ ነው ያለው።

▣ ***"ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ"*** ፍርድ የሚመሠረተው በሰው ልጆች የሕይወት ስልት ምርጫ ላይ ነው (ማቴ. 25:31-46)። የዘራነውን እናጭዳለን (ገላ. 6:7)። ሰዎች ሁሉ እንደየሥራቸው ፍርድን እንደሚያገኙ የሚለው ሥነ-መለኮታዊ ሐቅ ኤር. 17:10; ማቴ. 16:27; II ቆሮ. 5:10; ራዕ. 2:23; 20:13 ላይ ሊታይ ይችላል። ለተሟላ የማጣቀሻዎች ዝርዝር 2፡ 23 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**20:13 "ባሕርም... ሞትም... ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥"** ይህ ማለት ሙታን በሦስት የተለያየ ስፍራ ይቀመጣሉ ማለት አይደለም፤ ትይዩአዊው ዘይቤ የሚያስረግጠው ሙታን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መቆማቸውን ነው (ፊሊ.. 2፡10-11)።

**20:14 "ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ"** እነዚህ ቀደም ብሎ 6፡8 ላይ ተጠቅሰዋል። ሞት፣ የሰው ልጅ ታላቅ ጠላት (ዕብ. 2:14-15), ድል ተነሥቶ ተወግዷል (I ቆሮ. 15:26,54-55; II ጢሞ. 1:10; ራዕ. 1:18; 21:4)።

▣ ***"ሁለተኛው ሞት"*** መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሦስት ደረጃ ሞት ይናገራል፡

1. መንፈሳዊ ሞት፣ ዘፍጥረት 3; ኢሳ. 59:2; ሮሜ. 5:12-21; 7;10-11; ኤፌ. 2:1,5; ቆላ. 2:13; ያዕቆብ 1:15
2. ሥጋዊ ሞት፣ ዘፍጥረት 5
3. ዘላለማዊ ሞት፣ እሱም "ሁለተኛው ሞት" የሚባለው፣ ራዕ. 2:11; 20:6,14; 21:8, ይኸውም ገሃነምን የሚያመለክት

**20:15 *"ማንኛውም ስሙ"*** ይህ ዓረፍተ-ነገር አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ነው፣ እሱም የሚወስደው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ እንደሚኖሩ ነው (በዘይቤም በክርስቶስ ያላመኑት)።

▣ **"የሕይወት መጽሐፍ"** 13፡8 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መልካም፣ መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ አታኞች በዚህ ምዕራፍ ትርጓሜ ላይ ለምን ላይስማሙ ቻሉ?
2. ይህ መጽሐፍ በተምሳሌታዊ ቋንቋ ከተጻፈ (አፖካሊፕቲካዊ ዘውግ)፣ ለምን በርካታ ሰዎች ይሄንን ምዕራፍ እጅግ በእማሬያዊ (ጥሬ) እና በታሪካዊነት ይወስዱታል?
3. ሰይጣን ለምን ለጥቂት ጊዜ ታሰረ? ቁ. 3 እና 8 ላይ ያሉት አሕዛብ ከየት መጡ?
4. ቁ. 4 ላይ ምን ያህል ወገኖች ተካተዋል፣ ይህስ ጠቀሜታው ምንድነው?
5. በዚህ ምዕራፍ ላይ ሁለት ደረጃ ያለው ትንሣኤ ማግኘት ለምን እጅግ ያስደንቃል?
6. ከሞት የተነሡት ቅዱሳን ከሥጋዊ አሕዛብ ጋር እንዴት አብረው ሊኖሩ ይችላሉ?
7. በታላቂ ነጭ ዙፋን ፍርድ ላይ የሚካተቱት እነማናቸው፣ ቁ. 11-15?

# ራዕይ 21-22
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| ዩቢኤስ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር | ሁሉም ነገሮች አዲስ ሆኑ | የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ራዕይ | አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር | ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም |
| | | (21፡1-22፡5) | | |
| 21:1-4 | 21:1-8 | 21:1-4 | 21:1-4 | 21:1-4 |
| 21:5-8 | | 21:5-8 | 21:5-8 | 21:5-8 |
| አዲሲቱ ኢየሩሳሌም | አዲሲቱ ኢየሩሳሌም | የከተማዋ ልኬት | አዲሲቱ ኢየሩሳሌም | መሲሐዊዋ ኢየሩሳሌም |
| 21:9-14 | 21:9-21 | 21:9-14 | 21:9-21 | 21:9-14 |
| 21:15-21 | የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ክብር | 21:15-21 | | 21:15-22:2 |
| | 21:22 | የሕይወት ወንዝና ዛፍ | | |
| 21:22-22:5 | የሕይወት ወንዝ | 21:22-22:5 | 21:22-22:3ሀ | |
| | 22፡1-5 | | | |
| | ዘመኑ ቅርብ ነው | | 22፡3ለ-5 | 22፡3-5 |
| የክርስቶስ ምጽአት | 22:6-11 | ተቀጥላ | የኢየሱስ ምጽአት | |
| 22:6-7 | | 22:6 | 22:6 | 22:6-7 |
| | ኢየሱስ ለአብያተ ክርስቲያናት | 22:7 | 22:7 | |
| 22:8-11 | መሰከረ | 22:8-9 | 22:8-11 | 22:8-9 |
| | 22:12-17 | 22:10-11 | | 22:10-15 |
| 22:12-13 | | 22:12-13 | 22:12-13 | |
| 22:14-15 | | 22:14-15 | 22:14-15 | ተቀጥላ |
| 22:16-17 | | 22:16-17 | 22:16 | 22:16 |
| | | | 22:17ሀ | 22:17 |
| | | | 22:17ለ | |
| | ማስጠንቀቂያ | | 22:17c | |
| | 22:18-19 | | ማጠቃለያ | |
| 22:18-19 | ፈጥኜ እመጣለሁ | 22:18-19 | 22:18-19 | 22:18-19 |
| | 22:20-21 | | | |
| 22:20 | | 22:20 | 22:20 | 22:20 |
| | | 22:20ለ | 22:20ለ | 22:20ለ |
| 22:21 | | 22:21 | 22:21 | 22:21 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ v ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ vii)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

**ጽሑፋዊ ይዘት**

ሀ. ራዕይ 20-22 ሰባተኛውን ጽሑፋዊ ምድብ ያዋቅራል። ራዕይ 21-22 የእግዚአብሔርን ድርጊት በሰው ታሪክ ላይ ይደመድማል፣ እንዲሁም ዘላለማዊውን መንግሥት ያስገኛል (ዳን. 7:13-14,27; 1 ቆሮ. 15:27-28)። ራዕይ 22:6-21 የሙሉው መጽሐፍ ማጠቃለያ ነው።

ለ. ከሞላ ጎደል በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ ያሉት ነገሮች የ (1) ዘፍጥረት 1-3፤ (2) መዝሙር 110፤ ወይም (3) በይነ-ኪዳናዊ የአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፍ ጠቃሽ ናቸው።

ሐ. በርካታ ውይይቶች ተካሂደዋል፣ ስለነዚህ ያልተለመዱ ነገሮች፣ በዚህ የመጨረሻ ክፍል ያሉት።

1. "የአሕዛብ" መጠቀስ – 21:14; 22:2
2. "የምድር ነገሥታት" መጠቀስ – 21:24,26
3. "ከከተማው ውጭ ያለው ቆሻሻ" መጠቀስ – 21:27; 22:15

እነዚህን ነገሮች ለማካተት በርካታ ታሳቢ ምክንያቶች ይኖራሉ፡

1. ዮሐንስ የብኪ ነቢያትን ጠቅሷል። በወንጌላት እንዳሉ ምሳሌዎች፣ ተርጓሚዎች ዝርዝሮቹን በጥሬው እንዲተረጉሟቸው አይደለም፣ ግን ዋነኞቹን አጽንዖቶች እንዲለዩአቸው እንጂ።
2. የዮሐንስ ዓላማ በዳኑትና በጠፉት መካከል ያለውን የመዳረሻ ልዩነት ማሳየት ነው።
3. በዚህ ክፍል የተጠቀሱት "አሕዛብ" ለአጠቃላይ ዘራዊ ሐሳብ ጥቅም ላይ ይውላሉ፣ እንደ "የእግዚአብሔር ሕዝብ" 5:9; 7:9; 21:14 እና 22:5።
4. በእነዚህ ነገሮች ምክንያት አንዳንዶች፣ የዳኑ አይሁድን በከተማ ውስጥ እንዲሁም የዳኑ አሕዛብን ከከተማ ውጭ ያያሉ። ነገር ግን፣ በገላትያ 3፡29 እና ኤፌሶን 2፡11-3፡13 ምክንያት፣ ይህ ሁነኛ ሥነ-መለኮታዊ ሊሆን አይችልም።
5. ተደጋጋሚነት በምዕራፍ 17-19 እና 20-22 መካከል ያለ ይመስለኛል። ይህም ተደጋጋሚውን ጭብጥ በዚህ ክፍል ሁሉ ያስረዳል።

መ. በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ አንድ ተጨማሪ ተለጣጣቂ "ሰባት" ይገኛል። እነዚህም ከእንግዲህ በኋላ የማይኖሩት ናቸው

1. ባሕር — 21፡1
2. ሞት — 21፡4
3. ኀዘን — 21፡4
4. ልቅሶ — 21፡4
5. ሕመም — 21፡4
6. ጨለማ — 21፡25
7. ርግማን — 22፡3

ሠ. ፍርዶቹ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር እንደሚያያዙ፣ ተውኔታዊ በሆነ መልኩ በሦስቱ ራዕዮች ይታያሉ (ማኅተሞች፣ መለከቶች፣ እና ጽዋዎች)፣ ሰማይም በተውኔታዊ መልኩ በሦስት የብኪ ዘይቤዎች ሊታይ ይችላል፡

1. የማደሪያው ድንኳን (መቅደስ)፣ 21፡1-8
2. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ 21፡9-26
3. የዔድን ገነት፣ 22፡1-5

ይህም ደግሞ ስለ መቅድሙ ልክ ይሆናል (1፡1-8)፣ እሱም አጽንዖት የሚሰጠው

1. ለክርስቶስ መመለስ ድንገተኛነት
2. ለእግዚአብሔር ቃል የታመነ መሆን
3. ለእግዚአብሔር ሕዝብ የቅድስና አስፈላጊነት

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

***ራዕይ፡ 21፡1-4***

***1አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። 2ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። 3ታላቅም ድምፅ ከሰማይ። እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ 4እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።***

**21፡1 "አየሁም"** የተወሰነ የጊዜ ቆይታ አለ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ በትርጉማችሁ ይወሰናል፣ የምዕራፍ 20ው "ሺህ ዓመት"።

▣ **"አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር"** ይህ የግሪክ ቃል "አዲስ" *kainos*, አጽንዖት የሚሰጠው ለጥራት ነው እንጂ ለጊዜ ቅደም ተከተል አይደለም (ዝክ. 2:17; 3:12; 5:9; 14:3; 21:1,2,5)። ይህ የብኪ ጭብጥ ነበር፣ አዲስ የተፈጠረችው ምድር (ኢሳ. 11:6-9; 65:17; 66:22; ደግሞም ሮሜ. 8:18-25; II ጴጥ.3:10,12 ተመልከት)። አማኞች ሁሉ የአዲሱ መንግሥት ዜጎች ናቸው (ፊሊ. 3:20; ኤፌ. 2:19; ዕብ. 12:23) እና ይህ አዲስ ፍጥረት ይካፈላሉ (ዝክ. II ቆሮ. 5:17; ገላ. 6:15; ኤፌ. 4:24)። ትይዩ ሥነ-መለኮታዊ ጥንሰ-ሐሳብ ይህ ሊሆን ይችላል "የእግዚአብሔር ከተማ በሰው እጅ ያልተሠራች" ዕብ. 11:10,16; 12:22; 13:14።

አዲሱ ፍጥረት እንደ መነሻው ፍጥረት ይሆናል። ሰማይ የተመለሰው የዔድን ገነት ይሆናል። እግዚአብሔር፣ የሰው ልጅ፣ እንስሳት፣ እና ሁሉም የተፈጥሮ ፍጥረታት ኅብረት ይኖራቸዋል፣ እንደገናም ይደሰታሉ! መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው በእግዚአብሔር፣ በሰው ልጅ፣ እና በእንስሳት ነው፣ በገነት ውስጥ ፍጹም በሆነ ኅብረት (ዘፍጥረት 1-2)። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያበቃው በእግዚአብሔር እና በሰው ልጅ በገነት መቼት ነው (ራዕይ 21-22) እና በትንቢታዊ አንድምታ፣ እንስሳትም (ኢሳ. 11:6-8; 65:25)። አማኞች ወደ ሰማይ አይሄዱም፤ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ትወርዳለች (ራዕ. 21፡2) እናም አዲስ ወደ ተፈጠረችው እና ወደ ነጻችው ምድር ትመጣለች። እግዚአብሔርና ሰዎች በድጋሚ አንድ ላይ ይሆናሉ (ዘፍ. 3:15; ኢሳ. 7:14; 8:8,10; ራዕ. 21:3)።

▣ **"ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥"** የተመለሰ ፍጥረት ይኖራል (ሐዋ. 3:21; ሮሜ. 8:21; ቆላ. 1:20), የኃጢአት ተጽዕኖ አይኖርም (II ባሮክ 37:6; II ጴጥ. 3:10-12; ራዕ. 20:11)።

▣ **"ባሕርም ወደ ፊት የለም"** በርካታ የዚህ ሐረግ ትርጓሜዎች አሉ (4፡6 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት)፡

1. 4፡6 ላይ ባሕር በመጠቀሱ ምክንያት፣ እንደ እግዚአብሔር ቅድስና መግለጫ መንገድ፣ ይኸውም እሱን ከኃጢአተኛው የሰው ልጅ የሚለየው፣ አንዳንዶች እዚህ መቅረቱን የሚመለከቱት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ፍጹም ኅብረት መመለስ ነው
2. ራዕ. 20፡13 ላይ ባሕር የሚመስለው ከሦስቱ አንደኛው የሙታን ማቆያ ስፍራ ነው፣ ይኸውም፣ ሙታን ሁሉ ከሁለቱ ዘላለማዊ መዳረሻዎች በአንደኛው እንደሚሆኑ መግለጫ መንገድ ነው
3. የመጀመሪያው አውሬ ራዕ. 13፡1 ላይ ከባሕር በመውጣቱ ምክንያት፣ ባሕር ክፉ ሰዎችን አመልካች ጠቃሽ ይሆናል ኢሳ. 57፡20፣ ይኸውም፣ ክፉዎች ከእንግዲህ በኋላ አለመኖራቸውን ማሳያ ይሆናል
4. ራዕ. 17፡15 ከኢሳ. 17፡12-13 በመጠቀሱ ምክንያት፣ እዚያም ውኃ ለሰዎች ስለተመሰለ ብዙዎች የሚያስረግጡት እሱ የሚያመለክተው ክፉ ሕዝቦችን ነው፣ እንደ መዝሙር 2። እኔ ቁ. 1ን በተሻለ እመርጣለሁ።

**21፡2 "ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን አየሁ"** ኢየሩሳሌም በፍልስጥኤም የምትጠራው "ቅድስቲቷ ከተማ" ተብላ ነው ኢሳ. 52:1 (ኢሳ. 48:2; 64:10; ዳን. 9:24; ነህ. 11:1)። ይህች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በመጀመሪያ የተጠቀሰችው 3:12 ላይ ነው፣ እንዲሁም ዕብ. 11:10; 12:22; እና 13:14 ላይ ተጠቅሳለች። ይህም የሚያመለክተው፣ ዮሐንስ እንዴት አድርጎ የብኪ ትንቢቶችን፣ ቃላትን፣ መጠሪያዎችን፣ እና ተስፋዎችን እንደወሰደና ለአዲሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዳዋለው ነው። ይህች ከተማ በፍልስጥኤም ያለችው የብሉይ ኪዳኗ ኢየሩሳሌም አይደለችም፣ አንዳንድ ሚሊኒየማውያን እንደሚያስቡት፣ ነገር ግን የአዲሱ ኪዳን ሰማያዊ ኢየሩሳሌም እንጂ።

▣ **"ከሰማይ ዘንድ ስትወርድ"** ሁለት መውረዶች አይኖሩም፣ አንደኛው ቁ. 2 ላይ ሌለኛው ቁ. 10 ላይ። አፖካሊፕቲካዊ ቋንቋ እጅግ ተለዋዋጭ ነው፣ እናም በቅደም ተከተል፣ በሎጂካዊ፣ ወይም በአማሬያዊ (በጥሬው) መዋቀር አይችልም።

▣ **"ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥"** ይህ የኢሳ. 61:10 (ዝክ. 19:7) ጠቃሽ ነው። በእነዚህ የመጨረሻ ምዕራፎች በርካታ ዘይቤዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመግለጽ (1) ሙሽራ (ዝክ. 19:7; 21:2); (2) የሰርግ ታዳሚዎች (ዝክ. 19:9); እና (3) ከተማ (ዝክ. 21:22,9; 22:2)።

የብኪ የያህዌ ዘይቤ (በተለይ ሆሴዕ 1-3) እንደ ባል እና እስራኤል እንደ ሙሽራ፣ ቤተ-ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ ሙሽራ የመመሰሏ ዳራ ነው (ኤፌ. 5፡21-31)።

**21፡3 "እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው"** ይህ የግሪክ ሐረግ የሚደግመው የብኪን ተስፋ ነው፣ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር እንደሚያድር፣ በሦስት የተለያዩ መንገዶች፡

1. እሱ ለማደሪያው ድንኳን ጠቃሽ ነው፣ የያህዌ መገኘት ተምሳሌት
2. "በእነርሱ መካከል ያድራል" ማለት "አማኑኤል" የሚለው ቃል ነው፣ የኢሳ. 7፡14 (ዮሐንስ 1፡14)
3. "እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ" የኪዳን ቃል ነው፤ አሁን ሁሉም አማኝ ሕዝቦች (ዮሐንስ 10፡16) እግዚአብሔር የመረጣቸው ሕዝቦች ናቸው (ሌዋ. 26:11-12; ሕዝ. 37:23,27)።

**21፡4 "እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል"** ይህ የኢሳ. 25:8 (ማቴ. 5:4; 7:17) ጠቃሽ ነው። አዲሱ ዘመን የደስታ፣ የሰላም፣ የሙላት፣ እና የምስጋና ይሆናል!

▣ **"ከእንግዲህ ወዲያ ሞት አይሆንም"** ይህ የመጨረሻው ጠላት (ራዕ. 20:14) ይደመሰሳል (1 ቆሮ. 15:26)። አማኞች የራሳቸው አዲስ አካል ይኖራቸዋል፣ እንደ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል (1 ቆሮ. 15:50-57; II ቆሮ. 3:18; 1 ተሰ. 4:15-16; 1 ዮሐንስ 3:2)።

▣ ***"ከእንግዲህ ወዲያ ኀዘን አይሆንም፣ ወይም ልቅሶ፣ ወይም ሥቃይ"*** ይህ የኢሳ. 65፡19 ጠቃሽ ነው፣ እሱም ደግሞ ኢሳ. 35፡10ን ያንጸባርቃል።

▣ ***"የቀደመው ሥርዓት አልፏልና"*** የመጀመሪያው የፍጥረት ሥርዓት በውድቀት ምክንያት ተበላሽቶአል (ዘፍ. 3; 6:5,1-12,13), ነገር ግን አዲሱ ሥርዓት በኃጢአት የማይጎዳ ይሆናል (ዕብ. 12፡27-28)።

***ራዕይ፡ 21፡5-8***

**[5]በዙፋንም የተቀመጠው። እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም። እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ። [6]አለኝም። ተፈጽሞአል። አልፋና *ዖሜጋ*፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። [7]ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል። [8]ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞችም የአስማተኛዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።**

**21፡5 "በዙፋንም የተቀመጠው። አለ።"** እግዚአብሔር ራዕይ ላይ ብዙ ጊዜ ተናግሯል (ዝከ. 1:8 እና እንዲሁም 16:1,17)። ሆን ተብሎ የተደረገ አሻሚነት የተደረገ ይመስላል፣ ማን በዙፋኑ ላይ እንደሚቀመጥ፣ ያህዌ ወይስ መሲሕ (ዝከ. 22፡3)። 20፡11 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት። የመጀመሪያው ፍጥረት በእግዚአብሔር ወደ ሕላዌ እንደመጣ ሁሉ (ማለትም፣ አብ በወልድ በኩል) በተነገረ ቃል (ዘፍ. 1:3,6,9,14,20,24; መዝ. 33:6,9), እንዲሁ ደግሞ አዲሱ ፍጥረት ይሆናል።

▣ ***"ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ"*** ይህ የኢሳይያስ 60-66 ተስፋ ነው። ይህም አዲሱን የመንፈስ ዘመን ያመለክታል፣ የመሲሑ ዘመን፣ የጽድቅ ዘመን፣ ኢየሱስ እንደ መጀመሪያ ምጽአቱ የመረቀው፣ ብሎም በዳግም ምጽአቱ የሚቀዳጀው። ይህም የርግጠኝነት ዘይቤ ነው፣ የእግዚአብሔር ፍቃድ ወደ እውነታ እንደሚመጣ (ዝከ. 1:19; 14:13; 17:17; 19:9)።

▣ ***"እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና"*** ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው (1) ኢየሱስን፣ ዝከ. 1:5; 3:7,14; 19:11; (2) የኢየሱስን የከታዮች፣ ዝከ. 17:14; እና (3) የእግዚአብሔርን ቃል ዝከ. 19:9; 21:5; 22:6 ለመግለጽ ነው። እግዚአብሔር ዘወትር እንደ "ጻድቅና እውነተኛ" ነው የሚገለጸው (ዝከ. 15:3; 16:7; 19:2)። የዕብራይስጡ አስተሳሰብ በዚህ የግሪክ ሐረግ ላይ አንድምታው ታማኝነት ነው።

**21፡6 *"ተፈጽሞአል"*** ይህ የተጠናቀቀ የድርጊት አመላካች ነው። ይህም ከእግዚአብሔር ተስፋ ርግጠኝነት ጋር ይያያዛል፣ ከሁለቱም፣ ቁጣ ለማያምኑት እና ማዳን ለሚያምኑት በተመለከተ (ዝከ. 6:11; 10:7; 16:17), ወይም የእግዚአብሔር ቃል ዳርቻዎች (ዝከ. 1:1,3; 3:11; 10:6; 12:12; 22:7,10)።

▣ ***"አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ"*** ይህ ስለ እግዚአብሔር ጥቅም ላይ የዋለ ነው ኢሳ. 44፡6 እና ራዕ. 1፡8 ላይ፤ ሆኖም፣ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው፣ ይህ ሐረግ፣ ምንም እንኳ መጠሪያው ለአብ ቢሆንም፣ እሱ ደግሞ ለመሲሑም ጥቅም ላይ ይውላል፣ 1፡17 እና 22፡13። እሱም ሌለኛው ምሳሌ ነው፣ ለአኪ ደራስያን የእግዚአብሔርን መጠርያ ለወልድ መጠቀማቸው።

በርካታ አካታች ዓይነት ሐረጎች አሉ፣ እነርሱም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ፣ የተለየ ሕላዌ የሚገልጹ፡

1. *"መጀመሪያውና መጨረሻው፣"* ኢሳ. 41:4; 44:6; 48:12; ራዕ. 1:17; 2:8; 22:13
2. *"መጀመሪያውና መጨረሻው፣"* ዝከ. 21:6; 22:13; እና ኪጀት 1:8
3. *"ያለው የነበረውና የሚመጣው,"* ዝከ. 1:4,8; 4:8

እነዚህ ሁሉ የሚዛመዱት ከእግዚአብሔር የኪዳን ስም ጋር ነው፣ ያህዌ፣ እሱም የዕብራይስጡ ቃል "መሆን" መገኛ ቅርጽ (ዘጸ. 3:14; ኢሳ. 43:10,13; 46:41; መዝ. 90:2; 93:2)።

▣ ***"ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ።"*** የብኪ ጠቃሹ ኢሳይያስ 55 ነው። ግብዣው ለሁሉም ነው፣ እናም ፍጹም ነጻ ነው (ሮሜ. 3:24; 6:23; ኤፌ. 2:8)! እንዴት ያለው ታላቅ ግብዣ ነው፣ ከእግዚአብሔር ከራሱ የተገኘ ይቅርታ። የሰው ልጆች መዳን ዘወትር ማዕከላዊ ነው፣ በእግዚአብሔር ልብና ሐሳብ (ዝከ. 9፡20-21; 14:6-7; 16:9,11; 22:17)።

በብኪ የውኃ ምንጭ ዘወትር የሚያያዘው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መንፈሳዊ ፍላጎቶች ከሚሰጠው ጋር ነው (መዝ. 36:9; ኢሳ. 12:3; 44:3; 49:10; ኤር. 2:13; 17:13; ደግሞም ዮሐንስ 4:10)።

**21፡7 *"ድል የሚነሣ"*** ይህ የአሁን የድርጊት አንቀጽ ነው፣ ይኸውም ቀጣይነት ያለው የጽናት ዶክትሪን ማጣቀሻን የሚጠይቅ፣ ጽኑ በሆነ የስደት ጊዜ መሐል። ይህ ሐረግ በመልእክቶቹ ሁሉ ላይ ይገኛል፣ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት (ዝከ. 2:7,11,17,26; 3:3,5,12,21), ይኸውም የራዕይን የመክፈቻ ምዕራፎች ከመደምደሚያው ጋር የሚያያይዝ። ልዩ ርዕስ ጽናት 2፡2 ላይ ተመልከት።

▣ ***"ይህን ይወርሳል"*** የውርስ ሽልማት ቁ. 7 ላይ (1 ጴጥ. 1:4,5; ሮሜ. 8:17) እና ቁ. 8 ላይ ያሉት ማስጠንቀቂያዎች፣ ከጀርባ ያለው ዋነኛው ክህደት፣ ይኸውም በስደት ዘመን የሚሆነው ተቃርኖ ናቸው። ተለጣጣቂ ክፉ ከሐዲዎች (ዝከ. ቁ. 8)፣ 1 ቆሮ. 6:9-10 ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይ ነው።

▣ **“አምላከም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል”** እነዚህ የኪዳን ሐረጎች ናቸው (ዝከ. ቁ. 3) በብኪ እጅግ የተዘወተሩ (ዘዳ. 6:7; 29:45,46; ሌዋ. 26:11-12; II ሳሙ. 7:14; መዝ. 89:26-27; ኤር. 7:23; 11:4; 30:22; 33:38; ሕዝ. 11:20; 14:11; 34:30; 36:28; ሆሴ. 2:23; ዘካ. 8:8; 13:9) እና ደግሞ በአኪ ጥቅም ላይ የዋለው (II ቆሮ. 6:16,18)።

የኪዳን ጽንሰ-ሐሳብ የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብራዊ ጭብጥ ነው። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ተነጥሏል (ኢሳ. 53:6; ሮሜ. 3:9-18,23)። የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ሊያገኝ አይችልም። እግዚአብሔር ለእኛ ይደርስልናል፤ እግዚአብሔር ይይዘናል! የእርሱ የዳግም ኅብረት ግብዣ አንደኛው ኪዳን ነው። እሱ መነሻውን ያደርጋል (ኤር. 31:3; ዮሐንስ 6:44,65); አጀንዳውን ያሰናዳል፣ የሰው ልጅ ግን በተወሰኑ መንገዶች ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። እነዚህ መንገዶች በይዘት ይለያያሉ (አዳም/ሔዋን፣ የተከለከለው ዛፍ፤ ኖኅ፣ መርከብ፤ አብርሃም፣ ምድር፣ ልጅ፤ ሙሴ፣ የሕግ ቃላት)፣ የአቀባበሉ ቅርጽ ግን፣ እምነት በታማኙ እግዚአብሔር ላይ፣ እንዳለ ይቆያል (ሮሜ 4)። ብሉይ ኪዳን መስፈርቶች አሉት፤ አዲሱም እንዲሁ (ማርቆስ 1:15; ሐዋ. 3:16,19; 20:21)። የሰውልጅ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል በመነሻውም ሆነ በቀጣይነት፣ በእምነት፣ በንስሐ፣ በታዛዥነት፣ በአገልግሎት፣ በአምልኮ፣ እና በጽናት።

ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ 2፡18 ላይ ተመልከት።

**21፡8** እነዚህን ተለጣጣቂ ኃጢአቶች ማግኘት ያልተለመደ ነው፣ ፍርድ ቀደም ብሎ ከተሰጠ በኋላ፣ እናም ኃጢአተኞች ተወግደዋል ተብሎ ከታሰበ በኋላ (በኢየሱስ ድል በዳግም ምጽአቱ፣ ዝከ. 19፡5-21 እና ነጩ ዙፋን፣ ዝከ. 20፡11-15)። ይህ ማለት አንዳንድ አማኞች እነዚህን ኃጢአቶት አይፈጽሙም ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ሕይወታቸው በእነዚህ ኃጢአቶች ባሕርይ አያደርግም እንጂ (1 ዮሐንስ 3፡6፣9)። ይህም ሊሆን የሚችለው ጽሑፋዊ ዘዴ ነው፣ ዘላለማዊውን ልዩነት ለማሳየት፣ በዳኑትና በጠፉት መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት ወይም የአፖካሊፕቲካዊ ድራማ አንደኛው ገጽታ (ለአጽንዖት የተደገመ)።

▣ **“...በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።”** የእሳት ባሕር የሁለተኛው ሞት ተመሳሳይ መሆኑ ግልጽ ነው፣ ወይም የእኛ የገሃነም ጽንሰ-ሐሳብ፣ ኢየሱስ ገሃነም ብሎ የጠራው (የግሪክ ቃል፣ ራዕይ ላይ የማይገኝ)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው? 1፡18 ላይ።

**ራዕይ፡ 21፡9-14**

**9ሰባቱም ኋለኛዎች መቅሠፍቶች የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ። ወደዚህ ና፥**
**የበጉንም ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ ብሎ ተናገረኝ። 10-11በመንፈስም ወደ ታላቅና ወደ ረጅም ተራራ ወሰደኝ፥ የእግዚአብሔርም**
**ክብር ያለባትን ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ፤ ብርሃንዋም እጅግ እንደ ከበረ**
**ድንጋይ እንደ ኢያሰጲድ ድንጋይ ሆኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበረ፤ 12ታላቅና ረጅም ቅጥር ነበራት፥ አሥራ ሁለትም ደጆች ነበሩአት**
**በደጆቹም አሥራ ሁለት መላእክት ቆሙ፥ የአሥራ ሁለቱም የእስራኤል ልጆች ነገዶች ስሞች ተጽፈውባቸው ነበር። 13በምሥራቅ ሦስት**
**ደጆች፥ በሰሜንም ሦስት ደጆች፥ በደቡብም ሦስት ደጆች፥ በምዕራብም ሦስት ደጆች ነበሩ። 14ለከተማይቱም ቅጥር አሥራ ሁለት**
**መሠረቶች ነበሩአት፥ በእነርሱም ውስጥ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽፈው ነበር።**

**21፡9 “ከሰባቱ መላእክት አንዱ”** ይህ ቀጥተኛ የመልአኩ ገለጻ ነው 15:1,6-8; 16:1; እና 17:1 እሱም ሰባቱን ጽዋዎች ያፈሰሰ። በራቢያዊ ይሁዲነት ወግ ሰባት የመገኘቱ-መላእክት አሉ፣ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ። እዚህ ለእያንዳንዱ መቅሠፍት አንድ መልአክ አለ።

**21፡10 “በመንፈስም ወሰደኝ”** ይህ ጽሑፋዊ ዘዴ ነው፣ የተለያዩ ራዕዮችን ለማሳየት (ዝከ. 1:10; 4:2; 17:3; 21:10)።

▣ **“ወደ ታላቅና ወደ ረጅም ተራራ”** ብዙዎች የሚያምኑት ይህ ቀጥተኛ ተቃራኒ እንደሆነ ነው፣ በሜዳ ላይ ለነበረችው ታላቂቱ ጋለሞታ። ሆኖም፣ ዮሐንስ በርካታ የብኪ ምንባቦችን ጠቅሷል፣ ስለዚህ እዚህ ምሥጢራዊውን የሰሜን ተራራ መጥቀሱ ይሆናል፣ እግዚአብሔር የሚኖርበትን (ሕዝ. 40:2; ኢሳ. 2:2; 14:13; ሚኪ. 4:1; I ሔኖክ 18:8; 25:3)። እሱም የሰይጣንን ፈተና መጥቀሱ ይሆናል፣ የኢየሱስን፣ ማቴ. 4፡8።

▣ **“ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ስትወርድ አሳየኝ”** ይህች ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ነች፣ የእግዚአብሔር መገኘት ዘይቤ (ዝከ. ቁ. 2)። ምድራዊቷ ኃጢአተኛዋ ኢየሩሳሌም 11፡1-13 ላይ ተብራርታለች። የዳዊት ዋና ከተማ ወደ ፍጻሜ ዘመን የሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ማደሪያ ሆናለች (ዮሐንስ 14፡2-3)።

**21፡11 “ብርሃንዋም እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ እንደ ኢያሰጲድ ድንጋይ ሆኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበረ፤”** ከተማይቱ (ዝከ. ቁ. 11-27) የተገለጸችው እጅግ ውብ በሆነ፣ አካላዊ፣ እና ሞራላዊ ቃላት ነው። እንደ ሁሉም የራዕይ መጽሐፍ ይህ ምዕራፍ ተምሳሌታዊ ነው። የሰዎች ኃጢአተኛ፣ ውስን አስተሳሰብ እንዲያው በቀላሉ በእግዚአብሔር መገኘት የሚኖረውን የመዳረሻውን ደስታ እና ክብር ሊገነዘበው አይችልም (1 ቆሮ. 2፡9)። እማሬያዊ (ጥሬ) ጌጣጌጦች እና አስደናቂ ጥንታዊ ከተማ የተሻሉ ዘይቤዎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን እነርሱ የመዳረሻ እውነታ አይደሉም! ሰማይ በርግጥ ሁለቱም፣ አካል (ኢየሱስ)፣ እና ስፍራ (ኅብረት የሚደረግበት፣ በሦስትነት አንድ ከሆነው አምላክ ጋር) ነው።

**21፡12 "አሥራ ሁለትም ደጆች ነበሩአት በደጆቹም አሥራ ሁለት መላእክት"** ይህ የሕዝ. 48፡31-34 ጠቃሽ ነው። ቁጥር "አስራ ሁለት" በተደጋጋሚ ይከሰታል፣ ይህንን ምዕራፍ ለማስታወስ እንዲሁም የምዕራፍ 22 የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቁጥሮች። እሱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቁጥር ተምሳሌት ነው፣ ለድርጅት (አስራ ሁለት ወራት፣ አስራ ሁለት ነገዶች፣ ወይም አስራ ሁለት ሐዋርያት) ወይም የእግዚአብሔር ሕዝብ። ልዩ ርዕስ፡ ቁጥር አስራ ሁለት 7፡4 ላይ ተመልከት።

▣ **"የአሥራ ሁለቱም የእስራኤል ልጆች ነገዶች ስሞች ተጽፈውባቸው ነበር።"** *ራዕ.* 7፡5-8 ላይ ያለው የአስራ ሁለቱ ነገዶች ዝርዝር በመጠኑ ተለውጧል፣ ተምሳሌታዊ ተፈጥሯቸውን ለማሳየት። እዚህ፣ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው የብኪ የእግዚአብሔር ሕዝቦች፣ ቁ. 12 ላይ የተገለጹት፣ ከአኪ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር መተባበራቸውን ነው፣ ቁ. 14 ላይ የመሠረት ድንጋዩ ጋ የተጠቀሱት። አንድ ብቻ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው የሚኖረው፣ ነገር ግን ይህ ምሥጢር ጠርቶ አልተገለጸም፣ እስከ ወንጌል ድረስ (ኤፌ. 2:11-3:13)።

**21፡14 "ለከተማይቱም ቅጥር አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩአት፥ በእነርሱም ውስጥ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽፈው ነበር።"** እነዚህ ሁሉ ዘይቤዎች የተጠቀሱት ከሕዝቅኤል የፍጻሜ ዘመን መቅደስ ላይ ነው (ሕዝቅኤል 40-48)።

ብዙ አታቾች የሚያስረግጡት ይህ ቁጥር የሚያሳየው ደራሲው ሐዋርያው ዮሐንስ እንዳልነበረ ነው። ሆኖም፣ ጳውሎስ ተመሳሳይ ሐረግ ኤፌ. 2፡20 ላይ ተጠቅሟል።

---

***ራዕይ፡ 21፡15-21***

**[15]የተናገረኝም ከተማይቱንና ደጆችዋን ቅጥርዋንም ይለካ ዘንድ የወርቅ ዘንግ ነበረው። [16]ከተማይቱም አራት ማዕዘን ነበራት፥ ርዝመትዋም እንደ ስፋትዋ ልክ ነበረ። ከተማይቱንም በዘንግ ለካት አሥራ ሁለትም ሺህ ምዕራፍ ሆነች፤ ርዝመትዋና ስፋትዋ ከፍታዋም ትክክል ነው። [17]ቅጥርዋንም ለካ፥ መቶ አርባ አራት ክንድ በሰው ልክ፥ እርሱም በመልአክ ልክ። [18]ቅጥርዋም ከኢያሰጲድ የተሠራ ነበረ፥ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች። [19]የከተማይቱም ቅጥር መሠረት በከበረ ድንጋይ ሁሉ ተጌጦ ነበር፤ ፊተኛው መሠረት ኢያሰጲድ፥ ሁለተኛው ሰንፔር፥ ሦስተኛው ኬልቄዶን፥ አራተኛው መረግድ፥ [20]አምስተኛው ሰርዶንክስ፥ ስድስተኛው ሰርድዮን፥ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፥ ስምንተኛው ቢረሌ፥ ዘጠነኛው ወራውሬ፥ አሥረኛው ክርስጵራስስ፥ አሥራ አንደኛው ያክንት፥ አሥራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበረ። [21]አሥራ ሁለቱም ደጆች አሥራ ሁለት ዕንቆች ነበሩ፤ እየአንዳንዱ ደጅ ከአንድ ዕንቍ የተሠራ ነበረ። የከተማይቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረ።**

---

**21፡15 "የተናገረኝም ከተማይቱንና ደጆችዋን ቅጥርዋንም ይለካ ዘንድ የወርቅ ዘንግ ነበረው።"** ልኬት ድሮ ጊዜ ይወሰድ የነበረው የእግዚአብሔርን ጥበቃና ጥንቃቄ ለማሳየት ነው (ዝከ. 11:1-2; ኤር. 31:38-40; ዘካ. 2:1-5)። የሕዝቅኤል 40 የፍጻሜ ዘመን ትንቢት ደግሞ ልኬትን ያካትታል።

**21፡16 "ከተማይቱም አራት ማዕዘን ነበራት"** ይህ የቅድስተ ቅዱሳን ጠቃሽ ይሆናል (1 ነገሥ. 6፡19-20)፣ እሱም ደግሞ ፍጹም የሆነ ኩብ።

*መቅደስ ያሌለበት ምክንያት* (ዝከ. 21፡22) እግዚአብሔር ራሱ መቅደስ ስለሚሆን ነው። ይህም የዮሐንስ የማሳያ መንገድ ነው፣ የብኪ ትንቢቶች እንደ ሕዝቅኤል 40-48 የመሳሰሉት ተምሳሌታዊ ለመሆናቸው ወይም በሌላ መንገድ ስለ መፈጸማቸው።

▣ **"አሥራ ሁለትም ሺህ ምዕራፍ ሆነች"** ይህ በጥሬው "አስራ ሁለት ሺህ ስታዲየም ነው — አንድ መቶ አርባ አራት ኩብ።" እነዚህ የአስራ ሁለት ብዜቶች ናቸው፤ እግሬያዊ (ጥሬ) ከተማን አያመለክቱም፣ ነገር ግን ፍጹሞቹ ልኬቶች የሚያመለክቱት፣ እግዚአብሔር የተለየ ሁኔታ ያለው እንደሚሰጥ ነው፣ ቋሚ ደስታና ኅብረት በእርሱና በሕዝቡ መካከል የሚፈጥር (ዮሐንስ 14፡2-3) እንደ ፍጹሙ ኩብ ተምሳሌት፣ የብኪ "ቅድስተ ቅዱሳን።"

**21፡18-20 "የከተማይቱም ቅጥር"** ይህ ተለጣጣቂ የከበረ ድንጋይ ሊገለጽ የሚችለው

1. በሊቀ ካህኑ ኤፉድ ላይ የነበሩትን የከበሩ ድንጋዮች (ዘጸ. 28፡17-20)፣ ሆኖም፣ ቅደም ተከተሉና ስሞቹ የተለያዩ ናቸው። ይህ ያልተለመደ አይደለም፣ ምክንያቱም የጥንት የከበሩ ድንጋዮች ስም ከአገር አገር እና ከዘመን ዘመን ስለሚቀያየር ነው።
2. የኢሳ. 54፡11-17 የተጌጠች ከተማ
3. የጢሮስ ንጉሥ (ወይም ሰይጣን) ውበት፣ በንጉሣዊ የቀረበ (ወይም ሰማያዊ) ሕዝ. 28፡12-13 ላይ ያሉት ጌጣ ጌጦች
4. ዞዲያክ፣ ግን በተገላቢጦሽ ተራ የቀረበ (ፊሎ እና ጆሴፈስ)

**21፡21 "አሥራ ሁለቱም ደጆች አሥራ ሁለት ዕንቆች ነበሩ፤ እየአንዳንዱ ደጅ ከአንድ ዕንቍ የተሠራ ነበረ"** ይህ ተምሳሌታዊ ነው። እሱም ተመልሶ ወደ ራቢያዊ ወግ ወደ ታልሙድ ይሄዳል፣ "the *Sanhedrin*" (የጥንት አይሁድ ሸንጎ) $100_{ሀ}$፣ እሱም የፍጻሜ ዘመኑ ከተማ ደጆች ከአንድ የከበረ ድንጋይ እንደሚሠራ የሚገልጽ፣ 45 ጫማ ከፍታ ያለው።

▣ **"የከተማይቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረ።"** ይህ ተምሳሌታዊ ነው። መገንዘብ የሚኖርብን የእግዚአብሔር ከተማ የሰው ከፍ ያለ ብልጽግና አለመሆኑን ነው፣ ነገር ግን መለካት የማይቻለውን ዋጋ እና ጥራትን ተምሳሌት ያደርጋል፣ ይኸውም የእግዚአብሔር መገኘት።

**ራዕይ፡ 21፡22-27**

**[22]ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርስዋ ዘንድ አላየሁም። [23]ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለ ሆነ፥ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም ነበር። [24]አሕዛብም በብርሃንዋ ይመላለሳሉ፥ የምድርም ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርስዋ ያመጣሉ፤ [25]በዚያም ሌሊት ስለሌለ ደጆችዋ በቀን ከቶ አይዘጉም፥ [26]የአሕዛብንም ግርማና ክብር ወደ እርስዋ ያመጣሉ። [27]ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፥ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።**

**21፡22 "ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርስዋ ዘንድ አላየሁም።"** ይህ እጅግ ያልተለመደ ነው፣ ራዕይ ውስጥ ካሉ ከበርካታ ምንባቦች ጋር ሲተያይ፣ እዚያም ሰማያዊ መቅደስ የተመለከተበት (ዝከ. 3:12; 7:15; 11:1,2,9,19; 14:15,17; 15:5,6,8; 16:1,17)። ይኸው ተመሳሳይ የሰማይ መቅደስ ጽንሰ-ሐሳብ በዕብራውያን መጽሐፍ ተገልጧል (ዝከ. 8:2-5; 9:11,23-24።)

▣ **"ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ"** እዚህም ደግሞ ለእግዚአብሔር የሚሆኑ ሦስቱ እጅግ ተዘውታሪ መጠሪያዎች አሉ (*ያህዌ፣ ኤሎሂም፣ ኤል ሻዳይ)* በድብልቅ ጥቅም ላይ ውለዋል (ዝከ. 1:8; 4:8; 11:17; 15:3; 16:7; ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች 1:8 ላይ ተመልከት) የእርሱን ክብር ለማሳየት፣ ዙፋን ላይ የተቀመጠውን። ራዕይ 5 ላይ ካለው በግ ጋር ያለውን የቅርብ ግንኙነት ተገንዘብ። አንድ ላይ ነው የሚነግሡት፣ አንድ ዙፋን ብቻ ነው ያለው (ዝከ. 22:1፣3)።

**21፡23 "ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለ ሆነ፥ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም ነበር"** የአብና የወልድ ክብር ብቻ ነው እንዲያበራላት የሚያስፈልገው (መዝ. 36:9; ኢሳ. 24:23; 60:19-20; ዘካ. 14:6-7 እና ደግሞ ራዕ. 22:5)። ይህ የኮከብ አምልኮን በአጽንዖት ለመናቅ የታሰበ መንገድ ይሆናል።

**21፡24 "አሕዛብም በብርሃንዋ ይመላለሳሉ፥ የምድርም ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርስዋ ያመጣሉ፤"** ለመረዳት እጅግ አስቸጋሪ ነው፣ "አሕዛብ" ለምን አሁንም ገና ከነጩ ዙፋን የራዕይ ክፍል ወዲህ መጠቀሳቸው። እሱ የብኪ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል መዝ. 72:10-11; ኢሳ. 49:23; 60:3,15,16። እሱ በጥሬው አይደለም፣ ግን ጽሑፋዊ እንጂ! እሱ ሕዝቦችን ሁሉ ይወክላል፣ ከሁሉም ነገዶችና ሕዝቦች፣ እነርሱም የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሆኑት።

**21፡25 "በዚያም ሌሊት ስለሌለ ደጆችዋ በቀን ከቶ አይዘጉም፥"** ይህ የኢሳ. 60፡11 ወይም ዘካ. 14፡6-7 ጠቃሽ ነው። የጨለማ ጽንሰ-ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘወትር የክፉው ዘይቤ ነው (ማቴ. 6:23; 8:12; 22:13; 25:30)። ብርሃንና ጨለማ በተለይ ለዮሐንስ ጠቃሚ ሥነ-መለኮታዊ፣ ተምሳሌታዊ ተቃርኖዎች ናቸው (ዮሐንስ 1:4-5, 7-9; 3:19-21; 8:12; 11:9-10; 12:35-36,46; 1 ዮሐንስ 1:5-7; 2:8-11)። የበሮቹ ፈጽሞ አለመዘጋት ተምሳሌትነቱ ግልጽነት፣ መገኘት፣ ምንም ዓይነት የጥቃት ፍርሃት አለመኖሩ ነው።

**21፡27 "ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ"** ይህ የኢሳ. 52:1; ሕዝ. 44:9; ዘካ. 14:21 ጠቃሽ ነው፣ እሱም ጽሑፋዊ ዘዴ ሆኖ የመዳረሻውን ልዩነት የሚያሳይ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ እና የክፉው በሆኑት መካከል ያለውን (ዝከ. ቁ. 24)። አዲሱ ዘመን ባሕርይ ያደረገው ብርሃንማ፣ ያልተዘጋ ከተማ፣ ፍጹም የሆነ ጽድቅ ያለበት ከተማ ነው። ምንም ዓይነት ክፉ አይኖርም!

▣ **"ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት"** ይህ ዘይቤአዊ ሐረግ "የሕይወት መጽሐፍ" ደግሞ ራዕ. 20፡12-15 ላይ ይገኛል፣ እዚያም ሁለት መጻሕፍት የተጠቀሱበት፡

1. የሕይወት መጽሐፍ፣ ይኸውም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ስሞች ያለበት (ዘጸ. 32:32; መዝ. 69:28; ኢሳ. 4:3; ዳን. 12:1; ሉቃስ 10:20; ፊሊ.. 4:3; ዕብ. 12:23; ራዕ. 13:8; 17:8; 20:15; 21:27)
2. የድርጊት ወይም የመታሰቢያ መጽሐፍ፣ ይኸውም ሁለቱንም፣ ክፉውንም ሆነ የጽድቅን ሥራዎች የሚመዘግብ (መዝ. 56:8, 139:16; ኢሳ. 65:6; ሚል. 3:16)።

እነዚህ የእግዚአብሔር ፍጹም አስታዋሽነት ዘይቤዎች ናቸው።

## የዮሐንስ ራዕይ 22

**ራዕይ፡ 22፡1-5**

**[1]በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ። [2]በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፥ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ። [3]ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም። የእግዚአብሔርና የበጉም ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይሆናል፥ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ ፊቱንም ያያሉ፥ [4]ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል። [5]ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።**

**22፡1 "ከዚያም የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ።"** እዚህ ምንም የምዕራፍ ምድብ አያስፈልግም። ከእግዚአብሔር መገኛ የሚፈሰው ወንዝ ጽንሰ-ሐሳብ የብኪ ጠቃሽ ነው (መዝ. 46:4; ሕዝ. 47:1-12; ኢዩኤል 3:18; ዘካ. 14:8)። ውኃ የተለመደ ዘይቤ ነው፣

እግዚአብሔር በተትረፈረፈ መልኩ መንፈሳዊ መሻታቸውን ለሕዝቡ እንደሚሰጥ የሚጠቅስ (ኢሳ. 12:3; 44:3; 49:10; ኤር. 2:13; 17:13; ዮሐንስ 4:10-15; ራዕ. 7:17; 21:6)። ዮሐንስ ብቻ ነው ሕይወት *(zoē)* የሚለውን ቃል የሚጠቀመው፣ የትንሣኤ ሕይወትን ለመጥቀስ።

▣ **"ብርሌ የሚያንጸባርቀውን"** ይህም የእግዚአብሔርን ሰማያዊ ከተና ንጽሕና ያሳያል (ዝክ. 4፡6)።

▣ **"ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን"** አንድ ብቻ ዙፋን ነው ያለው (ዝክ. 21፡22)። ይህ የስው ባሕርያዊ ቋንቋ ነው፣ ከጥንታዊ ምስራቃዊ ንጉሣዊ ቤተ-መንግሥት ምናብ። እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንፈስ ነው፤ በሥጋዊ ዙፋን ላይ አይቀመጥም። ይህ ለሉዓላዊ ገዥነቱ ዘይቤ ነው።

**22፡2 "በወንዙም ወዲያና ወዲህ የሕይወት ዛፍ ነበረ"** ይኸው ተመሳሳይ ዛፍ ራዕ. 2፡7 ላይ ተጠቅሷል። ይኸው ሙሉ ራዕይ ከሕዝ. 47፡1-12 ነው (እዚህ፣ ቁ. 12)። በርካታ ማጣቀሻዎች በአይሁድ አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፍ ይገኛሉ፣ ለሕይወት ዛፍ፣ ዘፍ. 2:9; 3:22 (ሔኖክ 25:2; IV ኢስድራስ 7:53; 8:52; II ሔኖክ 8:3)። ያም አዳም ከእግዚአብሔር ያጣው (ኅብረት፣ እውቀት፣ የዘላለም ሕይወት)፣ እግዚአብሔር አሁን በነጻ ሰጠ፣ ለተዋጀው የሰው ልጅ (ፊሊ. 2፡6)።

▣ **"እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ"** ልዩ ርዕስ፡ ቁጥር አስራ ሁለት 7፡4 ላይ ተመልከት።

▣ **"የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ።"** ይህ እጅግ ያልተለመደ ነው፣ ምክንያቱም ምንም የሚፈወስ ነገር ስለማይቀር! ሆኖም፣ ይህ ከሕዝ. 47፡12 ላይ የተጠቀሰ ነው፤ ተደጋጋሚው ሥነ-መለኮታዊ ጭብጥ፣ እግዚአብሔር ሁሉም ("አሕዛብ") እንዲድኑ መሻቱ ነው (ኢሳ. 2:3-4; 45:22-25; 60:3; 66:18-19; ዘካ. 2:11; 8:20-23)።

**22፡3 "ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም።"** ይህ የዘፍ. 3፡17 እና ዘካ. 14፡11 ጠቃሽ ነው። አዲሱ ዘመን መጥቷል፣ እናም የብኪ ርግማን (ኤፌ. 2:15-16; ቆላ. 2:14) በክርስቶስ ሞት ተወግዷል (ሮሜ. 8:18,25; ገላ. 3:13; ኤፌ. 2:13,16)። ራዕይ ላይ የ4፡6ቱ የብርጭቆ ባሕር፣ የእግዚአብሔር ከአእምሮ በላይ የሆነ ቅድስና ተምሳሌት ነው። የወደቀው የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ሊቀርብ አይችልም፣ አሁን ግን ባሕሩ ተወግዷል (ዝክ. 21:1)።

ቃሉ የዕብራይስጡን ቃል *charam*ን ይወክላል፣ ፍችውም የተደመሰሰ፣ ወይም ሙሉ ለሙሉ የተደመሰሰ ነው (ዘካ. 14፡11)። ይህ የብኪ ጠቃሽ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ይህ ቁጥር የሚያመለክተው የአዲሲቷን ኢየሩሳሌም ደኅንነት ነው፣ እናም ከII ጴጥ. 1፡4-5 ተስፋዎች ጋር ተመሳሳይ ነው።

▣ የዚህን ሐረግ ያልተለመደ ሰዋሰዋዊ ገጽታ ተገንዘቡ። አንድ ዙፋን ነው ያለው፣ ግን በእርሱ ላይ ሁለት አሉ (ማለትም፣ እግዚአብሔርና በጉ)። ሆኖም፣ አገልጋዮች "እሱን" ያገለግሉታል (ነጠላ)። ይህም የሚያካትተው የአሀዳዊነትንና የሥጋዊነትን (የመለኮትን ሥጋ መልበስ) ምሥጢር ነው። አንድ አምላክ፣ ግን ደግሞ መለኮታዊ መሲሕ (እና አካላዊ መንፈስ ቅዱስ)።

**22፡4 "እነርሱ ፊቱን ያያሉ"** በብኪ እግዚአብሔርን ማየት ማለት ሞት ነው። ሙሴ የእግዚአብሔርን ፊት ፊት ለፊት እንዲያይ አልተፈቀደለትም (ዘጸ. 33፡20)። እግዚአብሔርን ማየት ወይም ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ንጹሕ ለሆኑ ሽልማት ነው (መዝ. 11:7; 16:11; 17:15; 140:13; ማቴ. 5:8)። በመነሻው ላይ የነበረው የዔድን ወዳጅነት ሙሉ ለሙሉ ተመልሷል (መዝ. 42፡1-2)!

▣ **"ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል"** ሰይጣን ተከታዮቹን ምልክት እንዳደረገባቸው (ዝክ. 13:1-17; 14:9; 20:4), እግዚአብሔርም የእርሱን ምልክት ያደርግባቸዋል (ዝክ. 3:12; 7:3; 14:1)። እሱም የባለቤትነትና የደኅንነት ምልክት ነው። ልዩ ርዕስ 7:2 ላይ ተመልከት።

**22:5 "ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥"** (ዝክ. 21:23-25; ኢሳ. 60:19-20; ዘካ. 14:7)

▣ **"ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።"** በሚሊኒየሙ መንግሥት ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡው ማን ነው? ምዕራፍ 20፡4-5 የሚያመለክተው ክርስቲያኖችን ነው፣ በመጨረሻው ዘመን መከራ ላይ የሚኖሩት፣ ግን ራዕ. 2፡26 እና 5፡10 የሚያመለክተው ቅዱሳን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር በምድር ላይ እንደሚገዙ ነው። ግልጽ የሆነ መለያ በመጽሐፍ ቅዱስ የለም፣ በዘላለማዊው ንግሥና (ዳን. 2:44; 7:14,18; ኢሳ. 9:7; ሉቃስ 1:33; II ጴጥ. 1:11; ራዕ. 11:15) መካከልና በሚሊኒየም ንግሥና። ከሥነ-ትርጓሜ አኳያ ዋነኛውን ዶክትሪን ከአፖካሊፕቲካዊ ምንባብ ላይ መውሰድ ተገቢ አይደለም። ይህ ቁጥር ዘላለማዊ ንግሥናን ያሳያል።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ምስያ ክፉ ወራሪ ይገጥመዋል፣ እሱም ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር የተደመሰሰ፣ የተወሰደው ከሕዝቅኤል 37-39 ነው። ዮሐንስ ይህ በጥሬው ይተረጎም ዘንድ ፈጽሞ ፍላጎት የለውም! እሱ የደራሲነትን ሐሳብ ማዛባት ነው፣ አፖካሊፕቲካዊ ምናብን ወደ ታሪካዊ እማሬያዊነት (ጥሬ) መቀየር። ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለን ፍቅር እና ስለ ወደፊቱ ያለን ጉጉት፣ ዘመናዊው ምዕራባዊ ቤተ-ክርስቲያን ትንቢትንና አፖካሊፕቲካዊ ጽሑፍን ባልተለመደና ተፈጥሯዊነቱን ባጣ መንገድ እንድትተረጉም አድርጓታል! ልዩ ርዕስ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት መግዛት 5፡10 ላይ ተመልከት።

**ራዕይ፡ 22፡6**

[6]**እርሱም፡- እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞዎች ናቸው፥ የነቢያትም መናፍስት ጌታ አምላክ በቶሎ ሊሆን የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ እንዲያሳይ መልአኩን ሰደደ።**

**22:6 "አለኝም"** ይህ የሚያመለክተው ሰባቱን የፍርድ ጽዋዎች የያዙትን መላእክት ነው (ዝከ. 21:9; 22:1,8,9,10)።

▣ **"እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞዎች ናቸው፥"** ይህ ሐረግ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለው

1. ኢየሱስ (ዝከ. 1:5; 3:7,14; 19:11)
2. የኢየሱስ ተከታዮች (ዝከ. 17:14)
3. የእግዚአብሔር ቃል (ዝከ. 19:9; 21:5; 22:6)

እግዚአብሔር ዘወትር የሚገለጸው እንደ "ጻድቅ እና እውነተኛ" ነው (ዝከ. 15:3; 16:7; 19:2)። ዕብራይስጡ ከዚህ ሐረግ ጀርባ የሚያመለክተው አጠቃላይ ታማኝነትን ነው።

▣ **"የነቢያትም መናፍስት ጌታ አምላክ"** ይህ ሊሆን የሚችለው፡

1. የ19፡10 ጠቃሽ
2. የብኪ ተመስጧዊነት ማጣቀሻ (II ጢሞ. 3:16; II ጴጥ. 1:20-21)
3. የአኪ ተመስጧዊነት ማጣቀሻ (II ጴጥ. 3:15-16)
4. በዮሐንስ ጊዜ የነበሩትን ወንጌል ሰባኪዎች ማጣቀሻ
5. የዮሐንስን መጽሐፍ (ራዕይ) ማጣቀሻ

ዋነኞቹ የግሪክ ጽሑፎች ትልቁ ፊደል የላቸውም። ዘወትር ተርጓሚዎች ወይም አታቾች ናቸው መወሰን የሚኖርባቸው "መንፈስ" የሚጠቅሰው መንፈስ ቅዱስን ወይም የሰው መንፈስ መሆኑን። ይህ ጽሑፍ የሚያመለክተው የሰውን መንፈስ ነው (1 ቆሮ. 14:32; ዕብ. 12:9)።

▣ **"መልአኩን ሰደደ"** ይህ የ1፡1 ጠቃሽ ነው። እነዚህ የመዝጊያ ቁጥሮች በሐሳባቸው ከምዕራፍ 1 ጋር እጅግ ተመሳሳይ ናቸው። ልማዳዊው የግል ደብዳቤ መልክ፣ በምዕራፍ 1 ጥቅም ላይ የዋለው በድጋሚ ምዕራፍ 22 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።

▣ **"በቶሎ ሊሆን የሚገባውን ነገር"** ተለጣጣቂ የሆኑ ጠቃሾች በጌታ መምጣት ቶሎ መሆን ላይ አሉ (ዝከ. 1:1,3; 3:11; ቁ. 6 [ሁለቴ], 7, 10, 12, እና 20)። የሁለት ሺህ ዓመት መዘግየት፣ ርቀቱ ለአማኞች ለመረዳት አስቸጋሪ ነው (መዘግየቱ 2 ተሰሎንቄ ላይ ተገልጧል)፣ ነገር ግን መታየት የሚኖርበት እያንዳንዱ የክርስቲያን ትውልድ በየራሱ ቀን የጌታ መምጣት ተስፋ አለው። ርግጠኛ የሆነ ተቃርኖ በአኪ አለ፣ በማንኛውም ጊዜ የጌታ መመለስ እና አንዳንድ ነገሮች ቀድመው መከሰት አለባቸው በሚለው መካከል። አማኞች ታማኝና ንቁ ሆነው መገኘት አለባቸው!

እዚህ አጭር ጥቅስ አለ፣ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ፣ በእኔ ሐተታ በማቴዎስ ላይ።

*"ሥነ-መለኮታዊ አያዎአዊ (ፓራዶክስ) ተቃርኖ አለ*

1. *በማንኛውም ጊዜ መመለስ (ዝከ. 24፡27፣44) እና አንዳንድ ሁነቶች በታሪክ መከሰት አለባቸው በሚለው ሐቅ መካከል*
2. *መንግሥቱ እንደ መጻኢ እና መንግሥቱ አሁን*

*አኪ የሚያስቀምጠው አንዳንድ ሁነቶች ከዳግም ምጽአቱ በፊት እንደሚከሰቱ ነው።*

1. *ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል (ዝከ. 24:14: ማርቆስ 13:10)*
2. *ታላቁ ክህደት (ዝከ. 24:10-13,21; I ጢሞ. 4:1; II ጢሞ. 3:1; II ተሰ. 2:3)*
3. *"የኃጢአት ሰው" መገለጥ (ዳን. 7:23-26; 9:24-27; II ተሰ. 2:3)*
4. *የሚከለክለው መወገድ (II ተሰ. 2:6-7)*
5. *የአይሁድ ተሐድሶ (ዘካ. 12:10; ሮሜ.11)"*

በመጽሐፉ ሰባት ጽሑፋዊ ምድቦች መካከል የጎላ ትይዩነት አለ ብለው የሚያምኑ ደግሞ እያንዳንዳቸው ከክርስቶስ የመጀመሪያና ዳግም ምጽአት መካከል ያለውን ጊዜ ይወክላሉ፣ ከተለያየ አተያይ አኳያ (ምሳ. ዊሊያም ሄንድሪክሰን፣ *ከድል ኣድራጊዎች በላይ*)። ይህ እውነት ከሆነ እንግዲያውስ የክርስቶስን የቅርብ ምጽአት የሚጠቅሱት ጽሑፎች (ዝከ. 1:3; 3:11; 22:7,10,12,20) የእነዚህን ትንቢቶች ፍጻሜ መጀመር ያሳያሉ፣ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ። የፍጻሜ ዘመኑ ኳስ እየተሽከረከረ ነው!

**ራዕይ፡ 22፡7**

[7]**እነሆም፥ በቶሎ እመጣለሁ። የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው አለኝ።**

**22:7 "እነሆም፥ በቶሎ እመጣለሁ።"** መልአኩ ባጠቃላይ የሚጠቅሰው መልአኩን ነው (ዝከ. ቁ. 12-15)። ይህም የተባለው በተለይ በኢየሱስ ነው 22፡16 ላይ። ቁ. 17 እና ቁ. 18-19 ላይ ማን በትክክል እንደተናገረው ርግጠኛ አይደለም፣ ኢየሱስ ግን በድጋሚ ተናግሯል፣ ቁ. 20 ላይ፣ እንዲሁም ዮሐንስ ቁ. 21 ላይ። ልዩ ርዕስ፡ የቅርብ ምጽአት 1፡3 ላይ ተመልከት።

▣ **"እሱ ብቁዕ ነው"** ይህ ሌለኛው ከሰባቱ ባርኮቶች አንዱ ነው፣ ለአማኞች፣ በመጽሐፉ ሁሉ የሚገኝ (ዝከ. 1:3; 14:13; 16:15; 19:9; 20:6; 22:7,14)።

▣ **"ትንቢት"** ይህ መጽሐፍ ትንቢታዊ ነው፣ እናም መተርጎም ያለበት ከትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ አኳያ ነው (ዝከ. ቁ. 9-10,18-19; 1:3; 10:11)። ይህ መጽሐፍ ታሪካዊ ትርክት አይደለም! ትንቢት ዘወትር ሁኔታዊ ነገሮች ይኖሩታል። የአዲስ ኪዳን የፍጻሜ ዘመን ምንባቦች የብኪን (ብሉይ ኪዳን) ትንቢታዊ ይዘት ያንጸባርቃሉ፣ ይኸውም የፍጻሜ ዘመንን በወቅቱ ከሚሆኑት ሁኔታዎች አኳያና በእምነት ምላሽ ይመለከታሉ። በርካታ ሊቃውንት የሚያምኑት አፖካሊፕቲካዊ ዘውግ ያደገው ከአይሁድ ትንቢታዊነት ነው። ልዩ ርዕስ፡ የአዲስ ኪዳን ትንቢት 1፡3 ላይ ተመልከት።

**ራዕይ፡ 22፡8-9**

**8 ይህንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ። በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። 9 እርሱም፡- እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ።**

**22፡8** ይህ እጅግ ያልተለመደ ቁጥር ነው። ይህም የዮሐንስ ተመሳሳይ ችግር ነው፣ 19፡10 ላይ ያለው። ባጠቃላይ እሱ ያሰበው መልአኩ መለኮት እንደሆነ ነው።

**22:9 "የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር"** ክርስትና በመነሻ ላይ የሚሆን የንስሐ፣ የእምነት ውሳኔን ያካትታል እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ንስሐ፣ እምነት፣ መታዘዝ፣ እና ጽናት! ራዕይ የተጻፈው ለተሰደዱት ክርስቲያኖች ነው፣ ለጽናት አጽንዖትን እየሰጠ። ዛሬ ለባህላችን ፈታኝ የሆነው ሥጋዊ መከራ አይደለም፣ ነገር ግን "የድርቀት ንቀዘት፣" ስሜት አልባነት፣ ተግባራዊ አምላክ የለሽነት፣ ቁሳዊነት፣ ጠባብ ክርስትና በሁሉም የመጠቀም፣ እና ኃላፊነት አልባነት!

**ራዕይ፡ 22፡10-11**

**10 ለእኔም። ዘመኑ ቀርቦአልና የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው። 11 ዓመፀኛው ወደ ፊት ያምፅ፥ ርኩሱም ወደ ፊት ይርከስ፥ ጻድቁም ወደ ፊት ጽድቅ ያድርግ፥ ቅዱሱም ወደፊት ይቀደስ አለ።**

**22:10 "በማኅተም አትዝጋው።"** ይህ በትክክል የኢሳ. 8:16; ዳን. 8:26 እና 12:4,9 ተቃራኒ ነው። የትንቢት ፍጻሜ ደርሷል። የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ለማያምኑት፣ እና ማበረታቻው ለአማኞች አሁን ነው! ዋነኛው ውሳኔ አሁን ተጠይቋል! መንግሥቱ ቀርቧል።

▣ **"ዘመኑ ቀርቧል"** ልዩ ርዕስ፡ በቅርብ መመለስ 1፡3 ላይ ተመልከት።

**ራዕይ፡ 22፡12-13**

**12 እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። 13 አልፋና ያሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።**

**22:11-12 "ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ (ኢዮብ 34:11; መዝ. 28:4; 62:12; ምሳ. 24:12; መክ. 12:14; ኤር. 17:10; 32:19; ማቴ. 16:27; 25:31-46; ሮሜ. 2:6; 14:12; I ቆሮ. 3:8; II ቆሮ. 5:10; ገላ. 6:7-10; II ጢሞ. 4:14; I ጴጥ. 1:17; ራዕ. 2:23; 20:12)። እግዚአብሔር የሚወዱትንና በወደቀው ምድር ሥርዓት መሐል ለእርሱ የሚኖሩትን ይሸልማል (ዝከ. 2:23; 20:12-13)። በሕይወት ይገለጣል፣ የውስጣዊ እምነት መንፈሳዊ እውነታና ጠቃሚነት (ማቴዎስ 7)። ሰዎች የሕይወት ስጦታ መጋቢዎች ናቸው፣ እናም ለእግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣሉ!

ይህም "የሥራን ጽድቅ" አያመለክትም። የሰው ልጅ የሚዋጀው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው፣ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እና በመንፈስ ቅዱስ መቃተት! ሆኖም፣ አንዱ እግዚአብሔርን ለመገናኘቱ ማስረጃው ክርስቶስን በመምሰል የተለወጠና እየተለወጠ ያለ ሕይወት ነው! አንዱ ቅድሚያ የሚሰጠውና፣ ሀብቱን የሚያኖርበት፣ ልቡን ይገልጣል!

**22፡11** ይህ የዳን. 12፡10 ጠቃሽ ነው።

**22:12 "ፈጥኜ እመጣለሁ"** ልዩ ርዕስ 1፡3 ላይ ተመልከት።

**22፡13** ይህ ቁጥር የብኪ የያህዌ መጠሪያዎች ነው፣ 1፡8 እና 21፡6 ላይ የሚገኘው፣ ነገር ግን እዚህ የሚጠቅሰው ክርስቶስን ነው። የእነዚህ የብኪ መጠሪያዎች ወደ ኢየሱስ መዛወር፣ የአኪ ደራስያን የእሱን መለኮትነት የሚያጸኑበት አንደኛው መንገድ ነው። ቁጥር 13 ይህን የመሰሉ ሦስት መጠሪያዎች ወይም ሐረጎች አሉት፣ እነርሱም በዋነኛነት ዘላለማዊውን አምላክ የሚገልጹ (ኢሳ. 41:4; 44:6; 48:12), አሁን ግን ለኢየሱስ ነው ጥቅም ላይ የዋሉት (ዝከ. 1:17; 2:8)።

**ራዕይ፡ 22፡14-15**

**[14]ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው። [15]ውሻዎችና አስማተኞች ሴሰኞዎችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትንም የሚያመልኩት ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ።**

**22:14 "ብፁዕ"** ይህ ለአማኞች ከሰባቱ ባርኮቶች የመጨረሻው ነው፣ ራዕይ ላይ የሚገኘው (ዝከ. 1:3; 14:13; 16:15; 19:9; 20:6; 22:7,14)።

▣ **"ልብሳቸውን የሚያጥቡ"** ይህ በክርስቶስ ምትክ ማስተሠርያነት የማመን ዘይቤ ነው (ዝከ. 7፡14)። አማኞች ተቀባይነት አግኝተዋል፣ እሱ ተቀባይነት በማግኘቱ (ኤፌ. 1፡6)። አማኞች በሕይወት ይኖራሉ፣ እሱ በመሞቱ ምክንያት። አማኞች የትንሣኤ ሕይወት አላቸው፣ እሱ ስለሚኖር!

የግሪክ ጽሑፎች ልዩነት አለ፣ በዚህ ሐረግ ላይ።

1. "ልብሳቸውን የሚያጥቡ" በMSS ℵ ነው (አራተኛ ክፍለ-ዘመን) እና (አምስተኛ ክፍለ-ዘመን)፣ ቫልጌትንም ጨምሮ። ዩቢኤስ[4] "ሀ" ደረጃ ይሰጠዋል፣ ማለትም "ርግጠኛ።"
2. "ትዕዛዛቱን የሚያከብሩ" በ046 ነው፣ ከአስረኛው ክፍለ ዘመን ኤምኤስ ክብ ትልልቁ ፊደላት፣ ክብ ቅጥልጣይ ፊደሎች ኤምኤስኤስ (1 እና 94) ከአስራ ሁለተኛው ክፍለ-ዘመን፣ እና ፔሺታ (ሶርያዊ) ቅጂ።

▣ **"ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ"** እነዚህ ሁለት ዘይቤዎች ናቸው፣ በክርስቶስ ላለው ዘላለማዊ ደኅንነት። አንደኛው ወደ ዘፍ. 2:9; 3:22 (ራዕ. 2:7; 22:2,14,19) ተመልሶ ይሄዳል፣ ሌለኛውም ወደ ራዕ. 21:2,9-22:5።

**22:15 "በውጭ አሉ"** ይህ ለመተርጎም እጅግ አስቸጋሪ ነው፣ ለእሳት ባሕር ዘይቤ እስካልሆነ ድረስ (ዝከ. 21፡8)።

▣ **"ውሻዎች"** ይህም ሌለኛው ያልተለመደ ዘይቤ ነው፣ ምክንያቱም በዚህ የመጽሐፉ ነጥብ ላይ ምንም ዓይነት ክፉ ሰዎች ስለማይቀሩ። ዘዳ. 23፡18 ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው ለከነዓን የወንድ አመንዝሮች የመራባት አምልኮ ነው። በሌሎቹ የብሉይ እና አዲስ ኪዳን ክፍሎች እሱ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው (መዝ. 22:16,20; ማቴ. 7:6; እና ፊሊ. 3:2)። በዚህ ነጥብ ላይ ሮበርት ኤች. ሞኡንስን ልጥቀስ፣ በራዕይ ላይ ካለው ሐተታ፣ ከአዲሱ ዓለም አቀፍ ቅጾች፡

"ቁጥሩ በዘላለማዊ አቋም፣ በሰማያዊ ከተማ ውጭ ሁሉም ዓይነት ክፉ ሰዎች ይኖራሉ የሚል ትምህርት ለማስተላለፍ የታሰበ አይደለም። እሱ እንዲያው የሚገልጸው መጻኢውን ነው፣ አሁን ባለው ምናብ እይታ። በታማኞቹ መባረክና በክፉዎች ዕጣ መካከል ያለው ተቃርኖ" (ገጽ 394)።

**ራዕይ፡ 22፡16**

**[16]እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ።**

**22:16 "እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ።"** "ለእናንተ" የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር እንደሆነ ተገንዘቡ፣ እንዲሁም ከምዕራፍ 2-3 ስለ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የጠቀሰው እጅግ ተለይቶ እንደሆነ ተገንዘቡ። መጽሐፉ የሚጀምረውና የሚያበቃው በመልእክት ዘውግ ነው፣ በመካከሉ ያለው ራዕይ ደግሞ የትንቢት (ፍጻሜው በአሁኑ ሌንስ ይታያል) እና አፖካሊፕቲካዊ (ምናባዊ ምስያ)።

▣ **"መልአኬ"** ላኪው ዘወትር እግዚአብሔር አብ ነው (ዝከ. 22፡6፣ "መልአኩ")። እዚህ ላኪው ኢየሱስ ነው ("መልአኬ")። ሐረጉ ደግሞ 1፡1 ላይ ይገኛል፣ ነገር ግን ተከታዩ ተውላጠ ስም አሻሚ ነው።

▣ **"ቤተ-ክርስቲያኖች"** ልዩ ርዕስ ተመልከት 1፡4 ላይ።

▣ **"የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥"** በርካታ ጠቃሾች አሉ፣ የዳዊት ዘር የሆነው መሲሕ፣ በብኪ ll ሳሙ. 7:12-16 እና ኢሳ. 11:1,10) እና በአኪ (ማቴ. 1:1; 9:17; 15:22; 21:9; ሮሜ. 1:3; ll ጢሞ. 2:8 ራዕ. 5:5)። ኢየሱስ የሁሉም የአኪ ትንቢቶች ፍጻሜ ነው።

**ልዩ ርዕስ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ**

በርካታ የተለያዩ የግሪክ ቃላት አሉ፣ አኪ ስለ ኢየሱስ ሲናገር የተጠቀመባቸው።

*ሀ. የአኪ ቃላት*

1. ናዝሬት — የገሊላ ከተማ (cf. Luke 1:26; 2:4,39,51; 4:16; Acts 10:38)። ይህች ከተማ በተጓዳኝ ምንጮች ላይ አልተጠቀሰችም፣ ነገር ግን በኋለኞቹ ጽሑፎች ላይ ተገኝታለች። ኢየሱስ ከናዝሬት ነው መባሉ ክብር አይደለም (ዮሐንስ 1፡46)። በኢየሱስ መስቀል ላይ ያለው ምልክት፣ ይኸውም የቦታ ስምን የሚያካትተው፣ የአይሁድ የንቀት ምልክት ነበር።
2. *Nazarēnos* – መልከዓ ምድራዊ አቀማመጡን የሚጠቅስ ይመስላል (ሉቃስ 4:34; 24:19)
3. *NazÔraios* – ከተማዋን ያመለክታል፣ ግን ደግሞ የዕብራይስጡ ቃል "ቅርንጫፍ" መሲሐዊ አገባብ ይሆናል (*netzer*, BDB 666, ኢሳ. 4:2; 11:1; 53:2; ኤር. 23:5 (BDB 855); 33:15; ዘካ. 3:8; 6:12; በአኪ፣ *ራዕ.* 22:16)። ሉቃስ ይህንን ለኢየሱስ ይጠቀማል 18:37 እና ሐዋ. 2:22; 3:6; 4:10; 6:14; 22:8; 24:5; 26:9 ላይ።
4. *ከቁ.* #3 ይዛመዳል *nazir* (BDB 634), ፍችውም "በመሐላ የተቀደሰ።"

ለ. ታሪካዊ አጠቃቀም ከአኪ ውጪ።
1. እሱ የሚጠቅሰው የአይሁድ (ቅድመ-ክርስትና) የመናፍቅ ወገኖችን ነው (አራምኛ *nasÔrayya*)።
2. እሱም በአይሁድ ማኅበራት ጥቅም ላይ የሚውለው በክርስቶስ የሚያምኑትን ለመጥራት ነው ሐዋ. 24:5,14; 28:22, *nosri*)።
3. እሱም መደበኛ ቃል ሆኗል በሶርያ ያሉትን አማኞች ለመጥራት (አራምኛ) አብያተ ክርስቲያኖች። "ክርስቲያን" በግሪክ አብያተ ክርስቲያናት ጥቅም ላይ የሚውለው አማኞችን ለመጥራት ነው።
4. በሆነ ጊዜ፣ ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ፣ ፈሪሳውያን በጃምኒያ ዳግም ተደራጅተው በምኵራብና በቤተ ክርስቲያን መካከል መደበኛ ልዩነት አደረጉ። ክርስቲያኖችን በመቃወም ከተደረጉት የርግማን ዓይነቶች ምሳሌ የሚሆነን፣ "በአስራ ስምንተኛው ቡራኬ" ላይ ይገኛል፣ ከ*ባርኮት* 28ለ-29ሀ፣ እሱም አማኞችን "ናዝራውያን" ብሎ የሚጠራ። "ናዝራውያንና መናፍቃን ወዲያውኑ ይጥፉ፤ ከሕይወት መጽሐፍ ላይ ይደመሰሳሉ፣ ከታመኑትም ጋር አይጻፉም።"
5. እሱም በጀስቲን ማርቲየር ጥቅም ላይ ውሏል፣ *Dial.* 126:1፣ እሱም የኢሳይያስን *netzer* ለኢየሱስ የተጠቀመ።

ሐ. የደራሲው አስተያየት

እኔ የምደነቀው በቃሉ እጅግ በርካታ ፊደላት ነው፣ ይህም ያልተሰማ አለመሆኑን ባውቅም እንኳ፣ በብኪ እንደ "ኢያሱ"፣ በዕብራይስጥ በርካታ የተለያዩ ፊደላት እንዳሉት። የሚከተሉት ዓይነቶች ርግጠኛ ሳልሆን እንድቀር አድርገውኛል፣ ቁልጭ ላለ ፍችው፡

1. "ቅርንጫፍ" ከሚለው መሲሐዊ ቃል ጋር ያለው የቅርብ ዝምድና (*netzer*) ወይም ተመሳሳዩ ቃል *nazir* (በመሐላ የተቀደሰ)
2. የገሊላ አሉታዊ ፍች
3. በገሊላ ላለችው የናዝሬት ከተማ አነስተኛ ወይም ምንም የዘመኑ ማስረጃ አለመኖሩ
4. እሱ የመጣው ከአጋንንት አፍ ነው፣ በፍጻሜ ዘመን ትዕይንት ላይ (ማለትም፣ "ልታጠፋን መጣህን?")

ይህን የቃል ምድብ በተሟላ ማጣቀሻ ለማጥናት፣ ኮሊን ብራውን (አዘጋጅ)፣ የአዲስ ኪዳን *ሥነ-መለኮት* አዲሱ ዓለም አቀፍ መዝገበ-ቃላት፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 346 ወይም ሬይሞንድ ኢ. ብራውን፣ *Birth*፣ ገጽ 209-213፣ 223-225።

▣ **"የሚያበራም የንጋት ኮከብ"** ይህ መሲሐዊ መጠሪያ ነው (ዘኍልቍ 24:17 ወይም ማቴ. 2:2 ወይም II ጴጥ. 1:19)። ይህም የኢሳ. 14፡12 ጠቃሽ ይሆናል፣ ተመሳሳዩ ቃል ሰይጣንን የሚጠቅሰው። ራዕይ ላይ ከፉው ዘወትር በሦስትነቱ አንድ የሆነውን አምላክ ይኮርጃል።

## ራዕይ፡ 22፡17

**[17]መንፈሱና ሙሽራይቱም። ና ይላሉ። የሚሰማም። ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።**

**22:17 "መንፈሱና ሙሽራይቱም። ና ይላሉ።"** ምንም እንኳ ይህ ምንባብ የተለያዩ ትርጉሞች ቢኖሩትም፣ ከዐውደ-ጽሑፉ መረዳት የሚቻለው ይህ የወንጌል ጥሪ ነው፣ እንደሚያስፈልገው ለተረዳ ሁሉና እግዚአብሔር በክርስቶስ ላደረገው ግብዣ ምላሽ ለሚሰጥ። ይህም የራዕይ መጽሐፍ ትኩረት ሆኖ ቀጥሏል፣ የዳኑትን ለማበረታታት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን የጠፉትን በደላቸውን ለማስታወቅና ለማበረታታት፣ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ላደረገው ነጻ ስጦታ ምላሽ እንዲሰጡ። "ና" የሚለው ቃል አራትዮሽ አጠቃቀም (አራቱም ሁሉ ለጠፉት ነው የሚያመለክቱት፣ ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሳይሆን)፤ "ማንም" የሚለው ቃል ተደጋጋሚ አጠቃቀም፤ እጅግ ታላቅ የሆነው የምስራች፣ ነጻ መሆኑ (ኢሳይያስ 55) ለማንም ማበረታቻ ይሆናል፣ ምላሽም ለመስጠት! ይህም ለእኔ የሚመስለኝ ምልሳት ነው በዮሐንስ ጊዜ ይኖሩ ለነበሩት (እና በየቀኑ)። ይህም ያልተለመዱ ነገሮችን ያብራራል (ከፍርድ ቀን በኋላ የሚጠፉት መኖር) ራዕይ 19-22 ላይ። በርካታ ምልሳቶች አሉ፣ በዮሐንስ በራሱ ጊዜ፣ ይኸውም በትይዩነት የተገለጹ፣ በራዕይ በሰባቱ ጽሑፋዊ ምድቦች መካከል። እሱ የጻፈው "ለተወደዱ ልጆች" ነው፣ ኤፌሶንን ግምት ውስጥ በማስገባት (ዝኪ. I, II, እና III ዮሐንስ)።

## ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ

የሥላሴን ሦስት አካላት እንቅስቃሴ በአንድ ወጥ በሆነ አውደ ተመልከታቸው፡፡ «ስላሴ» የሚለው መጠሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው በቱርቱስያን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም፡፡ ነገር ግን ሐሳቡ በጣም የተስፋፋ ነው፡፡

ሀ. ወንጌላት

1. ማቴ 3:16-17፤ 28:29 (እና ሌሎች ተመሳሳዮች)
2. ዮሐ 14:26

ለ. ሐዋርያት ሥራ - ሐዋ 2:32-33፤ 38-39

ሐ. ጳውሎስ

1. ሮሜ 1:4-5፤ 5:1፡5፤ 8:1-4፡8-10
2. 1ቆሮ 2:8-10፤ 12:4-6
3. 2ቆሮ 1:21: 13:14
4. ገላ 4:4-6
5. ኤፌ 1:3-14፡ 17፤ 2:18፤3:14-17፤ 4:4-6
6. 1ተሰ 1:2-5
7. 2ተሰ 2:13
8. ቲቶ 3:4-6

መ. ጴጥሮስ 1ጴጥ 1:2

ሠ. ይሁዳ ቁ. 20-21

በእግዚብሔር ውስጥ የብዙ ቁጥር መኖሩ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ፍንጭ አለ፡፡

ሀ. የብዙ ቁጥር ለእግዚአብሔር መጠቀሱ

1. “ኤሎሂም” የሚለው ስም ብዙ ቁጥሮችን አመልካች ነው፡፡ ግን ምን ጊዜም በእግዚአብሔር ሲጠቀም ነጠላ ግስን አመልካች ነው፡፡
2. “እኛ” በዘፍጥረት 1፡26-27፣ 3፡22፣ 11፡7

ለ. የእግዚአብሔር መልአክ መለኰትን በሚታይ መልኩ የወከለ ነበር

1. ዘፍ. 16፡7-13፣ 22፡11-15፣ 31፡11፣13፣ 48፤15-16
2. ዘፀ. 3፡2፣4፤ 13፡21፤ 14፡19
3. መሳፍንት 2፡1፣ 6፡2-23፤ 13፡3-22
4. ዘካሪያስ 3፡1-2

ሐ. እግዚአብሔር እና መንፈሱ የተለያዩ (ዘፍ1:1-2 መዝ 104:30፤ ኢሳ 63: 9-11፤ ሕዝ 37:13-14)

መ. እግዚአብሔር (ያህዌህ) እና መሲል (አዶናይ) የተለያዩ ናቸው መዝ 45:6-7፤ 110:1፤ ዘካ 2:8-11፤ 10:9-12

ሠ. መሲሑ እና መንፈስ የተያዩ ናቸው፤ ዘካ 12:10

ረ. ሦስቱም በኢሳ 48:16፤ 61:1 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡

የኢየሱስ መለኰትነት እና የመንፈስ ስብእና አጥባቂ እና የአንድ አምላክ አምልኰ ተከታዮች ለነበሩት ለቀደሙት አማኞች ችግር የፈጠረባቸው ጉዳይ ነበር፡፡

1. ቱርቱሊያን - ወልድ ከአብ እንደሚያንስ አስረዳ
2. ኦሪገን - የወልድን እና የመንፈስ መለኰታዊ ማንነት ዝቅ አደረገ
3. አርዮስ - የወልድን እና የመንፈስ መለኰትነት ካደ
4. ምናርኪያኒዝም - አንድ አምላክ ተከታታይነት ባው ሁኔታ እንደ አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ እንደ ተገለጠ የሚያምን

ስላሴ በታሪክ ሁሉ በቅዱሳት መፃህፍት አማካኝነት ሃሳቡ ሲገለፅ የኖረ ጉዳይ ነው፡፡

1. የኢየሱስ መለኰትነት፣ ከአብ ጋር እኩል መሆኑ በ325 ዓ.ም በኒቅያ ጉባኤ ፀደቀ
2. የመንፈስ ሙሉ ስብእና እና መለኰትነት ከአብ እና ከወልድ ጋር አኩል መሆኑ በኮንስታንቲኖፕል ጉባኤ (381 ዓ.ም) ፀድቋል፡፡
3. የስላሴ አስተምህሮ የአውግስቲን ሥራ በሆነው ውስጥ *Deir*ጽ*itae* በሙላት ተገልጿል፡፡

እዚህ ላይ ግን እንቆቅልሽ የሆነ ጉዳይ አለ፡፡ አዲስ ኪዳን ግን አንድ መለኰታዊ መንነት ያለው እና ሦስት ዘላለማዊ የስብእና መገለጦች እንዳሉት የሚያረጋግጥ ይመስላል፡፡

## ራዕይ፡ 22፡18-19

**[18]በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ [19]ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።**

**22፡18-19** እነዚህ ቁጥሮች በግልጽ የሚዛመዱት ከመልእክቱ የመጀመሪያ ሰሚዎች ጋር ነው፣ ብሎም ከወደፊቶቹ የመጽሐፉ አንባቢዎች/ሰሚዎች። እሱም የተለመደ የብኪ ጽሑፋዊ ልምምድ ነው፣ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ማስቀመጥ፣ የእግዚአብሔርን ቃል

ለመለወጥ ለሚፈተኑት (ዘዳ. 4፡2፤ 12፡32)። ይህ ማለት በጥሬው ይወሰዳል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን እሱ ጠንካራ የምስራቃውያን ግነታዊ መግለጫ ነው፣ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሚለውጡት። ይህ አማኝ ተርጓሚዎችን ወይም ጸሐፊዎችን አይመለከትም፣ በቅንነት በመጸለይ የእግዚአብሔርን ፍቃድ የሚፈልጉትን፣ ነገር ግን እንደ ኢሪኒዩስ ከሆነ፣ *መናፍቃንን በመቃወም* 30፡12፤ እሱ የሚያመለክተው ሐሰተኛ መምህራንን ነው፣ እነርሱም በቅዱስ ቃሉ ላይ የሚጨምሩ፣ የሚለውጡ፣ ወይም የሚሰርዙ፣ ይኸውም የዚህ ምንባብ ዋና ነገር የሆነ። እኛ አንዷቷን ቁጥር አቃቂር ልናወጣላት እንደመንችል ተገንዘቡ፣ ዶክትሪናችንን ለመመሥረት ብለን፣ ይኸውም ከሌሎች የቅዱስ ቃሉ ግልጽ ትምህርቶች ጋር የሚቃረን።

▣ **"እንደ... እንደ"** እነዚህ ሁለቱም ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፣ ጽኑ ድርጊትን የሚገልጹ።

---

***ራዕይ፡* 22፡20**

**[20]ይህን የሚመሰክር። አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና።**

---

**22:20 "በቶሎ እመጣለሁ"** የፍጻሜው ድንገተኝነት፣ የእግዚአብሔር ለፍርድ መምጣት የአይሁድ እና የክርስቲያኖች አፖካሊፕቲካዊ ሥነ-ጽሑፍ ባሕርያት ናቸው። ይኸው ተመሳሳይ ጭብጥ ማቴ. 13:34-36; 24:43; 25:1-13; ሉቃስ 12:29; I ተሰ. 5:2,4; II ጴጥ. 3:10 ላይ ይታያል። ከ2000 ዓመት መዘግየት አኳያ ይህን መረዳት ያለብን ከሕላዌ አንጻር ነው፣ በጊዜያዊ መልኩ ሳይሆን። ይመጣል! ዝግጁ ሆናችሁ ኑሩ! ልዩ ርዕስ 1፡3 ተመልከት።

▣ **"ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና"** ይህ አራማዊው ሐረግ ማራናታ ነው (1 ቆሮ. 16:22)። ይህንን በብዙ መንገዶች መተርጎም ይቻላል፡

1. *Maranatha* ከሆነ፣ እንግዲያውስ "ጌታችን መጥቷል" ነው
2. *marana tha* ከሆነ፣ እንግዲያውስ "ጌታችን ሆይ ና!" ነው

ቁጥር 1 ለዚህ ዐውድ በተሻለ ይስማማል። ከ*Didache* 10:6 እንደምንረዳው የአምልኮ መዝጊያ ነው፣ የጌታ ራት አገልግሎት፣ በዮሐንስ ጊዜ።

---

**ልዩ ርዕስ፡ ማራናታ**

ይህ አራምኛ ሐረግ ነው፣ እሱም የጥንት ፍልስጥኤማውያን ቤተክርስቲያን ሥነ-መለኮታዊ የቅዱሳት ምሥጢራት ማረጋገጫ (1) የኢየሱስን መለኮትነት (መዝሙር 110) ወይም (2) የኢየሱስን ዳግም ምጽዓት (ሐዋ. 3፡19-21)። የእሱም ትርጉም የሚወሰነው አንዱ እንዴት አድርጎ ቃሉን እንደከፋፍለው ነው፡

1. "ጌታችን፣ ና" (ማለትም፣ *marana-tha)* የተመሳሳይ ተተኳሪ ሐረግ ፍች ነው፣ ራዕ. 22፡20 ላይ። ስለዚህ አብዛኞቹ ትርጉሞች ያንን ትርጉም እዚህም ይወስዱታል። እንደዛ ከሆነ፣ እንግዲያውስ እሱ ሊሆን የሚችለው ለኢየሱስ መመለስ ጸሎት ነው።
2. "ጌታችን መጥቷል" (ማለትም፣ *maran-atha*) የአራምኛ የተጠናቀቀ ይሆናል። ይህ Chrysostom ትርጉም ነው (345-407 ዓ.ም) የሚመረጠው ስለ ኢየሱስ ሥጋዌነት (ሥጋ መልበስ) በመናገሩ ነው።
3. "ጌታችን ይመጣል" ሊያንጸባርቅ የሚችለው የዕብራይስጥ ትንቢታዊ የተጠናቀቀ ነው፣ እሱም ጥቅም ላይ የሚውለው በብዙዎች ለክርስቲያን አገልግሎት መነሻ ሐሳብ ተደርጎ ስለሚገመት ነው። ዳግም ምጽዓቱ በየዘመናቱ ለነበሩት አማኞች ዘወትር ማበረታቻ ይሆናቸዋል።
4. *Didache* (በአንደኛው ክፍለ -ዘመን መጨረሻ ወይም በሁለተኛው ክፍለ-ዘመን የተጻፈ ነው) 10፡6፣ ይሄንኑ ተመሳሳይ ሐረግ በጌታ ራት ዐውደ-ጽሑፍ ይጠቀምበታል፣ እዚያም የኢየሱስን የወቅቱን መገኘትና መጻዒውን፣ የፍጻሜ ዘመን ምጽዓት ሁለቱም በጸሎት አጽንዖት ይሰጣቸዋል።

---

***ራዕይ፡* 22፡21**

**[21]የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።**

---

22፡21 "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ" ከሕዝቡ ጋር ይሁን የሚለው፣ የመደምደሚያ እውነት የቀረበው በመከራ ላይ ለነበሩት ክርስቲያኖች ዘመን፣ እንዲሁም ለእያንዳንዱ የክርስቲያን ትውልድ ተስፋ መሆኑን ተገንዘብ!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. አማኞች ወደ መንግሥተ ሰማይ ይሄዳሉ ወይስ መንግሥተ ሰማይ ወደ ጸዳቸው ምድር ይመጣል?
2. ራዕ. 21፡3 "አማኑኤል" ከሚለው ቃል እንዴት ይዛመዳል?
3. በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ለምን መቅደስ አይኖርም (ዝከ. 21፡22)?
4. 21፡24 ላይ የተጠቀሱት ሰዎች እነማናቸው?
5. አማኞች የዚህን የትንቢት ቃል እንዴት "ይጠብቃሉ/አተኩረው ይይዛሉ (ዝከ. 22፡7)?
6. ይህ መንግሥተ ሰማያት ከሆነ፣ ከከተማይቱ ውጭ ያሉት ክፉዎች እነማናቸው፣ 22፡15 ላይ?
7. 22፡17 ለምን እጅግ ጠቃሚ ሆነ?
8. 22፡18-19 በጥሬው የሚወሰድ ነውን? ራዕይን አዛብቶ የተረጎመ አማኝ ደኅንነቱን/ቷን ያጣልን?
9. ምዕራፍ 22 ላይ ሦስት ጊዜ "በቶሎ እመጣለሁ" ይላል፣ (ዝከ. ቁ. 7፣12፣20)። ለምን 2000 ዓመት ሆነው?

# ተጨማሪ መግለጫ አንድ
# የግሪክ ሰዋሰዋዊ ቃላት አጭር መግለጫዎች

የኮኔ ግሪክ፣ ዘወትር ሔለናዊ ግሪክ የሚባለው፣ በሜዲትራኒያን የዓለም ክፍል አካባቢ ከታላቁ አሌክሳንደር ጀምሮ (336-323 ቅልክ) ዋነኛ ቋንቋ በመሆን አገልግሏል፤ ለ800 ዓመታት ገናና ሆኖ አክትማል (300 ቅልክ — 500 ዓም)። እሱም ቀለል ያለ የጥንታዊ ግሪክ አልነበረም፣ ነገር ግን በብዙ መንገዶች አዲሱ ግሪክ ሆኖ በጥንታዊው ቅርብ ምስራቅና በሜዲትራኒያን የዓለም ክፍል ሁለተኛ ቋንቋ ሆኖ ነበር።

የግሪኩ አዲስ ኪዳን በአንዳንድ መንገዱ የተለየ ነበር፣ ምክንያቱም ተጠቃሚዎቹ ከሉቃስና ከዕብራውያን ጸሐፊ በተቀር፣ ምናልባት አራማዊን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጠቅመው ይሆናል። ስለዚህ፣ ጽሑፎቻቸው የአራማዊ ፈሊጦችና መዋቅራዊ ቅርጾች ስላሉባቸው ነው። በተጨማሪም፣ ከሴፕቱዋጊንት (የግሪኩ የብኪ ትርጉም) ያነቡም ይጠቅሱም ነበር፣ ይህም ደግሞ በኮኔ ግሪክ የተጻፈው። ነገር ግን ሴፕቱዋጊንት ደግሞ የተጻፈው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ግሪክ ባልሆነ የአይሁድ ሊቃውንት ነው።

ይህም አዲስ ኪዳንን ወደ ጥብቅ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ወዳለው እንዳንገፋው እንደ ማስታወሻ ያገለግላል። እሱ የተለየ ያልሆነና ብዙ የሚጋራው ያለው ነው (1) ሴፕቱዋጊንት፤ (2) የግሪክ ጽሑፎች ለአብነትም የጆሴፈስ፤ እና (3) በግብፅ የተገኘው የወረቀት ጽሑፍ። ታዲያ እንዴት አድርገን የአዲስ ኪዳንን ሰዋሰዋዊ ትንታኔ እናካሂዳለን?

የኮኔ ግሪክ ሰዋሰዋዊ ባሕርይና የአዲስ ኪዳን ኮኔ ግሪክ ተወራራሽ ናቸው። በብዙ መንገዱ ሰዋሰውን በቀላል መልክ የማቅረብ ጊዜ ነበር። ጽሑፉ ዋነኛው መመሪያችን ይሆናል። ቃላቶች ትርጉም የሚኖራቸው በሰፊ ጽሑፍ ነው፤ ስለሆነም፣ ሰዋሰዋዊ መዋቅርን መረዳት የሚቻልበት ብርሃን (1) የጸሐፊው የተለየ ያጻጻፍ ስልት፤ እና (2) የተለየ የጽሑፍ አካል ነው። በግሪክ ቅርጾችና መዋቅሮች ላይ ለድምዳሜ የሚሆን ተስማሚ መግለጫ የለም።

ኮኔ ግሪክ በመጀመሪያ ግሣዊ ቋንቋ ነበር። ዘወትር ለትርጓሜው ቁልፉ የግሡ ዓይነትና ቅርጽ ነው። በብዙ ዋነኛ ሐረጎች ግሡ በመጀመሪያ ይመጣና፣ ዋነኛ ጠቀሜታውን ያስከትላል። የግሪክን ግሥ ለመተንተን ሦስት የሚሆኑ መረጃዎች የግድ ያሻሉ፡ (1) መሠረታዊ አጽንኦት የሰጠው ጊዜ፣ ድምጸት (ገቢር/ተገብሮ) እና ሁኔታው (ገጠመኙ ወይም የግሡ ርባታ)፤ (2) የተለየው ግሥ መሠረታዊ ፍቺ (ሥርወ ቃል)፤ እና (3) የጽሑፉ አወራረድ (አገባብ)።

I. ጊዜ

ሀ. ጊዜ ወይም ገጽታ የሚያካትተው የግሥን የተጠናቀቀ ድርጊትና ያልተጠናቀቀ ድርጊትን ግንኙነት ነው። ይህም ዘወትር "የተጠናቀቀ" እና "ያልተጠናቀቀ" በመባል ይታወቃል።

1. የተጠናቀቀ ጊዜ የሚያተኩረው የድርጊትን መከናወን ነው። አንድ ነገር ከመሆኑ ውጪ ተጨማሪ መረጃ አይሰጥም! አጀማመሩ፣ አካሄዱ ወይም ማብቃቱ አይካተትም።
2. ያልተጠናቀቀ ጊዜ የሚያተኩረው የአንድን ድርጊት ቀጣይነት ነው። linear action (ተሸጋጋሪ ድርጊት፣ በመካሄድ ላይ ያለ ድርጊት፣ ቀጣይ ድርጊት፣ ወዘተ።

ለ. ጊዜያቶች፣ ጸሐፊው ድርጊቶች እንዴት እንደተካሄዱ በተመለከተበት አግባብ ሊመደቡ ይችላሉ

1. ሆኗል = ያልተጠናቀቀ ግሥ
2. ሆኖአል እናም ውጤቱም ይገኛል = የተጠናቀቀ
3. ባለፈው ጊዜ ተጠናቋል እናም ውጤቱ ይኖራል፣ አሁን ግን አይደለም = በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ
4. እየሆነ ነው = የአሁን
5. ሆኗል = ያልተጠናቀቀ
6. ይሆናል = የወደፊት

እነዚህ ጊዜያቶች ለትርጓሜ እንዴት እንደሚረዱ ተጨባጭ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው "መዳን" የሚለው ቃል ነው። እሱም በበርካታ የጊዜያት ዓይነቶች ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከሂደቱንም ሆነ ፍጻሜውን ያመላክታል።

1. የድርጊት ግሥ — "ድኗል" (ሮሜ. 8፡24)
2. የተጠናቀቀ — "ድኗል እናም ውጤቱ ይቀጥላል" (ኤፌ. 2፡5፣8)
3. የአሁን — "የዳነ" (1ኛ ቆሮ. 1፡18፤ 15፡2)
4. የወደፊት (የትንቢት) — "ይድናል" (ሮሜ. 5፡9፣ 10፤ 10፡9)

ሐ. በግሥ ጊዜያቶች ላይ በማተኮር፣ ተርጓሚዎች፣ ዋናው ጸሐፊ ራሱን ለመግለጽ የመረጠበትን ምክንያት ይቃኛሉ። መደበኛው "ከስም በፊት የሚመጣቅ ግሥ" ጊዜያቱ ያልተጠናቀቀ የተግባር ግሥ ነበር። እሱም መደበኛው "ያልተወሰነ፣" "ያልተለየ፣" ወይም "ዘወትር ከስም በፊት" የሆነ ግሥ ነው። በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ጽሑፉ በሚወስነው መሠረት። እሱም አንድ ነገር መሆኑን ያሳያል። የኃላፊ ጊዜው ገጽታ ጥቅም ላይ የዋለው በአመላካች ተግባር ነው። ሌላ ጊዜ ጥቅም ላይ ከዋለ አንድ ልዩ ነገር አጽንዖት ተሰጥቶታል ማለት ነው። ግን ምን?

1. የተጠናቀቀ ጊዜ። ይህ የሚናገረው የተጠናቀቀ ድርጊትን ከሚኖረው ውጤት ጋር ነው። በአንዳንድ አገባቦች ያልተፈጸመ ጊዜ (የድርጊት ግሥ) እና የአሁን ጊዜን የደባለቀ ነው። ብዙውን ጊዜ የሚያተኩረው የተገኘው ውጤት ላይ ወይም የድርጊት መጠናቀቅ ላይ ነው። ለምሳሌ፡ ኤፌ. 2፡5 እና 8፣ "ድናችኋል፣ በመዳናችሁም ቀጥላችኋል።"
2. በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ። ይህም እንደ ተጠናቀቀ ጊዜ ሆኖ የሚኖረው ውጤት ያበቃበት ነው። ለምሳሌ፡ "ጴጥሮስ ከበሩ በስተውጭ ቆሞ ነበር" (ዮሐንስ 18፡16)።

3. የአሁን ጊዜ። ይህ የሚያሳየው ያላበቃለት ወይም ያልተጠናቀቀ ድርጊትን ነው። ትኩረቱም ብዙውን ጊዜ በሁኔታው ቀጣይነት ላይ ነው። ለምሳሌ: "በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን በመሥራት አይቀጥልም፣" "ማንም ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን በመፈጸም አይቀጥልም" (1ኛ ዮሐንስ 3:6 እና 9)።
4. ያልተጠናቀቀ ጊዜ። በዚህ ጊዜ ከአሁን ጊዜ ጋር ያለው ግንኙነት ከተጠናቀቀ እና በኃላፊ ጊዜ ከተጠናቀቀው ጊዜ ጋር ያለው ግንኙነት ተመሳሳይ ነው። ያልተጠናቀቀው የሚያሳየው ያላበቃለትን ድርጊት ማለትም ተጀምሮ አሁን ያበቃለትን ወይም ባለፈው ጊዜ የነበረውን ድርጊት መጀመሪያ ነው። ለምሳሌ: "ከዚያም ሙሉው ኢየሩሳሌም ወደ እሱ መውጣታቸውን ቀጠሉ" ወይም "ከዚያም ሞላው ኢየሩሳሌም ወደ እሱ መውጣት ጀመሩ" (ማቴ. 3:5)።
5. የትንቢት ጊዜ። ይህ የሚያሳየው ዘወትር በመጪው ጊዜ የሚፈጸምን ንድፍ አመላካች ነው። የሚያተኩረውም አሁን በተፈጠረው ሁኔታ ሳይሆን ወደፊት ሊፈጠር በሚችለው ላይ ነው። ዘወትር የሚናገረውም የሁኔታዎቹን እውንነት ነው። ለምሳሌ: "ብፁዓን ናቸው… እነሱ ወደፊት…" (ማቲ. 5:4-9)።

II. የግሥ ጊዜያት (ድምጸት)

ሀ. የግሥ ጊዜያት የሚገልጸው የግሥን ድርጊትና የባለቤቱን ግንኙነት ነው።

ለ. የአሁን ጊዜ ተራ፣ የሚጠበቅ፣ ያልተጋነነ መንገድን ይዞ ለማለት የሚፈልገውን ባለቤቱ የግሡን ድርጊት ሲከውን ነው።

ሐ. ተገብሯዊ ጊዜ ማለት ባለቤቱ የድርጊቱ ተቀባይ ሲሆን ማለት በውጭ አካል የተደረገውን። በውጭ አካል የሚፈጸመው ድርጊት በግሪክ አኪ ሲመለከት በሚከተለው መስተጻምራት እና አግባቦች ላይ ይታያል፡
1. ቀጥተኛ ሰዋዊ አድራጊ በ(hupo) ሲፈጸምና በስም፣ በተውላጠ ስምና በቅጽል የሚታይበት አግባብ ስከሰት (ማቲ. 1፡ 22፣ ሐዋ. 22:30)።
2. ሰዋዊ መካከለኛ ፈጻሚ በ(dia) በስም፣ በተውላጠ ስምና በቅጽል የሚታይበት አግባብ ሲከሰት (ማቲ. 1:22)።
3. ሰዋዊ ያልሆነ ፈጻሚ፣ ዘወትር በ(en) በቁሳቁሳዊ አግባብ።
4. አንዳንድ ጊዜ በሰዋዊ ሆነ ሰዋዊ ባልሆነ ፈጻሚ፣ በቁሳዊ አግባብ ብቻ።

መ. መካከለኛ ጊዜ ማለት ባለቤት የግሡን ተግባር ሲፈጽም እና እንዲሁም በቀጥታ በግሡ ድርጊት ላይ በቀጥታ ሲገባ ነው። ዘወትር ከፍ የተደረገ ሰዋዊ ፍላጎት የግሥ ድምጸት ተብሎ ይጠራል። ይህ አወቃቀር በተመሳሳይ መንገድ ለሐረጉ ወይም ለዓረፍተ ነገሩ ባለቤት አጽንዖት ይሰጣል። ይህ አወቃቀር በእንግሊዝኛ አይገኝም። እሱም ሰፋ ያለ የግሪክ ፍቺ እና ትርጉም አግባብ አለው። ለዚህ ዓይነት የሚሆኑ ጥቂት ምሳሌዎች፡
1. አነጻጻሪ — የባለቤቱ ቀጥተኛ ድርጊት በራሱ ላይ። ምሳሌ: "ራሱን ሰቀለ" (ማቲ. 27:5)።
2. የታሰበበት — ባለቤት ድርጊቱን ለራሱ ይፈጽማል። ምሳሌ: "ሰይጣን ራሱን እንደ ብርሃን መልአክ ይለውጣል" (2ኛ ቆሮ. 11:14)።
3. ባለ ሁለት ወገን — የሁለት ባለቤቶች ውስጣዊ ድርጊት። ምሳሌ: "እርስ በርሳቸው ተመካከሩ" (ማቲ. 26:4)።

III. አኳኋን (ወይም አገባብ)

ሀ. በኮኔ ግሪክ አራት አገባቦች አሉ። እነርሱም የግሥን እውነታዊ ግንኙነት ይጠቁማሉ፣ ይሄውም በተቻለ መጠን ጸሐፊው በራሱ ሐሳብ። አገባቦች በሁለት ሰፋፊ ምድቦች ይከፈላሉ፤ እውነታን የሚጠቁሙ (ጠቋሚ) እና በውስጥ ያለ አቅም ጠቋሚዎች (መሻታዊ ሁኔታ (አጠራጣሪ)፣ ትዕዛዝ አንቀጽ እና አማራጫዊ ናቸው።)

ለ. አመላካች አገባብ ሁነኛ አገባብ ሲሆን የተከናወነን ወይም ተከናውኖ የነበረን ማለትም ቢያንስ በጸሐፊው ልቦና የነበረን ለመግለጽ የሚያገለግል ነው። ይህም <u>ብቸኛው</u> የግሪክ አገባብ ሆኖ ትክክለኛን ጊዜ የሚገልጽ ነው፣ እዚህም ቢሆን ይህ ገጽታ ሁለተኛ ነው።

ሐ. ተያያዥ አኳኋን የሚገለጠው በምናልባታዊ የትንቢት ድርጊት ነው። አንድ ነገር ገና አልሆነም፣ ነገር ግን የመሆን ዕድል አለው። ከትንቢታዊ አመላካች ጋር በርካታ የሚጋራው አለው። ልዩነቱ መሻታዊው የሚገልጸው የተወሰነ ደረጃ ያለው አጠራጣሪነትን ነው። በእንግሊዝኛ ይህ ዘወትር "ይችላል፣" "ነበር፣" "ምናልባት፣" "ምናልባት።"

መ. አማራጫዊ ሁኔታ የሚገልጸው በንድፈ ሐሳባዊ ደረጃ ሊሆን የሚችለውን ነው። ከመሻታዊው አንድ ደረጃ ከእውነታ ቀደም ብሎ ይገኛል። አማራጫዊው አጠራጣሪነትን የሚገልጸው በተወሰኑ ሁኔታዎች ነው። አማራጫዊው በአዲስ ኪዳን አልፎ አልፎ ነው የሚገኘው። በጣም የታወቀው ድግግሞሻዊ አጠቃቀሙ የሚገኘው በታወቀው የጳውሎስ ሐረግ፣ "እንዲህስ አይሁን" (ኪጀቅ፣ "እግዚአብሔር አያርገው")፣ የሚለው አስራ አምስት ጊዜ (ሮሜ. 3:4፣ 6፣ 31፤ 6:2፣ 15፤ 7:7፣ 13፤ 9: 14፤ 11:1፣ 11፤ 1ኛ ቆሮ. 6:15፤ ገላ. 2:17፤ 3:21፤ 6:14) ጥቅም ላይ ውሏል። ሌሎች ምሳሌዎችም ተሰ. (?) 1:38፣ 20:16፣ ሐዋ. 8:20፣ እና 1ኛ ተሰ. 3:11።

ሠ. ትዕዛዛዊ ሁኔታ አጽንዖት የሚሰጠው ሊሆን የሚችል ትዕዛዝ ላይ ሆኖ አጽንዖቱ ግን በተናጋሪው ፍላጎት ላይ ነው። እሱም በፍቃድ ላይ የተመሠረተውን ብቻ አማራጭ አመላክቶ እንዲሁም በሌላው ሁኔታዊ አማራጭ ላይ ነው። ትዕዛዛዊ ሁኔታ በጸሎት እና በሦስተኛ መደብ ጥያቄዎች ላይ ልዩ አጠቃቀም አለው። እነዚህ ትዕዛዛት በአኪ የሚገኙት በአሁን እና በግብር ግሦች ነው።

ረ. አንዳንድ ሰዋሰዎች ቦዝ አንቀጽን እንደሌለኛው ሁኔታዊ ዐይነት ይመድቧቸዋል። እነዚህም በግሪክ አኪ የተለመዱ ናቸው፣ ብዙውን ጊዜ ግሳዊ ቅጽል በሚል። ከሚቀራረቡት ከዋናው ግሥ ጋር ተጣምረው ይተረጎማሉ። ቦዝ አንቀጽን ለመተርጎም የተለያየ ሰፋ ያለ አማራጭ አለ። እዚህ ላይ በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎችን መቃኘቱ ይበጃል። *መጽሐፍ ቅዱስ በሃያ ስድስት ትርጕሞች* በቤከር የታተመው ደኅና አድርጎ ይረዳል።

ሰ. የድርጊት አንቀጽ አመላካች፣ ሁነኛ ወይም "ያልተለየ" አንድን ሁኔታ (ድርጊት) ለመመዝገብ ይሆን ነበር። ማንኛውንም ጊዜ፣ ድምጸት ወይም የተለየ ትርጓሜያዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ይህም ዋነኛው ጸሐፊ ለማለት የፈለገውን ነው።

IV. የግሪክኛ ችሎታ ለሌለው ሰው የሚከተሉት የጥናት መርጃዎች አስፈላጊውን መረጃ ሊሰጡት ይችላሉ፡

ሀ. ፍሪበርግ፣ ባርባራ እና ጢሞቲ። *የተተነተነ የግሪክ አዲስ ኪዳን*። ግራንድ ራፒድስ፡ ቤከር፣ 1988።

ለ. ማርሻል፣ አልፍሬድ። *ኢንተርሳይነር (መስመራዊ) የግሪክ እንግሊዝኛ አዲስ ኪዳን*። ግራንድ ራፒድስ፡ ዞንደርቫን፣ 1976።

ሐ. ሞውንሲ፣ ዊሊየም ዲ. *የግሪክ አዲስ ኪዳን ቃላታዊ ትንታኔ*። ግራንድ ራፒድስ፡ ዞንደርቫን፣ 1993።

መ. ጭምቅ ሐሳቦች፣ ሬይ. *የግሪክ አዲስ ኪዳን ጠቀሜታዎች*። ናሽቪሊ፡ ብሮድማን፣ 1950።

ሠ. በከፍተኛ ትምህርት ተቀባይነት ያለው የኮኔ ግሪክ የተልእኮ ኮርስ ከሞዲ መጽሐፍ ቅዱስ ተቋም፣ ቺካጎ፣ IL ይገኛል።

V. ስሞች

ሀ. ከአገባብ አኳያ፣ ስሞች የሚመደቡት በየጉዳዩ ነው። ጉዳዩ ከስሙ አኳያ መልኩ የተቀየረ ሲሆን ይህም ከግሡ እና ከሌሎቹ የዓረፍተ ነገሩ ክፍሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ያመለክታል። በኮኔ ግሪክ ብዙዎቹ የጉዳዮ ተግባራት የሚጠቆሙት በመስተጻምሮች ነው። የጉዳዩ መልክ የተለያዩ በርካታ ግንኙነቶችን እንደመግለጡ መጠን፣ መስተጻምሮች ለእነዚህ ተግባራት የሚሆኑ ግልጽ መለያዎችን ያስቀምጣሉ።

ለ. የግሪክ ጉዳዮች በሚከተሉት ስምንት መንገዶች ይመደባሉ፡

1. ሳቢዎቹ ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውሉት ለስያሜ ሲሆን ዘወትርም የዓረፍተ ነገሩ ወይም የሐረጉ ባለቤት ይሆናሉ። በተጨማሪም ስም አመልካች ግሦችን እና ቅጽሎችን ከአያያዥ ግሦች ጋር "የመሆን" ወይም "የመኖር" ለመጠቀም ያስችላል።
2. አገናዛቢ ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውሉት የተለየ ባሕርይ ወይም ይዘት ለቃሉ እና ከእሱም ጋር ለተጎዳኙት የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ ነው። "ምን ዓይነት?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "የ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
3. የስም፣ የተውላጠ ስምና የቅጽል ጉዳዮች ተመሳሳይ የሆነ መልኩ የተቀየረ እንደ አገናዛቢ ያለ ይጠቀማል፣ ነገር ግን መለያየትን ነው የሚያሳየው። ዘወትር የሚገለጸውም በጊዜ፣ በቦታ፣ በምንጭ፣ በመነሻ ወይም በደረጃ ያለውን ልዩነት ለማሳየት ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "ከ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
4. ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ (የስም) ጥቅም ላይ የሚውለው ግላዊ መሻትን ነው። ይህም አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ግጽታዎችን ያሳያል። ይህም ዘወትር ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "ወደ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
5. አቅጣጫዊ ጉዳይ ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ተመሳሳይ የስም፣ የተውላጠ ስምና የቅጽል ጉዳዮች ዓይነት ሲሆን፣ ነገር ግን የሚያሳየው አቅጣጫን በቦታ፣ በጊዜ፣ ወይም በአመክኖአዊ ወሰን ነው። ብዙውን ጊዜም በእንግሊዝኛው መስተጻምር "በውስጥ፣ በላይ፣ በ፣ በመሐል፣ በጊዜ፣ በ፣ በላይ እና በላይ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
6. መገልገያዊ ጉዳይ ቀጥተኛ ካልሆነው ተሳቢ እና ለመገልገያዊ ጉዳዮች መልኩ የተቀየረ ተመሳሳይ ነው። እሱ የሚገልጸው ምንነቱንና መስተጋብሩን (ተያያዥነቱን) ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "በ"ን ወይም "ጋር"ን በመጠቀም ይታወቃል።
7. ቀጥተኛ ባለቤታዊ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የሚውሉት የአንድን ድርጊት ድምዳሜ ለመግለጽ ነው።ዋናው ጠቀሜታው ለቀጥተኛ ባለቤት ነው። "ምን ያህል ሩቅ?" ወይም "እስከ ምን ድረስ?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል።
8. የስም መልኮች ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጥተኛ ባለቤትን ነው።

VI. መስተዋድድ እና አያያዦች

1. ግሪክ በጣም ቁልጭ ያለ ቋንቋ ነው፣ ምክንያቱም በርካታ አያያዦች ስላሉት። እነሱም ሐሳቦችን ያያይዛሉ (ሐረጎች፣ ዓረፍተ ነገሮች፣ እና አንቀጾችን)። በጣም የተለመዱ ስለሆኑ፣ በሚቀሩበት ጊዜ በተለይ በትንታኔ ጊዜ ትርጉም ይኖረዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ መስተዋድዶች እና አያያዦች የጸሐፊውን ሐሳብ አቅጣጫ ያመላክታሉ። ብዙውን ጊዜ ጸሐፊው በትክክል ምን ለማለት እንደፈለገ ለመወሰን በጣም ጠቃሚ ናቸው።
2. ከዚህ ቀጥሎ የጥቂት መስተዋድዶች እና አያያዦች እና ትርጉሞቻቸው ይቀርባል፣ (ይህ መረጃ ባብዛኛው የተገኘው ከ ኤች. ኢ. ዳና እና ጆሊየስ ኬ. ማንቲ *የግሪክ አዲስ ኪዳን የሰዋሰው መመሪያ)* ላይ ነው።

ሀ. ጊዜ አያያዦች

1) epei፣ epeid e፣ hopote፣ hote፣ hotan (ተሳቢ) - "መቼ"
2) *hoes*፣ - "በ… ጊዜ"

3) *hotan፣ epan* (ተሳቢ) – “መቼም ቢሆን”
4) *hoes፣ achiri፣ mechri* (ተሳቢ) – “እስከ… መቼ”
5) *priv* (ንዑስ አንቀጽ) - “በፊት”
6) *hos* - “ከ… ጀምሮ” “መቼ” “እንደ”

ለ. አመክኖአዊ አያያዦች

1) ተግባር
   a) *hina* (ተሳቢ)፣ *hopos* (ተሳቢ)፣ hos - “እንደ…መሆኑ” “እንደ”
   b) *hoste* (አቀላጣፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) “እንደ”
   c) *pros* (አቀላጠፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) ወይም eis (አቀላጠፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) “እንደ”
2) ውጤት (በሰዋሰዋዊ ቅርጾች ተግባርና ውጤት መካከል የቀረበ ተወራራሽነት አለ)
   a) (ንዑስ አንቀጽ ይህ በጣም የተለመደ ነው) - “እንደ…መሆኑ” “እንደ”
   b) *hiva* (ተሳቢ) - “ስለሆነም”
   c) *ara*- “ስለዚህ”
3) መንሥኤ ወይም ምክንያት
   a) (ምክንያት/መነሻ ወይም ሳቢያ/ድምዳሜ) – “ለ፣” “ምክንያት”
   b) *dioti፣ hotiy* - “ምክንያቱም”
   c) *epei፣ epeide፣ hos*- “ከ… ጀምሮ”
   d) (ከ ተሳቢ) እና (አቀላጣፊ ተሳቢ ንዑስ አንቀጽ) “ምክንያት”
4) ተገቢ አስተያየት
   a) *ara፣ poinum፣ hoste*-“ስለሆነም”
   b) *dio* (ጠንካራው ምርመራዊ ተገቢ አስተያየት) – “በዚህም ምክንያት)
   c) *oun* “ስለሆነም” “ስለዚህ” “ከዚያም” “በዚህም ሳቢያ”
   d) *toinoun* “በመሠረቱ”
5) ተጻራሪ ወይም ተቃርኖ
   a) *alla* (ጠንካራ ተቃርኖ) - “ግን፣” “በተቀር”
   b) *de* - “ግን፣” “ቢሆንም፣” “ገና፣” “በሌላ በኩል”
   c) *kai* - “ግን”
   d) *mentoi፣ oun* - “ቢሆንም”
   e) *plên* “ቢሆንም ግን” (በአብዛኛው ሉቃስ ላይ)
   f) *oun* - “ሆኖም”
6) አወዳዳሪ
   a) *hôs*፣ (አወዳዳሪ ሐረጎችን ያሳያል)
   b) *kata* (በድብልቆች katho፣ kathoti፣ kathôsper፣ kathaper)
   c) *hosos* (በዕብራይስጥ)
   d) ê – “ከ…ይልቅ”
7) ተከታታይ ወይም ተለጣጣቂ
   a) *de* - ”እና” ”አሁን”
   b) *kai* - ”እና”
   c) *tei* - ”እና”
   d) *hina፣ oun* - ”እንደ”
   e) *oun* ”ከዚያም” (በዮሐንስ)

ሐ. ግነታዊ አግባብ

1) *alla* - ”በርግጠኝነት” ”አዎን” ”በእውነቱ”
2) *ara* - ”በርግጥ” ”በእውነቱ ” ”በርግጥ ”
3) *gar* - ”ግን በርግጥ” ”በርግጠኝነት” ”በርግጥ ”
4) *de* - ”በርግጥ”
5) *ean* - ”እንኳን”
6) *kai* - ”እንኳን” ”በርግጥ” ”በእውነቱ ”
7) *mentoi* ”በርግጥ”
8) *oun* ”በርግጥ” ”እንደ ምንም”

VII. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች

ሀ. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር አንድ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ሐረጎችን የያዘ ነው፡፡ ይህ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ለትርጓሜ ይረዳል፡፡ ምክንያቱም እሱ ነባሩ ግሥ ድርጊቱን ያደረገበትን ወይም ያላደረገበትን ሁኔታዎች፣ ምክንያቶች ወይም መንሥኤዎች

ስለሚያሳይ ነው። አራት ዓይነት ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉ። አካሄዳቸውም ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ሊል ለፈለገው እውነት ወደ ሆነው መሻት ነው።

ለ. አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር የሚገልጸው ድርጊትን ወይም ከጸሐፊው አስተሳሰብ አኳያ ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታመንበትን ወይም ሊል ከፈለገው አንጻር ነው— ምንም እንኳ "እንደሁ" በሚል ቢገለጥም። በብዙ ጽሑፎች "ከ… ጀምሮ" በሚል ቢተረጎምም (ማቲ. 4:3፤ ሮሜ.8:31)። ቢሆንም ይህ ግን ሁሉም አንደኛ መደቦች ከእውነታ ጋር ትክክል ናቸው ማለት አይደለም። ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉት አንድን ነጥብ በክርክራዊ መንገድ ወይም ስህተት ያለበትን አጉልቶ በማሳየት ነው (ማቲ. 12፡27)።

ሐ. ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ብዙውን ጊዜ "ከሐቅ ጋር ተጻራሪ" በመባል ይታወቃል።እሱም ነጥቡን ለመጥቀስ ትክክል ያልሆነን ነገር ወደ እውነት ያመጣል። ለምሳሌ፡

1. "በርግጥ ነቢይ ቢሆን ኖሮ፣ አይደለም እንጂ፣ ማን እና እንዴት ያለች ሴት እንደያዘችው ባወቀ ነበር፣ ግን አይደለም" (ተሰ. 7፡39)።
2. "ሙሴንስ ብታምኑት፣ አታምኑትም እንጂ እኔን ታምኑኝ ነበር፣ ግን አታምኑም" (ዮሐንስ 5፣46)።
3. "ሰዎችን ባስደስት ኖሮ ግን፣ አላደርገውም እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ ጨርሶ ባልሆንኩን ነበር፣ ነገር ግን ነኝ" (ገላ. 1፡10)

መ. ሦስተኛ መደብ ሊሆን የሚችል የትንቢት ድርጊትን ያመላክታል፡፡ ዘወትር የድርጊቱን የመሆን ግምት ያስቀምጣል፡፡ ዘወትርም ሊደርስ የሚችልን ያሳያል፡፡ የነባሩ ግሥ ድርጊት ርግጠኛ ባልሆነ መልኩ በሐረጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ ምሳሌዎች ከ1ኛ ዮሐንስ፡ 1፡6-10፤2፡4፣6፣15፣20፣21፣24፣29፤ 3፡21፤ 4፡20፤ 5፣14፣16፡፡

ሠ. አራተኛው መደብ ሊደርስ ከሚችል ራቅ ያለ ነው፡፡ በአኪ እምብዛም አይገኝ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የተሟላ አራተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር አይገኝም፣ ሁለቱንም የሁኔታዊ ክፍሎች መግለጫ ሊያሟላ የሚችል፡፡ ለከፊል አራተኛ መደብ ምሳሌ የሚሆን የመክፈቻ ሐረግ በ1ኛ ጴጥ. 3፡14፡፡ ለከፊል አራተኛ መደብ መዝጊያ ሐረግ የሚሆን ምሳሌ ሐዋ. 8፡31፡፡

VIII. ክልክሎች

ሀ. የአሁን ጊዜ ያልተጠናቀቀ፣ እኔ በሚል አገባብ (ግን የተለየ ያልሆነ) በሂደት ላይ ያለ ድርጊት መቆሙን አጽንዖት ይሰጣል፡፡ ጥቂት ምሳሌዎች፡ "ሀብታችሁን በምድር ላይ ማከማቸታችሁን አቁሙ…" (ማቲ. 6፡19)፤ "ስለ ሕይወታችሁ መጨነቃችሁን አቁሙ…" (ማቲ. 6፡25)፤ "ሥጋችሁን ለኃጢአት በመስጠት ክፉ የመፈጸሚያ መሣርያ አታድርጉ…" (ሮሜ. 6፡13)፤ "የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ ማሳዘን አይኖርባችሁም…" (ኤፌ. 4፡30)፤ እና ''በወይን ጠጅ አትስከሩ…'' (5፡18)

ለ. ያልተጠናቀቀ ድርጊት እኔ በሚል አገባብ "አንድን ድርጊት ወይም አትጀምር ወይም አትፈልም" ለሚለው አጽንዖት ይሰጣል። ምሳሌዎች፡ "እንደዛለማድረግ እንኳ አታስቡ…" (ማቲ. 5፡17)፤ "አትጨነቁ…" (ማቲ. 6፡31)፤ "አሳፋሪ መሆን አይኖርባችሁም…" (2ኛ ጢሞ. 1፡8)።

ሐ. ጥንድ አሉታ በተያያዥ አኳኋን የሚገለጠው በእጅጉን አጽንዖታዊ አሉታ ነው። "ፈጽሞ በፍጹም" ወይም "በምንም ምክንያት ቢሆን" ምሳሌዎች፡ "እሱ ፈጽሞ፣ በፍጹም ሞትን አያይም" (ዮሐንስ 8፡51)፤ "እኔ በፍጹም፣ ፈጽሞ…" (1ኛ ቆሮ. 8፡13)።

IX. መስተአምር

ሀ. በኮኔ ግሪክ የተወሰነ መስተአምር "ው" (the) ከእንግሊዝኛው ጋር ተመሳሳይ ጠቀሜታ ነው ያለው። ዋነኛው ተግባሩ "አመላካችነት" ሆኖ ለሚመለከተው ቃል፣ ስም ወይም ሐረግ አጽንዖት ማሰጠት ነው። አጠቃቀሙ በአዲስ ኪዳን ከጸሐፊ ጸሐፊ ይለያያል። የተወሰነው መስተአምር ለሌሎች ተግባራትም ሲውል፡

1. እንደ አመላካች ተውላጠ ስም ለተቃርኗዊ አግባብ፤
2. ቀደም ሲል ለተጠቀሰ ባለቤት ወይም ሰው እንደ ማጣቀሻ ምልክት
3. የዓረፍተ ነገሩን ባለቤት በአያያዥ ግሥ በሚገልጽ በሆነ መንገድ። ምሳሌዎች፡ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣" ዮሐንስ 4፡24፤ "እግዚአብሔር ብርሃን ነው፣" 1ኛ ዮሐንስ 1፡5፤ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣" 4፡8፣16።

ለ. የኮኔ ግሪክ እንደ እንግሊዝ "አንድ" (a እና an) ዓይነት የተወሰነ መስተአምር የለውም፡፡ የዚህ ያልተወሰነ መስተአምር አለመኖር ማለት፣

1. በአንድ ነገር ባሕርይ ወይም ዓይነት ላይ ያተኩራል፡፡
2. በአንድ ነገር ምድብ ላይ ያተኩራል፡፡

ሐ. የአኪ ጸሐፍት በስፋት የሚለያዩት በመስተአምር አጠቃቀማቸው ነው፡፡

X. በግሪክ አዲስ ኪዳን አጽንዖት የሚታዩባቸው መንገዶች

ሀ. በአዲስ ኪዳን አጽንዖት የሚሰጥባቸው ስልቶች ከጸሐፊ ጸሐፊ ይለያያሉ፡፡ ከሁሉም የተሻሉት ቋሚ እና መደበኛ ጸሐፍት ሉቃስ እና የዕብራውያን ጸሐፊ ናቸው፡፡
ለ. ቀደም ሲል ያልተጠናቀቀ ድርጊት የአሁን አመላካች መደበኛና ለአጽንዖት ያለተለየ ዳሩግን ሌላ ማንኛው ግሥ፣ ድምጸት ወይም አኳኋን ትርጉማዊ ጠቀሜታ እንዳለው ተመልክተናል፡፡ ይህም ማለት ያልተጠናቀቀ ድርጊት የአሁን አመላካች ተገቢያዊ በሆነ የሰዋሰው ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውልም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ፡ ሮሜ. 6፡10 (ሁለት ጊዜ)
ሐ. በኮኔ ግሪክ የቃላት ቅደም ተከተል
1. የኮኔ ግሪክ ተለዋዋጭ የሆነ የቃላት ቅርጽ ያለው ቋንቋ ሲሆን እንደ እንግሊዝኛው የቃላት ሥርዓት ሳይሆን ራሱን የቻለ ነው፡፡ ስለዚህም ጸሐፊው መደበኛውን የቃላት ቅደም ተከተል እነዚህን ለማሳየት ይለዋውጠዋል...
   ሀ. ጸሐፊው ለአንባቢው አጽንዖት እንዲሰጥ የፈለገውን
   ለ. ጸሐፊው ለአንባቢው ያስገርማል ብሎ ያሰበውን
   ሐ. ጸሐፊው በጥልቀት የተሰማውን ጉዳይ
2. ተገቢው የግሪክ የቃላት ቅደም ተከተል ጉዳይ ገና እልባት አላገኘም፡፡ ቢሆንም፡ ይሆናል የብሎ የታሰበው ተገቢ ቅደም ተከተል
   ሀ. ለአያያዥ ግሦች
      (1) ግሥ
      (2) ባለቤት
      (3) ማሟያ
   ለ. ለተሻጋሪ ግሦች
      (1) ግሥ
      (2) ባለቤት
      (3) ተሳቢ
      (4) ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ
      (5) መስተጻምራዊ ሐረግ
   ሐ. ለስማዊ ሐረጎች
      (1) ስም
      (2) አጎላማሽ
      (3) መስተጻምራዊ ሐረግ
3. የቃላት ሥርዓት ለማብራራት (ለትርጓሜ) ፍጹም ጠቃሚ ነጥብ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡
   ሀ. "ለእኔና ለበርናባስ የኅብረት ቀኝ እጃቸውን ሰጡን" (ገላ. 2፡9)። "የኅብረት ቀኝ እጃቸውን" ተከፍሎ ጠቀሜታውን ለማመልከት ከፊት ለፊት ሆኗል።
   ለ. "ከክርስቶስ ጋር" (ገላ. 2፡20)፣ ከፊት ሆኗል። ሞቱ ማዕከላዊ ነው።
   ሐ. "ጥቂት በጥቂት እና በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ነበር" (ዕብ. 1፡1)፣ ከፊት ሆኗል። ይህም እግዚአብሔር ራሱን እንዴት እንደገለጠ ነው አከራካሪ የሆነው እንጂ የመገለጥን እውነት በመቃረን አይደለም።

መ. ዘወትር የተወሰነ መጠን ያለው አጽንዖት ያሳያል
1. የተውላጠ ስሞች መደጋገም፣ በግሡ በተለያየ መልኩ ቀደም ሲል የነበረው። ምሳሌ፡ "እኔ፣ ራሴ፣ ከእናንተ ጋር በርግጥ እሆናለሁ..." (ማቴ. 28፡20)።
2. በቃላት፣ በሐረጋት፣ በዐቢይ ሐረጋት ወይም በዓረፍተ ነገሮች መካከል መኖር የሚገባው መስተጻምር ወይም ሌሎች አያያዥ ቃላት አለመኖር። ይህም (asyndeton) ("ያልታሰረ") በመባል ይታወቃል። አያያዡ ቃል እንዲኖር ተጠብቆ መቅረቱ ትኩረትን ይስባል። ለምሳሌ፡
   ሀ. የብፁአን ትሩፋቶች (ሰባቱ)፣ ማቴ. 5፡3 (ዝርዝሩን ለማግነን)
   ለ. ዮሐንስ 14፡1 (አዲስ ርዕስ)
   ሐ. ሮሜ. 9፡1 (አዲስ ክፍል)
   መ. 2ኛ ቆሮ. 12፡20 (ዝርዝሩን ለማግነን)
3. በተመለከተው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኝ የቃላት ወይም የሐረጎች መደጋገም። ምሳሌ፡ "ለክብሩ ምስጋና" (ኤፌ. 1፡6፣ 12 እና 14)፡፡ ምስጋናው ጥቅም ላይ የዋለው የእያንዳንዱን የሥላሴ አካል ሥራ ለማሳየት ነው፡፡
4. ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጥ ወይም ቃል (ድምጽ) በቃላት በካከል የሚኖረው ሚና
   ሀ. ተለዋጭ ቃል - ስም አይጠሬ ቃላትን ቀይሮ በሌላ መጠቀም ለምሳሌ "እንቅልፍ" ን ለሞት (ዮሐንስ 11፡11-14) ወይም "እግሮች" ለወንድ ብልት (ሩት 3፡7-8፤ 1ኛ ሳሙ. 24፡3)፡፡
   ለ. ጎናዊ አገላለጽ - ለእግዚአብሔር ስም ቃላትን መለወጥ፣ ምሳሌ "የሰማይ መንግሥት" (ማቴ. 3፡21) ወይም "ከሰማይ የሆነ ድምፅ" (ማቴ. 3፡17)፡፡
   ሐ. ዘይቤያዊ አገላለጾች
      (1) የማይቻል ግነት (ማቴ. 3፡9፤ 5፡29-30፤ 19፡24)፡፡
      (2) የተለዩ ግነታዊ አገላለጾች (ማቴ. 3፡5፤ ሐዋ. 2፡36)፡፡
      (3) ሰዋዊ ዘይቤዎች (1ኛ ቆሮ. 15፡55)፡፡
      (4) ውስጠ ወይራ (ገላ. 5፡12)

(5) ቅኔያዊ አንቀጾች (ፊሊ. 2፡6-11)፡፡
(6) በቃላት መካከል ያሉ ድምፆች
(ሀ) "ቤተ ክርስቲያን"
i. "ቤተ ክርስቲያን" (ኤፌ. 3፡21)
ii. "ጥሪ" (ኤፌ. 4፡1፣4)
iii. "የተጠራ" (ኤፌ. 4፡1፣4)
(ለ) "ነጻ"
i. "ነጻ ሴት" (ገላ. 4፣31)
ii. "ነጻነት" (ገላ. 5፡1)
iii. "ነጻ" (ገላ. 5፡1)

መ. ዘይቤአዊ ቋንቋ - ብዙውን ጊዜ ባህላዊ እና የተለየ ቋንቋን (ዘዬ) የሚያሳይ ነው፡
1) ይህ የ "ምግብ" ዘይቤአዊ አጠቃቀም ነበር (ዮሐንስ 4፡31-34)፡፡
2) ይህ የ "መቅደስ" ዘይቤአዊ አጠቃቀም ነበር (ዮሐንስ 2፡19፤ ማቴ. 26፡61)፡፡
3) ይህ የዕብራይስጥ የማወዳደሪያ ፈሊጥ ነው፡ "ጠላ" (ዘፍ. 29፡31፤ ዘዳ. 21፡15፤ ተሰ. 14፡36፤ ዮሐንስ 12፡25፤ ሮሜ. 9፡13)
4) "ሁሉም" ወይም (በተቃርኖ) "ብዙ፡፡" ኢሳ. 53፡6 ("ሁሉም")ን ከ53፡11 እና 12 ("ብዙ") ጋር አነጻጽር፡፡ ቃላቶቹ እንደ ሮሜ. 5፡18 እና 19 እንደታየው ተመሳሳይነትን ያመለክታሉ፡፡

5. በነጠላ ቃል ምትክ ሙሉ ሐረጋዊ ቋንቋ መጠቀም፡፡ ምሳሌ፡ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡"
6. የስሞች፣ የቅጽሎች፣ የተውሳከ ግሦች (የርስ በርሱ) ልዩ አጠቃቀም
ሀ. መስተአምሩ (ጠባያዊ ቦታ) ሲይዝ "አንድ ዓይነት" በሚል ይተረጎማል፡፡
ለ. ያለ መስትአምር (በአንቀጹ ቦታ) ሲይዝ አረጋጋጭ አገናዛቢ ተውላጠ ስም በሚል ይተረጎማል— "ራሱ፣" "ራሷ፣" ወይም "ራሱ፡፡"

ሠ. ግሪክኛ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ አጽንዖትን በተለያየ መንገድ ሊረዳ ይችላል፡
1. በትንተናዊ ቃላት አጠቃቀም፣ ማለትም በግሪክኛውና በእንግሊዝኛው ጽሁፍ በየመስመሩ በተጻፈው፡፡
2. የእንግሊዝኛን ትርጓሜዎች በማነጻጸር፣ በተለይም ከተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ ሐሳቦች አኳያ። ምሳሌ፡ "የቃል በቃል" ትርጓሜዎችን በማነጻጸር (ኪጀት፣ አኪጀት፣ አመት፣ አአሶመቅ፣ የተመት፡ አየተመት) ከ "ታደሰው አቻ" (ዊሊያምስ፣ አዓአት፣ አእመቅ፣ የተእመቅ፣ ኢበቅ፣ አኢመቅ፣ አእት ?እት)፡፡ ሻል ያለ ማብራሪያ ደግሞ *መጽሐፍ ቅዱስ በሃያ ስድስት ትርጉሞች* በቤከር የታተመው ላይ ይገኛል፡፡
3. ባለ *አጽንዖታዊ መጽሐፍ ቅዱስ* በጆሴፍ ብራያንት ሮዘርሃም (ክሪገል፣ 1994)
4. የጥሬ ትርጉም አጠቃቀም
ሀ. *የአሜሪካ መደበኛ ትርጉም* የ1901
ለ. *ለወጣቶች ተስማሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም* በሮበርት ያንግ (ጋርዲያን አሳታሚ፣ 1976)፡፡

ለተገቢ ትርጓሜ ሰዋሰዋዊ ጥናት አስፈላጊ ነው፣ አስቸጋሪ ቢሆንም፡፡ እነዚህ አጠር ያሉ መግለጫዎች፣ አስተያየቶች እና ምሳሌዎች የተፈለጉት ግሪክኛ አንባቢ ያልሆኑ ሰዎችን ለማበረታታትና በቅጹ ውስጥ የተመለከቱትን ሰዋሰዋዊ መግለጫዎች እንዲያገናዝቡ ነው፡፡ በርግጥ እነዚህ መግለጫዎች ቀለል ብለው ነው የቀረቡት፡፡ ቀኖናዊና ሊተጣጠፍ በማይችል መልኩ ጥቅም ላይ መዋል አይኖርባቸውም፤ ዳሩግን ወደ አዲስ ኪዳን አገባብ የተሻለ መረዳት የሚወስዱ ደረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መግለጫዎች አንባቢዎች የሌሎችን የጥናት መርጃዎች አስተያየቶችን ለምሳሌም፣ የአዲስ ኪዳን ስልታዊ ሐተታዎችን ለመረዳት ያስችሏቸዋል፡፡

የራሳችንን ትርጓሜ ከመጽሐፍ ቅዱስ በምናገኛቸው ጽሑፎች ላይ በመመሥረት ልንመረምረው ይገባል፡፡ ሰዋሰው በጣም ከሚረዱን ዓይነቶች መካከል አንዱ ነው፤ ሌሎች ዓይነቶች ደግሞ እንደ ታሪካዊ መቼት፣ ሥነጽሑፋዊ ጽሑፎች፣ የየዘመኑ የቃላት አጠቃቀም፣ እና አቻዊ አንቀጾች ይገኙበታል።

# ተጨማሪ መግለጫ ሁለት
# ጽሑፋዊ ትንተና

ይህ ርዕሰ ጉዳይ በዚህ መልኩ የቀረበው በዚህ ሐተታ ውስጥ የሚገኙትን ጽሑፋዊ ማስታወሻዎች ለማብራራት ነው። ቀጣዩ ማውጫ ጥቅም ላይ ይውላል።

I. የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ጽሑፋዊ ምንጮች
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   ለ. ሐዲስ ኪዳን
II. "የመለስተኛ ትንተና" ወይም "ጽሑፋዊ ትንተና" ተብሎ የሚጠራው ንድፈ- ሐሳባዊ ችግሮች አጭር ማብራሪያ
III. ለተጨማሪ ንባብ የተጠቀሱ ምንጮች

I. የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ጽሑፋዊ ምንጮች

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. ማሶረቲክ ጽሑፍ (ማጽ) - የዕብራይስጥ ተናባቢ ጽሑፍ የተቀናበረው በራቢ አቂባ በ100 ዓ.ም ነው። አናባቢው የሚያመለክተው የአነጋገር ዘዬን፣ የህዳግ ማስታወሻዎችን ሥርዓተ- ነጥብ እና አስረጅ ነጥቦች ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም መካተት ተጀምሮ በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም የተጠናቀቀው ነው። የተከናወነውም የአይሁድ ሊቃውንት ክፍል ከሆኑት ማሶሬተስ በሚባሉት ነው። የተጠቀሙበትም የጽሑፍ ዓይነት፣ በሚሽናህ፣ ታልሙድ፣ ታርጉምስ፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት አንድ ዓይነት ነው።
2. ሴፕቱዋጊንት (ሰባ) - ከባህል አኳያ ሴፕቱዋጊንት የተጻፈው በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት ሲሆን በ70 ቀናት ለአሌክሳንደሪያ ቤተ-መጻሕፍት ሆኖ በንጉሥ ፕቶለሚ 2ኛ (285-246 ቅ.ል.ክ) ነው። ትርጉሙ የተዘጋጀው ምናልባት በአሌክሳንደሪያ በሚኖሩ የአይሁድ መሪዎች ጥያቄ ሊሆን ይችላል። ይህ ልምድ የመጣው፣ "ከአሪስታስ መልእክት" ነው። ሰባ የተመሠረተው በተደጋጋሚ ከዕብራይስጥ ጽሑፋዊ ባህል ከራቢ አቂባ (ማጽ) በተለየ መልኩ ነው።
3. የሙት ባሕር ጥቅሎች (ሙባጥ) - የሙት ባሕር ጥቅሎች የተጻፉት በሮማ ቅ.ል.ክ ባለው ጊዜ (200 ቅ.ል.ክ እስከ 70 ዓ.ም) ሲሆን በአይሁድ የተለዩ ክፍሎች በሆኑ "ኤሰንስ" በተባሉ ተለይዎች ነው። የዕብራይስጥ የብራና ጽሑፎች የተገኙት፣ በሙት ባሕር አካባቢ በበርካታ ቦታዎች ሲሆን፣ ከሁለቱም ማለት ከማጽ እና ከሰባ በተለየ መልኩ የዕብራይስጥ ጽሑፋዊ ቤተሰብ ናቸው።
4. የእነዚህ ጽሑፎች ንጽጽር፣ ተርጓሚዎች ብሉይ ኪዳንን እንዲረዱት እንዴት እንደሚረዳ ጥቂት የተወሰኑ ምሳሌዎችን ስንመለከት
   ሀ. ሰባው ተርጓሚዎችንና ሊቃውንትን ማጽ (ማሲኒክ ጽሑፍ) ይገነዘቡ ዘንድ ረድተዋቸዋል
      (1) ሰባ በኢሳ. 52፡14፣ "ብዙዎች <u>በእሱ</u> ይደነቁበታል።"
      (2) ማጽ በኢሳ. 52፡14፣ "ብዙዎች <u>በአንተ</u> ይገረሙ ነበር"
      (3) በኢሳ.52፡15 ተውላጠ ስሙ ልዩነቱ በሰባ ላይ ያለው ተረጋግጧል
         (ሀ) ሰባ፣ "ስለሆነም ብዙ ሕዝቦች በእሱ ይደነቁበታል"
         (ለ) ማጽ፣ "እሱ ብዙ ሕዝቦችን ይረጫል"
   ለ. ሙባጥ (ሙት ባሕር ጥቅሎች) ተርጓሚዎችንና ሊቃውንትን ማጽ (ማሲኒክ ጽሑፍ) ይገነዘቡ ዘንድ ረድተዋቸዋል
      (1) ሙባጥ በኢሳ. 21፡8፣ "እናም ነቢዩ ጮኸ፣ በቆምኩበት መጠመቂያው ማማ..."
      (2) ማጽ በኢሳ. 21፡8፣ "እናም ጬኽኩ አንበሳው! ጌታዬ፣ ሁልጊዜ በመጠበቂያው ማማ ላይ ቆሜያለሁ ቀኑን..."
   ሐ. ሁለቱም ሰባ እና ሙባጥ ኢሳ. 53፡11ን ለማብራራት ረድተዋል
      (1) ሰባ እና ሙባጥ፣ "ከነፍሱ መከራ በኋላ ብርሃንን ያያል፣ ይደሰታል"
      (2) ማጽ፣ "ያያል... ከነፍሱ መከራ በኋላ፣ ይደሰታል"

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ከ5፣300 በላይ የእጅ ጽሑፎች ከግሪክ አዲስ ኪዳን በሙሉ ወይም በከፊል ጠፍተዋል። 85 የሚሆኑት በፓፒረስ የተጻፉ ሲሆኑ 268 ደግሞ በቁም ጽሕፈት የተጻፉ የብራና ጽሑፎች ናቸው። ቆይቶም፣ ወደ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ቅጥልጣይ ጽሑፍ እየተስፋፋ መጣ። የግሪክ ጽሑፎች የተጻፉት በቁጥር 2700 ይሆናሉ። በተጨማሪም 2100 የሚሆኑ ቅጂዎች የቅዱሳት መጻሕፍት ጽሑፎች ዝርዝር ለአምልኮ የሚሆኑ ሌክሽናሪስ ብለን የምንጠራቸው አሉ።
2. 85 የሚሆኑት የግሪክ የእጅ ጽሑፎች የአዲስ ኪዳንን የተወሰኑ ክፍሎች የያዙትና በፓፒረስ ላይ የተጻፉት ሙዝየሞች ውስጥ ተቀምጠዋል። አንዳንዶቹ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ያስቆጥራሉ፣ ነገር ግን አብዛኞቹ የሦስተኛውና የአራተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ናቸው። ከእነዚህ ጽሑፎች አንዳቸውም የተሟላ አዲስ ኪዳንን አልያዙም። እነዚህ ጥንታዊ የአዲስ ኪዳን ቅጂዎች ናቸው ማለት ግን በራሱ ጥቂት ልዩነት አላቸው ማለት አይደለም። አብዛኞቹ የእነዚህ ቅጂዎች ለአካባቢው ጥቅም ይውሉ ዘንድ በችኮላ የተጻፉ ናቸው። በሂደቱ ላይ ጥንቃቄ አልነበረም። በመሆኑም ብዙ ልዩነቶች አሏቸው።
3. ኮዴክስ ሲናይቲከስ፣ በዕብራይስጥ ፊደል ( ) (አሌፍ) ወይም (01) በመባል የሚታወቀው፣ በቅዱስ ካተሪኒ ገዳም በሲና ተራራ በቲስቼንዶርፍ ተገኝቷል። ዓመቱም ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ሲሆን በውስጡም የብኪን ሰባ እና የግሪክን አኪ ይዟል። እሱም "የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ" ዓይነት ነው።

4. ኮዴክስ አሌክሳንድሪነስ፣ “ሀ” ወይም (02) በመባል የሚታወቀው፣ የ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ በአሌክሳንደሪያ ግብፅ የተገኘው፣
5. ኮዴክስ ቫቲካነስ፣ “ለ” ወይም (03) በመባል የሚታወቀው፣ በሮም በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት የተገኘ ሲሆን፣ ዓመቱም ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓ. ም እኩሌታ ነው። በውስጡም የብሉይ ኪዳን ሰባ እና የግሪክን አዲስ ኪዳን ይዟል። እሱም “የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ” ዓይነት ነው።
6. ኮዴክስ ኤፍራሚ፣ “ሐ” ወይም (04) በመባል የሚታወቀው፣ የአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ በከፊል የተበላሸው፣
7. ኮዴክስ ቤዜ፣ “መ” ወይም (05) በመባል የሚታወቀው፣ የአምስተኛ ወይም የስድስተኛ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ነው። “የምዕራብ ጽሑፍ” ተብሎ ከሚጠራው ዋንኛው አስረጅ ነው። በውስጡም በርካታ ተጨማሪዎች የያዘ ሲሆን እንዲሁም ዋነኛው የግሪክ እማኝ ሆኖ በኪንግ ጀምስ ትርጉም ላይ አገልግሏል።
8. የአኪ MSS በሦስት ሊመደብ ይችላል፣ እንዲያውም በአራት፣ አንዳች ባሕርይ በሚጋሩ።
   (ሀ) የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ ከግብፅ
      (1) ገ[75]፣ ገ[66] (200 ዓ.ም አካባቢ)፣ ወንጌላት የተጻፉበት
      (2) ገ[46] (225 ዓ.ም አካባቢ)፣ የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉበት
      (3) ገ[72] (ከ225-250)፣ የጴጥሮስና የይሁዳ መልእክቶች የተጻፉበት
      (4) ኮዴክስ ለ፣ ቫቲካነስ የሚባለው (325 ዓ.ም)፣ ሙሉውን ብኪ እና አኪ የያዘ
      (5) ከዚህ የጽሑፍ ዓይነት የተጠቀሱ ምንጮች
      (6) ሌሎች MSS የዚህን የጽሑፍ ዓይነት የሚያሳዩት ?፣ C፣ L፣ W፣ 33፣
   (ለ) ከሰሜን አፍሪካ ምዕራባዊ ጽሑፍ
      (1) ከሰሜን አፍሪካ የቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሰ፣ ተርቱሊያዊ፣ ሲሪያዊ፣ እንዲሁም የጥንታዊ ላቲን ትርጉሞች
      (2) ከኤሪናዩስ የተጠቀሱ
      (3) ከቲታን እና ከጥንታዊ ሲሪያ ትርጉሞች የተጠቀሱ
      (4) ኮዴክስ መ “ቤዚ” የዚህን ጽሑፍ ጻይነት የሚከተል
   (ሐ) ከኮንስታንቲኖፕል የምዕራብ ባይዛንታይን ጽሑፍ
      (1) የዚህ ጽሑፍ ዓይነት ከ80% በላይ የሚሆነውን የ5300 MSS ያንጸባርቃሉ
      (2) በአንቲሆች በሶርያ የቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሰ፣ ካፓዶቅያ፣ ክሪሶስቶም፣ እና ቴሮዶሬት
      (3) ኮዴክስ ሀ፣ በወንጌላት ብቻ
      (4) ኮዴክስ ሠ (ስምንተኛ ክፍለ ዘመን) ለሙሉ አኪ
   (መ) አራተኛው ሊሆን የሚችል ዓይነት “ቄሳሪያዊ” ከፓለስታይን
      (1) በቅድሚያ የታየው በማርቆስ ብቻ ነው
      (2) ጥቂት አስረጅዎች ገ[45] እና W

II. “የመለስተኛ ትንታኔ” ወይም “የጽሑፋዊ ትንታኔ” ንድፈ ሐሳባዊ ችግሮች

ሀ. ልዩነቶች እንዴት ተፈጠሩ?

1. ሳይታወቅ ወይም በድንገት (አብዛኛው ሰፊ ክፍል የተፈጠረበት)
   ሀ. በዓይን የተፈጠረ ስህተት፣ ማለትም በእጅ በሚጻፍበት ጊዜ ሁለት ተመሳሳይ ፊደላት ላይና ታች መስመር ይዘው ሲመጡ ሁለተኛውን ጽፎ በመጀመሪያው መስመር ላይ ያሉትን ቃላት እንዳለ መግደፍ (ሆሞቲሉቶን)
      (1) የዓይን መሳሳት ጥንድ ቃላትን ወይም ሐረግ መግደፍ (ሀፐሎግራፊ)
      (2) የሐሳብ መሰረቅ ሐረግን ወይም መስመርን ሲደግሙ፣ የግሪክ ጽሑፍ (ዲቶግራፊ)
   ለ. የጆሮ ስህተት፣ በቃል ሲነገር በተጻፈ ወቅት የተሳሳተ ንባብ ሲቀርብ የሚፈጠር (ኢታሲዝም)። ብዙውን ጊዜ ይህ የተሳሳተ ንባብ ተመሳሳይ ድምፅ ባላቸው የግሪክ ቃላት ይፈጠራል።
   ሐ. የቀድሞዎቹ የግሪክ ጽሑፎች ምዕራፍም ሆነ የስድ ንባብ ክፍሎች አልነበራቸውም፣ ጥቂት ወይም ምንም ሥርዓተ ነጥብ ነበራቸው፣ በፊደልና ፊደል መካከልም ክፍተት አልነበረም። እናም መልእክቶቹን በተለያየ ቦታ መከፈልም ሆነ ሌሎች ቃላትን መመሥረት ይቻል ነበር።
2. ሆንተብሎ
   ሀ. የሚቀዳውን ጽሑፍ ሰዋስዋዊ ቅርፅ ለማሻሻል ሲባል ይደረጉ የነበሩ ለውጦች
   ለ. ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ጋር አረጋጋጭ እንዲሆኑ ይደረጉ የነበሩ ለውጦች (የአቻዎች ኅብር)
   ሐ. ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ የተለያዩ ምንባቦችን ወደ አንድ ወጥ ጽሑፍ ለመቀየር ሲባል የተደረጉ ለውጦች፣ (ድብለቃ)
   መ. በጽሑፉ ውስጥ ስህተት ያለ መስሎ ሲታሰብ ለማስተካከል የተደረጉ ለውጦች (1ኛ ቆሮ. 11፡27 እና 1ኛ ዮሐንስ 5፡7-8
   ሠ. ከተጨማሪ መረጃ፣ ከታሪካዊ አቀማመጥ ወይም ከተገቢ ትርጓሜ አንጻር በአንድ ጸሐፊ የሰፈረ በግርጌ ማስታወሻ በሌለኛው ጸሐፊ ደግሞ በጽሑፉ ውስጥ እንዲካተት ሲደረግ (ዮሐንስ 5፡4)

ለ. የጽሑፋዊ ትንታኔ መሠረታዊ መርሖዎች (በዋንኛው የጽሑፉ ንባብ ላይ ልዩነቶች ሲኖሩ ለመወሰን የሚሆን አመክኖአዊ መመሪያ)

1. በጣም አስቸጋሪው ወይም ሰዋሰዋዊ አገባቡ እንግዳ የሆነው ዋነኛው ጽሑፍ ሊሆን ይችላል
2. ቅልጥፍ ያለው ጽሑፍ ዋነኛው ሊሆን ይችላል
3. ከዋናው ጋር በታሪክ ይቀራረባል ስለሚሰጠው ብዙ ክብደት የሚሰጠው ለጥንታዊው ጽሑፍ ነው፣ ሌላው እኩል ሆኖ
4. MSS በመልክዓ ምድራዊ የሚለያዩት ብዙውን ጊዜ ዋነኛውን ምንባብ ይዘዋል
5. ደከም ያሉት የእምነት መግለጫዊ ጽሑፎች፣ በተለይም ከዋናዎቹ የሥነ-መለኮት ማብራሪያዎች ጋር የሚገናኙት የእጅ ጽሑፎቹ ጊዜ ሲለወጡ፣ እንደ ሥላሴ ያሉት ፣ በ1ኛ ዮሐንስ 5፡7-8 የተመለከቱት ይመረጣሉ።
6. የዋናውን ጽሑፍ በተሻለ መልኩ ሊገልጹ የሚችሉ ሌሎች ጽሑፎች
7. እነዚህን አስቸጋሪ ልዩነቶች ሚዛን ለመጠበቅ የሚረዱ ማሳያ ሁለት ጥቅሶች
   ሀ. የጄ. ሃሮልድ ግሪንሊስ መጽሐፍ፣ *የአዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ መግቢያ፣* “ማንኛውም የክርስቲያን መሠረተ እምነት በአከራካሪ ጽሑፍ መሆን የለበትም፤ የአኪ ተማሪም ጽሑፉ፣ ተመስጧዊ ከሆነው ከዋናው ጽሑፍ የተሻለ ቀጥተኛና ከመሠረተ እምነት አኳያ የጠነከረ እንደሆነ ከመፈለግ መጠበቅ ይኖርበታል” (ገ. 68)
   ለ. ደብልዩ. ኤ. ክሪስዌል ለጌርግ *ጋሪሰን የበርሚንግሃም ኒውስ* ሲናገር እሱ (ክሪስዌል) የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሁሉ ተመስጧዊ ናቸው ብሎ አያምንም፣ “ቢያንስ ቢያንስ ሁሉንም ቃላት ለዘመናዊው ሰው የቀረበው በምዕት ዓመታት ተርጓሚዎች” አለ ክሪስዌል፤ “በጽሑፋዊ ትንታኔ በጣም የማምን ነኝ። ይህ እንግዲህ፣ እንደማስበው፣ የማርቆስ 16ኛ ምዕራፍ የመጨረሻው አጋማሽ አጠራጣሪ ነው፤ ተመስጧዊ አይደለም፣ የተደባለቀ ፈጠራ ነው… እነዚያን የእጅ ጽሑፎች ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ብታነጻጽሩ እንደ ማርቆስ ወንጌል መደምደሚያ ያለ አታገኙም። አንዱ ጨምሮት ይሆናል።

የበቁ የSBC አባቶች እንደሚከራከሩት ከሆነ “ተጨማሪ” ነገሮች መኖራቸውን በዮሐንስ 5 ያለው በቤተሳይዳ መጠመቂያ የኢየሱስ ሁኔታ ማስረጃ ነው። ሁለቱንም የተለያዩ የይሁዳን የራሱን መግደል ሁኔታዎች የገለጸበት (ማቲ. 27 እና ሐዋ. 1)፡ “ይህ የተለየ ዓይነት ራስን የመግደል ሁኔታ ነው፣” ይላል ክሪስዌል። “በመጽሐፍ ቅዱስ ቢሆን ኖሮ፣ ለዚህ መግለጫ በኖረው ነበር። እናም ሁለቱ የይሁዳ ራሱን የመግደል ሁኔታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ፣” ክሪስዌል ጨምሮም፣ “ ጽሑፋዊ ትንታኔ በራሱ አስደናቂ ጥበብ ነው። ጊዜያዊ አይደለም። ተዳፋሪነትም አይደለም። በእንቅስቃሴ ላይ ያለና ማዕከላዊ ነው…”

III. የእጅ ጽሑፍ ችግሮች (ጽሑፋዊ ትንታኔ)

ሀ. ለተጨማሪ የንባብ ምንጮች ጥቆማ

1. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ፡ ታሪካዊ፣ ሥነጽሑፋዊ እና ጽሑፋዊ፣* በአር. ኤች. ሃሪሰን

2. *የአዲስ ኪዳን ጽሑፍ፡ አስተላለፉ፣ ጥፋቱ እና ዳግም መመለሱ* በብሩስ ኤም. ሜዝገር

3. *የአዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ መግቢያ፣* በጄ. ኤች ግሪንሊ

# መግለጫ ሶስት
# የቃላት ፍቺ

**ልጅነት መወከል**፡- ይህ ጥንት የነበረ አስተሳሰብ ሲሆን ኢየሱስ ከመለኮታዊነት ጋር የነበረውን ህግኙነት ያጣቅሳል። ፅንሰ ሃሰቡ መሰረት የሚያደርገው ኢየሱስ በማንኛውም መንገድ ሰው ሲሆን ልጅነትን ያገኘው በእግዚአብሔር በተለየ መልኩ ማለትም በጥምቀቱ /በማቴ 3፡17፤ ማርቆስ 1፡11/ ወይም /በሮሜ 1፡4/ በተመለከተው መሰረት ነው። ኢየሱስ ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ በዚህ ዓይነት እንደኖረ እግዚአብሔርም በአንዳንድ ሁነቶች /በጥምቀትና በትንሳኤ/ እንደ ገዛ ልጁ እንደሆነው /ሮሜ 1፡4 ፊሊጽ 2፡9/ በተመለከተው መሰረት ያሳያል። ይህ የእምነት መግለጫ በ8ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ የአናሴ ቤተ-ክርስቲያን ጥስታዊ አስተሳሰብ የነበረ ነው። አምለሰክ ሰው ሆነ /ስጋዌ/ ከማመልከት ይልቅ ገለባብጦ ሰው እንዴት አምላክ እንደሆነ ያመላክታል።
ኢየሱስ አምላክ የሆነው ወለድ ቀድሞ መለኮት ምሳሌያዊ ሕይወት በመኖሩ እግዚአብሔር አከበረው ብሎ በቃላት ለማስረዳት ይቸግራል። እሱ ከቀድሞ ጀምሮ አምላክ ከሆነ እንዴት ክብርን ይሸለማል? እሱስ ቀድሞ የነበረ መለኮታዊ ክብር እያለው እንዴት ተጨማሪ ክብር ይሰጠዋል? እርግጥ ይህን ልንደርስበት በርግጥ ይቸግረናል፤ ማለትም አብ ኢየሱስን በተለየ መልኩ የአባቱን ፍቃድ በመፈጸሙ መከበሩን ለማሳየት ይሆናል።

**የአሌክሳዳሪያ አስተምህሮት**፡- ይህ ዓይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ አግባብ በግብፅ አሌክሳንደሪያ በ2ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረ ነው። መነሻ ያደረገውን መሰረታዊውን ፊሎአዊ የፍቺ መርህ ተከታይ የሆነው ጀሎን ያመላክታል። ተምሳሌታዊ ዘዴ በመባል የታወቃል። እስከ ተሃድሶ ዘመን ድረስ በቤተ ክርስቲያን ሲሰራበት ኖሯል። የተርጓሚው ሊቃውንት ሲረገንና አውስጢኖስ ናቸው። /ለተጨማሪ መረጃ የMoises Silva "ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን አሳስታ ተርጉማው ይሆን?" የሚለውን አንብብ /1987 ዓ.ም/።

**አሌክሳዳሪያ**፡- ይህ በ5ኛው ክፍለ ዘመን በአሌክሳዳሪያ የተገኘ የግሪክ /ቅርፅ/ የብራና ፅሑፍ ሲሆን፣ በውስጡም ብሉይ ኪዳን፣ የራዕይና አብዛኛውን ሐዲስ ኪዳን ያካተተ ነው። ፅሁፉ የግሪኩን አዲስ ኪዳን ቅጂ በተመለከተ ዋናኛው ማጣቀሻ ነው። /ከማቴዎስ፣ ከዮሐንስ ወንጌል አንዳንድ ክፍሎች እና ከሁለተኛ ቆሮንቶስ በቀር/ይህ ጽሑፍ ማለትም ልዩ ስሙ "ሀ" የተባለውና የቫቲካሉ ጽሑፍ ልዩ ስሙ "ለ" የተባለው በንባብ ላይ ሲሰማ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቆች አማካኝነት በብዙ አገባቦች እንደ ዋነኛ ተደርገው ይወሰዳሉ።

**ተምሳሌታዊ**፡- ይህ አይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ በመጀመሪያ የተስፋፋው በአሌክሳንደሪያ የአይሁድ እምነት ነው። እያገነነ የመጣው በአሌክሳንደሪያው ፊሎ ነው። የመሰረታዊ እምነቱም ፍላጎት ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደየሰው ባህል፣ ፍልስፍናና ስርዓት በማጣጣም የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ መቼት /ቦታና ጊዜ/ ስነጽሁፋዊ ይዘት በመተው ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የተሸሸጉትን እያንዳንዳቸውን ትርጓሜዎች በመመርመር ላይ ያተኩራል። ኢየሱስ በማቴስ 13 እንዲሁም ጳውሎስ በገላትያ 4 እውነትን ለመግለጽ የተጠቀሙበትን ተምሳሌት ያመላክታው። ዳሩ ግን ይህ ተምሳሌታዊ ሳይሆን ጽሑፋዊ መልክ የያዘ ነው።

**ስርወቃላዊ ትንታኔ**፡- ይህ አንደኛው የምርምር ዘዴ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን የግሪክ ስርወ ቃላት ለመለየት ይረዳል። በግሪክ የፊደል ተራ መሰረት ቅርጹና ዋናው መግለጫ /ትርጓሜ/ የያዘ ነው። ግሪክኛን ለሚያነሱ አማኞች ሰዩ ትርጓሜ አያይዞ በማስቀመጥ የግሪክን የሐዲስ ኪዳን ሰዋሰውና ስነጽሑፋዊ አገባብ ለመረዳት ያስችላል።

**የቅዱሳት መጻሕፍት ተመሳስሎ**፡- ይህ ሐረግ ለማስረዳት የሚሻው ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና እርስ በርሱ የሚቃረን ሳይሆን የሚደጋገፍ እንደሆነ ለማመላከት ነው።
ይህ አይነቱ በውል የተቀመረ አቀራረብ ቃሉን መሰረታዊ በሆነ መልኩ በንጽጽር በማስቀመጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች ይተረጉማል።

**አሻሚ ትርጓሜ**፡- ይህ የሚያመላከተው አሻሚ ትርጓሜ ያላቸውን የጽሑፍ ሰነዶችን ሲሆን ሁለትና ከዚያም በላይ ፍቺ ሲኖር፤ ወይም ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ነገሮች በአንድ ጊዜ በማጣቀሻነት ሲቀርቡ የሚከሰት ነው። ዮሐንስ ሆን ብሎ በዚህ ዘዴ ተጠቅሟል /ማለትም በእጥፍ አገባብ/

**ሰዋዊ ምዕላድ**፤ ይህ አይነቱ ፍቺ ከሰው ልጆች ጋር የተያያዘውን ሲማመላከት ጥሬ ቃሉም ሃይማኖታዊ ቋንቋዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቁርኝት ነው። ስርወ ቃሉ ከግሪክኛ የመጣ ሲሆን የሰው ልጅ ማለት ነው። ፍቺውም እኛ ስለ እግዚአብሔር የምንናገረው በሰውኛ ዘይቤ ማለት ነው። እግዚአብሔር በአካላዊ፣ በማህበረሰባዊ፣ በስለልቦናዊ ቃላት ከሰው ልጆች ጋር በተጓዳኝ /ዘፍ 34፤ 1ኛ ነገስት 22፡19-23/ እንደተጻፈው ሲነገር ማለት ነው። እርግጥ ይሄ ተመሳስሎ ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ ከሰው ልጆች በቀር ልንጠቀምበት የምልኝልበት ምድብ ወይም ቃል የለም። ስለሆነም ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት እውነትን ተንተርሶ ውስንነት እንዳለው ያመላክታል።

**የአንቲሆች አስተምህሮት**:- ይህ አይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ ዘዴ በአንቲሆች ሶሪያ በ3ኛው ክፍለ ዘመን የተንሰራፋ ሲሆን የአሌክሳንደሪያ ግብጽን ተምሳሌታዊ ዘዴ የሚቃረን ነው። መሰረታዊ እምነቱን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ ትርጓሜ ላይ ያተኩራል። መጽሐፍ ቅዱስን እንደማንኛውም የሰው ልጆች ስነጽሑፍ ይተረጉማል። ይህ አስተምህሮት ከክርስቶስ ክልዔ /ሁለት/ ባሕርይ አለው ከሚለው /ንስጥሮሳዊ/ አስተምህሮትና ወይም ደግሞ አንድ ባሕርይ አለው /ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው/ ከሚለው አስተምህሮት መሐል በተነሳው ውዝግብ ውስጥ ገብቶ እንደነበር ይታወቃል። ኋላም በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተነቅፎ እንደመናፍቅ ስለተወሰደ ወደ ፋርስ ሊሄድና ድጋሚ ሊቋቋም ቢሞክርም ውል ያለው አቋም ሳይዝ ቀርቷል። መሰረታዊ የአተረጓም መርሆቹ ግን ለትርጓሜ አግባብ ይሆኑ ዘንድ ለሉተርፕ ለካልቪን የፕሮቴስታንት የተሀድሶ አራማጆች ጥቅም ላይ ሊውል ችሏል።

**አንቲሄትካል**:- ከሶስቱ አንደኛው ዓይነት ገላጭ ጽሑፋዊ ዘዴ ሲሆን የእብራይስጥን የቅኔ ሐረጎች ተዛምዶ ያመላክታል። ፍቺያቸው የማይገጣጠሙትን የቅኔ ሐረጎች/ዘውጎች ተዛምዷቸውን ይመለከታል/ምሳሌ 10፡1፤15፡1/።

**ራዕያዊ ስነጽሑፍ**:- ይህ በአብዛኛው፤ በተለየ መልኩ የአይሁድ የስነጽሑፍ ዘውግ ነው። ይህ ዓይነቱ ምስጢራዊ ጽሑፍ ከአዩዳውያን በውጭ ኃያላት ይወረሩና ሲገዙ የሚዘወተር ነው። በጽሑፉ ይዘትም እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ፣ ሙላዋ የሱ እንደሆነችና መበገቻት እንደሚችሉ አመላክቶ ለእስራኤልም የተለየ ዓላማ እንደሚጠነቀቅለት ያሳያል። ስነ ጽሑፉ የመጨረሻው ድል የሚገኘው በእግዚአብሔት ልዩ ክንድ እነደሆነ አጽንዖት ይሰጣል።

ጽሑፉ በጣም ተምሳሌታዊና ምስል ከሳች ምስጢራዊ ቃላት ይበዙበታል። ብዙውን ጊዜ እውነትን በቀለማት በቁጥሮች በምስል ከሳች ሁኔታ በሕልሞች በመላእክታዊ ክስታ በምስጢራዊ ቃላት የሚገለጽ ሆኖ ጊዜ በሰናይና በክፉ መሐል በመንታዊ ሰይፉ ከፍሎ ያልፋል።

የዚህ ዘውግ አነዳንድ ምሳሌዎች 1ኛ በብሉይ ኪዳን ሕዝቅኤል/36-48/ ዳንኤል /ምዕ 7-12/ ዘካሪያስ እና ዘርፍ ሲሆን ደግሞ ማቴ 2 ማር 13 2ኛ ተሰሎ 2 እና ራዕይ ናቸው።

**አፖሎጅስት**:- ይህ የግሪክ ስርወ ቃል ሕጋዊ ተከላካይ የሚል ነው። ከስነ-መለኮት አንደኛው የትምህርት ንዑስ ዘርፍ ሲሆን ለክርስትና እምነት ተገቢ የመከራከሪያ ማስረጃና አመክኗዊ የክርክር አግባብን ይቀምራል።

**ቀዳማይ**:- ይህ ቃል ቀደም ሲል ከተሄደበት አግባብ ጋር ጥብቅ መሰረታዊ ቁርኝት ያለው ነው። የሐሳብ አወራረዱም ቀደም ሲል ከወጡትና ከተቀበልናቸው ትርጓሜዎች መርሆች ወይም አቋሞች በመመስረት እንደ እውነት በመቀበል መቀጠል ነው። ያለ ምንም ተጨማሪ ምርምርና ትንታኔ የምንቀበላቸውን ማለት ነው።

**አርዮሳዊነት**:- አርዮስ በአሌምሳንደሪያ ግብፅ ፕሬስቤታሪያን ቤተ-ክርስትያን በ3ኛ እና በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበረ ነው። አጽንዖት ሰጥቶ የሚከራከረው ምሳሌ 8፡22-31 ያለውን ቃል ሲሆን እየሱስ ቀድሞ እንደነበረ ቢቀበልም መለኮትነቱ ከዷል። /ከአብ ጋር መስተካከል የለበትም ባይ ነው።/ ከአሌክሳንደሪያው ጳጳስ ተቋውሞ የገጠመው ሲሆን ይህም ከ318 ዓ.ም አንስቶ ለብዙ ዓመታት የቆየ ክርክር ነው። አርዮሳዊነት በተለይ የምስራቅ ቤተክርስቲያን መሰረተ እምነት ተደርጎ ተወስዶ ነበር። በ325 ዓ.ም በአቅያ የተሰበሰቡት ሊቃውንት አርዮስን አውግዘውና ነቅፈው ተወልድን የተካከለ መለኮትነት አጽንተዋል።

**አርስጣጣሊስ**:- የጥንታዊቷ ግሪክ ፈላስፋ ሲሆን የፕላቶ ተማሪና የታለቁ እስክስድር /አሴክሳንደር መምህር ነው። የሱ ተጽዕኖ እስካሁን ድረስ በዘመናዊው ጥናትና አስተምህሮት ላይ የጸና ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በማስተዋልና ምደባዊ ፈር በያዘ የማስተማር። ስልት አጽንዖት በመስጠቱ ነው። ይህም አንደኛው የሳይንሳዊ ምርምር ዘዴ እንደሆነ ይታወቃል።

**አውቶግራፐር**:- ይህ ለጥናታዊውና ወጥ ለሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች የተሰጠ ስያሜ ነው። እነዚህ ጥንታዊ ወጥ የብራና ጽሑፎች ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል። የቅጂ ቅጂ ብቻ ነው ያለው ይህም የጽሑፋዊ ይዘት ልዩነቶችን በዕብራይስጥና በግሪክ የብራና ጥንታዊ ጽሑፎች መሐል ሲፈጥር ችሏል።

**ቤዛ**:- ይህ የ6ኛው ክፍለ ዘመን የግሪክና የላቲን ጽሑፍ ነው። የሚል መለያ ሲኖረው ወንጎላትንና ግብረ-ሐዋርያትን እንዲሁም አንዳንድ መልዕክቶችን አካቷል። ከዚህም በላይ ሌሎት በርካታ ስንክሳሮችን /ጽሑፎችን/ ይዟል። በኪንግጀምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ወስጥ መካተት ስላለባቸው መሰተር ጥሏል። /እንደ መነሻ ሆኗል።

**አድልዖ**:- ይህ ቃል የሚያመለክተው በአንድ ነገር ወይም አመለካከት ላይ ቀደም ተብሎ የተያዘ አድሏዊ ግትር አቋምን ነው። አእምሮ በአንድ ነገር ከተያዘ ማድላቱ የማይቀር መሆኑል ያሳያል። ቀደም ብሎ የተያዘ ፍርደ-ገምድላዊ አቋምን ያመላክታል።

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት**:- ይህ ቃል በተለተ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ይህም ማለት የመጀመሪያው ፀሐፊ በዘመኑ ምን ለማለት እንደፈለገና አሁን በዘመናችን በምን መልኩ ተግባራዊ እንደምናደርገው ያለውን ያካትታል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ቃሉን ስልጣናዊ መመሪያ አድርጎ መውሰድ ነው። የሆነ ሆኖ የትርጓሜ መዛባት እንዳይከሰት የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጓሜ በታሪካዊና በሰዋሰዋዊ ዘዴ ብቻ መወሰኑ ይበቃል።

**ደንብ**፦ ይህ ቃል በተለይ ተመስጧዊ በሆነ ሁኔታ በተመስጧዊ የሆኑትን ጽሑፎች ይመለከታል። ይህም ሁለቱንም የብሉይና የሐዲስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያካትታል።

**ማዕከለ ክርስቶስ**፦ ይህ ቃል የኢየሱስን ማዕከላዊነት ያመላክታል። ቃሉን ለመጠቀም የተፈለገው ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጌትነቱን የሚያሳየውን ጽንሰ ሐሳብ ለማሳየት ነው። ብሉይ ኪዳን ወደ እሱ አመላካች ነው። እሱም የቃሉ ፍጻሜና ግብ ነው /ማቴ 5፡17-48/

**ሐተታ ትርጓሜ**፦ ይህ የተለየ ዓይነት የሐተታ መጽሐፍ ነው። ለመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ዳራ ያስነብባል። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ክፍልን ትርጓሜ ለመስጠት ይሞክራል አንዳንዶች በተግባራዊ አያያዝ ላይ ሲያተኩሩ ሌሎች ደግሞ በጽሑፍ ቴክኒካዊ አግባብ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። እነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት በጣም ጥቅም ይሰጣሉ። ዳሩ ግን ከእነሱ በፊት አጥኚው ግለሰብ የራሱን ጥናት መካሄድ ይጠበቅበታል። እነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት ሐተታዎችን መቀበል የሚገባው በወል መርምሮ መሆን ይገባል። ለዚሁም የተለያዩ ትርጓሜዎችን ከተለያየ ስነ-መለኮታዊ ትምህርቶች አቋም አኳያ መመልከቱ ተመራጭ ነው። ቃላት ዝርዝር ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምርምራዊ መጽሐፍ ነው። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ያሉትን ቃላት ሁሉ በየአገባባቸው በዝርዝር የያዘ ነው። በብቁ መንገድ እገዛ ያደርጋል። 1/ እያንዳንዱን የእንግሊዝኛ ቃል ምን መሆን እንዳለበት ከዕብራይስትና ከጽርዕ/ግሪክ/ እንደሆነ ያመላክታል 2/አንቀጾችን በማነጻጸር የመሳሳይ የሆነ የግሪክ ወይም የዕብራይስጥ ቃል ጥቅም ላይ መዋሉን ለማወቅ ያስችላል። 3/ሁለት የተለያዩ የዕብራይስጥም ሆነ የግሪክ ቃላት በተመሳሳይ የእንግሊዝኛ ቃል ተርጉመው እንደሆነ ያመላክታል። 4/ቃላቶች በምን ያህል ድግግሞሽ በየትኞቹ መጻሕፍትና ጸሐፋት እነደተፈረጉ ያሳያል። 5/ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ተጠቀሰው ቃል አመላካች የሆነ አንቀግ ያሳያል /ዋልተር ክላርክ የብሉይ ኪዳን ግሪክኛ እንዴት ጥቅም ላይ እነደዋለ የጥናት መረጃ መጽሐፍ ገጽ 54-55።

**የሙት ባሕር ጥቅሎች**፦ ይህ የሚያመለክተው የጥንታዊ ጽሑፍ ጥቅሎች የሆኑ በዕብራይስጥና በአረሚክ የተፃፉ ሙት ባሕር አጠገብ በ1947 የተገኙትን መጻሕፍትን ነው። እናዚህ ጥቅሎች ሃይማኖታዊ ቤተ-መጽሐፍት ሲሆኑ የይሁዳነት ክፍል የሆኑ በ1ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩትን ነው። የሮማ የግዛት መስፋፋትና በ60ዎቹ የተካሄዱት የቀናኢነት ውጊያዎች ገዳም በመሰሉና በዋሻዎች ውስጥ በሸክላ ታሽገው እንዲቀመጡ እንዳስገደደ ይገመታል። ጥቅሎች የ1ኛው ክፍለ ዘመን ፍልስጤምን ታሪካዊ መቼቶችን እንድንገነዘብና ማሰራዊ ጽሑፎች የሚባሉትን ትክክለኛነት እንድንረዳ /ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረውን/ አስችለውናል። በአድሕሮት በመባል ይታወቃሉ /ሙ/ባ/ጥ/ የሙት ባሕር ጥቅሎች።

**ዲዳክተር**፦ ይህ አይነቱ ተአመክንዮ አገባብ ከአጠቃላይ መርሕ ተነስቶ ወደ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ የሚገባ ሎጂካዊ አስተሳሰብ ነው። ከአንደክቲቭ አስተሳሰብ ተቃራኒ ነው። ማለትም ሳይንሳዊ የሆነውን ከዝርዝር አስተውሎች በመነሳው ወደ አጠቃላይ ንድፈ ሃሳብ የሚያደርሰውን።

**ዲያሌክቲካዊ**፦ ይህ አይነቱ የአስተሳሰብ ዘዴ ተቃራኒ የሆኑትን ነገሮች ያስቀምጥና /አይዎ/ በሁለቱም በኩል ያለውን ተቃርኖና ተዛምዶ የሚመረምር ነው። ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮቶች ዲያሌክታካዊ ጥንዶች አሏቸው። ለአብነትም ቀድሞ የተወሰነና - ነጻ ፍቃድ ደሕንነት - ጥረት እምነት ስራ ውሳኔ ስርዓታዊት ክርስትያናዊ ነጻነት ክርስትያናዊ ሐላፊነት።

**ዲያስፖራ**፦ ይህ ቃል የግሪክ ሲሆን ከነዓናዊ አይሁዶች አገራቸው ውጭ ያሉትን ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከተስፋይቱ ምድ ዳርቻ ወጭ የሚኖሩትን አይሁዳውያን ለመጥራት የሚጠቀሙበት ነው።

**ፍጹማዊ አቻነት**፦ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ ሐሳብ ሲሆን ትርጓሜዎቹም ቃል በቃል አቻ እና አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከዕብራይስጥም ሆነ ከግሪክ አቻውን አግኝተው መተርጎም የሚገባው ሲሆን ይህ ከልሆነም በሐረግ መልክ ሐሳብ በጥንቃቄ ከምንጩ ሳይዛባ እንዲተረጎም ይደረጋል። በእነዚህ ሁለት ንድፈ ሐሳቦች መሐል ፍጹማዊ አቻነት መነሻ ጽሑፉን አተኩሮ ይዚ በዘመናዊ ሰዋሰውና ፈሊጥ መተርጎም ይኖርበታል ይላል። የእነዚህ የትርጓሜ ንድፈ ሐሳቦች ትንታኔ መጽሐፍ ቅዱሳን እንዴት በመረዳት እናንብብ ገጽ 35 በሚለው ሰፊ እና ስታዋርት መጽሐፍ ላይ /ሮበርት ባራቸር/ መግቢያ በሰጡበት እናገኘዋለን።

**ኤሌክቲክ**፦ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የመጽሐፉን ቅኝት ለማከናወን ብቻ ነው። ጠቀሜታውም የተለያዩ ንባቦችን ከግሪክ ጽሑፎች ውስጥ በመምረጥና በመመርመር ዋነኛውን ወጥ ጽሑፍ ጋር ለመድረስ የሚያስችል ነው። ከግሪክ ጽሑፎች መሐከልም ዋነኛውን ተንተርሰው በግል አስተያየት መልክ የተሰጡትን አይቀበልም።

**ኤሲጀሲስ**፦ ይህ የኤክሰሳይስ ተቃራኒ ነው። ማለትም ኤክሲጂሰሲ ከዋነኛው ጸሓፊ ሐሳብ ያፈነገጠ /የወጣ/ ከሆነ ኤሲጀሲስ ደግሞ ባዕድ ሐሳብ ወይም አስተያየት ውስጥ ማጨቅን/በብዛት መግባትን ማስገባትን/ ይመለከታል።

**ስርወቃል**፦ ይህ የስርወ ቃላት የማጥኛ ዘዴ ሆኖ መነሻው ከምን እንደሆነ ይመረምራል። ከቃሉ ስር ፍቺ በመነሳትም ቃሉ እንዴት እቅም ላይ እነደዋለ ለማወቅ ያስችላል። በትርጓሜ ጊዜ ግን ኢቲሞለጂ ዋነኛ የትኩረት ነጥብ አይደለም። አወዳዊ ፍቺና የቃሉ አገባብ ነው የሚተኮርበት።

**ኤክሰጀሲስ**፡- የተወሰነ አንቀጽን ለመተርጎም የሚውል ቃል ነው። ይህም ማለት ከጽሑፉ ወጣ ባለ መልኩ በመርመር የዋነኛ ጸሐፊውን ሃሳብ ለመረዳት የሚያስችል ነው። ከታሪካዊ ዳራና መቼት /መቼ እና የት/ ስነ ጽሑፋዊ ፈርጅ ለዋሰውና ወቅታዊ የቃሉን ፍቺ ይቃኛል።

**ዣን**፡- የፈረንሳይ ቃል ሲሆን የተለያዩ የስነጽሑፍ ዘውጎች ማለት ነው። ተመሳሳይነት ያላቸውን የስነጽሑፍ ዓይነቶች አንድ ላይ ይመድባቸዋል። ለምሳሌም ታሪካዊ ትረካ ቅኔ ምሳሌ ትንቢታዊ /ምስል ከሳች/ ሕጋዊ ይገኙበታል።

**ግኖስቲስዝም**፡- ስለዚህ ጉዳይ ያለን እውቀት የሚመነጨው በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩይ የግኖስጢክ ጽሑፎች ሲሆን አስተሳሰቡ ግን ከ1ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት የግኖስጢክ ጽሑፎች ሲሆን አስተሳሰቡ ግን ከ1ኛው ክፍለ ዘመን ወይም ቀደም ሲል የነበረ ነው።
አንዳንዶች እንደሚሉት የቫለንታይን እና የቀረንታይን የ2ኛው ዘመን ግኖስጢስ 1/ቁስ አካልና መንፈስ ዘላለማዊ ሲሆኑ አንድነትም ምንታኤም /ሁለትነትም/ ይዘው። ቁስ አካል ክፉ ሲሆን መንፈስ ግን ሰናይ ነው። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር በቀጥታ ክፉ ነገርን በማበጀት ውስጥ አይገባም። 2/በእግዚአብሔርና በቁስ አካል መካከል የረጅም ጊዜ ወይም የመላዕከታዊ ደረጃ አለ። የመጨረሻው ወይም ዝቅተኛው ያህዌህ? /YHWH/ ሲሆን አለማትን የመሰረተ ነው። አንዳንዶች ከፍተኛ አድርገው በመመሰጥ ከእግዚአብሔር ያነሰ /በመለኮትነቱ ሳይሆን/ የሰው አካል ለብሶ መለኮት ሊሆን አይቻለውም። እሱ መንፈስ ነው 1ኛ ዮሐ. 1፡1-3 4፡1-6 /እና 4/ ደሕንነት ሊገኝ የሚችለው በኢየሱ በማመንና የተለያየ እውቀት በማግኘት ይህም ልዩ እውቀት በልዩ ሰዎች የሚታወቅ ነው። እውቀት /የማለፊያ ቃል/ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ያስፈልጋል። የአይሁድ የሕግ እውቀትም ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ይህ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ።
የግኖስቲክስ የሀሰት መምህራን ሁለት ዓይነት ስነ ምግባራዊ ተጻራሪ ስርዓቶች ያስቀምጣሉ። 1/ለአንዳንዶች የአኗኗር ስርዓት /ዘዬ/ ከደሕንነት ጋር ምንም ዓይነት ተዛምዶ የለውም። ለእነሱ ደሕንነትና መንፈሳዊነት ምስጢራዊ እውቀት /የማለፊያ ቃል/ በሚሰለው የተጎዳኘ በመላዕክት ክልል ነው ይላሉ። ወይም 2/ለሌሎች ደግሞ የአኗኗር ስርዓት በደሕንነት ላይ ትልቁ ነጥብ ነው። ለተሻለ የሕይወት ዘይቤም አጽንኦን በመስጠት ለእውነተኛ መንፈሳዊነት በማስረጃ ያቀርባሉ።

**ሄርሜኒዩኒክስ**፡- ቴክኒካዊ ቃል ሲሆን ለ ኤክሴጂሲስ እንደ መርሕ ያገለግላል። ሁለትዮሽ የሆነ የተወሰነ መመሪያና ተሰጧዊ ጥበብ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም የተቀደሰ በሚል ሄርሜሊዮኒክስ በሁለት ምድብ ማለትም፡- አጠቃላይ መርህና ዝርዝር መርሆች በሚል። ይህም ከተለያዩ መከጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ስነ ጽሑፎች ጋር ይዛመዳል። እያንዳንዱ የተለየ የስነጽሑፍ ዘውግ የየራሱ የተለየ መመሪያ ያለው ሲሆን ከሌሎች ጋር ደግሞ ግምቶችንና የትርጓሜ አገባቦችን ይጋራል።

**ኃየር ክርቲዝም**፡- ይህ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የትርጓሜ አገባብ /ደንብ/ ሲሆን አተኩሮቱም በአንድ በመጽሐፍ ቅዱስ መጽሓፍ ላው በታሪካዊ መቼትና በስነጽሑፋዊ መዋቅር ላይ ነው።

**ፈሊጥ**፡- ይህ ሐረግ የተለያዩ ባህሎችን ተንተርሶ ከዋናው ቃል ትርጉም ጋር ያልተያዘ ትርጉም የሚሰጥ ነው። አንዳንድ ዘናዋ ምሳሌዎች፤ የመጥፎ ጥሩ ነው ገደልከኝ የሚሉ አሉ። መጽሐፍ ቅዱስም የዚይ ተመሳሳይ የሆኑ ሐረጎች አሉት።

**ማብራሪያ**፡- ይህ ስያሜ የተሰጠው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መናገሩን ለማመልከት ነው። ሙሉ ጽንሰ ሐሳቡ የሚገልጸው በሶስት መልክ ነው። 1/ራዕይ እግዚአብሔር በሰው ታሪክ ውስጥ መስራቱ 2/ ተመስጦ፡- ለድርጊቱ ተገቢ የሆነ ትርጓሜ እና ፍቺ ለተመረጡ ሰዎች በተመስጦ በማስታወቅ መዝግበው ለሰው ልጅ እንዲያስተላልፉ ማድረጉ 3/ማብራሪያ፡- መንፈሱን ለሰው ልጆች በሰጡት ስለ እሱ እንዲያውቁና እንዲያስተውሉ ማስቻሉ።

**ኢንዳክሪቭ**፡- የሎጂክ አንዱ ዘዴ ሲሆን ከዝርዝር ነገሮች ተነስቶ ወደ አጠቃላይ የሚተነትን ነው። ለዘመናዊው ሳይንስ በተግባር ዘዴ በመሆን በማገልገል ላይ ነው። ዘዴው በመሰረቱ የአርስቶትል ነው።

**ኢንተርላይነር**፡- ይህ የምርምር መሳሪያ ዘዴ ዓይነት ሲሆን የመጽሓፍ ቅዱስን ቋንቋ የሚያነቡትን እንዲተነትኑና ፍቺውንና መዋቅሩን እንዲረዱ ያስችላል። የእንግሊዝኛውን ትርጉም ቃል በቃል በማስቀመጥ ከዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ጋር አነጻጽሮ ያስቀምጣል። ይህ የምርምር አግባብ ትንተናዊ ስርወቃልን በመደባለቅ ለሰው ልጆች የተናገረው መሰረታዊ ለሆኑት የዕብራይስጥና ግሪክ ፍችዎች መልክ ይሰጣል።

**ተመስጦ**፡- ይህ ጽንሰ ሐሳብ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተናገረው የመጽሐፍ ቅዱስን በጸሐፍት በትክክልና በግልጽ መገለጡን እንዲያፍሩ ነው። ሙሉ ጽንሰ ሐሳቡ በሶስት መልኩ ይገለጻል።
1/መገለጥ /ራዕይ/ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ መስራቱ 2/ ተመስጦ ለድርጊቱ ተገቢ ይርጓሜ እና ፍቺ ለተመረጡ ሰዎች በተመስጦ ለማስታወቅ መዝግበው ለሰው ልጅ እንዲያስተላልፉ 3/ ብርሃነ /ማብራሪያ/ መንፈሱን ለሰው ልጆች በመስጠት እሱ ሸሽግነት እንዲያውቁና እንዲያስተውሉ ማስቻል።

**የገለጻ ቋንቋ**፡- ይህ ብሉይ ኪዳን የተጻፈውንና ፈሊጦቹን ለማገናኘት ታስቦ ነው። እሱም የዓለማችንን የአበጋገር አግባብ በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት በማስመርኮዝ ያቀርባል። ሳይንሳዊ ገለፃ ማለት ግን አይደለም።

**ሕጋዊነት**፡- ይህ አዝማሚያ የሚያመለክተው ለሕግጋትና ለክብረ በዓላዊ አምልኮተ ስነስርዓት አፅንኦት የመስጡትን ነው። የሰው ልጆች የሚያደርጉትን ደንቦችና ስርዓቶች እግዚአብሔር ይቀነለዋል ብሎ መወሰን ነው። ግንኙነትን ዝቅ የሚያደርግና ክዋኔዎችን ከር የሚያደርግ ሆኖ ሁለቱንም ኪዳናዊ ግንኙነቶች /በቅዱሱ በእግዚአብሔርና በኃጢያተኛው ሰውነት እንደሚካህወድ ያስምጣል።

**ጽሑፋዊ ፍቺ**፡- ይህ የጽሑፋዊ ፍቺ ላይ የሚያተኩር እና ታሪካዊ የአተረጓጎም ዘዴ የሆነውን የአንቲሆችን ባህል ይከተላል። ይህም ማለት ትርጓሜ መያዝ ያለበት ተራ ወኔና ግልጽ የሆነውን ፍቺ በሰው ልጆች ቋንቋ እንዳለ ነው ይላል። ይህም ማለት ግን በተምሳሌታዊ ቋንቋ የተጻፉ ክፍሎች መኖራቸውን አይክድም።

**ጽሑፋዊ ዘውግ /ክፍል**፡- ይህ የሰው ልጆች መግባቢያ የሆነ የጽሑፍ ክፍሎችን ማለትም ቅኔ ታሪካዊ ትረካ የመሳሰሉትን ያካትታል። እያንዳንዱ ዓይነት ስነ ጽሑፍ የየራሱ የትርጓሜ አገባብ ሲኖረው በተጨማሪም ለሁሉም የስነ ጽሑፍ መርሖችን ይከተላል።

**ጽሑፋዊ አሃድ**፡- ይህ የሚያመለክተው ዋነኞቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ያስተሳሰብ ክፍሎችን ነው። ይህም በጥቂት ምንባቦች አንቀጾች ወይም ምዕራፎች ሊዘጋጅ ይችላል። በየራሱ ሙሉ የሆነና ማዕከላዊ የጽሑፍ ዓይነት የያዘ ነው።

**ሎወር ክርቲዝም**፡- /ቴክስቲወሐነ ክርትዝም/ ተመልከት የእጅ ጽሑፍ /የብራና ጽሑፍ/። ይህ ቃል የግሪኩን የሐዲስ ኪዳን ልዩ ልዩ ኮፒዎች ያመላክታል። ብዙውን ጊዜ በልዩ ልዩ ዓይነት ይመደባሉ። 1/ከተጻፈባቸው ቁሳቁስ /ፓፒረስ፤ ብራና/ ወይም 2/ የጽሑፍ የራሱ ቅርጽ /በካፒታል/ በቁም ጽሑፍ ወይም በቅጥልጣይ መሆኑ። በአጽሕሮተ ቃልም "MS" የብዙ ቁጥር ይባላሉ።

**ማአሶሪቲክ ቴክስት**፡- የዘጠነኛውን ክፍለ ዘመን በብሉይ ኪዳን የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፎችን ያመለክታል። ይህም በአይሁዳዊ ጠበብት የተጻፈና አካባቢ ድምጾችን ተጓዳኝ እዝሎችን የግርጌ ማስታወሻዎችን ያካተተ ነው። ለእንግሊዝኛው ብሉይ ኪዳን የሚሆነው ጽሑፍ ከዚህ የተገኘ ነው። ጽሑፍ በታሪካዊ መልኩ በዕብራይስጥ እንደሆነ የተረጋጠ ሲሆን በተለይ ትንቢተ ኢሳያስ በሙት ባሕር ጥቅሶች ታውቋል። በአጽሕሮትም "MS" ይባላል።

**ሚኢቶናሚ**፡- ከንግግር ክፍሎች ሆኖ የአንድ ነገር ስም ከሌላው ጋር በተጓዳኝ በመጥቀስ የሚገለጥበት ነው። ለምሳሌ ጀበናው እተፈላ ነው ሲል በጀበናው ውስጥ ያለው ውኃ እየፈላ ነው ለማለት ነው።

**ሙርአቶርያን ፍራግመንትስ**፡- ይህ የደንብ /የሕግ/ መጻሕፍትን ዝርዝር ያካተተ ኪዳን ክፍል ነው። የተጻፈውም በሮሜ ከ200 ዓ.ም ቀደም ብሎ ነው። እነዛኑ 27 የሐዲስ መጽሐፍት በፕሮቴስታንት አዲስ ትርጉም ነው። ይህም በሮም ግዛት የሚገኙት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ዋነኞቹ የቤተክርስቲያን ምክር ቤቶች /በ4ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት/ በፊት እንደተበጀ ያመላክታል።

**ተፈጥሯዊ መገለጥ**፡- ይህ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች የሚገልጽበት አንደኛው ክፍል ነው። ተፈጥሯዊ ስርዓትን /ሮሜ 1፡19-20/ እና ሞራላዊ የሕሊና ሚዛንን /ሮሜ 2፡14-15/ ያካትታል። በመዝሙር 19፡1-6 እና ሮሜ 1-2 ተጽፏል። ከልዩ መገለጥ ይለያል፤ ማለትም የእግዚአብሔር የራሱ መገለጥ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በናዝሬቱ ኢየሱስ ማለት ነው።
ይህ የስነ መለኮት ምድብ እንደገና አጸንዖት እየተሰጠው እንደ ሁግሮስ በመሳሰሉ ክርስቲያን ጸሐፍት በአሮጌው ዓለም ንቅናቄ ላይ ተመልክቷል። እነሱም ይህን ምድብ ሁሉም እውነት የእግዚአብሔር እውነት እንደሆነ ያጸኑበታል። ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ለማወቅ የተከፈተ በር ነው ይህም ካልተመሰጥ /ከመጽሐፍ ቅዱስ/ ይለያል ዘመናዊው ሳይንስ የተፈጥሮ ስርዓትን እንዲያጠና ነጻነትን ይሰጠዋል። እንደኔ አስተያየት ለዘመናዊው ሳይንሳዊ የምዕራቡ ዓለም ለመመስከር አዲስ አስደናቂ ዕድል ነው እላለሁ።

**ንስጥሮላዊነት**፡- ንስጥሮስ በ5ኛው ክፍለ ዘመን የኮንስተንበኖፕል ፓትርያርክ የነበረ ነው። የተማረውም በንሪሆች ሶርያ ሲሆን የመከራከሪያ ነጥቡም ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት ሲኖሩት አነደኛው ሙሉ ለሙሉ ሰው፤ ሌላኛው ሙሉ ለሙሉ መለኮት ነው ባይነው። ይህም ከአሌክሳንደሪያው የኦርቶዶክስ አንድ ባሕሪ /በተዋህዶ/ ከሚለው ያፈነገጠ ነው። የንስጥሮስ ዋነኛው አትኩሮቱ ለማርያም የተሰጠው የአምላክ እናት የሚለው ስያሜ ነው። ንስጥሮስ በሌክሳንደሪያው ሲሪል ነቀፋ ገጥሞታል። ይህም ዞሮ ዞሮ በተማረበት በአንቲሆች ማለት ነው። በወቅቱ አንቲሆች የታሪካዊ ሰዋሰዋዊ ጽሑፋዊ አገባብ ያለው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረጓሜ ማዕከል ስትሆን አሌክሳንደሪያ ደግሞ በአራትዮሹ /ተምሳሌታዊ/ ጉባዔያት የትምህርት ትርጓሜ ማዕከል ነበረች። ንስጥሮስ ከማዕረጉ ወርዶ በግዞት እንዲቀመጥ ተደርጓል።

**ዋነኛው ጸሐፊ**፡- ይህ የሚያመለክተው ዋነኞቹን የቅዱሳን መጻሕፍት ጸሐፊዎችን ነው።

**ትይዩ አንቀጾች**፡- እኒህ የጽንሰ ሐሳብ ክፍሎች፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እና ፍጹም የሆነው የሆነው ተርጓሚም እሱ እንደሆነ፤ አደናጋሪ የመሰሉንን እውነቶች እንኳ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚፈታ ነው። ይህም አንድ ሰው ግልጽ ያልሆነለትን አሻሚ አንቀጽ ሲተረጎም ሲሻ ሊረዳው ይችላል። አንቀጾቹ በተጨማሪም ግልጽ ተዛማጅ ክፍሎችን በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ከቅዱሳት መጻሕፍት ያመላክታሉ።

**አጽሕሮት**፡- ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ይረጓሜ ንድፈ ሐሳብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ቃል በቃል የተረገና ተያያዥነት ቅርጽ የያዘ ሆኖ የእንግሊዝ ቃል ለዕብራይስጥም ሆነ ለግሪክ ቃል ፍቺነት ተፈልጎ፤ የክፍሉ /የአንቀጹ/ ፍሬ ሐሳ ዝቅ ባለ ግምት ከዋናው ጽሑፍ ጋር እየተያየ የሚተረጎምበት ነው። ከእነዚህ ሁለት ዓይነት ንድፈ ሐሳቦች ፍጹም አቻዎች የሚባለው ግን ዋናውን ጽሑፍ በዘመናዊ ሰዋሰው እና በዘይቤና በፈሊጥ ለመተርጎም የሚሞከር ነው። ይህን በተመለከተ ደህና መብራሪያ /የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች /በ Fee እና Stuart መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት በመረዳት እናንብ ገጽ 35 ተመልከት።

**አንቀጽ**፡- ይህ በስድ ንባብ የሚደረግ ዋነኛው የትርጓሜ ክፍል ነው። አንድ ዋነኛ ሃሳቡን ይዞ እያዳበረ ይሄዳል። አንዳንድ በአነቀጽ ላይ ብቻ አኩረን ትርጉሙን ስነሻ /አናሳ አንቀጽ ላይ/ የዋናውን ጸሐፊ ሃሳብ ላናገኘው እንችላለን።

**ፖራኮሊዝም**፡- ይህ የሚያሳየው በአድሏዊነት የተያዘን የአጥቢያ ስነመለኮታዊና ባህላዊ ጉድኝትን ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም ባህል /የባህሎች ሁሉ የበላይነት/ እና የአተገባበር እውነቱን ግምት ውስጥ እያስገባም /አይቀጠልም/።

**አያዎ**፡- ይህ የሚያመላክተው ተቃራኒነት ያላቸው የመሰሉ እውነቶችን ሲሆን /ይሆናሉ አይሆኑም/ የሚል መልክ ይዞ ነው። እውነትን የሚያቀርበው ተቃራኒ አቅጣጫዎችን ይዞ ነው። ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የሚቀርቡት በዚህ /አያዎ/ ወይም በዲያሌክታካዊ ጥንዶች ተቃርኖ አገባብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ተለያይተው እንደተቀመጡ ከዋክብት ሳይሆኑ ምድብ ምድብ በያዙ የክዋክብት ክምችት ይመስላሉ።

**ፕላቶ**፡- ከጥንታዊ ግሪክ ፈላስፎች አንደኛው ነው። የሱ ፍልስፍና የጥንታዊዋን ቤተክርስትያን በአሌክሳንደሪያ ግብፅ ሊቃውንት እንዲሁም በአውግሰጦስ አማካኝነት ተጽዕኖ አሳድሯል። ፕላቶ በምድር ላይ ያለ ማንኛውም ነገር የመንፈሳዊ ዓለም ግለባጭ /ቅጅ/ ነው ብሎ ያምናል። የስነመለኮት ጠበብት በኋላ ይህን ተፕላቶን አስተሳሰብ ቅርፆች/ሐሳቦች በሚል ለመንፈሳዊ ተግባር ጥቅም ላይ አውለውታል።

**ቅድመ ግምት**፡- ይህ ስለ አንድ ነገር ቀድመን የምናስበው ወይም የምንገምተው ነው። ጽሑፉን ከመመርመራችን በፊት ብዙ ጊዜ አስተያየትና ፍርድን /አቋምን/ ስለ አንድ ነገር ማድረግ ይዘወተርብናል። ይህ ቅድመ ግምት፤ አድልዖ በመባልም ይታወቃል። ግምት ወይም ቅድመ እውቅና ይባላል።

**ፕሩፍ ቴክስቲንግ**፡- ይህ ተግባት ከለን በቁጥር ብቻ /ሙሉ ክፍልን ሳይሆን/ ወይም ዋናውን የክፍሉን አጠቃላይ ሃሳብ ሳይሆን የመተርጎም ስራ ነው። ይህም ቁጥሮቹን ከዋናው የጸሐፊው ሐሳብ ባፈነገጠ መልኩ የግል አስተያየትን በሚካተት የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ትቶ ማለት ነው።

**ይሁዳዊ መምህርነት**፡- ይህ ዓይነቱ የአይሁድ ሕዝቦች የኑሮ ስርዓት የተጀመረው ከ586-538 ቅ.ል.ክ ከባቢሎን ግዞት በኋላ ነው። የአይሁድ ቀሳውስትና ቤተመቅሰሱ ከቀሩ በኋላ የአጥቢያ ምኩራቦች የአይሁድ ብሔራዊ የዕምነት ማዕከላት ለመሆን ቻሉ። እነዚህ አጥቢያ ማዕከላት የአይሁድ ባህል፤ ሕብረት የአምልኮና የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ማካሄጃ በመሆን የብሔራዊ ሃይማኖታዊ የትኩረት ማዕከላት ሆነዋል። በጁሊየስ ዘመን እነዚህ የጸሐፍት ሃይማኖት ተብለው የሚታወቁት ቀሳውስቱ ጋር በትይዩ መልኩ አገልግለዋል። በ70 ዓ.ም ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ ጸሐፍቱ አካል የፈሪሳውያን የበላይ ለመሆን ከመቻሉም በላይ የአይሁድን ሃይማኖታዊ ሕይወት መቆጣጠር ችሏል። ባሕርዩም ተግባራዊ ሕጋዊ ትርጓሜዎች ላይ የሚያተኩር ሆኖ ባህላዊ /ስነ ቃለዊ/ የሆነውን ዘዴ በመጠቀም ታልሙድን ማብራራት ነው።

**ራዕይ**፡- ይህ እግዚአብሔር ሰለው ልጆች የሚናገርበትን ጽንሰ ሐሳብ የሚገልጽ ስያሜ ሙሉ ሐሳቡ ብዛውን ጊዜ በሶስት መንገዶች ይገለፃል። 1/ራዕይ፡- ማለትም እግዜአብሔርን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የሚከናውነውን 2/ ተመስ፡- እሱ ትክክለኛውን ትርጓሜ ለድርጊቱ ሁሉ የሚሰጥበትን ይህም በተመረጡ ሰዎች አማከኝነት ሆኖ መዝግበው ለሰው ልጆች የሚያስተላልፍበት አገባብ። 3/በማብራሪያ ማለትም መንፈስን በመስጠት የሰው ልጆችን በማገዝ ስለ እሱ ይበልጥ እንዲረዱ ማድረግን ያጠቃልላል።

**የቃላት የዓረፍተነገር ትርጉም**፡- ይህ አጠቃላይ የቃላት ትርጉም ጋር የተያያዙ ደረጃዎችን ያመላክታል። በመሰረቱ የቃላት የተለያየ ትርጉም በየአግባቡ /በየጽሑፉ/ /በየወርዱ/ የሚታየበት ነው።

**ሴፕቱኤጀንት**፡- የዕብራይስጥ ብሉይ የግሪክ ትርጉም ነው። ከባህል አንፃር በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት በሰባ ቀናት ተጽፎ ለአሌክሳንደሪያ ግብፅ የተፃፈ እንደሆነ ይነገራል። ባሕላዊ ጊዜውም 250 ቅ.ል.ክ እነደሆነ ሲገመት /በተግባር ግን ጽፎ ለመጨረስ ከመቶ ዓመት በላይ እነደወሰደ ይገመታል/ ይህ ትርጉም ጠቀሜታው የላቀ ሲሆን፤ ይህም 1/ጥንታዊ የሆነውን ጽሑፍ ከዕብራይስጥ ማስረቲካ ጋር እንዲነጻጸር 2/የአይሁድን የትርጉም አገባብ በ3ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ የነበረውን ያሳየናል። 3/የአይሁድን ሜስነክ መረዳት /አስተሳሰብ/ ማለትም ክርስቶስን ካለመቀበላቸው በፊት የነበረውን ያሳያል። አጽሕሮቱም "LXX" ነው።

**ሲናቲኮስ**፡- የ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም የነበረ የግሪክ የብራና ጽሑፍ ነው። የተገኘውም ቲስከስዶርፍ በተባለ የጀርመን ሊቅ በቅድነት ናተሪኒ ገዳም፤ በጃቤሳ መሳ የተባለ ባሕላዊ ስም ባለው በሲናይ ተራራ ክልል ነው። ይህ የብራና ጽሑፍ /የእጅ ጽሑፍ/

በዕብራይስ የመጀመሪያ ፊደል በሆነው በአልፋ [x] ይታወቃል። እሱም ብሉይ ኪዳንና የተጠቃለለውን ሐዲስ ኪዳንን ይዟል። በጣም ጥንታዊ ከሆኑት የተለየ የእጅ ጽሑፎች አንደኛው ነው።

**የመንፈሳዊ**፡- ይህ ቃል ተምሳሌታወኰ ከማድረግ ጋር ተመሳሳሰይ ሲሆን ሃሳቡም ታሪካዊና ተራ የሆነውን የፅሁፉን ክፍል በማስቀረት በልቶ መስፈርት የመተርጎም አግባብ ነው።

**ተመሳሳይ**፡- ይህ የፅሁፉን ፍቺ ያመለክታል። 15/ምንም እንኳ ሁለት ቃላት ፍፁም ተመሳሳይ ትርጉም ባይኖራቸውም /በጣም የተቀራረቡ ከመሆናቸው የተነሳ በአረፍተ ነገር አወቃቀር ላይ የትርጉም ለውጥ ሳይኖር አንዱ አንዱን ሊተካው ይችላል። በተጨማሪም የእብራይስጥ ቅኔ ከሆኑት 3 የትይዩ ዘርፎች አንደኛውን ለመመስረት ያስችላል። በዚህ መሰረት ባለሁለት መስመር የሆኑትን ቅኔዎች /ግጥሞች/ ያመላክታል። /መዝ 1-3-3/

**ሰዋሰዋዊ**፡- ይህ የግሪክ ቃል ሲሆን የአረፍተ ነገርን አወቃቀረአ ያሳያል። ይህም የአረፍተ ነገር አደራደር ሙሉ አስተሳሰብን እንዲገልፅ ተደርጎ ሲዋቀር ያለውን ያሳያል።

ሳይንዚቲካል፡- ከእብራይስጥ ቅኔ /ግጥሞች ከሶስቱ አይነቶች አንደኛውን ያመለክታል። ይህም የቅኔ /የግጥም/ መስመሮች /ሀረጎች/ አንደኛው ከአንደኛው በመቀናኗጀት አጠቃላይ ስሜት ሊሰጡ በሚችሉ መልኩ ሲዋቀሩ ነው። አንዳንዴም ተለዋዋጭ ይባላል። /መዝ 19፡7-9/

ስልታዊ የስነ መለኮት ትምህርት፡- ይህ ትርጉም ደረጃው አይነት የመፅሀፍ ቅዱስን እውነት ህብር እና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ሲያቀርቡ ነው። ከታሪካዊነቱ ይልቅ ሎጂካዊነቱ /ምክንያታዊነቱ/ ያመዝናል። የክርስትና የስነመለኮት ትምህርት በየምድቡ በማድረግ /እግዚአብሄር፣ ሰው፣ ሀጢያት፣ ደህንነት ወዘተ/ እያለ ይቀርባል።

**ታልሙድ**፡- ይህ የአይሁድ የስነ ቃል /ባህል መለያ ነው። አይሁድ እግዚአብሄር በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ በቃሉ እንደተናገረው ያምናሉ። በተግባር ሲታይ ግን ለዓመታት የተከማቸ። የአይሁድ መምህራን የጥበብ ክምችት ነው። ሁለት ዓይነት የተለያዩ የፅሁፍ ቅጂዎች /እትሞች/ አሉት ታልሙድ እነሱም የባቢሎኑና ያልተጠናቀቀው በአጭር የተፃፈው የፍልሰጥሙ /የከነአኑ/።

**የቃሉ ምርመራ**፡- ይህ የቅዱሳን መፃህፍትን ጡናት ማካሄድ በተመለከተ ነው። ይህ አይነቱ ጥናት አስፈላጊ የሚሆነው ዋነኞቹ ፅሁፎች ስለማይገኙ ቅጂዎቹ የተለያዩ በመሆኑ ነው። ልዩነቶችን ለማብራራትና በተቻለ መጠን ወደ ዋነኞቹ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ፅሁፎች መነሻ ለማድረስ ነው ብዙውን ጊዜ ዝቅተኛው ምርመራ ይባላል።

**የፅሁፍ አቀባበል**፡- ይህ ስያሜ የተሰፋፈው ወደ አኤልዚጎር ትርጉም ከሆነው በ1633 የግሪክ አዲስ ኪዳን እትም ነው። በመሰረቱ ይህ የግሪክ የአዲስ ኪዳን የወጣው /የተገኘው/ ጥቂት ቀደም ሲል ተፅፈው ከነበሩ የግሪክ የእጅ ፅሁፎች እና የላቲን እትሞች ማለትም ከአራሳመስ /1510-1535/ እስጢፋኖስ /1546-1559/ እና ኤልዚጎር /1624-1678 ከተፃፉት ነው የአዲስ ኪዳን ፅሁፋዊ ምርመራ /ገፅ 27 መግቢያው ላይ ኤቲ ሮበርትስን/ የባይዘንታይን /የግሪክ/ ፅሀፀፍ በተግባር ሲታይ ፅሁፎችን መቀበል ነው ብሏል። የባይዘንታይን ፅሁፍ የመጨረሻው ዝቅተኛው የሆነ በጣም ጠቃሚ ከሆነፀ ከሶስቱ ከቀደምት የብራና /የእጅ ፅሁፎች/ /በምዕራብ በሌክሳንደሪያና በባይዘንታን/ ካሉት የሚመደብ ነው። በውስጡም በእጅ ሲፃፍ ለዘመናት የተደረጉትን ግድፈቶች /ስህተቶች/ አከማችቶ ይዟል። ሆኖም ግን ኤ ቲ ሮበርትሰን ደግሞ እንዳለው፣ ፅሁፎቹ የተወልን ነገር በውስጡ ያለው ተገቢ ፅሀፀፍ ነው ብሏል /ገፅ 21 ላይ/ ይህ የግሪክ ፅሀፀፍ /በተለይም የአራስመስ 3ኛ እትም በ1522 /የንጉስ ጀምስ እትም ማለትም 1611 ዓ.ም የታተመውን መሰረት እንደሆነ ይታመናል።

**ቶራ**፡- ይህ የዕብራይስጥ ቃል ማስተማር ማለት ነው። እሁም ለሙሴ ፅሁፎች /ከዘፍጥረት እሰከ ዘዳግም/ ያለውን የሚያካትተ ርዕስ ነው። ይህ ለአይሁድ ታላቅ ስልጣን /ተቀባይነት/ ያለው ክፍል ነው።

**ታይፖሎጂካል**፡- ይህ ጥልቀት ያለው ሙያዊ ትራጓሜ ነው። ብዙውን ጊዜ የሀዲስ ኪዳን እውነት ከብሉይ ኪዳን ተምሌታዊ መልኩ የሚያስጠቅስና የሚያስማማ ነው። የትርጉም ምድብ ዋነኛው የአሌክሳደሪያን ዘዴ የተከተለ ነው። የዚህ አይነቱን ትርጉም በአግባቡ አለማከናወንን ለማስቀረት ትርጓሜው ሲካሄድ በተወሰኑ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች መሆን ይኖርበታል።

**ቫአቲካነስ**፡- ይህ የ4ኛ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ፅሑፍ ነው። የተገኘውም በቫቲካን ቤተመጽሀፍት ሲሆን ዋናውን ብሉይ ኪዳን ተነባቢት /ራዕይ/ እና አዲሰ ኪዳንን ያካትተዋል። የተወሰኑ ክፍሎች ማለትም ከዘፍጥረት፣ ከዕብራውያን፣ ከሌዋውያን ሆኖም የተወሰኑ ከፍሎች ማለትም ከዘፍጥረት፣ ከዕብራውያን፣ ከሌዋውያን ፊሊሞና እና ከራዕያ ጎድለውብታል። ዋናውም የቃሉን የእጅ ጽሑፍ በመወሰን በኩል በጣም ጠቃሚ የሆነ ጽሑፍ ነው። መለያውም ፊደል "ቢ" ነው።

**ቫልጌት**፡- ይህ የጀሮም የላቲን ትርጉም የሆነ መጽሀፍ ቅዱስ ነው። ይህ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዋነኛ ትረጉም ተደርጎ ተወስዷል። በ380 ዓ.ም ነው የተፃፈው።

ጥበባዊ ሥነ-ጽሁፍ፡- ይህ ቃል የሥነ-ጽሑፍን ዘውግ/ዓይነት/ የተለመደ ዓይነት ሆኖ በቅርብ ምስራቅ የጥንት አካባቢ /ዘመናዊው ዓለም/ የሆነውን ያመለክታል። ይህ በቅኔ/በግጥም/በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በወገዊ ጽሁፍ አማካኝነት አዲሱን ትውልድ ለማስተማርና ስኬታማ ሕይወት እንዲኖር የሚያስችል ነው። መልእክቱም ለአጠቃላይ ለማህበረሰቡ ሳይሆን በግለሰቦት ላይ

ያተኮረ ነው። የታሪክን ሁኔታ በማጣቀስ አይጠቀምም፣ ይልቁንም የሕይወትን ልምድና አስተውሎትን ይቃኛል። ከመጽሀፍ ቅዱስ ከእዮብ ከመሃልየ ማሃልየ የሚታሰበው የያህዌን መገኘትና ማምለክን ሲሆን ይኼውም መንፈሳዊ ዓለም አስተሳሰቡ በግልፅ በየሰው የሕይወት ልምድ በሁሉም ጊዜ እንደማይደረግ ያታወቃል።

እነደ ሥነ-ጽሁፍ ዘርፍ በአጠቃላይ እውነት ላይ ያተኩራል። ይህ የሥነ-ጽሑፍ ክፍል /ዕይነት/ግን በእያንዳንዱ ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውልም። እነዚህ አጠቃላይ ሀሳቦች በእያንዳንዱ ሰው ባለበት ሁኔታ ላይ የማይከናወኑ ናቸው።

አነዚህ እነዚህ ፅሑፎች የሕይወትን ጠንካራ /ዋነኛ/ ጥያቄ ያነሳሉ። ብዙውን ጊዜ ሀይማኖታዊ ሆነው ባህል የሚደባለቁ አመለካከቶችን /ኢዮብ/መክብብ/ ያነሳሉ /ይከራከራሉ/። ለሕይወት ጥያቄዎች ሚዛናዊ ምላሽ በመስጠት በተለይ አሰዛኝ/ሰቆቃዊ/ በሆኑት ላይ ያተኩራሉ።

**ወርድ ፒክቸር እና ወርደ ቪው፡-** እነዚህ ተጓዳኝ ቃላት ናቸው። ሁሉም ፍልስፍናዊ ጽነሰ ሃሰቦች ሲሆኑ በአፈጣጠር ላይ ያተኩራሉ። የዓለም ምስል የሚሰጠው እንዴትን ሲያመለክት ስለአፈጣጠር ደግሞ የዓለም አመለካከት የሚለው ማን የሚለውን ያሳያል። እነዚህ ቃላት በተለይ ዘፍጥረት 1-2 ለመተርጎም በመጀመሪያ በመጀመሪያ ማን፣ የሚለውን ያነሳሉ "እንዴት" የሚለውን የአፈጣጠር ጥያቄ ትተው።

**ያህዌ፡-** ይህ የእግዚአብሄር የቃል ኪዳን ስም በአዲስ ኪዳን ነው። ይህም ዘፀአትን 3.14 ያለውን ያነትናል። ይህ የዕበራይስጥ ምክነያታዊ ስም በመጥቀስ መሆን የሚሰውን ያሳያል። አይሁዶች ይህን ስም ለመጥራት ፍርሐት አለባቸው ምንም አንኳ ቢቀበሉትም። በመሆኑም ወደ ዕብራይስጥ ለውጠው አዶናይ/ጌታ/ ይሉታል። በዚህም ምክንያት ነው ይህ የቃል ኪዳን ስም ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው።

# ተጨማሪ መግለጫ አራት
# የእምነት መግለጫ

በግል በተለይ በእምነት መግለጫም ሆነ የዕምነት ማስታወቂያ ብዙ አያሳስበንም ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን ማፅናቱ ይሻለኛል። ዳሩ ግን እኔ የዕምነት ሁኔታ ለመረዳትና ለመፈተሽ ለሚፈልጉ የዕምነት መግለጫው ይረዳቸው ይችላል። በርካታ ሥነ-መለኮታዊ ሕጸጾችና የተዛቡ አመለካከቶች ባሉበት ሁኔታ የእኔን ሥነ- መለኮታዊ ትምህርት አጭር ማጠቃለያ አቀርባለሁ።

1. መጽሀፍ ቅዱስ ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን ሁለቱም ተመስጧዊ የሆነ የማይወድቅ /የማይሻር / ሙሉ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ቃል ነው።

ቃሉ የራሱ የእግዚአብሔር መገለጥ ሲሆን በመንፈሳዊ ምሪት በሰዎች አማካኝነት የተመዘገበ /የተፃፈ/ ነው። ስለ እግዚአብሄር ንፁህ እውነት እና ስለ ተግባሩ የሚገልፅ ብቸኛ ምንጭ ነው። እሱም ለራሱ ቤተክርስቲያን የዕምነትና የተግባር ብቸኛ ምንጭ ነው።

2. አንድ ብቻውን የሆነ ዘለዓለማዊ ፈጣሪ የሚቤዥ እግዚአብሔር አለ። እሱም የሚታየውንም ሆነ የማይታየውንም የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው። ራሱን በአፍቃሪነቱና በጠባቂነቱ /በተንከባካቢነቱ/ የገለፀ ሲሆን ራሱም ፍፁምና /መልካም/ ትክክለኛ ነው። ራሱን በሦስት አካላት ገልጧል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በእኩል አካል የተለያዩ ባህርያ ግን አንድ የሆነ።

3. እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር ሁሌም ነው። እናም ዘለዓለማዊ እቅድ ለፍጥረቱ ያለ ሲሆን ይህም ማስተካከያ የማይደረግለት በእያንዳንዱ ሰው ነፃ ፍቅር ላይ ያተኮረ ነው። ያለ እግዚአብሔር እውቅናና ፍቃድ የመሆን ነገር የለም ይህም ቢሆን ግን ለሰዎችም ሆነ በመላእክት ነፃ ፍቀድን ፈቅዷል። እየሱስ አብ የመረጠው ሰው ነው። ሁሉም የሚመረጡት በሱ ነው። የእግዚአብሄር የሁኔታዎች ቀድመ እውቅና የሰው ልጆችን ቅድመ ፅሑፍ ቃሉን ከመቀበል ለመወሰን አያዳግታቸውም። እያንዳንዳችን ለምናስበውም ሆነ ለምንሰራው ሃላፊነትን እንወስዳለን።

4. የሰው ልጅ ምንም እንኳን በእግዚአብሄር አምሳል ቢፈጠርና ከሃጥያት ነፃ ቢሆንም በእግዚአብሄር ላይ ማመፅን መረጠ። አዳምና ሄዋን ምንም እንኳ ከተፈጥሮ በሆነ ወኪል ቢፈተኑም ፈቅደውና ወደው በግለኝነት በወሰዱት አቋም ሃላፊነት አለባቸው። የእነሱ አመፅ ነው የሰው ልጅንም ሆነ ፍጥረትን ለጉዳት የዳረገው። እኛ ሁላችንም ከእግዚአብሔር ምህረት ከአዳም ለወረስነውም ሆነ በሰውነታችን ለፈፀምነው አመፅ ያስፈልገናል።

5. እግዚአብሔር ይቅርታውንና ምህረቱን ለወደቀው ሰውነታችን ስጥቶናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ ሰው የሆነ፣ ያለ ሃጥያት የተመላለሰ እኛን ውጦ በሞተልን፣ የሰው ልጆችን የአሃጢአት ቅጣት ተቀበለ። እሱ የደህንነት መንገድና ከእግዚአብሔር ጋር ለሚምረው ስውረት ብቸኛ መንገድ ነው። ስለደህንነት ሌላ ምንም መንገድ የለም ራሱ ሰርቶ በጨረሰው ሥራ ከማመን በስተቀር።

6. እያንዳንዳችን በግል የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስጦታ በእየሱስ የሆነውን ደህንነት መቀበል ይኖርብናል። ይንንም ማግኘት የሚቻለው በእግዚአብሔር ተስፋ በማመን፣ በኢየሱስ በኩል ፍቃደኝነት ከሃጢአት መራቅ ነው።

7. ሁላችንም ሙሉ ምህረት እና መመለስ የምናገኘው ክርስቶስ እምነትና ሃጢአት በመመለስ ነው። የአዲስ ህይወቱ ማስረጃም በተለመደና እየተለወጠ ባለ ህይወቱ ይታወቃል። እግዚአብሄር ለሰው ሰጆች ያለው ዓላማ አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያት የሚሆን ሳይሆን አሁን ክርሰቶስ በመሰለ ሕይወት መመላለስ ነው። በትክክል መቤዠትን ያገኙ በስህተት ሃጢአት ቢሰሩም በዕምነታቸው ቀጥለውበት በንሥሐ ህይወት በሕይወት ዘመናቸው ሊመላለሱ ይገባል።

8. መንፈስ ቅዱስ ሌላው እየሱስ ነው። እሱም በዓለም ላይ አለ፣ የጠፉትን ወደ ክርስቶስ ለመምራትና በዳኑትም ክርስቶስ የመሰለ ሕይወት እንዲኖሩ በማስቻል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ደህንነታችን ስንቀበል ይሰጡናል። እነርሱም የእየሱስ ሕይወትና አገልግሎቶች ሲሆኑ ለአካሉ ለቤተክርስቲያን የተሰጡ ፀጋዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍላጎቱንና ሐሳቦቹን ለማስፈፀም በመንፈስ ፍሬ የሚታዩ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ፊት እንደነነረ አሁነም ይጠራል።

9. አብ ከሙታን የተነሳውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሁሉም ፈራጅ አድረጎታል። ወደ ዓለም ይመለሳል በሁሉም የሰው ልጆች ላይ ለመፍረድ በኢየሱስ ያመኑና ስማቸውም በበጎ ሕይወት መጽሀፍ ላይ የፃፈ ሰማያዊ የከበረ አካላቸውን በዳግም ምፅአቱ ያገኛሉ ከእሱም ጋር ለዘለዓለም ይሆናሉ። የእግዚአብሄርን እውነት ለመቀበል ያልፈለጉ ለዘለዓለም ከእግዚአብሄር ህብረትና ደስታ ይለያሉ። ከሰይጣንና ከመልአክቱ ጋር ይፈረድባቸዋል።


ይህ በእውነቱ የተጠናቀቀና የጠለቀ ባይሆንም የልቤን ሥነ-መለኮታዊ መዓዛ ይሰጣቸኋል ብዬ አምናለሁ። ጽሑፉን እወደዋለሁ። "ከአስፈላጊዎች ሁሉ – ህብረት፣ ከምርጫዎች- ነፃነት ከሁሉም ነገር- ፍቅር"

# የዳግም ምጽአት አመለካከቶች

__መግቢያ__

ሀ. ይህ ርዕሰ-ጉዳይ ታላቅ ክርክር ፈጥሯል
ለ. እንዴት የሚለው አልተረጋገጠም፣ መቼ የሚለው አልተረጋገጠም፣ ሁነቱ ግን ርግጥ ነው!
ሐ. የምታምኑትን ከየት አገኛችሁት?
መ. የዳግም ምጽአቱ ዓላማ ምንድነው?
ሠ. መጽሐፍ ቅዱስ ስልታዊ የፍጻሜ ዘመንን ያስተምራልን?
ረ. ዘመናችን በዳግም ምጽአት ላይ ለምን እጅግ ፍላጎት አደረበት?
ሰ. የክርስቶስን በሥጋ መመለስ በተመለከተ ያሉት ንድፈ-ሐሳቦች ሁሉ ወግ-አጥባቂ አመለካከቶች ናቸው።

__የጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን ቅድመ-ሚሊኒየማዊነት__ (ታሪካዊ ቅድመ-ሚሊኒየማዊነት)





**ቅድመ-ግምቶች**
1. የዓለም ታሪክ በ7 ቀናት የፍጥረት ማሳያ (የበርናባስ መልእክት፣ ኢሪነዩስ፣ ሜቶዲዩስ)
2. እያንዳንዱ ቀን 1000 ዓመትን ይወክላል (2 ጴጥ. 3፡8፤ መዝ. 90፡4)

**ደጋፊዎች**
1. ፓፒያስ ኢሪነዩስ፣ ጀስቲን ማርተር፣ ተርቱሊያን ሂፖሊተስ፣ ሜቶዲዩስ
2. ጆርጅ ላድ (ታሪካዊ ቅድመ-ሚሊኒማዊነት)

**ጥንካሬ**
1. አንዳንድ ሁነቶች ከዳግም ምጽአቱ በፊት መሆን አለባቸው
ሀ. ወንጌል ለአሕዛብ ሁሉ (ማቴ. 24፡14)
ለ. የእስራኤል መለወጥ (ሮሜ. 11፡25)
ሐ. ታላቁ ክህደት (ማቴ. 24፡10፤ ተሰ. 2፡3)
መ. ታላቁ መከራ (ማቴ. 24፡21)
ሠ. የኃጢአት ሰው - የክርስቶስ ተቃዋሚ መገለጥ (2 ተሰ. 2፡3)
የሚታይ፣ ሁሉን-አቀፍ መነጠቅና ምጽአት

__ሚሊኒየማዊ__ **(እውን የሆነ ወይም የተመረቀ ሚሊኒየም)**





**ቅድመ-ሚሊኒየም**
1. ቤተ-ክርስቲያን መንፈሳዊዋ እስራኤል ነች (ገላ. 3:9,29; 6:16; Rom. 2:5,9, 28-29; ራዕ. 1:6; 1 ጴጥ. 3:6)
2. አንድ ኪዳን (ኦሮጌና አዲስ፣ ሮሜ 4 – አብርሃም በጳውሎስ ምሳሌ ጽድቅ በእምነት)
3. የክርስቶስ መንግሥት ጊዜያዊ አይደለም (ዮሐንስ 18፡36)
4. አንድ ዳግም ምጽአት
አንድ ትንሣኤ
አንድ ፍርድ
ዘላለማዊ መንግሥት

**ደጋፊዎች**
1. አንዳንድ የጥንት ቤተ-ክርስቲያን አባቶች
2. አውግስቲን
3. ዝዊንግሊ
4. ካልቪን (ብሬስቤተርያናዊነት)
5. ሬይ ሰመርስ (ባፕቲስት)
6. ጄይ አዳምስ (ተሐድሷዊ)
7. ብዙዎቹ የክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያኖች

**ጥንካሬ**
1. ድል የተገኘው በቀራንዮ ነው፣ በሚሊኒየም ሳይሆን
2. አሁን ሰይጣን ታስሯል
3. የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ አንድነት

**ድኅረ ሚሊኒየማዊ (ሚሊኒየም አሁን)**





**ቅድመ-ግምቶች**
1. የሰው ጥረት ወደ መንግሥቱ ያመጣል (2 ጴጥ. 3፡12፤ ማቴ. 6፡10)
2. ነገሮች እየተሻሉ፣ እየተሻሉ ይሄዳሉ

**ደጋፊዎች**
1. ጆናታን ኤድዋርድስ
2. ኤ. ኤች. ስትሮንግ
3. ደብልዩ. ቲ. ኮነር

**ጥንካሬ**
1. ዳግም ምጽአቱን ከምር ይወስደዋል
2. ሰው በእግዚአብሔር ዕቅድ ድርሻ አለው
3. ስለ ዘመነኛ ባህል ተስፈኛ

4.አብዛኞቹ የ19ኛ ክፍለ-ዘመን ሊቃውንት

## የተከፋፈለ ቅድመ-ሚሊኒየማዊነት




(ራዕ. 20፡11-15)

¹ ለምሥጢራዊ ምጽአቱ 3 አተያዮች አሉ

1) ቅድመ መከራዊ
2) ማዕከላዊ መከራዊ
3) ድኅረ መከራዊ

² የአማኞች ፍርድ (2 ቆሮ. 5፡10)
³ የአሕዛብ ፍርድ (ማቴ. 25)

### ቅድመ-ግምቶች

1. መጽሐፍ ቅዱስ በሰባት የተለዩ ምድቦች ይከፋፈላል
2. የእያንዳንዱ የብኪ የእስራኤል ትንቢት እማሬያዊ (ጥሬ) ፍጻሜ
3. ቤተ-ክርስቲያንና እስራኤል ሙሉ ለሙሉ ተለያይተዋል። ቤተ-ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዕቅድ ለ ነው አይሁድ ኢየሱስን እንደ መሲሕ አንቀበልም ሲሉ
4. ቤተ-ክርስቲያን በምሥጢር ትነጠቃለች፣ ከታላቁ መከራ በፊት። የራዕይ መጽሐፍ፣ ከምዕራፍ 5 በኋላ አይሁዳዊ ነው።
5. አኪ የሚተረጎመው በብኪ ትንቢት አኳያ ነው


### ደጋፊዎች

1. ጆን ዳርቢይ (ፕሌይሙዝ ብረዘረን)
2. ክሌረንስ ላርኪን
3. ዲ.ኤል. ሞዲ
4. ሲ.አይ. ስኮፊልድ (የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ)
5. ዳላስ ሴሚናሪ (ጰንጠቆስጤ፣ ሬይሪን፣ ዋልቮርድ)
6. ደብልዩ. ኤ. ክሪስዌል (ደቡባዊ ባፕቲስት)
7. ሃል ሊንድሴይ
8. ቲም ላሃዬ
9. የመጽሐፍ ቅዱስ ቤተ-ክርስቲያኖች (ዳላስ ሴሚናሪ)

### ጥንካሬ

1. የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት በጽኑ ይወስዳል (በተለይ ዳንኤልን)
2. ያልታሰበ ምጽአት (ማቴ. 24፡40-42)

## የቦብ ታሳቢ አስተያየት (ታሪካዊ ሚሊኒየማዊነት/ድኅረ-ታላቁ መከራዊ/ሚሊኒየማዊ ያልሆነ)




### ቅድመ-ግምት

1. አንድ ዕቅድ (ዘፍ. 3፡15)
2. የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነት (ሮሜ. 2:28-29;4; ገላ. 3:29; 6:16)
3. የዳንኤል፣ ሕዝቅኤል፣ እና ራዕይ አፖካሊፕቲካዊ ባሕርይ (ጽሑፋዊ ዘውግ)
4. ብኪ አንድ ምጽአት (ሁለት ዘመናት)፣ አንድ የሚታይ ምጽአት ተመልክቷል
5. አንድ የሚታይ ምጽአት (ማቴ. 24፡27)
   አንድ መነጠቅ (1 ተሰ. 4፡13-18)
   አንድ ትንሣኤ
   አንድ ፍርድ (ማቴ. 25፤ ራዕ. 20)
   ዘላለማዊ መንግሥት

### ዲያሌክቲካዊ ተቃርኖዎች፡

1. በብሉይ ኪዳን ትንቢት ሞዴሎች እና በአዲስ ኪዳን ሐዋርያዊ ሞዴሎች መካከል
2. በመጽሐፍ ቅዱስ አሐዳዊነት (አንድ አምላክ ለሁሉም) እና በእስራኤል መመረጥ መካከል
3. በመጽሐፍ ቅዱስ ኪዳናትና ተስፋዎች ሁኔታዊ ገጽታ ("እንደ ሆነ... ከዚያም") እና ሁኔታዊ ባልሆነው በአምላክ ታማኝነት፣ የወደቀውን የሰውልጅ በመዋጀት፣ መካከል
4. በቅርብ ምስራቅ ጽሑፋዊ ዘውጎች እና በዘመናዊው ምዕራባዊ ጽሑፋዊ ሞዴሎች መካከል
5. በአምላክ መንግሥት አሁን እና ገና ለወደፊት መካከል
6. የክርስቶስ የቅርብ ምጽአት በሚለው እምነት እና በቀዳሚነት አንዳንድ ሁነቶች መሆን አለባቸው በሚለው እምነት መካከል

## ማጠቃለያ

1. ጆን ካልቪን ስለ ራዕይ የሚለው፣ “ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው።”
2. በዳግም ምጽአቱ ላይ የተረጋገጠ ወይም ብዙኃናዊ አስተያየት የለም።
3. እያንዳንዱ የአማኝ ትውልድ መጽሐፍ ቅዱስን ወደየራሱ ታሪካዊና ባህላዊ መቼት ያስገድደዋል (ይጎትተዋል)።
4. በአኪ ምንም ስልታዊ የፍጻሜ ዘመን አተያይ የለም፣ ነገር ግን ሐቁ ተገልጦልናል፣ “ዝግጁ” እና “ንቁ” እንድንሆን።”
5. ወግ አጥባቂዎች ብቻ ናቸው በዚህ ጉዳይ ላይ የሚወዛገቡ።
6. እሱ የሁሉም የአማኞች ትውልድ ተስፋ፣ ማበረታቻ፣ እና ማነቃቂያ ነው፣ ዳግም ምጽአቱን በሕይወት ዘመናቸው እንዲጠብቁ (ማርቆስ 13፡33-37)።

**የቅጂ መብት © 2000 ቦብ አትሌይ**
**ማርሻል፣ TX, ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት**
**መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።**

# ራዕይ

እንዲያው ያስፈራኛል በጥቂቱ
የዚህ የራዕይ ምሥጢራዊነቱ።
ግን ደግሞ የማወቅ ጉጉቴን ያመጥቃል
ምናቤንም ያነቃንቃል።
ግን የተማርኩት እጅግ እንድጠነቀቅ ነው
እዚያ ያለውን መልእክት ሳጤነው፣
ቀኖናዊ አለመሆኔን አስረግጬ፣
ጥንቁቅ ትርጓሜን ጨብጬ።
አውቃለሁ የቋንቋውን ተምሳሌትነትም፣
እናም ያልተገራና ነጻ አልሆንም
በራሴ ትርጉም እየጠቀስኩ
አሻሚ የሆነውን ችላ እያልኩ።
ዋና ነገሩ ዘውጉ ነው
ማሰብ ያለብኝም እሱን ነው፣
ሳላስብ ለእኔ ብቻ ምላሾች
እንደ ፍጹም ብቸኛ ሐቆች።
ግና ተስፋ አደርጋለሁ እንድሰማ ቃሎቹን
ከአብ አንደበት የወጣውን፣
የክርስቶስን ምጽአት ጠብቁ ዳግም፣
አሳዩ ለሌሎችም እሱ እውነት እንደሆነ፣ ሕይወትም መንገድም።
እንግዲያውስ ያንን በየቀኑ ስታገል አስታውሳለሁ
በምድራዊ ሚናዬ እቆማለሁ፣
አምላክ ያሸንፋል እላለሁ፣
እሱ በሉዓላዊነት ይገዛል፣
ሁሉንም ይቆጣጠራል

ፓት በርጌሮን 7/21/1999